አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂውማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ሥነፅሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

# ባህልና ልማት በበርታ ብሔረሰብ

በ

ስንቅነሽ አጣለ ገብሬ

2007 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ባህልና ልማት በበርታ ብሔረሰብ

**አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**

**የሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ**

**የአማርኛ ቋንቋ ሥነፅሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል**

**የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር**

## በፎክሎር ለዶክተሬት ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

**በ**

**ስንቅነሽ አጣለ ገብሬ**

**አማካሪ**

**ሀብታሙ ወንድሙ (ፕሮፌሰር)**

2007 ዓ.ም

አዲስ አበባ

**አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**

**የሒውማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ**

**የአማርኛ ቋንቋ ሥነፅሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል**

**የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር**

**ባህልና ልማት በበርታ ብሔረሰብ** በሚል ርዕስ በፎክሎር ለዶክተሬት ዲግሪ ማሟያ በስንቅነሽ አጣለ ገብሬ በታህሳስ 2007 ዓ.ም. የቀረበው ይህ ጥናት የዩኒቨርሲቲውን የጥራትና የወጥነት መስፈርት ስለሚሟላቱ በፈታኞች ተረጋግጦ ተፈርሟል፡፡

## የፈታኝ ቦርድ አባላት

**አማካሪ፡-** **ሀብታሙ ወንድሙ (ፕሮፌሰር)** **ፊርማ** ________________

**የውጪ ፈታኝ፡-** **ቀለመወርቅ ታፈረ (ዶክተር)** **ፊርማ** ________________

**የውስጥ ፈታኝ፡-** **ዘሪሁን አስፋው (ተባባሪ ፕሮፌሰር)** **ፊርማ** ______

# ማረጋገጫ (Declaration)

**ባህልና ልማት በበርታ ብሔረሰብ** በሚል ርዕስ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂውማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ሥነፅሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል በፎክሎር ለዶክተሬት ዲግሪ ማሟያ ያቀረብኩት ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሠራ የራሴ ወጥ ሥራ መሆኑንና የተጠቀምኩባቸው ዋቢ መረጃዎችም በትክክልል ዋቢ የሆኑ ናቸው፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም የጥናቱ ህጋዊ የባለቤትነት መብት ያለው መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም፡- ስንቅነሽ አጣለ ገብሬ ፊርማ ____________________ ቀን ________

# ምስጋና

በመጀመሪያ በድካሜ ኃይል እየሆነ ለረዳኝና እዚህ ላደረሰኝ አምላኬ እግዚአብሔር ከሁሉም በላይ ክብርና ምስጋና ይገባዋል።

ውድ ጊዜአቸውን ሰውተው ጥናቱን በተደጋጋሚ በማረምና በማስተካከል፣ ልዩ ልዩ ጠቃሚ መረጃዎችንና መጻሕፍት በማዋስ፣ ተግቼ እንደሰራ ያልተቆጠበ ምክርና እገዛቸው ላልተለየኝ አማካሪዬ ፕሮፌሰር ሀብታሙ ወንድሙ ከታላቅ አክብሮት ጋር ምስጋናዬ ይድረሳቸው።

ትምህርቱን እከታተል ዘንድ ለፈቀደልኝና ጥናቱን ለማድረግ መጠነኛ የገንዘብ ድጋፍ ላደረገልኝ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ምስጋና ይገባዋል።

የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ጥናቱ በተገቢው ሁኔታ እንዲሠራ ላሳደረው ፍላጎትና፣ ጥናቱን ለማገዝ ላደረገልኝ የገንዘብ ድጋፍና የተሸከርካሪ አቅርቦት ሥራዬን ካለችግር እንድወጣ ከፍተኛ አቅም ፈጥሮልኛልና ከልብ አመሰግናለሁ። በተለይ የክልሉ ፕሬዘዳንት ክቡር አቶ አህመድ ናስር የጥናቱን ጠቀሜታ በመረዳትና እንደራሳቸው ሥራ በመቁጠር ላደረጉልኝ ቅንነት የተሞላበት እርዳታ፣ ድጋፍና ማበረታታት ሳመሰግናቸውና በአርአያነት ስጠቅሳቸው እኖራለሁ።

ለክልሉ መንግሥት የጤና፣የግብርና፣ የባህልና ኮሚኒኬሽን ቢሮዎች፤ ለአሶሳ ዞን መስተዳድር፣ ለዞኑ የጤና፣የግብርና፣ የባህልና ኮሚኒኬሽን ጽ/ቤቶች፤ ለሸርቆሌ፣ ለመንጌ፣ ለአሶሳና ለባምባሲ ወረዳ አስተዳደሮች፤ ለመቃዚን፣ ለከሸፍ፣ ለጊዘን፣ ለጊዜጠሪያ፣ ለአቡራሙ፣ ለቆሽመንገል፣ ለቱመት ጡቤና ለጠይባ ቀበሌዎች አስተዳዳሪዎች ምስጋናዬ ይድረሳችሁ።

ወ/ሮ ሲቲና አደም የጥናቱ መረጃ ስብሰባ ከተጀመረ ጀምሮ ከጎኔ ሳትለይ አብረሽኝ ከቦታ ቦታ በመዘዋወር፣ መረጃ ሰጪዎችን ፈልጎ በማገናኘት፣ መረጃ በመስጠት፣ በማስተርጎም፣ አብስለሽ በማብላት፣ በቤትሽ በማኖር፣ ለሥራዬ ስኬት ምክርና

አስተያየትሽን በመስጠት ወዘተ ላደረግሽልኝ ከቁጥርና ከግምት ለበዛ ቸርነት አመስግኜሽ አልጠግብም። ሲቲዬ ዕውነተኛ የበርታዎች አሻራ በመሆንሽ ካንቺ የተነሳ ድካሜ ቀሎልኛልና አምላክ ከነ ልጆችሽ ዘመንሽን ሁሉ ይባርከው።

ሀሰን አልመሃዲ፣ ጋሽ ዓለማየሁ ሽፈራው፣ ዮርዲ፣ ሰብሪ፣ ኢብራሂም፣ አኖሂ፣ሀሺም፣ ቢተልሚና የሚያስፈልገኝን ሁሉ በሟሟላት፣ አብራችሁኝ በመንከራተት፣ መንገድ በመምራትና በማስተርጎም ካለዋጋ ለሰጣችሁኝ ፍቅርና እንክብካቤ ምስጋናዬ ያንስባችኂል።

በአካባቢያችሁ መገኘቴን እንደበረከት ቆጥራችሁ በዕውነተኛ እንግዳ ተቀባይነታችሁ በፍቅር እየተቀበላችሁ የምፈልገውን መረጃ ካለስስት የሰጣችሁኝ በአባሪነት ስማችሁን ያያያዝኩት መረጃ ሰጪዎቼና ሌሎች በርታዎች በሙሉ ባሰብኳችሁ ቁጥር ቸርነታችሁ ወሰን ያልፍብኛልና ምስጋናዬን ውሰዱ። ወላሂ ስማችሁን ልዘርዝር ብል ማዳላት ይሆንብኛል፤ ሁላችሁም ቤተሰቦቼ ናችሁ፤ መልካምነታችሁን አውርቼ አልጠግብም።

ልጆቼ ፍቅር፣ ቤዛና ሚካኤል ግርማ በሁኔታዎች ሁሉ እየተገነዘባችሁኝ ክፍተቴን ሞልታችሁ እናታችሁ እንድጠነክር ረድታችሁኛልና ተባረኩልኝ።

ይህ ጥናት ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ በገጠሙኝ መሰናክሎች ሁሉ እንዳልወድቅ ከጎኔ ሳትለዩ ምክርና ድጋፋችሁን ስታደርጉልኝ የነበራችሁ ጓደኞቼና የስራ ባልደረቦቼ ዶ/ር ጌታሁን አማረ፣ ረዳት ፕሮፌሰር ደረጀ ገብሬ፣ አቶ ጌታቸው እንዳላማው፣ ተባባሪ ፕሮፌሰር ዘሪሁን አስፋው፣ አቶ አበረ አዳሙ፣ አለኝታነታችሁ ለዚህ አድርሶኛልና ምስጋናዬ ከልብ ነው።

ጥናቱ በተገቢው ጊዜ እንዲጠናቀቅ የተዘናጋሁ ሲመስላችሁ በርቺ እያላችሁ ስትጎተጉቱኝ የነበራችሁ የልጅ አዋቂዋ አስቴር ሙሉ፣ ዶ/ር ሙሉሰው አሥራቴ፣ ዶ/ር ዳኛቸው አሰፋ፣ ዶ/ር ጌታቸው፣ ዶ/ር ጉዳይ እምሬ፣ ዶር/ ዘላለም ዶ/ር ታዬ አሰፋ፣ አቶ ቢኒያም ኤፍሬም፣ አቶ ብርሃኑ ኡርጋ፣ አቶ ግዛቸው አግማስ፣ አቶ ብርሃኔ ገብሩ፣ አቶ ሳሙኤል በፍቃዱ፣ አቶ አያልቅበት ደጉ፣ ወ/ሮ ሙሉ ምክረ ማበረታቻችሁ ጉልበት ሆኖኛልና አመሰግናችኂለሁ።

# ማውጫ


ምስጋና ____ vi

አጠቃሎ/ Abstract ____ xii

የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ካርታ ____ xiv

የአህፅሮተ ቃላት መፍቻ ____ xv

ምዕራፍ አንድ ____ 1

1. መግቢያ ____ 1

1.1. የጥናቱ ዳራ ____ 3

1.2. የጥናቱ አካባቢ ____ 9

1.2.1. የቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልል አጠቃላይ ገፅታ ____ 9

1.2.2. የበርታ ብሔረሰብና አካባቢው ____ 12

1.2.3. የበርታ ብሔረሰብ ታሪካዊ አመጣጥና ስያሜ ____ 12

1.2.4. የበርታ ብሔረሰብ መተዳደሪያ ____ 17

1.3. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ____ 19

1.4. የጥናቱ ዋነኛ ዓላማ ____ 22

1.4.1. ዝርዝር ዓላማዎች ____ 22

1.4.2. የምርምሩ ጥያቄዎች ____ 23

1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ ____ 23

1.6. የጥናት አካባቢው መረጣና የጥናቱ ገደብ ____ 24

1.7. ያጋጠሙ ምቹ ሁኔታዎች፣ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሔ ርምጃዎች ____ 26

1.7.1. ያጋጠሙ ምቹ ሁኔታዎች ____ 27

1.7.2. ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሔ ርምጃዎች ____ 28

1.8. የጥናቱ ሥነምግባር ____ 30

ምዕራፍ ሁለት ____ 32

2. የፅንሰ ሃሳብ ማዕቀፎች ____ 32

2.1. የባህል ፅንሰ ሀሳብ ____ 32

2.2. የልማት ፅንሰ ሀሳብ ____ 37

2.3. የባህልና የልማት ቁርኝት ____ 42

2.4. ግብርና ኤክስቴንሽን 49

2.5. ጤና ኤክስቴንሽን 50

*ምዕራፍ ሶስት* 54

*3. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝትና ንድፈ ሃሳባዊ መሠረቶች* 54

3.1. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት 54

3.2. ንድፈ ሃሳባዊ መሠረቶች 60

3.2.1. ተግባራዊ ቲዎሪ / Functionalist Theory / 63

3.2.2. የክዋኔ ቲዎሪ / Performance Theory / 64

3.2.3. የዘመናዊነት ቲዎሪ (Modernaization Theory) እና የልማት ቲዎሪ (Developmental Theory) 70

3.2.4. የቲዎሪ አመላካች ሞዴል ("የባህላዊ ፈርጦች ተደጋጋሚነትና ተመሳስሎ ዙር ገጠም ስረጻ መረብ") 72

*4. የጥናቱ አሠራር ዘዴ* 75

4.1. የጥናቱ ዘዴ 75

4.1.1. የጥናቱ መልክ 75

4.1.2. የመረጃ ማሰባሰቢያ ስልቶች 76

4.1.2.1. ምልከታ እና ተሳትፎአዊ ምልከታ 76

4.1.2.2. ቃለ መጠይቅ 80

4.1.2.3. የተተኳሪ ቡድን ውይይት 81

4.2. ከመስክ ውሎ የተገኘ ልምድ 83

4.3. የጥናቱ አካሄድና አተናተን ዘዴዎች 86

*ምዕራፍ አምስት* 89

*5. የበርታ ብሔረሰብ ዋና ዋና ባህላዊ መልኮች* 89

5.1. የበርታ ብሔረሰብ መልክና አለባበስ 89

5.1.1. አካላዊ መልክ 90

5.1.2. አለባበስና አጋጊያጥ 92

5.2. የምግብ አሠራርና አመጋገብ 97

5.2.1. "ዱቃ" / ገንፎ 98

5.2.2. አል ኪሥራ/አልጉራሳ (ስስ እንጀራ) 101

5.2.3. "አላብሬ"/ ስስ የእንጀራ ድርቆሽ 101

5.2.4. ሥጋ ነክ ምግቦች 102

5.3. በርታና እንግዳ ___ 105
5.4. የበርታ ብሔረሰብና ሀገረሰባዊ ልማዶች ___ 110
5.4.1. ክብረ በዓላት ___ 110
5.4.1.1. የፌዳ ሥርዓት ___ 110
5.4.1.2. የ"ኢሮ" ወይም የ"አጱምጱም" በዓል ___ 112
5.4.1.3. የዘመቻ ክተት ጥሪዎች ___ 115
5.5. ሀገረሰባዊ ዕምነቶችና ባህላዊ መድሃኒቶች ___ 120
*ምዕራፍ ስድስት ___ 124*
*6. ጋብቻ ልደትና ሞት በበርታ ብሔረሰብ ___ 124*
6.1. የጋብቻ ሁኔታ ___ 124
6.1.1. "ፌዳ" የጋብቻ ጥያቄ/ ማጨት ___ 125
6.1.2. "አል በረካ"/ የመጀመሪያ ጥሎሽ ___ 128
6.1.3. አል ፋተሃ/ ዳግም ጥሎሽ ___ 129
6.1.4. ሠርግ "እሪስ" ___ 130
6.1.5. ክብረ ንፅህና ___ 133
6.2. እርግዝናና ልደት ___ 136
6.2.1. ሰሚያ (የሥም አወጣጥ ሥርዓት) ___ 138
6.2.2. ግርዛት ___ 139
6.3. ሞትና የሀዘን ሥርዓት ___ 141
6.3.1. የቀብርና የሀዘን ሥርዓት ___ 144
6.3.2. የአያት ሞትና የልጅ ልጆች የካሳ ጥያቄ /አጉቤፁ ___ 145
*ምዕራፍ ሰባት ___ 151*
*7. የአካባቢውን ልማት ለማፋጠን ያሉ አዎንታዊ ባህላዊ ጉዳዮች ___ 151*
7.1. የበርታ ብሔረሰብ ሁለንተናዊ የጋራ ሕይወትና አኗኗር ___ 151
7.2. ግጭቶችን በጋራ መፍታት ___ 161
7.3. ሀቀኝነት፣ ግልፅነትና ያልተገባ ጥቅምን አለመፈለግ ___ 164
7.4. የዘመዳሞች ጎረቤታሞች የጋራ ትብብሮች ___ 176
7.4.1. "አመሃ" / የደቦ ሥራ ___ 176
7.4.2. "አታማተባ" /ዕቁብ ___ 177
7.4.3. "ሙጅባ" / የሠርግ መዋጮ ___ 177
7.4.4. "ሀፍለታ ሻሂ"/ የሻይ እንጠጣ ፕሮግራም ___ 178

7.5. የመንደር ማሰባሰቡ በጎ ጅምሮች ____ 180
7.6. ገንቢ የሆኑ የጤና ጉዳዮች ____ 182
7.6.1. የግልና የአካባቢ ንፅህና አጠባበቅ ____ 182
7.6.2. ለጤና ተስማሚ የሆነ መኖሪያ ቤት አሠራርና አያያዝ ____ 184
ምዕራፍ ስምንት ____ 189
8. የአካባቢውን ልማት የሚያስተጓጉሉ አሉታዊ ባህላዊ ጉዳዮች ____ 189
8.1. የግብርና ልማት እና የበርታ ብሔረሰብ ባህል ተግዳሮቶች ____ 189
8.1.1. ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ____ 190
8.1.2. ሰፊ ጊዜውን በእርሻ ሥራ ላይ አለማጥፋትና ለነገ አለመጨነቅ ____ 194
8.1.3. "የታታሪነት ችግር" ወይስ ባህሉን አለመገንዘብ ____ 197
8.2. የጤና ኤክስቴንሽን እና የበርታ ብሔረሰብ ባህል ____ 209
8.2.1. ባህላዊ ህክምና ____ 209
8.2.2. የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎትና ተግዳሮቶቹ ____ 225
8.2.3. የቅድመና የድህረ ወሊድ ክትትል አገልግሎትና ተግዳሮቶቹ ____ 231
8.2.4. የሴት ልጅ ግርዛትና የሀርሻ ጭፈራ ____ 235
ምዕራፍ ዘጠኝ ____ 240
9. ማጠቃለያና ይሁንታ ____ 240
9.1. ማጠቃለያ ____ 240
9.2. ይሁንታ / Recommendations ____ 246
ዋቢ ሠነዶች ____ 253
አባሪዎች ____ 262
አባሪ አንድ የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር ____ 262
አባሪ ሁለት የበርታ ተረቶች ____ 271
አባሪ ሶስት ተጨማሪ ፎቶዎች ____ 305
አባሪ አራት የየቀን ውሎ ማስታወሻ ____ 320
አባሪ አምስት ____ 359
በመስክ ስራ በቃለ ምልልስ የተሰበሰበ መረጃ ማሳያ ____ 359

# አጠቃሎ/ Abstract

የዚህ ጥናት ዋነኛ ዓላማ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልል ነባር ብሔረሰቦች ከሚባሉት መካከል የበርታን ብሔረሰብ ባህል በማጥናት በሀገር አቀፍ ደረጃ በመንግስት ታቅደው እንዲተገበሩ የሚሰራጩ የልማት ዕቅዶችን ለመተግበር የብሔረሰቡ ባህል ለአካባቢው ልማትም ሆነ "በልማት ወደ ኋላ መቅረት" ያደረገው አስተዋጽኦ ወይም ተፅዕኖ ይኖር እንደሆነ መመርመርና ባህላዊ ጉዳዮችን የልማት መሣሪያ በማድረግ የአካባቢውን ልማት ለማፋጠን የሚቻልበትን መንገድ ማሳየት ነው፡፡


ጥናቱ ዓይነታዊ (Qualitative) የአጠናን ዘዴን ተከትሎ የተደረገ ሆኖ ተንታኝ (Interpretative) የአጠናን ስልትን የሚከተል ነው፡፡ በጥናቱ የበርታ ብሔረሰብ ከሚኖርበት አሶሳ ዞን ስምንት ወረዳዎች ውስጥ አራቱን በመምረጥ በቃለ መጠይቅ፣ በተሳትፎአዊ ምልከታና በተተኳሪ ቡድን ውይይት መረጃዎች ተሰብስበው ተተንትነዋል፡፡ በመስክ ቆይታው እንዳጋጠመው ምቹ ሁኔታም በየቀበሌዎቹ የተለያየ ቁጥር ያላቸው ሃያ ስምንት ሴቶችና አርባ ስምንት ወንዶች በጠቅላላው ሰባ ስድስት ሰዎች መረጃ በመስጠት ተሳትፈዋል፡፡ ከነዚህ ውስጥ አሥራ አንድ ሴቶችና ሃያ ሦስት ወንዶች በድምሩ ሰላሳ አራት ሰዎች በቃለ መጠይቅ የተሳተፉ ሲሆን በዋና መረጃ ሰጪነት የተሳተፉት ጥንት የማህበረሰቡ መሪዎች የነበሩት ሰዎች ቤተሰቦች ሶስት ወንዶችንና ሁለት ሴቶችን ይጨምራል፡፡

በጥናቱ የበርታ ብሔረሰብ የማንነቱ መገለጫዎችና የራሱ የሆኑ የጋብቻ፣ የልደትና ሞት ሥርዓቶች፣ ሀገረሰባዊ ልማዶች፣ ክብረበዓላት፣ የአምልኮ ሥርዓቶችና ባህላዊ መድሃኒቶችም እንዳሉት ተረጋግጧል፡፡ በብሔረሰቡ ባህል ቢያሳድጓቸውና ቢያጎለብቷቸው

ጠቃሚ የልማት መሣሪያ የሚሆኑ የጋራ ትብብሮችና የአኗኗር ልማዶች፣ መልካም አስተዳደርን፣ ከሙስናና ከአድሏዊ አሰራር የፀዳ ማህበረሰብን መገንባት የሚያስችሉ ሃቀኝነትና ዕውነተኛነት መሠረታቸው የሆነና ሌብነትና ቅጥፈትን የሚጠየፉ ባህላዊ ፈርጦች እንዳሉ በጥናቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ብሔረሰቡ በባህሉ በጋራ ተረዳድቶና ያለውን ተካፍሎ የሚኖርና ለነገ ሳይጨነቅ ኑሮዬ ይበቃኛል ብሎ የሚያድር በመሆኑ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፣ ጥሪት መቋጠር፣ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ምርቶች ማምረት፣ ምርጥ ዘር ማዳበሪያን የመሳሰሉትን የግብርና ግብዓቶችን በብድር ወስዶ መጠቀም የሚሉት የመንግስት ተልዕኮዎች ተግዳሮት እንደገጠማቸው በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ ጤና ኤክስቴሽኑንም አስመልክቶ ብሔረሰቡ የራሱንና የአካባቢውን ንፅህና መጠበቅ በባህሉ የተለመደ ጉዳይ በመሆኑ ይህን አስመልክቶ ለታቀደው የጤና ኤክስቴንሽን አፈፃፀም  አወንታዊ ባህላዊ አስተዋፅዖ ሲኖረው በሌላ መልኩ ደግሞ በባህሉ ተፅዕኖ ምክንያት የቤተሰብ ምጣኔ፣ በጤና ተቋማት መጠቀም፣ የሴት ልጅ ግርዛትና የመሳሰሉት ጉዳዮች ተፈፃሚነታቸው ተግዳሮት እንደገጠመው ተረጋግጧል፡፡

በአካባቢው ልማት ላይ የባህላዊ ፈርጦቹ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ተፅዕኖ የማሳደራቸው ሃይል የሚገለፀው ደግሞ እርስ በርስ እየተጋመዱና እየተሰናሰሉ የራሳቸውን መረብ ዘርግተው በተደጋጋሚ መገለጣቸውና በብሔረሰቡ ውስጥ ሰርጅተው መኖራቸው መሆኑ በጥናቱ በተለያዩ ምሳሌዎች ተተንትኖ ተረጋግጧል፡፡ ይህም **የባህላዊ ፈርጦች ተደጋጋሚነትና ተመሳስሎ ዙር ገጠም ሥረጃ መረብ** የተሰኘውን የቲዎሪ ሞዴል አስገኝቷል፡፡ ከጥናቱ በመነሳትም የተለያዩ ይሁንታዎች ለሚመለከታቸው አካላት ተሰጥተዋል፡፡

**ቁልፍ ቃላትና ሐረጎች፡- ባህል፣ ልማት፣ አዎንታዊ ባህላዊ ተፅዕኖ፣ አሉታዊ ባህላዊ ተፅዕኖ፣ በርታ**


Administrative Region, Zone and Woreda Map of Benishangul Gumuz
የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ካርታ
Administrative Boundaries
Region
Woredas
Woreda name
Zones
Asosa
Kemashi
Metekel
34°0'0"E
36°0'0"E
12°0'0"N
10°0'0"N
Guba
Dangura
Pawe Special
Mandura
Wenbera
Bulen
Dibat
Sherkole
Kurmuk
Homosha
Menge
Sirba Abay
Bilidigilu
Assosa
Bambasi
Maokomo Special
Yaso
Agalometi
Kamashi
Bio Jiganifado
SUDAN
AMHARA
OROMIA
OROMIA
Tigray
Afar
Amhara
BGumuz
Dire Dawa
Addis Ababa
Hareri
Gambela
Oromia
Somali
SNNPR
N
0
30
60
120
Km
Disaster Risk management and Food Security Sector
Administrative Map of Benishangul Gumuz
The delineation of national and international boundaries must not be considered authoritative
Data courtesy of DRMFSS
©DRMFSS Information Managment 2004 E.C

# የአህፅሮተ ቃላት መፍቻ

| ተ.ቁ | አህፅሮተ ቃል | የአህፅሮተ ቃሉ መፍቻ |
|---|---|---|
| 1 | ቃመ | ቃለመጠይቅ |
| 2 | ቡውይቆሽ | የቡድን ውይይት ቆሽመንገል ቀበሌ |
| 3 | ቡውይአቡ | የቡድን ውይይት አቡራሙ ቀበሌ |
| 4 | ቡውይመቃሴብቻ | የቡድን ውይይት መቃዚን ቀበሌ ሴቶች ብቻ |
| 5 | ቡውይመቃወብቻ | የቡድን ውይይት መቃዚን ቀበሌ ወንዶች ብቻ |
| 6 | ቡውይሽር | የቡድን ውይይት ሽርቆሌ ቀበሌ |
| 7 | ቤጉክማባቱማቢ | የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ማስታወቂያ፣ባህል፣ቱሪዝምና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ |
| 8 | ቡጉክመየ5ዓዕትዕ | የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የ5ዓመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ |
| 9 | የቤጉክዕትዕአግሪ | የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የ5ዓመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ግምገማ ሪፖርት |

# ሙዳየ ቃላት[1]

| ተ.ቁ | የበርትኛ/ የሩጣና ስያሜ | የአማርኛ ፍቺ |
|---|---|---|
| 1. | ሀሻሁር | የወተት ዕቃ ማጠኛ ለባህላዊ ሽቶም መቀመሚያ የሚሆን እንጨት |
| 2. | ሀፍለታ ሻሂ | አንድን የገንዘብ ችግር ያጋጠመውን ሰው ለመርዳት ሻይ ተፈልቶ የሚካሄድ መረዳጃ |
| 3. | ሁምራ፣ዱፍራ | በባህላዊ መንገድ የሚሠሩ ጣፋጭ መዓዛ ያላቸው ሽቶዎች |
| 4. | ሃቤ | የሙሽሮችን ሰውነት በባህላዊ መዋቢያ የምታሽ ሴት ሚዜ |
| 5. | ሃራ | የደም ጨርቅ ማስቀመጫ ሙዳይ ወይም ባለክዳን ሳህን |
| 6. | ሃርሻ | በክብረ በዓላትና በሠርግ ጊዜ ሌሊቱን ሙሉ ባብዛኛው ወጣቶች የሚሳተፉበት ጭፈራ |
| 7. | ሙሼ | ሞት |
| 8. | ሙጀባ | ለሠርግ የሚደረግ መዋጮ |
| 9. | ሚጂሊሎ | በጫጉላ ቤት ተደብቀው የብር አምባር አሠባበሩን ሥርዓት የሚከታተሉ አሮጊቶች |
| 10. | ምህር | ለሠርግ መደገሻ ከወንዱ ለሴቷ ቤተሰቦች የሚሠጥ ገንዘብና ቁሳቁስ |
| 11. | ሰምሰም | ሴቶች ጭስ ሲገቡ የሚቀቡት የሰሊጥ ዘይት |
| 12. | ሳዳቅ | ጥሎሽ |
| 13. | ስልምስቂ | ማሽላ |
| 14. | ስሚያ | ለህፃን ልጅ ስም የማውጣት ሥርዓት |
| 15. | ሽክሽካ፣ | ፍሬያቸው ወይም ተፈጭተው የሚገቡ የባህላዊ ሽቶ መቀመሚያ ዕጽዋት |
| 16. | ቂቂስ | የግርዛት ሥርዓት |
| 17. | ቄንቄጽ | ቄንቄፅ በሩጣንኛ (በበር በበርታ ቋንቋ ሲሆን "ባሚያ"፣ "ዋይካ"፣ በሚሉ የተለያዩ መጠሪያዎች የሚታወቅ ሲሆን እንደ እህል ተዘርቶ ከሚበቅል ተክል ለገንፎና ለእንጀራ ማባያነት የሚያገለግል |
| 18. | ቆጭቆጫ | ከሚጥሚጣ ቃሪያ ተቀምሞ የሚዘጋጅ የሚያቃጥል ማባያ፣ በደቡብ አካባቢ ዳጣ ተብሎ የሚጠራውን የመሰለ |
| 19. | ባንግ | የተዋደደ መጥረቢያ ቅርፅ ያለው የተጠረበ እንጨት |
| 20. | ባፃ | ብቅል ኖሮት የሚሰራ ባህላዊ ጠላ |
| 21. | ቤቤ | የለቅሶ ሙሾ |
| 22. | ቦሎቂያ | ባህላዊ የጭስ ጉድጓድ |
| 23. | ኔሪ | አዋቂ፣ ጠንቋይ፣ መድሃኒተኛ |
| 24. | አላብሬ | ውሃ ላይ ተበትኖ የሚጠጣ የእንጀራ ሰበከት ፍቅፋቂ የመሰለ ድርቆሽ |
| 25. | አሞሌ | በቆሎ |

[1] አህፅሮተ ቃላቱና ሙዳየ ቃላቱ በሠንጠረዥ የሆኑት ለአንባቢ ግልፅ አድርጎ ለማሳየት ነው፡፡

| ተ.ቁ | የበርትኛ/ የሩጣና ስያሜ | የአማርኛ ፍቺ |
| --- | --- | --- |
| 26. | አል መራራ | ፍየል በታረደ ጊዜ የሚሠራ በሃሞት የተቀመመ ዱለት |
| 27. | አል ሙስሊያ | ከሰሌን የሚሰራ ለሰላት መስገጃና ዲልካ ሲቀቡና ሲታሹ የሚቀመጡበት |
| 28. | አል ማህለብ | ለዲልካና ለሁምራ መቀመሚያ የሚሆን የሎሚ ፍሬ የመሰለ ፍሬ |
| 29. | አል ሬቴርታ | ለገንፎ የሚሆኑ የማሽላ ዓይነቶች |
| 30. | አል በረካ | የጥሎሽ መጀመሪያ/ አይን መግለጫ |
| 31. | አል አሲድ | ሳይቦካ ዱቄት ተነስንሶ ለድንገት ወይ ልጆች እንዳይርባቸው የሚዘጋጅ ገንፎ |
| 32. | አል ከበሬት | በባህላዊ መንገድ የሚሰራ እንደ እጣን የሚጨስ ልዩ ማዕዛ ያለው እንጨት |
| 33. | አል ከልዋ | የአንድ ሠፈር ወንዶች ብቻ ተሰብስበው የሚቀመጡበት፣ የሚመከሩበት፣የሚሰግዱበት፣ የሚመገቡበትና እንግዳ የሚቀበሉበት ዳስ የመሰለ ቤት |
| 34. | አል ኪስራ | ስስ የማሽላ እንጀራ |
| 35. | አል ደሁል | ለዲልካ መቀመሚያ የሚሆን  የተመረጠ ማሽላ |
| 36. | አልገዳ | የገንፎ ማቅረቢያ ጣባ |
| 37. | አል ጠለህ | ለዲልካ መቀመሚያ የሚሆን የበሰለ ቀይ የግራር እንጨት |
| 38. | አል ፋተሃ | ለሁለተኛ ጊዜ የሚሰጥ ጥሎሽ ሆኖ የሙሽርዋ እህቶችና አክስቶች በያሉበት የምትደርሳቸውን ያህል የሚከፋፈሏት ገንዘብ |
| 39. | አመሃ | የደቦና የሕብረት ሥራ ዘፈኖች |
| 40. | አባ ፂፂኢኝ | የባህል መድሃኒት አዋቂ |
| 41. | አሴራ | የሠርግ ዘፈን |
| 42. | አሪስ | ሙሽራ |
| 43. | አሸራምቤ | የገንፎ ማማሰያ/ መላጊያ |
| 44. | አቀንፃ | በጣም የሚነድ እንጨት ሆኖ ሰባቱ ታስሮ በሃዘንተኞች ዓይን ላይ ሰባት ጊዜ የሚበራ እንጨት፤ ሀዘንተኞች ሀዘናቸውን እንዲተው ማለት ነው |
| 45. | አጉቤፁ | አያት ስትሞት የልጅ ልጆች ተሰብስበው እናት አባታቸውን፣አክስት አጎታቸውን ካሳ የሚጠይቁት ሥርዓት |
| 46. | አተምባ | ከተቦረቦረ እንጨት ውስጡ ክፍት ሆኖ ባንድ ወገን በቆዳ የተለበጠ እንደከበሮ የሚመታ ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያ |
| 47. | አተሉቃ | ሦስት በቁመትና በውፍረት የተለያዩ ውስጡ ክፍት ተደርጎ ከተቦረቦረ እንጨት በቆዳ ተለብጠው የተሠሩ ሦስቱም አንድ ላይ ታስረው በፍጥነትበጣትና በመዳፍ እየተመቱ የሚሠሩ ባህላዊ ከበሮዎች |
| 48. | አታማተባ | በሚቀራረቡ ሰዎች መካከል የሚሰበሰብ ዕቁብ |
| 49. | አዳሁኔ፣ሰርኔ፣አድብሬ፣ አልሬቴርታ | ለገንፎ የሚሆኑ የማሽላ ዓይነቶች |
| 50. | አዴንሺ | ለጋብቻ ጥያቄ ሽማግሌ የመላክ ሥርዓት |
| 51. | አጹምጹም | በጥቅምት ወር እንደዘመን መለወጫ በሚቆጥሩት በዓል ላይ የሚጫዎቱት ጭፈራ |

| ተ.ቁ | የበርትኛ/ የሩጣና ስያሜ | የአማርኛ ፍቺ |
|---|---|---|
| 52. | አፍሪንቆ | ጭልፋ |
| 53. | እማ | ወንድ ሙሽራ ራሱ ላይ የሚጠመጥመው ጨርቅ |
| 54. | እሪስ | ሡርግ |
| 55. | ወዚር | ሚዜ |
| 56. | ዱቃ | ገንፎ |
| 57. | ዲልካ | በባህላዊ መንገድ የሚሠራ ጣፋጭ መዓዛ  ያለው የሰውነት መታሻ |
| 58. | ጋሂ | የገንፎ ማገንፊያ ጎድጎድ ያለ ድስት |
| 59. | ጨሬ | ገንፎ ማገንፊያው ላይ ከሥር ተጋግሮ የቀረው ስስ የገንፎ ቅርፊት |
| 60. | ጳሌ | የእርሻ መሬት ለመቆፈር የሚጠቀሙበት ዶማ |
| 61. | ፊዳ | የጋብቻ ጥያቄ /ማጨት |

# ምዕራፍ አንድ

## 1. መግቢያ

ባህል የሰውን ልጅ አጠቃላይ ባህሪን የሚያደራጁና የሚተክሉ ማህበራዊ ልማዶች፣ መንፈሳዊና ቁሳዊ ሁኔታዎችን አጠቃሎ የሚይዝና በአመለካከት፣ በንግግር፣ በአስተሳሰብና በድርጊት የሚገለፅ ማህበራዊ ሁኔታ ነው:: አንድን ማህበረሰብም ሆነ ግለሰብን ከባህሉ ውጪ ማሰብ አይቻልም የሚባለውም ለዚህ ነው::

ባህል የአንድ ማህበረሰብ ሁለንተና የሚገለጥበት በመሆኑም ስለማህበረሰቡ ሕልውና፣ ማንነት፣ ዕድገት፣ ጤና፣ ትምህርት፣ አስተዳደር፣ ፖለቲካ፣ ልማት ወዘተርፈ ስናነሳ ልንዘለው የማንችል ጉዳይ ባህላዊ መሠረቱ ነው:: ማህበረሰቡ ባህሉን እንደፈጠረው ሁሉ ለባህሉ ሕግና ሥርዓት ካለማንገራገር ይገዛል:: በባህሉ ትክክል የሆነ ነገር ትክክል፣ ውጉዝ የሆነ ነገር ውጉዝ ሲሆን ይስተዋላል:: ምንም ያህል የሚጠቅም ጉዳይ ይሁን ተቀባይነት ለማግኘት በባህሉ ሚዛን ነጥሮና ተፈትኖ ማለፍ እንደሚኖርበት አንዳንድ ዕውነታዎች ያመለክታሉ::

የሀገራችንን ልማት ለማፋጠን በሀገር አቀፍ ደረጃ በመንግሥት ታቅደው በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች እንዲተገበሩ የሚፈለጉ በርካታ የልማት ፖሊሲዎች፣ ዕቅዶችና ስትራቴጂዎች አሉ:: እነዚህ የልማት ፖሊሲዎች፣ ዕቅዶችና ስትራቴጂዎች በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች ተተግብረው ተመሳሳይ በሆነ መልኩ የሚፈለገውን ስኬት ሲያስገኙ አይታይም:: ለዚህም በምክንያትነት ከሚጠቀሱት መካከል የየክልሉ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ባህላዊ ተጨባጭ ሁኔታዎች ዋነኞቹ ናቸው::

እነዚህ የተለያዩ ጉዳዮች በምክንያትነት ቢጠቀሱም የማህበረሰቡ ባህል የሚያሳድረው አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ ሁነኛ ድርሻ ይኖረዋል ተብሎ ይታሰባል:: በዚህ ሃሳብ መነሻነት ይህ ጥናት አንፃራዊ በሆነ መልኩ "በልማት ወደ ኋላ ቀሩ" ከሚባሉት የሀገሪቱ

ክልሎች አንዱ በሆነው ክልል ላይ የተደረገ ነው። እነዚህ ክልሎች የአፋር፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ ጋምቤላና ሱማሌ ብሔራዊ ክልሎች ሲሆኑ በተለያየ ጊዜ "በልማት ወደ ኋላ የቀሩ"፣ "ልዩ ድጋፍ የሚሹ"፣ "ታዳጊ ክልሎች" በሚል የሚጠሩ ናቸው። ከ1998 ዓ.ም. ጀምሮም በፌዴራል መንግስት ደረጃ ስድስት ሚንስትሮችንና የየክልሎቹን ፕሬዘዳንቶች ያካተተ የፌዴራል እገዛ ቦርድ ተቋቁሞ በጋራ በማቀድና በመገምገም የባለሙያ እገዛም በማድረግ ለየክልሎቹ ልማት ትኩረት ተሰጥቶ እንቅስቃሴ እየተደረገ ይገኛል (የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር፣1995፣1999፣2003ዓ.ም) ይህ ጥናት የተደረገው በቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልል ሆኖ በክልሉ ከሚገኙ ነባር ብሔረሰቦች አንዱ ከሆነው ከበርታ ብሔረሰብ ባህል አኳያ ለሚካሄዱ የልማት ስራዎች ስኬታማነት ያሉ ምቹ ሁኔታዎች እና ተግዳሮቶች ምን መልክ እንዳላቸው ለመመርመር ነው።

ጥናቱ በዋናነት ዘጠኝ ምዕራፎች ይኖሩታል። በመጀመሪያው ምዕራፍ መግቢያ፣ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አካባቢ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ ዋናና ዝርዝር ዓላማዎች፣ የምርምሩ ጥያቄዎች፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የጥናቱ አካባቢ መረጣና የጥናቱ ገደብ፣ ያጋጠሙ ምቹ ሁኔታዎች፣ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሔ ርምጃዎች ይቀርባሉ። በምዕራፍ ሁለት የፅንሰ ሃሳብ ማዕቀፎች፤ በምዕራፍ ሦስት የተዛማጅ ጥናት ሥራዎች ቅኝትና ንድፈ ሃሳባዊ መሠረቶች ይተነተናሉ።

ምዕራፍ አራት በጥናቱ ሂደት የታለፉ ደረጃዎች፣ የጥናቱ ዘዴ፣ የጥናቱ አሠራር፣ የጥናቱ መልክና የመረጃ አሰባሰብና አተናተን ዘዴዎች ማብራሪያ ይቀርባሉ። በምዕራፍ አምስት ደግሞ የበርታ ብሔረሰብ ዋና ዋና ባህላዊ መልኮች የሆኑት አካላዊ መልክ፣ አለባበስና አጊያጊያጥ፣ የምግብ አሠራርና አመጋገብ፣ እንግዳ አቀባበል እንዲሁም ሀገረሰባዊ ልማዶች ይገለፃሉ።

ምዕራፍ ስድስት የበርታ ብሔረሰብ የህይወት ዑደት ምን እንደሚመስል የቀረበበት ሲሆን ጋብቻ፣ ልደትና ሞት በብሔረሰቡ ምን እንደሚመስል ለማሳየት ተሞክሯል።

ምዕራፍ ሰባት የአካባቢውን ልማት ለማፋጠን ያሉ የብሔረሰቡ አዎንታዊ ባህላዊ ጉዳዮች በስፋት የተተነተኑበት ሲሆን በምዕራፍ ስምንት ደግሞ ልማቱን የሚያስተጓጉሉ አሉታዊ ባህላዊ ጉዳዮች ተተንትነውበታል፡፡

ምዕራፍ ዘጠኝ የጥናቱ ውጤት ማጠቃለያና የይሁንታ ሃሳቦች የቀረቡበት ሲሆን በመጨረሻም ዋቢ መፅሐፍት፣ ልዩ ልዩ መረጃዎችና ፎቶግራፎች በአባሪነት ቀርበዋል፡፡

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

የባህልና ልማት ቁርኝትን በተለይም ባህል በኢኮኖሚ ልማት ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ ሲነሳ የማይታለፈው የMax Weber ሥራ ነው፡፡ Weber "The Protestant Ethic and the Spirit of Capitalism" በሚል ርዕስ እ.ኤ.አ. በ1930 ባሳተመው መፅሐፍ በአውሮፓ የመጣው የካፒታሊዝም መሰረት የፕሮቴስታንት እምነት ነው ይላል፡፡

በካፒታሊዝም የመጣው ዘመናዊ የኢኮኖሚ ዕድገት በፕሮቴስታንት ዕምነት ባህላዊ እሴቶች ላይ የመጣ ቀዳሚ ለውጥ ነው ባይ ነው፡፡ በፕሮቴስታንት እምነት መከሰት የተነሳ የዕምነቱ አራማጆችና ተከታዮች በብዛት ማምረትና መሸጥን፣ ቁጠባን፣ ፍትሃዊ የሆነ የንግድ ልውውጥን እንደ ዕምነቱ ምሶሶዎች አድርገው በመተግበራቸው ካፒታሊዝም ሥር መስደድ ጀመረ፡፡ በዕምነቱ ጠንካራ ሠራተኛ መሆን፣ በቁጠባ መኖር፣ ጊዜን በሥራ ማሳለፍ የገንዘብ ጥሪት መያዝና ማጠራቀም ተገቢ ብቻ ሳይሆን የሞራል ግዴታና ሃላፊነት እንደሆነ መቆጠር ሲጀመር ለካፒታሊዝም መሠረት ሆኗል ይላል (Weber, 1930)፡፡

በሌላ በኩል የሚታየው ደግሞ ከኢስያ ሀገሮች ዕድገት ጋር ተያይዞ የመጣው አስተሳሰብ ነው፡፡ ይሄ ደግሞ በተለይ የጃፓን ዕድገትን ከConfucian ዕምነት ጋር የሚያያዝ ነው፡፡ የኮንፊሺያን እምነት ለጃፓን የኢኮኖሚ ዕድገት መሠረት እንደሆነ የሚናገሩ ወገኖች

አሉ፡፡ (Kahn, 1993).ለምሳሌ የጃፓን ዕድገት ሊመጣ የቻለው ለዓለም ዝግ ያደረጉትን በራቸውን በመክፈት ከአሜሪካ ጋር በመርከብ ንግድ በመጀመራቸው እና አንድን ነገር አስመስሎ የመሥራት ተስጥኦ ስላላቸው ነው የሚሉ አስተሳሰቦች ቢኖሩም በ Tokugawa ዘመን የነበረው ሃይማኖታዊ አስተምህሮ ነው ይላል፡፡ በ1929[2] ሺ.ጋጉ በሚል ንቅናቄ መርህ የሆነው ከተለያዩ ዕምነቶች መልካም መልካም ሀሳቦችን አንድ ላይ አድርጎ የያዘ መንፈሳዊ ሆኖ ዓለማዊ መልክ ያለው እንቅስቃሴ በመሪዎቹና በሃይማኖት አባቶች ተቀባይነት በማግኘቱ ለጃፓን ዕድገት መሠረት ሆነ ይላል፡፡

የኮንፊሺያን እምነት ጠንካራ የቤተሰብ ትሥሥርን የሚያጎለብት ለቤተሰብ ስምና ደህንነት ሲባል ራስን እስከመሰዋት የሚደርስ ፈቃደኝነትን የሚያሰርፅ ነው፡፡ ታማኝነት፣ ዕውነተኝነት፣ ግለሰቦች መብታቸውን ለቡድን መብቶች ማስገዛትን፣ ለቡድን ዓላማ መሥራትን፣ በቡድኖች መካከል ጠንካራ ግንኙነት መኖርን የሥራ ትጋትና የቁጠባ ባህልን የሚሠብክ ስለሆነ በነዚህ የዕምነቱ ሥነምግባራት አማካይነት ካፒታሊዝም ሊያድግ ቻለ ይላሉ (Kahn, 1993, 169-172)፡፡

Landes David እንደሚሉት ጃፓኖች የመልካም ልምዳቸው መገለጫ በሆነው ውጤታማ አስተዳደራቸው፣ በከፍተኛ ደረጃ በመማራቸው፣ በጠንካራ ቤተሰባዊ ትሥሥራቸው፣ በሥራ ባህላቸውና ራስን የመግዛት ችሎታቸው፣ በብሔራዊ ማንነታቸው ባላቸው ስሜትና ውስጣዊ የበላይነታቸው አማካይነት ከጥንካሬዎቹ፣ ከባህሪያቱና ከዘዴዎቹ ጋር ወደተሟላ ዘመናዊነት ገብተዋል ይላሉ፡፡( Landes,2000;8)

በአፍሪካ ያለው ደግሞ ከዚህ በተለየ መልኩ ለኋላ ቀርነትና ለድህነት መነሻው ዕምነቶችና ሃይማኖቶች እንደሆኑ ይነሳል፡፡ አፍሪካ ማደግ ከፈለገች ከባህላዊ ማነቆዎቿ ተላቃ የምዕራባውያንን አስተሳሰብ መቀበል አለባት ብለው የሚከራከሩ ወገኖች እንዳሉ የአፍሪካን የልማት ሁኔታ ያጠኑ ምሁራን ያስረዳሉ (Ojameruay, 2005, Gebre,2005)፡፡

---

[2] በጥናቱ ውስጥ የኢትዮጵያ አቆጣጠር የሆኑት ዓ.ም. በሚል የተገለፁ ሲሆን ከዚህ ውጪ የሆኑት በአውሮፓውያን አቆጣጠር ናቸው፡፡

**ከእነዚህ ተመራማሪዎች መካከል** Gebre Yntiso **Culture and Development in Africa በሚለው ሥራቸው በባህልና ልማት ያለው ግንኙነት በተለያዩ ሁለት መንገዶች ሲገለፅ የኖረ እንደሆነ ገልፀው፡-**

> The link between culture and development has been conceptualized in many different ways. … There are two lines of arguments about the relationship between culture and development. The first one (now less popular) either denies any positive role culture in development or holds that the culture of developing countries are obstacles to development (Huntington and Weiner,1987; Black,1991; Crewe and Harrison, 1998). The assumption is related to the theory of modernization that explaind underdevelopment partly interms of cultural barriers and traditinalism, which are seen as internal problems of poor countries. The proponents of modernization theory proposed the replacement of indigenous practices in developing countries by modern practices to be borrowed from the developed nations…
>
> The second line of argument underlines that culture contributes to and benefits from development… Conceptually, this study inspired more by the approach that appreciates the complmentaritis of culture and development (Gebre, 2005; 12-13).

**በባህልና ልማት መካከል ያለው ግንኙነት በተለያዩ መንገዶች ሲገለፅ ይታያል፡፡ … በሁለቱ መካከል ያለው ግንኙነት የሚገልፁ ሁለት የክርክር ነጥቦች አሉ፡፡ አንደኛው የመከራከሪያ ነጥብና በአሁኑ ሰዓት ብዙም ተሰሚነት የሌለው፡- ባህል በልማት ውስጥ ምንም ዓይነት**

> አወንታዊ ሚና የለውም እንደውም የታዳጊ ሀገሮች ባህል ለልማታቸው እንቅፋት ነው የሚለው ሲሆን አስተሳሰቡ ከዘመናዊነት (Modernization) ቲዎሪ ጋር የተዛመደ ሆኖ የታዳጊ ሀገሮች ባህል ላለመልማታቸው ምክንያቱ በባህላዊና ልማዳዊ ተፅዕኖዎቻቸው ሳቢያ ያለ ውስጣዊ ክፍተትና ችግር እንደሆነ የሚገልፅ ነው፡፡ የዘመናዊነት ቲዎሪ አቀንቃኞች የሚመክሩትም ደሀ ሀገራት ለማደግ ከፈለጉ ሀገር በቀል እውቀታቸውንና ልማዳቸውን ካደጉ አገሮች በሚዋሷቸው ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች መተካት አለባቸው ብለው እንደሚከራከሩ ያስረዳሉ፡፡
>
> ሁለተኛው የመከራከሪያ ነጥብ ደግሞ ባህል ለልማት አስተዋፅዖ ሲኖረው ባህሉ ራሱ ከልማቱ ተጠቃሚ ይሆናል፡፡ ስለሆነም ባህልና ልማት እርስ በርስ የሚደጋገፉ ናቸው፡፡ ስለልማት ጉዳዮችም ስናነሳ ባህሉን ወደ ጎን ጥለን መሆን የለበትም፤ ብለው የሚከራከሩ እንደሆነ አሳይተው እሳቸውም ይህን ሁለተኛውን ሀሳብ ወስደው በጥናታቸው ለማሳየት እንደሞከሩ ገልፀዋል (Gebre, 2005; 12-13, ትርጉም የኔ)፡፡

Gebre በዚህ ሥራቸው የአፍሪካን ሁኔታ መሠረት በማድረግ የባህልንና የልማትን ግንኙነት ለማስረዳት ባህል ለልማት የሚኖረውን አዎንታዊ አስተዋፅዖ ለማሳየት ሞክረዋል፡፡ መነሻ ያደረጉትም የባህልን አሉታዊ ጎኖች ከማሳየት ይልቅ ጠቃሚ ጎኑን በማጉላት የልማት መሳሪያና ባህሉንም ለማልማት እንደሚቻል አዎንታዊ ጎኖች ያሏቸውን ጉዳዮች በአራት ዋና ዋና ክፍሎች በማስቀመጥ እንደሚከተለው ይዘረዝሯቸዋል፡፡ አንደኛ ድህነትን ለማጥፋት ያሉትን ማህበራዊ ትብብሮች፣ (የጋራ የሥራ ቡድኖች፣ የዕርሻ የጋራ የልማት ሥራዎች፣ የጎረቤታሞች የቁጠባና ብድር ማህበራት፣ ባህላዊ መረዳጃዎች፤ከተማ ምስርት ባህላዊ ማህበራት)፤ ሁለተኛ ባህላዊ የተግባቦት ሥርዓቶች በተለይም ኤች አይ ቪ ኤድስን ለመከላከል (ከባህላዊ ት/ ቤቶች

ጋር መስራት፣ ካለዕድሜ ጋብቻንና ብዙ ማግባትን ማስወገድ፣ ባህላዊ መድሃኒት አዋቂዎች ጋር መሥራት፣ ባህላዊ የመረጃ ልውውጦች)፤ ሦስተኛው የፆታ ዕኩልነትና የሴቶች ሚና (የሴቶችን መብት የሚጠብቁ ባህላዊ ተቋማት፣ የሴቶች የኢኮኖሚ አቅም፣ የሴቶች የበጎ ፈቃድ ማህበራት)፤ አራተኛው የህፃናት ጥበቃና አስተዳደግና የእናት ጡት ወተት ምገባ የሚሉ ናቸው።

ከላይ የተዘረዘሩትን ባህላዊ መሠረቶች ከ30 በላይ ሀገሮች ላይ ጥናቱን በማካሄድ በባህልና ልማት መካከል ያለው ግንኙነት የጠበቀና እርስ በርሱ የሚደጋገፍ መሆኑን አንዱ ለአንዱ አስተዋፅዖ የሚያደርግና እርስ በርስም ተጠቃቃሚ እንደሆኑ ይህ ደግሞ ሰዎች ኢኮኖሚያዊ፣ ዕውቀታዊ፣ መንፈሳዊ፣ ሞራላዊና ስሜታዊ ተጠቃሚነትን እንዲያገኙ ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥርላቸው ይገልፃሉ። በባህልና ልማት መካከል ያለው ግንኙነት ባህላዊ ጉዳዮች በልማት ስትራቴጂዎች ውስጥ መካተት እንዳለባቸው የሚያመለክት ነው ይላሉ።

Gebre በአፍሪካ ያለው ተግዳሮት የባህልን ውጤታማ ጠቀሜታ እንዴት ለላቁ የልማት ግቦች እንጠቀምበት የሚለው እንደሆነ ገልፀው ጥናቱ የአፍሪካን ባህል አዎንታዊ መልኮች በማሳየት ድህነትን ለማጥፋት ፣ ኤች አይ ቪ ኤድስን ለመዋጋት፣ ለፆታ ዕኩልነትና ሴቶችን ለማብቃት እንዴት መጠቀም እንደሚቻል ያመላከተና የአፍሪካ ማህበረሰብ ሀገር በቀል ዕውቀት ለልማት አስተማማኝ ሀብት የሚያስገነዝብ ነው በማለት ያጠቃልላሉ (Gebre, 2005; 35)።

ሀገራችን ኢትዮጵያንም አስመልክቶ እስከ ዛሬ ድረስ በልማት ወደፊት ላለመግፋቷና ለኋላ ቀርነቷ በውጪውም ሆነ በሀገር ውስጥ ምሁራን የተለያዩ ምክንያቶች ሲቀርቡ እንደቆዩ ይታወቃል። የራስወርቅ እንደሚሉት በተለይ ከ18ኛው ምዕተ ዓመት ወዲህ በብዛት ወደሃገራችን መግባት የጀመሩት ሚሲዎናውያንና ሀገር ጎብኚዎች ለሀገሪቷ ወደኋላ መቅረት የሚሰጡት ምክንያት በአብዛኛው በሀገሬው ዕምነት፣ ወግና ልምድ ላይ

የሚላክክ ነበር። የክርክራቸው አቅጣጫም ከሃይማኖታዊ ጉዳይ ይልቅ ወደ ባህላዊ ጉዳዮች ማመዘኑን የተመለከተ ነበር (የራስ ወርቅ፣2004፣14)።

ከሀገራችን ምሁራንም የአውሮፓንና የጃፓንን ሥልጣኔ በቦታው ተገኝተው የተመለከቱት ነጋድራስ ገብረህይወት ባይከዳኝንና ከበደ ሚካኤልን መጥቀስ ይቻላል። እነዚህ ምሁራን ሀገሪቱን ቀፍድዶ የያዘው በጊዜው የነበረው ሥርዓት የመሬት ሥሪት፣ ኋላ ቀር የአስተዳደር ሥርዓቶችን፣ የትምህርትና የሥልጣኔ አለመስፋፋት ወዘተ በዋናነት ቢያነሱም ባህላዊ ጉዳዮችንም ሳይጠቃቅሱ አላለፉም። (ገብረህይወት፣1916፣ከበደ ሚካኤል፣1946)

ይሁንና ባህል በልማት ላይ የሚያሳድረውን ተፅዕኖ አስመልክቶ በተለይ የተደረገና ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታ የሚመሳሰል ጥናት እስካሁን አላገኘሁም። ሆኖም በዚህ ዙሪያ በዋናነት የሚነሳ ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ ከመጋቢት 2001 እስከ ጥር 2003 ዓ.ም ድረስ "ባህልና ልማት" በሚል ርዕስ በየሁለት ወሩ ያዘጋጅ በነበረው የውይይት መድረክ ላይ በተጋበዙ ምሁራን በርዕሱ ዙሪያ የቀረቡ አስራ ሁለት ጥናታዊ ጽሑፎችን አንድ ላይ በማሰባሰብ በሺፈራው በቀለ አርታኢነት **ባህልና ልማት በኢትዮጵያ** በሚል ርዕስ በ2004 ዓ.ም ያሳተመው መጽሀፍ ይገኛል። በመጽሀፉ ከተካተቱት ውስጥ የየራስ ወርቅ አድማሴ "ባህልና ልማት፡- ምንነታቸውና ትስስራቸው"፣ የዘውዴ አበጋዝ "ባህል ከልማትና ከሥርዓተ ፆታ ጋር ያለው ግንኙነት"፣ የአሉላ ፓንክረስትና የገብሬ ይንቲሶ "አገራዊ ዕውቀትና ተዛማጅ ቴክኖሎጂ በኢትዮጵያ"፣ የፈቃደ አዘዘ "ቁዘማ፡- ፎክሎር (ባህል) እና ልማት በኢትዮጵያ" የሚሉት ጥናቶች በሀገራዊነታቸውና በሚያነሱት ጉዳይ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያያዙ ጭብጦች ስላሏቸው የጥናት አቅራቢዎቹን እየጠቀስኩ በጥናቴ የምጠቀምባቸው ይሆናሉ።

በአጠቃላይ ሲታዩ ግን በተለይ ይህ ጥናት የሚያተኩርበትን የቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልልን በተለይም ደግሞ የበርታን ብሔረሰብ የማይመለከቱ በመሆናቸው ከዚህ ጥናት ይለያሉ። ይህ ጥናት ባህልና ልማት የሚኖራቸውን ቁርኝትን ለማሳየት ዕውን

በሆነው በበርታ ብሔረሰብ ባህል አውድ ላይ ተገኝቶ ተጨባጭ ማስረጃዎችን እያቀረበ የሚያሳይ በመሆኑ ከተጠቀሱት ጥናት አቅራቢዎች የተነሱ የባህልና የልማት ቁርኝትን የሚመለከቱ ጉዳዮችን ለማስረገጥ(ለማረጋገጥ) የሚያስችል መረጃ ሊያስገኝ ይችላል ተብሎ ይታመናል፡፡

የዚህ ጥናት ትኩረት በሆነው በበርታ ብሔረሰብ ላይ ጥናት በማድረግ Alessandro Triulzi የተባለ የታሪክ ተመራማሪ **Salt, Gold and Legitimacy** በሚል ርዕስ እኤአ በ1981 ያሳተመውን መፅሃፍ እናገኛለን፡፡ ይህ መፅሃፍ የጥናቱ ትኩረት የሆነው የበርታ ብሔረሰብን ማንነትና አመጣጥ፣ አሠፋፈር፣ የአኗኗር ባህል፣ ሃይማኖትና ልማድ የዳሰሰ ነው፡፡ መፅሐፉ በውጪ አጥኚ የተፃፈና፣ ዘመኑም ራቅ ያለ ቢሆንም የያዛቸው አንዳንድ መረጃዎች ለዚህ ጥናት ግብዓት ማመሣከሪያዎች በመሆን አገልግለዋል፡፡ ሌሎች የበርታን ብሔረሰብ አስመልክቶ የተሰሩ ጥናቶች ዳሰሳ በተዛማጅ ሥራዎች ቅኝት ሥር የሚቀርብ ይሆናል፡፡

## 1.2. የጥናቱ አካባቢ

በዚህ ክፍል የጥናቱ አካባቢ የሆነው የቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልል አጠቃላይ ገፅታና የጥናቱ ዋነኛ ትኩረት የሆነው የበርታ ብሔረሰብና አካባቢው፣ ታሪካዊ አመጣጥ፣ አኗኗር፣ ማህበራዊ፣ መንፈሳዊ ገፅታና ልዩ ልዩ መገለጫዎቹ በዝርዝር ይቀርባሉ፡፡

### 1.2.1. የቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልል አጠቃላይ ገፅታ

የቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልል ከኢትዮጵያ ዘጠኝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት አንዱ ሆኖ በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍል የሚገኝ ክልል ነው፡፡ 50 ሺህ 380 ስኩዌር ኪሎ ሜትር ስፋት ይዞ የሚገኘው ይ□ው ክልል 3 ዞኖችና 20 ወረዳዎች ያሉት ሲሆን በሰሜን ከአማራ፣ በምስራቅ ከኦሮምያ፣ በደቡብ ከጋምቤላና በምዕራብ ከሱዳን ይዋሰናል

(CSA, 2007)። በአሁኑ ሰዓት የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታም የሚካሄደው በዚሁ ክልል ነው።

የኢፌዴሪ ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ እ.ኤ.አ. በ2007 ባደረገው የሕዝብ ቆጠራ እንደሚያመለክተው በክልሉ 784 ሺህ 345 ህዝብ የሚኖር ሲሆን በርታ፣ ጉሙዝ፣ ሽናሻ፣ ማኦና ኮሞ የተሰኙ አምስት ነባር ብሔረሰቦችን ጨምሮ አማራ፣ ኦሮሞ፣ አገው፣ ትግራይ፣ ሀድያና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎችም በክልሉ ይኖራሉ። ከነዚህ መካከል የበርታ ብሔረሰብ ብዛት 199 ሺህ 303 ወይም 25.4% በመሆኑ ከፍተኛውን ቁጥር

ይይዛል።

ከክልሉ ህዝብ ሁለተኛውን ደረጃ የሚይዘው የአማራ ብሔር ሲሆን ብዛቱም 170 ሺህ 132 (21..7%) ነው። በህዝብ ብዛት ጉሙዝ፣ ኦሮሞ፣ ሺናሻ፣ አገው፣ ማኦ፣ ኮሞ፣

ትግራይ፣ ሃዲያ በቅደም ተከተል እንደሚገኙ የማዕከላዊ ስታትስቲክስ መረጃ ያስረዳል (CSA, 2007)። ዝርዝሩን ከሠንጠረዥ አንድ መመልከት ይቻላል። የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የተለያዩ የተፈጥሮ ሀብቶች እና ሰፋፊ የኢንቨስትመንት አማራጮች ያሉበት ክልል ነው። በክልሉ ከሚገኙ ተፈጥሮኣዊ ሀብቶች መካከል ወርቅ፣ እምነበረድ፣ የእጣንና የሽቶ ዛፎች የሚጠቀሱ ናቸው።

## ሠንጠረዥ አንድ፡- በቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አንድ ሺህና[3] ከዚያ በላይ ቁጥር ያላቸው ብሔረሰቦች ቁጥርና የመቶኛ ስሌት

| ብሔረሰብ | 1994 | | 2007 | |
|---|---|---|---|---|
| | የህዝብ ብዛት | | የህዝብ ብዛት | |
| | ቁጥር | % | ቁጥር | % |
| በርታ/ጀብላዊ | 115602 | 14.7 | 199303 | 25.4 |
| አማራ | 102061 | 13.0 | 170132 | 21.7 |
| ጉሙዝ | 107495 | 13.7 | 163781 | 20.9 |
| ኦሮሞ | 58833 | 7.5 | 106275 | 13.5 |
| ሺናሻ | 32105 | 4.1 | 60587 | 7.7 |
| አገው | 17545 | 2.2 | 33061 | 4.2 |
| ማኦ | 2732 | 0.3 | 15384 | 2.0 |
| ኮሞ | 1109 | 0.1 | 7773 | 1.0 |
| ትግራይ | 3918 | 0.5 | 5562 | 0.7 |

ምንጭ፡- የኢፌዴሪ ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ 2007 የሕዝብና ቤት ቆጠራ ውጤት

[3] ሠንጠረዡ የሚያመለክተው በክልሉ የሚኖሩ ቁጥራቸው አንድ ሺህና ከዚያ በላይ የሆኑ ብሔረሰቦችን ብቻ በመሆኑ ጠቅላላ ድምሩ ላይ የሚኖረው ልዩነት ከዚያ የተነሳ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

### 1.2.2. የበርታ ብሔረሰብና አካባቢው

በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ከሚገኙ አሶሳ፣ ካማሽና መተከል ከሚባሉት ሦስት ዞኖች የበርታ ብሔረሰብ የሚገኘው በአሶሳ ዞን ውስጥ ነው:: ዞኑ አሶሳ፣ ባምባሲ፣ መንጌ፣ ሸርቆሌ፣ ሆሞሻ፣ ኩርሙክ፣ አዳቢልና ዳጉላ የተሰኙ ስምንት ወረዳዎች አሉት:: የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነው የበርታ ብሔረሰብ መኖሪያ የሆነው አሶሳ ዞን ትንንሽ ኮረብታዎችና ጉብታዎች ያሉትና ከባህር ጠለል በላይ በአማካይ ከ1500-1800 ሜትር ከፍታ ላይ የሚገኝ ነው:: በጣም ዝቅተኛ በሆነው የዞኑ ሰሜናዊ ድንበር ላይ ጥቁር አባይ ኢትዮጵያን አቋርጦ ወደ ሱዳን የሚፈስበት ስፍራ ይገኛል::

በክልሉ የሚገኙት ጠማትና ዱባስ የሚባሉት ወንዞች የጥቁር አባይ ገባሮች ሲሆኑ ሸርቆሌ ወንዝ ደግሞ በሱዳን በኩል ወዳለው ድንበር ወደሚገኘው ረግረጋማ ሥፍራ በመፍሰስ ሀገሪቱን ከሱዳን ያዋስናል (ቤጉክማባቱማቢ፣1996፣20፣ Tariku, 2002, 13) :: የወረዳውና የክልሉ ዋና ከተማ አሶሳ ከአዲስ አበባ በ687 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች::

### 1.2.3. የበርታ ብሔረሰብ ታሪካዊ አመጣጥና ስያሜ

በርታ በምስራቅ ሱዳን ያለውን የገሪን ሰፊ ግዛትና በኢትዮጵያ ውስጥ የአባይና የደቡብ ሸለቆን አካባቢ ይዞ ለረጅም ጊዜ የቆየ ጥንታዊ የአፍሪካ ማህበረሰብ እንደሆነ መረጃዎች ያመለክታሉ:: በርታዎች ከጥንት ጀምሮ ከሚኖሩባቸው አንዱ በሆነው የአሁኑ መንጌ[4] ወረዳ ውስጥ የነገስታቱ አፅም ማረፊያ የሆነ "ቤላ ሻንጉል" የሚሉት ትክል ድንጋይ ይገኛል:: "ቤላ ሻንጉል" የሚለው ቃል የብሔረሰቡ ቋንቋ በሆነው ሩጣንኛ "ቤላ" እና

---

[4] ድንጋዩ የሚገኘው በመንጌና ሸርቆሌ ወረዳዎች ድንበር ላይ በመሆኑ ሥፍራው የሸርቆሌ ወረዳ ክልል ነው የሚሉ ሰዎች አጋጥመውኛል::

“ሻንጉል” የተሰኙ ሁለት ቃላት ጥምር ሆኖ “ቤላ” ማለት ድንጋይ ማለት ሲሆን “ሻንጉል” ደግሞ ህዝብ ወይም ልጅ ማለት እንደሆነ የአካባቢው ሽማግሌዎች ይገልፃሉ። ንጉስ ወዳጅነህ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያው ባቀረበው ጥናት ድንጋዮቹ ሰባት እንደሆኑና እስከዛሬ ድረስ የአምልኮ ሥርዓት እንደሚካሄድባቸው (ንጉስ፣2001 ዓ.ም.) የገለፀ ቢሆንም እኔ ባገኘሁት መረጃ ድንጋዩ አንድ ብቻ መሆኑን አረጋግጫለሁ (አባ አቶም፣ቃመ25/04/05 ፣አባ ሀሰን አጁሰሌ፣ቃመ11/04/05፣ አዲስ ምዕራፍ፣2000፣21)። የድንጋዩ ቁመት አንድ ሜትር አካባቢ እንደሚሆንና ከላዩም ላይ ሌላ ክብ ድንጋይ እንደተቀመጠበት ይናገራሉ። ድንጋዩ በቆመበት ቦታ ሾላ ዛፍ የነበረ ሲሆን ዛፉ ከማርጀቱ የተነሳ ወድቋል። ድንጋዩን ለማየት ሄጄ “ጊዜጠሪያ” ቀበሌ አግኝቻቸው ቃለመጠይቅ ያደረኩላቸው የ80 ዓመቱ አባ ሀሰን አጁሰሌ እንደሚሉት ብሔረሰቡን የሚያስተዳድሩ የቀደሙ ነገስታት አፅም የሚያርፈው እዚሁ ሥፍራ ነበር። “ድንጋዩ የተተከለው ጥንት በአጉር (ንጉሥ) አሆም ሆምና በቶር አልቡሪ ጊዜ ነው። ከዚያም ደጃች ሙሃመድ፣ ደጃች ሙስጠፋ ድንጋዩን ከሱዳን አምጥተው ተክለውት ነገሥታቱ ሲሞቱም የሚቀበሩበት ቦታ ነበረ። “ቤላ” ማለት ድንጋይ “ሻንጉል” ደግሞ ልጆች ማለት ነው። ሲፈታ የሻንጉል ልጆች ማለት ነው” (*አባ ሀሰን አጁሰሊ፣ቃመ*11/04/05*)* ብለዋል።



ፎቶ1 ቤላ ሻንጉል የተሰኘው ድንጋይ

የድንጋዩን ተምሳሌታዊ ፍቺም ሲያስረዱ የቆመው ድንጋይ ንጉሱን፣ ከላዩ ላይ የተቀመጠችው ክብ ድንጋይ ደግሞ ህዝቡን እንደምትወክል ያስረዳሉ፡፡ ተምሳሌቱም ህዝቡ በንጉሱ ዙሪያ እንዳለና የበላይ እንደሆነ ንጉሱም ህዝቡን እንደምሰሶ ቆሞ በዙሪያው ሰብስቦ እንደሚጠብቅ የሚያሳይ ነው ይላሉ፡፡ “..ይህቺ ክብ ድንጋይ ንጉሱ ሲሞት ማንም ሳይነካት ወዲያውኑ ከቆመው ድንጋይ ላይ ተንከባላ አቅራቢያው ከሚገኝ ጉድጓድ ውስጥ ትወድቃለች፡፡ ሌላ ንጉስ ሲተካም ጥቁር በሬ፣ ፍየል፣ ወይም ዶሮ ታርዶ ወደ ቦታዋ ትመለሳለች እንጂ ይህ ሳይሟላ ማንም ሰው አንስቶ ወደ ሥፍራዋ አይመልሳትም” (አባ ሀሰን አጁሰሊ፣ቃመ11/04/05) ይላሉ፡፡

የማህበረሰቡን መጠሪያ በሚመለከትም "ቤላ ሻንጉል" የሚለው እንጂ ሌላው ስያሜ እንደማይገልፃቸው ይናገራሉ:: "እኔ አሁን ምንድነህ ብባል ቤላ ሻንጉል ነኝ ነው የምለው፤ በርታ ማለት 'ባሪያ' ተገዝቶ የሚኖር ማለት ነው፤ እኛ ባሪያ አይደለንም:: ይህንን ስያሜ ያመጣብን አቶ ያረጋል ነው" (አባ ሀሰን አጁስሊ፣ቃመ11/04/05):: በርታ በሚለው መጠሪያ የማይስማሙት አባ ሀሰን ብቻ አይደሉም:: አብዛኞቹ የማህበረሰቡ አባላት እንደማይቀበሉት ጥያቄውን ያነሳሁላቸው ብዙዎቹ ሰዎች ይናገራሉ::[5] እነዚህና ሌሎች ጥያቄውን አንስቼ አስተያየታቸውን የጠየቅኳቸው ሁሉ በርታ የሚለውን ስያሜ እንደማይቀበሉት ይናገራሉ:: በሸርቆሌና መቃዚን በተደረጉ የቡድን ውይይቶችም ይሄው ሀሳብ ተነስቶ ስያሜው እንደማያስደስታቸውና "ቤላ ሻንጉል" መባልን እንደሚመርጡ ተናግረዋል::

በሌላ በኩል አቶ አልሀሰን አብዱራሒም ሆጀሌ የተባሉት መረጃ ሰጪዬ ይህንን ጉዳይ አንስቼ ስጠይቃቸው "ቤላ ሻንጉል" የአንድ አካባቢ ስም እንጂ የብሔረሰቡ ስም ሊሆን እንደማይችልና በርታ የሚለው መጠሪያ ትክክለኛው የብሔረሰቡ መጠሪያ እንደሆነ ይናገራሉ:: "ቤላ ሻንጉል የብሔረሰብ ስም ሳይሆን የእስቴት ስም ነው፤ የአንድ አካባቢ መጠሪያ ስም ማለት ነው፤ ትርጉሙም የሻንጉል ልጆች ሳይሆን በልሻንጉሩ ማለት በበርታ የውቃቢ ድንጋይ ማለት ነው፤ ድንጋዩም አሁን እዛ አለ፤ በዚያ ሰው ሲያልፍ አንድ ድንጋይ ጥሎ ይሄዳል ሲመለስ አንድ ድንጋይ ይጥላል እና "እስቴት" ደሞ የብሔረሰብ መጠሪያ አይሆንም" (አቶ አልሀሰን አብዱራሒም፣ ቃመ15/ 03/05)::

---

[5] (አባ አቶም ሙስጠፋ፣ቃመ25/04/05፣ አባ ናይል አሚር፣ቃመ14/04/05፣ አባ ኢብራሂም አደም ቃመ14/04/05፣ ወ/ሮ ሲቲና አደም፣ ቃመ25/04/05፣ ወ/ሮ ቢተሚና አልቃሲም፣ ቃመ28/02/05 እና ወ/ሮ አስያ ረጃ፣ ቃመ11/04/05)

(መረጃዎችን በግርጌ ማስታወሻ ለማምጣት የተፈለገው ከሁለት በላይ ሲሆኑ መደዳውን በመዘርዘር የሚፈጠረውን የገፀ ንባብ አሰልቺነት ለመቀነስ ነው::)

እሳቸው ይሄንን ቢሉም የብሔረሰቡ ዋነኛ መኖሪያ በሆኑት ይሄ ጥናት በሚያካትታቸው ሸርቆሌና መንጌ ወረዳዎች ያለው ማህበረሰብ “በርታ” የሚለውን መጠሪያ እንደማይቀበልና “ፀያፍ” አድርጎ እንደሚመለከተው በቡድን ውይይት ወቅት አረጋግጫለሁ:: በሌላ በኩል ግን ይህንን የሳቸውን ሃሳብ የሚጋራ የብሔረሰቡ አባል ከመረጃ አቀባዮቹ ማግኘት አልቻልኩም::

የማህበረሰቡን መጠሪያ አስመልክቶ በተለያዩ ጊዜያትና ህዝቦች የተለያየ መጠሪያ ሲሰጠው ይታያል:: ቀደም ባለው ጊዜ በርታዎች ከሜዳማ ሥፍራ ይልቅ በተራራማ አካባቢዎች የመስፈር ልማድ ስላላቸውም ለንግድ የመጡ አረቦች ይህንን በማየት "ጀብላዊ" የሚል ስያሜ ሰጥተዋቸዋል፤ በአረብኛ "ጀብላዊ" ማለት በተራራ ላይ የሚኖሩ ህዝቦች ማለት ነው *(Triulzi,1981፣* Tesfaye, *1990, ንጉስ፣2001)*:: በርታዎች በተራራ ላይ የመኖራቸው ምክንያቶች አንድም በጥንት ጊዜ በአካባቢው ከነበረው ጥቅጥቅ ደን ውስጥ በብዛት ከሚኖሩ የዱር እንስሳት ጥቃት ራሳቸውን ለመከላከል ሲሆን አንድም ከባዕድ ወራሪዎች ራሳቸውን ለመጠበቅ ስትራቴጂክ ቦታዎችን መምረጣቸው እንደሆነ ይገመታል:: ከዚህ በተጨማሪም በርታዎች ውጥዋጥ፣ ሻንቅላ፣ መዩ (ቅይጥ ህዝብ)፣ ወዘተ በሚሉ ስያሜዎች ሲጠሩ እንደነበር መረጃዎች ያመለክታሉ (ቤጉክማባቱማቢ፣ 1996፣ 25፣ Tesfaye, 1990,3፣ ንጉስ፣ 2001፣ 13-14)::

በአሁኑ ጊዜ ሌሎች በአካባቢው የሚኖሩ ማህበረሰቦች በርታዎችን “አረብ” እያሉ ይጠሯቸዋል:: መነሻውም ከሱዳን የመጡ ጥቁር አረቦች ናቸው ከሚል ነው:: አሶሳ ከተማ ውስጥም “አረብ ሠፈር” የሚባል በተለይ የብሔረሰቡ ተወላጆች የሚኖሩበት ሠፈር ይገኛል::

የበርታ ህዝብ በርካታ ጎሳዎችና የጎሳ መጠሪያዎች አሉት:: ጎሳዎቹን “ፋ” የሚል መጠሪያ በማስቀደም ይለያቸዋል:: “ፋ” ማለት በበርትኛ ሰው ማለት ሲሆን ጎሳዎቹ ከየመጡበት አካባቢ አንፃር ለመጠራት እንጂ በአሁኑ ወቅት በባህልና በስነልቡና የተሳሰሩ አንድ ህዝቦች ለመሆን ችለዋል:: ከነዚህም መካከል “ፋ ሁንሁን”፣ “ፋ ሶቤ”፣ “ፋ ቤጉ”፣ “ፋ

ናርባንዱ"፣ "ፋ መድቡዕ"፣ "ፋ ሀሩ"፣ "ፋ ሁንዱ"፣ "ፋ ዱሽ"ና "ፋ ዱል" አንጋፋዎቹ ናቸው።[6]

ህዝቡ በአብዛኛው የሩጣና (የበርትኛ) እና የአረብኛ ቋንቋን የሚናገር ሲሆን አማርኛና ኦሮምኛም በአብዛኛው ማህበረሰብ ዘንድ በተለይ በወጣቱና በከተሜው ይነገራሉ። አሁን ባለው የክልሉ መንግስት አስተዳደር የብሔረሰቡ ስያሜ በጥቅል "በርታ" በሚባለው ስያሜ በመሆኑ በዚህ ጥናትም ይህንኑ ስያሜ እጠቀማለሁ።

### 1.2.4. የበርታ ብሔረሰብ መተዳደሪያ

በርታዎች ከጥንት ጀምሮ በእርሻና ከብት በማርባት የሚተዳደሩ ነበሩ። በአካባቢው በሽታ ገብቶ ከብቱ በማለቁ ምክንያት አሁን በከብት እርባታው ብዙም አይታወቁም። አካባቢው አሁንም ድረስ ጥቅጥቅ ባለ ደንና ረጃጅም ሰንበሌጥ (ፊላ) እና ቀርከሃ የተሸፈነ ነው። ቀርከሃ ለበርታዎች ለቤት መስሪያ፣ለአጥር፣ ለመዝጊያ፣ እህልን ለማከማቻ ጎተራ፣ለቤት ውስጥ ቁሳቁስ መስሪያ፣ለሙዚቃ መሳሪያዎች፣ ለዘንግና ማገዶን ጨምሮ ለሌሎች ልዩ ልዩ አገልግሎቶች ይውላል።

አካባቢው ለእርሻ ሥራ ተስማሚ ለም መሬት ያለው በመሆኑም የበርታዎች አንዱ መተዳደሪያ እርሻ እንዲሆን አድርጎታል። በርታዎች የመሬት ጥበት ስለሌለባቸው መሬታቸውን አፈራርቀው የማረስ ልምድ አላቸው። ይህንኑ የእርሻ ሥራ የሚያካሂዱት በሬ ጠምደው በማረስ ሳይሆን "ጳሌ" በሚሉት ዶማ ቆፍረው በመዝራት ነው። አሁን አሁን ግን በደጋማ አካባቢዎች የተለመደው የእርሻ መሬት ምንጣሮና የበሬ እርሻ በባምባሲና አሶሳ ወረዳዎች ላይ በአካባቢያቸው ከሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎች በመምጣት

[6] (አባ አልሀሰን አብዱራሂም፣ ቃመ15/03/05፣ አባ አቶም ሙስጦፋ፣ ቃመ25/04/05፣ ቤጉክማባቱማቢ፣1996፣25፣ Tesfaye, *1990,3፣*)

በሰፈሩ ህዝቦች ሲከወን ይታያል። በእርሻ ሥራ ማሽላ፣ በቆሎ፣ ቁንቁፅ[7]፣ እና የጓሮ አትክልቶችን ያመርታሉ።



ፎቶ 2. የበርታ አርሶ አደር በጻሌ መሬቱን እየቆፈረ

[7] ቁንቁፅ በሩጣንኛ (በበርታ ቋንቋ) ሲሆን "ባሚያ"፣ "ዋይካ"፣ በሚሉ የተለያዩ መጠሪያዎች የሚታወቅ ፣ በዓለም ላይ "Okra(ኦክራ)" እና "gumbo( gumebo)" በሚል የሚታወቅ መሆኑን በክልሉ ማስታወቂያ ቢሮ የሚታተመው አዲስ ምዕራፍ መፅሔት፣(2000፣ከገፅ15-16) ይገልፃል። ስለ ቁንቁፅ አገልግሎትና አጠቃቀም ወደፊት ስለብሔረሰቡ አመጋገብ ሳነሳ የምመለከተው ይሆናል።

በርታዎች በእርሻ ብቻ ሳይሆን ንብ በማነብና አሁን እየቀረ ቢመጣም በአደን ሥራም ይተዳደራሉ፡፡ ሌላው የበርታዎች መተዳደሪያ ባህላዊ የወርቅ ቁፋሮ ነው፡፡ ከጥንት ጀምሮ ትልቅ ጉድጓድ በጥልቀት በመቆፈርና ወርቅን ከደለል አፈር አንገዋሎ በመለየት ባህላዊ በሆነ መንገድ አምርቶ በመሸጥ መተዳደር የበርታዎች መለያ ነው፡፡ የወርቅ ቁፋሮውንና ከአፈር የማጣራቱን ሥራ እስከ ዛሬ ድረስ በአብዛኛው የሚከውኑት ሴቶች ናቸው፡፡ አካባቢው በወርቅ ሀብቱ የበለፀገ በመሆኑም ክልሉ ቀደም ባሉት ጊዜያት ለማዕከላዊ መንግሥት ሳይቀር በዓመት እስከ 96 ኪሎ ግራም ወርቅ በመገበር ይታወቅ ነበር (*Triulzi*,1981,1፣ *ንጉሴ፣2001 ፣18)* ፡፡

በርታዎች አነስተኛ የንግድ ልውውጥ በማድረግም የታወቁ ናቸው፡፡ ከእርሻውም ሆነ ከወርቅ ቁፋሮው ጎን ለጎን እስከ ሱዳን ድረስ ገብቶ አነስተኛ ንግዶችን በመነገድና በመስራት ይተዳደራሉ፡፡ በጥንት ጊዜ ወርቅ ቆፍረው ከሱዳን ሰዓት፣ ራድዮና አልባሳትንም ጭምር ይለውጡ ነበር (*Triulzi,* 1981,5)፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የሸክላና የቀርከሃ ሥራን የመሳሰሉ አነስተኛ የእደጥበብ ውጤቶችን አምርተው በመሸጥም ኑሯቸውን ይደጉማሉ፡፡

## 1.3. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

በኢትዮጵያ ካሉት ዘጠኝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት ውስጥ "በልማት ወደኋላ የቀሩ" የሚባሉ አራት ክልሎች ይገኛሉ፡፡ ለእነዚህ ክልሎች በልማት ወደ ኋላ መቅረት ምክንያት የሆኑ ብዙ ጉዳዮች ቢኖሩም አንዱ ዋነኛ ጉዳይ የየክልሎቹ ማህበረሰቦች ባህል በወጉ ተጠንቶ የልማት ዕቅዱን ለማስተግበር የሚኖረው አስተዋፅዖ ግምት ውስጥ አለመግባቱ ይሆን የሚል አመለካከት ካደረብኝ ቆይቷል፡፡ ይህ አመለካከት እንዲያድርብኝና እንድገፋበትም ያደረጉኝ ምክንያቶች አንደኛ በዘርፉ ምሁራን የተፃፉና ስለባህልና ልማት ቁርኝት የሚያስረዱ የተለያዩ ፅሑፎችን ማንበቤና ይልቁንም ደግሞ ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ ይህንኑ ጉዳይ አስመልክተው በክፍል ውስጥም ሆነ በልዩ ልዩ ጽሑፎችና መድረኮች

የሚያነሷቸው ነጥቦች ትኩረቴን ስለሳቡት ነው (ፈቃደ፣1996፣ 2002፣ 2004፣[8]፣ Sims & Stephens, 2005, Radcliffe, 2006; UNESCO, 2005, 2010 )::

ሁለተኛ ቀደም ሲል እሠራበት ከነበረው ግብርና ሚኒስቴር ውስጥ ለሥራ ጉዳይ ወደ ተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በምዘዋወርበት ጊዜ አንዳንድ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ተቀባይነታቸውና ተግባራዊነታቸው እምብዛም የሚሆነው ለማህበረሰቡ ባህልና ሀገር በቀል ዕውቀት እንግዳ ሲሆኑ መሆኑን በመታዘቤ ነው። ለምሳሌ በጨንቻና አካባቢው ውጤታማ የሆነው የደጋ ፍራፍሬ አፕል ለቋሚ ተክሎች እንግዳ ለሆነው የመንዝ አርሶ አደር ብዙም ትኩረት ሳይቸረው "ላም አለኝ በሰማይ ወተቷንም አላይ" ዓይነት ጉዳይ አድርጎ እንደቆጠረው ማየቴ ነው።

ሦስተኛ ለመጀመሪያ ዲግሪ ተማሪዎች የሚሰጠውን ፎክሎርና ልማት (Folklore and Development) የተሰኘውን ኮርስ ሳስተምር ተማሪዎቹ በየአካባቢያቸው በመንግስት ታቅደው የተላኩ ማህበረሰቡ ዘንድ ሲደርሱ ተቀባይነት ያገኙና ያላገኙ፣ ተተግብረውም ውጤት ያመጡና ያላመጡ የልማት ዕቅዶችን በማንሳት እንዲወያዩ አደርጋለሁ። በውይይቱም ውጤታማ የሚሆኑት ብዙዎቹ የልማት ዕቅዶች ከማህበረሰቡ ባህል ጋር ስምም የሆኑት፣ ያልተተገበሩት ግን በአብዛኛው ከባህሉ ጋር ያልተጣጣሙት መሆናቸውን ስለታዘብኩ በሀሳቤ እንድገፋና "በልማት ወደ ኋላ ከቀሩት" ክልሎች አንዱን በመምረጥ ባህልና ልማት ያላቸውን ቁርኝት ለማጥናትና የማህበረሰቡ ባህል በልማት ሥራዎች ላይ የሚያሳድረው አወንታዊም ሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ መኖሩን በመገንዘብ ባህሉን የልማት መሣሪያ ማድረግ የሚቻልበት መንገድ ይኖር እንደሆነ ለመፈተሽና ለማረጋጋጥ መሻቴ ነው።

---

[8] ዶ/ር ፈቃደ ባህልና ልማት በሚል ርዕስ ሰኔ 18 ቀን 1996 ዓ.ም. "የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር" ባዘጋጀው "የርዕይ 2020" መድረክና መጋቢት 17 ቀን 2002 ዓ.ም. "ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ" ባዘጋጁት መድረክና በ2004 ዓ.ም ባሳተመው መጽሐፍ ላይ ጉዳዩን በተደጋጋሚ አንስተዋል፡፡

አራተኛ "በልማት ወደኋላ የቀሩ" ከሚባሉት ክልሎች አንዱ የሆነው የቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልል ማህበረሰብ በሀገሪቱ ምዕራባዊ ጠረፍ የሚገኝ፣ የራሱ የሆነና የዳበረ ባህል ያለው ነው:: በተጨማሪም አጎራባች ከሆኑት ከጋምቤላ፣ ከኦሮሚያ፣ ከአማራና ከሱዳን ሕዝቦች ጋር ግንኙነት የሚያደርግ ሕዝብ በመሆኑ ከሌሎች ማህበረሰቦች ባህል ጋር ሰፊ ግንኙነትና ተራክቦ ያለው አካባቢም ነው:: ከመሃል አገርም በብዙ ኪሎ ሜትሮች የራቀ ነው:: ይሄ ሁሉ ሆኖ ባህሉ እስከዛሬ በወጉ ያልተጠና በመሆኑ ለክልሉ ልማት የሚያበረክተው አስተዋፅዖና ያስከተለው ተግዳሮት ይኖራል ብዬ በማሰቤ ነው::

አምስተኛ በ 2003 ዓ.ም Contemporary Issues in Ethiopian Folklore (FOLK 806) ለተሰኘው ኮርስ የመስክ ስራ የምንሠራበትን ወረዳ እንድንለይ ሲነገረን የመረጥኩት ታዳጊ ከሆኑት የሀገራችን ክልሎች አንዱን ወስጄ በዚያው በመገኘት የአንድ ወረዳ ፎክሎር መሰብሰብ ነበር:: ለዚህም ትኩረቴን የሳበው የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልል ነበር::

ክልሉን የመረጥኩበት ዋና ምክንያት ቀደም ሲል የተጫረብኝን ሃሳብ ማረጋገጥ የሚያስችል ፍንጭ አገኝ እንደሆነ ብዬ በማሰቤ ነበር:: በተጨማሪም የክልሉን ማህበረሰብ ባህል አስመልክቶ የተሠራ ብዙ ነገር ስላላጋጠመኝ አንዱን ወረዳ መርጬ የተገኘውን ፎክሎር ብሰበስብ አንደኛ የኮርሱን የቤት ሥራ አሟላለሁ፤ ሁለተኛ መጀመሪያ በሀሳቤ የተጫረውን ጉዳይ ገፍቼ ለመሄድ የሚያስችል መነሻ አገኛለሁ የሚል እምነት ስላደረብኝ ነው:: በመሆኑም ምንም እንኳን አካባቢው ሩቅና እኔም ከዚህ በፊት ሄጀበት የማላውቅ ቢሆንም እንዲሁም ለመስክ ስራው የተመደበው ገንዘብ ዕቅዴን የሚያሳካ መስሎ ባይታየኝም ችግሩን ተቋቁሜ መሄድ እንዳለብኝ በመወሰን ሐምሌ 11 ቀን 2003 ዓ.ም. ጉዞዬን ወደ ክልሉ ዋና ከተማ አሶሳ በማድረግ ለ28 ቀናት በክልሉ በመቆየት ያገኘሁትን መረጃ ሰብስቤ ተመልሻለሁ::

ከላይ እንደተገለፀው በዚህኛው የመስክ ቆይታ ለተሰጡኝ Contemporary Issues in Ethiopian Folklore (FOLK 806) ለተባለው ኮርስ ማሟያነት “የሸርቆሌ ወረዳ ፎክሎር” በሚል ርዕስ Advanced Seminar in Folklore and Development (FOLK804)

ለተባለው ኮርስ "ልማትና ባህላዊ ተግዳሮቶች በቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት" በሚል ርዕስ፣ Seminar in Cultural Policy (FOLK 802) ለተባለው ኮርስ ማሟያነት ደግሞ "የሸርቆሌ ወረዳ የባህል ፖሊሲ" በሚል ርዕስ በ2004 ዓ.ም. ለቀረቡት የቤት ሥራዎች የሰበሰብኳቸው መረጃዎች ስለ ማህበረሰቡ ብዙ እንዳውቅና በተለይም ባህሉና ልማቱ ያላቸውን ቁርኝት በሰፊው እንዳጠና ያነሳሱኝ ምክንያቶች ናቸው።

## 1.4. የጥናቱ ዋነኛ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋነኛ ዓላማ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልል ነባር ብሔረሰቦች ከሚባሉት መካከል የበርታን ብሔረሰብ ባህል በማጥናት በሀገር አቀፍ ደረጃ በመንግስት ታቅደው እንዲተገበሩ የሚሰራጩ የልማት ዕቅዶችን ለመተግበር የብሔረሰቡ ባህል ለአካባቢው ልማትም ሆነ "በልማት ወደ ኋላ መቅረት" ያደረገው አስተዋጽኦ ወይም ተፅዕኖ ይኖር እንደሆነ መመርመርና ባህላዊ ጉዳዮችን የልማት መሣሪያ በማድረግ የአካባቢውን ልማት ለማፋጠን የሚቻልበትን መንገድ ማሳየት ነው።

### 1.4.1. ዝርዝር ዓላማዎች

በዚህ ዋነኛ ዓላማ ሥርም የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች ተነድፈዋል።

1. የበርታ ብሔረሰብ አጠቃላይ ባህላዊ እሴቶች ምን እንደሆኑ ማጥናት፤
2. ባህሉ ልማትን ለማፋጠን የሚያግዙ ምን ዓይነት እሴቶች እንዳሉት መመርመር፤
3. የልማት ዕቅዱን የሚገዳደሩ ብሎም የሚያደናቅፉ ባህላዊ ሁኔታዎች ካሉ መለየት፤
4. ያሉትን ባህላዊ ምቹ ሁኔታዎች ተጠቅሞና እንደ ጥሩ መነሻ ቆጥሮ የሚታሰበውን ልማት ማምጣት የሚቻልበትን መንገድ መግለፅ የሚሉት ናቸው።

### 1.4.2. የምርምሩ ጥያቄዎች

ከላይ በቀረበው ዋነኛ ዓላማ ሥርም ጥናቱ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይመልሳል።

1. የብሔረሰቡ ዋና ዋና ባህላዊ መገለጫዎች ምንድናቸው?
2. ልማት በእነዚህ ባህላዊ ጉዳዮች ውስጥ እንዴት ይገለፃል? ማህበረሰቡ ስለልማት ያለው አጠቃላይ አመለካከትና እሳቤስ ምን ይመስላል?
3. በበርታ ብሔረሰብ ዋና ዋና ባህላዊ መገለጫዎች ውስጥ ልማትን ለማፋጠን ያሉት አዎንታዊና አሉታዊ ( ደጋፊና አደናቃፊ) ጉዳዮች የትኞቹ ናቸው?
4. ለአካባቢው ልማት መፋጠን ባህሉን በማልማት ምን ዓይነት መፍትሔዎች ማምጣት ይቻላል?

## 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

ሀገራችን የብዙ ብሔር ብሔረሰቦችና ባህሎች አገር ናት። በእነዚህ ብሔረሰቦች ዘንድ ያለው የልማት ሁኔታና የልማት ግንዛቤም እንደብዛታቸው የተለያየ መሆኑ አይቀርም። ይህ የባህል ልዩነት ለልማት የሚኖረው አስተዋፅዖ እስከዛሬ በወጉ ያልተጠና በመሆኑ ጥናቱ ባህልና ልማት ያላቸውን የጠበቀ ቁርኝት አውጥቶ በማሳየት የልማት ዕቅዶች ሲታቀዱና ለትግበራ ሲዘጋጁ ለማህበረሰቡ ባህል ትኩረት መስጠት እንደሚገባ የሚያስገነዝብ ጠቃሚ ማስረጃ በመሆን ያገለግላል።

ለክልሉ መንግሥት ለብሔረሰቡ ባህል ትኩረት በመስጠት ባህሉ በውል ተጠንቶና ለልማት ያለው ጠቀሜታ ታውቆ ማህበረሰቡን ለልማት ለማነሳሳትና ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል መሳሪያ አድርጎ መጠቀም እንደሚቻል የሚያሳይና የሚያነቃ መነሻ ማስረጃ የሚሠጥ ጥናት ይሆናል።

በክልሉ በየደረጃው ላሉ መንግሥታዊም ሆኑ መንግስታዊ ያልሆኑ የልማት ድርጅቶች፣ አስተግባሪዎችና ባለሙያዎች ዕቅዳቸው ውጤታማ እንዲሆንና ተቀባይነት እንዲያገኝ በቅድሚያ የማህበረሰቡን ባህል ጠንቅቀው መረዳት፣ ለባህሉ ዕውቅና መስጠትና በማህበረሰቡ ባህላዊ ወይም ሀገር በቀል ዕውቀት /indigenous knowledge/ ላይ በመመስረት ዕቅዳቸውን ለማስተግበር እንደሚያስችል ጥናቱ መረጃ ይሰጣል፡፡

ፖሊሲ አውጪዎች ማንኛውንም የልማት ዕቅድ ከማውጣታቸው በፊት በየአካባቢው ያሉ ባህላዊ ምቹ ሁኔታዎችና ተግዳሮቶች ምን እንደሆኑ ማጤንና ለእነሱም ትኩረት መስጠት እንደሚገባቸው ያስገነዝባል፡፡

የበርታን ብሔረሰብ ባህል ባጠቃላይና አንዳንድ በመጥፋት ላይ ያሉ ልማዳዊ ድርጊቶች ከመጥፋታቸው በፊት በቅርስነት ለማቆየት የራሱን አስተዋጽዖ ያደርጋል፡፡

ለተመራማሪዎችና በርዕሱ ዙሪያ ጥናት ለሚያደርጉ ባለሙያዎች መነሻ መረጃዎችን ይሰጣል ተብሎ ይታመናል፡፡

## 1.6. የጥናት አካባቢው መረጣና የጥናቱ ገደብ

ይህን ጥናት ለማድረግ ከሚያስፈልገው ጊዜና ወጪ አኳያ በክልሉ ከሚገኙት ብሔረሰቦች በአንዱ ላይ አተኩሮ መሥራት የተሻለ ነው ብዬ ስላሰብኩ ከክልሉ አምስት ነባር ብሔረሰቦች መካከል በበርታ ብሔረሰብ ላይ ብቻ አተኩሬአለሁ፡፡ ብሔረሰቡ የተመረጠበት ዋነኛ ምክንያት በክልሉ በህዝብ ብዛት ሰፊውን ድርሻ በመያዙ የክልሉን ሁኔታ ያሳያል ብዬ ስላመንኩ ነው፡፡

የጥናቱን ወካይነት ለማጎልበትም የበርታ ብሔረሰብ ከሚኖርባቸው የአሶሳ ዞን ስምንት ወረዳዎች መካከል ሁለት ከተማ ቀመስ (አሶሳና ባምባሲ ወረዳዎችን) እና ሁለት የገጠር ወረዳዎችን (ሸርቆሌና መንጌ ወረዳዎችን) ይሸፍናል፡፡ ወረዳዎቹ የተመረጡበት ምክንያት ከጥናቱ ዓላማ ጋር በተያያዘ ከተማ ቀመሶቹ ወረዳዎች ለከተሜነትና ለዘመናዊነት

አንፃራዊ በሆነ መልኩ ቅርብ ስለሆኑ የተለየ ባህላዊ ሁኔታ ይታይባቸው ይሆናል ተብሎ ስለተገመተ ነው። አሶሳ የክልሉ ዋና ከተማ ቢሆንም ለመንግስታዊ አስተዳደሩ ቅርብ የሆኑ ብዙ የገጠር ቀበሌዎች ያሉት በመሆኑ፣ ባምባሲ ደግሞ ከክልሉ ዋና ከተማ በ47 ኪሎ ሜትር ርቀት ከዋናው አስፓልት መንገድ ላይ የሚገኝ ሆኖ በ1977 ዓ.ም. በሀገራችን ተከስቶ በነበረው ድርቅ ሳቢያ ወደ ክልሉ እንዲሰፍሩ የተደረጉ ህዝቦች ከነባሩ በርታ ጋር ተቀላቅለው የሚኖሩበት በመሆኑ አሁንም የተለየ ባህላዊ ሁኔታ ይታይበት ይሆናል ተብሎ ስለተገመተ ነው።

የገጠር ወረዳዎቹ መንጌና ሸርቆሌ ደግሞ በጣም ገጠራማና ለጎረቤት ሀገር ሱዳን የቀረቡ፣ እጅግ በጣም ጥቂት ከሆኑ የሌላ ብሔረሰብ አባላት በቀር ብዙዎቹ የበርታ ብሔረሰብ አባላት የሚኖሩባቸው በመሆናቸው ከዋናው ብሔረሰብ መኖሪያ ተኣማኒ መረጃ ለመሰብሰብ እንዲቻል ጠቃሚነታቸው ታምኖበት የተመረጡ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ ብሔረሰቡ ለብቻው ተገልሎ የሚኖር ባለመሆኑ በአቅራቢያው የሚኖሩ ሌሎች ማህበረሰቦች ባህል ለልማቱ ያደረገው አስተዋፅዖ ካለ አነፃፅሮ ለማሳየት ይሞከራል።

ጥናቱ ስለ ባህልና ልማት ሲያነሳ የሚመለከተው የማህበረሰቡን መንፈሳዊም ሆነ ቁሳዊ ልማትን በመሆኑ በዚህ ረገድ በማህበረሰቡ ዘንድ ያሉ ባህላዊ ክንዋኔዎች ሁሉ ይዳሰሳሉ። በተለይ ደግሞ የማህበረሰቡ የሥራ፣ የቁጠባና ጥሪት የመቋጠር፣ የመረዳዳት፣ አብሮ የመኖርና የማደግ፣ የጤና አጠባበቅና የአኗኗር ዘይቤ ምን እንደሚመስል በተገኙት ባህላዊ ዘውጎች መነሻነት የሚመረመር ይሆናል።

ጥናቱ በዋናነት የሚያተኩረው በሀገር አቀፍ ደረጃ በመንግስት ታቅደው ወደ ክልሉ የሚሰራጩ የልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች አተገባበሮች የገጠሟቸውን ባህላዊ ምቹ ሁኔታዎችና ተግዳሮቶችን በመመርመር ላይ በመሆኑ በገጠር ልማት ላይ የሚያተኩረው የግብርና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም በጥናቱ የሚፈተሽ አንዱ ዋነኛ ጉዳይ ይሆናል።

ህብረተሰቡ አምራች ዜጋ እንዲሆንና ራሱንና አካባቢውን እንዲያለማ ጤናው የተጠበቀ መሆን ስላለበት የጤናን ጉዳይ ከልማት ነጥሎ ማየት አይቻልም። ስለዚህ የማህበረሰቡን

ጤና አጠባበቅ የሚመለከተው የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አተገባበር ሌላው በጥናቱ የሚዳሰስ ጉዳይ ይሆናል፡፡

ትምህርት ለአንድ ሀገር ልማት የሚኖረው ጠቀሜታ በቀላሉ የሚታይ ባለመሆኑ ስለ ልማት ሲነሳ የትምህርትን ጉዳይ መመልከት ተገቢ እና የማይታለፍ ጉዳይ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ይሁንና ትምህርትን ከባህል ጋር አያይዞ ማጥናት እጅግ ሰፊና ራሱን ችሎ መጠናት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት በዚህ ጥናት የትምህርትን ጉዳይ በእግረመንገድ ከማንሳት ዉጪ በጥልቀት መርምሮ ለማካተት አልተሞከረም፡፡ ዋነኛው ምክንያትም ካለው የጊዜ፣ የገንዘብና የጉልበት ውስንነት አኳያ ጥናቱ እንዳይሰፋና ተገቢውን ጥልቀት ሳይዝ ላይ ላዩን እንዳይሄድ ከመስጋት የመነጨ እንጂ የትምህርትን ጉዳይ ለማካተት ካለመፈለግ እንዳልሆነ ከግምት ውስጥ ገብቶ ይህም የጥናቱ ውስንነት እንደሆነ ተወስዷል፡፡

ጥናቱ ከግብርና ልማትና ከጤና አክስቴንሽን ውጪ ያሉትን ሌሎች የልማት ፕሮግራሞችንም አይመለከትም፡፡

## 1.7. ያጋጠሙ ምቹ ሁኔታዎች፣ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሔ ርምጃዎች

ማንኛውንም ጥናት ለማድረግ ሲታሰብ በተለይም በመስክ መረጃ ስብሰባ ያልተገመቱ ምቹ ሁኔታዎችና ችግሮች ማጋጠማቸው የማይቀር ነው፡፡ በዚህ ጥናትም ካጋጠሙት ዋና ዋናዎቹን ብቻ ማንሳት ወደፊት የባህል ጥናት ለሚያደርጉ ትምህርት ይሰጣል ተብሎ ስለሚታመን እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 1.7.1. ያጋጠሙ ምቹ ሁኔታዎች

ይህን ጥናት ለማድረግ ወደ መስክ ስወጣ ብዙ ምቹ ሁኔታዎች አጋጥመውኛል። የመጀመሪያው የክልሉ መንግሥት ሀላፊዎች የክልሉ ብሔረሰቦች ባህል እንዲጠና ያላቸው ከፍተኛ ፍላጎት ነው። ይህም ቀደም ሲል እንዳነሳሁት በ2003 ዓ.ም ለወረዳ ፎክሎር መረጃ ስብሰባ ወደ አካባቢው ስሄድ በቀናነት ተቀብለው የሄድኩበት ዓላማ እንዲሳካ ወደ ወረዳ የምሄድበት የመስክ መኪናና አስፈላጊዋን ቁልፍ ሰው ፈልገው ያስተዋወቁኝ የክልሉ ፕሬዘዳንት አቶ አህመድ ናስር ራሳቸው መሆናቸው ዋነኛው ነው።

ፕሬዘዳንቱ ያስተዋወቁኝ ሴት ሲቲና አደም የተባለች የበርታ ብሔረሰብ ተወላጅ ስትሆን ያኔም ሆነ በተደጋጋሚ ለመረጃ ስብሰባ በምወጣበት ሁሉ ያላንዳች ደከመኝ ሰለቸኝ የግል ሥራዋን ሳይቀር እየተወች ከእኔ ጋር ሳትለይ ከማህበረሰቡ ስቀላቀል ዓላማዬን በማስረዳትና የምፈልገውን መረጃ እንዲሰጡኝ በማድረግ፣ መረጃ ሰጪዎችን አፈላልጎ በማገናኘት፣ መንገድ በመምራት፣ አስተርጓሚ ሲያስፈልገኝ በማስተርጎም፣ ራሷም መረጃ በመስጠት፣ የማድርበትን፣ የምመገበውን፣ በግል የሚያስፈልገኝን ሁሉ በማመቻቸት አስቸጋሪ ሊሆኑብኝ የሚችሉ ነገሮችን ሁሉ ምቹ እንዲሆኑ አድርጋልኛለች።

ማህበረሰቡም ገር፣ እንግዳ ወዳድና አክባሪ በመሆኑ ለግል ሥራዬ እንደሄድኩ ሳይሆን እነሱን ለመጠየቅ እንደሄድኩ፣ ከሩቅ ቦታ እነሱን ብዬ እዚያ መምጣቴን እንደትልቅ ነገር በመቁጠር ለማወቅ የምፈልገውን ሁሉ ሳይቆጥቡ እንድጠይቅ፣ እንድመለከት፣ እንድሳተፍና በድምፅም ሆነ በምስል እንድቀርፅ በፍፁም ደስታ ፈቃደኛ ሆነውልኛል። በተለይ ለሙከራና ለዋናው ጥናት ተመላልሼ መሄዴ ልክ ናፍቀውኝ ልጠይቃቸው በመካከላቸው እንደተገኘሁ በመቁጠር ሥራዬን ሁሉ ምቹ አድርገውልኛል። የለጋስነታቸውና እኔን የመቀበላቸው ማሳያ አባ አቶም ሙስጦፋ የተባሉት የድሮ ንጉስ ልጅ አሶሳ ግቢያቸው ካሉት በርካታ የማንጎ ዛፎች ውስጥ አንዱን ለኔ ሰጥተውኛል። ምን ያደርግልኛል ስላቸው "ሲያፈራ በየዓመቱ በካርቶን አሽገን እንልክልሻለን አሁን እኮ ልጃችን ነሽ" በማለት ቸርነታቸውን አሳይተውኛል።

በመረጃ ስብሰባ ወቅት መረጃ ሰጪዎቼ ከአንዳንድ ቦታዎች በስተቀር በአብዛኛው ለሚሰጡኝ መረጃ ገንዘብ አለመጠየቃቸው ዋነኛው ምቹ ሁኔታ ነው ለማለት ይቻላል። አልፎ አልፎ ለሚደረጉ ባህላዊ ክዋኔዎች የሚያስፈልጉ ጥቂት ነገሮች መግዢያ ካልሆነ ያን ያህል የጎላ የገንዘብ ጥያቄ አልቀረበልኝም። አንዳንዴ ከሥራቸው ላይ አስነስቼ ያመጣኋቸው ከሆነ የስኳር መግዢያ ካለኝ እንድሰጣቸው በግልፅ ጠይቀውኛል፤ ይበቃል ያልኩትን ስሰጣቸው "ሹኩረን" (አመሰግናለሁ) ከማለት በቀር አነሰኝ ብለው አልተከራከሩኝም። ማህበረሰቡ ፍፁም ሰላማዊ መሆኑም በምንቀሳቀስበት ቦታ ሁሉ ምንም ዓይነት የደህንነት ስጋት ሳያጋጥመኝ በሰላም ሥራዬን አጠናቅቄ ለመመለስ ረድቶኛል።

### 1.7.2. ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሔ ርምጃዎች

በዚህ ጥናት መረጃ አሰባሰብ ጊዜ የሚነሳው ዋነኛ ችግር የታወቀው የገንዘብ እጥረት ነው። ለጥናቱ የተመደበው ገንዘብ አነስተኛ በመሆኑ መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን አሟልቶ በጥናቱ አካባቢ ለረዥም ጊዜ ለመቆየትም ሆነ በተደጋጋሚ ተመላልሶ በመሄድ መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችል አልነበረም። ከዚህ የተነሳ የድምፅ እና የምስል መቅረጫዎችንና የሚያስፈልጓቸውን ግብዓቶች በራሴ ወጪ እንድገዛ ተገድጃለሁ። አሶሳ ከተማ በምቆይበት ጊዜም የምኖረውና የምመገበው የመስክ ረዳቴ ከነበረችው ከሲቲና ቤት ስለነበር እንዲሁም መረጃ ለመሰብሰብ ወደ ገጠሮቹ ስሄድ ውሎየና አዳሬ በበርታዎቹ ቤት ስለነበር፣ ለበርታ የእንግዳ ተቀባይነት ባህል ምስጋና ይግባውና ችግሬ ተቃሎልኛል።

ይህም ሆኖ ጥናቱን የተሟላ ለማድረግ ከደረጃ ማበልፀጊያ በኋላም ወደ ጥናቱ አካባቢ ተመልሼ የዋናውን ጥናት መረጃ ለማጠናቀር አስፈላጊ በመሆኑ ወጪዬን በግሌ ለመሸፈን ተገድጃለሁ። የክልሉ መንግሥትም ለጥናቱ ዋጋ በመስጠት መጠነኛ የገንዘብ ድጋፍ ባያደርግልኝ ኖሮ ጥናቱን በተገቢው መንገድ ለማካሄድ የሚኖረው ጫና ከፍተኛ

ይሆን ነበር። እንደሚታወቀው የባህል መረጃ ስብሰባ ለረዢም ጊዜ ከማህበረሰቡ ጋር መኖርን የሚጠይቅ በመሆኑ የክልሉ መንግሥት ካደረገልኝ የገንዘብ ድጋፍ በተጨማሪ የመጓጓዣ መኪና በመመደብ ባያግዘኝ ኖሮ ከዩኒቨርሲቲው በተሰጠኝ ገንዘብ ረዢም ጊዜ ለመቆየትና በተደጋጋሚ ወደ መስክ በመሄድ ለጥናቱ አስፈላጊውን መረጃ በመሰብሰብ ጥናቱን ለማጠናቀቅ ፈፅሞ የማይታሰብ ነበር።

ሌላው እንደችግር የማነሳው የአካባቢው ሙቀት ከፍተኛ መሆንና ውሃ እንደልብ አለመገኘትን ነው። ሙቀቱ ከፍተኛ በመሆኑ ለመልመድ ከማስቸገሩም በላይ እንደልብ ለመተጣጠብ ውሃ በቅርብ አለመገኘቱ አስቸጋሪ ቢሆንም ችግሬን የተረዱት በርታዎች የምታጠብበትን ውሃ ከርቀትም በማምጣት አገልግለውኛል። ዕርቀቱንና እነሱን ማሸከሜን ሳስብ ግን አሁንም ድረስ ያሳቅቀኛል።

በአንድ ሠርግ ክዋኔ ላይ "ሀርሻ" የሚሉትን የምሽት ጭፈራ እስከ ሌሊቱ 8፡00 ሰዓት ስቀርፅ አምሽቼ በማግስቱ ባላወቅሁት ምክንያት በመታመሜ የሠርጉን ክዋኔ ሳልከታተል ወደ አሶሳ ለመመለስ ተገድጃለሁ። ህመሙም ለአንድ ሳምንት በመቆየቱ ከሥራዬ ቢያስተጓጉለኝም ያመለጠኝን የሠርግ ክዋኔ በሌላ ሠርግ ላይ ተገኝቼ ማሟላት ችያለሁ።

ከደረጃ ማበልፀግ በኋላም ወደ ጥናቱ አካባቢ ተመልሼ በሄድኩበት ወቅት ወላጅ እናቴ በማረፏ፣ እዛው እያለሁ በመስማቴና ቀብሯ ላይ ለመድረስ ባለመቻሌ ውስጤ እጅግ ቢያዝንም ሀዘኑንና አጋጣሚው የፈጠረብኝን ጫና እንደምንም ተቋቁሜ የሚያስፈልገኝን መረጃ ሰብስቤ ተመልሻላሁ።

ይሄን "ያጋጠሙ ችግሮች" የሚለውን ጉዳይ የፃፍኩት እንደው ደንብ ስለሆነ ይመስለኛል። እኔ የበርታን ማህበረሰብ ሰው ወዳድነት፣ እንግዳ ተቀባይነትና የፈለግሁትን መረጃ ካለስስት መስጠት ሳስብ ከመልካም አጋጣሚዎቹ በቀር እዚያው እያለሁ በግል ያጋጠሙኝ ህይወቴን የፈተኑ ከባድ ችግሮች እንኳን ፈፅሞ የሚታወሱኝ አይደሉም። ይልቁንም በመስክ መረጃ ስብሰባ ያገኘሁት ልምድ ከሁሉም ችግሮች በላይ ያተረፍኩት ስንቅ ነው።

## 1.8. የጥናቱ ሥነምግባር

የአንድን ማህበረሰብ ባህል የምታጠና ተመራማሪ ጥናቱን በምታካሄድበት ወቅት መረጃ የሚሰጡ፣ የሚያስተረጉሙ፣ የጥናቱን አካባቢ ምቹ የሚያደርጉ ወዘተ፣ ሰዎች እገዛና ትብብር ሳይታከልበት የተዋጣለት ጥናት ማድረግ አይቻላትም። ጥናቱን ውጤታማ ለማድረግ በማህበረሰቡ ዘንድ መታመንና ወግና ባህላቸውን ጠብቆ መቆየት፣ ተገቢውን ክበሬታ መስጠትና የጥናቱን ዓላማ በግልፅ ማሳወቅ ከተመራማሪዋ በዋነኝነት የሚጠበቁ ሥነምግባሮች ናቸው (Dawson, 2002) ።

በማህበረሰቡ ዘንድ ተኣማኒነትን ለማግኘት ስለ ጥናቱ ዓላማ በግልጽ ማስረዳት ተገቢ በመሆኑ የመጀመሪያ ሥራ የሚሆነው በየደረጃው ላሉ የመንግሥት አስፈፃሚ አካላት የጥናቱን ዓላማ በማስረዳት ፈቃድና ትብብራቸውን መጠየቅ ነው። ወደ ማህበረሰቡ ዘንድም ሲገባ እንዲሁ በግልፅ የጥናቱን ዓላማ አስረድቶና መረጃ የመስጠት ፈቃዳቸውን አግኝቶ መግባት ተገቢ በመሆኑ ለዚህ ጥናት መረጃ ስብሰባ ወደ አካባቢው በተመላለስኩ ቁጥር ከአማርኛ ቋንቋ ሥነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የጥናቱን ዓላማና የጥናቱን ሂደት ደረጃዎች የሚገልፅ ደብዳቤ ለክልሉ መንግስት እያፃፍኩ ነበር።

የበርታ ብሔረሰብ በአብዛኛው ሙስሊም በመሆኑ ባህላዊና ዕምነታዊ ሥርዓቱን ከአለባበሴ ጀምሮ ተገቢውን ሥርዓት በመጠበቅ፣ የሚበሉትን በመብላት፣ በሚኖሩበት በመኖር ያለኝን ግንኙነት የሠመረ ለማድረግ ጥረት በማድረጌ ውጤታማ ሆኛለሁ።

በጥናቱ ወቅት በቪዲዮ፣ ፎቶ ካሜራና በመቅረፀድምፅ የሚቀረፁ መረጃዎች የመረጃ አቀባዮችን ፈቃድ መሠረት ያደረጉ ሲሆን የተቀረፀውን በማሳየት ለመረጃነት ከማገልገሉ በፊት በትክክለኛነቱ እንዲስማሙበት ተደርጓል። በምስል የተቀረፀውን መረጃ መልሼ ማሳየቴም በከፍተኛ ደረጃ ጠቅሞኛል። ማህበረሰቡ የባህል ዘውጉን ክዋኔ መልሶ እያየው አስተያየት እንዲሰጥበት በመደረጉ የተሰበሰበውን መረጃ ትክክለኝነት ለማረጋገጥ ከማስቻሉም በላይ የጎደለም ካለ ለማሟላት፣ በክዋኔው ወቅት ለአጥኝዋ እንግዳ የሆኑና ግልፅ ያልሆኑ ጉዳዮችን እንዲያብራሯቸው ለማድረግ አስችሏል። በሌላ በኩል ደግሞ

ማህበረሰቡ በክዋኔው ሲሳተፍ የራሱን ምስል መልሶ በማየቱ ውስጣዊ ደስታን ከማሳደሩም በላይ በአጥኚዋ ላይ ያለውን ዕምነት በማጎልበት በድጋሚ ሌሎች መረጃዎችን ለመስጠት አነሳስቷል።

በተቻለ መጠን አንዳንድ ምስሎችን/ ፎቶግራፎችን አሳትሞ መስጠቱ ገንዘብ አስለምዶ መረጃን በብር ለመግዛት የሚደረግን አጉል ጥረት በማስቀረት ጥሩ የምስጋና ማቅረቢያም ሊሆን እንደቻለም ተረጋግጧል። በተጨማሪም በአንድ አካባቢ የተቀረፀን ክዋኔ ለሌሎች አካባቢዎች በማሳየት እዚህኛውም አካባቢ ተፈላጊ መረጃዎችን በቀላሉ ለማግኘት እንደሚቻል ትምህርት ተወስዶበታል።

ከዚህ ሌላ ሩቅ የሆኑ መንገዶችን አብረውኝ ለተጓዙ፣ መረጃ የክዋኔውን ቦታ ላመቻቹ፣ አልፎ አልፎ በማስተርጎም እገዛ ላደረጉ፣ መንገድ በመምራት ወዘተ ለሚተባበሩ ሰዎች ጊዜና ጉልበታቸውን ሰውተው የሚተባበሩ ስለሆነ መጠነኛ ክፍያ እንዲያገኙ ተደርጓል።

# ምዕራፍ ሁለት

## 2. የፅንሰ ሃሳብ ማዕቀፎች

የዚህ ክፍል ትኩረት ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውንና በተደጋጋሚ የሚነሱትን ባህል (Culture)፣ ልማት (Development)፣ የባህልና ልማት ቁርኝት፣ ግብርና ኤክስቴንሽንና ጤና ኤክስቴንሽን የሚሉትን ጽንሰ ሃሳቦች ምንነት ማብራራት ይሆናል።

### 2.1. የባህል ፅንሰ ሀሳብ

ባህል የአንድ ማህበረሰብ መገለጫና የህልውናው መሠረት የሆነ ማህበረሰቡ ራሱ የሚፈጥረው፣ የሚተገብረው፣ የሚከውነው፣ የሚያከብረውና የሚገዛለት ትልቅ ትእምርት ነው። አንድ ማህበረሰብ ከሌላው የሚለይበት የራሱ የሆኑ ዕውቀቶች፣ ወጎች፣ ልምዶች፣ ሥነ ምግባራዊ፣ ማህበራዊ፣ ፓለቲካዊ መለያዎች የሚገለጡት በባህሉ ውስጥ ነው። ማንኛውም ማህበረሰብ ስለ ራሱና ስለዓለም ያሉትን አመለካከቶቹን፣ የአኗኗር ዘይቤዎቹን፣ ዕምነቶቹን፣ ቁሳዊና ህሊናዊ ሀብቶቹን የሚገልጽበት፣ የሚተገብርበት ለእነሱም ተገዝቶ የሚኖርበት የማንነቱ መገለጫ የሆነ የራሱ ባህል አለው። “Culture should be regarded as the set of distinctive spiritual, material, intellectual and emotional features of society or a social group, and that it encompasses, in addition to art and literature, lifestyles, ways of living together, value systems, traditions and beliefs” (UNESCO, 2001). This definition of culture is very closely related to the ways in which societies, groups and communities define their identity (UNESCO, 2009፣18). “ባህል የሰው ልጅ የማንነቱ መገለጫና ከዓለም ጋር ያለውን መስተጋብር የሚያመለክቱ መንፈሣዊ፣ ቁሳዊ፣ አዕምሮኣዊ፣ ጥበባዊና ገቢራዊ እሴቶች ስብስብ፤ የእርስ በእርስ ግንኙነቶች፣ ዕምነቶች፣ ልማዶችና ባህሪዎች ውስብስብ እንቅስቃሴና ፍቺ ነው”

(UNESCO, 2009፣ 18፣ ትርጉም የኔ) ። ይሄ የባህል ፍቺም ህብረተሰቦች፣ ቡድኖችና ማህበረሰቦች ማንነታቸውን የሚበይኑበት እንደሆነም ያሳያል።

ባህል የማይነካው የማህበረሰቡ ጉዳይ ስለሌለ በአብዛኛው የዘርዝሪነት ይዘት ያላቸው በርካታ ብያኔዎች ሲሰጠው ይታያል። የኢፌዴሪ የባህል ፖሊሲ ለባህል በሰጠው ብያኔ ሰውን ሰው ያሰኘውና ከሌሎች ፍጡራን የሚለየው ዋነኛ ጉዳይ እንደሆነና ዝርዝር ሁኔታዎችን የሚያካትት ሰፊ ጽንሰ ሀሳብ እንደሆነ ያሳያል።

> …ባህል የሰው ልጅ ሰብዓዊና ምክንያታዊ ፍጡር እንዲሆን ያስቻሉት ወይም ከሌሎች ፍጡራን ለመለየት ያበቁት ማንኛቸውም ምሁራዊ፣ ሥነምግባራዊ፣ አካላዊ፣ ቴክኒካዊና ሌሎችም ሥራዎች ሁሉ፤ እንዲሁም የሰው ልጅ የመማር፣ በሞራል በቴክኒክና በአዕምሮ ዕውቀት ራሱን የማሰልጠን ሁኔታዎችን የሚያጠቃልል ጽንሰ ሃሳብ ነው። እንዲሁም አንድ ህዝብ ከሌላው ተለይቶ የሚታወቅባቸው ሁኔታዎች ማለትም የአኗኗር ዘይቤዎቹን፣ ዕምነቶቹን፣ ትውፊቶቹን፣ ባጠቃላይም ቁሳዊና ህሊናዊ ሀብቶቹን የሚያካትት ሰፊ ጽንሰ ሀሳብ ነው (የወጣቶችና ባህል ሚኒስቴር፣1995፣5)።

ባህል ሰዎችን ከበርካታ ሁኔታዎች ጋር የሚያስተሳስር ፍቺ አለው። የራስወርቅ የበርካታ ምሁራንን ፍቺ ዘርዝረው "ባህል … ሰዎች እንደ ህብረተሰብ አባላት ያላቸው፣ የሚያስቡትና የሚያደርጉት ማንኛውም ነገር ሁሉ ነው…" በማለት ይነሱና የሶሻል አንትሮፖሎጂ የዕውቀት ዘርፍ ባህልን የሚገነዘበው እጅግ ሰፊና መላ የሕብረተሰብ ይዘቶችን በሚያካትት መልኩ እንደሆነ ይጠቅሳሉ። "ባህል ማለት የአንድ ህብረተሰብ

አባላት የሚረከቧቸውን የተጠራቀሙ ዕውቀቶች፣ ዕምነቶች፣ ኪነጥበባት፣ መመሪያዎች፣ አርማዎች፣ አመለካከቶች፣ ስነምግባራት፣ ህግጋት፣ ወጎች፣ ተለምዶዎችና ሰዎቹ የሚገለገሉባቸውን ቁሳዊ ንብረቶችን ጭምር የሚያጠቃልል ውህድ ነው::" በማለት ይፈቱታል (የራስወርቅ፣2004፣3)::

የባህልን ፍቺ እቅጩዊ በሆነ ነጠላ ዐ.ነገር ለመፍታት እንደማይቻልና ከተለያዩ የዕውቀት መስኮች አንፃር ከታሪክ፣ ከአንትሮፖሎጂና ማህበረሰብ ጥናት አኳያ እንዲሁም ከፖለቲካ፣ ከሚዲያ፣ ከዕለት ተዕለት ተግባራት ወዘተ አንፃር የተለያየ ብያኔ እንደሚሰጠው የሚገልፁ አሉ:: Schech & Haggis,2000 (Robert Bocok 1992) ጠቅሰው ባህል ከእርሻና ከብት እርባታ አንስቶ አዕምሮንና ጥበብን ከማሳደግ፣ ማህበራዊ ሂደትን ከማልማት፣ እሴቶችን የአኗኗር መንገዶችንና ፍችዎችን ከማሳደግና ለህይወት ትርጉም ከመስጠት፣ ከመለማመድና ከማልማት ጋር የሚያያዝ ነው በማለት ባህልን አጠቃሎ ለመፍታት ይሞክራል ይላሉ:: በሌላ መልኩ ባህል እንደ አንድ የተለየ ቡድን ትዕምርቶች፣እሴቶችና የኑሮ ዘዴዎች፣ ግለሰቡ ከቡድኑ የሚጋራውና ያለውን ተፈጥሮአዊ ደረጃ የሚሠጠው አገልግሎት ነው:: ስለዚህ ባህል ለኑሮ/ ለህይወት የሚቀመር፣ የማህበረሰቡን ደረጃ የሚያረጋግጥ፣ የሚመረትና ቀጣይነትና ዘላቂነት ያለው አጠቃላይ የማህበረሰቡ እሴት ነው (Schech & Haggis , 2000;16)::

ቀዳሚው ዘመን ላይ የነበረው የባህል ፍቺ ተፈጥሮን የማልማት ወይም የእርሻ (cultivation) ፍቺ እየተስፋፋ ሄዶ የሰውን ልጅ አዕምሮ ማልማትን የሚመለከት ተደርጎ እንደሚወሰድና ይህ ፍቺ ቀድሞ ያልነበሩትን የመደብ ደረጃዎችን አካቶ የማህበረሰቡ ቡድኖች፣ እንቅስቃሴዎች፣ የኑሮ ዘዬዎችና ሁነቶች ሆኖ እየተወሰደ እንደመጣ አስረድተው ከአውሮፓውያን ቴክኖሎጂና ኢንዱስትሪ ልማት መስፋፋት ጋር ሲያያዝ ደግሞ ባህል የአዝግሞታዊ አስተሳሰብና ያልሰለጠኑ ህዝቦች መገለጫ እየተደረገ መምጣቱን ያስገነዝባሉ (Schech & Haggis, 2000; 23)::

አንዳንዶች ይህን መቋጫ የሌለውን የባህል ፍቺ ተመልክተው ዓላማውን ከማዝናናት ጋር ብቻ እንደሚያያይዙትና ባህልን በቀላሉ ሙዚቃ፣ መዝፈንና መደነስ ብቻ አድርገው እንደሚገልፁት ይናገራሉ (Cumming, 1990; Mbakogu, 2004, 37)። ባህል ግን ማዝናናት ብቻ ሳይሆን ከዚያም በላይ የሆነ ጥልቅና ሰፊ ፍቺ እንዳለው ብዙዎች ይስማሙበታል።

ባህል የሰዎችን አጠቃላይ የኑሮ አቅጣጫ የሚወስን ሆኖ የማህበረሰቡን ቁሳዊና መንፈሳዊ ጉዳዮች ሁሉ አጠቃሎ የሚይዝ ጽንሰ ሀሳብ ነው የሚሉም አሉ። እነዚህኞቹ ባህል የሰዎችን ቁሳዊና መንፈሳዊ አገላለፆችና በነዚህም አገላለፆች የሚግባቡበትን ሁሉ የሚያጠቃልልና በሁሉም ማህበራዊ፣ ምግባራዊ፣ ሳይንሳዊ፣ ጥበባዊና፣ ቴክኖሎጂያዊ አገላለፆችና ተግባቦቶች ከሰዎች ዘወትራዊ ምግባራዊ እና ብሔራዊ… ጉዳዮች ጋር የሚዛመዱበትና እነዚሁ ጉዳዮች እንዴት እንደሚገለፁ የሚተነተንበት ነው። በመሆኑም ባህል በተመሳሳይ ድንበር ክልል በሚገኙ ህዝቦች መካከል እየተተገበረ የህዝቦችን ተመሳሳይነትና አንድነት የሚያሳዩና ለመጪው ትውልድ እንዲቆዩለት የሚፈልጓቸውን ጉዳዮች የሚወክል ነው ይላሉ (Mbakogu, 2004; Storey፣2009)።

ሌሎች ደግሞ ባህል ረቂቅ የሆነና በተለያየ መልኩ የሚገለፅ የአንድ ማህበረሰብ ዕውቀት ማስተላለፊያ መንገድ እንደሆነ ይገልፃሉ። የሰውን ልጅ አጠቃላይ ልማዳዊ ባህሪን የሚያደራጁ ማህበራዊ ልማዶችና ቁሳዊ ሁኔታዎች በአመለካከት፣ በንግግር፣ በድርጊት፣ በዕደጥበብ የተገመዱበትና የሚገለፁበት ትምህርትና ዕውቀት የሚተላለፍበት ረቂቅ አስተሳሰብ/ ዕምነት ነው፤ ይህም ዕምነቶችን፣ ሞራሎችን፣ ህጎችን፣ ልማዶችን አስተያየቶችን፣ ሀይማኖቶችን፣ ምልኪዎችንና ጥበቦችን ያጠቃልላል፤ በቀላሉ ባህል የሰው ልጅ የኑሮ አቅጣጫ ነው ይሉታል (Ojameruaye,2005;2)።

የባህልን ፍቺ ከባህሪው ጋር በማያያዝ ብዙ ጉዳዮችን በዝርዝር በማምጣት የሚበይኑትም አሉ። ባህል የማህበረሰቡ አባላት የሚጋሩት፤ በደም ወይም በዘር የማይተላለፍ፤ ከአንድ ትውልድ ወደ ሌላው በታሪክና በልማድ የሚተላለፍ፤ ራስን ከማህበራዊ መቼት ለማዛመድ በሚደረግ መስተጋብር የሚፈጠር፤ በማንኛውም ማህበረሰብ ዘንድ የሚገኝ

የጋራ ባህሪ እና ተለዋዋጭ የሆነ እሳቤ ነው፡፡ ሲጠቃለልም ማንኛውም ባህል ሳናውቀው ባህሪያችንን፣ አመለካከታችንን፣ እሴታችንን፣ ግባችንን፣ ወይም ማንነታችንን በመቅረፅ ኑሯችንን የሚያረጋጋ ነው፡፡ በሁሉም መልኩ ሲታይ ሰው ከባህል ውጪ ምንም ማለት አይደለም፡፡ የማንኛውም ማህበረሰብ የማንነት ኩራት የሚመሰረተውም በባህሉ ላይ ነው፡፡ በዓለም ላይ ከባህሉና ከባህላዊ ልማዱ ውጪ ማንኛውም ማህበረሰብ እንደታላቅ ህዝብ ሊቆጠር አይችልም፤ ብለው ሁለንተናዊ መልኩን በመዘርዘር ይገልፁታል (Mbakogu, 2004;40)፡፡

ባህል ይህን ያህል ትኩረት የሚሰጠው ከሆነ ሞራላዊና መንፈሳዊ ህልውናን ለመትከል፣ ድህነትን ለማጥፋትና የኢኮኖሚ ልማት ለማምጣትም በቀላሉ የማይገመት አቅም አለው ማለት ይቻላል፡፡ ይህንን አቅሙን የUNESCO (2005) ዶክመንት እንዲህ ይለዋል፡፡

> **Culture** is what has shaped societies' and individuals' ways of life; while certainly rooted in ancestral values, it is also a source of dialogue, exchange, innovation and creativity, and the foundation stone of indigenous systems of solidarity, forms of expression and ways of transmitting knowledge that are as valid for meeting the challenges of tomorrow as for preserving traditions. As such, culture is therefore, in today's world, a means of achieving a more satisfactory intellectual, moral and spiritual existence, while having often unrecognized potential in terms of economic development and efforts to combat poverty (UNESCO,2005፣1-2).

ባህል ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፍ እሴት ሆኖ የማህበረሰቡንም ሆነ የግለሰቡን የኑሮ አቅጣጫ የሚቀርፅ ነው፡፡ የፈጠራና የአዳዲስ ግኝቶች ምንጭና የሀገር በቀል ዕውቀቶች

> ትብብር የመሠረት ድንጋይ፣ የዕውቀት መገለጫና ማስተላለፊያ መንገድ በመሆን የነገን ተግዳሮቶች ለመቋቋምና የማህበረሰቡን ልማድ ለመጠበቅ ያስችላል። ባህል ይሄ ከሆነ በዛሬው ዓለምም እጅግ የሚያረኩ ምሁራዊ፣ ሞራላዊና መንፈሳዊ ህልውናዎችን ለመቀዳጀት ወሳኝ ጉዳይ ከመሆኑም በላይ ለኢኮኖሚ ዕድገትና ድህነትን ለመዋጋትም ትልቅ አቅም አለው (UNESCO, 2005፣1-2,ትርጉም የእኔ)።

ከላይ በዝርዝርና በስፋት ያየናቸው የባህል ብያኔዎች ባህል የአንድ ማህበረሰብ ህልውና መሠረት፣ የማንነቱ መገለጫ፣ የአመለካከቱ ማሳያ፣ የዕውቀት ማሸጋገሪያው ባጠቃላይ የኑሮ አቅጣጫውን የሚወስን ከመሆኑም በላይ የሰውን ልጅ ከባህሉ ውጪ ማሰብ እንደማይቻል የሚያረጋግጡ ናቸው። በመሆኑም ባህል በሰው ህይወት ውስጥ የማይነካውና የማይዳስሰው ጉዳይ ስለሌለ የልማትን ጉዳይ ስናነሳ የባህልን ጉዳይ ወደጎን መተው እንደማይቻልና በሁለቱ መካከል ያለው ቁርኝትና መስተጋብርም ከፍተኛ እንደሆነ አፍን ሞልቶ መናገር ይቻላል።

## 2.2. የልማት ፅንሰ ሀሳብ

እንደ ባህል ሁሉ ልማት የሚለው ፅንሰ ሀሳብም ሰፊና ውስብስብ ፍቺ ያለው በመሆኑ በየጊዜው የተለያየ ብያኔ ሲሰጠው ይታያል። ባለፉት በርካታ ዓመታት በልማት ዙሪያ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ልማት ለሚለው ፅንሰ ሀሳብ ቁርጥ ያለ እቅጫዊና የጠራ ፍቺ መስጠት እንደማይቻል (Schech & Haggis, 2000) ያመለክታሉ። ለዚህም አንደኛው ምክንያት ልማት በራሱ መፍትሄና ግብ እየተደረገ መወሰዱ ነው። ልማት ምንድነው? የሚለው ጥያቄ በልማት ምን ለማድረግ እየታሰበ ነው? ከሚለው ጥያቄ ጋር ይምታታል። የመጀመሪያው ጥያቄ ልማት ቋሚ ከሰው ልጆች ጋር አብሮ የተፈጠረ

ሂደት እንደሆነና አሮጌውን በማጥፋት አዲስ እንደሚበቅል ተክል ዓይነት ነው ማለት ሲሆን ሁለተኛው ጥያቄ በልማት ስም ለሂደቱ ደረጃ በመስጠት አሉታዊ ጎኖቹን ከማሳየት መቆጠብን የሚያመለክት ነው፡፡ በዚህ ፅንሰ ሃሳብ መሠረት ልማት ቋሚና ዑደታዊ አይደለም በሰብዓዊ ፍላጎት እንቅስቃሴና ሃይል የሚገኝና ሊፈጠር እንደሚፈለገው ግብ የሚቀረፅ ነው ይላሉ፡፡

በ20ኛው ምዕተ ዓመት አጋማሽ ልማት የለውጥ ሂደት እንደሆነ ባብዛኛው ነፃ በወጡ የ3ኛው ዓለም ሀገራት መጠቀስ እንደ ጀመረ ገልፀው ፅንሰ ሃሳቡ በተጨማሪ የካፒታሊዝም መስፋፋት ተፈጥሮኣዊ ሂደት ተደርጎ የተወሰደና የኢንዱስትሪና የተፈጥሮ ሀብት ልማትን የሚመለከት እየሆነ በመምጣቱ በሀገር ውስጥ መንግሥታትና የዓለም ባንክን በመሰሉ ዓለም አቀፍ ድርጅቶችም ትኩረት ተችሮት የደሃ ሀገራትን ችግር ለመቀነስና ኑሯቸውን ለማሻሻል ድጋፍ ማድረግ መጀመራቸው ልማት ለተሻለ ህይወት የምንተገብረው እንጂ የሚፈጠርልን ነገር እንዳልሆነ እየተረጋገጠ መጣ ይላሉ (Schech & Haggis, 2000)፡፡

ብዙዎች ልማትን ከሰው ልጅ የተሻለ ህይወት ጋር ያያይዙታል (Peet and Hartwick. 2009,1)፡፡ የተሻለ ህይወት ለሁሉም ማለትም ከመነሻው መሠረታዊ ፍላጎቶች የሆኑትን በቂ ምግብ፣ የተሻለ ጤንነት፣ ምቹና ተስማሚ የመኖሪያ አካባቢ፣ ሁሉም ሰው ሊገዛቸው የሚችላቸው አገልግሎቶችን ማግኘትና ክብሩና ማንነቱ ተጠብቆ የሚኖርበት ህይወት መገኘት ማለት ነው፡፡

ለሰው ልጅ እነዚህን ፍላጎቶቹን ከማሟላት ባለፈ በህይወት ለመኖር በልማት ውስጥ ዋነኛ የሆነው ጉዳይ የተለያዩ የማህበረሰቡ ቁሳዊና ባህላዊ ገጽታዎች ልማት ነው፡፡ ብዙዎች እንደሚገልፁት የተሻለ ህይወት ለሁሉም የሚለው ጽንሰ ሃሳብ ተፈላጊ ግብ ቢሆንም ሁሉም ልማት ግን ይህን ግብ ሲመታ አይታይም (Peet and Hartwick. 2009,1)፡፡

ፈቃደ አዘዘ የልማት ፍቺ ከሰው ልጆች ህይወት አወንታዊ ለውጥና ከተሻለ ህይወት ጋር የሚያያዝ መሆኑን፡-

> "ልማት የሰው ልጆችን ህይወት አዎንታዊ በሆነ መንገድ ለመለወጥ የሚደረግ እንቅስቃሴና ውጤቱ ይመስለኛል። ሁልጊዜ ካለው የአኗኗር ሁኔታ ወደ ተሻለው ለመንዝ የሚደረግ የሃሳብና የድርጊት እንቅስቃሴ … ወደ ተሻለ ሰብእና፣ ወደ ተሻለ አመጋገብ፣ ወደ ተሻለ ሥነምግባር፣ ወደ ተሻለ ጤና፣ ወደ ተሻለ ትምህርት፣ ወደ ተሻለ ትራንስፖርት፣ ወደ ተሻለ አስተዳደር፣ ወደ ተሻለ ሰላም ወዘተ. ለማምራት የሚደረግ እንቅስቃሴና ትግል ይመስለኛል" (ፈቃደ፣2004፣109) ፡፡

በማለት ልማት ለማህበረሰቡ ህይወት የተሻለ ነገርን ለማምጣት የሚደረግ እንቅስቃሴና የማህበረሰቡን መንፈሳዊና ቁሳዊ ጉዳዮች የሚመለከት እንደሆነ ያስረዳሉ።የራስ ወርቅ አድማሴ በበኩላቸው የልማትን ፅንሰ ሃሳብ ሲያስረዱ "…ልማት አዎንታዊ፣ በጎ ወይም ጠቃሚ ህብረተሰባዊ ለውጥ ማለት ነው። … ልማት በምንለው አጠቃላይ አርዕስት ሥር የሚካተቱት ህብረተሰባዊ ለውጦች… በአብዛኛው ጠቃሚ የሆኑትን መሻሻሎች ነው። …" (የራስ ወርቅ፣2004፣6)። በማለት ልማትን ከህብረተሰባዊ ለውጥ ጋር ያያይዙታል። ለውጥ ደግሞ በጎም መጥፎም ገጽታ ስለሚኖረው ከልማት ጋር የሚያያዘው በአብዛኛው በጎ የሆነው ለውጥ እንደሆነ ያስረዳሉ።

ልማት ማለት በማህበረሰቡ መንፈሳዊና ቁሳዊ ጉዳዮች ረገድ የተሻለ ህይወት ማምጣት ከሆነ የልማት (Development) ፍቺ በመሠረቱ ከኢኮኖሚያዊ ዕድገት (Economic Growth) የሚለይ ነው። የኢኮኖሚ ዕድገት ማለት በርካታ የፍጆታ ዕቃዎችን እና አገልግሎቶችን ማምረት እንዲሁም አጠቃላይ የሀገራዊ ምርት (GDP) መጨመር፣ እና አጠቃላይ የሀገራዊ ገቢ (GNI) ዕድገት ማለት ነው። ሆኖም የኢኮኖሚ ዕድገት የማህበረሰቡ ዋነኛ ጉዳይ የሆነው ድህነት ላይ ለውጥ ሳይመጣ ዕድገቱ በጥቂት ሰዎች ላይ ብቻ የመጣ ሊሆን ይችላል (Peet and Hartwick. 2009)።

በብዙ ምዕራባውያን ሀገሮች ባለፉት 30 ዓመታት የመጣው ዕድገት በዚህ መልኩ የመጣ ነው። ይህ ደግሞ ሀብታምና ታዋቂ የሆኑ ጥቂት ሰዎችን ብቻ የጠቀመ በመሆኑ

ብዙሃኑን አይመለከትም:: የኢኮኖሚ ዕድገት ሀብትን በጥቂቶች እጅ ማስገባት ከሆነ ለብዙሃኑ የተሻለ ህይወትን ስለማያመጣ ልማት ሊሆን እንደማይችል ብዙዎች ይስማማሉ (Peet and Hartwick. 2009፣):: ቀደም ባለውም ጊዜ በተለይ በ1950ዎቹና 60ዎቹ ልማት ማለት ከኢኮኖሚ ዕድገት ጋር አንድና ስምም ተደርጎ የመውሰድ አመለካከት እንደነበርና ባሁኑ ጊዜ ግን ተለውጦ ልማት ሲባል በሰፊው ትርጉሙ በመውሰድ የኢኮኖሚ ልማትንና የህዝብን የፖለቲካና የሶሻል ደህንነትን እንዲያቅፍ መደንገጉን የራስ ወርቅ UNDPን ጠቅሰው ያስረዳሉ (የራስ ወርቅ፣ 2004፣7) ::

የምዕራባውያን የልማት ፖሊሲ ችግሮች ዋነኛ ምንጭ የሆነው ምዕራባዊነትን በሌላው ላይ የመጫን አዝማሚያ ነው፤ የሚሉት Cumming (1990) በበኩላቸው ይህ የምዕራባውያን አስተሳሰብ ሥልጣኔን ከምዕራባዊነት ጋር ብቻ የሚያያዝ፣ ለባህል ልዩነት ቦታ የማይሠጥ፣ ከግብርና ይልቅ በኢንዱስትሪ ዕድገት ላይ የሚያተኩር በመሆኑ በልማት ዙሪያ የሚሠሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እታች ድረስ ወርደው ማህበረሰቡን በማግኘት እንደሚሠሩ ላይ ላዩን ቢያሳዩም የማህበረሰቡን ባህል ማወቅና የልማት ተልዕኮአቸውን በዚያ ላይ መመሥረት የማይፈልጉ መሆናቸው ትልቅ ችግር እንደሆነ ይገልፃሉ::

የማህበረሰቡን ፍላጎት፣ የለውጥ ተነሳሽነቱንና አቅሙን መገንዘብ ለልማቱ ውጤታማነት ዋነኛ ጉዳይ እንደሆነና ፍላጎቱንና ተጨባጭ ሁኔታውን ያላገናዘበ የልማት ፕሮግራም ሊሳካ ካለመቻሉም በላይ በማህበረሰቡ ውስጥ የጥገኝነትን መንፈስ እንደሚፈጥርም ያሳያሉ (Cumming, 1990)። Ojameruaye የተባሉ ተመራማሪ የኢኮኖሚ ልማትን ፍቺ እንደሚከተለው ይገልፁታል::

> In a more robust form, economic development is defined as the process of improving the quality of all human lives that involves four aspects. Firstly, it involves economic growth, i.e. increase in the

production of goods and services. Secondly, it involves raising peoples' living standards their income, consumption of food, access to health and education, housing, sanitation, modern technology etc. Thirdly, it involves creating conditions for conducive to the growth of peoples' self-esteem through appropriate social, political, and economic systems/institiutions/processes that promote human diginity and respect. Fourthly, it involves increasing people's freedom to choose by enlarging the range of options available to individuals including consumer goods and services as well as other social and poltical variabls (Ojameruaye,2005;2).

ልማት በጠንካራ መልኩ ሲፈታ የሰው ልጅ ሁለንተናዊ ህይወት ጥራት ባለው ደረጃ ከአራት ጉዳዮች ረገድ ማደግ ነው ብለው ነጥቦቹን እንደሚከተለው ይዘረዝሯቸዋል፡፡ አንደኛ ከኢኮኖሚ ልማት ጋር የሚታየው የዕቃዎችና አገልግሎቶች ምርት መጨመር ነው፤ ሁለተኛ ከሰዎች የኑሮ ደረጃ ማደግ ጋር የሚያያዘው የገቢያቸው መጨመር፣ የምግብ የጤና የትምህርት፣ የዘመናዊ ቴክኖሎጂ ፍላጎት መሟላት ነው፤ ሶስተኛ ሰዎች በራስ መተማመን እንዲኖራቸውና ሰብዓዊ ክብራቸውና ተቀባይነታቸው እንዲከበር የሚረዱ ተገቢ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት/ ተቋማትና ምቹ ሁኔታዎች መኖርና መጠበቅ፤ አራተኛ የሰዎች መሠረታዊ ፍላጎቶችን የሚያሟሉ ምርቶችና አገልግሎቶችና ሌሎች ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች የሚቀርቡላቸው የተለያዩ አማራጮችና ለመምረጥ ያላቸው ነፃነት ማለት ነው (Ojameruaye,2005;2 ትርጉም የእኔ)፡፡

ከላይ በዝርዝር ልማት የሰው ልጆች የተሻለ ህይወት እንዲኖሩ ለማስቻል የሚደረገውን ሁለንተናዊ ለውጥና መሻሻል ከሆነ የዚህ ጥናትም ትኩረት በዚሁ ሁለንተናዊ ፍቺው ላይ የተመሠረተ ይሆናል፡፡ ጥናቱ የሚመለከተው የኢኮኖሚ ዕድገትን (Economic Growth) እና ከዘመናዊነትና ከሥልጣኔ ጋር ብቻ የሚያያዘውን ጉዳይ አይደለም፡፡ ይልቁንም የሰው ልጅ ሁለንተናዊ መገለጫ የሆነውን ባህል በማልማትና ቁሳዊና መንፈሳዊ ፍላጎቶቹን በጥምር አርክቶ የተሻለ ህይወት እንዲኖርር ማድረግን የሚጠይቀውን የልማት ጉዳይ ነው፡፡ ለዚህም ልማት የሚለውን ፅንሰ ሃሳብ ከዚሁ ከማህበረሰቡ ቁሳዊና መንፈሳዊ ጉዳዮች ልማት ጋር በማያያዝ ከባህሉ ጋር ያለውን ቁርኝትና መስተጋብር የሚመለከት ጥናት ነው፡፡

## 2.3. የባህልና የልማት ቁርኝት

**"Development in the 21st Century will be cultural or nothing at all."**
(UNESCO 1997, quoted in Radcliffe, 2006, 17)

ባህልን ወደ ልማት ጉዳይ ስናመጣው የልማቱን ዓላማዎችና ከባህል ውስብስብ ፅንሰ ሀሳቦች ጋር ያለውን መስተጋብር አጠንክሮ ማሰብ ይስፈልጋል፡፡ የልማትንም ሆነ የባህልን ሰፊና ውስብስብ ፍቺዎች በማሳየት ባህል ለልማት ቁልፍ ጉዳይ እንደሆነ ቀደምት አስተሳሰቦች ያሏቸውን ዋነኛ ችግሮች በማንሳት የሚያስረዱ አሉ፡፡ እነሱም የቀደሙት የልማት አስተሳሰቦች ውድቀቶች፣ የሉላዊነት (globalization) አስተሳሰብ፣ ለባህላዊ ብዝኀነት (cultural diversity) የሚሰጠው ግምት አናሳነት፣ በማህበራዊ ልዩነቶች ዙሪያ (በሥርዓተ ፆታ፣በኀሳዊነት እና በዘረኝነት) ያለው አቀንቃኝነት፣ የምስራቅ እስያ

የልማት ስኬቶችና ድሎች እና የማህበራዊ ትስስር ፍላጎቶች የባህልንና የልማትን ቁርኝት ጎልቶ እንዲታይ አድርገውታል ይላሉ (Radcliffe, 2006; Cumming, 1990)።

ባህል በልማት ውስጥ ሊኖረው የሚገባው ስፍራና አስፈላጊነት ተጠቃሽ እየሆነ የመጣውና ዋነኛ ጉዳይ እየሆነ መታየት የጀመረው ከ19ነኛው ምዕት ዓመት የመጨረሻዎቹ ዓመታት ወዲህ እንደሆነ መረጃዎች ያመለክታሉ። Radcliffe (2006) እንደሚሉት ባህልና ልማት ያላቸውን ቁርኝት በዋነኛ አጀንዳነት ይዘው የተነሱ ዩኔስኮን የመሰሉ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ከ1988-1997 ባለው አሰርት ባህል ለልማት ያለው አስተዋፅዖ ትኩረት እንዲያገኝ አድርገዋል። በነዚህ ዓመታት በሀገራት የልማት አጀንዳ ውስጥም ባህላዊ እሴቶች አስተሳሰቦችና መስተጋብሮች በስፋት ግምት ውስጥ እየገቡና ትኩረት እያገኙ መጥተዋል። የባህል ልዩነቶችና ብዙህነቶች በልማት መስተጋብር ውስጥ በተገቢ ሁኔታ ከተስተናገዱ ውጤታማ የልማት መሣሪያዎች እንደሆኑ እየተረጋገጠ እንደመጣ ያስረዳሉ። (Radcliffe,2006;10)

Cumming (1990) እንደሚገልፁት ባህል ከልማት ቲዎሪዎች ጋር የሚያያዝ ሰፊ እሳቤ ያለው በመሆኑ ለልማት ዕቅዶችና ስትራቴጂዎች መሳካት ለተለያዩ ባህሎች ክብርና ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል። በልማት ዙሪያ የሚሰሩ የተወሰኑ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ለልማት ግባቸው መሳካት ለማህበረሰቡ ባህል ትኩረት መስጠት እንዳለባቸው እየተገነዘቡ ቢመጡም ለእነሱ ባህል ማለት ጥበብ፣ ሙዚቃ፣ ዳንስና ሥነ ጽሁፍ ብቻ እንደሆነ እንደሚያስቡ፣ እያንዳንዱ ማህበረሰብ ለእነሱ እንግዳ የሆነና በልማቱ ሥራ ላይ ሳይቀር ተፅዕኖ ሊያሳድር የሚችል ቴክኒካዊ፣ ማህበረ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ባህል እንዳለው እንደማይቀበሉ ያስረዳሉ።

ይሄ በመሆኑም በትምህርት ስም የማህበረሰቡን ቃላዊ ባህል እንደሚያጠፉ፣ በግብርና ዘመናዊነት ስም የተሻለውን የመሬት አያያዝና አከፋፈል፣ ሀብት፣ ቁጥጥር የሌለበት የሚመስለውን ኢኮኖሚያዊ ባህላቸውን፣ ትብብራቸውንና ጓዳዊነታቸውን እንደሚደመስሱ፣ በዴሞክራሲ አስተሳሰብ ስም ሰላማዊ የሆኑ አስተዳደራቸውንና

መሪዎቻቸውን፣ በሰብዓዊ መብት ስም ሀገረሰባዊ የፍትህ ሥርዓታቸውን እንደሚያጠፉ ይተነትናሉ፡፡

Cumming, 1990 አያይዘውም የምዕራባውያን የልማት ቲዎሪና ተግባር "ዘመናዊነትና" (Modernizetion) "ምዕራባዊነትን" (Westernization) በሌሎች ላይ መጫንን መሠረት አድርጎ ስለሚነሳ ነው፡፡ የ3ኛው ዓለም ድህነት ኢኮኖሚውን በማዘመን ብቻ ሊቀረፍ የሚችል የታሪካዊ ኋላ ቀርነት ውጤት ሳይሆን ይልቁንም "ምዕራቡ በደቡቡ" ላይ የፈጠረው ዘዴያማ የቅኝ ግዛት ውጤት እንደሆነና ለልማት ስትራቴጂዎችና ፕሮጀክቶች አለመሳካት በዋና ምክንያትነት የሚነሱት ማህበረ ኢኮኖሚያዊ ወይም ፖለቲካዊ ጉዳዮች ሳይሆኑ በእያንዳንዱ ማህበረሰብ ውስጥ ያለው የባህል ልዩነትና ከዚህ አንፃር ማህበረሰቡ የሚኖረው ፍላጎት ነው በማለት ያስረዳሉ (Cumming, 1990) ፡፡

(Schech & Haggis, 2000) እንደሚሉት የዘመናዊነት (Modernizetion) አስተሳሳብ አራማጆች ባላደጉ ሀገሮች ማህበረሰቦች ውስጥ የድህነትን ዑደት ለመስበርና ከገቡበት ማጥ ለማውጣት ኋላ ቀር አመለካከቶችን የሚንድ ሁለንተናዊ ለውጥ ያስፈልጋል፤ እነዚህ ሀገራት ማደግ እንዲችሉም የምርት ዕድገትና የኢኮኖሚ ለውጥ ብቻ ሳይሆን የትምህርት ሥርዓቱ፣ የአስተሳሰብ ሂደቱና መንገዱ፣ የአኗኗር ዘይቤው ሁሉ ከኋላ ቀርነት ተላቆ መዘመን ባይ እንደሆኑ ይገልፃሉ (Schech & Haggis, 2000;9)፡፡

እነዚሁ ሰዎች የዘመናዊነት አስተሳሰብ አራማጆች የመከራከሪያ ነጥብ እንደማይሠራ ሲያሳዩም ከላይ ወደታች የሚዘረጋ የዘመናዊነት አስተሳሰብና የልማት አቅጣጫ ውጤት አልባ መሆኑ የልማት ድርጅቶች ከድህነትና ከረሃብ ጋር የያዙትን ውጊያ መኮላሸትና ለውጥ አለማምጣት ጥሩ ማሳያ ነው፡፡ ለግብርና ሥራ ከፍተኛ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀምና ግብርናውን በኢንደስትሪ መተካት የዓለም ደሃ ህዝቦችን የኑሮ ደረጃ ውድቀት በተለይም የሴቶችንና የህፃናትን ድህነት አባብሷል በማለት የዘመናዊነት አስተሳሰብን ችግር ያመለክታሉ (Schech & Haggis, 2000;9)፡፡

**ከላይ ከቀረቡት ሃሳቦች የምንረዳው ባህላዊ ሁኔታዎችን መሠረት ያላደረገና በዘመናዊነት ላይ ብቻ የተመሠረተ የልማት አስተሳሰብና አካሄድ ውጤታማ መሆን እንደማያስችል ነው:: ለዚህም ይመስላል ዛሬ አለም አቀፍ ተቋማት ሳይቀሩ የልማት አጀንዳዎችን ይዞ የሚነሳ አካል ገና ከመነሻው የባህል ጉዳዮችን አብሮ ማሰብ እንዳለበትና ሀገራትም በየልማት ፖሊሲዎቻቸው ውስጥ የባህልን ጉዳይ አካተው እንዲሠሩ የሚያሳስቡት::**

**ባህል የልማት ዋነኛ ጉዳይ ሆኖ በልማት ክርክሮች ውስጥ ተጠቃሽ እየሆነ የመጣው ከ19ነኛው ምዕት አመት የመጨረሻዎቹ ዓመታት ወዲህ እንደሆነ መረጃዎች ያስረዳሉ:: እንደ የተባበሩት መንግስታት ያሉት ዋነኛ ዓለም አቀፋዊ ተቋማት የልማት አሰርት ዓመታት በሚባሉት ከ1988-1997 ባሉት ዓመታት ባህልና ልማት ሳይነጣጠሉ እንዲታዩ አድርገዋል:: ዓለም ባንክና ሌሎች አለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማት ባህል በሰፊ ትርጉሙ በልማት ጉዳይ ውስጥ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ እንደሆነ መናገር መጀመራቸውን ያስረዳሉ** (Radcliffe, 2006;2 )::

**የባህልንና የልማትን ጉዳይ ዋነኛ አጀንዳው አድርጎ እየሠራ ያለው የተባበሩት መንግስታት የትምህርት፣ የሳይንስና፣ የባህል ድርጅት** (**ዩኔስኮ**) **ፓሪስ ላይ በ**2005 CONVENTION **on the Protection and Promotion of the Diversity of Cultural Expressions በሚል ባወጣው ሰነድ ባህል ለዘላቂ ልማት ያለውን ፋይዳ አስመልክቶ አንቀፅ 13 ላይ INTEGRATION OF CULTURE IN SUSTAINABLE DEVELOPMENT በሚል ርዕስ ሥር የሚከተለውን ደንግጓል::** "Parties shall endeavour to integrate culture in their development policies at all levels for the creation of conditions conducive to sustainable development and, within this framework, foster aspects relating to the protection and promotion of the diversity of cultural expressions." **በማለት አባል ሀገራት በሙሉ በልማት ፖሊሲ ሰነዳቸው ሁሉ የባህልን ጉዳይ ትኩረት እንዲሰጡት ያስገነዝባል::**

ይሄው ድርጅት "The Power of Culture for Development" በሚል ርዕስ በ 2010 ባዘጋጀው ሌላ ሰነድ ባህል በሁለንተናዊ መልኩ ለዘላቂ ልማት መሠረታዊ ጉዳይ እንደሆነ በማረጋገጥ ባህል በቁሳዊና መንፈሳዊ (ተጨባጭና ረቂቅም ማለት ይቻላል) መልኮቹ (tangible and intangible) ፣ በፈጠራ ኢንዱስትሪና በተለያዩ ጥበባዊ መገለጫዎቹ፣ በኢኮኖሚያዊ ልማት፣ ማህበራዊ መረጋጋትን ለመፍጠርና ለአካባቢ ጥበቃ ዓይነተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ይገልፃል።

በተጨማሪም ሰዎች በአካባቢያቸው እንዴት መኖር እንዳለባቸውና በሀገራዊም ሆነ በዓለማቀፋዊ መስፈርት እንዴት ግንኙነት እንደሚያደርጉ የሚበይን ዋነኛ ጉዳይ እንደሆነ አንስቶ ባህል የአዳዲስ ሃሳቦችና የፈጠራዎች ምንጭ፣ የአንድ ማህበረሰብ የተለያዩ ውስብስብ የሆኑ መንፈሳዊና ቁሳዊ ዕውቀቶችና ውስጣዊ ስሜቶች ተዛምዶዎች፣ ዕምነቶችና እሴቶች መገለጫና ከዓለም ጋር የሚያስተሳስሩ የራሱ ቅርፆችና ድሮች ያሉትና በእነዚህ የዓለም አተያዮችና የአገላለፅ ቅርፆች ላይ ተፅዕኖ የሚያደርግና የሚደረግበትም በመሆኑ በአግባቡ ከተያዘ ታዳሽ ሀብት እንደሆነ ያመለክታል።

ባህል የኢኮኖሚ ልማትም አንቀሳቃሽ ሞተር በመሆኑ ሥራና የገቢ ምንጭን በመፍጠር፣ በባህላዊ ቱሪዝም፣ በማክሮ ኢንተርፕራይዞች፣ በባህላዊ መሠረተ ልማቶችና ተቋማት ጠንካራ ዓለማቀፋዊ የኢኮኖሚ ምንጭና ሃይል እንደሆነም ያስረዳል። በባህሎች መካከል ያለን ብዙኀነትን እውቅና በመስጠት በጎና ገንቢ ግንኙነትን በመፍጠርና ዕውቀትን በማሸጋገር፣ የጋራ መግባባትንና መስማማትን ፈጥሮ ግጭትን በማስወገድና ሰላምን በማስፈን፣ ለማህበራዊ ህይወት መረጋጋትና ዘላቂነት አንቀሳቃሽ ሞተር በመሆን የሚያገለግል እንደሆነ ይሄው የዩኔስኮ ሰነድ ያትታል።

በተጨማሪም ሰዎች ከተፈጥሮኣዊ አካባቢያቸው ጋር ያላቸውን ዝምድና፣ እንዴት እንደሚጠብቁትና እንደሚያስተዳድሩት የሚኖራቸው አመለካከት የሚቀረፀው በባህላቸው በመሆኑ ባህል ለዘላቂ የአካባቢ ጥበቃና ልማት አንቀሳቃሽ ሞተር ነው። የተፈጥሮና

ሰው ሰራሽ አደጋዎችና ግጭቶች ጥለውት ከሚያልፉት በጎ ያልሆኑ አሻራዎች፣ ስሜቶችና መጥፎ ትዝታዎች ማህበረሰቡ እንዲያገግም ባህል ዋነኛ መሣሪያ እንደሆነ በመዘርዘር ባህል ለልማት የሚጫወተውን ሚና በስፋት ያስረዳል (UNESCO, 2010) ፡፡

ከዚህ ባለፈ የባህል ኢንዱስትሪዎች መስፋፋት ለሀገራት ልማት ዓይነተኛ አስተዋጽዖ እንደሚኖረው "Culture: a driver and an enabler of sustainable development" በሚል ርዕስ በ2012 የተዘጋጀ ሌላ የዩኔስኮ ሰነድ እንደሚከተለው በምሳሌ አስደግፎ ያስረዳል፡፡

> Cultural and creative industries represent one of the most rapidly expanding sectors in the global economy with a growth rate of 17.6 % in the Middle East, 13.9 % in Africa, 11.9 % in South America, 9.7 % in Asia, 6.9 % in Oceania, and 4.3 % in North and Central America. Promoting this sector requires limited capital investment, involves low entry barriers and can have a direct impact on vulnerable populations, including women. In Ecuador, recent studies show that the formal and private cultural activities contributed 4.76% to the 2010 GDP and in the same year, 2.64% of the total employed population worked in cultural occupations. Almost 60% of the latter were women. (UNSCO, 2012,4)

> ባህላዊና የፈጠራ እንዱስትሪዎች በዓለም ኢኮኖሚ ውስጥ በአብዛኛው በፈጣን ሁኔታ በመስፋፋት ላይ ካሉ ሴክተሮች ዋነኞቹ እየሆኑ መጥተዋል፡፡ በዚህም በመካከለኛው ምስራቅ 17.6፣ በአፍሪካ 13.9፣ በደቡብ አሜሪካ 11.9፣ በኢስያ 9.7፣ በኦስኒያ 6.9፣ በሰሜንና በመካከለኛው አሜሪካ ደግሞ 4.3 በመቶ የመጣውን የኢኮኖሚ ዕድገት ይሸፍናሉ፡፡ እነዚህን ሴክተሮች (ዘርፎች) ለማስፋፋት የሚጠይቀው ካፒታል የተወሰነ ከመሆኑም ባሻገር ሴቶችን ጨምሮ

> የተለያዩ ህዝቦችን ማሳተፍ የሚያስችሉና ሰፊ የሥራ ዕድልን የሚፈጥሩ ሆነው ተገኝተዋል። የቅርብ ጊዜ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በ2010 በኢኳደር ከአመታዊ ገቢያቸው ከመደበኛና የግል ባህላዊ እንቅስቃሴዎች የተገኘው 4.76 በመቶውን ድርሻ ይይዛል። በዚሁ ዓመት 2.6 በመቶው ህዝባቸው በባህላዊ ኢንዱስትሪዎች የሚሠራ ሲሆን ከዚሁ ውስጥ 60 በመቶው ደግሞ ሴቶች ናቸው (UNSCO,2012,4 ትርጉም የእኔ)።

ከዚህ የምንረዳው ባህል ለሀገር ልማት ያለውን ጉልህ አስተዋፅዖ ሲሆን ባህልን ኋላ ቀርና ለልማትና ለዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች መስፋፋት እንቅፋት እንደሆነ አድርጎ ከመውሰድ ይልቅ ባህላዊ ኢንዱስትሪዎችን በማስፋፋትና በማልማት ለአንድ ሀገር የገቢ ምንጭ የሚፈጥር ከመሆኑም በላይ ለዜጎች ከፍተኛ የሥራ ዕድል ፈጣሪና በተለይም ለሴቶች ፍትሃዊ የሆነ የሀብት ማግኛ ምንጭም ማድረግ እንደሚቻል ነው።

በመሆኑም ከላይ የቀረቡት የባህልና ልማት ቁርኝትን የሚያመለክቱ ማስረጃዎች የሚያሳዩት የዘመናዊነት (Modernizetion) አስተሳሰብ አራማጆች እንደሚሉት ለአንድ ሀገር ልማት የሚበጀው ጉዳይ ዋነኛ እንቅፋቶች ናቸው የሚሏቸውን ባህላዊ ሁኔታዎች አሽቀንጥሮ በመጣልና ዘመናዊነትን በመጠመቅ ሳይሆን ይልቁንም ለባህላዊ መሠረቶች ትኩረት ሰጥቶ ከልማቱ ጋር በማዋሃድ ሁለንተናዊ ዕድገት ማምጣት እንደሚቻል ነው። ስለዚህ ባህል የማይነካው ማህበረሰባዊ ጉዳይ ስለሌለ ስለአንድ ማህበረሰብም ሆነ አካባቢ ልማት ስናወራ ባህሉን ጎን ለጎን ማየትና ራሱን እያለሙ የልማት መሣሪያ ማድረግ ተገቢ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል። የዚህ ጥናት ትኩረትም ይህ የባህልና ልማት ቁርኝት በበርታ ብሔረሰብ እንዴት ባለ ሁኔታ እንደሚገለፅ ማሳየት ይሆናል።

## 2.4. ግብርና ኤክስቴንሽን

የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት በሀገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ የተዋወቀው እ.ኤ.አ. በ1953 በቀድሞው ዓለማያ እርሻ ኮሌጅ በአሁኑ ሀሮማያ ዩኒቨርሲቲ እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ (Spielman & Others, 2011)። አገልግሎቱ የተጀመረው የተሻሻሉ ዘሮችን፣ ሰው ሰራሽ ማዳበሪያንና ብድርን ለአነስተኛ አርሶ አደሮች ለማቅረብና ከኋላቀር አስተራረስ ዘዴ አላቆ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግን ግቡ አድርጎ በመነሳት ነው።

በ1960ዎቹ የኤክስቴንሽን አገልግሎቱ እየተጠናከረ መጥቶ በተቀናጀ ፓኬጅ ፕሮጀክት አማካይነት ለበርካታ ገበሬዎች ይሰጥ ጀመር። በ1980ዎቹ የኤክስቴንሽን አገልግሎቱ በፍጥነት እየታወቀና እየተለመደ ስለመጣ ሥልጠናና ጉብኝት(Training and Visit) የሚሉትን አገልግሎቶች አካቶ በዓለም አቀፍ ረጂ ድርጅቶች እየታገዘ መስፋፋት ቀጠለ። ቆይቶ አሳታፊ ሰርቶ ማሳየትንና የኤክስቴንሽን ሥልጠና ዘዴ (Participatory Demonstration and Extension Training System /PADETS) ፕሮግራምን ከሥልጠናና ጉብኝት (Training and Visit) ጋር በማቀናጀት በተለይ ምርጥ ዘሮችንና ሰው ሰራሽ የኬሚካል ማዳበሪያዎችን ለአርሶ አደሩ ለማሰራጨት በተካሄደው እንቅስቃሴ ከ2007-2008 ለ9 ሚሊዮን አርሶ አደሮች እንደተዳረሰ እነ (Spielman& Others, 2011) ያስረዳሉ።

በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ያለው የግብርና ኤክስቴንሽን ዘዴ ከላይ የተጠቀሰው የPADETS ፕሮግራም ሲሆን በአርሶ አደሩ ማሳ ላይ ሠርቶ በማሳየት ላይ ትኩረት በማድረግ የግብርና ግብዐቶችንና ብድር በማቅረብና በገጠር የልማት ኮሚቴዎችን በማደራጀት ለሴቶችና ለወጣቶች ትኩረት በሚሠጥ መልኩ እየተተገበረ እንደሚገኝ ከላይ የተጠቀሰው ማስረጃ ያመለክታል።

በኤክስቴንሽን አገልግሎቱ የተካተቱት የምግብ እህል ፓኬጆች በቆሎ፣ስንዴ፣ ጤፍ፣ ገብስ፣ ማሽላ እና በገበያ አዋጪ የሆኑ ቡና፣ ለውዝ፣ ቀይ ሽንኩርት፣ ቲማቲም፣ ጥቅል ጎመን፣ ካሮትና ስኳር ድንች የመሳሰሉት ሰብሎች ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ የእንስሳት

እርባታ፣ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ፣ የድህረ ምርት ኤክስቴንሽን ፓኬጆችም አሉ (Carlsson & Others, 2005)፡፡

ለኤክስቴንሽን ፓኬጆቹ ተግባራዊነት እንዲረዱ በዋንኛነት የሚቀርቡት ግብዐቶች ደግሞ ሰው ሠራሽ ማዳበሪያና ምርጥ ዘር ናቸው፡፡ አርሶ አደሩ እነዚህን ግብዐቶች ለመግዛት እንዲችል ከመንግሥት የብድር አገልግሎት የሚቀርብለት ሲሆን በግብርና ሙያ በዲፕሎማ ደረጃ የሰለጠኑ እስከ ሦስት የሚደርሱ የልማት ሠራተኞችም በየአካባቢው ተመድበውለት ፓኬጆቹን እንዴት እንደሚተገብር ሥልጠናና ድጋፍ ይሰጠዋል፡፡

ይሁንና ይሄ በሀገር አቀፍ ደረጃ ከረጅም ጊዜ አንስቶ እየተተገበረ ያለው የግብርና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች ለምሳሌ በአማራ፣ በትግራይ፣ በኦሮምያና በደቡብ ክልሎች በተወሰነ መልኩ የሚፈለገውን ለውጥ በማምጣት ላይ የሚገኝ ቢሆንም ይሄ ጥናት በሚደረግበት በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ውጤታማነቱ እጅግ ዝቅተኛ በመሆኑና ክልሉን "በልማት ወደ ኂላ የቀሩ" ካሰኙት ምክንያቶች አንዱ በመሆኑ ለተግባራዊነቱ በአዎንታዊም ሆነ በአሉታዊ መልኩ የበርታ ብሔረሰብ ባህል ያደረገው አስተዋፅዖ በጥናቱ ይፈተሻል፡፡

## 2.5. ጤና ኤክስቴንሽን

ስለ ልማት ጉዳይ ስናነሳ የማህበረሰቡን ቁሳዊና መንፈሳዊ ልማት የሚመለከት እንደሆነ ከላይ በስፋት ተገልፆአል፡፡ ማህበረሰቡ በዚህ መልኩ እንዲለማ ከሚያደርጉት ጉዳዮች አንዱ ደግሞ ጤናው የተጠበቀ እንደሆነ ነው፡፡ ጤናው ያልተጠበቀ ማህበረሰብ እራሱንም ሆነ አካባቢውን ለማልማት አይችልም፡፡ ስለዚህ የጤና ጉዳይ አንዱ የልማት ጉዳይ ከመሆኑም በላይ ከባህል ጋር በእጅጉ ስለሚያያዝ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አፈፃፀም ከበርታ ባህል ጋር ተያይዞ በዚህ ጥናት አንዱ የሚተኮርበት ጉዳይ ይሆናል፡፡

በሀገር አቀፍ ደረጃ በመንግሥት ታቅደው እየተተገበሩ ካሉት የልማት ፕሮግራሞች የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አንዱ ነው። ፕሮግራሙ የተጀመረው የኢፌዲሪ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በ 1995 ዓ.ም. የመጀመሪያ ደረጃ የጤና አጠባበቅ ሽፋንን ለማስፋፋት አዲስ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ዕቅድ ይፋ በማድረጉ ነው (የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣1995)።

የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም በማህበረሰብ ጤና ላይ የተመረኮዘ የግል የጤና እንክብካቤ አቅርቦት ስርዓት ሲሆን አስፈላጊ የሆኑ የጤና የማስፋፊያ እና የመከላከያ አገልግሎቶችን ማቅረብ ላይ ያለመ ነው። በመጀመሪያ ላይ እንዲተዋወቅ የተደረገው በሀገሪቱ ከከተማ ራቅ ባሉ አካባቢዎች ለሚገኙ ማህበረሰቦች አስፈላጊ የሆነ የጤና አገልግሎት ለማቅረብ አለመቻሉን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ቢሆንም አሁን ግን በከተሞችም የጤና ኤክስቴንሽን አገልግሎት እየተካሄደ ይገኛል።

የጤና ኤክስቴሽን ፕሮግራም አገልግሎቶች የአርብቶ አደሩን፣ የአርሶ አደሩን እና የከተማ ነዋሪ ሕዝቦችን ፍላጎቶች፣ ጥያቄዎች እና የሚጠብቋቸውን ሁኔታዎች ለማሟላት እንዲቻል ታስቦ የተዘጋጀ ነው። ይህ ፕሮግራም የሚሊኒየሙን የልማት ግቦች ለማሳካት በጣም ወሳኝ ተቋማዊ ማዕቀፍ ተደርጎ ይቆጠራል።

የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ዓላማ ብዛት ያለው የአገሪቱ ሕዝብ ወደሚኖርባቸው ገጠራማ አካባቢዎች ተፈላጊ የጤና አገልግሎቶችን ማዳረስ ነው። በዚህ ዓላማ ሥርም አስፈላጊ የጤና አገልግሎቶችን በፍትሃዊነትና ባልተማከለ አሰራር የማግኘት እድልን በመንደር እና በአባወራ ደረጃ ለማሻሻል፤ የጤና ግንዛቤን፣ እውቀትን እና ክህሎትን በማህበረሰቡ አባላት መካከል በማሳደግ ባለቤትነትን እና ተሳትፎን ለማረጋገጥ፤ የጤና አገልግሎቶችን በማግኘት ረገድ የፆታ እኩልነትን ማራመድ፤ በማህበረሰቡ እና በጤና ተቋማት መካከል ያለውን ክፍተት በጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች በኩል በማገናኘት የአካባቢ ጤና አገልግሎቶችን አጠቃቀም ለማሻሻል፤ የወሊድ እና የሕፃናት ሞትን

ለመቀነስ እና ጤናማ የሕይወት ዘይቤን ለማራመድ የሚሉ ዓላማዎችን ይዞ የተዘጋጀ ነው (የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣1995)።

በፕሮግራሙ የሚተገበሩት የጤና አገልግሎቶች በዋናነት በሥራቸው ብዙ አገልግሎቶችን የያዙ አራት የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጆች ናቸው። ከእነሱም ውስጥ አንደኛው በሽታን የመከላከልና የመቆጣጠር ፓኬጅ ሲሆን በሥሩ ኤችአይቪ/ኤድስንና በፆታ ግንኙነት ሳቢያ የሚተላለፉ በሽታዎችን እና ቲቢን መከላከል፣ ወባን መከላከል እና መቆጣጠር፣ የመጀመሪያ እርዳታና አስቸኳይ ጊዜ እርምጃዎች የተሰኙ አገልግሎቶችን ያጠቃልላል።

ሁለተኛው ደግሞ የቤተሰብ ጤና እንክብካቤ ፓኬጅ ነው። ይህም የእናቶችና የሕፃናት ጤና ክብካቤ፣ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት፣ በሽታን መከላከል፣ የተመጣጠነ ምግብ አዘጋጃጀት እና የወጣቶች የሥነ ተዋልዶ ጤና እንክብካቤ የተሰኙ አገልግሎቶችን ያካተተ ነው።

በሦስተኛነት የምናገኘው ደግሞ የግል ጤናና የአካባቢ ንጽሕና አጠባበቅ ፓኬጅ ሆኖ በሥሩ የአይነ ምድር አወጋገድ፤ የደረቅ እና ፈሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ፣ የንፁህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦትና አቀራረብ፣ የጤናማ ምግብ አጠባበቅ፣ ንፁህ መኖሪያ አካባቢ እንክብካቤ እና የግል ንፅህና አጠባበቅ የተሰኙ አገልግሎቶችን ይዟል። አራተኛው የጤና ትምህርት አገልግሎትና ተግባቦት ላይ የሚያተኩር አገልግሎት ነው (ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣1995፣ Pathfinder,2008)።

ይህንን አገልግሎት ተግባራዊ ለማድረግ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ካላቸው ጊዜ 75% ያህሉን ቤት ለቤት በመዘዋወር የማስተማር ተግባራትን በማከናወን ማሳለፍ ይጠበቅባቸዋል። በእነዚህ ጉብኝቶች ወቅት፣ ባለሙያዎቹ እናቶች ለሕፃናት እንክብካቤ ሲያደርጉ መርዳት፣ የተመጣጠኑ ምግቦች አብስሎ ማሳየት፣ የመፀዳጃ ቤት እና የቆሻሻ ማስወገጃ ጉድጓዶች አብሮ መገንባትና የመሳሰሉትን ሥራዎች ከማህበረሰቡ ጋር አብረው

መሥራት ይኖርባቸዋል፡፡ ይሄ ተግባር ደግሞ ማህበረሰቡ እስከዛሬ ሲጠቀምበትና ሲተገብረው ከነበረው የአኗኗር ባህል ጋር በእጅጉ የሚያያዝ ነው፡፡

ማህበረሰቡ ስለግልና የአካባቢ ጤና እንክብካቤ፣ ስለ ተላላፊ በሽታዎች ቁጥጥርና ህክምና፣ ስለቤተሰብ ምጣኔና የአመጋገብ ሥርዓት የራሱ የሆነ ዕምነት፣ ልማድና ባህላዊ ወይም ሀገር በቀል ዕውቀት (indigenous knowledge) አለው፡፡ አሁን ደግሞ ዘመናዊ አገልግሎቶችን እንደ "አዲስ እየተማረ" እንዲተገብር እየተደረገ ነው፡፡ በመሆኑም በነባሩና በአዲሱ የአኗኗር ብልሃቶች መካከል ትግልና ተቃርኖ ስለሚፈጠር የአዲሱ ተግባራዊነት ፈተና ይገጥመዋል፡፡ ይሄ ክፍተት ደግሞ ልማቱ ወደ ኋላ እንዲጎተት ምክንያት ሊሆን ይችላል ተብሎ ስለሚታሰብ የጤና ኤክስቴንሽን አተገባበሩም እንደ ግብርናው ሁሉ በዚህ ጥናት የሚዳሰስ ሁለተኛ ዋነኛ ጉዳይ ይሆናል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

## 3. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝትና ንድፈ ሃሳባዊ መሠረቶች

በዚህ ክፍል በጥናት ርዕሱና በበርታ ብሔረሰብ ባህል ዙሪያ የተሠሩ የቀደሙ ጥናቶች ይከለሳሉ። በዚህም ይሄ ጥናት ከሌሎቹ የሚለይበትንና ይዞት የተነሳውን አዲስ ጉዳይ ለማሳየት ይሞከራል። ከዚህ በተጨማሪ ጥናቱ የሚገዛባቸው የንድፈ ሃሳብ መሠረቶች ምን እንደሆኑም ይቀርባል።

### 3.1. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ማህበረሰብ ባህልን አስመልክቶና በተለይም የጥናቱ ትኩረት በሆነው በበርታ ብሔረሰብ ባህል ላይ የተሠሩ ጥናቶችን ስንመለከት በክልሉ በሚገኙ ነባር ብሔረሰቦች ባህል ላይ የሚያተኩሩ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ ጽሑፍ፣ በውጪ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ፣ በታሪክ፣ በሶሻል አንትሮፖሎጂ፣ Regional & Local Development Studies ትምህርት ክፍሎች የተወሰኑ የሁለተኛና በርከት ያሉ የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፎች ተገኝተዋል። እነዚህ ሥራዎች ከርዕሱ ጋር በቀጥታ የሚዛመዱ ባይሆንም አንደኛ በባህል ዙሪያ የተሠሩ በመሆናቸው ሁለተኛ የክልሉን ነባር ብሄረሰቦች የሚመለከቱ በመሆናቸው እዚህ መጥቀሱ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል።

በኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የተሠሩ ጥናቶችን ስንመለከት አሰፋ ወርቁ በ1995 “የሺናሻ ብሔረሰብ ባህላዊ ጋብቻ”፣ ተሾመ ሙሉጌታ በ1998 ዓ.ም. “በቤንሻንጉል ጉሙዝ በድባጢ ወረዳ የለቅሶ ሥነሥርዓት”፣ አቡበከር ሀሰን በ1998 ዓ.ም. “የሺናሻ ብሔረሰብ የሀዘንና የተስካር ሥርዓት”፣ አክሊሉ ባይሳ በ2000 ዓ.ም “የበርታ ብሔረሰብ ጋብቻ ሥነ ሥርዓትና የሠርግ ዘፈኖች”፣ ሳሙኤል አክሊሉ “የጉሙዝ ብሔረሰብ ሀገረሰባዊ ልማድ በተለይ

የጋብቻ ሥርዓትና ክዋኔ"፣ ጌታመሳይ ግዛው በ2002 ዓ.ም "የሺናሻ ብሔረሰብ የቀብር ሥርዓት ክዋኔ ከፎክሎር ዘውጎች አንፃር" በሚሉ ርዕሶች የተሰሩ ጥናቶችን እናገኛለን።

እነዚህ ጥናቶች የየብሔረሰቦቹን የጋብቻ ወይም የሀዘን ባህላዊ ገጽታ በመግለፅ ላይ የሚያተኩሩ ናቸው። ከዝርዝሩ ውስጥ የዚህ ጥናት ትኩረት በሆነው በበርታ ብሔረሰብ ላይ የተሰራው የአክሊሉ ጥናት፣ የብሄረሰቡን የጋብቻ ስርዓትና የሠርግ ዘፈኖችን በማሳየት ብቻ ላይ ያተኮረ በመሆኑና የጋብቻ ሥርዓቱ ከልማት ጋር ያለውን ግንኙነት የማያሳይ በመሆኑ ተዛምዶ ቢኖረውም ከዚህ ጥናት ጋር አይመሳሰልም።

በዚሁ ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረቡ ጥናቶች ደግሞ የእታገኘሁ አስረስ "በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የማኦ ብሔረሰብ ባህላዊ የምግብ አዘገጃጀትና አመጋገብ" በ2002 ዓ.ም. እና የንጉስ ወዳጅነው "የበርታ ብሔረሰብ የባህል ምግቦችና መጠጦች አዘገጃጀትና አቀራረብ" በሚል ርዕስ በ2001 ዓ.ም. የተሠሩ ጥናቶች ናቸው። ሁለቱም ጥናቶች በተመሳሳይ የሚመለከቱት የሁለቱን ብሔረሰቦች ባህላዊ ምግቦች አዘገጃጀትና አቀራረብ ላይ እንጂ ከልማት ጋር ያላቸውን ግንኙነት አይደለም። የንጉስ ጥናት ይሄ ጥናት በሚያተኩርበት በበርታ ብሔረሰብ ላይ ተመሥርቶ በቅርብ ጊዜ የተሠራ በመሆኑ ስለክልሉና ስለብሔረሰቡ የሚነሳውን ታሪካዊ ዳራ በአብዛኛው ተመሳሳይ ያደርገዋል። በተጨማሪም ንጉስ በተለይ የተመለከተውን የበርታ ባህላዊ ምግብ አዘገጃጀትና አቀራረብ ሁኔታ በዚህ ጥናትም የሚዳሰስ በመሆኑ በመጠኑ ተዛምዶ ቢኖረውም ንጉስ ባላየው አቅጣጫ ከልማት ጋር አያይዞ የሚነሳ በመሆኑ ይሄ ጥናት ከንጉስ በእጅጉ ይለያል።

ጥናቱ በሚመለከተው ብሔረሰብ ላይ በውጪ ቋንቋዎችና ስነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት በTesfaye G. Mariam, "A Study of Major Themes in Jablawi Folktales" በሚል ርዕስ እ.ኤ.አ. በ1990 የተሠራ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ እናገኛለን። Tesfaye

ከሰበሰባቸው 115 የጀብላዊ[9] ተረቶች ውስጥ 72ቱን ወስዶ የይዘት ትንተና በማድረግ የማህበረሰቡን ማንነት፣ የአኗኗር ብልሃት፣ ስለዓለም ያላቸውን አመለካከትና ያልተዳሰሱ የቆዩ ልማዶቻቸውንና እሴቶቻቸውን አጥንቷል፡፡

Tesfaye የጥናቱን ጥቅም (purpose of the study) ሲገልፅ የጀብላዊ ተረቶች ሳይጠፉ ሰብስቦ ለመቅረስ፣ የተረቶቹን ይዘትና መባያ (motifs) በመመርመር ማህበረሰቡ ስለዓለም ያለውን አመለካከት፣ ልማድና እሴት ለማሳየት የተጠና እንደሆነ በመግለፅ የጥናቱ ውጤት ደግሞ በአካባቢው ልማትን ለማፋጠንና የማህበረሰቡን አኗኗር የተሻለ ለማድረግ የሚረዱ ፖሊሲዎችን ለመቅረፅ እንደሚረዳ ይናገራል፡፡

የTesfaye ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር መጠነኛ መመሳሰል የሚኖረው ከመነሻው ከላይ የተጠቀሰውን የልማት ጉዳይ በሰበሰባቸው ተረቶች የይዘት ትንታኔ ውጤት ለማሳየት እንደሚቻል አንስቶ ማለፉ ነው፡፡ የፎክሎር አንድ ዘውግ ከሆነው የሥነቃል አንድ መልክ የሆኑትን ተረቶችን ብቻ ወስዶ ይዘታቸውን በመተንተን የማህበረሰቡን ማንነትና አመለካከት ለማሳየት ይቻል ይሆናል፡፡ ግን የሚጎድለው ዋነኛ ጉዳይ አለ፡፡ ተረቶቹን ሰብስቦ ብቻ ቁጭ ብሎ ይዘታቸውን በመተንተን በአጠቃላይ የፎክሎር በተለይም የሥነቃል ወይም የተረቶች መከሰቻ የሆነውን አውድና ክዋኔ ሳይመለከቱ እንዲህ ያለ ትልቅ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ግን ያስቸግራል፡፡ ምክንያቱም የፎክሎር ነገረ ይዘቶችና (Texts) የክዋኔ አውድ (Context) ሊነጣጠሉ የማይችሉ በመሆናቸው ነው፡፡ ይሄን ጥናት ከተስፋዬ ስራ ጋር የሚለያየውም አንዱ ዋነኛው ጉዳይ ይኸው ነው፡፡

ይሄ ጥናት በእርግጥ Tesfaye የተመለከታቸውን የማህበረሰቡን ተረቶች ሊመለከት ይችላል፡፡ ጥናቱ የሚለየው ግን አሁን ያሉ ተረቶችን ስለሚያካትት፣ ተራቾቹ (መረጃ አቀባዮቹ) የተለዩ ሊሆኑ ስለሚችሉና ተረቶቹ በክዋኔ አውዳቸው ላይ ተፈጥሯዊ በሆነው

[9] "ጀብላዊ" ተስፋዬ የተጠቀመበት የበርታ ብሔረሰብ የጥንት መጠሪያው ነው፡፡ እርሱ እንደሚለው በርታ የጥንት ቅድማያቶቻቸው መጠሪያ እንደነበርና እሱ ጥናት ባደረገበት ጊዜ ጀብላዊ የሚለውን ስያሜ ማህበረሰቡ የሚመርጠው ነበር፡፡ አሁን ግን በርታ የሚለውን ስያሜ እየተጠራበት ይገኛል፡፡

መቼታቸው በሚተረቱበት ጊዜ ተራቹ፣ ታዳሚው፣ ቦታው፣ ጊዜውና አጠቃላይ ሁኔታው ምን እንደሚመስልና ምን እንደሚያመለክት በጥልቀትና በንቃት በመከታተል ሰብስቦ በመተንተን የሚሠራ በመሆኑ ነው፡፡

ሁለተኛ ይህ ጥናት Tesfaye የተመለከታቸውን ተረቶችንም ሊመለከት ስለሚችል በጥቂቱ ይመሳሰላል ተባለ እንጂ ከዚህ በሰፋ መልኩ የማህበረሰቡን ሁለንተና ቁልጭ አድርገው የሚያሳዩትን ሁሉንም የፎክሎር ዘውጎች ከክዋኔ አውዳቸው ጭምር የሚመለከትና ከልማት ጋር በማያያዝ የሚኖራቸውን በጎም ሆነ መጥፎ ተፅዕኖ የሚመረምር በመሆኑ ከተስፋዬ ጥናት በእጅጉ የሚለይና እሱ ያልዳሰሳቸውን ጉዳዮች ሁሉ የሚሸፍን ይሆናል፡፡

የዚህ ጥናት ትኩረት በሆነው ብሔረሰብ በሚገኝበት ወረዳ ላይ የተሠራ ሌላ ጥናት ከታሪክ ትምህርት ክፍል ተገኘው የ Adinew Abetew " Poletical and Socio- Economic History of Asossa Warada,1941-1991 በሚል ርዕስ እ.ኤ.አ በ2011 ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የተሠራ ጥናት ነው፡፡ ጥናቱ ከአፄ ኃይለስላሴ ዘመነ መንግስት እስከ ደርግ ድረስ ያለውን የአሶሳ ወረዳንና የበርታ ብሔረሰብን ታሪክ የሚተነትን ነው፡፡ በዚህም የወረዳውን ስትራቴጂያው አቀማመጥና ተፈጥሮአዊ ሀብቶች የውጪ ሃይሎችን እንዴት እንደሳበ የውስጥ ሃይሎችም የፖለቲካ ስልጣንና ሀብትን ለመያዝ ያደርጉ ነበሩትን ግጭቶች፣ በሁለቱ መንግስታት ጊዜ ብሔረሰቡ ጥንት የነበረውን ራስን በራስ የማስተዳደር መብት እንዴት እየተነጠቀ እንደመጣና ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ ወደ አካባቢው ከሰፈሩ የማህበረሰብ ክፍሎች ጋር ያለውን ማህበራዊ ግንኙነትና ሠፈራውን ተከትለው የመጡትን ማህበረ ባህላዊ ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ ለውጦች የሚመለከት ነው፡፡ ጥናቱ የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነውን ብሔረሰብ ታሪክ የሚመለከት ስለሆነ የጋራ ጉዳዮች ይኖሩታል፡፡ አንዳንድ ጥሬ መረጃዎችም ተመሳሳይ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ይሁንና የብሔረሰቡ ባህል ከአካባቢው ልማት ጋር ያለውን መስተጋብር የማይመለከት በመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር አይመሳሰልም፡፡

የዚህ ጥናት ትኩረት በሆነው ክልል ላይ የተሠራ ሌላው ጥናት የ Mulualem Bassie Desta ከ Regional & Local Development Studies ክፍለ ትምህርት "Institutional and Administrative Capacity for Development: The case of Benshangul Gumuz National Reginald state: Efforts, Problems and Prospects" በሚል ርዕስ በ2001 የቀረበው ጥናት ነው፡፡ Mulualem በዚህ ጥናት የክልሉ መንግሥት ተቋማዊና አስተዳደራዊ አቅም ለክልሉ ልማት ያለውን አስተዋፅኦ ለመዳሰስ ሞክሯል፡፡ ትኩረት ያደረገውም የክልሉ የሰው ኃይል በትምህርት፣ በባለሙያ ብዛትና አቅም እጥረት ምክንያት የልማት ፖሊሲዎችን ከማስፈፀም አንፃር የገጠመውን ችግር ማጥናት ነው፡፡ የክልሉን ልማት ለማፋጠን የመንግሥት ሠራተኛውን በተገቢው መንገድ መያዝ፣ ማበረታታትና ፍልሰቱንም ለመቀነስ ማትጊያዎችን ማስቀመጥ፤ ተከታታይ ሥልጠናዎችን በመስጠት ማብቃት ተገቢ እንደሆነና ይህ ካልሆነ ግን በክልሉ ልማት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ እንደሚያስከትል ለማስገንዘብ ሞክሯል፡፡ ይሄ ጥናት የሚመለከተው የማህበረሰቡ ባህል በክልሉ ልማት ላይ የሚያሳድረውን በጎም ሆነ መጥፎ ተፅዕኖ በመሆኑ ከሙሉዓለም ጥናት ፈፅሞ የተለየ ያደርገዋል፡፡

Bayissa Iffa "Adaptation Culture and Changing Environment: The Case of the Gumuz of the Diddessa Valley (Kamashi Zone)" በሚል ርዕስ ለሶሻል አንትሮፖሎጂ ክፍለ ትምህርት በ2001 ጥናት አድርጓል፡፡ ጥናቱ የጉሙዝ ብሔረሰብ ወደ ዴዴሳ ሸለቆ በመፍለስ ከአካባቢው ጋር እንዴት ተስማምቶ እንደኖረና እንደሚጠብቀው የተመለከተ ነው፡፡ Bayissa በጥናቱ "Cultural Adaptation: Change and Continuty of Culture" በሚል ንዑስ ርዕስ ስር ባህል አካባቢን በእጅጉ በመለወጥና ለኑሮ ተስማሚ ለማድረግ ትልቅ ሚና እንዳለውና ሰዎች ከአንድ አካባቢ ወደሌላው ቢፈልሱ፣ የተፈጥሮ አካባቢ ለውጥ ቢከሰት፣ ቴክኖሎጂ ቢያድግ፣ የህዝብ ቁጥር ቢጨምር፣ ወዘተ ባህሉ ከመጣው አዲስ ክስተት ጋር እራሱን የሚያላምድበት መልክ (Adaptive Dimension of Culture) እንዳለው ለማስረዳት ይሞክራል፡፡ ይሁንና የ Bayissa ጥናት የማህበረሰቡ ባህል ከልማት ጋር የሚያያዝበትን መንገድ ለማሳየት ያልተነሳ በመሆኑና የሚያተኩረውም የጉሙዝ

ማህበረሰብ በዱዱሳ ሽለቆ ራሱን እንዴት አላምዶ እንደኖረ ማሳየት ላይ በመሆኑ ከእኔ ጥናት ጋር አይመሳሰልም፡፡

ከዚሁ ትምህርት ክፍል የምናገኘው ሌላው ጥናት Tariku Feyissa "The Berta Economy: An Ethnographic Study of Social Organization of Production in the Western Ethiopia Borderlands " በሚል ርዕስ ያደረገው ጥናት ነው፡፡ ጥናቱ የሚያተኩረው የበርታ ብሔረሰብን ማንነት በመግለጽ (ethnographic description) ላይ ሆኖ በተለይ ከእርሻ ሥራ ጋር የተያያዘውን የማህበረሰቡን ልማድና የኢኮኖሚ ሁኔታ ተመልክቷል፡፡ አጥኚው የበርታ ማህበረሰብ ከሚገኝባቸው ስምንት ወረዳዎች አንዱ በሆነው መንጌ ወረዳ አንድ መንደር ላይ እና የማህበረሰቡ አንዱ መተዳዳሪያ በሆነው አዚዙሮ/አፈራርቆ በማረስ ላይ ብቻ በማተኮር የማህበረሰቡን ማንነትና የኢኮኖሚ ሁኔታ ዳስሷል፡፡ በመሆኑም አንደኛ ለልማት አንድ ገፅታ በሆነው የእርሻ ሥራና አደረጃጀት ላይ ብቻ ስለሚያተኩር እንዲሁም ለማሳያነት የተወሰደው ናሙና ከአንድ ወረዳ አንድ መንደር ብቻ በመሆኑ፣ የእኔ ጥናት የሚያተኩረው በሁሉም የማህበረሰቡ የልማት እንቅስቃሴዎች ላይና የሚሸፍነውም አራት የማህበረሰቡ መኖሪያ የሆኑ ወረዳዎችን በመሆኑ፣ እንዲሁም ሁሉንም የማህበረሰቡን ባህላዊ ዘውጎች ከልማት ጉዳዮች ጋር በማያያዝ የሚመለከት በመሆኑ ከታሪኩ ጥናት በእጅጉ ይለያል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በዚሁ ትምህርት ክፍል "Natural Resource Competition and Inter-Ethnic Relations: The Case of Indigenous Berta and the Settlers in Bambasi Woreda of Benshangul Gumuz Regional State, Western Ethiopia " በሚል ርዕስ በ2010 የተደረገውን የBiniyam Nishanን ጥናት እናገኛለን፡፡ የጥናቱ ትኩረት በክልሉ ነባር ብሔረሰብ አንዱ በሆነው በርታና በአካባቢው በ1977 ዓ.ም በሰፈሩት "ደገኞች" መካከል ያለውን ግንኙነት በማጥናት ላይ ሆኖ ዋነኛ ትኩረቱ ሁለቱ ማህበረሰቦች ባላቸው የእርስ በርስ ግንኙነቶች በተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ላይ በሚያደርጉት ሽሚያ ሳቢያ የሚነሱ ግጭቶችን መሠረት በመመርመር ላይ ነው፡፡ ጥናቱ የእኔ ጥናት ትኩረት የሆነውን የበርታን ብሔረሰብና በጥናቴ የሚሸፈነውን አንዱን ወረዳ (ባምባሲ ወረዳ) ላይ የተሰራ ቢሆንም የእኔ ጥናት

በበርታ ባህልና ከልማት ጋር ያለውን ቁርኝት የሚመለከት በመሆኑ በይዘት ከእኔ ጥናት ጋር አይመሳሰልም።

ከላይ ከቀረበው የተዛማጅ ሥራዎች ዳሰሳ እንደተመለከተው የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነውን ባህልና ልማትን አስመልክቶ በተለይም በክልሉና በተመረጠው ብሔረሰብ ላይ የተደረገ ጥናት የለም። ስለዚህም ይህ ጥናት በዘርፉ ያለውን ክፍተት የሚሞላ የመጀመሪያ ሥራ ነው ለማለት ያስችላል።

## 3.2. ንድፈ ሃሳባዊ መሠረቶች

በባህል ጥናት የንድፈ ሃሳብ /የቲዎሪ/ ሞዴልን በመጠቀም ዙሪያ የተለያዩ ምሁራን የተለያየ አመለካከት አላቸው። አንዳንዶቹ ሌሎች የጥናት መስኮች የሚገዙባቸውን የንድፈ ሃሳብ ወይም የቲዎሪ መሰረቶችን መነሻ አድርጎ ባህልን ማጥናትና በዚያ ማዕቀፍ ውስጥ መገዛት እንደሚገባ ይናገራሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ባህል ባለቤት እንደሆነው ማህበረሰብ፣ እንደሚገኝበት አካባቢና ሁኔታ የተለያየ መልክ ስላለው የባህል ጥናት የግድ በተለመዱት የቲዎሪ ሞዴሎች መገዛት የለበትም፤ መጠናት ያለበት እንደተገኘበት ማህበረሰብ ሁኔታ የራሱ በሆነ የንድፈ ሃሳብ /ቲዎሪ ሞዴል ነው የሚሉም አሉ።

Ben-Amos (1975) "ፎክሎር በአፍሪካ ማህበረሰብ" (Folklore in African Society) በሚል ርዕስ በፃፉት መጣጥፍ (Article) መነሻ ላይ ያነሷቸው ፎክሎር በአፍሪካ ምንድነው? አፍሪካዊው በባህሉ ውስጥ ስላሉት ትረካዎችና ግጥሞች ምን ያውቃል? በምናቡ እንዴት ይስላቸዋል? ከቅርፃቸውና ከጭብጣቸውስ ምን ይረዳል? በማህበረሰቡ ውስጥስ እንዴት በአግባቡ ይጠቀምባቸዋል? ለእርሱስ ምን ማለት ናቸው? የሚሉትን ጥያቄዎች በቅድሚያ በማንሳት መልሶቹ ከአንዱ የአፍሪካ ማህበረሰብ ወደ ሌላው ስንሄድ ሊለያዩ እንደሚችሉ የተለያዩ ሀገራት ምሳሌ በመስጠት የባህል/ፎክሎር ጥናት በአንድ ወጥ ቀመር (formula) ሊካሄድ እንደማይችል በዝርዝር ያስረዳሉ። ይህም የአፍሪካ ፎክሎር የተለየ ባህሪ፣

መልክና ይዘት ያለው መሆኑን በመገንዘብ የሚያጠናውም እንደራሱ ባህሪ እንጂ በተለመደው አውሮፓዊ መንገድ መሆን እንደሌለበት ለመረዳት ያስችላል፡፡

የፎክሎር ቅርፆች እንደ ማህበረሰቡ አገላለጽና እንደሚሰጣቸው ቦታ የራሳቸው የሆነ ባህላዊና ትዕምርታዊ ፍቺ አላቸው፡፡ ነገረ ይዘቶች (Texts) በቁማቸው ከሚሰጡት ፍቺ ውጭ በዘውጎች (Genres) ተከፋፍለው በማህበረሰቡ ውስጥ እንደሚከወኑበት ተግባቦታዊ ሁነቶች ይፈታሉ፡፡ ስለዚህ የአፍሪካን ፎክሎር በአውሮፓውያን የአከፋፈል መንገድ ለመከፍል መሞከር አጥኚውን ግራ ማጋባት እንደሆነ Ben-Amos አጠናክረው ይገልፃሉ፡፡

በመሆኑም በአፍሪካ የእያንዳንዱ ባህል ተግባቦት ሥርዓት የሚመሠረተው የፎክሎር ቅርፆችን የመገንዘብ (cognitive)፣ የመግለፅና (expressive) የማህበራዊ ሁኔታዎችን (social features) በመለየትና በመተንተን ላይ እንደሆነ በማሳየት ፎክሎሩ ሲጠና እነዚህን ጉዳዮች ከግምት ውስጥ ማስገባት እንዳለበትና ይህ ሲሆን ደግሞ የአፍሪካ ፎክሎር[10] መጠናት ያለበት በራሱ አፍሪካን በሚገልፅበት መልክ እንጂ ከሌሎች ቲዎሪዎች ጋር አስገድዶ ለማዛመድና ለማስገዛት በመሞከር እንዳልሆነ ያስገነዝባሉ (Ben-Amos,1975)፡፡

Alan Barnard በበኩላቸው የዘመናዊ አንትሮፖሎጂ ጥናት አባት የሚባለው Franz Boas ን cultural relativissm ቲዎሪን ለባህል ጥናት ያለውን ጠቃሚነት ሲያብራሩ Boas እንደሚለው እያንዳንዱ ባህል ከሌላው የሚለይበት የራሱ የሆነ ባህሪ ስላለው መታየት ያለበት ከዚያው ከራሱ ባህሪ አንፃር እንጂ ከሌላ ባህል ጋር እየተነፃፀረ መሆን የለበትም፡፡ ባህል በራሱ ማህበረሰቡ ዓለምን እንዴት እንደሚገነዘበው የሚወስን ነው፡፡ ስለዚህ የተለያዩ ባህሎች እንደየራሳቸው ውስጣዊ ሁኔታዎች ይታያሉ እንጂ ሁሉን በአንድ የሚሰፍርና ደረጃ የሚሰጥ ዓለማቀፋዊ መለኪያ የለም፡፡ አንዱ ባህል ውስጥ ያለ ጠንካራ ነገር ሌላው ዘንድ ቢጎድል ያኛውም የራሱ ጠንካራ ነገር አለውና እርስ በርስ አወዳድሮ

[10] Ben-Amos ለፎክሎር ጥናት ያነሱት ጉዳይ ለባህል ጥናትም የሚያገለግል በመሆኑ ነው እዚህ የተጠቀሰው፡፡

አንዱን የሠለጠነ ሌላውን ኋላ ቀር ማለት አይቻልም:: ሁሉም አንፃራዊ በሆነ መልኩ መታየት አለበት የሚል አስተሳሰብ እንደሚያራምድ ገልፀው ይህም ለባህልም ሆነ ለአንትሮፖሎጂ ጥናት ጠቃሚ አካሄድ ነው ይላሉ (Barnard,2004;100-101)::

በሌላ በኩል ያሉት ደግሞ (Sims & Stephens) ባህልን ለመተንተን የተለያዩ ቲዎሪዎችን መጠቀም እንደሚቻል ጠቅሰው አንዱ መንገድ ፎክሎሩ ለማህበረሰቡ ከሚሰጠው ጥቅም አንፃር እየተመለከቱ መተንተን ሲሆን ይህ የትንታኔ ስልት መሰረት የሚያደርገው ተግባራዊ (Functionalist) ቲዎሪ እንደሆነና በዚህም የBascomን አራት የፎክሎር ተግባሮች ወይም ጠቀሜታዎች ማለትም የማስተማር፣የማጠናከርና የመትከል፣የማምለጭና የመግታት ተግባሮች መሠረት በማድረግ ባህሉ ለማህበረሰቡ ከሚሰጠው ጠቀሜታዎች አኳያ ሊጠና እንደሚችል በመጥቀስ ያብራራሉ (Sims & Stephens,2005) ::

ከዚሁ ጋር በማያያዝም በአሁኑ ሰዓት የባህል ጥናት ትኩረት ሰዎች ባህላዊ መገለጫቸው በሆነው በአንድ የተለየ የክዋኔ አውድ ውስጥ እርስ በእርስ እንዴት እንደሚግባቡ ተንትኖ ማሳየት ነው:: በባህል/ፎክሎር ጥናት የትንታኔ አስኳል የሆኑት ነገሮችም ነገረ ይዘቱና የክዋኔው አውድ፣ በዚያም የሚንፀባረቁ አስተሳሰቦችና የመስተጋብሮች ውስብስብነት፣ የክዋኔው ተያያዥነት፣ ታዳሚዎቹ፣ ተመራማሪዎቹና ማህበረሰቡ ናቸው:: ስለዚህ አጥኚው ከዚህ አንፃር ትንታኔውን ለማድረግ ከተለያዩ ቲዎሪዎች አኳያ ተመልክቶ መረጃውን መሰብሰብ አለበት ይላሉ (Sims & Stephens, 2005)::

በመሆኑም ይህ ጥናት የBen-Amosንና የFranz Boasን ሀሳብ ከግምት ውስጥ አስገብቶ የሚጠናው ባህል የራሱ መልክ ካለው በዚያው የንድፈ ሀሳብ ማዕቀፍ እንደሚገዛ በታሳቢነት በመውሰድ፤ የእነ Sims & Stephens ንም ሀሳብ በመቀበል የሚገዛባቸውን የቲዎሪ ማዕቀፎች መሠረት አድርጎ የሚሠራ ይሆናል::

### 3.2.1. ተግባራዊ ቲዎሪ / Functionalist Theory /

ይህ ቲዎሪ አንድ ባህል፣ ባህል ሆኖ ለመዝለቅ ለማህበረሰቡ የሚሰጠው አንዳች አገልግሎት መኖር እንዳለበት የሚያመለክት ሲሆን ባህል ማህበረሰቡን ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ የሚገለገልበትና ማህበረሰቡንም ለማስተማር፣ ንቁና ጥበበኛ ለማድረግ፣ ውስጣዊ ስሜቱን ለመግለጽና ከራሱ ከማህበረሰቡ ህግና ደንብ ለማምለጥ እንዲሁም ባህሉን ራሱን ለመትከል ያገለግላል። ስለሆነም ባህል ለማህበረሰቡ ከሚሰጠው ጥቅም አኳያ ታይቶ መዳኘት አለበት (Sims & Stephens, 2005, 174; Bascom 1954, 334; Okpewho, 1992, 10)።

በዚህ ዓይነት ባህል ለማህበረሰቡ ከሚሠጣቸው ጠቀሜታዎች አኳያ እየተመለከቱ ማጥናት ማህበረሰቡ ስለራሱ፣ ስለአካባቢውና ስለዓለም ያለውን አመለካከት ለማወቅ ዓይነተኛ መንገድ ነው (Sims & Stephens, 2005, 174-176፣ ፈቃደ 1991፣18-20)። ማህበረሰቡ ባህሉ ለሚደነግጋቸው ሥርዓቶችና ደንቦች ይገዛል፤ የተገዛውን ያህል ደግሞ ያፈነግጣል። ማፈንገጡን የሚገልፅበት መንገድ ደግሞ በባህሉ ዘውጎች በራሳቸው ነው። በሌላ መልኩ ደግሞ ባህላዊ ደንቦቹ እንዳይጣሱ ባህሉ ራሱ ያስጠነቅቃል፤ ይከለክላል፣ ቅጣትም ይጥላል።

በባህሉ ውስጥ ለሚስተናገዱ ሁነቶችና ነገሮች ሁሉ በዚያው በባህሉ ምንነታቸውን ይገለጣል። ከዚህ አልፎ ተርፎም ባህሉን ራሱን የመማሪያና የማስተማሪያም አድርጎ ይገለገልበታል። እነዚህ ባህል ለማህበረሰቡ የሚያከናውናቸው ተግባራት ደግሞ የባህልን ጠቀሜታ እያጎሉ የማህበረሰቡ መለያዎች ሆነው ይዘልቃሉ።

ከዚህ በተጨማሪ የመስኩ ምሁራን እንደሚያስረዱት ባህሉ በራሱ የማስተማሪያና የመግባቢያ መሣሪያ በመሆኑ (Green 1997; 386) አዲስ የመጣውን ዘመናዊ ቴክኖሎጂ እንደ የቤተሰብ ምጣኔ ዘዴ ያለውን ለማህበረሰቡ ለማስተማርና እንዲቀበለው ለማድረግ በዚያው በባህሉ አማካይነት ሥራ ላይ ማዋል አስፈላጊ በመሆኑ ይህንን ቲዎሪ ተጠቅሞ ከዚህ ጥናት ዓላማ ጋር በማያያዝ መፈተሽ ተገቢነት አለው።

እንዲሁም ባህሉ በራሱ ስለመጣው የልማት አቅጣጫ ያለው ቀዳሚ ዕውቀት /indigenous knowledge/ ካለና የመጣውን ዘመናዊ ቴክኖሎጂ የማህበረሰቡ ባህል የሚቀበለው ወይም የሚገፋው መሆኑን ለማየት ይህ ቲዎሪ ለጥናቱ ተመርጧል፡፡

ሆኖም የ Bascom ተግባራዊ ቲዎሪ የራሱ የሆነ እጥረት እንዳለበት Sims Mullenን ጠቅሰው "…Bascom's system ignores the way folklore questions, critiques, protests, and sometimes undermines stability" ይላሉ (Mullen 2003 in Sims& Stephens,2005,176)፡፡ ሌሎች ደግሞ ቲዎሪው ባህልን ከሚሰጠው ጠቀሜታ አኳያ ብቻ የሚመለከት በመሆኑ የተሟላ እንዳልሆነ ያነሳሉ፡፡ "Functionalism is a theory which tries to explain social and cultural institutions and relation in terms of the functions they perform within the system; heavily criticized because it fails to take account of historical factors such as change, conflict and disintegration" (Gardener and David,1996).

ከዚህ እንደምንረዳው ባህሉ ለማህበረሰቡ የሚሰጠውን አገልግሎት ብቻ በማየት ጥናቱን የተሟላ ማድረግ እንደማይቻል ነው፡፡ ስለዚህ ከተግባራዊ ቲዎሪ በተጨማሪ የባህል ዋነኛ መገለጫ የሆነውን የክዋኔ ቲዎሪ በአጋዥነት መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

### 3.2.2. የክዋኔ ቲዎሪ / Performance Theory /

በአንድ ባህላዊ ጥናት የማህበረሰቡን ቃላዊ ጥበባት (Verbal Arts) ብቻ ሰብስቦ የተወሰኑ ቲዎሪዎችን በመጠቀም እየተነተኑ ስለማህበረሰቡ ባህል የተወሰነ ማጠቃለያ ላይ መድረስ ይቻል ይሆናል፡፡ ሆኖም እነዚህን የባህል ዘውጎች ማህበረሰቡ ሲተርታቸው፣ ሲዘፍናቸው፣ ሲያንጎራጉራቸው፣ ሲያከብራቸው በአጠቃላይ የራሱን ሥርዓት ተከትሎ ሲከውናቸው ስናይ የሚሠጡት ፍቺ የተለየና ሚዛን የሚደፋ ይሆናል፡፡ ለባህል ጥናት ክዋኔ ብቻ ሳይሆን የክዋኔው አውድ፣ (*context)* ከዋኙና (performer) ተሳታፊዎቹ (audiences) ትልቅ ድርሻ አላቸው (Green, 1997; Sims & Stephens,2005)፡፡ ክዋኔው ብቻም

ሳይሆን ማህበረሰቡ ስለክዋኔው ምንነትና ፋይዳ የሚሰጠውን ፍቺ ምን እንደሆነ መገንዘብም አስፈላጊ እንደሆነ አጠንክረው ያስረዳሉ፡፡

> In studying a certain folk text we cannot simply lift it from the context and begin to understand its importance to a particular group accurately. It must be seen within a larger context, as part of a cultural system. In addition, it is necessary to understand that the folklorist's interpretation of its significance should not be the final word. As the text is an element of a group's folklore, the members of the group are the experts on what those items or practices mean, so the folklorist can't just walk away from the culture with an interpretation in good conscience or good scholarship and consider her work complete. Folklorists consult extensively with group members throughout the process of fieldwork and analysis in order to understand as clearly as possible the significance of texts within specific contexts (Sims, & Stephens 2005.138).

አንድን የፎክሎር ነገረ ይዘት (text) ስናጠና ከአውዱ ነጥለን ለቡድኑ የሚሠጠውን ጥቅም በቀላሉ መናገር አይቻልም፡፡ ነገረ ይዘቱን (text) ከሰፊ የክዋኔ አውድ ላይ ሲከወን መመልከትና መገንዘብን የግድ ይላል፡፡ አንድ የፎክሎር ነገረ ይዘት (text) ከሰፊው የፎክሎር ባህር ውስጥ አንድ ቅንጣት እንደመሆኑ ያ ቅንጣት በፎክሎሩ ቁሶች ውስጥ ምን ማለት እንደሆነና ለምን እንደሚጠቅም የሚያውቁትና መግለፅ የሚችሉት የፎክሎር ቡድኑ አባላት ናቸው፡፡ በመሆኑም ፎክሎረኛው ነገረ ይዘቶቹን (text) ሌጣቸውን ይዞ ለትንታኔ ከመነሳቱ በፊት በክዋኔ አውዳቸው ላይ በጥንቃቄ መመልከትና የቡድን አባላቱን

> ስለነገረ ይዘቱ (text) ፍቺና ጠቀሜታ መጠየቅና ማወያየትና ለመገንዘብ መጣር አለበት (Sims & Stephens, 2005; 138፣ ትርጉም የኔ)።

የክዋኔ አውዶች ማህበረሰቡ በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎቹ የሚያከናውነውን ድርጊትና ስለሚከውነው ነገር ያለውን አመለካከት የመግለጽ ጉልበት ስላላቸው በየደረጃው የሚደረገውን ክዋኔ ከአውዱ፣ ከከዋኞቹ፣ ከተሳታፊዎቹና ከታዳሚዎቹ አንፃር ጭምር በደንብ መረዳት ያስፈልጋል። በመሆኑም ጥናቱን የተሟላ ለማድረግ የክዋኔ ቲዎሪ በዚህ ጥናት በተጨማሪነት ሥራ ላይ ውሏል።

በክዋኔ አውዶች ላይ በማተኮርና ንቁ ተሳታፊ በመሆን የሚሰበሰቡ መረጃዎች በኋላ ለሚደረገው ትንታኔ ያላቸው ጉልበት ከፍተኛ ነው። Ben- Amos "Context in Context" በሚለው መጣጥፋቸው የነገረ ይዘትን ፍቺ ከሚከወንበት አውድ ጋር አያይዞ ማየት ለተዋጣለት ትንታኔ እንዴት እንደሚጠቅም እንዲህ ይገልፁታል።

> …The meaning of a text is its meaning in context. The transference of any folklore to a different literary, historical, or cultural context grants it a new meaning. Because of their transient nature, folklore texts do not have single meanings, and any repeated, historically conscious use connotes previous contexts as an integral part of their set of meanings. A valid interpretation is an interpretation of a text in context (Ben-Amos, 1993, 209).

> … የነገረ ይዘት ፍቺ ማለት አውዳዊ ፍቺው ማለት ነው። ማንኛውም ፎክሎር ወደ ተለያዩ ጥበባዊ፣ ታሪካዊ፣ ወይም

> ባህላዊ አውዶች ሲተረጎም አዳዲስ ፍቺዎች ይኖሩታል፡፡ በፎክሎሩ ቋሚ ባልሆነ ባህሪ የተነሳም የፎክሎር ነገረ ይዘት (text) አንድ ነጠላ ፍቺ አይኖረውም፡፡ የተዋጣለት ትንታኔ የሚባለውም ነገረ ይዘቱ ከአውዱ ጋር ተሰናስሎ የተተነተነ እንደሆን ነው (Ben- Amos, 1993, 209፣ ትርጉም የኔ)፡፡

ከዚህ ስንነሳ የነገረ ይዘት ፍቺ በሚከወንበት አውድ ውስጥ የሚገለጽ ሆኖ የተዋጣለት ትንተና የሚባለውም ነገረ ይዘቱን በክዋኔ አውድ ውስጥ እየተመለከቱ የሚደረግ ትንተና ነው፡፡ በባህል ጥናት የበሰለ ትንታኔ ለማድረግ ከላይ እንደተጠቀሰው መረጃዎቹ በዳጎሰ መልኩ መሰብሰብ ይኖርባቸዋል፡፡ ይሄ ደግሞ የባህሉን ነገረ ይዘት በጥልቀት መመርመርን ይጠይቃል፡፡

የባህል መረጃ ነገረ ይዘት የምንለው የተለያዩ የባህል ዘውጎችን ይዘት በሙሉ የሚያጠቃልል ነው፡፡ ይሄ የባህል ዘሩን ክዋኔ፣ አውዳዊ ቁሶች፣ ከበራዎችን፣ መረጃዎችን ወዘተ ሁሉ ይጨምራል፡፡ (Sims & Stephens 2005) Ἓvery thing can be regarded as a text፡ plays and platters, billboards and blackboards, guns and gowns, statistics and stats are all, in diferent ways, texts: namely, objects and data that are always open to varying readings and interpretations" (Cavallaro,2001,59). "ማንኛውም ነገር እንደ ነገረ ይዘት (text) ሊቆጠር ይችላል፡፡ ጨዋታዎችና ቅደም ተከተሎች፣ ቢልቦርዶችና ጥቁር ሰሌዳዎች፣ የተለያዩ መሣሪያዎችና አሠራሮች፣ አልባሳትና አለባበሶች፣ ቀመሮችና ደረጃዎች ወዘተ ነገረ ይዘቶች ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ነገረ ይዘቶች ሁልጊዜ የፎክሎር ንባቦችንና ትንታኔዎችን የተለያዩ የሚያደርጉ ቁሶችና መረጃዎች ናቸው ማለት ይቻላል" (ትርጉም የኔ) ፡፡

የክዋኔ አውድ የሚባለው ደግሞ ባህሉ የሚከወንበት መቼት፣ የባህሉ ባለቤቶች የሚጋሩት ማህበራዊ ሁኔታ፣ በታዳሚው፣ በአባላቱና በከዋኞቹ መካከል ያለ ግንኙነትና በአጠቃላይ

በነገረ ይዘቱ እና በክዋኔው ዙሪያ የሚገኙ ማናቸውም ነገሮች ማለት ነው:: የክዋኔ አውድ አንድ ባህላዊ ጉዳይ የሚከወንበትና የሚቀርብበት በመሆኑ ልዩ ልዩ መልኮች እንዳሉት የመስኩ ምሁራን ያመለክታሉ::

(Schoemaker, 1990) Bauman ን ጠቅሰው ሁለት ዓይነት የክዋኔ አውዶች እንዳሉ ያስረዳሉ:: አንደኛው ባህላዊ አውድ (Cultural Context) የሚባለው ሲሆን የሚከወነው ባህል/ፎክሎር ባህላዊ ፍቺ፣ የፍቺው ዘዴ፣ ትዕምርታዊ ግንኙነቱ፣ የሚወክለው ነገርና የሚያስተላልፈውን መልዕክት እንዲሁም በወካዩና በተወካዩ መካከል ያለውን መስተጋብር የሚመለከት ነው::

በዚህ ውስጥ የፍቺ አውድ Context of Meaning (የባህሉን ይዘት፣ፍቺና ጭብጥ ለማወቅ የሚያስፈልግ የሰዎቹ መረጃና ዕውቀት)፣ ተቋማዊ አውድና (Institutional Context) ባህላዊ ተቋማቱ/ቤተሰባዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ትምህርታዊና ፖለቲካዊ ቁመናና በማህበረሰቡ ጠባይ፣ አስተሳሰብ፣ ስለዓለም ባለ አመለካከት፣ የዕምነት ሥርዓት፣ ባህላዊ አገላለፆች የሚያሳድሩትን ተጽዕኖ የሚመለከት ነው:: የመግባቢያ ሥርዓት አውድ /Communicative System Context ደግሞ የባህላዊ ቡድኑንና የባህል/ፎክሎር ዘውጉን ክፍፍል የሚመለከት ሆኖ አንድ የባህል/ፎክሎር ዘውግ በዚያው ባህል ከሌላ ዘውግ ጋር ያለውን ዝምድና የምንመለከትበት ነው::

ሁለተኛው ማህበራዊ አውድ (Social Context) ደግሞ ማህበራዊ መሠረትን፣ ግለሰባዊ አውድና ሁኔታዊ አውድን የሚያጠቃልል ነው:: ባህላዊ አውድ (Cultural Context) እና ማህበራዊ አውድ (Social Context) አጠቃለን ስናያቸው ከላይ በሁለቱም ውስጥ ያሉትን መሰረታዊ አውዶች ከግምት ውስጥ በማስገባት ተፈጥሮዓዊ አውዶቹ ላይ በመገኘት ከተለያየ አቅጣጫ ትኩረት ሰጥቶ በመመልከት፣ ጥያቄ ማዘጋጀት ከዋኞቹን፣ ታዳሚዎቹንና የባህል ባለሙያዎችን በመጠየቅና የተገኘውን መረጃ ለማረጋገጥና ክፍተቶችን ለመሙላት በቡድን በማወያየት መረጃው ተሰብስቧል:: ይህም ስለተሰበሰበው ባህል የተሟላ ስዕል ማግኘት ያስችላል (Schoemaker,1990;8)::

Ben-Amos በበኩላቸው የክዋኔ አውድን የሁኔታዎች አውድ (Context of Situation) እና የባህል አውድ (Context of Culture) በማለት በሁለት ይከፍሉታል፡፡ የመጀመሪያው ለባህል ጠባብና እጅግ ቀጥተኛ የሆነው አውድ ሲሆን ሁለተኛው "The Context of Culture comprises the reference to, and the representation of, the shared knowledge of speakers, their conventions of conduct, belief systems, language metaphors and speech genres, their historical awareness, and ethical and judicial principles" (Ben-Amos,1993,215-216). "የባህል አውድ (Context of Culture) የከዋኞቹን የጋራ ዕውቀቶች፣ የባህሪ ስምምነቶች፣ የዕምነት ሥርዓቶች፣ የቋንቋ ዘይቤዎች፣ የንግግር ዘውጎች፣ ታሪካዊ ዕውቀቶች፣ ሥነምግባራዊና ህጋዊ መመሪያዎችን ዋቢ የሚያደርግ ነው" (ትርጉም የእኔ)፡፡ በማለት ሰፊና ብዙ ጉዳዮችን እንደሚያካትት ይገልፃሉ፡፡

በባህል መረጃ ስብሰባ ሦስተኛው ዋነኛ ጉዳይ ነገረ ሁኔታ (Texture) ነው፡፡ ነገረ ሁኔታ (Texture) የፎክሎር ዘሩ ሥነ ጽሑፋዊ፣ ሥነ ልሳናዊ፣ ተፈጥሮአዊ ባህሪና የከዋኙ የአቀራረብ ሁኔታ፣ የአከዋወን ቅጥ (የሰውነት እንቅስቃሴው፣ የፊቱ መልክ፤ የሚይዛቸው ቁሳቁስና እንቅስቃሴያቸው)፣ ለነገረ ይዘቱ (Text) ታዳሚው የሚሰጠው ምላሽ፣ በቃላዊ ይዘተ ነገሮች (Text) የዜማ አወራረዱን፣ የድምፁን ቅላጼና ምት፣ የዘይቤ አጠቃቀሙን፣ የቃላቱን የእርስ በርስ ግንኙነትና የሚሰጡትን ፍቺ ሁሉ የሚመለከት ሆኖ ስለአንድ የባህል/ፎክሎር ዘር ስለከዋኙ፣ ስለቡድኑና ስለ ዘውጉ ስለራሱ ሳይቀር ብዙ ሊነግረን የሚችል ነው[11]፡፡

የባህል መገለጫው ክዋኔው በመሆኑ ባህልና ክዋኔ እንደ ነፍስና ሥጋ መነጣጠል የማይችሉ ድሮች ናቸው፡፡ ባህሉ ነፍስ የሚዘራው በሚተገበርበት፣ በሚከበርበት፣ በሚመለክበት፣ በሚዘፈንበት፣ በሚተረትበት፣ በአጠቃላይ በሚከወንበት ወቅት ነው፡፡ ክዋኔው ደግሞ እንደ ባህሉ መልክ የራሱ የሆነ አውድ ይፈልጋል፡፡ በአንዱ የክዋኔ አውድ

[11] Sims & Stephens, 2005, 139; Schoemaker, 1990,7; Green,1997, 791; Lewandowski, 2001, 7

ሌላው የባህል ዘውግ አይከወንም። በለቅሶ ጊዜ የሠርግ ዘፈን እንደማይዘፈነው ማለት ነው። በመሆኑም ስለባህሉ ዘውግ የተሟላ መረጃ ለመሰብሰብና የጠለቀና የተዋጣለት ትንታኔ ለማድረግ ህልው በሚሆንበት የክዋኔ አውድ ላይ ተገኝቶ በጥንቃቄ፣ በንቃትና በጥልቀት መረጃውን ከሁነኛው ምንጭ አሳምሮ መቅዳትን በመጠየቁ መረጃዎች ከክዋኔው አውድ ላይ በሚገባ ተሰብስበው ተተንትነዋል።

በዚህ ጥናት በዋናነት ከሚነሱ ጉዳዮች መካከል አንዱና ዋነኛው ባህሉ ከልማቱ ጋር ያለውን ቁርኝት መሳየት በመሆኑም ይህን ጉዳይ ለመፈተሽ የሚያስችሉ ናቸው ተብሎ የታመነባቸው የዘመናዊነት ቲዎሪ (Modernaization Theory) እና የልማታዊ ቲዎሪ (Developmental Theory) በተጨማሪ ከጥቅም ላይ ውለዋል።

### 3.2.3. የዘመናዊነት ቲዎሪ (Modernaization Theory) እና የልማት ቲዎሪ (Developmental Theory)

ባህልና ልማት ያላቸውን ቁርኝት አስመልክቶ ሁለት ዓይነት አስተሳሰቦች አሉ። አንዱ የተዋጣለት ልማት ለማምጣት ከተፈለገ ባህላዊ አመለካከቶችን ሰብሮ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም መፍትሔ ነው የሚለው የዘመናዊነት አስተሳሰብ ሲሆን፤ ከዚህ አስተሳሰብ በተቃራኒው ባህል ለልማት ያለውን አዎንታዊ አስተዋፅዖ የሚያሳዩና የዘመናዊነት አስተሳሰብ የምዕራባዉያኑ የዘረኝነት አመለካከት እንደሆነ የሚከራከሩ አስተሳሰሰቦች ናቸው። እነዚህን አስተሳሰቦች ቀደም ሲል ለማንሳት የተሞከረ በመሆኑ[12] እዚህ የምናነሳው የዘመናዊነት አስተሳሰብን ነው::::

[12] በጥናቱ ዳራ ላይ ተነስተዋል።

የዘመናዊነት ቲዎሪ አንድን ግለሰብም ሆነ ማህበረሰብ ከልማድ እስረኝነት፣ በማህበራዊ ዕኩልነት፣ በአዳዲስ ፈጠራዎችና ለውጦች በላቀ ልዩነት ማላቀቅ ነው፡፡ ይህም ከካፒታሊዝም፣ ከኢንዱስትሪያላይዜሽንና ከከተሜነት ጋር የሚያያዝ አስተሳሰብ ነው፡፡

የዘመናዊነት ቲዎሪዎች በጣም የተስፋፉ የልማት ቲዎሪዎች እንደሆኑና የምዕራባውያን ትኩረት የሆነው የልማት አስተሳሰብ መገለጫዎች እንደሆኑ ዘመናዊነትን ከልማት ጋር መለየት እሲኪያቅት ድረስም የተጣመዱና ከካፒታሊዝምና ከኢኮኖሚ ዕድገት ጋር የተፈተሉ ናቸው የሚሉ አሉ፡፡ በዘመናዊነት ቲዎሪ አቀንቃኞች ዐይንም ዘመናዊነት ማለት በሥርነቀልና ሁለንተናዊ ለውጥ የሚመራ አብዮታዊ ሂደት ሆኖ ኢንዱስትሪያላይዜሽንን፣ ከተሜነትን፣ ማህበራዊ ንቅናቄን፣ የሚዲያ፣ የፖለቲካ ተሳትፎ፣ የትምህርትና የተማረ ሰው መስፋፋትን የሚያጠቃልል ውስብስብ ሂደት ተደርጎ እንደሚታይ ይገልፃሉ (Schech & Haggis, 2000; 3;9)፡፡

ይሄ የዘመናዊነት አስተሳሰብ ለባህላዊ ጉዳዮች ቦታ የማይሰጥ ከመሆኑም በላይ ባህልን የልማት እንቅፋትና በድህነት አዙሪት ውስጥ የሚከት አድርጎ የሚመለከት በመሆኑ ደሃ ሃገራት ከድህነት አዘቅት ተላቀው በሁለንተናዊ መልኩ ለመልማት ከጎታች ባህሎቻቸውና ኋላ ቀር አመለካከታቸው ተላቀው ዘመናዊነትን መጠመቅ አለባቸው የሚል ነው፡፡

ይሁንና ከዚህ አስተሳሰብ በተቃራኒው መልኩ በኢስያ ሀገሮች የመጣው የሚያስገርም ልማት መነሻ ባህላዊ ጉዳዮችን ከልማት ጋር አያይዞና መሣሪያ አድርጎ የመጣ እንደሆነ ቀደም ሲል ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ ይህ የዘመናዊነት ቲዎሪና በተቃራኒው የሚነሱት የልማት ቲዎሪዎች (Developmental Theories) አስተሳሰቦች በበርታ ባህላዊ መሠረቶች ላይ በምን መልኩ እንደሚሠሩ ለማየት በዚህ ጥናት ትንታኔ ከጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

ጥናቱ እነዚህን ከላይ የቀረቡ ቲዎሪዎች መሠረት አድርጎና ቲዎሪዎቹ በየራሳቸው ምሉዕ ባለመሆናቸው ያንዱን ክፍተት በሌላው ጥንካሬ በማሟላት የተሠራ ነው፡፡ በጥናቱ የክዋኔን ቲዎሪ ባህላዊ ዘውጉ ዕውን ሲሆን የሚሰጠውን ፍቺ ለመመርመር፤ የባህላዊ ዘውጉ ለብሔረሰቡ የሚሰጠው ጥቅም ደግሞ በተግባራዊ ቲዎሪ ተደግፎ ተተንትኗል፡፡

የብሔረሰቡ ባህል ከአካባቢው ልማት ጋር ያለውን ተዛምዶ ለማየትና ባህሉ በልማቱ ላይ የሚያሳድረውን አዎንታዊና አሉታዊ ተፅዕኖ እንዲሁም ባህሉን መሣሪያ በማድረግ ለአካባቢው ልማት ለማፋጠን እንዴት ጥቅም ላይ መዋል እንደሚቻል ለማየት የዘመናዊነትና የልማት ቲዎሪዎችን ተጠቅሞ ትንታኔ ተደርጓል፡፡

### 3.2.4. የቲዎሪ አመላካች ሞዴል ("የባህላዊ ፈርጦች ተደጋጋሚነትና ተመሳስሎ ዙር ገጠም ስረጃ መረብ")

የተሰበሰበውን መረጃ ከላይ በተጠቀሱት ቲዎሪዎች አጋዥነት ለመተንተን በተደረገው ሙከራ መረጃዎቹ በየዘውጋቸው ሲመደቡ ከሚሠጡት ስዕል በመነሳት በተደጋጋሚ የሚታዩትን የጋራ ጉዳዮችና ባህላዊ ፈርጦች አንጥሮ በማውጣት የተመሳስሎ መረባቸው (Network) ምን እንደሚመስልና እንዴት እንደሚሰናሰል ለማየት ተችሏል፡፡ በመሆኑም የማህበረሰቡን ባህል ባጠቃላይና የልማት አስተሳሰቦችን በተለይ አጉልቶ የሚያሳይ **"የባህላዊ ፈርጦች ተደጋጋሚነትና ተመሳስሎ ዙር ገጠም ስረጃ መረብ"** የሚል የቲዎሪ አመላካች ሞዴል ተግኝቷል፡፡ የተገኘው የቲዎሪ አመላካች ሞዴልም በጥናቱ ትንታኔ ውስጥ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ የቲዎሪ አመላካች ሞዴሉ መግለጫ የሚከተለው ነው፡፡

**ባህላዊ ፈርጦች፡-** የተባሉት በማህበረሰቡ ባህላዊ ዘውጎች (ሥነቃል፣ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት፣ ሀገረሰባዊ ልማዶችና ቁሳዊ ባህል) ውስጥ የሚታዩ ዕውነቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ባህላዊ ፈርጦች በየዘውጎቹ ቅርፃቸውን እየለዋወጡ ተደጋግመው በመምጣትና እርስ በእርስ በመሰናሰል ራሳቸውን በማህበረሰቡ የዕለት ተዕለት ህይወት ውስጥ ያንሰራፉ፣ ዞረው የሚገጥሙና ይህ ባህሪያቸው በተሰበሰበው ባህላዊ መረጃ ውስጥ በዚህ መልኩ ጎልቶ ስለሚታይ **"ባህላዊ ፈርጦች"** በሚለው ስያሜ ተገልፀዋል፡፡

**መረብ፡-** የተባለው የባህላዊ ፈርጦቹን እርስ በእርስ መሻረብና በማህበረሰቡ ባህል ውስጥ መዘርጋትን የሚያመለክት ነው፡፡

**ሰረጀ/ስርጃ፡-** የሚለውን ቃል የተለያዩ የአማርኛ መዝገበ ቃላት እንደሚከተለው ይፈቱታል፡፡

- ሰፋ፤ ተበተበ አወላከፈ (ባህሩ፣ ገፅ 104)
- ሰርዶው፣ ሀረጉ፣ ሣሩ፣ የቁጥቋጦው ክንፍ እርስ በርሱ በመብዛት ክንፉና ዐፅቁ እያቆጠቆጠ በመንዘራፈፍና በመንሠራፋት በምድር ላይ ሰረጀ፣ ሰፋ ተንሰራፋ፣


**ስረጃ፡-**

- እንደ ሰርዶ በምድር ላይ መስፋፋት፣ አንጓው፣ ብርኩ፣ ከመሬት ሥር እየሰደደ መዝመት ወይም እንደ ዱባና ቅል በምድር ላይ መንሰራፋት፣ መስፋፋት ወይም እንደ ወርካ በህዋ ላይ መስፋት፣ ክንፍን ማጥላት፣ መንዛፈፍ፣
- ገመድ፣ ሐረግ፣ሰርዶ፣ ሽቦ ወይም ሰንሰለት በምድር ላይ በመስፋፋቱ እየጠለፈ ጣለ፣ሰረጀ፣ አላስኬድ አለ፣ከለከለ፣ አሥሮ አጠላልፎ አወላከፈ (ተሰማ፣2002፣ገፅ 235)

ከላይ እንደተመለከተው ሰረጀ/ስረጃ የሚለው ቃል አንድም መስፋፋትን፣ መንሰራፋትን፣ ስር መስደድን እርስ በእርስ መጋመድን፤ አንድም ከዚህ ባህሪው የተነሳ አላራምድ ብሎ ማወላከፍን፣ መጥለፍን እንዲያም ሲል ጠልፎ መጣልን የሚያመለክት ነው፡፡

ከተሰበሰበው መረጃ በመነሳት የበርታ ብሔረሰብ ባህላዊ ፈርጦች እራሳቸውን በመደጋገምና በማሰናሰል በማህበረሰቡ ውስጥ እንዴት እንደሚሰረጁ በማጤን ለአካባቢው ልማት መፋጠንም ሆነ ወደኋላ መቅረት ያላቸውን ሚና በግልፅ ለማሳየት የተገኘውን የቲዎሪ አመላካች ሞዴል ጥቅም ላይ በማዋል ለማረጋገጥ ተሞክሯል፡፡

## የቲዎሪ አመላካች ሞዴሉ ሥዕላዊ መግለጫ




**<u>መግለጫ</u>**

**ባፊ-----** ባህላዊ ፈርጥ

**አዎተ----** አዎንታዊ ተፅዕኖ

**አሉተ----** አሉታዊ ተፅዕኖ

**የቀስቱ ነጭ ክፍል---** አዎንታዊ ተፅዕኖ

**የቀስቱ ጥቁር ክፍል---** አሉታዊ ተፅዕኖ

**ከውስጥ የሚታዩት ቀስቶች---** ተደጋጋሚነትን፣ ተመሳስሎንና እርስ በእርስ መጋመድን ያመለክታሉ።

**መሃል ላይ የሚዞሩት ሁለት ነጫጭ ቀስቶች---** ባህላዊ ፈርጦቹን እርስ በእርስ በማጋመድ ለስርጀታ የሚያሾሩ መቂናጦች[13] ሲሆኑ ባህላዊ ፈርጦቹ ሥር እየሰደዱና ራሳቸውን አጠናክረው መሰርጀታቸውን ያመለክታሉ።

**ከውስጥ የሚታየው መረብ---** ባህላዊ ፈርጦቹ እርስ በርስ እየተሰናሰሉ በሁሉም አቅጣጫ መዘርገታቸውን ይገልፃል።

---

[13] እንደ መኪና ሆኖ አቀብና ቁልቁል ቁንጥ ቁንጥ የሚል ... ከሙኑና ከሁለቱ አርቦች ጋር ተሳስሮ ድሩንና ማጉን እያጠላለፈ ለመወርወሪያው መንገድ የሚሰጥ መቂናጥ(ከሣቴ ብርሃን፣1951፣96)

# ምዕራፍ አራት

# 4. የጥናቱ አሠራር ዘዴ

በዚህ ክፍል የጥናቱ ዘዴና አጠቃላይ የጥናቱ መረጃ አሰባሰብና ናሙና አወሳሰድ ስልቶች፣ የጥናቱ አካሄድና አተናተን ዘዴዎች ይቀርባሉ፡፡

## 4.1. የጥናቱ ዘዴ

ይሄ ክፍል የሚመለከተው በመረጃ ስብሰባው ወቅት የተከናወኑ ተግባራት፣ ጥናቱን ለማካሄድ ያገለገሉ መረጃዎች መልክ፣ የመረጃ ምንጮች ስብጥር፣ መረጃው የተሰበሰበባቸው ዘዴዎች፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ቁሶች፣ የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች ምን ምን እንደሆኑ፣ ጠቀሜታቸውና በምን መልኩ ከጥቅም ላይ እንደዋሉ ነው፡፡

### 4.1.1. የጥናቱ መልክ

ጥናቱ ዓይነታዊ (Qualitative) የአጠናን ዘዴን መሠረት አድርጎ የተሠራ ሆኖ ተንታኝ (Interpretative) የአጠናን ስልትን የሚከተል ነው፡፡ የጥናቱን ዓላማዎች ለማሳካትና የምርምር ጥያቄዎችን ለመመለስ ቀዳማይና ካልዓይ የመረጃ ምንጮች ከጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ ካልዓይ የመረጃ ምንጮች ከጥናቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው መፅሃፎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ቀድመው በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ የተደረጉ ጥናቶች፣ የክልሉ ኮሚኒዩኬሽን ቢሮ ያሳተማቸው መፅሄቶች፣ የክልሉ መንግስት ስትራቴጂክ ዕቅዶችና የአፈፃፀም ሪፖርቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ምንጮች ከቤተ መፃህፍት፣ ከፌዴራል ግብርና ሚኒስቴር፣ ከፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ከፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር፤ ከፌድራል ስታስቲስቲክስ መስሪያ ቤቶች፣ ጥናቱ በሚደረግበት አካባቢ በሚገኙ የክልል፣ የዞንና፣ የወረዳ መስሪያ ቤቶች

ውስጥ የተገኙ ናቸው፡፡ እነዚህ ከካልዓይ የመረጃ ምንጮች የተገኙ መረጃዎች ለጥናቱ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያበረከቱ ሲሆን በተለይም የጥናቱን መነሻ ሃሳብ ለማጠናከርና ከመስክ የተገኘውን መረጃ ለመተንተን ማመሳከሪያና ማመዛዘኛ ሆነው አገልግለዋል፡፡ በቀዳማይ የመረጃ ምንጭነት ከጥናቱ አካባቢ የመስክ መቼቶች ጥሬ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

### 4.1.2. የመረጃ ማሰባሰቢያ ስልቶች

በዚህ ጥናት በመረጃ ማሰባሰቢያነት ያገለገሉት ዘዴዎች ቃለ መጠይቅ (Interview) ፣ ምልከታ (Observation) ፣ ተሳትፎአዊ ምልከታ (Participatory Observation) እና ተተኳሪ ቡድን ውይይቶች (Focus Group Discussions) ናቸው፡፡

#### 4.1.2.1. ምልከታ እና ተሳትፎአዊ ምልከታ

በባህል መረጃ ስብሰባ ዋነኛ ጉዳይ በሆነው በባህሉ የክዋኔ አውድ ላይ በመገኘት ምልከታ፣ በአብዛኛው ደግሞ ተሳትፎአዊ ምልከታ በማድረግ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ ይህ ደግሞ የአጥኚዋን ንቁ ተሳትፎና የአተያይ ብቃትና ጥበብ የሚጠይቅ ከመሆኑም በላይ የማህበረሰቡን ህይወት በቅርበት እየተመለከቱና እየኖሩትም የሚሰበሰብ በመሆኑና በተጠኚው ህብረተሰብ ዘንድም አመኔታንና ተቀባይነትን ስለሚያመጣ የማህበረሰቡን ወጎችና ልማዶች በማክበር ውጤታማ መረጃን ለመሰብሰብ ያስችላል፡፡ “Participant observation … in which the Anthropologist seeks to immerse herself as fully and as unobtrusively as possible in the life of a community under study” (Gardener & Lewis,1996 ,xv) .

በዚህ መሠረት ማህበረሰቡ ውስጥ ለመግባት አብረው እየኖሩና እየተሳተፉ መረጃ ለመሰብሰብ መጀመሪያ የማህበረሰቡን አመኔታና ተቀባይነትን ለማግኘት የቀደመው የመስክ ቆይታዬ ምቹ ሁኔታን የፈጠረልኝ በመሆኑ በባህሉ መሠረት ከአለባበሴ ጀምሮ በአመጋገብም ሆነ በአኗኗር ማህበረሰቡን መስዬ አብሬያቸው እየዋልኩ እያደርኩ ለመጀመሪያ ጊዜ ለ21 ቀናት ቀጥሎም ለሦስት ወራት በመጨረሻም ለ15 ቀናት በጥናቱ አካባቢ በመቆየቴ እንደ ማህበረሰቡ አባል ቆጥረውኝ ምንም መረጃ ሳይደብቁ እንዲሰጡኝ ያደረግሁ ይመስለኛል፡፡



ፎቶ 3 ለመረጃ ስብሰባ ጉዞ ወደ መቃዚን ቀበሌ

በባህል ጥናት ከመስክ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ሦስት አይነት መቼቶች (አውዶች) እንዳሉ፤ እነሱም ተፈጥሯዊ (Natural Setting)፣ ቅንብር ተፈጥሯዊ (Induced Natural Setting) እና አርቲፊሻል መቼቶች (Artificial Setting) እንደሆኑ (Goldstein, 1974, 80-90፤ፈቃደ፣1991፣122-124) ይገልፃሉ። በዚህ የሙከራ ጥናት እንደ አመችነቱ በብዛት ተፈጥሯዊ አልፎ አልፎ ደግሞ አርቲፊሻል መቼቶችን በማዘጋጀት መረጃዎቹ ተሰብስበዋል።

አርቲፊሻል መቼቶቹ በመቃዚንና በሸከፍ ቀበሌ የተደረጉ ናቸው። በመቃዚን ቀበሌ የባህላዊ ጭፈራ ዓይነቶችን የሚገልፁና የቀበሌው ማህበረሰብ በነቂስ ወጥቶ የተሳተፈበት አውድ ለእኔ ተብሎ የተዘጋጀ ይሁን እንጂ ልክ አንድ በዓል ያለ እስኪመስል ድረስ ፍፁም ተፍጥሮኣዊ መቼት ነው ለማለት ይቻላል።

የከሸፍ ቀበሌው ግን ማህበረሰቡ ጥንት ጦርነት በሚኖርበት ጊዜና አሁንም አንዳንድ ባህላዊና የእምነት በዓላት በሚኖሩበት ጊዜ እያወጣ የሚጠቀምባቸውን እነሱ "አል ጡሩንቢያ" የሚሏቸውን ባህላዊና ዘመናዊ[14] የሙዚቃ መሣሪዎችና አጠቃቀም ባህል የሚገልፁ ሲሆኑ እኔ በሄድኩበት ሰዓት ሁለቱም አውዶች ባለመኖራቸው አርቲፊሻል መቼት ለኔ ሲባል ተዘጋጅቶ የተከወነ ነው።

ምልከታው ወንዶች ብቻ በሚቀመጡበትና በሚመገቡበት "አልከልዋ"፣ በመኖሪያ ጎጆዎች፣ በእርሻ ቦታዎች፣ በፀሎት ቦታዎች በ"ኤሪ" (ጠንቋይ፣ አዋቂ) ቤት፣ በባህል መድሃኒት አዋቂ ቤት፣ በወርቅ ቁፋሮ ቦታዎች፣ በገበያ፣ በሠርግና በሀዘን ቤቶች፣ በስብሰባዎች፣ ወዘተ ሁሉ በቅርብ ተመልካችነትና በተሳታፊነት ተካሂዷዋል።

[14] ዘመናዊ ያልኩት ከበሮውና 3 ጡሩምባዎች ጥንት በንጉስ ሙስጠፋ ጊዜ ከእንግሊዝ የተላኩ ናቸው ብለው ስለነገሩኝና ባህላዊ በሆነ መንገድ እዚያው ያልተሠሩ መሆናቸውን በማረጋገጤ ነው። እምቢልታዎቹና ሌሎች የትንፋሽ መሣሪያዎቹ ግን በባህላዊ መንገድ በራሳቸው የተሠሩ ናቸው።

የተሳትፎ ምልከታው በመኖሪያ ጎጆዎች ከሴቶቹ ጋር አብሮ በመሆን ምግብና መጠጦችን ሲያበስሉ፣ መዋቢያዎችን ሲያዘጋጁና ሲጋጌያጡ፣ ሙሽራ ሲያስጌጡ፣ ባህላዊ ጭፈራዎችን ሲጨፍሩ፣ በለቅሶ ቤት ሀዘን ሲቀመጡ አብሮ በመሳተፍ፣ የሚሠሩትን በመሥራት ጌጣቸውን በእጆቼና እግሮቼ ላይ በማድረግ፣ ባህላዊ ጢሳቸውን በመሞቅ፣ አብሬያቸው ወርቅ ቁፋሮ፣ ገበያና ዘመድ ጥየቃ፣ ለቅሶ መድረስና በልዩ ልዩ ጥሪዎች አብሮ በመሄድ ወዘተ የተካሄደ ነው፡፡

በዚህም አንዳንዴ ምንም ዓይነት የድምፅ ወይም የምስል ቀረፃ ሳይኖር እንደዋዛ አንስተው ከሚጫወቷቸው ጉዳዮች ከሚሠሯቸው ነገሮች በመነሳት ብዙ ጠቃሚ መረጃዎች ከመሰብሰባቸውም በላይ እነሱም የመቅረጫ መሣሪያዎች ተፅዕኖ ሳያድርባቸው ነገሮችን እንድገነዘብና እንድረዳ እንድሞክረውም በማሳየትና በማብራራት ብዙ መረጃዎችን ሰጥተውኛል፡፡ በተለይ እነሱ የሚዋቡባቸውን ጌጦች ስጠቀም፣ የሚበሉትን ስበላ፣ የሚለብሱትን ስለብስና አብሬያቸው ውዬ ሳድር የነበራቸው ደስታ የተለየ ነበር፡፡ ለእኔም የበለጠ ወደራሳቸው እንዲያቀርቡኝና እንደራሳቸው እንዲቆጠሩኝ ያስቻለኝ ይኸው ተሳትፎዬ እንደሆነ ማረጋገጥ ችያለሁ፡፡

እነዚህ ምልከታዎች የማህበረሰቡን ባህላዊ ይዘቶች እና ክዋኔዎች በተገቢው ሁኔታ ለመመልከትና ጠቃሚ መረጃዎችን ከመሰብሰብ በላይ ወደፊት የጥናቱ ትኩረት ለሆነው የባህልና የልማት ቁርኝትና የልማት አጀንዳዎች ሆነው በዚህ ጥናት ለሚዳሰሱት የግብርናና ጤና ኤክስቴንሽን አፈጻጸም በተጨባጭ መሬት ላይ ያሉትን ምቹ ሁኔታዎችንና ተግዳሮቶችን ለማጤን ያስቻሉኝ ናቸው፡፡

### 4.1.2.2. ቃለ መጠይቅ

በባህል መረጃ ስብሰባ የባህሉን ነገረ ይዘት (Text) የማህበረሰቡን ልዩ ልዩ አካላት የፆታ፣ የዕድሜና የማህበራዊ ደረጃ ስብጥር ጠብቆ ቃለ መጠይቅ በማድረግ መረጃ መሰብሰብ ተገቢ በመሆኑ ይኸው ተጠብቆ ቃለ ምልልስ በማድረግ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ መረጃ ሰጪዎች በብድግ ብድግ (random sampling) እና በታለመ (purposive sampling) የናሙና አመራረጥ ስልት እንደየባህላዊ አውዱ ሁኔታ ከሦስት እስከ ሰባት የሚደርሱ ሰዎች ከየባህላዊ አውዱ ላይ መርጦ ቃለ መጠይቅ (Interview) በማድረግ ዝርዝር መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

ለጥናቱ ከተመረጡ አራት ወረዳዎች ውስጥ በነበረው የሦስት ወራት ቆይታ ከየወረዳዎቹ ሁለት ሁለት ቀበሌዎች ተመርጠው መረጃውን ለመሰብሰብ ጥረት ተደርጓል፡፡ ለዚህም በዋናነት የነባሩ ብሔረሰብ መኖሪያ ከሆኑት ሸርቆሌና መንጌ ወረዳዎች በስፋት የታዩ ሲሆን ከከተማ ቀመሶቹ ከአሶሳ ዙሪያና ባምባሲ ወረዳዎች ተካተዋል፡፡ ከሁሉም ወረዳዎችም ከእያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት ቀበሌዎች ተመርጠው የተሰበሰበውን መረጃ በትንታኔው ላይ በሰፊው በግብዓትነት ለማካተት ተሞክሯል፡፡

በመስክ ቆይታው እንዳጋጠመው ምቹ ሁኔታም በየቀበሌዎቹ የተለያየ ቁጥር ያላቸው ሃያ ስምንት ሴቶችና አርባ ስምንት ወንዶች በጠቅላላው 76 ሰዎች መረጃ በመስጠት ተሳትፈዋል፡፡ ከነዚህ ውስጥ አሥራ አንድ ሴቶችና ሃያ ሦስት ወንዶች በድምሩ 34 ሰዎች ቃለ ምልልስ በማድረግ የተሳተፉ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ በቃለመጠይቅ በዋና መረጃ ሰጪነት ያሳተፍኳቸው ጥንት የማህበረሰቡ መሪዎች ከነበሩት የደጃዝማች ሙስጠፋ አብድራህማን ልጅ የሆኑትን፣ የሼህ ሆጀሌ የልጅ ልጅ የሆኑትና የአባ ሞቲ የልጅ ልጅ የሆኑትን ሶስት ወንዶችን እና ሁለት ሴቶችን ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች ማህበረሰቡን ሲመሩ የነበሩ በጊዜው አጉር ወይም ንጉስ ተብለው የሚታወቁ ሰዎች ቤተሰቦች በመሆናቸው በተለይ ስለብሔረሰቡ አመጣጥና ባህል በዋና መረጃ ሰጪነት ልጠቀምባቸው ችያለሁ፡፡ የብሔረሰቡን አመጣጥ አስመልክቶ በአንዳንድ ጉዳዮች የተለያየ ሃሳብ ቢያቀርቡም

አጠቃላይ የበርታን ባህል አስመልክቶ ጠቃሚ መረጃ ሰጥተውኛል። በዚህ ጥናት ስለብሔረሰቡ ስያሜ የሰጡኝ የተለያየ መረጃ በማሳያነት የቀረበ ነው።

### 4.1.2.3. የተተኳሪ ቡድን ውይይት

የሚሰበሰበውን መረጃ የበለጠ አስተማማኝ ለማድረግ ከላይ ከቀረቡት ዘዴዎች በተጨማሪ የተተኳሪ ቡድን ውይይቶች ማድረግ ተገቢ በመሆኑ የፆታ፣ የዕድሜና የማህበራዊ ደረጃ ስብጥሩን ጠብቆ በቡድን ስለባህላዊ ዘውጉና ስለማህበረሰቡ ልማት ባላቸው የጋራ አመለካከት ላይ እንዲወያዩ በማድረግ ያልተሟሉ መረጃዎች እንዲሟሉና የተሰበሰቡትም እንዲጠናከሩ ተደርጓል።

በአምስት የተተኳሪ ቡድን ውይይቶች አሥራ ሰባት ሴቶችና ሃያ አምስት ወንዶች በጠቅላላው አርባ ሁለት ሰዎች ተሳተፈዋል።[15] የመረጃ ሰጪዎቹ የዕድሜ ስብጥርም ከ17 እስከ 95 ዓመት የሚደርስ ነው።

የቡድን ውይይቱ መረጃ የተሰበሰበው ከአሶሳ ዙሪያ ወረዳና ከሽርቆሌ ወረዳ በተመረጡ በአራት ቀበሌዎች ነው። ከአሶሳ ዙሪያ ወረዳ በቆሽመንግልና አቡራሙ ቀበሌ ከሽርቆሌ ወረዳ ሽርቆሌና መቃዚን ቀበሌ ላይ አምስት የቡድን ውይይቶች በማድረግ መረጃ ተሰብስቧል።

በአሶሳ ዙሪያ ወረዳ የተካሄዱት ሁለት የተተኳሪ ቡድን ውይይቶች ናቸው። በቆሽመንገል ቀበሌ አራት ሴቶችንና ሰባት ወንዶችን በጠቅላላ አስራ አንድ ሰዎችን፣ በአቡራሙ ቀበሌ አራት ሴቶችና አምስት ወንዶችን በድምሩ ዘጠኝ ሰዎችን፣ የዕድሜና የማህበራዊ ደረጃውን ስብጥር ጠብቆ በተተኳሪ ቡድን ውይይት በማሳተፍ መረጃዎች ተሰባስበዋል።

---

[15] የመረጃ ሰጪዎቹ ዝርዝር መግለጫ በአባሪነት ተያይዟል።

መረጃ ሰጪዎቹ በቡድን ውይይቱ ሀሳባቸውን በነፃነት እንዲገልፁ እንደ የመረጃ አውዱ ሁኔታ ተመልክቶ ማደራጀትን ተገቢ የሚያደርገው ጉዳይ የቡድኑ አባላት ሳይፈሩና ሳይሸማቀቁ ሃሳባቸውን በነፃነት እንዲገልፁ የሚያስችላቸውን ቡድን ማደራጀት ጠቃሚ በመሆኑ (Dawson;2002, Bloor& Others,2001) የቀሩት ሦስት ቡድኖች በሸርቆሌ ወረዳ በመቃዚንና በሸርቆሌ ቀበሌ የተደራጁ ሆነው በመቃዚን ቀበሌ አንዱ ሰባት ሴቶች ብቻ የተሳተፉበት፣ አንዱ ሰባት ወንድ አባላት ብቻ ያሉት አዛውንት የጎሳ መሪዎች፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ የእጅ ሙያተኞች፣ የባህል መድሃኒት አዋቂዎች ብቻ የተገኙበት የተተኳሪ ቡድን ተደራጅቷል። በሸርቆሌ ቀበሌ ደግሞ ሁለት ሴትና ስድስት ወንድ በድምሩ ስምንት አባላት ያሉት የታወቁ ወጣት የባህል ሙዚቃ ተጨዋቾች፣ ተረት ነጋሪዎች፣ ባህላዊ ሥርዓቶች ላይ ማህበረሰቡን በመምራትና በማስተባበር የሚታወቁ ሰዎች የተካተቱበት የተተኳሪ ቡድን ውይይት ተደርጎ አጥጋቢ መረጃዎች ተሰብስበዋል።

በተተኳሪ ቡድን ውይይት ጊዜ አማርኛ ለማይችሉ[16] አባላት በአስተርጓሚነት የተጠቀሙኳቸው ከተሳታፊዎቹ እንደ አንዱ አባል ሆነው ሃሳባቸውን ከሚገልፁት መሃል በመሆኑ ውይይቱን የተሳካ አድርጎልኛል። በአምስቱም የተተኳሪ ቡድኖች 17 ሴቶችና 24 ወንዶች በጠቅላላው 42 ሰዎችን ተሳታፊ በማድረግ በቃለ መጠይቅና በምልከታ የተገኙ መረጃዎች ተረጋግጠውበታል፤ የጎደሉ መረጃዎችም አጥጋቢ በሆነ መልኩ ተሟልተውበታል።

በተተኳሪ ቡድን ውይይቶቹ የተሳተፉት ሰዎች በዋናነት የማህበረሰቡ መሪዎች፣ የጎሳና የሀይማኖት አባቶች፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ የእጅ ሙያተኞች፣ የባህል መድሃኒት አዋቂዎች፣ ተራቾች፣ የባህላዊ ዘፈን አቀንቃኞች ወዘተ ሲሆኑ የዕድሜ፣ የፆታና የማህበራዊ ደረጃ ስብጥሩ እንደ ባህላዊ የክዋኔ አውዱ ሁኔታ ከፍተኛ ትኩረት ስለተሰጠው የቡድን ውይይቱን ውጤታማ አድርጎታል።

[16] አብዛኞቹ የተተኳሪ ቡድን አባላት አማርኛ የሚናገሩ ቢሆንም አንዳንድ አማርኛ የማይችሉ አባላት በቋንቋቸው ሀሳባቸውን ሲገልፁ አስተርጓሚዎችን ከቡድን አባላት ተጠቅሜአለሁ፡፡

## 4.2. ከመስክ ውሎ የተገኘ ልምድ

ከዚህ ጥናት የመስክ ውሎ የተገኙ ትምህርቶች በርካታ ሲሆኑ በዋናነት የሚጠቀሱትን ጥቂቶቹን ብቻ ቀጥሎ አነሳለሁ፡፡

የባህል ጥናት ሰፊና ውስብስብ በመሆኑ በመረጃ ስብሰባው ወቅት የተፈለገውን መረጃ ለመሰብሰብ የባህሉ ባለቤት የሆነውን ማህበረሰብ ተቀባይነትና አመኔታ ማግኘት ቀዳሚው ተግባር መሆን አለበት፡፡ ይሄን አመኔታ ለማግኘት ደግሞ በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸውን አባላት ፈልጎ ማግኘት ጠቃሚ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የኔን ስራ ያቀለለችልኝ ሲቲና ናት፡፡ እሷን ይዤ ለመጀመሪያ ጊዜ በምገባባቸው መንደሮች ሁሉ የፈለኩትን መረጃ ይዤ ለመውጣት አልቸገርም ነበር፡፡ ለሁለተኛ ጊዜ ብቻየን ስሄድም አንዴ ስላወቁኝ እንደቤቴና እንደቤተሰቤ የፈለኩትን ለማግኘት ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮልኝ ነበር፡፡

ይህንን ለማለት ያስቻለኝ የአንድ ቀን ገጠመኜ ነው፡፡ መንጌ ወረዳ ላይ የሠርግ ሥርዓትን ለማየት ሠርጉ ከሚከናወንበት አንድ ቀን በፊት ወደ ሴቷ ሙሽራ ቤት በሄድኩበት ወቅት ሲቲና ስላልተመቻት ለመጀመሪያ ጊዜ አብራኝ አልሄደችም ነበር፡፡ ከቀኑ 5፡00 ሰዓት ላይ በሥፍራው ስደርስ ለአስተርጓሚነትና አንዳንድ ሁኔታዎችን እንዲያመቻችልኝ ከወረዳው ኮምዩኒኬሽን ቢሮ አቶ ዘካሪያ የሚባል ሰው አብሮኝ ነበር፡፡ ሠርጉ ቤት እንደደረስን ሰውየው ሙሽራዋ ያለችበት ጎጆ ውስጥ አስገብቶኝ ወደ ወንዶቹ አልከለዋ አመራ፡፡ ለአካባቢው እንግዳ ስለነበርኩ ሰዎቹ ሁሉ ሠርጉን ለመታደም ከአዲስ አበባ የመጣሁ እንግዳ መስያቸዋለሁ፡፡ ቆይቶ አቶ ዘካሪያ ዓላማየን ለሙሽራዋ ወንድም አስረድቶት ኖሮ እሱ መጥቶ ተዋወቀኝና ለሴቶቹም የመጣሁበትን ነግሮልኝ ሄደ፡፡

ማታ የሀርሻ ጭፈራ ሌሊቱን ሙሉ ስለሚጨፈር አዳሬም እዚያው ቤት ነው፡፡ እንደገባን አካባቢ የተጠበሰ ብስኩትና ሻይ መብላቴን አስታውሳለሁ፡፡ ከዚያ በኋላ የተለያየ ምግብ ቢቀርብም ስላላስፈለገኝ አብሬያቸው አልበላሁም፡፡ ሲመሽ ግን ራት አቅርበው ሲበሉ እኔን ብይ የሚለኝ ይጠፋል፡፡ እኔ ደሞ ካሁን አሁን ብይ ይሉኛል ብየ እጠብቃለሁ፡፡

እየመሸ ሲመጣ  የምግብ መስተንግዶው አልቆ ሁሉም ለጭፈራው መሰነዳዳት ጀመረ፡፡ እኔን ያስታወሰኝ የለም፡፡ ይዞኝ የመጣውም ሰውዬ የት እንደሄደ አላውቅም ባስፈልገው ላገኘው አልቻልኩም፡፡ ረሃብ እየጠናብኝ ሲመጣ ስጡኝ እንዳልል ይሉኝታ ያዘኝ፡፡ እንደምንም ችየው ውጪ ተቀምጬ የጭፈራውን መጀመር እየተጠባበቅሁ ሳለ ሰውየው ከምሽቱ 4፡30 አካባቢ መጣ፡፡

አንዳንድ ነገር ስለሚቀጥለው ሥርዓት ከነገረኝ በኋላ እራት በላሽ ብሎ ጠየቀኝ፡፡ አለመብላቴን ነገርኩት፡፡ ወደ ሴቶቹ ሄደና ለምን እራት እንዳልሰጡኝ ሲጠይቃቸው “እኛ ስንበላ አብራን ቀርባ ባለመብላቷ የእኛን ሥጋ አትበላ ይሆናል ብለን ዝም አልናት አሁን ጠይቃትና ከፈለገች እንሰጣታለን እንጂ ጦሟን ታድራለች እያልን ስንጨነቅ ነው የመጣሽው” እንዳሉት መጥቶ ይነግረኛል፡፡ እኔም ረሃብ ስለሞሸለቀኝ የሰጡኝን እንደምበላ ነግሬው እንደገና አልኪስራ/ የማሽላ እንጀራ በሥጋ ወጥ አቅርበውልኝ ከበላሁ በኋላ ወደ ቀረፃዬ ገብቻለሁ፡፡ ለዚህ የእኔ በይሉኝታ ተይዞ የምፈልገውን አለመጠየቅና የእነሱ አትበላ ይሆናል ብሎ ዝም ማለት የዳረገን የሲቲና አጠገቤ አለመኖር ነበር፡፡ ይሄን የመስክ ገጠመኜን በስፋት ያነሳሁት በእንደዚህ ዓይነት የሀሳብ አለመግባባት ሊቀሩ የሚችሉ ጠቃሚ መረጃዎችን ለማሳየት ያስችላል ብዬ ነው፡፡ በመሆኑም በባህል መረጃ ስብሰባ ሲቲናን የመሰሉ “በር ከፋቾች” የሚኖራቸው ሚና ቁልፍ መሆኑን ተረድቻለሁ፡፡

ሌላው ከዚህ ጥናት የተገኘው ትምህርት በባህል መረጃ ስብሰባ የማህበረሰቡን አመኔታ ማግኘትና ባህላዊ እሴቶቻቸውን ማክበር ተገቢ መሆኑን ነው፡፡ የባህል መረጃ የማህበረሰቡን ኑሮ እየኖሩ እነሱን መስሎ የሚሰበሰብ በመሆኑ በቅድሚያ ዓላማን ለማህበረሰቡ በግልፅ አስረድቶ ተቀባይነት ማግኘትን ይጠይቃል፡፡ ይህ ከሆነ ማህበረሰቡ ይጠቅማል ብሎ የሚያስበውን ሁሉ በራሱ ተነሳሽነት መረጃ ይሰጣል፡፡ ምንም የሚደብቀውና ለመስማት የምትፈልገው ይሄ ነው በማለት መረጃን አይሸሽግም፡፡ ይህንን ተቀባይነት ለማግኘት ደሞ ከአለባበስ ጀምሮ የባህሉን እሴቶች መጠበቅ፣ የሚበሉትን አብሮ መብላት የሚሰሩትን አብሮ መስራትና መሳተፍ ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡ እኔ ከሀገር ልብሶች በስተቀር ቀሚስ የመልበስ ልማድ የለኝም፡፡ ለመረጃ ስብሰባ ከበርታዎች

መንደር ስገባ ግን ሴቶቻቸው የሚለብሱትን ቶብ ለብሼ፣ እነሱ የሚተኙበት እየተኛሁ፣ የሚበሉትን እየበላሁ፣ ጭሳቸውን እየሞቅሁ፣ በጌጣቸው እያጌጥሁ በመሆኑ ለሴቶች መግባት በማይፈቀድበት ወንዶች ቁርአን በሚቀሩበት ቤት እንኳን ሳይቀር የሚያስፈልገኝ ከሆነ ገብቼ እንድቀርፅ እኔ ሳልጠይቃቸው ራሳቸው ሽማግሌዎቹ ፈቅደውልኛል።

በባህል መረጃ ስብሰባ መደበኛ ከሆኑት የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች ከቃለ መጠይቅ፣ ከምልከታና ከቡድን ውይይት የድምጽና የምስል መሣሪያዎችን እየተጠቀሙ ከሚሰበሰቡ መረጃዎች ይልቅ አንዳንዴ/ ባብዛኛውም ማለት ይቻላል መደበኛ ባልሆነ ሁኔታ የሚሰበሰበው መረጃ ጠቀሜታው የጎላ ሊሆን እንደሚችል ሌላው ከመስክ ቆይታየ ያገኘሁት ትምህርት ነው። ይሄንንም ከሚያረጋግጡት በርካታ ምሳሌዎች ከላይ በክፍል አምስትና ስድስት ጥቂቶቹን አንስቻቸዋለሁ።

ሌላው ጠቃሚ ትምህርት ደግሞ በምስል የተቀረፀውን መረጃ መልሶ የማሳየት ጠቃሚነት ነው። የዚህ ጠቀሜታ ማህበረሰቡ ክዋኔውን መልሶ እያየው አስተያየት እንዲሰጥበት በማስቻሉ አንድም የተሰበሰበውን መረጃ ትክክለኝነት ያረጋግጣል፤ የጎደለም ካለ ለማሟላት ያስችላል። በሌላ በኩል ደግሞ ማህበረሰቡ የራሱን ምስል በክዋኔው ሲሳተፍ መልሶ በማየቱ ውስጣዊ ደስታን ከማሳደሩም በላይ በአጥኚው ላይ ያለውን ዕምነት በማጎልበት ድጋሚ ሌሎች መረጃዎችን ለመስጠት ይነሳሳል። ከተቻለ ደግሞ አንዳንድ ምስሎችን/ ፎቶግራፎችን አሳትሞ መስጠቱ ገንዘብ አስለምዶ መረጃን በብር ለመግዛት የሚደረግን አጉል ጥረት በማስቀረት ጥሩ የምስጋና ማቅረቢያም ሊሆን እንደሚችል ታይቷል። በተጨማሪም በአንድ አካባቢ የተቀረፀን ክዋኔ ለሌሎች አካባቢዎች በማሳየት እዚህኛውም አካባቢ ተፈላጊ መረጃዎችን በቀላሉ ለማግኘት እንደሚቻል ትምህርት ተወስዷል።

## 4.3. የጥናቱ አካሄድና አተናተን ዘዴዎች

ማንኛውም ዓይነት የባህል መረጃ ከመስክ ከተሰበሰበ በኋላ የተገኘውን መረጃ አደራጅቶ የመተንተን ሥራ ከአጥኚው በዋነኛነት የሚጠበቅ ጉዳይ ነው:: የሚደረገው ትንታኔ የጠበቀ እንዲሆን ደግሞ መረጃው ታስቦበትና በቂ ዝግጅት ተደርጎበት የተሰበሰበ መሆን ይኖርበታል:: እንዲሁ እንደተገኘ በስሱ የሚሰበሰብ መረጃ ለትንታኔ ሲዘጋጅ የጠለቀና የጠበቀ ትርጉም ያለው ትንታኔ ለማድረግ ካለማስቻሉም በላይ ትንታኔው እንዲሁ ላይ ላዩን የሚደረግ ገለፃ ብቻ ይሆናል:: ይህንንም Bronner እንደሚከተለው ገልፀውታል:: "…Naive analyses can result from inadequate or inaccurate identification." (Bronner, 2007, 70)

ከመስክ የተገኘን የባህል መረጃ በሁለት መልኩ ልንገልጸው እንደምንችል ምሁራን ያስረዳሉ:: (Schoemaker,1990, p8, Geertz,1973,p6, Lewandowski,2001,p6) አንደኛው ስስ ገለፃ (Thin description) ሲሆን የታየውን ወይም የተሰበሰበውን መረጃ እንዳለ ከላይ ከላይ መግለጽ ማለት ነው:: ሁለተኛው የዳጎሰ (Thick description) የሚባለው ገለፃ የተገኘውን መረጃ ትርጉም በሚሰጥ መልኩ በጥልቀት መተንተን ማለት ነው:: Lewandowski የሚተነተኑትን የፎክሎር ነገረ ይዘቶች (Texts) ራሳቸው ከመነሻው ስስና የዳጎሱ ሊሆኑ እንደሚችሉ በመጥቀስ "Planar and Deep texts" በማለት ገልፆአቸው የሚደረገውን ትንታኔ ስስነትና ጥልቀትም ሊወስኑ የሚችሉ መሆናቸውን ያስረዳል:: ጥልቅ ትንታኔ የሚባለውም ለአጠቃላይ ባህላዊ ክንውኑ ፍቺ መስጠት የሚችልን ትንታኔ እንደሆነ ያስገነዝባል:: (Lewandowski,2001,p6)

በባህል ጥናት ጥሩ ትንተና የሚባለውም የተገኘውን መረጃ ይዞ የዳጎሰ ትንተና (Thick description) የተደረገ እንደሆነ ነው፡፡ የዳጎሰ ትንተና ለማድረግ ደግሞ መረጃው ገና ከመነሻው እንደሚገባው መሰብሰብ ይኖርበታል፡፡ ይህ ማለት ደግሞ አጥኚው መረጃ በሚሰበስብበት ጊዜ ለሚሰበሰበው ፎክሎር ነገረ ይዘት (Text)፣ ለክዋኔ አውድ (Context) እና ነገረ ሁኔታ (Texture) ትኩረት ሰጥቶ መረጃውን መሰብሰብ ይኖርበታል፡፡ (Schoemaker,1990, p7) እነዚህ ጉዳዮች በውል ከተጤኑ መረጃውን በበሰለ መንገድ ለመተንተን አይቸግርም፡፡

ስለ አንድ ማህበረሰብ ባህልና ከልማት ጋር ያለውን ቁርኝት ለማጥናት በቅድሚያ የማህበረሰቡን ዋና ዋና ባህላዊ መልኮች በጥልቀት ማጥናትን የግድ ይላል፡፡ ጥናቱንም አስተማማኝና ወጥ ያደርገዋል፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት ሰፊ መረጃዎችን በጥልቀት በመሰብሰብ የገለፃና የትንተና ዘዴዎች ከጥቅም ላይ በማዋል የቀረበ ነው፡፡ ይህም የባህሉንና የልማቱን ቁርኝት ከማንሳት በፊት ስለብሔረሰቡ አጠቃላይ ባህል መረዳት ጠቃሚ በመሆኑ የብሔረሰቡን ዋና ዋና መገለጫዎች፣ የህይወት ዑደቶችና ሀገረሰባዊ ልማዶች የሚገልፁት ሁለት ምዕራፎች (በምዕራፍ 5 እና 6) በቅድሚያ ቀርበው ስለ ብሔረሰቡ ባህል አጠቃላይ ገፅታ ግንዛቤ እንዲኖር ያደርጋሉ፡፡ እዚህ ላይ ከጥቅም ላይ የዋለው ዘዴ ባህሉን እንዳለ መግለፅ እንጂ ትንታኔ ማድረግ አይደለም፡፡

ቀጥለው የሚመጡት ሁለት ተከታታይ ምዕራፎች (ምዕራፍ 7 እና 8) ደግሞ ተሰብስበው ከተደራጁት አጠቃላይ የብሔረሰቡ ባህላዊ መረጃዎች በመነሳት ለአካባቢው ልማት ያሉ አሉታዊና አዎንታዊ ባህላዊ ሁኔታዎች ከላይ ከተጠቀሱት ቲዎሪዎች ጋር በማገናዘብ በጥልቀት ተተንትነው የቀረቡባቸው ናቸው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞም ባህሉን ራሱን በማልማት ልማቱን ማፋጠን እንዴት እንደሚቻል አመላካች ሃሳቦችም ይቀርባሉ፡፡ ከጥናቱ በተገኙ ውጤቶች ማጠቃለያነት በመነሳትም ወደፊት ማን ምን ማድረግ እንዳለበት በመጠቆም ጥናቱ ይደመደማል፡፡


በርታ

# ምዕራፍ አምስት

## 5. የበርታ ብሔረሰብ ዋና ዋና ባህላዊ መልኮች

የጥናቱ ዓላማ የሆነው የበርታ ብሔረሰብ ባህል ለአካባቢው ልማት ያደረገውን አስተዋጽኦ ወይም ተፅዕኖ ለመመርመር ከመነሳት በፊት በቅድሚያ የማህበረሰቡን ባህል በጥልቀት ማጥናት ተገቢ ነው:: በመሆኑም ለጥናቱ በስፋት በግብዓትነት የሚያገለግሉት የብሔረሰቡን ባህል አጠቃላይ ገፅታ የሚያሳዩ ባህላዊ እሴቶች በጥቅሉ በቅድሚያ ይዳሰሳሉ:: ለአቀራረብ እንዲያመችም የበርታ ብሔረሰብ ማህበረ ባህላዊ (Socio cultural) ህይወትን የሚያመላክቱ ጉዳዮች በዚህ ምዕራፍ ይቀርባሉ::

የአንድ ማህበረሰብ ማህበረ ባህላዊ (Socio cultural) ህይወት መገለጫዎች ከሌላው የሚለዩበት ጉዳዮች የሚጀምሩት የዚያ ማህበረሰቡ አባላት በግልም ሆነ በጋራ ከሚለዩባቸው የራሳቸው የሆኑ መስተጋብሮች ነው:: ከግለሰቡ አካላዊ አቋም፣ አለባበስና አጋጊያጥ፣ አመጋገብ፣ አነጋገር (ቋንቋ) ብንነሳ አንድን ሰው በማየት ብቻ ከየትኛው ብሔረሰብ እንደሆነ ለመለየት የሚያስችሉ የተለያዩ ባህላዊ መገለጫዎች አሉ:: የበርታም ብሔረሰብ የራሱ ባህላዊ መገለጫዎች አሉት:: እነዚህም በዚሁ ክፍል ይቀርባሉ::

### 5.1. የበርታ ብሔረሰብ መልክና አለባበስ

በርታዎች በአካላዊ መልካቸው፣ በአለባበስና በአጋጌያጣቸው፣ በምግብ አሠራርና አመጋገባቸው፣ በእንግዳ አቀባበላቸው ከሌላው ብሔረሰብ ተለይተው ይታወቃሉ:: እነዚህ መለያዎቻቸው  የጥናቱ ግብዓት ስለሆኑ ቀጥለው ቀርበዋል::

### 5.1.1. አካላዊ መልክ

የአብዛኞቹ በርታዎች ቀለም በጣም ጠቆር ያለ ሲሆን በሰውነት ቀጫጭኖችና ረጃጅሞች ይበዙበታል፡፡ ፊታቸው ላይ በሚያደርጉትም ባለሦስት መሥመር የትልትል ምልክት በቀላሉ ተለይተው ይታወቃሉ፡፡ ምልክቱን ሴቶቹም ሆኑ ወንዶቹ በግራና ቀኝ ጉንጮቻቸው ላይ በስለት በመተልተል ያደርጉታል፡፡ ምልክቱ አራት ዓይነት ነው፡፡ አንደኛውና በአብዛኞቹ በርታዎች ፊት ላይ የሚገኘው በሁለቱም ጉንጮች ላይ ከላይ ወደታች ቀጥ ብሎ የሚወርድ ሦስት ሦስት መስመር ነው፡፡ ሌሎቹ የእንግሊዘኛውን የቲ (T) እና የኤች (H) ፊደል ቅርፅ የያዙ ሲሆን አራተኛው  የክብ ምልክት ቅርፅ ያለው ነው፡፡ በርታዎች ምልክቱን ከጥንት ጀምሮ የሚጠቀሙበት ሲሆን ከመነሻው የራሳቸውን ሰው ከሌላው ለመለየት በሚል ምክንያት እንደተጀመረ መረጃ ሰጪዎቹ ያስረዳሉ፡፡

> ድሮ ጦርነት በጦርና በጎራዴ በነበረበት ሰዓት የአንዱን ጎሳ ከሌላው የሚለይ ምልክት ባለመኖሩ ሳይቀድመኝ ልቅደም በሚል የራሱን ጎሳ አባል መግደልና እርስ በእርስ መፋጀት ስላስከተለ ለመለያ እንዲሆን ምልክቱን ማድረግ ተጀመረ፡፡ በተጨማሪም ከሌላ አካባቢ የሚመጣና የሚሰልል ሰው ይኖራል፡፡ መልኩም የእኛን የሚመስልና ቋንቋውን የሚችል ሆኖ የጠላት ወገን ሊሆን ስለሚችል እሱን ለመለየት እንዲቻል በሚል የተጀመረ ሆኖ እየቆየ ሲሄድ እንደጌጥ እየተጠቀሙበት አለ (አቶ አልሀሰን አብደዱራሂም፣ቃመ15/ 03/05) ፣ አባ አቶም፣ቃመ25/04/05)፡፡
>
> ከዚህ በተጨማሪም ለጀግንነት መገለጫነት፤ ራስ ምታትንም ለመፈወስና መልክንም ለማሳመር እንደሚጠቅም በሌሎች የማህበረሰቡ

አባላት ይታመናል::[17] የትልትሉን አሠራርም ሲገልጹ መጀመሪያ የሚተለተለው ቦታና ቅርፁ በአመድ ምልክት ይደረግና በጣም ስለት ባላት ትንሽ ቢለዋ አንዱን ጉንጭ በሦስት ምት ወደ ታች ያወርዱታል:: ከዚያ ጥቀርሻና ጨው ተጨምሮበት ይደመደማል:: በጣም የሚያመው በዚያን ጊዜ ነው ሲቆረጥ ግን ምንም አያምም:: ሁለት ቀን ካደረ በኋላም ጥጥ ያመጡና ይለጥፉበታል:: ከሰባት ቀን በኋላ ከቁስሉ ጋር የተያያዘውን ጥጥ ቅቤ ቀብተው ያነሱና እንደገና ሌላ ጥጥ ለጥፈዉ በሰባት ቀኑ ሲያነሱት የቁስሉ መስመር እየሰፋና እየጎደጎደ ሄዶ የማይጠፋ ምልክት ይተዋል:: አንዳንዱ ያመረቅዝና ወደ ሥር ከመጎድጎድ ይልቅ ወደ ላይ ተነፋፍቶ ሊቀር ይችላል:: ትልተላውን የሚያከናውኑት ሴቶች ሲሆኑ ተተልታዩ እንዳይፈራና እንዳይሸሽ ሴቶች በእልልታና በጭፈራ ያበረታታሉ (ወ/ሮ ቢተሚና፣ቃመ28/02/05፣ አቶ አልሀሰን አብዱራሒም፣ ቃመ15/ 03/05)::

በርታዎች በሁለት ጉንጮቻቸው ላይ በሚያደርጓቸው ትልትሎች ተለይተው ከመታወቃቸውም ሌላ እንደ ጌጥም ይቆጥሯቸዋል:: ይሄ ፊትን የመትልተል ባህል በብሔረሰቡ አዛውንቶች ፊት ላይ አሁን ድረስ አሻራው የሚታይ ቢሆንም ከጊዜ ወደ ጊዜ ግን እየቀረ መጥቷል::

---

[17] ራስ ምታትን ይፈውሳል በሚለው ሃሳብ አቶ አልሃሰን እንደማይስማሙ ገልፀውልኛል::

## 5.1.2. አለባበስና አጋጊያጥ

የወንዶቹ አለባበስ ከእስልምና ዕምነት ጋር የተያያዘ ሲሆን አጠር ያለ ሱሪና "ሱሪዋል" ረዥም ሰፊ ጀለቢያ "አልገቢ"፣ ኮፊያ ወይም ተለቅ ያለ ጥምጥም "አልኢማ" ያዘወትራሉ። አንዳንዶቹ በተለይም ወደ ከተማ አቅራቢያ ያሉት ሸሚዝና ሱሪ ይለብሳሉ። ቀለል ያለ ነጠላ ጫማ የሚያዘወትሩ ሲሆን ይነስም ይብዛም አቅማቸው የሚፈቅደውን ዓይነት ጫማ ያደርጋሉ እንጂ በርታ ሆኖ በባዶ እግሩ የሚሄድ ሰው ማየት የተለመደ አይደለም። በጥንት ጊዜ ጀምሮ በባህላዊ መንገድ የሚሰሩት "መርኩብ" የተባለ በእጅ ከቆዳ የሚሠሩትን ጫማ ሲጫሙ እንደኖሩም ይገለፃል።

ሴቶች ከብረት፣ ከነሃስና ከወርቅ የተሰሩ የአንገት፣ የእግርና የእጅ አምባሮችን በማድረግ ይዋባሉ። ልጃገረዶችን ጨምሮ በአፍንጫቸው ላይ ጌጦችን ያደርጋሉ። በአንገታቸው ላይ ጨሌዎችን ያደርጋሉ። ያገቡ ሴቶች ቀለመ ደማቅ የሆነ "ቶብ" የተሰኘ ባህላዊ ልብስ ይለብሳሉ። "ቶብ" አራት ሜትር ተኩል የሆነ ብትን ጨርቅ ሲሆን ሲለበስ ከውስጥ ፒጃማ ወይም ውስጥ ልብስ መሰል ቀሚስ ይለበስና "ቶቡ" አንዱ ጫፍ በአንድ በኩል ከብብት ውስጥ ተይዞ የሚተርፈው ሰውነት ላይ በመጠምጠም እስከ ራስ ጭምር በመሸፈን የሚጣፋ ነው። ያገቡ ሴቶች እግራቸውን ሂና መቀባትም ይፈቀድላቸዋል። በገጠሩ አካባቢ ያሉት ሴቶች ባብዛኛው ኮንጎ ጫማዎችን ጥቂቶቹ ደግሞ ነጠላ ጫማዎችን ያደርጋሉ። ህፃናት አልፎ አልፎ ባዶ እግራቸውን አይቻለሁ እንጂ በቆይታዬ በባዶ እግሩ የሚሄድ ሰው አላጋጠመኝም።





ፎቶ 4 የበርታ ሴቶች ባህላዊ አለባበስ

የበርታ ሴቶች በባህላዊ መንገድ እዚያው ከሚገኙ ተፈጥሮአዊ ከሆኑ ነገሮች የሚቀምሟቸው "ዲልካ"፣ "ሁምራ"፣ እና "ሰምሰም" የሚሰኙ ሽቶዎች፣ የሰውነት መታሻዎችና ባህላዊ ጢሳ ጢሶች አሏቸው። "ዲልካ" ለበርታ ማህበረሰብ የተለየ መዓዛ ያለው ሽቶ ነው። ከአሠራሩ ጀምሮ እስከሚቀመሙበት ነገሮች የራሱ የተለየ ሂደት አለው። የሚያገለግለው በአብዛኛው ለሴቶቹ ጢስ በሚገቡ ጊዜና ከጢስ ከወጡ በኋላ ታጥበው ገላቸውን ለመቀባት ነው። በጣም ጥሩ መዓዛ ያለው ቅባት ሲሆን ሚስት ያላቸው ወንዶችም አልፎ አልፎ ይጠቀሙበታል።

የዲልካን ጠረን የበርታ ወንዶች በቀላሉ ይለዩታል። ማንኛውም የማህበረሰቡ አባል ዲልካና ሁምራን ለመጠቀም ባለትዳር መሆን ይጠበቅበታል። የትዳር ጓደኛቸው በአካባቢው የሌለ፣ የሞተ፣ ወይም የፈቱ ሴቶችና ያላገቡ ልጃገረዶች "ዲልካ"ን መጠቀም አይፈቀድላቸውም። ምክንያቱም መዓዛው ስሜት ቀስቃሽ በመሆኑና ወንዱን ስለሚያነሳሳ ወይም እነሱ እንደሚሉት “ስለሚያሳስት” ነው።



ፎቶ 5. የበርታ ወንዶች አለባበስ

ይሄ ባህላዊ መታሻ የሚዘጋጀው በባህላዊ መንገድ በመሆኑ በግብዐትነት የሚያገለግሉትም አብዛኞቹ እዚያው በቅርብ የሚገኙና የሚዘጋጁ ባህላዊ ነገሮች ናቸው። የበርታ ወጣቶች ወንዶቹም ሆኑ ሴቶቹ በጉጉት ከሚጠብቁት ባህላዊ ክዋኔ አንዱ በሙሽርነታቸው ጊዜ በ"ዲልካ" መታሸትን ነው። በእነሱ አባባል ገላቸው ለመጀመሪያ ጊዜ "ዲልካ" የሚቀምሰው በሙሽርነታቸው ጊዜ ነው። ዲልካ የራሱ የሆነ ጥቅም እንዳለውም ይታመናል። ስለ አሰራሩ ሲቲና እንደዚህ ታብራራዋለች።

> …ዲልካ፣ እሚባል አለ፤ የእህል ዘር ነው፤ እሱ ተፈጭቶ ዱቄቱ ይቀርባል። ከዛ በኂላ እሱ በጭስ ነው እሚበስለው ዘጠኝ ቀን ስምንት ቀን ይፈልጋል እሱን ለማድረስ ያ የሰንደል እንጨት ይጨመራል ….ለመታጠን አንድ ክንድ ያህል ቦሎቅያ ወይም የጭስ ጉድጓድ ይቆፈራል። ከዚያ በኂላ "አልጠለሀ" የሚባል የእንጨት ዘር አለ፤ የዚህ ሁኖ ቀዩ ቀዩ የግራር እንጨት በጣም የቆየ ያረጀ እንጨት ነው እሚፈለገው ለሱ። ከዚያ ደግሞ የወተት ቅል የምናጥንበት አለ፤ ወይራ አይደለም፤ ሌላ አለ "ሀሹህር" ይባላል በበርትኛ….
>
> …የዲልካው ጠረን ላንቺ አይሸትሽም አጠገብሽ ለተቀመጠ ሰው ግን ሌላ ነው ይታወቃል። …ማንኛውም የበርታ ሴት ሆነ ወንድ ይህንን ባህል ያውቀዋል። ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮላት ሴቷ ማዘጋጀት የምትችልበት ሁኔታ ካለ ታዘጋጃለች። ባሏ አሁን <u>ያመው ይሆናል፤ ይደክመው ይሆናል፤ እንዲዝናና ማድረጊያ ነው።</u> ሰውነቱ የደከመውን ለማነቃቃት ምን ለማድረግ ነው እሚፈለገው እሱ። ስለዚህ ሁል ጊዜ ሴትየዋ ባሏን አክብራ ወዳ እምትኖር ከሆነ እሱ አይጠፋም ከቤቷ። ዲልካና ሁምራ ምናምን እምንለው ነገር <u>ባል</u>

> የሌላት ሴት አታደርግም፡፡ ባል የሌላት ሴት የማታደርግበት ምክንያት አንድ የፍላጎት ማነቃቂያ ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡ ስለዚህ እሷ ካደረገች ሌላ ወንድ ሊመኛት ነው እ.. ዲልካ ማድረጓ ደግሞ ሌላ ነገር እያደረገች መሆኑን አመልካች ነው ስለዚህ ትዳር የሌላቸው ሰዎች ራሳቸውን ከዚህ ነፃ ማድረግ ይፈልጋሉ፡፡ የፈቱ፣ ባላቸው በአካባቢው የሌለ፣ የሞተ ዲልካና ሁምራ አይጠቀሙምም፤ ለምን ወንዱ ውስጡ ሊያስብ ስለሚችል ፍራቻም ይሉኝታም ነው፡፡...አሁን ሁምራ ካደረግሽ ሁሉም የበርታ ወንድ ልቡ ይቆማል፡፡ ምን እንደሆነ አታውቂውም፤ ግን ስለሸተተው ነው፡፡ እኛ ዝም ብለን ተቀብተን እንሄዳለን፤ ግን የሆነ ወንድ ብታገኚ ይጨንቀዋል፡፡ ምን ሆኖ ነው እሚጨነቀው? ብለሽ ስትዪ ዲልካው ነው፡፡ ለምንድነው ይህን ሽቶ አድርገሽ የመጣሽው?[18] ብሎ እሚቆጣሽ ሁሉ አለ ሊመታሽ ሁሉ እሚነሳ ሰው አለ በቃ ቤተሰብ የሆነ በቃ ሊመታሽ ይነሳል... (ወ/ሮ ሲቲና አደም፣ ቃመ22/03/05፣ አፅንኦቱ የኔ ነው)፡፡

ማህበረሰቡ ስለባህላዊ መዋቢያው በሚሰጠው አስተያየት ዲልካ ሌላም ጥቅም አለው፡፡ ለወንዶች ድካምን ያስወግዳል፤ ሰውነትን ያፍታታል፤ ሴቶች እሱን ተቀብተው ቢታጠኑ የወገብ ቁርጥማትና የማህፀን ችግሮችን ያስወግዳል ተብሎ ይታመናል ፡፡

[18] ከሸርቆሌ አሶሳ ተመልሰን እራት ከምበላበት ሆቴል ሲቲና ተቀብታ መጥታ ከዚህ በፊት የማያውቃት ሰው ሱዳን የኖረ የትግራይ ተወላጅ የሆነ ሰው "አቤት ዲልካሽ!" ብሎ በመጎምጀት ሲያናግራት አጋጥሞኝ በሁኔታው እጅግ ተገርሜአለሁ፡፡

## 5.2. የምግብ አሠራርና አመጋገብ

በበርታ ለምግብነትና ለመጠጥነት የሚውሉ ነገሮች ባብዛኛው የአገዳ እህሎች፣ ጥራጥሬዎች፣ አትክልት፣ ፍራፍሬዎችና ሥራስሮች እንዲሁም እንስሳትና የእንስሳት ውጤቶች ናቸው። ለምግብ የሚውሉት ነገሮችና ማባያዎቻቸው በብዛት ከተፈጥሮኣዊ ነገሮች የሚሠሩ በመሆናቸው ከምግብነታቸው በተጨማሪ በሽታን የመፈወስ አቅማቸው እንደሚጎላ መረጃ ሰጪዎቹ ይናገራሉ (ወ/ሮ ሲቲና፣ ቃመ22/03/05፣ ወ/ሮ ቢተሚና፣ ቃመ28/02/05፣)።

ሻይና ቡና በመደበኛነት ተደጋግመው የሚጠጡ ሲሆኑ በርከት ያለ ስኳር በሁሉም ውስጥ ያስፈልጋል። የማህበረሰቡ የስኳር ፍቅርና ፍጆታ ከፍ ያለ ነው። የበርታ ሰው ካለ ስኳር ምንም ነገር መቅመስ አይፈልግም። ለስኳር ክፈል የተባለውን ሳያቅማማ ይከፍላል። ይሄ በመሆኑ ስኳር በተወደደ ጊዜ ለአንድ ኪሎ እስከ ሰባና ሰማኒያ ብር ሲጠየቅ ገዝቶ መግባቱ ይነገራል።

መጠጥን አስመልክቶ በርታዎች የእስልምና ዕምነት ተከታዮች በመሆናቸው አልኮልነት ያላቸውን መጠጦች የማይጠጡ ቢሆንም አልፎ አልፎ በባህላዊ መንገድ የሚዘጋጁ እነሱ **“ባፃ”** የሚሉት ጠላ እና አረቄ ከዘመናዊዎቹም ቢራና ሌሎች አልኮሎችን የሚጠጡ ሰዎች አሉ። ባፃ ከበቀሎ ወይም ከማሽላ የሚሠራና ብቅል ገብቶበት ከ3-7 ቀናት ተደፍድፎ ከቆየ በሁዋላ እየተቆነጠረ በውሃ በመበጥበጥ የሚጠጣ በደቡብ የሀገራችን ክፍል ቦርዴ በመባል የሚታወቀው ዓይነት አልኮልነት ያለው መጠጥ ነው።

**“አልሰልያ”** የሚሉት የመጠጥ ዓይነት ደግሞ በርከት ያለ የማሽላ ወይም የበቆሎ ብቅል በውሃ ተበጥብጦ ለ2 ቀናት ከቆየ በኋላ ውሃውን በማጥለል ቀሪውን ሊጥ ቀቅሎ ከጥላዩ ውሃ ጋር አቀላቅሎ በመክደንና በማሳደር እንደገና በስሎ የሚጠጣ ሲሆን ብዙ ጊዜ ለሠርግ፣ ለደቦ ሥራና ለበዓላት ድግስ ጥቅም ላይ የሚውል ነው።

ሌላው የበርታ መጠጥ "ባሳ" የሚባለው ሲሆን የማሽላ ወይም የበቆሎ ዱቄት ተነኩሮ ከኑግ ወይም ከሰሊጥ ጋር ቀላቅሎ ፈጭቶ በማስቀመጥ እየተቆነጠረ በውሃ በመበጥበጥ የሚጠጣ ሲሆን አልኮልነት የሌለውና ረሃብንም የሚያስታግስ ነው ይሉታል፡፡

**"ከርከዴ"** በአካባቢው የሚገኝ ቦሎቄ መሰል የበረሃ ፍሬ ዘፍዝፎ በማጥለል ጥላዩን ከስኳርና ከሎሚ ጋር ቀላቅሎ የሚጠጣ ሌላው የበርታ ባህላዊ መጠጥ ነው፡፡ ከርከዴ የሚባለውም ሻይ ከዚህ ፍሬ የሚዘጋጅ ነው፡፡

## 5.2.1. "ዱቃ" / ገንፎ

የበርታ ማህበረሰብ ዋነኛ ባህላዊ ምግብ ገንፎ ነው፡፡ ገንፎው የራሱ አሰራር ሲኖረው ለገንፎ የሚሆኑት የማሽላ ዘሮችም የተመረጡ ናቸው፡፡ ለገንፎ ማባያ የሚሆነው ቅቤ ሳይሆን ባህላዊ በሆነ መንገድ ተዘርቶ ከሚበቅል ተክል የሚሠራ "ቁንቁጽ" ነው፡፡

በበርታ ማህበረሰብ አባላት ወፍራም ሰዎች እምብዛም አይገኙም፡፡ ሴቱም ወንዱም በአብዛኛው ረጃጅምና ቀጫጭኖች ናቸው፡፡ መወፈር በማህበረሰቡ ስለማይደገፍ ባህላዊ ምግባቸው የሆነው ገንፎ እንዳያወፍር ዱቄት እየተነሰነሰ ወዲያው የሚሠራ ሳይሆን ተቦክቶ አድሮ የሚሠራ ነው፡፡ ማባያውም ተዘርቶ ከሚበቅለው ተክል የሚሰራ ነው እንጂ ገንፎ በቅቤ አይታወቅም፡፡ በርታ የሚያውቀው ገንፎ በ"ቁንቁጽ" ነው፡፡ "ቁንቁጽ" ደግሞ የራሱ ጥቅም አለው፡፡ ምግብ እንዲፈጭ ያደርጋል፤ ልብን ያቀዘቅዛል ወዘተ ተብሎ በማህበረሰቡ ይታሰባል፡፡



**ፎቶ 6 የበርታ ገንፎ በመገንፋት ላይ**

በበርታ ባህል ሦስት ዓይነት ገንፎዎች አሉ። የገንፎዎቹ ዓይነት እንደሚሠሩበት የእህል ዓይነትና እንዳሰራራቸው ይለያያል።

**"ዱቃ ቁዚ"፦** ለዚህ የገንፎ ዓይነት የሚሆነው "ስልምስቂ"/ ማሽላ ወይም "አሞሌ"/ በቆሎ ልሞ የተፈጨና ዱቄቱ እርሾ ገብቶበት ተቦክቶ ማደር ወይም ጠዋት ተቦክቶ እስከማታ መቆየት አለበት። እንደ አፍለኛ እንጀራ ማለት ነው። ከላይ በፎቶው እንደሚታየው የቦካው የገንፎ ሊጥ "ጋዚ" በሚሉት የገንፎ ማገንፊያ ጎድጎድ ያለ ድስት በ "አሸራምቤ"/ ማማሰያ እየተላገ ለአንድ ሰዓት ተኩል ከበሰለ በኂላ "አፍሪንቆ"/ ጭልፋ በመጠቀም በ "አልገዳ"/ ጣባ ላይ ወጥቶ ማባያው ቁንቁፅ ተደርጎበት ማገንፊያው ላይ ተጋግሮ የቀረው ስስ የገንፎ ቅርፊት/ "ጨሬ" ተልጦ ከላይ ይሸፈንበትና ይቀርባል። ጨሬውን መጀመሪያ አንስተው የሚበሉት ለምግብ ከቀረቡት ሰዎች መሃል በዕድሜ ገፋ ያሉት አዛውንት ናቸው።

**“ዱቃ ጠቀዱ”፡-** ዱቁቱ በጣም ሳይልም ሽርክት ሆኖ ብዙ ሳይቆይና ሳይቦካ ወዲያው ተለንቅጦ የሚገነፋ ሲሆን አብዛኛውን ጊዜ ለህፃናት የሚሰጥ ነው።

**“አሽንሽሪ”፡-** ለዚህኛው ገንፎ ከበቆሎና ማሽላ በተጨማሪ ስንዴም ከጥቅም ላይ ይውላል። ዱቄቱ ሽርክትና ወደ ቅንጬነት የሚያደላና ለማብሰል የሚፈጀውም ጊዜ ከሌሎቹ አንፃር ሲታይ ያነሰ ነው።



ፎቶ 7 ገንፎ በቁንቁፅ አቀራረቡና አበላሉ

ቅቤ ለገንፎ ብቻ ሳይሆን ለመቀባትም አያገለግልም በበርታ፡፡ በሌላ አካባቢ ሴቶች ወይባ ጢስ ሲገቡ ፀጉራቸውን ጨምሮ ገላቸውን የሚቀቡት ቅቤ ነው፡፡ የበርታ ሴቶች ግን ይህን አያደርጉም "ሰምሰም" ከሚሉት የሰሊጥ ዘይትና ከማር ሰፈፍ ወይም ሰም የሚያዘጋጁት ጠረኑ ውብ የሆነ ቅባት አላቸው፡፡ የሰውነታቸው ቆዳ እንዲከፈትና ጪሱ በመላ ሰውነታቸው እንዲሠራጭ ያደርጋል ብለው ያምናሉ፡፡

### 5.2.2. አል ኪሥራ/አልጉራሳ (ስስ እንጀራ)

"አል ኪሥራ" ከገንፎ ቀጥሎ በማህበረሰቡ ዘንድ የሚዘወተር ከቀይ ማሽላና ከበቆሎ የሚዘጋጅ  እንጀራ ነው፡፡ ዱቄቱ በወፍራሙ ተጠቅሎ ይቦካና ከ2-4 ቀን ድረስ ይቆያል፡፡ በሚጋገርበት ቀን "ጉጉሪና"/ አብሲት ይጣልና ይጨመርበታል፡፡ከዚያም በ "ጋሂ"/ ጎድጎድ ባለ የሸክላ ምጣድ ላይ በስሱ በእጅ እየተሰፋ ይጋገራል፡፡ እንጀራው በጣም ስስ ሆኖ ብዙ ብትክትክ ያለ አይን የለውም፡፡ ለእንጀራ ማባያ ቁንቁፅ፣ ከሥጋ፣ ከክክና ከቦለቂ  የተሠሩ ወጦች ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡

### 5.2.3. "አላብሬ"/ ስስ የእንጀራ ድርቆሽ

**"አላብሬ"፡-** እህሉ ልሞ ይፈጭና አብሽ፣ ጥቁር አዝሙድና ዝንጅብል አብረው ተወቅጠውና ደርቀው ይቀላቀሉበታል፡፡ ከዚያም ብቅል ተጨምሮበት ይቦካና  እንደ እንጀራው በስሱ ምጣዱን የመቀባት ያህል ይጋገራል፡፡ ቶሎ ቶሎም ስለሚደርቅ እያወጡ እንደ እንጀራ ድርቆሽ ተሰባብሮ ይቀመጣል፡፡ በውሃ ላይ በትንሹ በተን እየተደረገ ይጠጣል፡፡ "አላብሬ" በተለይ ከመንገድ ለገባ ሰው መጀመሪያ የሚቀርብለት ነው፡፡ መንገድ አድክሞትና ተጠምቶ የመጣ ሰው መጀመሪያ ውሃ ብቻውን ከጠጣ ልቡን ይሰብረዋል ተብሎ ስለሚታሰብ ውሃው ከእህል ዘር ጋር ተገናኝቶ መጠጣት አለበት፡፡ ስለዚህ አላብሬውን ውሃ ላይ በጥቂቱ በተን አድርገው እንዲጠጣው በመስጠት ጥሙን

እንዲቆርጥና ሰውነቱንም እንዲያቀዘቅዝ ያደርጋሉ፡፡ አላብሬ ለእንግዳ ብቻ ሳይሆን ውሃ ብቻውን መጠጣት የማይፈልግ ሰውም ስለሚጠቀምበት ሁሌም ተዘጋጅቶ ከቤት ውስጥ እንዳይጠፋ ይደረጋል፡፡ ለአደን፣ ለወርቅ ቁፋሮና ለመሳሰሉት ስራዎች ለረጅም ጊዜ ከቤቱ የሚርቅ ሰውም ለስንቅነት ያገለግላል፡፡ በበርታ ባህል ከነዚህ ምግቦች በተጨማሪ አልጉራሳ ቡቡዶ፣አልጅማት፣ ሴራሊያ የሚሏቸው ምግቦች አሉ፡፡

**"አልጉራሳ ቡቡዶ":-** ሊጡ በወፍራሙ ይቦካና በእጅ እየተገመተ በኮባ ወይም አከርዳ በሚሉት ሰፊ ቅጠል እየተጠቀለለ በምድጃ አመድ ውስጥ ይቀበርና ከላይና ከታች የእሳት ፍም እየለበሰ እንዲበስል ተደርጎ የሚቀርብ ነው፡፡

**"አልጅማት":-** ዱቄቱ ወዲያው ታሽቶ ይቦካና በዘይት የሚጠበስና ለቡና ቁርስ የሚቀርብ ከተማ ፓስቲ የምንለው ዓይነት ነው፡፡

**"ባንጉጉ":-** የሚባለው ቂጣ ደግሞ ወዲያው ተቦክቶ በስሱ ይጋገርና በትኩሱ ከሰሊጥና ከኑግ ጋር ተወቅጦ ለቡና ቁርስ ይቀርባል፡፡ ይህንንም እንደ አላብሬ ለስንቅነትም ይገለገሉበታል፡፡

**"ሴራልያ" (ሲልማይ እፉፉል) ንፍሮ:-** በርታዎች ጥራጥሬዎችን ቀቅለው የመመገብ ልምድም አላቸው፡፡ **ሴራልያ** ቦሎቄ፣ ባቄላ፣ ቦቆሎ፣ ማሽላና ሌሎች ጥራጥሬዎች በተናጠል ወይም አንድ ላይ ተቀቅለው የሚበላ ንፍሮ ነው፡፡

### 5.2.4. *ሥጋ* ነክ ምግቦች

**"አሽያ"/ በእሳት የሚጠበስ ዝልዝል ጥብስ:-** በርታዎች በአብዛኛው *ሥጋ* መመገብን በጣም ይወዳሉ፡፡ በተገኘው አጋጣሚ ፍየል አርደው በእሳት ጠባብሰው መመገብ ያዘወትራሉ፡፡ *ሥጋ*ውን ዘልዝለው በሚነድ እሳት ወይም በደንብ በፋመ ከሰል ላይ

በመጥበስ የሚበላውን ጥብስ **"አሽያ"** ይሉታል። ለማባያም በሎሚ የተለወሰ ቆጭቆጫና ያልበሰለ ቀይ ሽንኩርት፣ በማድረግ ትኩሱን እየቆረጡ ይመገባሉ።

**"አዱዱሽ"/ አሮስቶ:-** ይህ ፍየሉ ከታረደ በሁዋላ የሆድ ዕቃው ይበጣና ብልቱ ሳይቆራረጥ ከሥር እሳት በማንደድ እንደ አሮስቶ ተጠብሶ የሚበላ ነው። ብዙ ጊዜ ለድግሥና ለበዓላት ጊዜ ይዘጋጃል።

**"አልመራራ":-** የታረደው ከብት አንጀት፣ ጉበት፣ ጨጓራ፣ ሳምባ፣ ይታጠብና በድስት ተጥዶ ይቀቀላል። ቶሎ እንዲበስል አግምባኝ የሚሉትን ቅጠል ይጨምሩበታል። እነሱ "አልመራራ" ይሉታል። ሲበስል ወጥቶ ይከተፍና "ከለዋን"/ ሀሞት ከበርበሬና ጨው ጋር ተለውሶ በፍቅር ይበላል። ዱለት ከሚባለው ምግብ ጋር ይመሳሰላል።



ፎቶ8 "አሽያ" ዝልዝል ጥብስ

ከዚህ በተጨማሪ ሥጋን በድስት ጠብሰው **"ሁኡ ማኢ ሃርሜጋ"** በሚሉትና በድስት ቀቅለው **"ሁኡ ማኢ እፉፉሉ"** በሚሉት መልኩ (ጥብስና ቅቅል ልንለው እንችላለን) ይመገባሉ:: ዕንቁላልና ዶሮንም ጠብሰውና ቀቅለው የመመገብ ባህል አላቸው::

ከአትክልት ድንች፣ ስኳር ድንች፣ "**አትሚሽ**"/ ዱባ መሰል ፍሬ፣ ቀይሳ/ የእንሰት ሥር፣ ይመገባሉ:: በአካባቢው ማንጎ በብዛት ስለሚበቅል በደረሰ ጊዜ አዘወትረው ይመገቡታል::

የበርታ ወንዶችና ሴቶች አንድ ላይ አይመገቡም:: የአንድ ሰፈር ወንዶች ተሰብስበው ከቤት ውጪ በተሰራ "አል ከለዋ" በሚሉት ዳስ ውስጥ ከየቤታቸው የተላከላቸውን ምግብ በጋራ የሚመገቡ ሲሆን ከሚስቶቻቸው ጋር አብረው ለምግብ መቅረብ ነውር ነው:: ህፃን ልጅ እንኳን ቢሆን ሰባት ዓመት ከሞላው ቤት ውስጥ አይመገብም፤ ከወንዶቹ ጋር ይቀላቀላል:: እንግዳ ካለና ወንድ ከሆነ የሚስተናገደው እዚያው ከወንዶቹ ጋር ነው:: ሴት ከሆነችም እቤት ከሴቶቹ ጋር እንጂ ከወንዶች ጋር አትቀላቀልም::

በአል ከለዋው ውስጥ የተገኙት ወንዶች በሙሉ ከቤታቸው ተላከም አልተላከም ቀድሞ የደረሰውን አብረው ይመገባሉ:: ሴቶቹም እንዲሁ ለባሎቻቸው ድርሻቸውን ከላኩ በኋላ ሁለት ሦስት ሚስቶች ከሆኑ ትልቋ ሚስት ቤት ወይም ሴት አዛውንቶች ቤት "ህምጺዩ" የየድርሻቸውን ይዘው በመሄድ በጋራ ይመገባሉ:: በግል ማዕድ መቅረብ በብሔረሰቡ አይታወቅም::

በበርታ የተወሰነ የምግብ ሰዓት የለም ከቤት ደርሶ በተላከበት ሰዓት በጋራ የመጣውን መመገብ ነው:: ድንገት ከሌላ ሰፈር የመጣ ሰውም ሲበላ ከደረሰ እጁን ታጥቦ መቅረብ ነው እንጂ እስኪጋበዝ መጠበቅ፣ አይ በልቼ ነው የመጣሁት ብሎ መግደርደር አልተለመደም:: መብላት ከፈለገ ይበላል፤ ካልፈለገም ይተዋል እንጂ አብሬአቸው ብቀርብ ምን ይሉኛል ብሎ ሆድን ከምግብ መከልከል በበርታ አይታወቅም:: ምናልባት ምግቡ ሊያልቅ ሲል የደረሰ ከሆነ ለእሱ ሌላ እንዲዘጋጅለት ይደረጋል::

## 5.3. በርታና እንግዳ

የበርታዎች ሌላው መለያ የእንግዳ ተቀባይነት ባህላቸው ነው። በማህበረሰቡ ዘንድ እንግዳ የመጣለት ሰው እድለኛ ነው ይባላል። የመጣው የማያውቀውም ሰው ቢሆን ባለእንግዳው እድለኛ እንደሆነ ይታመናል። የመጣው እንግዳ የባለ እንግዳው ብቻ ሳይሆን በአካባቢው የሚገኝ የማንኛውም በርታ የጋራ እንግዳ ነው። ስለእንግዳ አቀባበል የበርታዎች ተረት እንዲህ ይላል።

> በድሮ ጊዜ አንደኛው ሃብታም ሌላኛው ደሃ የሆኑ ሁለት ወንድማማቾች ነበሩ። ሃብታሙ እጅግ ስስታም ደሃው ደግሞ ያለውን የሚያካፍል ቸር ነበሩ። ከእለታት አንድ ቀን ሦስት ሰዎች ደሃው ቤት መጥተው "እባካችሁ አሳድሩን መንገደኞች ነን" ብለው ይጠይቁታል። ሰውየው በጣም ይደነግጥና "እንደምታዩት ቤቴ ጠባብ ነው ለእናንተ አይበቃችሁም፤ ይልቅ የወንድሜ ቤት ሰፊ ስለሆነ እሱ ጋ ሄዳችሁ ብትጠይቁት ይሻላል" ብሎ ቤቱን ያሳያቸዋል። እንግዶቹም ወደዚያው አምርተው "አሳድረን: ይሉታል። ወንድሙ ግን "ማሳደሪያ የለኝም" ብሎ ያባርራቸዋል። እንግዶቹም ወደ ደሃው ቤት ይመለሱና "ግድየለም ከውጪ በርህ ላይም ቢሆን እናድራለን፤ አንተ ብቻ ፍቀድልን" ሲሉት ወደ ሚስቱ ይገባና ጉዳዩን ያዋያታል። እሷም "አትጨነቅ እኛ መኝታ ላይ ያድራሉ፤ ለሚበሉትም አትሳቀቅ የእኛን እራት ይበላሉ፤ ለነገ አላህ ያውቅልናል።" ብላ ታፅናናውና ለሰዎቹ ያላቸውን ሰጥተውና አስተናግደው መኝታቸውን በመልቀቅ ያስተኟቸውና እነሱ ወጥተው ከውጪ ያድራሉ። ሲነጋ ባልና ሚስቱ ቀደም ብለው ተነስተው እንግዶቹን ለመሸኘት በሩን ሲከፍቱ እንግዶቹ ሄደው ቤታቸው ግን በወርቅ ተሞልቶ አገኙት ይባላል (እማ ፋጢማ አሊ፣ቃመ16/04/05፣ ተረት ዘጠኝ)።

የበርታ እንግዳ የማክበርና የመቀበል ባህል በተረቱም እንዲህ እየተረጋገጠ የሚሄድ ነው። አንድ ሰው እሱ ዘንድ እንግዳ እንደሚመጣ ካወቀ አስቀድሞ ለአካባቢው ሰው ሁሉ መናገር አለበት። ከዚያ ያ እንግዳ የሁሉም እንግዳ በመሆኑ እሱን ለመቀበል ሁሉም ይዘጋጃሉ። ይህ ሳይሆን ቀርቶ እንግዳው ከመጣ የመጣበት ሰውዬ ለምን እንዳልተናገረ ጥያቄ ይቀርብለታል። ድንገተኛ እንግዳ ካልሆነ በቀር ይህን አለመናገር ነውር ነው።

እንግዳው ወንድ ከሆነ እንደደረሰ የሚሄደው ወደ "አል ከለዋው" ነው። በባህሉ መሠረት “አሰላማሊኩም” ብሎ እጁን ከየሰዎቹ ትከሻ ወይም ደረት ላይ በማስነካት ወይም ትክሻ ለትክሻ ተቃቅፎ በመሳሳም ሰላምታ ይሰጣል። ሰላምታው በአንዴ የሚቋረጥ ብቻ አይደለም፤ ከቆየም በኋላ በጨዋታ መሃል እንደገና ተደጋግሞ ሊደረግ የሚችል ረዘም ያለ ሰላምታ ነው።

እንግዳው እንደተቀመጠ መጀመሪያ የሎሚ ጭማቂ፣ ወይም “አላብሬ” የተጨመረበት ውሃ አለዚያም ትንሽ እርሾ ጠብ ያለበት ውሃ ይቀርብለታል። እሱም ሰውነቱ በረድ ሲል የሚፈልገውን ወስዶ ይጠጣል። ይህ የሚሆነው ከሩቅ ቦታ የመጣ እንግዳ ውሃ ይጠማዋል ስለሚባልና እንደደረሰ ባዶ ውሃ ግጥም አድርጎ ሲጠጣ “ልቡ ቀጥ እንዳይል” ነው። ባዶ ውሃ “ደረት ይሰብራል” ይባላል (አቶ አልሀሰን አብዱራሒም፣ቃመ15/03/05፣ ወ/ሮ ሲቲና አደም ቃመ22/03/05)።

ከዚህ በኋላ ሁሉም ሰው ያለውን ይዞ እንግዳው ወደ አረፈበት "አልከለዋ" በመሄድ ያስተናግዱታል። ከቤት ሴቶች ቶሎ ብለው ገንፎ አገንፍተው ይልካሉ፤ ፍየል ይታረድለታል፤ ከየቤቱ የመጣውንም ምግብ በጋራ ያስተናግዱታል። እንግዳዋ ሴትም ከሆነች ሁሉም ከየቤታቸው ማስተናገጃዎችን ይዘው በመምጣት በጋራ በቤት ውስጥ ያስተናግዷታል።

…እንግዳ ደግሞ ይሻማሉ፤ አንድ ቀን መንጌ ሄድኩኝ፤ መንጌ ስሄድ ረመዳን ነበረ፤ አጎቴ ና አለኝ ሄድኩኝ አልከልዋ 30 አርባ ሰው አለ ሄድኩኝ ሜዳ ላይ ነው፤ እኔ ስሄድ ነገር ይነሳል፤ እንግዳዬ መጣ ብሎ አጎቴ ሲነግራቸው ለምንድነው ያልነገርከን? አንተ ወንድም ከእኛ በላይ የምትበልጠን ለምንድነው? አንተ እንግዳ ይዘህ ትመጣለህ አትነግረንም? እና ከመጥላት ሳይሆን እንግዳ ከመውደድ ያኔ እኔ ተሳስቷል እሱ እኔ በራሴ ነው የመጣሁት አልኳቸው ለማስታረቅ እኔ በራሴ መጣሁ እንጂ እሱ አልጠራኝም፡፡…

እና ይሄ የተለመደ ነው ከሱዳን ሳይቀር ሰው ቢመጣ የት ነው የአባ አብዱራሂም ቤት ብሎ ቀጥታ ይመጣል፡፡ ምንም ችግር የለም ሲመጣ እኔ ባልኖርም አል ከለዋው አለ ዕቃውን አውርዶ፣ አልጋ አለ፣ ፍራሽ አለ፣ ገብቶ እዚያ እየተስተናገደ ይጠብቀኛል፡፡ ቤተሰቦቼም ወዲያውኑ እንግዳው እንደመጣ ወዲያው ቡና ውሃ ይሰጣሉ፡፡ አይጠብቁኝም፡፡ እንደዚህ ካላስተናገደች ሴትየዋ ብቁ አይደለችም፤ ትፈታለች፤ እንግዳ ካላስተናገደች፤ አለሁኝ የለሁም እኔን ስሜን ጠርቶ የሚመጣ ካዲሳባ ይምጣ፣ ከየት ከመጣ በፈለገበት ሰዓት መስተናገድ አለበት፡፡ …እና የእኛ ባህል እንዲህ ነው ጦም የሚያድር ብቻውን የሚበላ የለም፤ ነውር ነው (አባ አብዱራሂም ሀሰን፣ ቃመ22/03/05)፡፡

ከላይ እንደተገለፀው በበርታ እንግዳ በረከት ነው፤ እንግድነቱም በፀጋ የሚቀበሉትና መስተንግዶውንም በደስታ የሚፈፅሙት፣ የአንድ ግለሰብ ብቻ ሳይሆን የጋራ ነው፡፡ እንግዳው ከእንግድነቱ ቀን ጀምሮ የፈለገውን ያህል ጊዜ ቢቀመጥ የመሰልቸት ባህሪ አይታይባቸውም፡፡ አባ ቤሎ የተባሉ የባህል መድሃኒት አዋቂ መረጃ እንዲሰጡኝ ቀጠሮ

ለመያዝ ወደሚኖሩበት ገጠር ስንሄድ ሲቲናን "እንግዳ ይዘሽ እንደምትመጪ አስቀድመሽ መንገር ነበረብሽ" ብለው ሲገስፅዋት ሰምቻለሁ። ለምንድነው ስል እኔ ለራሴ ጉዳይ መሄዴ ቀርቶ ጭራሽ ፍየል አርደው ስላላስተናገዱኝ ቅር እንዳላቸው ነግረውኛል።

ይህን የበርታ እንግዳ ተቀባይነት በመጀመሪያው ጉዞዬ መረጃ ለመሰብሰብ ሸርቆሌ ወረዳ ስገባ አይቻዋለሁ። የእኔን በእንግድነት መምጣት አሶሳ እያለን ሲቲና[19] አስቀድማ ተናግራ ነበር። የገባነው አምሽተን በመሆኑና ብዙ ሰዎች የዛን ቀን መግባታችንን ስላላወቁ ማታ መጥተው የጠየቁኝ ጥቂት ሰዎች ነበሩ። ሲነጋ ግን የሲቲና ቤት በሰው ተጨናነቀች። ፍየል ታረደ። ምግብ ተዘጋጀ። እኔ ክርስቲያን ስለሆንኩ ሙስሊም ያረደውን በልቼ አላውቅም። እነሱ ግን ለዚህ ብዙም ትኩረት አልሰጡም እንግዳቸውን ለማስተናገድ ሽር ጉድ ይላሉ።

እኔን ለማስተናገድ የመጡት ሰዎች ስብጥር ብዙ ነው። ከወረዳዋ የመንግስት ሹማምንት እስከ ህፃናት ድረስ ብዙ ሰዎች አሉ። ከነሱ ውስጥ አንዱ የወረዳዋ ምክትል አስተዳዳሪ ሲሆኑ ኢብራሂም ይባላሉ። ሌላኛው አፈጉባኤው ናቸው፤ ስማቸው አህመድ ነው። ወደ መታጠቢያ ቤት ደርሼ ተጣጥቤ ስመለስ እውጪ በተንተረከከ የከሰል ፍም ላይ ወንዶቹ ሥጋ እየዘለዘሉ ይጠብሳሉ፤ ሲቲና ማባያውን ታዘጋጃለች።

ሰላም ብያቸው ወደ ውስጥ ገባሁና ዕቃዎቼን አስቀምጬ ወደ እነሱ ወጣሁ፤ ሥጋውን አሰብኩት እነሱ ሙስሊም ናቸው። አርደው የሚጠብሱት ሥጋ ያው የሙስሊም ነው። እንዴት ልሆን ነው ልበላ? ወይስ ላልበላ? እነሱ አንዴ እንደ ብሔራቸው አባል ተቀብለውኛል፤ እንዴት ባደርግ ይሻላል? ነብሴ በመብላትና ባለመብላት እንደተወጠረች አስተዳዳሪውና አፈ ጉባኤው ትንሽ "ዘመናዊ" ናቸው ብዬ ስላሰብኩ ጥያቄ ሰነዘርኩ።

---

[19] ሲቲና መረጃ ሰጪዬ፣ አስተርጓሚዬ፣ መንገድ መሪዬ በአጠቃላይ ለጥናቱ መሳካት ከፍተኛ ድርሻ ያላት የብሔረሰቡ ተወላጅ ሴት ስትሆን፣ ዋና መኖሪያዋ አሶሳ ከተማ ሆኖ ሸርቆሌ የንግድ ቦታ ስላላት እዚያ ስሄድ እሷ ቤት ነበር የማርፈው፡፡

“ኢብራሂም” አልኩት ከሚጠብሰው ሥጋ ላይ ዐይኑን ሳያነሳ "አቤት!" አለኝ “አሁን ይሄ ሁሉ ዝግጅት የእስላም ሥጋ አብልተህ ልታሰልመኝ ነው?” አልኩት በቀልድ መልክ "አይ ስንቅነሽ እኔ በዘመኔ እስላምና ክርስትያን ፍየል አይቼም ሆነ ለይቼ አላውቅም፤ አንቺ የምታውቂ ከሆነ ግን ክርስትያኗን መርጠሽ አምጪና አርድልሻለሁ!" ሲለኝ ያልጠበቅሁት መልስ ስለነበር በጣም አሳቀኝ። ቀጠል አድርጎም "ይልቅ አንቺ ይሄንን በሽንኩርትና በቆጭቆጫው እያደረግሽ ብይ ወባ እሚባል በዞርሽበትም አይዞር፤ ከፈለግሽ አዲስ አበባ ስትደርሺ ክርስትና ተነሺ፤ አሁን በርታ ነሽ በቃ!" ሲለኝ እየሳቅሁ ተቀብየው ያለምንም መሸማቀቅ በላሁ፤ በጣም የሚጣፍጥ ጥብስ ነበር። እዚህ ውሳኔ ላይ ያደረሰኝ ለእንግዳ ያላቸው ክብርና እንክብካቤ ነው።

በርታዎች ከተሜነትን ቢለምዱ እንኳን ይሄ አብሯቸው ያደገ እንግዳ የማክበርና የመቀበል ባህላቸው አይለወጥም። በዚህ ሁኔታ ሸርቆሌ ከርሜ ወደ አሶሳ ስመለስ ረመዳን ገብቶ ነበር። የክልሉ ፕሬዘዳንት ሚስት በእንግድነት አሶሳ መምጣቴን ሰምተዋል። አሶሳ ብዙ ሳልቆይ ሸርቆሌ በመሄዴ ቤታቸው ጠርተው አላስተናገዱኝም ኖሯል። በእኔ ግምት ግን እሳቸው ቤት መስተናገድ የሚገባኝ አይደለሁም፤ የሄድኩት ለራሴ ሥራ ስለሆነና የቀደመ ትውውቅም ስለሌለኝ እንግዳቸው መሆኔን አላሰብኩትም። እሳቸው ግን በርታ ስለሆኑ መጣችን ሲሰሙ እንግዳቸው መሆኔን አረጋግጠዋል። ተገቢውን መስተንግዶ ባለማድረጋቸው ቅር ተሰኝተው ኖሮ አሶሳ እንደገባሁ ለፈጥር ሰዓት ከአንድ ዘንቢል ሙሉ ልዩ ልዩ ምግቦች ጋር ይቅርታቸውን ጨምረው ሲልኩልኝ ያልጠበቅሁት በመሆኑ በጣም ደነገጥኩ። በስልክ ላመሰግናቸው ስሞክር ጭራሽ ጥፋተኛ እንደሆኑ ሁሉ ይቅርታ ሲጠይቁኝ ባህላቸው ዛሬም ድረስ አብሯቸው እንዳለ መሆኑ አስገረመኝ።

ከላይ በብዙ ማሳያዎች እንደቀረበው በርታዎች ተለይተው የሚታወቁባቸው በርካታ የሆኑ መለያ ያላቸው ሁሉን በጋራ የሚከውኑ፣ ፍቅርና አክብሮታቸውን ያለዋጋና ያለስስት የሚለግሱ፣ ዕውነተኛ እንግዳ ተቀባዮች ናቸው።

## 5.4. የበርታ ብሔረሰብና ሀገረሰባዊ ልማዶች

በአንድ ማህበረሰብ ባህል ውስጥ በጋራ ከሚታመንባቸውና በህብረት ከሚከወኑ የእለት ከዕለት ተግባራት ውስጥ ወቅትን ጠብቀው የሚከበሩ ባህላዊ ክብረ በዓላት፣ ባህላዊ መዝናኛዎችና ውድድሮች፣ ባህላዊ መድሃኒቶችና ልዩ ልዩ አምልኮዎች የማህበረሰቡ መገለጫዎች ናቸው:: የበርታ ብሔረሰብም የራሱ መለያ የሆኑ እነዚህን መሰል ሀገረሰባዊ ልማዶች አሉት::

### 5.4.1. ክብረ በዓላት

በበርታ ባህል ልጅ ሲወለድ ስም ለማውጣት፣ የወለደች ሴት የአራስነት ጊዜዋ ሲያበቃ፣ለግርዛት፣[20] ወዘተ የሚደረጉ ልዩ ልዩ ሥርዓቶች በተጨማሪ ከጥንት ጀምሮ የሚታወቁና የእርሻንና የአደን ጊዜያትን ተከትለው የሚከናወኑ ማህበረሰቡ በጋራ ወጥቶ የሚያከብራቸው ባህላዊ ሥርዓቶች ቀጥለው ይቀርባሉ::

#### 5.4.1.1. *የፌዳ ሥርዓት*

የበርታ ብሔረሰብ በተለይ የገጠሩ ኗዋሪ በጋራ ተሰብስቦ ከሚያከብራቸው በዓላት አንዱ የፌዳ ሥርዓት ነው:: ሥርዓቱ አሁን መንግሥት የእንስሳት አደንን በመከልከሉ አደኑ እየቀረ መጣ ቢባልም በገጠሩ አካባቢ አሁንም በመተግበር ላይ ነው::

በዓሉ የማህበረሰቡ አባላት በመሪያቸው[21] አማካይነት ተሰብስበው ጫካ በማቃጠል አውሬዎችን አድነው በጋራ እየበሉ እየጠጡና እየጨፈሩ የሚያከብሩት በዓል ነው:: በዓሉ በዓመት አንድ ጊዜ የሚከበር ሆኖ ከአደንና ከምርት መድረስ ጋር ይያያዛል:: መሪው

---

[20] እነዚህ በሚቀጥለው ምዕራፍ በዝርዝር ይቀርባሉ::

[21] መሪው በጥንት ጊዜ አጉሩ/ ንጉሱ ነበር አሁን ደግሞ በአካባቢው ተቀባይነት ያላቸው የአገር ሽማግሌ ናቸው::

የፌዳውን ቀን ወስኖ አስቀድሞ ለህዝቡ ሁሉ ያስነግራል። በዚህ ጊዜ ወንዶች ለአደን የሚሆናቸውን ቁሳቁሶች "ጡርንባሽ ባምብ"/ የተጠረበ የመጥረቢያ ቅርፅ ያለው እንጨት፣ "ባን"/ ጦር፣ "ሲኪኒ"/ ጨቤ ወይም ሜንጢና መሰል የአደን መሣሪያዎችን ያዘጋጃሉ። ጦሮቹ የፌዳው ወቅት እስኪደርስ ቤት ውስጥ ተሰቅለው ጢስ እንዲጠግቡ የሚደረግ ሲሆን ፌኤዳው ቀን ሲታወጅ ከተሰቀሉበት እየወረዱ ይዘጋጃሉ። ከሚዘጋጁት ጦሮች የአደን አዝማቹ/ "ኤዳ"ው ብቻ የሚይዘው መንታ ጦር "አሻንባኒ" የሚባለው ሲሆን ሌሎቹ የሚይዙት "ባን" የሚሉትን ነጠላ ጦር ይሆናል። ኤዳው በማህበረሰቡ መሪ የሚሾም የፌዳውን ሥርዓት የሚመራና እንደ ጦር አዝማችም የሚቆጠር የታወቀ ጎበዝ አዳኝ ነው። ሴቶች አዳኞቹ ተመርቀው ከመሄዳቸው በፊት የሚጠጡትን "ባፃ"/ ቦርዴና ምግብ ያዘጋጃሉ። ዝግጅቱም በመሪው ቤት አካባቢ ሆኖ የሚበላውንና የሚጠጣውን ማህበረሰቡ በጋራ ያዋጣል።

የፌዳው ቀን ዋዜማ የፌዳ ጡርምባ "ቡሉና" ሲነፋ ሁሉም ሰው ወደ መሪው መኖሪያ ይሰባሰባል። ሌሊቱን ሙሉ እየተበላና ባፃ ፎርቴ እየተጠጣ ሲጨፈር ይነጋል። ጎህ ሲቀድ በመሪው ትዕዛዝ የአደን አዝማቹ/ ኤዳው ጪስ ከጠገበ ሰንበሌጥ የተዘጋጀውን ችቦ አቀጣጥሎ የመጀመሪያውን እሳት ይለኩስና ሰደዱን በማቀጣጠል ወንዶቹ ወደ አደን ይሠማራሉ።

ለአደን የተሠማራው ሁሉ የቀናውም ያልቀናዉም የተገኘውን ይዞ ወደ ተነሳበት የመሪው መኖሪያ ተመልሶ ይሰባሰባል። ሴቶቹ መቀበያ ባፃ ፎርቴ አዘጋጅተው በእልልታ ይቀበላሉ። ከአደን የተገኘው ሁሉ እዚያው ይዘጋጅና ለሁሉም ታዳሚ ዕኩል መዳረሱን የአደን መሪው እያረጋገጠ ይታደላል፤ ይበላል፤ ይጠጣል፤ ይጨፈራል።

የፌዳ ሥርዓት ጫካውን በእሳት በመመንጠር ለበጋው እርሻ የሚዘጋጁበት፣ተበታትነው የነበሩ ሁሉ ተሰባስበው የሚገናኙበት፣ በጋራ አድነው ዕኩል ተካፍለው በልተው የሚደሰቱበት በመሆኑ ይህ ክብረ በዓል በብሔረሰቡ ዘንድ ትልቅ ግምት የሚሰጠውና በናፍቆት የሚጠበቅም ነው።

በበርታ ባህል በሌሎች የሀገራችን ክፍሎች እንደሚደረገው አዳኝ የተለየ የክብር ቦታ አይሰጠውም። በጋራ ይታደናል፤ የተገኘውን በለስ ከቀናውም ካልቀናውም ጋር ሆኖ ልዩነት ሳይኖር ለሁሉም ዕኩል መካፈሉ እየተረጋገጠ በጋራ ይበላል (አብዱልናስር አልሀሰን፣ቃመ16/03/05፣ አባ ሃሚድ ቶንኮሮ፣ ቃመ29/03/05)።

### 5.4.1.2. የ"ኢሮ" ወይም የ"አጹምጹም" በዓል

የ"ኢሮ" ወይም የ"አጹምጹም" በዓል ትኩረቱ በዓደን ላይ ሳይሆን ከእህል ምርቶች መድረስ ጋር የተያያዘ ነው። ክረምት አልፎ በጋ ማህበረሰቡ በነቂስ ወጥቶ በደስታ በጭፈራና በእልልታ የሚያከብረው ነው። ከበራው የሚጀመረው በጥቅምት ወር የመጀመሪያ ሳምንት ላይ ሲሆን እንደ አዲስ ዘመን መግቢያም ይቆጠራል። ለበዓሉም ዝግጅት ሁሉም ያመረተውን እህል፣ ፍየል፣ ዶሮ፣ ልዩ ልዩ ለምግብና ለመጠጥ የሚውሉ ነገሮች ከየቤቱ ይሰበሰቡና በማህበረሰቡ መሪ ቤት አጠገብ ዳስ ተሰርቶ የሚበላና የሚጠጣ ነገር ይዘጋጃል።



ፎቶ 9. የበርታ ሴቶች ተውበው በአጹጹም በዓል ላይ ታድመው

ሁሉም ሰው አዳዲስና ንፁህ ልብሱን ለብሶ በነቂስ በመውጣት ወደ ስፍራው ይሰበሰባል፡፡ የሙዚቃ መሣሪያዎች ዙምባራ (አዋዛ)፣ በሎ፣ በልድንጉሉ፣ አተንባ፣ አልተሉቃ፣ ክራር[22] የመሳሰሉት ሁሉ አንድም ሳይቀሩ ወጥተው ለጨዋታ ይዘጋጃሉ፡፡ ይበላል፤ ይጠጣል፤ ጭፈራው ምሽት ላይ ይጀመራል፡፡ በዚህ ወቅት የሚደረገውን ጭፈራ "አጹምጹም" ይሉታል፡፡ አባ ሙሳ እንደሚናገሩት መሬት ላይ በተለያዩ ጥልቀትና ስፋት ጉድጓድ ይቆፈርና እሱን በእጅ በማፈን ሲመቱት ልዩ ልዩ ድምፆች ያሰማል፡፡ የጭፈራውን ስም የወሰዱት ከዚሁ ድምፅ ነው፡፡ በአንዳንድ አካባቢዎች እንደ በዓሉም መጠሪያ ይጠቀሙበታል፡፡[23]

ጭፈራው የሚጀመረው ከምሽቱ አንድ ሰዓት ጀምሮ ሲሆን እስከ ንጋት ድረስ ይካሄዳል፡፡ ዱባ፣ አደንጓሬ፣ ጎመን፣ የቀርከሃ እምቡጥና የመሳሰሉት ለምግብነት የሚደርሱበትጊዜ ነው፡፡ ልዩ ልዩ አትክልት ዘሮች፣ ጥራጥሬዎች ሁሉ ከየቤቱ ይሰበሰቡና ንፍሮ ይቀቀላል፤ እንጀራም ከየቤቱ ይመጣል፤ ለሚጠጡ ሰዎች ተጠምቆ የተዘጋጀው ባፃ ፎርቴ ይመጣል፡፡ "የተሰበሰበውን እህል ዘንድሮ ያገኘነውን ለከርሞም አታጉድልብን ያመረትነውንም ባርክልን እየተባለ ይመረቃል" (አባ ሃሚድ ቶንኮሮ፣ ቃመ29/03/05)፡፡ ሁሉም ሰው ይበላል ይጠጣል ሲጨፍር ያነጋል፡፡ ሲነጋ ወደ ቤቱ ሄዶ አርፎ ደግሞ ለማታው ጭፈራ ተጣጥቦ ይመጣል፡፡ ወሩ ሊያልቅ አንድ ሳምንት ሲቀረው በየቀኑ ጨዋታው እየደመቀ ይሄዳል፡፡

በመጨረሻው ዓርብ ጠዋት እሳት የመወርወር ልማድ አለ፡፡ እሳት የሚወረውረው የአካባቢው ማህበረሰብ መሪ ነው፤ ሲነድ ካደረው እንጨት አንስቶ በየአቅጣጫው ይወረውራል፡፡ ፍቺውም ከዚህ በፊት በክረምቱ የማይበሉ የነበሩ አትክልቶችና

[22] የበርታ ብሔረሰብ የሙዚቃ መሣሪያዎችና የጭፈራ ዓይነቶች በጣም በርካታ ከመሆናቸውም በላይ ሰፊ ጥናት የሚያስፈልጋቸው ናቸው፡፡ በዚህ ጥናት የቀረቡት ከጥናቱ ጉዳይ ጋር በማያያዝ ብቻ እንጂ በስፋትና በጥልቀት ተጠንተው አይደለም፡፡

[23] አባ ሙሳ ባበከር፣ቃመ20/02/05፣አባ አልኑር መሀመድ፣ቃመ11/04/05፣ ቡውይመቃወብቻ22/02/05)

ፍራፍሬዎች መበላት ይችላሉ ማለት ነው። "መሪው ይሄን ሲያደርግ ብሉ ፈቅደናል ማለቱ ነው። ሳይፈቀድ ከተበላ ግን ህመም ያስከትላል ተብሎ ይታመናል። እንደሚበላው ነገር ሁሉ የአጹምጹም ጭፈራም በዚህ ወቅት ብቻ ነው የሚጨፈረው ካለወቅቱ ከተጨፈረ እግር ይሰብራል ተብሎ ይታመን ነበር። ይሄ እንደ አዲስ ዘመን መለወጫ ይቆጠራል" (አባ አልኑር መሀመድ፣ ቃመ11/04/05)።

ይሄ በዓል በየአካባቢው የሚከበር ሲሆን በየቀበሌውም የበርታን በርካታ የሙዚቃ መሳሪያዎች መጫወት የሚችሉ ሰዎች በመኖራቸው በእያንዳንዱ መንደር ራሱን የቻለ የሙዚቃ ባንድ አለ ለማለት ይቻላል። በዚህ ወቅት በሠፈሮች መካከልም የሙዚቃና የጭፈራ ውድድር ይደረጋል። ውድድሩ ዘፈኑንና ጭፈራውን ሳይቀዘቅዝና ሳያቋርጥ ህብር ፈጥሮ መጨረስ የሚችልና የማይችል የሚለይበት ነው።




ፎቶ 10. በኢሮ በዓል ወንዶች ዙምባራ (አዋዛ) ሲጫወቱ

ዙምባራ (አዋዛ) የሚባለው የትንፋሽ የሙዚቃ መሣሪያ ከቅልና ከቀርከሃ የሚሠራ ሆኖ "ዋዛሉ"፣ "ሙሻህር"፣ "ቡንየሬ"፣ "አቡንዱ"፣ "አሸሮ"፣ "አንዱኜጌ"፣ "አፀጉም"፣ "አጉንዱ"፣ "ዴሬም"፣ "ሁሩምባኔ" እና "ዳኔ" የሚባሉ በቅደም ተከተል ከትንሽ እስከትልቅ የሚደርሱ አሥራ ሁለት ዓይነት መጠንና የተለያዩ ዓይነት ድምፅ የሚያወጡና ህብር ፈጥረው በአንድ ላይ ሲነፉ ስሜትን ለጭፈራ የሚቀሰቅስ ከፍተኛ ድምፅ አላቸው(አባ ሃሚድ ቶንኮሮ፣ ቃመ29/03/05)። የበርታ ሰዎች ዙምባራ ሲሰሙ ከህፃን እስከአዋቂ ግልብጥ ብለው ለጭፈራ ይነሳሉ። የጥቅምት ወር የመጨረሻ አርብ ጭፈራው የበለጠ የሚደምቅበት ሆኖ የእሳት ውርወራውን መሪው ካከናወነ በኋላ የሥርዓቱ ፍፃሜ ይሆናል። ማህበረሰቡም በሙሉ ለዓመቱ በሰላም ያድርሰን በመባባል ወደየቤቱ ይመለሳል።

### 5.4.1.3. የዘመቻ ክተት ጥሪዎች

በርታዎች ጥንት በአጉሮቹ/ ንጉሶቹ ዘመን በአካባቢው ግጭት ሲነሳ ህዝቡን ለጦርነት እንዲሰባሰብ የሚያደርጉባቸው ከደጃዝማች አብዱራህማን ጀምሮ በአገልግሎት ላይ ሲውሉ ቆይተው አሁንም በመንጌ ወረዳ በከሸፍ ቀበሌ በሁለት ሀገር ሽማግሌዎች ቤት የተቀመጡ ዘመናዊና ባህላዊ መሣሪያዎች አሏቸው። እነዚህ መሣሪዎች ጥንት ለጦርነት ጊዜ የሚጠቀሙባቸው ቢሆኑም አሁን ጦርነት ስለሌለ ኢድና አረፋን ለመሠሉ ሃይማኖታዊ በዓላትና ታላላቅ እንግዶች ወደ አካባቢው ሲመጡ አውጥተው ይጠቀሙባቸዋል።

ብሔረሰቡ በጥንት ጊዜ በአካባቢው ግጭትና ጦርነት ተከስቶ ለውጊያ ሲሠማራ ጦሩን በማነቃቃት የሚመራው በዚሁ በእምቢልታ በመለከትና በከበሮ የሚታጀብ ባህላዊ የሙዚቃ ቡድን ነበር። የሙዚቃ መሣሪዎቹ አሁን ጦርነት ባይኖርም በበዓላትና ትላልቅ

ሰዎች ሲሞቱ እንደሚወጡ መሣሪያዎቹን ከአያቶቻቸው ጊዜ ጀምሮ ተካፍለው የሚያስቀምጡት አባ ናይል አሚር እና አባ ሃሚድ ናስር ይገልፃሉ፡፡

የሙዚቃ መሣሪያዎቹ ከቀርከሃ ጢሥ ጠግበው የተሠሩ ስድስት "ኡራ"ዎች/ እምቢልታዎች ፣ ሁለት ከበሮዎችና ሶስት "አልቡሪ"ዎች/ ጡሩምባዎች ናቸው፡፡ ስድስቱ እምብልታዎችና አንዱ እንጨት ተቦርቡሮ በቆዳ ተለብጦ የተሠራው ከበሮ በባህላዊ መንገድ እዚያው የተሠሩ ሲሆኑ ሦስቱ ጡሪምባዎችና አንዱ ከነሃስ የተሠራ ከበሮ ከውጪ እነሱ እንደሚሉት ከጣሊያን[24] በደጃዝማች አብዱራህማን አማካይነት የመጡ ወይም በስጦታ የተሠጡ ናቸው (አባ ናይልና አባ ሀሚድ፣ ቃመ14/04/05)፡፡

ጦርነት ወይም ግጭት በአካባቢው ሲከሰት ህዝቡና ለውጊያ የሚሠማራው ሠራዊት አማካይ ቦታ ላይ ይከትና የሙዚቃ መሣሪያዎቹ ወጥተው በባህላዊ ዕምነታቸው መሰረት በሬ ወይም ፍየል ታርዶ ከደሙ በለምለም ቅጠል መሣሪያዎቹ ላይ ይረጫል፡፡ የደሙ ተግባር መሣሪዎቹ ላይ የሠፈረውን እርኩስ መንፈስ አሷርፎ ማባረር ስለሆነ ትንሽ ቆይቶ ደሙ ከመሣሪያዎቹ ላይ ዘይት በተነከረ ጨርቅ ይወለወልና ይፀዳል፡፡ ከዚያ በኂላ ሁሉንም መሣሪያዎች ተጫዋቾቹ አንስተው ይቃኙና ቅድም ደም የተረጨበትን ቅጠል በያዘው ሰው መሪነት ሁለቱ ከበሮ መቺዎች፣ ቀጥሎ ሶስቱን ጡሩምባዎች የያዙት ሰዎች፣ ከዚያም ስድስቱ እምቢልታ ነፊዎች በቅደም ተከተል ተሰልፈው ህብር ፈጥረው እየተጫዋቱ ወታደሩንና ህዝቡን መርተው እዚያው ወደሚገኝ እድሜ ጠገብ ዋርካ ያመራሉ፡፡ ሴቶች በእልልታ እያጀቡ ሙዚቃውን ያደምቃሉ፡ አባቶች "አብሸር አብሸር!!" እያሉ ያበረታታሉ፡፡

[24] እነሱ በ1912 አካባቢ ከጣሊያን መጡ ይበሉ እንጂ መሣሪያዎቹ ላይ ለንደንና ፓሪስ የሚል መረጃ ተከትቦ ይታያል፡፡ ቀኑ ግን የደበዘዘ በመሆኑ ለመለየት አልተቻለም፡፡



ፎቶ 5 ዶሮው ታርዶ በእርጥብ ቅጠል የሙዚቃ መሣሪያዎቹ ሲቀቡ፣ ተጠብሶ ሲቆራረጥና ህፃናት ሳይቀሩ እንዲቀምሱት ሲታደል

በዚህ አውድ ላይ ያለው ረጅም ዘመን ያስቆጠረና ከጥንት ጀምሮ እንደነበረ የሚናገሩት ትልቅ ዋርካ አለ። በዋርካው ውስጥ ንብ አለ፤ የሙዚቃ ቡድኑ ወታደሩንና ህዝቡን እየመራ ወደ ዋርካው ሄዶ ሙዚቃውን እያሰማ ዋርካውን ይዞራል።

በጦርነት ጊዜ ወደዛ ሄደን ዋርካውን እንዞራለን ዋርካው ውስጥ የጦር መሣሪያችን ጥይታችን አለ። ጥይታችን ንቡ ነው ሙዚቃውን እያሰማን ዋርካውን ስንዞር በአካባቢያችን ችግር መከሰቱን፣ ጦርነት መኖሩን ንቡ ይገነዘባል። ከዚያም ይነሳና ከእኛ ቀድሞ ወደ ጦርነቱ ቦታ ይመራናል እኛም እንከተለዋለን። ውጊያው ላይ ስንደርስ ቀድሞ ጠላቶቻችንን ያጠቃልናል። ንቡ ሲነድፋቸው መሣሪያቸውን እየጣሉ ይሸሻሉ፤ ቢተኩሱ እንኳን አንድም ሰው አይመቱም። እኛም ሳንዋጋ ድል እናደርጋለን። ጠላት መባረሩንም ሲያረጋግጥ እየመራን ወደ ሰፈራችን እንመለሳለን። እሱም ዋርካው ውስጥ ይገባል፤ እኛም በደስታና በሆታ ወደቤታችን እንገባለን (አባ ሀሚድ፣ ቃመ14/04/05)።




ፎቶ 12 መሣሪያዎቹን እየተጫወቱ ወደ ዋርካው ሲሄዱ

ንቡ የሙዚቃ መሣሪያው ድምፅ የሰላምና የጦርነት መሆኑን ይለየዋል። በሰላም ጊዜ ለበዓላት ቀን ወይም በአካባቢው ትልቅ እንግዳ ሲመጣ መሣሪዎቹ ይወጡና ዋርካውን ዞረው ወደ በዓሉ ቦታ ይሄዳሉ። በዚያን ጊዜ ንቡ ካለበት አይነቃነቅም። ንቡ ያለበት ዋርካ እጅግ ትልቅና የተንዘረፈፈ ነው አርጅተው የወዳደቁ ትላልቅ ቅርንጫፎች አጠገቡ አሉ። በእርቀት ወደ ጫፉ ሊደርሱ ሲሉ የተንዠረገገ ማር ይታያል። ንቡ ግን አይታይም። ማህበረሰቡ የወደቁትን ቅርንጫፎች ፈልጦ አያነዳቸውም፤ ማሩንም ቆርጦ አይበላም። "ከንቡ ጋር ቃል ኪዳን አለን እሱ ጠባቂያችን ነው ማሩን ለምን እንነካበታለን? ከፈለግን ጫካ ሄደን ሌላ ማር እንቆርጣለን፤ የጥይታችንን ግን አንነካም፤ ቢንጠባጠብም እዚያው ይቀራል እንጂ አንነካውም ይሄ ቃልኪዳን ነው እሱ የእኛ ሃቅ አይደለም አንበላም"(አባ ሀሚድ፣ ቃመ14/04/05)።



ፎቶ13 በዋርካው ላይ የተንዠረገገው ማር

## 5.5. ሀገረሰባዊ ዕምነቶችና ባህላዊ መድሃኒቶች

በርታዎች በአሁኑ ጊዜ ሁሉም ማለት ይቻላል የእስልምና ዕምነት ተከታዮች በመሆናቸው በጥንት ጊዜ የነበሯቸው ባህላዊና መንፈሳዊ ዕምነቶች የደበዘዙ ቢመስሉም እስከ ዛሬ ድረስ የሚተገብሯቸው ሀገረሰባዊ ዕምነቶች በተለይ በገጠሩ አካባቢዎች ይታያሉ። በአካባቢው በሽታን የሚፈውሱ ነገን የሚተነብዩና ከሚመጣ ክፉ እንዲጠበቁ አስቀድመው የሚያስጠነቅቁ ብሎም መፍትሔ የሚሰጡ አዋቂዎች በቁጥር ጥቂት ቢሆኑም አሁንም ድረስ አሉ (ቡውይመቃሴብቻ18/02/05)።

እነዚህን አዋቂዎች "ኤሪ" በማለት ይጠሯቸዋል። ትርጉሙ ጠንቋይ፣ አዋቂ ማለት ነው። ኤሪዎች በጥንት ጊዜ እንደመንፈሳዊ አባት የሚታዩና የሚከበሩ፣ መጪውን የሚተነብዩና በባህላዊ መድሃኒት የሚፈውሱም ናቸው ተብሎ ይታሰቡ ነበር። በጊዜውም ለ"አጉር" (ለንጉሱም/ለመሪው) እንደ አማካሪም ሆነው ያገለግሉ እንደነበር ይነገራል። ንጉሱ ወይም መሪው ማንኛውንም ነገር ከማድረጉ በፊት የሚያማክረው እነሱኑ ነው። ይህን ለማድረግ በመቻላቸውም በማህበረሰቡ ዘንድ የተለየ ክብር ይሰጣቸዋል (ንጉስ፣2001፣ Tariku, 2002)።

በአሁኑ ጊዜ እነዚህ "ኤሪዎች" በቁጥር ጥቂት ከመሆናቸው የተነሳ አንዳንድ ከተማ አካባቢ ያሉ የብሔረሰቡ አባላት አሁን የሉም ቢሉም የጥንት ተግባራቸውን ግን ሲናገሩ ይሰማሉ። ለምሳሌ የኤሪዎችን ልዩ ችሎታ አቶ አልሃሰን አብዱራሂም ሆጀሌ እንዲህ ይገልፁታል። "አንድ ጊዜ ሼህ ሆጀሌ የደቦ ሥራ ሲያሰሩ አንድ ሰው ሥራ ሳይሠራ በወንበር ላይ ቁጭ ብሎ ይመለከታሉ፤ ምንድነው ለምንድነው የማይሠራው ብለው በቁጣ ሲጠይቁ ኤሪ እንደሆነ ይነገራቸዋል። ያስጠሩትና  እስቲ ችሎታ ካለህ አሁን በጋ ነው ዝናብ አምጣና ልመንህ ሲሉት ወደ ወንዝ ወርዶ ሲደግም በጠራራ ፀሐይ ዝናብ ይዘንባል። ከዚያ በኋላ ሥራውን አፅድቀውለት ቀለብ ከእሳቸው ዘንድ እንዲሠፈርለት አድርገዋል" (አቶ አልሀሰን አብዱራሒም ቃመ15/03/05)።

እነዚህ ኄሪዎች አሁን በብዛት የሚሠሩና የሚገኙ ባይሆንም ማህበረሰቡ በስፋት በሚኖርባቸው የገጠር አካባቢዎች ዛሬም እንደሚገኙ በመረጃ ስብሰባው ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል። በተለይ ዛርና ልዩ ልዩ የጥንቆላ ሥራዎች እንደሚከናወኑ በመቃዚን ቀበሌ ሴቶች ብቻ በተሳተፉበት የቡድን ውይይት አንስቼው ከሰባቱ ሴቶች አራቱ ባለውቃቢዎች እንደሆኑ አረጋግጠውልኛል። ክዋኔውንም እየቀለዱ ሊያሳዩኝ ሲሞክሩ የወ/ሮ ሲኪና ዛር እዚያው ተነስቶ ተለማምነው አረጋግተውታል (ቡውይመቃሴብቻ18/02/05)።

በዚሁ ቀበሌ አባ አደም ቤት ለቅሶ ለመድረስና የአያት ሞት ክዋኔን ለመመለክት በሄድኩበት ወቅት ዛር ያልተረጋጋላቸው ሁለት ሴቶች ለቅሶው ጭፈራ ላይ ሲያስጮሃቸውና ሌላ አንዲት ወጣት ደግሞ በአንድ ጎጆ ውስጥ ስትጮህ የዛሩን መንፈስ ለማረጋጋት ሌላ ነባር ባለውቃቢ መጥታ ስታረጋጋት በተገኘው አጋጣሚ የባለውቃቢዎችን መኖር ለማረጋገጥ ተችሏል።



ፎቶ 14 የአባ አደም ለቅሶ ላይ ውቃቢ ተነስቶባት የሚያስጮሃትን ሴት በጋራ ተሸክመው ወደ አረጋጊዋ ዘንድ ሲያደርሱ



ፎቶ 15 ያልተረጋጋ ውቃቢ የሚያስጮሃትን ወጣት ሌላዋ ባለውቃቢ እያረጋጋችላት፡፡

ያልተረጋጋ ዛር ለሚያስጮሃቸው ሴቶች ሌላዋ ባለውቃቢ በዕለቱ የምታደርገው ጊዜያዊ የማረጋጋት ሥራ ነው፡፡ ዛሩን በማባበልና በማስተዛዘን በቅርቡ ምሱ እንደሚቀርብለትና አስፈላጊው ሥርዓት ተከናውኖ በልጅቷ ላይ እንደሚሾም፣ ሥርዓቱ የዘገየውም በለቅሶው ምክንያት በመሆኑ ይቅርታ እንዲያደርግላቸው መጠየቅና ልጅቷን እንዳይጎዳትና እንዳያስጮሃት ተለማምና ማረጋጋት ነው፡፡ ይህንኑ ከፈፀመች በኋላም የምትጮኸው ልጅ ከእንቅልፉ እንደባነነ ሰው ነቅታ አካባቢዋን ስትቃኝ ወደ አዕምሮ እንደተመለሰች አረጋግጣ አይዞሽ ትንሽ አረፍ በይ ብላት ወደ ለቅሶው መስተንግዶ ተመለሰች፡፡

ኤሪዎቹ አሁን የሚያከናውኑት ተግባር መጪውን መተንበይና ልዩ ልዩ በሽታዎችን መፈወስ ነው። በዚህ ጥናት ቦሪዲ አሻጉድ የተባሉ አንድ ኤሪ በመረጃ ሰጪነት የተሳተፉ ሲሆን አገልግሎት በሚሰጡባቸው ሁለት ቦታዎች በመገኘትም በተሰበሰበው መረጃ ልዩ ልዩ በሽታዎች ኖሯቸው ፈውሳቸውን ፍለጋ የሚመጡ በርካታ ሰዎች መኖራቸው ተረጋግጧል።

ከዚህ ሌላ በበርታ የባህል መድሃኒት አዋቂዎች ሲኖሩ ለልዩ ልዩ በሽታዎች መድሃኒቶችን በባህላዊ መንገድ በማዘጋጀት ይሰጣሉ። እነዚህ ከኤሪዎቹ የሚለዩት ነገን የመተንበይ ሥራን ባለመስራታቸው ነው። በዚህ ጥናት አባ ቤሎ የተባሉ የባህል መድሃኒት አዋቂ ተሳትፈዋል።[25] ይህ ሁኔታ የሚያስገነዝበው ደግሞ የበርታ ብሔረሰብ ከእስልምናው ዕምነት ጎን ለጎን የሚተገብራቸው ሀገረሰባዊ ዕምነቶችና የሚጠቀምባቸው ባህላዊ መድሃኒቶች መኖራቸውን ነው።

[25] እነዚህን የኤሪ፣ የባለውቃቢዎችና ባህል መድሃኒት አዋቂ አሠራር ከዋኔ ኋላ በትንታኔው ላይ ስለሚታይ ላለመደጋገም በዝርዝር እዚያው ይቀርባል።

# ምዕራፍ ስድስት

## 6. ጋብቻ ልደትና ሞት በበርታ ብሔረሰብ

ለአንድ ማህበረሰብ መሠረቱና መነሻው ቤተሰብ ነው፡፡ ቤተሰባዊ ትስስር ሲያድግና ሲሰፋ ማህበረሰባዊ ትስስሩ ይፈጠራል፡፡ ቤተሰብ በጋብቻ ተመስርቶ በመውለድ ይለመልማል፤ ይጠናከራል፡፡ ከዚያ ደግሞ በሰው ህይወት አይቀሬ የሆነውም ሞት ይከተላል፡፡ እነዚህ የህይወት ዑደቶች ደግሞ እንደየማህበረሰቡ ባህል የተለያዩ ሥርዓትና ክዋኔ ስለሚኖራቸው የማህበረሰቡን ባህላዊ መልክ ለማወቅ ያስችላሉ፡፡ እነዚህ ባህላዊ መልኮች ከዚህ ጥናት ዓላማ ጋር ያላቸው ቁርኝት ሰፊ በመሆኑ በዚህ ርዕስ ሥር በቅደም ተከተል ይቀርባሉ፡፡

### 6.1. የጋብቻ ሁኔታ

በበርታ ብሔረሰብ ሦስት ዓይነት ጋብቻዎች አሉ፡፡ አንደኛው በሁለቱ ተጋቢዎች መካከል በሚደረግ ስምምነት ሲሆን ሁለቱ ተጫጪዎች በተለያዩ በዓላት ጭፈራዎች ላይ፣ በገበያ፣ በወንዝና በተለያ አጋጣሚዎች ተገናኝተው ከተዋወቁና ተጠናንተው ከተስማሙ በኂላ ለሴቷ ወላጆች ሽማግሌ በመላክ የሚፈፀም የጋብቻ ዓይነት ነው፡፡ ይህ የጋብቻ ዓይነት በማህበረሰቡ ዘንድ በብዛት የሚተገበር ነው፡፡

ሁለተኛው ደግሞ የሁለቱን ተጋቢዎች ስምምነት ሳይጠይቁ በወላጆች መካከል በሚደረግ ስምምነት ብቻ የሚፈፀም የጋብቻ ዓይነት ነው፡፡ ጋብቻው ወላጆች እርስ በርስ በመጠናናትና በመፈቃቀድ የሚወስኑት ስለሆነ ልጆችም የወላጆቻቸውን ፈቃድ ለማክበር ሲሉ ይፈፅሙታል፡፡

ሶስተኛው የጋብቻ ዓይነት አልፎ አልፎ ብቻ የሚፈፀምና “አሲፉ” የሚሉት የውርስ ጋብቻ የሚመስል ጋብቻ ነው፡፡ ይኸውም ታላቅ ወንድም ሲሞት ታናሽየው ሚስቱን የሚያገባበት ሁኔታ ነው፡፡ በዚህ ጋብቻ የሚቹ ሚስት ፈቃደኝነት ስለሚካተትበት ብሔረሰቡ ውርስ አይደለም ባይ ነው፡፡ “ውርስ አይደለም ውርስ ለንብረት እንጂ ለሰው አይሆንም፤ጋብቻው ሟችን ልጆች ባዕድ እንዳይበድላቸውና ንብረቱም የትም ተዘርቶ እንዳይቀር ታስቦ የሚደረግ ነው፤ የሟቹም ሚስት ብትሆን ፈቃዷ ተጠይቆና ጥሎሽ ተጥሎላት ነው የሚያገባት፤ ይሄም ሁሉ ደግሞ ሽማግሌዎች አይተው ሲወስኑ የሚፈፀም ነው”፡፡ (አቶ አልሀሰን አብዱራሒም፣ ቃመ15/03/05፣ ወ/ሮ ሲቲና አደም ቃመ22/03/05)

በርታዎች ከላይ የተጠቀሱት የጋብቻ ዓይነቶች ቢኖሯቸውም በዋነኛነት የሚፈጽሙት በተጋቢዎች ስምምነት የሚደረገውን ጋብቻ ነው፡፡ ጋብቻ ሲፈልጉ አብዛኛውን ጊዜ የሚጋቡት ከአጎትና ከአክስት ልጆች ጋር ነው፡፡ ጋብቻውን “ወተት ለወተት” ይሉታል፡፡ ይህንንም እርስ በእርስ እንዳይጨካከኑ፤ በተለይ ወንዱ በሴቷ ላይ ግፍና በደል እንዳይፈፅም፤ የሥጋ ዘመዱ ስለሆነች እንዲራራላት፤ በማሰብ ነው ይላሉ (አባ አብዱራሂምሀሰንና ወ/ሮ ሲቲና አደም ቃመ22/03/05)፡፡ ይህ መሠረቱ የእስልምናው ዕምነትም እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ አልፎ አልፎ ግን የሥጋ ዝምድና ከሌላቸውም ሰዎች ጋር ቢጋቡ የሚከለክል ነገር የለም፡፡

### 6.1.1. “ፌዳ” የጋብቻ ጥያቄ/ ማጨት

የቤተሰብ ትልቅ መሠረት የሆነው የጋብቻ ሥነ ሥርዓት ከሴቷ ቤተሰቦች ዘንድ ሽማግሌ በመላክ ይጀመራል፡፡ ሽማግሌ የመላኩ ሥርዓት “አዬንሺ“ ይባላል፡፡ ወንዱ በ”ሃርሻ” ጭፈራ ላይ፣ በገበያ ቦታ፣ ውሀ ስትቀዳ፣ ወይም በልዩ ልዩ ሥፍራ አይቷት የወደዳትን ልጃገረድ ቀርቦ ያናግራታል፤ ያጠናታል፡፡ የምትስማማው መሆኑን ሲያረጋግጥ ለአባቱ ሊያገባት እንደሚፈልግ ይነግረዋል፡፡ አባትየውም ጉዳዩን ያጤንና ሁለት ሽማግሌዎች ወደ ልጅቷ ቤት ይልካል፡፡

ሽማግሌዎቹም ወደ ልጅቷ ወላጆች አስቀድመው እንደሚመጡና ቤት እንዲጠብቋቸው መልክተኛ ይልኩና እንመጣለን ባሉት ቀን በጠዋት ይሄዳሉ። እንደደረሱም ሰላምታ ሰጥተው ወደ ቤት ይገባሉ። የልጅቷ ቤተሰቦች "ከቤት ጠብቁን ብላችሁ የላካችሁብን በደህና ነው?" ብለው ይጠይቃሉ። ሽማግሌዎቹም ይቆሙና "እንድንነግራችሁ አማን ስጡን" ይላሉ። "የአላህ አማንን ሰጥተናችኋል፤ ተቀመጡና ንገሩን" ይላሉ፤ ሽማግሌዎቹም አመስግነው ይቀመጡና "የመጣነው ልጃችሁን እገሊትን ለልጃችን ለእገሌ እንድትሰጡን ነው" ይላሉ።

አባትና እናት "ሰጪው አላህ ነውና ልጅቷም የእኛ ብቻ ስላይደለች እስቲ ከዘመድ አዝማድ እስክንማከር ጊዜ ስጡን" ብለው ከወር ወይም ከ15 ቀን በኋላ እንዲመለሱ ቀጠሮ ይሰጧቸዋል። በበርታ ባህል ወላጆች ለብቻቸው በሴት ልጃቸው ጋብቻ ላይ ውሳኔ አያሳልፉም። ልጅቷ የማህበረሰቡ ጭምር እንጂ የእነሱ ብቻ አይደለችምና። የጋብቻ ጥያቄው ሲቀርብ የአከባቢው አዛውንትና ዘመዶቿ ሁሉ ተሰብስበው በጠያቂው ሁኔታ ላይ ይወያያሉ። ለዚህም የሴቷ ወላጆች ቀን ቀጥረው ለዘመድ አዝማድ ያሳውቃሉ። በቀጠሮው ቀን ዘመድ ጎረቤት ተሰብስቦ የሚካሄድ ሥርዓት አለ።

> ሽማግሌዎች … በቀጠሮ ቀን ዘመዶችና ጎረቤቶች በሙሉ ይሰበሰባሉ ይነጋገሩበታል፤ እሚሆን ከሆነ በተደረሰበት ውሳኔ ይሰጣል አንዳንድ ጊዜ ምንድነው እሚያረጉት ልጁ የሚያጨው ልጅ በነበረበት ባደገበት ጊዜ ውስጥ ተወልዶ እስከ አሥራ ስምንት ሃያ ዓመት ድረስ እዚያው የኖረ ነው ያውቁታል አንድ ተሳስቶ ወይ ተጋፍቶ ወይ ዝም ብሎ አንድ ቀን ያጠፋው ካለ ያስታውሳሉ፤ አንድ ቀን ስሄድ በመንገድ ላይ ገፍቶኝ አለፈ፤ እና ይቀጣልኝ ይላል ለዚህ ነው እሚሰበሰቡ፣ ይቀጣልኝ፤ አንዳንዶቹ ደግሞ አንድ ቀን ገበያ ልኬው ወይ የሆነ ነገር እንደዚህ

> አልተላከልኝም፣ እና ይነሳል ማንኛውም የማይረቡም ቢሆኑ ይነሳሉ፤ እሚረቡም ይነሳሉ መጨረሻ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፤ የተባለውም እንትን ይቀጣል ከፈለገ መቶ ብር፣ ሃያ ብር፣ አሥር ብር እንደዚህም ይቀጣና ይወሰንለታል ማለት ነው (አባ አብዱራሂም ሀሰን፣ ቃመ22/03/05)::

መረጃ ሰጪው እንደሚሉት በጋብቻው ላይ የሚወስኑት የልጅት እናትና አባት ብቻ ሳይሆኑ ማህበረሰቡ በጠቅላላ ነው:: ልጁ ለትዳር ከመብቃቱ በፊት ማሟላት የሚኖርበት የማህበረሰቡ ሥነ ምግባር አለ:: ለአዋቂዎች መታዘዝ፣ መላላክ፣ ተገቢውን አክብሮትና ሰላምታ መስጠት፣ ወዘተ:: ይህንን ሥነ ምግባር አክብሮ ሳይተገብር ከቆየ ለጋብቻ ብቁ አይደለም:: የጋብቻ ጥያቄ ባቀረበ ጊዜ ማህበረሰቡ ተሰብስቦ ይጠይቀዋል:: የሠራው ጥፋት፣ የጣሰው ባህላዊ ህግ ካለ "ብቁ አይደለም" ብሎ ብቻ አንቅሮ አይተፋውም:: ጥፋቱን አውቆ ከጥፋቱ እንዲማር ይደረጋል:: ስለዚህ ቀድሞ ላጠፋው ጥፋት ተቀጥቶና ክሶ፣ ወደ ጥፋቱ እንዳይመለስ፣ ተመክሮና ተወቅሶ፣ጋብቻው ይፈቀድለታል:: ልጅት የማህበረሰቡ እንደሆነች ሁሉ እሱም የማህበረሰቡ በመሆኑ እነዚህን የማህበረሰቡን ወጎች መጠበቅ ግዴታው ነው::

የልጅቷ ቤተሰቦች ለሽማግሌዎች በሰጡት ቀነ ቀጠሮ ጋብቻውን እንደፈቀዱ ከገለፁ በኋላ ለመደገሻ “ምህር” እና ጥሎሽ “ሳዳቅ” የሚሆን ብር እንዲከፍሉ ይጠይቃሉ:: ሽማግሌዎቹ የልጅቷ ቤተሰቦች የጣሉባቸውን ክፍያ እንዲቀንሱላቸው ይደራደራሉ:: “ሰው በገንዘብ አይመዘንም የተጣለብን ምህር ይከብደናል ቀንሱልን ብለው ይደራደራሉ” (አባ አልሃሰን አብዱራሂም፣ ቃመ15/03/05፣ አባ አልኑር አበደላ፣ ቃመ14/04/05):: ከተስማሙ በኋላ ገንዘቡን ይዘው እንዲመለሱ ቀጠሮ ተቀብለው ይሄዳሉና በቀጠሮው ቀን የተባሉትን ይዘው ይመጣሉ:: ይሄ የመጀመሪያ ጥሎሽ "አል በረካ" ይባላል::

### 6.1.2. "አል በረካ"/ የመጀመሪያ ጥሎሽ

“አል በረካ” ለሠርጉ መደገሻና ለልጂቷ የሚከፈል የመጀመሪያ ጥሎሽ ነው። ሽማግሌዎች በቀጠሮው ቀን የታዘዙትን ይዘው ሲመጡ መጠነኛ የእንግዳ ማስተናገጃ ይዘጋጅና ፍየል ታርዶ ሙሽራው ይመረቃል። “የመጀመሪያ በር መክፈቻ ነች እሷ በፊት የነበረው ምንድነው ማር ይቀርባል፤ ጨው ይመጣል፤ ማለት ለምግብና ለምን የሚሆን ነው ይሄ የተወሰነ ማሩም ይበጠበጥና በሳህን ተደርጎ ይጠጣል፤ ብዙ ጊዜ በስኒ በስኒ በማንኪያ በማንኪያ ተደርጎ ይበሉታል፤ ማር ይበላል በቃ ደስ ይላቸዋል ትልቅ ነገር ሆኖ ማለት ነው” (አባ አልኑር አብደላ፣ ቃመ14/04/05፣ ወ/ሮ ሲቲና አደም ቃመ22/03/05)።

በድሮ ጊዜ ይሄ የመጀመሪያ ጥሎሽ በእህል፣ በማር፣ በፍየልና በሌሎች የምግብ ዓይነቶች የሚከፈል ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ ተቀይሮ በገንዘብ እንደሚከፈል መረጃ ሰጪዎቹ ይናገራሉ። ክፍያው ብቻ ሳይሆን የድግሱም መልክ መቀየሩን ከእሳቸው የድሮ ልምድ በመነሳት አባ ቤሎ እንደሚከተለው ይገልፁታል። “ድሮ እህል ነው የወሰድኩት ገንዘብ አልሰጠሁም አሁን አምስት ሺህ፣ አስር ሺህ፣ ሰባት ሺህ፣ ጥሎሽ ይጠየቃል ልዩነቱ እሱ ነው፤ ሁለተኛ ፍየል ድሮ ሁለት አሁን አምስት ስድስት ነው እሚጠየቁት ብዙ ነው፤ ድሮ ልዩነቱ ጠላ ተጠምቆ … በቃ በጠላ ብቻ ሰው ድብልቅልቅ እስከሚል እስከሚሰክር ነበር አሁን ግን ጠላ የለውም ጭፈራ ብቻ ነው፤ ሰው ወደ ቤቱ ቶሎ ይመለሳል ድሮ ሳምንት ተብሎ ነበር ድግስ አሁን የለም” (አባ ቤሎ አዲቴ፣ ቃመ02/03/05)።

የ “አል በረካ” ው ድግስ ከተበላ በኋላ ሙሽራው ቀጥሎ ማምጣት ያለበትን ዋና ጥሎሽ ቁጭ ብለው ይወስናሉ። ለሙሽሪት እናት አንድ ጣቃ ማሙዲ ወይም አቡጀዲ፣ ለአሳዳጊዋ ወይም ለሞግዚቷ 4 ሜትር ጨርቅ ወይም ቶብ፣ለሙሽሪቷ የተሟሉ አልባሳትና ጌጣ ጌጦች፣ ለዋናው ድግስ የሚሆን ብር፣ ፍየል፣ በግ፣ ወይም በሬ እንዳቅሙ፣ ለማብሰያ ዘይት፣ ሽንኩርት፣ በርበሬ፣ ጨው፣ ቡና፣ ስኳር ሁሉ

የሚያመጣው በዝርዝር ተነግሮት ይመዘግባል፡፡ ከሠርጉ ቀን በፊት እነዚህን ይልካል፡፡ ከዚህ ሌላ "አልፋ ተሃ" እሚባል ሌላ ጥሎሽ ይቀረዋል፡፡

### 6.1.3. አል ፋተሃ/ ዳግም ጥሎሽ

የጥሎሽ መጀመሪያ የሆነው "አል በረካ" ከተደረገ በኋላ የጥሎሹ ሥርዓት ደረጃ በደረጃ ይቀጥላል፡፡ ለሙሽሪትና ለቤተሰቦቿ እንዲሁም ለመደገሻ የሚሆነው ጥሎሽ ከተጣለ በኋላ ቀጥሎ የሚመጣው "አል ፋተሃ" ይሰኛል፡፡ አል ፋተሃ የሚጣለው በገንዘብ ነው፡፡ “እህታችንን ሠጥተናል በፈለገው ጊዜ መውሰድ ይችላል” ብለው ጋብቻውን የሚመርቁ የልጅቷ እህቶችና አክስቶች ብቻ የሚሳተፉበት የጥሎሽ ድግስ ነው፡፡

ሙሽራው "አል ፋተሃ" ብሎ የቻለውን ያህል ገንዘብ ይሰጣል፡፡ በዚያች ገንዘብ የሙሽሪት እህቶችና አክስቶች ተሰብስበው የቻለውን ያህል በመደገስ እየበሉ እየጠጡ ይዘፍናሉ፤ ይጨፍራሉ የሙሽሪትን ጋብቻ በበኩላቸው ያፀድቃሉ፡፡ በዚህ ሥርዓት ከእነሱ በቀር ሌሎች አይሳተፉም፡፡ ከመካከላቸው የሌለች እህት ወይም አክስት ካለች ድርሻዋ ባለችበት ይላክላታል፤ ወይ ስትመጣ ይሰጣታል እንጂ ከአል ፋተሃ ሳይደርሳት አይቀርባትም፡፡

> …እንደገና ለሁለተኛ ጊዜ "አል ፋተሃ" ከመክፈቻው ቀጥሎ ሰጥተናል ብለው ከወሰኑ በኋላ የሚፀድቅበት ነው፡፡ ሃምሳ ብርም ሊሆን ይችላል፤ መቶ ብርም፣ መቶ ሃምሳ ብርም ሊሆን ይችላል፡፡ አቅሙ የፈቀደውን "አል ፋተሃ" ብሎ ይሰጣል፡፡ ከዚያ በኋላ ያችን "አል ፋተሃ" ሁሉም አክስቶችና ታላላቅ እህቶቿ ናቸው እሚካፋሉት እነዚህ ደግሞ ይህቺን የእገሌ ልጅ ያገባችው የመጣላት "አል ፈተሃ" ነው ተብሎ ቡና ካለ እዚያው ትጠጫለሽ፤ የመጣውን ነገር ከቀመስሽ

> ቀምሰሻል፤ ካልቀመስሽ ግን በብር ተቀይሮ ባለሽበት አገር ይላክልሻል። ለምን አዲስ አበባ አትሆኚም፣ይህቺ የእከሌ ልጅ ያገባችው አል ፋትሃ ነው ተብሎ አሥር ሳንቲምም ብትሆን ትደርስሻለች። ይቺ በባህሏ እሷ ናት ያለችው… (ወ/ሮ ሲቲና አደም ቃመ22/03/05)።

በዚህ መልኩ ጥሎሹ ከተጠናቀቀ በኋላ የሠርጉ ዝግጅት በሁለቱም ቤት ይጀመራል። ሙሽራው በቅድሚያ ከሙሽሪት ቤተሰቦች ቤት አጠገብ ቤት ይሠራል። ቤቱ ከጫጉላ ጊዜያቸው ጀምሮ ልጂት እስከምትወልድበት ጊዜ የሚቆዩበት ነው። ሙሽራው ሚስቱን ወደ ቤቱ ይዞ የሚሄደው ልጅ ስትወልድ ከእነልጇ ከአንድ ዓመት በኋላ ነው። ይህም የሚሆነው ልጅቷን እናቷ ከእርግዝናዋ ጀምሮ ተንከባክባና አርሳ ስለ ትዳር አያያዝ አስተምራም እንድትሸኛት ስለሚፈለግ ነው። በሌላ በኩል የልጅቷ አባት ቤቱን አጠገቡ የሚያሠራውም ልጁን ስለወሰደበት እንደቅጣትም እንደሆነ አቡራሙ ቀበሌ አባ አልበሽር ነግረውኛል፡

### 6.1.4. ሠርግ "እሪስ"

የሠርጉ ዝግጅት በሁለቱም ቤት የሚደረግ ሲሆን ጎረቤቶችና ዘመዶች ሥራውን ተከፋፍለው በመውሰድ የመሥራት ባህል አላቸው። የሚፈጭ እህል ካለ ተከፋፍለው ፈጭተው አቡክተው ጋግረው ያመጣሉ፤ ሌላውንም ሥራ እንዲሁ በጋራ ያከናውናሉ።

ለሙሽራዋ የሚሆኑ መዋቢያዎች ዝግጅትና ሙሽራዋን የማስዋብ ሥራም ይጧጧፋል። ሠርጉ ሳምንት ሲቀረውም ጀምሮ ዘፈንና ጭፈራው ይደምቃል። ለሰርጉ ሦስት ቀን ሲቀረው ከምሽት እስከ ለሊት የሚቆይ "ሃርሻ" የሚባለውን ጭፈራ የሰፈሩ ወጣቶች በሙሉ ተሰብስበው ሲጨፍሩ ያነጋሉ።

ሙሽሪት በዚያን ግዜ ፀጉሯን ትሠራለች፤ ሂና ትቀባለች፤ ትዋባለች። ማታም ከጎጆዋ ወጥታ ሃርሻውን ትቀላቀላለች። "ጭፈራው ማታ ማታ ነው፡ የሚመራው በባህላዊ

የሙዚቃ መሣሪያዎች በክራር፣ አተንባ፣ አተሉቃ፣ የሚታጀብ ባህላዊ ባንድ ነው ሰርግ ባለበት ሁሉ እየዞርን ወላዒ እስከ ሁለት ሺህ እየተከፈለን እንዘፍናለን፡፡ እሰከሚነጋ እናስጨፍራለን እሰከ ሠርጉ ቀን ድረስ" (ፋይዝ አብዱልቃድር፣ቃመ13/03/05)፡፡

የሠርጉ ቀን ከቀትር በፊት ሙሽራው ዋናውን የልጅቷን ጥሎሽ ለሚዜዎቹ ይልክና በትክክል ስለመጣሉ እየታዬ ይረጋገጣል፡፡ ከቀኑ አሥር ሰዓት አካባቢም ሙሽራው ራሱ ላይ ነጭ ጨርቅ "እማ" በቁንጥ ጠምጥሞ፣ሱፍ ልብስ ለብሶ፣ በእጁ ሙሽርነቱን የሚያመለክት አክርባጅ አለንጋ ይዞ በ"ወዚሮቹ"/ሚዜዎቹና ሠርገኞች ታጅቦ በቅሎ ካለ በበቅሎ አለዚያም በሲናር አህያ ተቀምጦ ይመጣል፡፡ በልጅቷ ቤት አቅራቢያ ሲደርስም እልልታና ሆታው ይቀልጣል፤ የልጂቷ ቤተዘመዶችም ሙሽራውን አናስገባም በማለት ይጋፈጣሉ፤ የገማ እንቁላል ወደ ሠርገኞቹ ይወረውራሉ፤ በዘፈንና በእልልታ የታጀበ ታላቅ ግርግር ይፈጠራል፡፡ የሙሽራው ሚዜዎች እንደምንም በሽቶና በግፊያ ጥሰው ይገቡና ሙሽራውን ከሠራው ቤት አስገብተው ያስቀምጡታል፡፡ የሙሽሪት ሚዜዎች በበኩላቸው ሙሽሪት በቀላሉ እንዳትገኝ ከመንደሩ ቤቶች በአንዱ ይደብቋታል፡፡ የሙሽራው ሚዜዎችም ፍለጋቸውን ይቀጥላሉ፡፡ ከብዙ ድካምና ግርግር በኋላ ገንዘብ ይከፍሉና ሙሽራዋ ያለችበትን ያሳዩዋቸዋል፡፡ ሲገቡ ሙሽሪት ለማንሳት በማያስችል መልኩ በቶቧ ተጠቅልላ ታስቸግራለች፤ በመከራ ተሸክመው ወደ ሙሽራው እልፍኝ ያደርሷታል፡፡



ፎቶ16. የበርታ ሙሽራ ለሠርጓ ጓደኞቿ እግሯን ሂና እየቀቡ፣ ፀጉሯን እየሠሩ ሲያስውቧት



ፎቶ 7. ለሠርግ እድምተኞች ለማቅረብ የተዘጋጀ ምግብ

### 6.1.5. ክብረ ንፅህና

በበርታ ማህበረሰብ የሴት ልጅ ከነክብረ ንጽህናዋ መገኘት ትልቅ ክብር አለው። ማንኛዋም ሴት ልጃገረድ ሆና መገኘቷን ቤተሰቦቸዋ፤ ጎረቤቶቿ፣ አል ፋተሀዋን የበሉ ሁሉ በጉጉት የሚጠብቁት ነው። በበርታ ድብብቆሽና ውሽት ስለሌለ ልጅት በክብረ ንፅህናዋ አለመኖር ጥርጣሬ ካላት ጋብቻው ተፈቅዶ ጥሎሽ ከመጀመሩ በፊት ለአጎቷ መናገር ይኖርባታል። ይህ ከሆነ ቤተሰብ ችግሩን ለጋብቻ ጠያቂው በግልፅ ተናግሮ፣ ከፈቀደ ካለጥሎሽ ሊያገባት ይችላል፤ አለዚያ ክብረ ንፅህና እንደሌላት ተነግሮት ሌላ ፈቃደኛ የሆነ ሰው ጥሎሽ ሳይጠየቅ ሊያገባት ይችላል። ይህ ሳይሆን ቀርቶ ልጅት ዝም ብትልም የክብረ ንጽህና

መኖር አለመኖር በአዋቂ ሴቶች ይረጋገጣል:: አቡሙ ቀበሌ ያገኘሁዋቸው በዚህ ምርመራ የታወቁት እማ አልመል ሀሰን እንደገለፁልኝ "ልጅቷን ልጃገረድ እንዳልሆነች ከተጠራጠርን አስቀድመን እንመረምራታለን ከእጇ መዳፍ መገጣጠሚያ ላይ፣ በቅንድቧ መገጣጠሚያ ላይ፣ ከጉልበቷ በተቃራኒ ባለው የእግሯ መገጣጣሚያ ላይ፣ ወይም በብልቷ አካባቢ በአውራ ጣታችንና በመሃል ጣታችን አጥብቀን ይዘን ትንሽ አቆይተን ስንለቀው ቶሎ ወደ ቦታው ከተመለሰ ልጃገረድ ናት ተሰርጉዶ ከቀረ ግን አይደለችም::" (እማ አልመል ሀሰን፣ ቃመ20/04/05) የድንግልና መኖር የሚረጋገጠው በዚህ ብቻ አይደለም:: በሰርጉ ቀን ማታ ሁለት አሮጊቶች በጫጉላ ቤቱ ገብተው ይደበቁና እውነታውን አረጋግጠው የምስክርነት ቃላቸውን ይሠጣሉ:: ሥርዓቱ እንደዚህ ነው::

> ህግ እሚጠፋ ቀን በእኛ ባህል ማለት ነው እንግዲህ ዛሬ ሠርግ ተደርጓል ቤተሰብ ሁሉ አለ፤ ሁለት አሮጊት ሴቶች ይሰጣሉ፤ልጅቷ ቤት እነሱ እሷ ከመሄዷ በፊት አንድ ሜትር አቡጀዴ ይገዛና ይሸረጥላታል በእናንተ ሙዳይ ነው የሚባለው በእኛ "ሃራ" ነው እሚባለው የደም ጨርቅ ማስቀመጫ እሱን ይዘው ይሄዱና ሁለቱ አሮጊቶች ቁጭ ይላሉ እቤት ውስጥ ልጅቷ ከመሄዷ በፊት… እነሱ ብቻ ናቸው ያንን ሁኔታ የሚከታተሉ ሌላው ይሄዳል፤ከዛ ልጁ እዚያው ቤት አለ ከዚያ ልጁን ልትመታው ትችላለች ልትተናኮለው ትችላለች ተብሎ ይታሰባል ጉልበት ምናምን ሊኖር ይችላል ቤተሰብም ይጨነቃል ምን ሆና ይሆን እንዴት ስማችን ጠፋ ወይ ምንድነው ክብራችን በቃ የዚያን ቀን ማታ የሴቷ ቤተሰብ ጭንቀት ላይ ነው እሚሆነው፤ ከዚያ በኋላ ያ ሲፈፀም እነሱ እልል ይላሉ፤ ያችን ይዘው ይመጣሉ::..ባሉበት ነው! ክፍል እንደዚህ ጓዳ ነገር ይኖራል እዚህ በር ላይ ነው እሚቀመጡት ማየት አለባቸው (ወ/ሮ ሲቲና አደም ቃመ22/03/05)::

አሮጊቶቹ ተደብቀው የሚቀመጡት በብዙ ምክንያቶች ነው። አንዱ በጫጉላ ቤት ልጅት ክብረንጽህናዬን አላስነካም ብላ ወንዱን ትታገላለች፤ በአክሮባጅም ልትገርፈው ትችላለች። አቅም አንሶት መግሰስ ካልቻለ ልጃገረድ አይደለችም ብሎ ሊያወራ እንዳይችል ነው። ሌላው ደግሞ ልጅት ልጃገረድ ሳትሆን አሁን አሁን በአንዳንድ አካባቢ እንደሚደረገው የሌላ ነገር ደም እንዳይቀርብ ለመቆጣጠር ነው። ከዚህ ሌላ ደግሞ ምናልባት ክብረ ንፅህና ባይኖርና በዚያ ንዴት ወንዱ በሴቷ ላይ የሃይል ጥቃት እንዳይፈፅምም ለመቆጣጠር ነው (ወ/ሮ ሲቲና፣ አባ አልሃሰን፣ እማ አልመል፤ አባ አብዱራሂም)።

እነዚህ ሁኔታዎች ታልፈው ልጂት ከነክብረ ንፅህናዋ ከተገኘች የተደበቁት አሮጊቶች ደስታቸውን በእልልታ ሲያሰሙ ሁሉም ቤተሰብና ሰርገኛ ተቀብሏቸው እልልታና ፉከራው ይቀልጣል፤ ወንዶች መሳሪያ ይተኩሳሉ ዘፈንና ጭፈራው ይደምቃል። እናት ትፎክራለች፤ እህቶች ይፎክራሉ ሁሉም ቤተሰብ ይፎክራል ልጃችን ጨዋ ናት ይባላል። …በጣም ክብር ነው! በጣም! በጣም! በጣም! በጣም! (አባ አብዱራሂም፣ ቃመ22/03/05)።

በዚህ መልኩ ሁለት አሮጊቶች ሁሉንም ነገር አረጋግጠው ክብረ ንፅህናው ከተገኘ ደስታቸውን በእልልታ በመግለጽ፣ ካልሆነም ችግሩ የእሱ ይሁን የእሷ ለይተው ለማህበረሰቡ ሽማግሌዎች ያሳውቃሉ።



ፎቶ 6. እኔም እንደሙሽሪት

ሙሽሮቹ እስከ አርባ ቀን በጫጉላ ከቆዩ በኋላ ቤት ለማስተዳደር እንደደረሱ ይታመናል። እሱም ወደ ቤተሰቦቹ ዘንድ ሄዶ ቤቱን እንዴት ማስተዳደርና መምራት እንዳለበት ሲመከር ቆይቶ አዳሩን እዛው በማድረግ በማግስቱ ወደ ሚስቱ ይመለሳል። ሙሽሪትንም እናቱዋና አክስቶቿ ስለቤት አያያዝ ምክር ሲሰጧት ይቆያሉ። ከዚህ በኋላ የግል ቤታቸውን መምራት ይጀምራሉ።

## 6.2. እርግዝናና ልደት

ሙሽሪት ስታረግዝ ከፍተኛ ጥንቃቄ ይደረግላታል፤ ከባድ ሥራ እንዳትሰራ፣ ከባድ ሸክም እንዳትሸከም እረፍት እንድታደርግ ምክር ይሰጣታል፤ በተለይም ሰባተኛ ወሯ ከገባ ጀምሮ እስከምትወልድ ድረስ ከፍተኛ እንክብካቤና ጥበቃ ይደረግላታል። ከወለደች በኋላም እስከ አርባ ቀን ከቤት ሳትወጣ ትታረሳለች። አብዛኞቹ ባሎች ሚስታቸው ጡሃራ

/ንፁህ እስክትሆን በሚል በነዚህ አርባ ቀናት ወደ ቤት አይገቡም። አዳርና ውሎዋቸው ሌላ ቤት ይሆናል።

አራሷን እናቷ እየተንከባከበች ታርሳታለች፤ ልጅ ታጥብላታለች፤ የባሏ እናት አክስቷ ልትሆን ስለምትችልም በጋራ ይንከባከቧታል። ልጁን በአራስነቱ ሰይጣን ይተናኮለዋል ተብሎ ስለሚታሰብ ብቻውን ተትቶ አይወጣም። እናቱም እስከ አሥራ አምስት ሃያ ቀን ውሃ እየተሞቀ ትታጠባለች እንጂ በቀዝቃዛ ውሃ አትታጠብም። ሰውነቷ እንዲፀናና መልካም ጠረን እንዲኖራትም በዲልካ ትታሻለች።

እስከ አርባ ቀን ድረስ ከአራሷ ቤት አመድ አይወጣም፤ እሳት አይጫርም፤ ልጁም እትብቱ ተቆርጦ እስከሚወድቅበት ቀን ድረስ እሳት ሌት ከቀን ይነዳል እንጂ አይጠፋም፤ አመዱ ወደ ውጪ አይፈስም። የልጁ ቁጣጥ ወይም ሠገራ ውጪ ከተጣለና ሰው ቢረግጠው ሆዱን ይቆርጠዋል ተብሎ ስለሚታሰብ ነው፤ ሠገራው እስከ አርባ ቀን እቤት ነው እሚሰበሰበው፤ የልጁ ገላ እጣቢም አልጋ ሥር ነው እሚደፋው፤ አራሷዋም ብቻዋን አትወጣም፤ ሽንት ቤት መሄድ ከፈለገች ሰው አጅቧት የጥላ መድሃኒት እጇ ላይ ታስሮ ነው እምትወጣ እሱንም በፀሐይ አትወጣም፤ ወይ ጥዋት ወይ ማታ እንጂ እነዚህ የነበሩ ባህሎች ናቸው (ወ/ሮ ሲቲና አደም ቃመ22/03/05)።

አርባ ቀን ሲሞላት ዘመዶቿና የሰፈር ሴቶች ተሰብስበው አመዱን ጠርገው አውጥተው እልል እያሉ በሰልፍ በመሄድ አርቀው ደፍተው ይመለሳሉ። ከዚያ መልስ ገላዋን አጥበው ንፁህ ልብስ ያለብሷታል፤ ይኳሏታል፤ በአራስነቷ ጭስ እየሞቀች፣ በዲልካ እየታሸች፣ መልካም እየበላች ስለከረመች ሙሽራ ትመስላለች። ከዚያም ይደገሳል፤ ይበላል ይጠጣል። ከዚያን ቀን በኋላ ወደ ውጪ መውጣት ትጀምራለች።

### 6.2.1. ስሚያ (የሥም አወጣጥ ሥርዓት)

በበርታ ባህል ህፃን ሲወለድ ስም የማውጣት ባህላዊ ሥነሥርዓት አለ። "ስሚያ" ይባላል። ልጅ በተወለደ በስምንተኛው ቀን ይከናወናል። በዕለቱ የስም ማውጫ ድግስ ይደገስና የተወለደው ወንድ ይሁንም ሴት ስም ይወጣለታል። ለመጀመሪያ ልጅ ስም የማውጣት ድርሻ የአባት ብቻ ይሆናል። "ስም ሲሰጥም አባት ነው ስም የሚሰጠው አባት በሌለበት ወኪል ያስቀምጣል ለምሳሌ በአካል የለም ሌላ ቦታ ሄዷል ለሥራ ወይም የለም፤ ወይ የእሱን ታላቅ ወንድም ወይ የእሱን ታናሽ ወንድም እንጂ ማንም ሊሰይምለት አይችልም ራሱ ነው ስም የሚያወጣው ወይ አባቱ፤..." (አባ አብዱራሂም፣ ቃመ22/03/05፣)። "በስም አወጣጡ የልጅቷ ቤተሰቦችም ድርሻ አላቸው ሴት ልጅ ከሆነች በእናቴ ስም ይሰየምልኝ፤ በእናቴ ስም ነው እማስጠራት ብላ ከባሏ ጋራ ትስማማለች፤..." (ወ/ሮ ሲቲና አደም፣ ቃመ22/03/05)።

ከመጀመሪያው ልጅ በኋላ ሦስት አራት ልጅ ከወለዱና ቤተሰብ በበዛ ቁጥር ከቤተሰቡ ስም ሌላ የቁርዐን ስሞች ፈልገው ሊያወጡ ይችላሉ። በሬድዮ ወይም ሲጠራ የሰሙትንም ሊሰይሙ ይችላሉ። “አሁን ተቀይሯል ይሄ የለም አሁን ዓለማቀፉ ስሞች ገቡ እኮ እነ ሜሪ፣እነ ቢላደን እነ ኦባማ አሁን አለ እኛ ጋ በዕውነት!” (ወ/ሮ ሲቲና አደም ቃመ22/03/05)።

የበርታ ስሞች ተደጋጋሚና በአብዛኛው ተመሳሳይ የሆኑት ከዘመዶቻቸው የሚወዱትን፣ በአካባቢያቸው ደግሞ መልካም ስነምግባርና ጀግንነት ያለውን ስም ስለሚሰይሙ ነው። ይሄን ልብ ያልኩት የመረጃ ሰጪዎቼ ስም በአብዛኛው ተመሳሳይ በመሆኑ ነው።

### 6.2.2. ግርዛት

የበርታዎች አንዱ መለያ የግርዛት ሥርዓታቸው ነው፡፡ አሁን የሴት ልጅ ግርዛት ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት ነው በመባሉ የቀረ[26] ቢሆንም ቀደም ባሉት ግዜያት የሴቶችና የወንዶች ግርዛት በሰፈሩ ያሉ ልጆች ሁሉ በአንድ ላይ ሆነው ትልቅ ድግስ ተደግሦ የሚከናወን ሥርዓት ነው፡፡ መረጃ ሰጪዎቼ ከራሳቸው የግርዛት ወቅት ትውስታ ገልፀውልኛል፡፡

> ሁላችንም በዚህ ነገር ውስጥ አልፈናል፤እኔ አሁን አያቴ እዚህ ገዢ ነበሩ እና እኔ በምገረዝበት ሰዓት ትልቅ ዳስ ነው፤ የአሁኑ የማንም ሀብታም ሠርግ እንደዚህ አይደለም፤ በሬ ይታረዳል፤ ነጋሪት ይጎሰማል፤ በቃ ጭፈራው ሦስት ቀን አራት ቀን እስከ ሳምንት ይጨፈራል፤ ስድስት ዓመቴ ነው ስገረዝ፡፡ ማልቀስ ጥሩ አይደለም፤ ካለቀሰ ፈሪ ነው የሚባለው፤ ስለዚህ እኔ ሁሉን ነገር ችዬ ጥርሴን ነክሼ ካሳለፍኩኝ ሽልማቴ በጣም ብዙ ነው፤ ሁሉም እየመጣ አምበሳ እኔን የሚተካኝ እሱ ነው ከብት እሚሰጠኝ አለ፤ብር እሚሰጠኝ አለ ብዙ ነገር አገኛለሁ፡፡ እንክብካቤ ይደረግለኛል (አባ አብዱራሂም፣ ቃመ22/03/05)፡፡
>
> የእኔ ጊዜ አርባ ሁለት ሴቶች ሁነን ነው የተገረዝነው፤እኔ የመጨረሻዋ ትንሽ ነኝ አርባ ሁለት ሴት ማለት እንግዲህ በጣም ብዙ ነው፤ እንግዲህ ዳስ ተጥሎ አልጋሽ ይመጣል እናትሽ ትመጣለች በቃ ተሰብስበሽ ልብስ ይገዛልሻል፤እንደሙሽራ ሂና ይደረግልሻል፤ በቃ ጎበዝ እንደዚህ ግዝረት ሊደረግ ነው እዚያ ሰፈር ተብሎ ህዝብ

[26] ቀርቷል የሚባለው የሴት ልጅ ግርዛት የቀረው በአደባባይ ቢሆንም ውስጥ ውስጡን እቤት እየተደበቁ እንደሚያስገርዙ ብዙ መረጃ ሰጪዎች ነግረውኛል፡፡ ይሄን ከጤና ጉዳዮች ጋር አያይዤ ወደኋላ በስፋት አብራራዋለሁ፡፡

ይሰበሰባል፤ ዙምባራው፣ ጭፈራው፣ በቃ ሶስት ቀንና አራት ቀን ጠላው እዚያው ጠላ ይሰጣቸዋል፤ የሚጨፍሩ ሰዎች እዚያ ጠጥተው ሰክረው እንዲጨፍሩ ይፈለጋል፤ የእከሌ ቤተሰቦች ግርዛት ነገ ሊፈፀም ነው ተብሎ ገራዢዋ በቅሎ ተሞሽራ ተሸልማ በቃ ጠቅላላ ነጭ በነጭ ለብሳ ሰው በብዛት ሆኖ ሄዶ ያመጣታል፤ እሚገረዝበት በሙዳይ ተደርጎ ነው እሚመጣው፤ እኔ ካደግሁ በኋላም የእኔ ዘመድ ነበረች ገራዥ እና ብዙ ቦታ ይዛኝ ትሄዳለች፤ ብዙ ቦታ ተጠርታ ስትሄድ ያለው ክብር ሌላ ነው፤ ዶሮ ብቻ ነው እምትበላው፤ ሳምንት ሙሉ ልጆቹ እስከሚሻላቸው ማለት ነው፤ እዚያው ሆና ይሄን ቀቡ፤ ይሄን አድርጉ የባህሉ ይሄ የሚፈጨው ጥላሸቱ ምኑ አይቀርም እና ጥሩ ነበረ በዚያን ጊዜ… (ወ/ሮ ሲቲና አደም ቃመ22/03/05)፡፡

በባህሉ ያልተገረዘች ሴት እቃ ትጨርሳለች፤ እምታቦካው እምትጋግረው አይበረክትም፤ ቤት ውስጥ አርፋ አትቀመጥም፤ ትባልጋለች፤፤ ዱርዬ ትሆናለች፤ ለባሏ ታስቸግራለች፤ ያልተገረዘች ነጃሳ ናት ወዘተ ተብሎ ስለሚታሰብ በቀደመው ጊዜ ተገረዘች መባል በራሱ ክብር እንደነበረው መረጃ ሰጪዎቹ ይናገራሉ፡፡

ግርዛቱ ልጆቹ ትልልቅ እስኪሆኑና ለትዳር እስኪደርሱ ሊቆይ ይችላል፡፡ ምክንያቱ አንድም ላሉት ልጆች ሲገረዙ ለድግስ የሚወጣውን ወጪ በአንድ ላይ ለማውጣት፣ አንድም ቤተሰቡ በሙሉ ያለውም የሌለውም ሀብታሙም ደሃውም ተሰብስቦ አንድ ላይ ለመደገሥና ሥርዓቱን ተመሳሳይና የጋራ እንዲሆን በማሰብ ነው፡፡ የግርዛቱ ጊዜ በዓመት ሰብል ተሰብስቦ ከገባ በኋላ ዝናብ በማይኖርበት ሰዓት ሌሎች ሥራዎችም በማያባክኑበት ባብዛኛው የጥር ወር አካባቢ ነው፡፡ በዚህ ወቅት በጋ በመሆኑ ወርቅ ቢቆፈርም በቀላሉ ስለሚገኝ ለድግሱ ወጪ መሸፈኛ አያሳስብም፡፡ በክረምቱ የተወለዱ ፍየሎችም ለድግሱ

ይደርሳሉ። ከዚህ በተጨማሪም ግርዛቱ በክረምት ቢሆን ቁስሉ ሊያመረቅዝ ይችላል ተብሎም ስለሚታሰብ ግርዛት ሁል ጊዜ በበጋ ወራት የሚከናወን ነው። የተገረዙት ልጆች በግርዛቱ አውድ ላይ በሚሰራላቸው የጋራ ጎጆ ለአንድ ሳምንት በገራዦቻቸው ክትትል እየተደረገላቸው ከቆዩ በኋላ ቁስላቸው ሲጠግግ ወደየቤታቸው ይመለሳሉ። ቤታቸውም ሌላ ድግስ ተደግሶ ይጠብቃቸዋል።

## 6.3. ሞትና የሀዘን ሥርዓት

በበርታ ሰው ሲሞት ከዕድሜና ከአሟሟት ሁኔታ ጋር ተያይዞ የሀዘኑ ሥርዓት በተለያየ መልክ ይከናወናል። በአንድ አካባቢ ሰው መሞቱ እንደተሰማ በቅርብና በሩቅ ያለው ዘመድ ሁሉ እንዲሰማ ይደረጋል። ለቅርቡ በመልክተኛ ለሩቁ ደግሞ ደብዳቤ ይላካል። አዋቂ ሰዎችም አስከሬኑን ገንዘው የእስልምና እምነት በሚፈቅደው መሠረት ወንዶች ብቻ ወደ ቀብሩ ሥፍራ በመሄድ ቀብረው ይመለሳሉ። በበርታ የመረረ ሀዘን አይፈቀድም። አንድ ሰው ምርር ብሎ የሚያዝን ከሆነ አላህ የፈጠረውን በፈለገው ጊዜ ይወስዳል፤ ስለዚህ መሪር ሀዘን ተገቢ አይደለም ብለው የዕድሜ ታላላቆች ይቆጣሉ።

> ሴቶች ቀብር ቦታ አይሄዱም ለምንድነው? ስለሚጮሁ፤ ስለማይችሉ፤ ስለሚያለቅሱ አንዳንዶቹ በጣም እሚችሉ ቢሄዱ ምንም አይደለም እኔ አላለቅስም ብላ አስፈቅዳ የሄደች ሴት አይቻለሁ። ሌላው ቀርቶ ቤት ውስጥ እንኳ ማልቀስም የተከለከለ ነው። ማልቀስ ማለት ቁጪት ነው ንዴት ነው ለምን ሞተብኝ ማለት ነው። እና ከማን ጋር ነው እሚጣላው ከፈጣሪው ጋር? ሁለተኛ በፈሰሰው እምባ ልክ ሚቹ ይቃጠላል ይባላል" (አባ አብዱራሂም፣ቃመ22/03/05)።

የሌለው ሰው ካለም የዝን ይዤ ሳልሄድ ብሎ አይሰጋም ካለምንም ይሉኝታ የሀዘን ቀናቱን ሁሉ ባዶ እጁን እየሄደ ያስተሳዝናል፡፡ ሴቶች ከቤታቸው እህል ውሃ እያሰናዱ ያመጣሉ፡፡ ከቀብር በኂላ ሁሉም በሀዘንተኛው ቤት ተሰብስቦ እንደሚቼ የእድሜና አሟሟት ሁኔታ ከአምስት እስከ አሥራ አምስት ቀን ያስተዛዝናል፡፡[27] በሃዘኑ ወቅት ሴቶችና ወንዶቹ እንደተለመደው በጋራ አይቀመጡም፡፡ ሴቶቹ ከቤት ውስጥ ወንዶቹም በአልከለዋ ውስጥ ይቀመጣሉ፡፡ የምግብና መጠጥ መስተንግዶዉን የሚያደርጉትም ለወንዶቹ ወጣት ወንዶች፣ ለሴቶቹም በማንኛውም ዕድሜ ላይ ያሉ ሴቶች ናቸው፡፡ ለወንዶቹ ለማስተዛዘኛ የመጣውን ሻይና ቡና አፍልተው የሚያቀርቡት ወጣት ወንዶች ናቸው ምግብም ከሴቶቹ ዘንድ አምጥተው ያስተናብራሉ፡፡ ሀዘንተኞች በሀዘኑ ወቅት እስከ ሰባት ቀን ድረስ ሥጋ አይመገቡም፡፡ ለእነሱ ለብቻቸው ሥጋ የሌለው ወጥ ይሠራላቸዋል፡፡ ሌሎች ለማስተዛዘን የሚመጡ ሰዎች ግን የተገኘውን መመገብ ይችላሉ፡፡



ፎቶ 7. ለአስተዛዛኞች ለመታደል የተዘጋጀ ሻይ (መቃዚን ቀበሌ በአባ አደም እናት ሞት ላይ

[27] አባ ቤሎ፣ ቃመ02/03/05 አብዱልናስር አልሀሰን ቃመ16/03/05፣ ቡውይአቡ09/03/05 እና ቡውይቶሽ18/04/05

**ከቤት ውስጥ የሟቹ አስክሬን የነበረበት አልጋ[28] ወደ መሬት ተገልብጦ ይጋረድና ከሥሩ ሴት ሀዘንተኞች ይቀመጣሉ፡፡ በአካባቢው ባለ ቤት ያለ አልጋ ሁሉ በሠፈሩ ሀዘን መኖሩን ለማሳወቅ አራት እግሮቹ ወደላይ ሆነው ይገለበጥና ፍራሽ ተደርጎበት ይተኛበታል፡፡ ይሄ ሀዘን ላይ መሆናቸውን ለመግለፅ የሚደረግ ነው፡፡**



ፎቶ 8. በአካባቢው ሀዘን እንዳለ ለመግለፅ የተገለበጠ አልጋ

[28] አልጋው በገጠር ባብዛኛው የጠፍር አልጋ ሲሆን አልፎ አልፎ በፕላስቲክ ገመድ የተወጠረ የብረት አልጋም ይኖራል፡፡

### 6.3.1. የቀብርና የሀዘን ሥርዓት

በበርታ ሰው ሲሞት የሀዘኑ ልክና መልክ እንደሟቹ ዕድሜና የአሟሟት ሁኔታ የተለያየ ነው። የሞተው ህፃን ልጅ ከሆነ ለዚህ ዓለም ህይወት እንግዳ የሆነ፤ ኃጢያት የሌለበት ጨቅላ በመሆኑ ሃዘኑ አጭር ነው። ወላጆቹ ብቻ በመውለዳቸው በመጠኑ ያዝናሉ። በወሊድ የሞተች ሴት ሰውነቷ ቁስል ነው ተብሎ ስለሚታሰብ ብዙ አይለቀስላትም፤ ለቅሶ በበዛ ቁጥር ሰውነቷ ስለሚቆስል አታልቅሱ ተብሎ ይከለከላል።

በመብረቅ፤ በውሃ ሙላት በመሳሰለው አደጋ የሞተ ሰው ከሆነ ሰው በሚቀበርበት ቦታ ሳይሆን ለብቻው ነው የሚቀበረው። አዲስ ከፈን ተገዝቶም አይከፈንም። ይህ የሚሆነው ደግሞ በሰውየው ችግር ሳይሆን ሞት በዚህ ተደስቶ ዳግም ሌላ ሰው በመብረቅ ወይም በውሃ ሙላት እንዳይገድል ነው። ሰውየው ራሱን ያጠፋ ከሆነ ደግሞ ጭራሽም አይታዘንለትም። “ራሱን ያጠፋ የሱን ነፍስ ያስቀመጠው እግዚአብሔር ነው እሱ ነው መውሰድ ያለበት፤ ራሱ ግን እግዚአብሔር ሳይፈልገው ራሱ አደረገው አይደል አይለቀስለትም፤ አይታዘንለትም፤በቃ ይቀበርና ቤተሰብ ብቻ ሊሰማው ይችላል ግን ማስተዛዘን የለም፤ "ራሱን ላጠፋ አትዘንለት" የሚል ተረት አለ” (አባ ቤሎ፣ ቃመ02/03/05)።

በበርታ ባህል በእድሜ የገፋ ሰው ሲሞት በበቂ ሁኔታ ኑሮ ስለሞተ ለቅሶ የለም፤ እየተዘፈነና እየተጨፈረ ይሸኛል። “የእናቴ አክስት ስትሞት ትልቅ ሆና ነው የሞተችው፤ መቶ ዓመት ምናምን ይሆናታል። እሳቸው ሲሞቱ በጭፈራ ነው የተሸኙት፤ አልተለቀሰላቸውም።[29] እንደውም በእልልታ እየተጨፈረ ለምንድነው ሲባል ዕድሜአቸው በጣም ሄዷል በጣም በልተዋል ኖረዋል ምንም እሚለቀስላቸው የለም ተብሎ ነው ያኔ በእልልታ ነው የተሸኙት፤ ዘመዶቻቸው እየፎከሩ ነው የሸኘዋቸው ማለት ነው”(ወ/ሮ ነፊሳ መሀመድ፣ ቃመ22/03/05)።

---

[29] አንቱና አንቺ የሚሉት መረጃ ሰጪዋ ራሳቸው ናቸው።

በበርታ በዕድሜ ለገፉ ሰዎች፤ ለመሪዎችና ታሪክ ሰርተው ላለፉ ሰዎች ጭፈራ፣ እልልታ፣ ፉከራ፣ እንጂ ለቅሶ አያስፈልግም ተብሎ ይታመናል። ጭፈራው ዘፈኑ በራሱ ይለያል፤ የራሱ አካሄድ የራሱ ባህላዊ ክዋኔ አለው። የማስተዛዘኑ ሥርዓት እንደሁኔታው ከ5- 15 ቀናት የሚቀጥል ቢሆንም እጅግ በጣም ቅርብ የሆኑ ሰዎች የሃዘን ስሜት እንዳይሰማቸውና ሀዘናቸውን እንዲረሱ በተለያየ መንገድ ጥረት ይደረጋል።

### 6.3.2. የአያት ሞትና የልጅ ልጆች የካሳ ጥያቄ /አጉቤፁ

ከዚህ ሁሉ የበርታን የሀዘን ሥርዓት ልዩ የሚያደርገው አያት ስትሞት የልጅ ልጆች የሚያነሱት የካሳ ጥያቄ ነው። ይህ ጥያቄ በሀዘኑ የመጨረሻ ቀን ከሚከናወነው የልብስ አጠባ ሥርዓት ጋር ተያይዞ የሚቀርብ ነው። በመቃዚን ቀበሌ መረጃ ሰጪዬ የነበሩት የአባ አደም አልኑር እናት ሞተው በመጨረሻው ቀን ለቅሶ ለመድረስ ሄጄ በምልከታ ያገኘሁት መረጃ ሥርዓቱን ለማስገንዘብ ጥሩ ማስረጃ ስለሚሆን ቀጥሎ አቀርበዋለሁ።

በበርታ ባህል በማስተዛዘኛው የመጨረሻ ቀን የሚችና የሀዘንተኞች የልብስ አጠባ ሥርዓት ይደረጋል። በዚያ ቀን ብዙ ሰው ስለሚመጣና የመጨረሻ ድግስ ስለሚኖር የአካባቢው ሴቶች በጠዋት ከየቤታቸው ለማስተናገኛ የሚሆኑ ምግብና መጠጦች ይዘው ይመጣሉ፤ ቤት ያፈራውም ነገር ካለ እዚያው ይዘጋጃል።

በእነ አባ አደም ቤት ወንዶቹ በአልከለዋ ውስጥ ሴቶቹም ከሴት ሀዘንተኞች ጋር እቤት ውስጥ  ቁርስ ከተበላ በኋላ ሴቶቹ ወደ አጠባ ለመሄድ መሰነዳዳት ጀመሩ። በቅድሚያ ሚች የነበሩበት አልጋ ተገልብጦ ከተቀመጠበት ተነሳና መሬቱ በጭቃ ተለቀለቀ። ሥራው ቤትን በእበት እንደመለቅለቅ ዓይነት ሆኖ የሚለቀለቀው ሙሉ ቤቱ ሳይሆን አልጋው የነበረበትና ሀዘንተኞቹ ተቀምጠው የነበረበት አካባቢ ብቻ ነው። የሚቹ ልብስ፣ የተጠቀለሉበት ሰሌን፣ የሃዘንተኞቹ ልብስ በሳፋና በፕላስቲክ መዘፍዘፊያ ተደርጎ በሴቶች እልልታና ሞትን "አትችለንም፣ አናዝንልህም፣ አንፈራህም" በሚልና ሁለተኛም

በአካባቢው እንዳይደርስ በሚያስፈራራ ፉከራ እየታጀበ ከቤት ወጥቶ ከውጪ ተቀመጠ። ከዚያም ልብስ ለማጠብ ወደ ወንዝ የሚወርዱት ሴቶች የራሳቸውን የሚታጠብ ልብስ በየሳፋቸው ላይ አድርገው ይዘው በመሰባሰብ በእልልታና በጭፈራ አካባቢውን አናወጡት። በዚህ ጊዜ የሚች የልጅ ልጆች ተሰብስበው አባ አደምን ወንዶቹ ተቀምጠውበት ከነበረው አልከለዋ በማውጣት ከጀለብያቸው በላይ በለበሱት ነጭ አንገት ልብስ ነገር እየጎተቱ ከጭፈራው መሃል አስገቡዋቸው።



ፎቶ9 አባ አደም ካሳ እንዲከፍሉ ተይዘው

እልልታው እየናረና ጨዋታው እየደመቀ ሄደ። ለአካባቢው እንግዳ ለሆነ ሰው የሠርግ እንጂ የሀዘን ቤት ፈፅሞ አይመስልም። ሀዘንተኛውን ይጎነትሉዋቸዋል፣ ይጎትቷቸዋል፣ በቀልድ መልክ ያንገላቷቸዋል። በመሃል አንድ ልጅ 200 ብር ወደ ላይ ይዞ ሰውየው አጠገብ ቆመ፣ እልልታው፣ ጫጫታውና ጭፈራው በጣም ሞቀ፣ ክርክሩም ጦፈ። አንድ

ፍየል እንደሚሰጡ ቃል ገቡ፤ ዋስም ጠሩ፤ ከዚያ በጭፈራና በሁካታ እንዳጀቡ ወደ አልከለዋው ሸኙዋቸው፤ ሴቶቹ ዘፈናቸውን ሳያቋርጡ አንድ የሚጨስ እጣን በገል በያዘች ሴት እየተመሩ በየሳፋዎቻቸው የያዙትን የሚታጠብ ልብስ ጭንቅላቶቻቸው ላይ ቂብ ቂብ አድርገው እልል እያሉ በሰልፍ ወደ ወንዝ ወረዱ። የልጅ ልጆች ግን በተሰጡት ገንዘብና ፍየል ባለመርካታቸው አይበቃንም ብለው መከራከር ቀጥሉ። ልብሱም ታጥቦ ሲመጣ አናስገባም ብለው ዛቱ።

የሟች የልጅ ልጆች ወላጆቻቸውን፣ አጎቶቻቸውንና አክስቶቻቸውን በመያዝ ካሳ የሚጠይቁበት ምክንያት አላቸው። አያታቸው ለእነሱ ብዙ ነገር ናቸው ስለዚህ በሞት ሲያጧቸው ደህና ካሳ መካስ አለባቸው።

> አያታችን ስለሞተች እምንቀልድባት፣ እምንጫወትባት፣ እምታዝናናን፣ ተረት እምትነግረን፣ ምሳሌ እምትነግረን፣ ሄደን እምናርፍባት፣ እምትንከባከበን፣ አጣን ማለት ነው። እሷን በማጣታችን ካሳ ስጡን ብለን ልጆቿን እንጠይቃለን። ከዚያ በኋላ እነሱ አንድ ፍየል ተሰጥቷችኋል ይባላል። ካሳው ካልተሰጠን ልብስ እቤት አይገባም ብለን ተሰልፈን ቤት እንዘጋለን። ከዛ በቃ ይሄን ሰጥተናል፤ ይሄን ሰጥተናል፤ እባካችሁ ፀሐይ ነው፤ ልብስ ይግባ እንባላለን፤ አይሆንም አምጡ ብለን እንይዛለን። አያታችንም ለዚያን ቀን የሚሆነን ከሞቷ በፊት ለእኛ ትታው የምትሄደው አለ እኔ ከሞትኩ ለልጆቼ ይሰጥልኝ ትላለች።
>
> ወንድ አያትም ቢሆን ሁሉም አያት እንዲሁ ነው ትቶልን የሚሄድ ነገር ይኖራል። ከዚያ በኋላ በሚበላበት ቀን ሁሉም አያት የሆነ በሙሉ ይገኛል። በላሽም አልበላሽም ትገኛለሽ። ካልተገኘሽ የልጅ ልጆቹ አንቺን ይቀጡሻል። የተሰጡት ፍየል ታርዶ ይበላል፤ ህፃናት

> በሙሉ የልጅ ልጅ አይቀሩም ተሰብስበው ይጨፈራል፤ ይደነሳል፤ ፀሐይ ላይ በቃ ሲጨፍሩ ነው እሚውሉ የዚያን ቀን ለእነሱ ብቻ ነው። ለሌላ ትልቅ ሰው አይደርስም። ሌላ ሰው ጣልቃ አይገባም። ከዚያ በኋላ ይበላል፤ ይጠጣል፤ እህል ይሰጣቸዋል፤ ብርም ይከፈላል፤ በቃ በልተው፣ ጠጥተው ወደ ቤታቸው ይሄዳሉ፤ ይሄ አያት ሲሞት ደንብ ነው (ወ/ሮ ሲቲና አደም፣ ቃመ25/04/05፣ ቡውይመቃሴብቻ18/02/05)።

በበርታ ለልጅ ልጆች የአያት ሞት እንደዚህ ነው። አያቶችም ይህን ሥርዓት ስለሚያውቁ የበኩላቸውን ለዚያ ቀን የሚሆን ነገር ሰጥተው ነው የሚሞቱት። በአጠቃላይ ሲታይ ለሰው ልጆች ሁሉ አይቀሬ የሆነው የሞትና የሀዘን ሥርዓት በበርታዎች ዘንድ የበዛ ሃዘንና የመረረ ለቅሶ ሳይኖረው እንዲህ ቀለል ተደርጎ የሚያልፍ ነው። በተለይ ሟች በማህበረሰቡ ትልቅ ስፍራ የሚሰጠው ዕድሜ ጠገብ ጀግና ከሆነ የሚሸኘው በለቅሶ ሳይሆን ቅልጥ ባለ ዘፈንና ጭፈራ ነው።



**ፎቶ 10. ተወካዩን አሥረው በመያዝ ካሳውን በጭፈራ እየጠየቁ**



**ፎቶ 11. ካሳቸውን ብር 200 እና ፍየል ከተቀበሉ በኋላ የበቂ አይደለም ክርክር**

እነዚህ ከላይ ባየናቸው ሁለት ተከታታይ ምዕራፎች በስፋት የቀረቡት ጉዳዮች የበርታ ብሔረሰብን ማንነትና ባህላዊ ተራክቦ የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ ብሔረሰቡ ከአካላዊ መልኩ፣ ከአለባበሱና አጋጊያጡ ጀምሮ የራሱ የሆኑ መለያዎች ያሉት ነው፡፡ በተለያዩ ሀገረሰባዊ ዕምነቶቹ የሚገለፁና በጋብቻ፣ በወሊድና በሀዘን ሥርዓቶቹ የሚለይባቸው የራሱ የሆኑ ባህላዊ እሴቶች ያሉት እርስ በርስ ተረዳድቶ በመኖር የሚታወቅ ብሔረሰብ እንደሆነ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡



ፎቶ 12 ጉዞ የሀዘንተኞች ልብስ አጠባና ከአጠባ መልስ

# ምዕራፍ ሰባት

# 7. የአካባቢውን ልማት ለማፋጠን ያሉ አዎንታዊ ባህላዊ ጉዳዮች

ቀደም ባሉት ምዕራፎች የበርታን ብሔረሰብ ማንነት የሚገልፁ ዋና ዋና ባህላዊ መልኮች በስፋት ቀርበዋል። በዚህ ምዕራፍ ደግሞ ባህሉ በአካባቢው ልማት አንፃር ያለውን አወንታዊ ሚና የሚገልፁ ጉዳዮች ይቀርባሉ። ከመስክ የተሰበሰቡት መረጃዎች በየመልካቸው ተደራጅተው ሲታዩ በእያንዳንዱ ዘውግ ውስጥ በዋነኛ ጉዳይነት የሚነሱ ቁም ነገሮች በሌሎችም ዘውጎች በሌላ መልክ ተደጋግመው በመምጣት እርስ በርስ እየተሰናሰሉ ሲገለጡ ይታያሉ። ይሄ የጭብጥ መተሳሰር ደግሞ የማህበረሰቡን ማንነት፣ ዕምነት፣ ልማድና ስለዓለም ያለውን አመላካከት ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ ከመሆኑም በላይ ባህሉ ማህበረሰቡን እንዴት ሊቀርፀው እንደቻለም ያመለክታል። በዚህ ሁኔታ የተሰናሰለው ባህላዊ ጭብጥ በክዋኔ አውድ ላይ በተደጋጋሚ በተግባር ሲከወን ደግሞ እራሱን እያጠናከረ ይሄዳል። በዚህ መልኩ የደረጀው የበርታ ባህል ለልማት የሚኖረው አዎንታዊ አስተዋፅዖ ቀጥሎ ይተነተናል።

## 7.1. የበርታ ብሔረሰብ ሁለንተናዊ የጋራ ሕይወትና አኗኗር

የበርታ ብሔረሰብ አባላት የአኗኗር ባህል የተመሠረተው በጋራ አብሮ በመኖር ላይ ነው። በጋራ አብሮ መብላት፣ ደስታንና ችግርን በጋራ መወጣት፣ እንግዳን በጋራ ተቀብሎ አስተናግዶ መሸኘት፣ ጋብቻንና ግጭት አፈታትን በመሰሉ የማህበረሰቡ ዋነኛ ጉዳዮች ላይ በጋራ መወሰን የበርታ ዋነኛ መለያ ነው።

ከላይ በቀረቡት ምዕራፎች በስፋት እንደተዘረዘረው እነዚህ ባህላዊ እሴቶች እርስ በእርስ የተያያዙ የማህበረሰቡን ወግና ልማድ ሳያዛቡ በመደጋገምና እንደ ሰንሠለት በመቀጣጠል ዘወትር የሚከወኑ ናቸው። የበርታ ማህበረሰብ ለባህላዊ ሥርዓቶቹ ተገዢ ነው። በሠርግ፣ በሞት፣ በግርዛት፣ በእንግዳ አቀባበል፣ በወሊድ፣ ወዘተርፈ ጊዜ ሲያከናውናቸው የኖሩ ሥርዓቶች ወጎችና ልምዶች ዘመናዊነትና ሌሎች ሁኔታዎች ሳያግዱት እስከዛሬ ጠብቋቸው ይኖራል።

የማህበረሰቡ አባላት የጋራ አኗኗራቸው ሁኔታ ከመኖሪያቸው ይጀምራል። በርታዎች በአንድ ሰፈር ሰብሰብ ብለው የመኖሪያ ጎጆዎችን ከሠንበሌጥ ሣርና ከቀርከሃ ሠርተው ይኖራሉ። በቤታቸው ዙሪያ አጥር አያጥሩም። ለፍየሎቻቸው ማደሪያም አይሠሩም፤ ከብቶቻቸው እንዲሁ ሰው በሚተላለፍበት መንገድ ላይ በጋራ ያድራሉ። ሌባ ይነዳቸዋል ብለውም አይሰጉም።

በአንድ መንደር በተለይ በሀገር ሽማግሌዎች መኖሪያ አካባቢ የሚሠራ “አል ከለዋ” የሚሉት ትልቅ ዛኒጋባ የመሰለ ቤት ይኖራል። ይህ ቤት የሰፈሩ ወንዶች በሙሉ ተሰብስበው ከየቤታቸው የሚላከውን የሚመገቡበት፣ በጋራ ጉዳዮች ላይ የሚመክሩበት፣ መረጃዎችን የሚለዋወጡበትና ቀኑን የሚያርፉበት ቤት ነው። ማንም የማህበረሰቡ ወንድ ምግቡን ከግል ቤቱ ውስጥ አይመገብም፤ ከቤቱ ተሠርቶ ወደ “አል ከለዋ”ው ይላክለታል፤ በጋራ ይበላል። ሴቶቹም እንደዛው ሰብሰብ ብለው ከልጆቻቸውና ከጎረቤቶች ጋር በጋራ ከቤት ውስጥ ይመገባሉ። “በአል ከለዋ ተገኝቶ አብሮ የማይበላ እንደ “ከልቢ” (እንደውሻ) ይቆጠራል” ይላሉ በርታዎች፤ይህንን እሴታቸውን በምሳሌያዊ ንግግራቸውም እንዲህ ያጠናክሩታል።

"አዱኒ መተተኪ፤ አዱኒ መተተኪ አጫ አታታግራ"

"አብረን እንብላ፤ ሁልጊዜም አብረን እንኑር"

(አባ አልኑር አብደላ፣ቃመ 14/04/05)

ከላይ የቀረበውን የበርታዎች ምሳሌያዊ አነጋገር ስንመረምረው አብሮ መብላትና አብሮ መኖር የብሔረሰቡ እሴት እንደሆነ እንገነዘባለን:: አብሮነት ነጠላነትን ይጠየፋል፤ ነጠላነት ራስ ወዳድነት፣ ስስት፣ ግለኝነት ነው:: በበርታ ይህ የዘመናዊነት (Modernization) መርህ የሆነው ግለኝነት ፈፅሞ አይታወቅም:: በርታዎች ሁልጊዜም አብረን እንኑር የተገኘውን ተካፍለን እንደር ባይ ናቸው:: እንደውም ስስታምንና የማያካፍልን ሰው "ቢጎን ቡፉኩንዴ" "ሆዱ የተቀደደ አሞራ" ይሉታል:: ሆዱ የተቀደደ አሞራ ቢበላ ቢበላ እንደማይጠረቃ ሁሉ ያለውን የማያካፍልና ብቻውን መብላት የሚወድ ሰው ሲሰበስብ ቢኖር አይረካም፤ አብሮ በመብላትና በማካፈል ግን እርካታ አለ ማለት ነው:: ይሄ ስስትን መጠየፍ በተረቶቻቸው ተደጋግሞ የሚገለፅ ነው ቀጥሎ ያለውን ተረት ለአብነት እንመልከት::

> በድሮ ጊዜ አንድ ስስታም ሰው ከሚስቱ ጋር በአንድ ሰፈር ውስጥ ይኖር ነበር:: ሁለቱም ስስታሞች ስለነበሩ እንግዶችን ተቀብለው አያስተናግዱም፤ ያላቸውንም አያካፍሉም:: ሰውየው ታናሽ ወንድም ነበረው:: ታናሽየውና ሚስቱ ግን ለጋሶች ናቸው:: እንግዶችን ተቀብለው ማስተናገድና ተካፍሎ መብላት የዘወትር ተግባራቸው ነው:: ከዕለታት አንድ ቀን ሁለቱን ወንድማማቾች ራቅ ወዳለ ሥፍራ የሚያስኬድ ጉዳይ ይገጥማቸውና አብረው ለመሄድ ይስማማሉ:: ስስታሙ ሰው ገና ካሁኑ ለወንድሙ ላለማካፈል ስለፈለገ "በል

> ሚስቶቻችንን ሄደን ስንቅ እንዲያዘጋጁልን እንንገር" ይለዋል። ለጋሱ ደግሞ "እኔ ስንቅ አያስፈልገኝም የሚስቴን እጅ እበላለሁ" ይለዋል። ስስታሙም እንደሱማ ከሆነ ደግ ይልና እቤቱ ገብቶ የሚስቱን እጆች ይቆርጥና ለስንቁ ይዞ ጉዞ ይጀምራሉ፤ አምሻሽ ላይ ከአንድ መንደር ሲደርሱ ወደ አንድ አልከለዋ "አሰላማሌያኩም" ብለው ይገባሉ። እዚያም ያሉ ሰዎች ተቀብለው በደንብ ያስተናግዷቸዋል። አረፍ እንዳሉም ቤቱን የሚያስቀይም ሽታ ይሞላዋል፤ ምንድነው ብለው ሲፈልጉ ስስታሙ ለስንቅ የቋጠረው ነገር መሆኑ ይታወቅና ፈተው ሲያዩት ሁለት የተቆረጠ እጅ ይሆናል። በዚህ ጊዜ ሽማግሌዎች ነገሩን ሲያጣሩ ስስታሙ ሰው ጥፋቱን በለጋሱ ወንድሙ ላይ "እሱ ነው እንዲህ እንዳደርግ የመከረኝ" በማለት ለመላከክ ይጀምራል። ለጋሱም ሰው "ለጉዟችን ስንቅ እንዲያዘጋጁልን ለሚስቶቻችን እንንገር ስለኝ የሚስቴን እጅ እበላለሁ ያልኩህ ቆርጬ እበላዋለሁ ማለቴ አልነበረም። ሚስቴ በሚገባ ስታስተናግዳቸው የቆየችው ሰዎች በሄድኩበት ያስተናግዱኛል ማለቴ ነበር። የስስታምነትህ መጨረሻ ነው የሚስትህን እጅ ያስቆረጠህ" አለው ይባላል[30]። (አባ መሃመድ አልሀሰን፣ ተረት 19)

በርታዎች የስስትን ነውርነት በተረቶቻቸው በተደጋጋሚ የሚያነሱት ስለሆነ ኑሮዋቸው በመረዳዳትና ተካፍሎ በመብላት ላይ እንዴት እንደተገነባ መመልከት ይቻላል። ከላይ በቀረበው ተረት የሚታየው ስስታሙ ለስንቅ የሚሆን ነገር እሱ ይዞ ቢመጣ ወንድሙ

[30] በዚህ ጥናት የተሰበሰቡና ከጥቅም ላይ የዋሉ ተረቶች አብዛኞቹ ተረት ነጋሪዎቹ በራሳቸው ቋንቋ ተርተውልኝ ወዲያው በአስተርጓሚዎቼ በአማርኛ እየተመለሱ የተነገሩኝ ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ ተራቾቹ ራሳቸው በአማርኛ ቋንቋ የነገሩኝ ናቸው። ለትንታኔ ከጥቅም ላይ የዋሉትም ሆነ አባሪ የተደረጉት በአማርኛ ቋንቋ የሆኑት በዚህ ምክንያት ነው።

እንዳይካፈለው አስቦ ነው ወደየቤታቸው ሄደው በየግላቸው ስንቅ እንዲያዘጋጁላቸው ለሚስቶቻቸው እንዲነግሩ ያሳሰበው። ለጋሱም ሰው ሲያደርግ የኖረውን መልካም ተግባር ስለሚያውቅ የሚስቴን እጅ እበላለሁ ብሎ በኩራት ይመልሳል። እዚህ ላይ የለጋሱና የንፉጉ ሚስቶች እጅ በተነፃፃሪነት የቆመ የንፍገትና የልግስና ተምሳሌት ነው። የስስት አስከፊነት የሚስትን እጅ እስከመቁረጥና እጅ አልባ እስከማድረግ እንደሚያደርስ የሚያካፍል እጅ ግን ለምልሞ እንደሚቆይ በማሳየት ብሔረሰቡ የስስትን አስከፊነትና የልግስናን ጥቅም እንዲህ በተረቱ አማካይነት ሲተክለው ይታያል። ሌላው ተረት ደግሞ እንዲህ ይላል፡-

> በዱሮ ጊዜ አንድ ልጅ የነበረው ስስታም ሰው ነበረ። ያለውን ለማንም ሰው አያካፍልም። የሚያውቀው ሀብትን ለራሱ ብቻ ማከማቸት እና ከሌሎች መሰብሰብ፣ መቀበልና ማጠራቀም ብቻ ነበር። መስጠት የሚባል ነገር ፈፅሞ አያውቅም። አንድ ቀን ከልጁ ጋር ሆነው መንገድ ሲሄዱ ወንዝ ያጋጥማቸውና ለመሻገር አባትየው ቀድሞ እንደገባ ደራሽ ውሃ ይመጣና ሊወስደው ያንገላታዋል፡፤ በዚህ ጊዜ ልጁ ከወንዙ ሊያድነው ፈልጎ "አባዬ እጅህን ስጠኝ! እጅህን ስጠኝ!" እያለ ሲጮህ መስጠት ያለመደው ስስታም እምቢ ብሎ ወንዙ ይወስደዋል። በኋላም ልጁ አባቱን "እጅህን ስጠኝ እያልኩት እምቢ ብሎ ወንዝ ወሰደው" ብሎ ሲነግራቸው አንድ ሽማግሌ "አይ ልጄ የአንተ አባት ስጠኝን መች ይወድና ነው? እጄን እንካ ብትለው ይተርፍ ነበር።" አሉት ይባላል (እማ ፋጢማ፣16/04/05፣ተረት20)።

በዚህ ተረት የምናየው የሰውየው ንፍገት የት ድረስ እንደሆነ ነው። ስጠኝን ስለማይወድ ራሱን ለማዳን ለተዘረጋለት እጅ እንኳ እጁን ነፈገ። ከሞት ሊታደገው የነበረው ደግሞ

ልጁ እንደነበር ስናይ ሰውየው ለልጁ እንኳን ቢሆን መስጠትን እንደማይፈቅድ የሚያስገነዝብን ሆኖ የሰውየው ስስት የከፋ መሆኑን ያመለክታል። ውጤቱ ደግሞ አጋብሶ አጋብሶ ሳይበላው ለሞት መዳረግ ነው ይላል ተረቱ። (ተረት 30፣36 በተጨማሪ ማየት ይቻላል) በርታ ስስትን እንዲህ በተለያየ ምሳሌ እያንቋሸሸ አብሮ ተካፍሎ የመብላትን ተገቢነት እያፀደቀ ስለሚኖር ያለውን ማካፈልና ለጋስነት መለያ ባህሉ እንዲሆን አስችሎታል።

በብሔረሰቡ ባህል በጋብቻ ግዜ አንድ ሰው ለትዳር የተመረጠችውን ልጁን ከማህበረሰቡ ጋር ቁጭ በማለት ለማግባት የጠየቃትን ሰው በጋራ ገምግሞ፣ ነውር ካየበት ጠባዩን እንዲያርም መክሮ፣ ቀጥቶ፣ በጋራ ተስማምቶ እንዲጋቡ ይፈቅዳል። ለሠርግና ለጥሎሽ የሚያስፈልገውን ወጪ በጋራ ይከፍላል፤ ሥራውን በጋራ ይሠራል፤ ደስታውንና ግብዣውን በጋራ ይታደማል። አንድም በግል የሚያስጨንቅ ጉዳይ የለም። ሁለቱም ተጋቢዎች የወላጆቻቸው የግል ልጆች ሳይሆኑ የማህበረሰቡ የጋራ ልጆች ናቸው። ስለዚህ የጋብቻውና የሠርጉ ጉዳይ የጋራ ነው።

“አል ፈተሃ” የተባለውን የታጨችው ልጅ እህቶችና አክስቶች ብቻ የሚሳተፉበትን ጥሎሽ አንዷ እህት ወይም አክስት ከመካከላቸው ባትኖር ድርሻዋ ይቀመጥላታል እንጂ ሌሎች አይጠቀሙበትም። የአንዱ “ሃቅ” ለሌላው አይተላለፍም።

በበርታዎች ባህል የግል ጉዳይ የግል ችግር፣ የግል ሀዘን፣ የግል ደስታ፣ የግል ገቢ አይታወቅም። አንዱ ዘንድ ያለ ነገር የሁሉም ነው። አንድ ሰው ወርቅ ቆፍሮ ሸጦ ዳጎስ ያለ ገንዘብ ቢያገኝ ለግሉ ብቻ አይጠቀምበትም፤ ዘመዶቹን ሰብስቦ ያበላል። በርቀት ላሉት ሳይቀር ይልካል፤ አብሮ ይደሰታል። ይሄኛው የሩቅ ዘመዴ ስለሆነ አይገባውም፤ ብሎ ነገር አይታወቅም። የተገኘውን ተካፍሎ ይበላል፤ ሲያጣ "በብድሬን ልክፈል ስሜት ወይም የቸገረኝ ቀን ይረዳኛል" በሚል ሳይሆን እሱ ቢቸገር በቸርነት የሚሰጠው ሌላ በርታ ስለሚኖር ለነገው ሳይጨነቅ በልግስና ያካፍላል። የእሱ ገንዘብ የሁሉም፣ የማንም

ገንዘብ የእሱ ነው። እንግዳም በአካባቢው ሲመጣ የሁሉም እንግዳ ነው፤ በጋራ ይስተናገዳል፤ ተቸግሮ ከሆነ የጋራ መፍትሔ ይፈለግለታል። ሲሸኝም በጋራ ይሸኛል።

በርታ ግለኝነት ያልገበኘው ተካፍሎ መብላትንና በጋራ መኖርን ከምር የሚተገብር ገር ብሔረሰብ ነው። ለበርታ  አንድ ሰው አንድ ነገር አድርጎ ታላቅ ምስጋና የሚጠብቅ ወይም አደረግሁ ብሎ ለመኩራራት የሚቃጣ ከሆነ ተሳስቷል። ያደረው ስላለውና ማድረግ ስለቻለ እንጂ ውለታ ለመጣል ወይም ምስጋና ለማግኘት አይደለም። በርታ እንደዚህ አይገነዘበውም። የፈለገ ከባድ ነገር ቢሰጠው ወይ ቢያደርግለት ፈገግ ብሎ ሊቀበለው፣ ከበዛም በአጭሩ "ሽኩረን" ብሎ ምስጋናውን ሊገልፅ ይችላል ። ከዚያ ባለፈ እዚህ አንድ በያይነቱ ጋብዞ ድምፁን ከፍ አድርጎ ሲያወራ እንደሚውለውና የምስጋና መዓት እንዲዥጎደጎድለት እንደሚጠብቀው እዚያ ፍሪዳ ቢጥል ከዚህ በላይ ምስጋና አያገኝም።

በአንፃሩ አንድ ሰው ሰስቶ ወይም ላለማካፈል ፈልጎ ማድረግ እየቻለ ዝም ቢለው በርታ ባይኖረው ነው ብሎ ያስባል እንጂ ስስቱን አይገነዘበውም። ስስት የሚባል ቃል በበርታ አይታወቅም፤ "ካለ ማካፈል እንጂ መሰሰትን ምን አመጣው?" ይላል። እናም የለኝም ቢለው ያምነዋል። እሱን ካልከበደው ካንዱ “አል ከለዋ” ወደ ሌላው “አሰላማሊኩም” እያለ ካለምንም ወጪ መቀለብ ይችላል። ይህን እሴት “ባመዊካሪም” “እንደወገኖችህ ለጋስ ሁን!” በሚለው ምሳሌያዊ ንግግሩ ያፀድቀዋል፤ ያጠናክረዋል።

ሴቶች ጠዋት ተነስተው በአንዱ ጎጆ ውስጥ ጭስ ሲጨስ ባያዩ እገሊት የምታበስለው ቸግሯት ይሆናል ብለው ካላቸው ላይ ከፍለው ይልኩላታል እንጂ አይተው ዝም አይሏትም። እሷም የምትፈልገው ነገር ካለ አንዷ ቤት ሄዳ ስጪኝ ብላ ትወስዳለች እንጂ “በምን ይሉኝ” አትቀመጥም። የምትወስደውም ብድር አይደለም፤ በቃ ያለው ለሌለው ማካፈል ባህላቸው ስለሆነ ካለስጋት የምትፈልገውን ጠይቃ ትወስዳለች ሰጪም በልግስና ያላትን ታካፍላለች።

ብሔረሰቡ በጥንት ጊዜ በአካባቢው ግጭትና ጦርነት ተከስቶ ለውጊያ ሲሠማራ ጦሩን በማነቃቃት የሚመራ በእምቢልታ በመለከትና በከበሮ የሚታጀብ ባህላዊ የሙዚቃ ቡድን እንደነበረ እና የሙዚቃ መሣሪዎቹ አሁን ጦርነት ባይኖርም በበዓላትና ትላልቅ ሰዎች ሲሞቱ እንደሚወጡ ከላይ ሀገረሰባዊ ልማዶችን በሚዳስሰው ምዕራፍ ተነስቷል። ይህ የሙዚቃ ባንድ በሙዚቃ መሣሪያዎቹ እንዴት እንደሚጠቀምባቸውና ምን ምን ባህላዊ ክዋኔዎች ይካሄዱ እንደነበር ሲነግሩኝ መሣሪያዎቹ ለሥራ ሲወጡ በእነሱ ባህላዊ ዕምነት መሰረት ደም ሳይፈስ አይሆንምና ሙዚቃው የሚጀመረውም በሬ ወይም ፍየል ታርዶ ከደሙ መሣሪያዎቹ ላይ ተረጭቶ እንደነበር አይተናል።፡ ክዋኔውን እዚህ የማነሳው ለበርታ ተካፍሎ የመብላትና በጋራ የመኖር ባህል ጥሩ ማሳያ ይሆንልኛል ብዬ ነው። እኔ እዚያ በተገኘሁበት ወቅት በዓል ስላልነበረ የመሣሪያዎቹን አጠቃቀም ያሳዩኝ በአርተፊሻል መቼት[31] ነበር። ለዚህም የሙዚቃ መሣሪያዎቹን በደም ለመፈወስ የታረደው ዶሮ ነበር። የዶሮው ደም ሙዚቃ መሣሪያዎቹ ላይ በቅጠል ነገር ከተረጨ በኋላ ሙዚቀኞቹ ሥራቸውን ጀመሩ።

እዚያ ከታደሙት ሰዎች መካከል ሁለት ወንዶች ትንሽ እልፍ ብለው እሳት አያያዙና የታረደውን ዶሮ ከነላባው መለብለብ ጀመሩ። አንደኛው ሰውዬ የተለበለበውን ዶሮ በብልት በብልቱ እየቆራረጠ በድጋሚ ወደሚነደው እሳት ይወረውራል። አንደኛው ሲገነጥል በመያዝና እሳቱን በመቆስቆስ ይራዳል። የተቆራረጠውን ብልት እያገላበጡ በሚነደው እሳት ላይ ካበሰሉ በኋላ እያወጡ ትሪ ላይ አድርገው እንደገና በትንንሹ መከትከት ጀመሩ። እያንዳንዱ ብልት ቅርፁን አጥቶ ጠጠር እስኪመስል ድረስ ተከተከተ። ጉዳዩ ስለገረመኝ ምክንያቱን ጠየቅሁ። "ከዶሮው በዚያ የተገኘው ሁሉ ህፃን አዋቂ ሳይል መቅመስ ስላለበት ነው" (ኢብራሂም አልፈኪ፣ ቃመ14/04/05) አሉኝ። ከዚያም ህፃናቱን ጨምሮ በግምት ከሃምሳ በላይ ለሚሆኑ ሰዎች ዶሮው ታደለ። "የዶሮ ብልት አስራ

[31] አርተፊሻል መቼት ያልኩት ለሙዚቃ መሣሪያዎቹ ወጥቶ ከጥቅም ላይ መዋል ቀድሞ እንደነበረው ጦርነት፣ ወይም አሁን እንደሚጠቀሙበት በዓልስላልሆነ፣ ወይም ታላቅ እንግዳ ወደሥፍራው ስላልመጣ ነው፡፡ መሣሪያዎቹ ወጥተው የተደረገው ክዋኔ ግን ፍፁም ተፈጥሮኣዊ ነበር

ሁለት፣ ለአባወራ ፈረሰኛ፣ ለባልና ሚስት መቋደሻ…" የሚሉ የግለኝነት አስተሳሰቦች በበርታ ባህል አይታወቁም፡፡ የተገኘውን ህፃን አዋቂ ሴት ወንድ ሳይባል አብሮ መቃመስ ስለነበረበት ለሁሉም ተዳረሰ፡፡

አባ አቶም የተባሉት መረጃ ሰጪዬ ከራሳቸው ገጠመኝ ተነስተው የነገሩኝ ይህንኑ የበርታን የጋራ ህይወት የሚያረጋግጥ ሌላ ዕውነት ይህንኑ የሚያጠናክር ነው፡፡ አባ አቶም ሙስጦፋ ጥንት የበርታ "አጉር" ወይም ንጉስ የነበሩት የደጃዝማች ሙስጦፋ መሀመድ ልጅ ናቸው፡፡ የሚኖሩት አሶሳ ከተማ ሲሆን ቀድሞ የክልሉ ፕሬዘዳንት ነበሩ፡፡ አሁን በጡረታ ላይ ስለሚገኙ ኑሯቸውን ለመደጎም አነስተኛ የህዝብ ማመላለሻ (ሚኒ ባስ) ገዝተው ከአሶሳ የበርታ ብሔረሰቦች ዋነኛ መኖሪያ ወደሆኑት ሆመሻ፣ መንጌና ሸርቆሌ ለመሥራት በመፈለግ ለሾፌር ይሠጣሉ፡፡ አባ አቶም መኪና መግዛታቸውን ሁሉም በርታ ይሰማል፡፡ ትንሽ ቆይቶም መኪናዋንም ለይቶ ያውቃታል፡፡ ከዚያ ከአሶሳም ሆነ ከተጠቀሱት ወረዳዎች ወደሚፈልገው አቅጣጫ ለመሄድ መኪናዋን ካገኘ ግጥም አድርጎ ይሞላና ሒሳብ ሲጠየቅ "መኪናው የአባ አቶም አይደለም እንዴ? ብሎ ይጠይቃል፡፡ አዎ የሚል መልስ ሲሰጠው "ታዲያ ለሱ ለምንድነው የምከፍለው? " በማለት ክርክር እየገጠመ ስላስቸገረና ሰውየው ሥራው በነፃ ማመላለስ ሲሆንባቸው ራሳቸው መኪናዋን በመያዝና ቤታቸው ድረስ መኪና ኮንትራት ፈልገው የሚመጡ የሌላ ብሔረሰብ አባላትን በእሳቸው አጠራር ሀበሾችና የውጪ ዜጎችን ብቻ ለማመላለስ መገደዳቸውን አጫውተውኛል፡፡[32]

በርታዎች እንዲህ ናቸው፣ ለዚያውም የጥንቱ አጉራቸው ንጉሳቸው ልጅ መኪና ቀርቶ የሌላውም በርታ ንብረት የሁሉም ነው፡፡ አባ አቶም የሁሉም በርታ ናቸው መኪና ቢገዙ መኪናዋም እሳቸውም የራሱ ናቸው፡፡ ለራሱ ደግሞ መክፈል የለበትም ከአሰኘው ቦታ

[32] ይህንን መረጃ ያገኘሁት መንጌ ላይ ራሳቸው መኪናዋን ይዘው ሳገኛቸው "ለምን ለሾፌር አይሰጡም?" ብዬ በመጠየቄ ነው፡፡

በነፃ ይመላለሳል እንጂ ክፊል ተብሎ መገደድ የለበትም፤ እሱም ከመነሻው እከፍላለሁ ብሎ አያስብም፡፡

ከላይ በቀረቡት ማሳያዎች በግልፅ እንደሚታየው በርታዎች ግለኝነት አያውቁም፤ ያገኙትን በጋራ ተካፍለው ይኖራሉ፡፡ በግላቸው ሃብት ማፍራት ጥሪት ማካበት የሚባል ነገር አይገባቸውም፡፡ የአንዱ አባላቸው ሀብት የራሳቸው ነው፤ የእነሱም የሌላው ነው፡፡ ሁሉን በጋራ ይከውናሉ፤ በጋራ ይኖራሉ፡፡ "ብዙ ሆኖ መስገድና ተካፍሎ መብላት የፈጣሪ ስጦታ ነው!!" ይላሉ በርታዎች እናም ይህን የፈጣሪ ስጦታ አክብረው ይተገብሩታል፡፡ ንፉግና የማያካፍልን ሰው "መአን ህንዲ" (የበጋ ዛፍ) ይሉታል:: የበጋ ዛፍ ፍሬ አይሰጥ፣ አያስጠልል፤ ያለውን ለራሱ ብቻ እየበላ የሚቀመጥ ንፉግ ነው ለማለት፡፡

የባህልን የአስተማሪነትና የአጠናካሪነት ተግባር የሚገልፁት ምሁራን እንደሚያስረዱት ባህል የአኗኗር ሥርዓትንና በጎ ምግባርን እያስተማረ ይኸው ሰናይ ምግባር በማህበረሰቡ ውስጥ እንዲተከል የራሱንም ሚና ይጫወታል ይላሉ (Sims& Stephens, 2005፣ ፈቃደ 1991)፡፡ ከላይ የተመለከትነው ይሄን ተግባሩን ነው፡፡ በርታዎች በዘልማዳዊ ተግባሮቻቸው፣ በምሳሌያዊ ንግግራቸውና በአስተሳሰባቸው ሁሉ ይህንኑ ባህላቸው የሰጣቸውን ተካፍሎ የመብላትና የጋራ ህይወት ሲተገብሩት ይታያሉ፡፡ ለበርታዎች ከዚህ ውጪ ግለኛ የሆነ ህይወት ፈፅሞ የተወገዘ ነው፡፡ ይኸው የጋራ ህይወታቸው በልዩ ልዩ መልኩ ራሱን እየደጋገመ በመከሰት እየተንሰራፋ ሥር እየሰደደና እየሠረፀ ይሄዳል፡፡

በዚህ የተነሳም በበርታ ማህበረሰብ ደግም ሆነ ክፉ፣ ማግኘትም ሆነ ማጣት፣ መብላትና መጠጣት በጋራ እንዲሆን ባህሉ ራሱን በሁለንተናዊ መልኩ ተክሎ እንደኖረ ማየት ይቻላል፡፡ ይህን የጋራ አስተሳሰብ በማልማትና በማጠናከር ደግሞ በጋራ የመስራትን፣ በጋራ የማደግናን አካባቢን የመለወጥን አስተሳሰብ በብሔረሰቡ ውስጥ ለማምጣት የሚያስችል ጥሩ መሠረት ማድረግ ይቻላል፡፡

## 7.2. ግጭቶችን በጋራ መፍታት

ይህ የጋራ አስተሳሰብና አኗኗር ባህላዊ እሴት በብሔረሰቡ እያንዳንዱ እንቅስቃሴ ውስጥ እየተደጋገመ በመምጣት እየሠረጀ የኖረ በመሆኑ ግጭቶችን ለመፍታትና የአካባቢን ሰላም ለማስፈን እንዴት ያለ ምቹ ሁኔታ እንደሆነ በተለያዩ ማረጋገጫዎች ማሳየት ይችላል፡፡

በርታዎች ችግሮቻቸውንም በጋራ ተወያይተው ስለሚፈቱ አልፎ አልፎ ካልሆነ በቀር በመካከላቸውም ይሁን ከሌላው ብሔረሰብ ወይም ማህበረሰብ ጋር ግጭት የማያውቁ ሰላማዊ ሰዎች ናቸው፡፡ እርስ በእርስ በተፈጠረ አለመግባባት እንዳጋጣሚ የሰው ህይወት ቢያልፍ እንኳን ገዳይ ለሀገር ሽማግሌዎች ሄዶ ጉዳዩን ያስታውቃል፡፡ ሽማግሌዎቹ ጉዳዩን እንደሰሙ ገዳይን ያስቀምጡና ሟችን ለመቅበር በጋራ ይነሳሉ፡፡ የሟች ቤተሰቦች ለበቀል እንዳይነሳሱ "አንዱን አጥተናል፤ ሁለተኛውን ደሞ ማጣት የለብንም፡፡ የፀቡ መንስኤ ምን እንደሆነ እስከምናጣራ የሞተውን በጋራ እንሸኝ"[33] ብለው ሁኔታውን በማረጋጋት ቀብሩንና ሀዘኑን ያስፈፅማሉ፡፡

ሟችም ገዳይም የጋራ ልጃቸው ስለሆኑ ከሃዘኑ በኋላ በጋራ ሆነው ጉዳዩን ያጣራሉ፡፡ በምን ምክንያት እንደገደለው እንዲያስረዳ የሚጠየቀው ገዳይ ነው፡፡ በባህላቸው ውሸትና ቅጥፈት ስለሌለ ገዳይ ዕውነቱን ያስረዳል፡፡ ሽማግሌዎች ለመግደል ያነሳሳውን ጉዳይ ያጣሩና ጥፋቱ የሟች ከሆነ የሞተው በሥራው ነው ብለው በእርቅ ይፈቱታል፡፡ የሟች ቤተሰቦችም ጥፋቱ የልጃቸው መሆኑን ካወቁ ወዲያው ገዳይን ይቅር ይላሉ እንጂ ለበቀል አይነሳሱም ወይም ወደ ህግ ቦታ አይሄዱም፡፡ ገዳይ ከዋሸ እና መግደሉን ሳይናገር ከቀረ ግን ጉዳዩ ተጣርቶ ሲታወቅ ዕውነትን መሸሸግ የበርታ ባህል ስላልሆነ ሽማግሌዎቹ

---

[33] አባ አልሀሰን፣ ቃመ15/03/05፣ወጣት አብዱልናስር፣ቃመ16/03/05፣ አባ አቶም፣ ቃመ25/04/05

“በእጃችን ልናጠፋህ አንፈልግም ግን ዓይናችን ወደማያይህ ሀገር ጥፋ፤ በችግርህም ሆነ በደስታህ ተመልሰህም እንዳትመጣ” በማለት ከማህበረሰቡ አካባቢ እንዲርቅ ይነግሩታል፤ እሱም ላይመለስ ተነጥሎ ይጠፋል። ይሄ ከማህበረሰቡ መነጠል እንደትልቅ ቅጣት ስለሚቆጠርና ሀሰተኛ መሆንም በባህሉ ስለሚወገዝ ማንም ሰው ጥፋቱን ሰው ቢገድል እንኳን ሄዶ መግደሉን እስከምክንያቱ ለሽማግሌዎቹ ያስረዳል እንጂ ጥፋቱን አይሸሽግም። ከዚህ አልፎ ሰውን ካለአግባብ ገድሎ ቢደብቅ አላህ ራሱ ያጋልጠዋል ብለው ያምናሉ። ለዚህ ማሳያ የሚሆን ተረታቸውን እንመልከት።

> በድሮ ጊዜ ሰባት ወንዶች ልጆች ያሉት ሃብታምና አንድ ልጅ ያለው ደሃ በአንድ መንደር ይኖሩ ነበር። ሁሉም ልጆች ለንግድ የሚጠቀሙባቸው አንዳንድ አህዮች ነበሯቸው። ሰባቱ ወንድማማቾችና ብቸኛው ልጅ ለንግድ የሚሄዱበት መንገድ ተመሳሳይ በመሆኑ ሁሌም ይገናኙ ነበር። ከዕለታት አንድ ቀን ሰባቱ ወንድማማቾች ወደ ንግድ ሲሄዱ ይደክማቸውና  ዛፍ ጥላ ሥር አርፈው ሳለ የደሃው ልጅ ብቻውን አህያውን እየነዳ ሲመጣ ያዩታል። ከሰባቱ ወንድማማቾች አንዱ ይነሳና “ተመልከት እኛ ሰባት ነን፤ አንዳችን ብንጠቃ ሌሎቻችን ተጋግዘን ጠላታችንን እናጠፋለን፤ አንተ ግን ነጠላ ነህ ማን ያግዝልሃል?” ብሎ ይጠይቀዋል ብቸኛው ልጅም “ለእኔ አላህ አለኝ፤ እሱ ያግዝልኛል” ይላቸዋል። በዚህ ጊዜ የጠየቀው ልጅ ይናደድና “እስቲ አሁን ሲያግዝልህ እንይ” ብሎ ጭንቅላቱን ሲለው ልጁ ይሞታል። እነሱም ሬሳውን ጥለውት ወደ ንግዳቸው ይሄዳሉ። ጥቂት ወራት ቆይተው ወደ ሠፈራቸው ሲመለሱ ብቸኛውን ልጅ ከገደሉት ሥፍራ ላይ አንድ እራስ የበሰበሰ በቆሎ ያገኛሉ። በቆሎ የመድረሻው ወቅት ባለመሆኑ ተገርመው እየተነጋገሩ ሳለ አንደኛው ልጅ የሚሆነው አይታወቅም እስቲ ልያዘው ይልና ከኮሮጆው ውስጥ ጨምሮት ወደቤታቸው ይሄዳሉ። ከንግድ

> እንደተመለሱ ያወቀው የሟች አባት የእሱን ልጅ አይተውት እንደሆን ይጠይቃቸዋል፡፡ እንዳላዩት ከመለሱለት በኋላ አንዱ ወንድማቸው “እሱንስ አላየነውም በመንገዳችን ላይ ግን የበሰበሰ በቆሎ አግኝተን ተገርመናል ቆይ ላሳይህና ምን ታምር እንደሆነ ትነግረናለህ” ብሎ በኮረጆው የያዘውን በቆሎ ሊያሳየው ሲያወጣው የሰውየው ልጅ ጭንቅላት ይሆናል፡፡ ከዚያም “ልጄን ገደላችሁት” ብሎ ሲጮህ ሰዎች ይወጡና ይይዟቸዋል፤ ተገቢውንም ቅጣት ያገኛሉ፡፡ (እማ ሀጂጂ አልጣህር፣16/04/05፣ ተረት18)

በበርታ ባህል ከመነሻውም ሀሰት መናገር ሀራም ነው፡፡ ነገርግን ሰውን ካልበደሉ አጥፍቶ ራሱን ለመደበቅ የሚፈልግ ቢኖር እንኳን ሁሉን የሚመለከት አላህ በይፋ ያጋልጠዋል ማለት ነው፡፡ የተጋለጠ ዕለት ደግሞ ከብሔረሰቡ ተነጥሎ መጥፋትንና መሰደድን የመሰለ ከባድ ቅጣት ስለሚያስከትል ማንም ሰው የሰውን ህይወት ካለአግባብ ለማጥፋት እንዳይነሳ በተረቱም እንዲህ እያስጠነቀቀ ሰላምን በአካባቢው ያሰፍናል፡፡

በብሔረሰቡ ውስጥ የተፈጠረን ግጭት እንዲህ ባለው ባህላዊ መንገድ መፍታት በአንድ በኩል ሰላማዊ ኑሮን የበለጠ እንዲጎለብት ያግዛል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የፍርድ ቤቶችንና የፀጥታ አካሎችንም የሥራ ጫና ይቀንሳል፡፡ ራሱና አካባቢው ሰላም የሆነን ማህበረሰብ ደግሞ አካባቢውን ለማልማት ማነሳሳት በቀላሉ ሊከወን የሚችልና ለዘላቂ ልማትም ዋነኛ ምቹ ሁኔታ ነው ማለት ይቻላል፡፡ የዩኔስኮ የ2012 ሰነድ እንደሚለው ለባህላዊ ሁኔታዎች ለማህበረሰቡና ለአውዱ የተለየ ትኩረት የሚሠጡ የልማት ተግባራት ዘላቂና እርስ በርስ የተዋሃዱ፣ ፍትሃዊና አመርቂ የልማት ውጤቶችን ያስገኛሉ፡፡ ለባህል እሴቶች ትኩረት መስጠት የሰብዓዊ መብት አከባበር አካሄዶችንና ያለመግባባትንና ግጭቶችን ለማስወገድ ይረዳል፡፡ ይህ ሲሆን ደግሞ የልማት ግቦችን ለማሳካት ምቹ

ሁኔታን ይፈጥራል፤ ባህላዊ እሴቶችን በጎ መልክ መረዳት ለዘላቂ ልማት ዓይነተኛ መሣሪያ ነው (UNESCO,2012,5)።

የበርታዎች ሰላማዊ ሰዎች መሆንና በአጋጣሚ የተከሰቱ ግጭቶችን በራሳቸው መንገድ መፍታታቸው በአካባቢያቸው ሰላማዊ ሁኔታን የሚፈጥር በመሆኑ ለልማት አስፈላጊ ምቹ ሁኔታ እንደሆነ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

ከላይ በተለያዩ ማሳያዎች የተነሳው የበርታዎች ሁለንተናዊ የጋራ ህይወት ከአኗኗራቸው ጀምሮ በሁሉም የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴያቸው ተደጋግሞ እየመጣ በመንሰራፋትና ሥር በመስደድ የብሔረሰቡን አስተሳሰብ እየተከለ፣ እያጠናከረ እያረጋገጠም የሚሄድ ነው፡፡ ይህ ሁለንተናዊ የጋራ አኗኗር ሕይወት ደግሞ በጋራ ሰፋፊ የእርሻ መሬቶችን አልምቶ በጋራ ተጠቃሚ ለመሆን፣ በጋራ ስለአካባቢ ልማቶች ተወያይቶ የጋራ ውሳኔዎችን ለማሳለፍና የጋራ ህይወትን የተሻለ ለማድረግ ጠንካራ ባህላዊ መሠረት ስለሆነ እንደ ምቹ አጋጣሚ ቆጥሮ ቢጠቀሙበት የአካባቢውን ልማት ለማፋጠን ዓይነተኛ መሣሪያ መሆን ይችላል፡፡

## 7.3. ሀቀኝነት፣ ግልፅነትና ያልተገባ ጥቅምን አለመፈለግ

በበርታ ማህበረሰብ ታማኝነት ትልቅ ስፍራ ይሰጠዋል፡፡ ዕውነት መናገር፣ አለማታለል፣ ሀቀኝነት፣ ያላቸው ቦታ ከፍተኛ ነው፡፡ ሀሰት መናገር አይታወቅም፤ ጥፋት እንኳን ቢሆን ማንኛውም ሰው ያጠፋሁት እኔ ነኝ ብሎ ዕውነቱን ይናገራል እንጂ አይዋሽም፡፡ ሁሉን በግልፅ ይሠራል፤ ሲጠየቅ የሚያውቀውን ይናገራል፡፡ ይሄው ጭብጥ ከዕለት በዕለት ኑሮዋቸው በዘለለ በሥነቃሎቻቸውም በተደጋጋሚ ሲመጣ ይታያል፡፡ ለዚህ ማሳያ እንዲሆን አንዱን ተረታቸውን ቀጥለን እንመልከት፡፡

> አንድ ሰውዬ ነበር። ማሳ አለው። ማሳውን እያፀዳ እያለ የሆኑ ሶስት ሰዎች የሆነን ልጅ ሌባ ነው ብለው ያባርሩታል፤ ሲያባርሩት፣ ሲያባርሩት፣ ሲያባርሩት፣ ወደ ሰውየው ማሳ ይደርሳል። ሰውየው ደሞ ቆሻሻውን እያፀዳ ከምሯል ከዚያ እዚያ ሲደርስ እያባረሩኝ ነው ሊገሉኝ ነው አድነኝ ሲለው ሂድ እዚያ እተከመረው ሥር ግባና ተደበቅ ይለዋል። ሰዎቹ ሲደርሱ አንተ ሰውዬ የሆነ ልጅ በዚህ አላለፈም? ብለው ሲጠይቁት ያው እዚያ ቆሻሻ ውስጥ አለ ይላቸዋል። አይ ይሄስ እብድ ነው፤ ሰውየው አብዷል እንዴ? ምን ይሠራል ቆሻሻ ሥር? ብለው ጥለውት ይሄዳሉ። ሰዎቹ ከሄዱ በኋላ ልጁ ውጣ ሄደዋል ይለዋል። ይወጣና ትደብቀኛለህ ስል ታጋልጠኛለህ እንዴ? ሲለው ልጁ አለው ሃቅ ካላወጣህ ውሸት አያወጣህም፤ እኔ የለም ብል ኖሮ ይፈትሹና ያገኙህና ይገሉህ ነበር ሃቅ ስለተናገርኩ ነው አንተ የዳንከው አለው ይባላል። (አቶ ኢብራሂም ቃሲም፣ ቃመ29/03/05፣ተረት አሥራ አራት)

ይህ ተረት እንደሚያመለክተው ተሳዳጁን እንዲደብቀው የተጠየቀው ሰው አልደብቅም ብሎ አልከለከለውም፤ አሳዳጆቹ መጥተው ሲጠይቁትም ዕውነተኛውን ቦታ ጠቆማቸው እንጂ "አላየሁትም" ብሎ አልዋሸም። እነሱ ሀሰት ነው ብለው በመደምደማቸው ግን ያሳያቸውን ቦታ ሳይፈትሹ ጥለውት ሄዱ። ምናልባት የተጠራጠሩት በርታዎች ስላልሆኑ ሊሆን ይችላል። የተደበቀው ሰው ከወጣ በኋላ ያነሳው ጥያቄ "ለምን ዕውነቱን ተናገርክ? ልታስገድለኝ ነበር?!" ነው። እሱም በርታ አይመስለኝም፤ ቢሆን እንዲህ አይጠይቅም ነበር። የሰውየው መልስ ግን ***"ሃቅ ካላወጣህ ውሸት አያወጣህም "*** ነው። በተረቱም የታየው ይሄው የበርታ ዕውነት ተናጋሪነት ነው። በርታ እንዲህ ዕውነቱን ተናግሮ እመሸበት የሚያድር ማህበረሰብ ነው።

ይህ የታማኝነትና የዕውነተኝነት ጭብጥ በሌሎቹም ተረቶች እንዲሁ ተደጋግሞ ይነሳል፡፡ ካለፈቃድ የተወለደችው የንጉስ ሴት ልጅ እንዳትገደል ከሀገሯ ኮብልላ ራሷን ደብቃ ስትኖር ሀቁ ሲወጣና ማንነቷ ሲገለጥ የኮበለለችበትን ሀገር ንጉስ የሚስትነት ክብርን ትጎናፀፋለች፡፡ (አባ ኢብራሂም አደም፣ ቃመ14/04/05፣ ተረት 11)፡፡ ጉጉት በምሽት ባልና ሚስት ሲወያዩ የሰማውን ጉዳይ መሠረት አድርጎ ዕውነታውን በምሳሌ ለባልየው በማስረዳቱ የአዕዋፍ ዘርን ከመገደል ያድናል፡፡ (አቶ ኢብራሂም ቃሲም፣ ቃመ29/03/05፣ ተረት 12)፡፡ አጎት አዎር ሰዎችንና እንስሳትን ሲያታልል ቆይቶ መጨረሻው በስቃይ ይደመደማል (አባ ጂማ ነሱር፣ 09/03/05፣ ተረት 10)፡፡

በበርታ ያልተገባ ጥቅምን መፈለግና በሰው ላይ ተንኮል መስራት እንዲሁ የተወገዙ ናቸው፡፡ የተንኮልን መጥፎነት የሚያስረዳው ተረታቸው ደግሞ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

> በአንድ አካባቢ ጦርነት ተነስቶ ኑዋሪው ሁሉ ወደ ሌላ ቦታ ሽሽት ሲያደርግ አንድ ሽባ[34] እና አንድ ዐይነ ስውር ብቻ ይቀራሉ፡፡ ሁለቱም ለመሸሽ ስላልቻሉ ጨንቆዋቸው ሲወያዩ ሽባው ዐይነስውሩን አንተ እዘለኝና እኔ እየመራሁህ መሸሽ እንችላለን ብሎት ተስማምተው ሽሽት ይጀምራሉ፡፡ ሲሄዱ ሲሄዱ ቆይተው ከአንድ ቦታ ሲደርሱ እነሱን ቀድመው የሸሹ ሰዎች ሚዳቁዋ አርደው በልተው የተረፋቸውን ሥጋ ጥለው ሄደው ያገኛሉ፡፡ ሽባው ለዐይነስውሩ ያገኙትን ሲሳይ ይነግረውና አውርዶት ጠብሰው እንዲበሉ ይነግረዋል፡፡ ከዚያም ሽባው የመጥበሻ እንጨት ሲሰበስብ እባብ ያገኝና ይገድለዋል፡፡ እሳቱን አቀጣጥሎ የሚዳቋዋን ሥጋ እየጠበሰም አንድ ተንኮል ያስባል፡፡ የሚዳቋውን ሥጋ ለእሱ ብቻ ለመብላትና የእባቡን ሥጋ ጠብሶ ለዐይነስውሩ ለመስጠት፤

[34] ሽባ የሚለውን ቃል የሚጠቀሙት ተራቹ ናቸው፡፡

> ከዚያም በዕቅዱ መሠረት እባቡን ጠብሶ ለዐይነሥውሩ ሰጥቶ የሚዳቋዋን ሥጋ ለብቻው ይበላል። በዚህ ጊዜ ዐይነ ሥወሩ ያልበሰለ የእባብ ሥጋ አጋጥሞት በልቶት ኖሮ ዐይኑ ይበራል። በጣም ይደሰታል። ወደ በሉት ሥጋ ሲመለከትም ይለያይበታል። ምንድነው ብሎ ሲጠይቀው ለእሱ የሰጠው የእባብ ሥጋ መሆኑን ይገነዘባል። የሸባውም ተንኮል ስላናደደው አንተ ተንኮለኛ ሰው ነህ እዚሁ ትቀራታለህ ብሎ እዚያው ጥሎት ይሄዳል። ወደፊት ሲገሰግስም ቀድመዋቸው ከሸሹት ሰዎች ዘንድ ይደርሳል። ሰዎቹም በጣም ተገርመው እኛ አንተንና ሸባውን እዚያው ጥለናችሁ አልነበረም እንዴ የመጣነው? አንተ እንዴት ደረስክብን? ዐይንህንስ ምን አበራው? ሲሉት የእኔን ዐይን ያበራው ተንኮል ነው። ሁለታችን እኔ ልሸከመው እሱ መንገድ ሊመራኝ ተስማምተን ጉዞ እንደጀመርን ለእኔ ሳያዝን ይሄንን ክፉ ተግባር ዋለብኝ አምላክ ግን መድሃኒት አደረገልኝና ዐይኔን አበራልኝ እኔም በተንኮሉ መቀጣት አለበት ብዬ እዚያው ጥየው መጣሁ አላቸው ይባላል። ስለዚህ ተንኮል መሥራት ጥሩ አይደለም፤ ተንኮል መሥራት የሚጎዳው ተንኮለኛውን ስለሆነ ተንኮል መሥራት እንዳታስቡ (አባ ሙሳ ባበከር፣ ቃመ20/02/05፣ ተረት 15)።

ከላይ የቀረበው ተረት እንደሚያሳው የአካል ጉዳተኛውና ዐይነስውሩ በቅንነት ለመረዳዳት አስበው ነበር፤ በአካል ጉዳተኛው ተንኮል ግን ስምምነታቸው ፈረሰ። ሰውየው በርታ አይደለም ማለት ይቻላል። ምክንያቱም በርታ ያገኘውን ነገር ለብቻው የመጠቀም ባህል የለውም። ማታለልንም አያውቅም ስለዚህ መልካሙን ምግብ ለባልንጀራው ያካፍለው ነበር እንጂ ለራሱ የተሻለውን በልቶ ለባልደረባው የእባብ ሥጋ ጠብሶ አይሰጠውም ነበር። በሌላ መልኩም ሲታይ ከስንዴ መሃል እንክርዳድ ስለማይጠፋ ሰውየው በርታም ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ካለባህሪውና ካለባህሉ

ተንኮል አሰበ፤ ፈፀመውም፡፡ በበርታ ባህል ተንኮልና ክህደት የተወገዘ በመሆኑና ይህን አልፎ ክህደት የፈፀመ መቀጣት ስላለበት ተንኮሉ እሱን ለሞት ባልንጀራውን ለብርሃን አበቃቸው፡፡ በተረቱ አማካይነት የተተከለው ባህላዊ እሴት ክህደትና ተንኮለኝነት ለሞት ያበቃሉና አታድርገው የሚል ሲሆን የዐይነስውሩ ዓይን መብራትም የተገፋና በሃቅ ያገለገለ ሰው ብርሃን ይወጣለታል፤ ዘመኑም የፈካ ይሆናል የሚል ትዕምርት ያለው ነው፡፡

እነዚሁ ዕውነተኛና ታማኝ የመሆንን ተገቢነት የሚያጎሉ ጭብጦች በበርታ ትረካዎች በስፋት ተደጋግመው ይመጣሉ፡፡ ስለውሻና ድመት ጠላትነትና ተፈጥሮኣዊ ሁኔታ የሚተርከው ትረካ የሚያስተምረው ይህንኑ ታማኝና ሀቀኛ የመሆንን ተገቢነት ነው፡፡

> በጥፋት ውሃ ጊዜ ኖህ ከፍጥረታት ሁሉ ተባዕትና እንስት እያደረገ ወደ መርከቡ ካስገባ በኋላ አንድ ትዕዛዝ አስተላለፈ፡፡ ይኸውም አምላክ ምህረቱን እስኪልክልን ድረስ በመርከቡ ውስጥ የግብረ ሥጋ ግንኙነት የተከለከለ በመሆኑ ማንም ይሄንን እንዳይፈፅም ብሎ ትዕዛዝ አስተላለፈ፡፡ ሌሊት ላይ ውሻ ተደብቆ ሚስቱን ሲገናኝ ድመት አይታ ኖሮ ሲነጋ ለኖህ ትናገራለች፡፡ ውሻ ተጠርቶ ሲጠየቅ አላደረኩም ብሎ ይክዳል፡፡ ኖህም ሁለተኛ እንዳይደረግ ድጋሚ ያስጠነቅቃል፡፡ ማታ ውሻ እንደለመደው ሲሰርቅ ተጣብቆ ይቀራል፡፡ ውሻ ከግብረስጋ ግንኙነት በኋላ ተጣብቆ የሚቀረው እምነቱን በማጉደሉና በመዋሸቱ ነው፡፡ ውሻና ድመትም የማይስማሙት ከዚህ የተነሳ ነው (እማ ሀጂጁ አልጣህር፣ቃመ16/04/05 ተረት 16) ፡፡

ከላይ የቀረበው ትረካ ለተፈጥሮኣዊ ጉዳዮች ሳይቀር መልስ እየሰጠ ሃቀኝነትን የሚተክል ነው፡፡ ውሻ አልታየሁም ብሎ ሰረቀ፤ ሲጠየቅም ካደ፤ ስላልተቀጣ ስህተቱን ደገመ፡፡ በድብቅ የተሰራውን በግልፅ የሚመልስ አምላክ ግን ሀሰትን ስለሚጠየፍ እጅ ከፍንጅ እንዲያዝ አደረገው፡፡ ስለዚህ ሰው አላየንም ብለን ብንሰርቅ፣ ትዕዛዝ ብንተላለፍ ሁሉን

የሚያይ አምላክ ያጋልጠናል። ነው የትረካው መልዕክት፤ ባህሉ በብሔረሰቡ ውስጥ የዕውነተኛነትን እሴት በዚህ መልኩ ነው እንዲሰረጅ የሚያደርገው። ይህ ደግሞ የሥነቃል ዋነኛው ተግባር ነው። (በተጨማሪ በተረት 17፣ መመልከት ይቻላል)

በበርታ ብሔረሰብ ተረቶችና ትረካዎች ተደጋግሞ እንደታየው ቅጥፈት፣ ሃሰትና ያልተገባ ጥቅምን መፈለግ በብሔረሰቡ ውግዝ ናቸው። ይሄ በመሆኑም በአካባቢው የሌባ ስጋት የለም። ሴቶቹ ወርቅን ያህል ውድ ነገር ቆፍረው ብቻቸውን ከበረሃ ሲመጡ የሚነካቸው ሰው የለም። የወርቁ ግብይት ራሱ በጠራራ ፀሃይ በክፍት ገበያ ላይ እንደሌላው ሸቀጥ ተራ ተይዞለት የሚከናወን ነው። ካለምንም ጥበቃና ከለላ ወርቅ ገዢዎቹ ብራቸውን በቦርሳ ይዘው ገበያተኛ በሚተላለፍበት መንገድ ላይ እየመዘኑ ይገዛሉ። ከቦርሳቸው በርካታ ብር አውጥተው እዚያው ቆጥረው ይሰጣሉ፤ ሻጭ ስንት ግራም ቆፍሮ እንዳገኘ፣ በስንት ብር እንደሸጠ ሲጠየቅ ዕውነቱን ይናገራል። ገዢም ስንት ግራም እንደገዛ አትርፎ ሲሸጥም ምን ያህል እንደሚያተርፍበት በግልፅ ይናገራል። በመንጌ እና ሸርቆሌ ገበያ ተገኝቼ ቃለምልልስ ሳደርግ ያየሁት ይሄ ዕውነት በጣም ያስደነቀኝ ነው።



ፎቶ 13 የወርቅ ግብይት መንጌ ቅዳሜ ገበያ ላይ ወርቅ ተራ

ከላይ እንደተመለከትነው የእነዚህ ትረካዎችና ተረቶች ሚና ደግሞ የመስኩ ምሁራን የፎክሎር ተግባራት ብለው ከሚያነሷቸውና ጉዳዮች ውስጥ የማስተማር፣ የመትከል፣ የመቆጣጠርና የመግታት ተግባራትን የሚያሳዩ ናቸው (Sims & Stephens,2005፣ ፈቃደ፣1991፣2010; Finnegan,1992)።

በበርታ ባህል የሰው ንብረት መንካትና ሌብነትም ፈፅመው የተወገዙና የማይታወቁ ናቸው። መረጃ ሰጪዬ አባ አቶም የሰው ፍየል ሰርቆ ያረደው ሰው የደረሰበትን ሁኔታ እንደዚህ ያስረዳሉ።

> አንድ ጊዜ አንድ ሰው የሰው ፍየል አስገብቶ ያርዳል። የፍየሉ ባለቤት ፍየሌ ጠፋብኝ ብሎ ቢፈልግ ያጣዋል። በዚህ ጊዜ አባቴ ደጃዝማች ሙስጦፋ የሆነውን ይሰማሉ። ዛሬ ፍየልም ሆነ በሬ ያረደ ስለሌለ ትኩስ ሥጋ እማን ቤት እንዳለ በየቤቱ እየገባችሁ ፈትሹ ብለው ያዙና ፍተሻ ሲደረግ ሰውየው ፍየሏን አርዶ ሥጋውን ለመጠባበስ ሲዘጋጅ ያገኙትና አባቴ ጋ ያቀርቡታል። ያረድካት ፍየል የማናት ብለው ሲጠይቁት ገና ተሳስቻለሁ የኔ ያልሆነችውን ነው ደብቄ ያረድኩት ይላል። በዚህ ጊዜ አባቴ የፍየሏን ቆዳ ተልትላችሁ ራሱ ላይ ጠምጥሙና ስጋውን ተሸክሞ ሌባ ነኝ እያለ ገበያ ውስጥ ይዙር ብለው አዘዙ ከዚያ በቀደም ባየሽው እንቢልታና ጡሩምባ እየተነፋ ከበሮ እየተመታ ሲዞር ሰው ሁሉ ሲሰድበውና ሲያንቋሽሸው ይውላል፤ በመጨረሻ አባቴ የፍየሏን ዋጋ ለባለፍየሉ ከፍለው ፍቱና ልቀቁት ቅጣቱ ይበቃዋል ይሉና ይፈታል። ከዚያ በሮ ሱዳን ይገባል ሁለተኛ ወደዚህ ሳይመለስ እዚያው ኖሮ ይሞታል። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ አንድም ሰው የሰው ገንዘብ አይነካም። ብር እንኳን ወድቆ ቢያገኝ አምጥቶ ያስረክባል። ከዚያም ብር የጠፋው ካለ ለሁሉም ሰው ይነገራል። መቶ ብር ከሆነ የተገኘው ሰው አጭበርብሮ እንዳይወስድ የተገኘው ገንዘብ ልክ አይጠቀስም። የኔ ነው ባይ ሲመጣ ልዩ ልዩ የማጣሪያ ጥያቄዎች ቀርበውለት የሱ መሆኑ ሲረጋገጥ ይሰጠዋል (አባ አቶም ሙስጦፋ፣ ቃመ25/04/05፣)። ለተጨማሪ ማስረጃ ተረት 24ን ማየት ይቻላል።

በጋራ መኖር ባህላቸው ለሆነው በርታዎች ከማህበረሰባቸው መነጠል ማለት የሞት ሞት ነው። ይህንን ታላቅ ቅጣት ሊያስከትሉ የሚችሉትን ነገሮች ፈፅመው ይጠየፏቸዋል። እጃቸውን ወደነዚህ ጥፋቶች ለመሰንዘር ከቶውኑም አያስቡም። ይህ በመሆኑ ነው ሌብነት፣ ማጭበርበርና ቅጥፈት በብሔረሰቡ ዘንድ የማይታወቀው።

ለመረጃ ስብሰባ መቃዚን ቀበሌ በተዘጋጀ በጥቅምት ወር በሚከበር የ"ኢሮ" ወይም "አጹምጹም" በዓል ላይ በተገኘሁበት ጊዜ ያጋጠመኝ አንድ ዕውነት ከላይ የቀረበውን ሃሳብ ዕውነተኝነት የሚያረጋግጥ ጥሩ ማስረጃ ይሆንልኛል። በዓሉ የአካባቢው ህዝብ በነቂስ ወጥቶ የሚያከብረው ትልቅ በዓል ነበር። የበዓሉ ድምቀት ታቦታት የሉም እንጂ የጥምቀትን በዓል ይመስላል። የዘፈኑና የጭፈራው ዓይነት እጅግ ብዙ ነው። የሙዚቃ መሣሪያዎቹ በሙሉ ወጥተዋል።

ክዋኔውን ለመቅረፅ ቪዲዮ ካሜራየን አወጣሁና ቦርሳዬን ተቀምጬበት ከነበረው ወንበር ላይ አስቀምጨው ተነሳሁ። ሥፍራው በጭፍራ ሲናጥ ልብን የሚመስጥ በጣም ማራኪ ትዕይንት ስለነበር ቀልቤን ስቼ በጉጉት ክዋኔውን በካሜራዬ ማስቀረቴን ተያያዝኩት። በዙምባራዉ ዜማ ሁሉም ሰው ወደ ጭፈራው ሲቀላቀል ንብረቴን የማስታውስበት ፋታ አልነበረኝም። በቀረፃዬ መሃል በካሜራው መስኮት ቦርሳዬን ከአንዱ ወጣት ትክሻ ላይ ሳየው ግን የተሰማኝ ድንጋጤ ልክ አልነበረውም። ልጁ የኔን ቦርሳ አንግቦ ይጨፍራል። አልፎ አልፎ ማንገቻው ከትከሻው እየተንሸራተተ ቢያስቸግረውም "ባንግ" የሚሉትን የተዋደደ መጥረቢያ የሚመስል ቅርፅ ያለውን የተጠረበ ዱላዉን በአንድ እጁ ይዞ እያወዛወዘ ጭፈራውን አላቋረጠም። አጠገቤ ያገኘሁትን አንድ በርታ "ቦርሳዬ..." አልኩት፤ ስጋቴ ገብቶት ፈገግ አለና "አይዞሽ አትጨነቂ ሲጨፍሩ ወድቆ እንዳይረጋግጡት ብሎ ነው አንስቶ የተሸከመው ሥራሽን ስትጨርሺ ያመጣልሻል" አለኝ፤ አላመንኩትም። ቦርሳው ውስጥ ያለው ሁሉም ነገሬ ነው ቢጠፋ ባዶየን ቀረሁ ማለት ነው፤ ሌላው ቀርቶ ለትንሽ ጉዳይ የምትሆን ሰባራ ሳንቲም እንኳን አይኖረኝም። በግማሽ ልብ ሆኜ ወደ ቀረፃዬ ስመለስ ክዋኔው ስለማረከኝ ስጋቱ ጥሎኝ ጠፋ፤ እንደውም እረሳሁት።

አምሻሽ ላይ ጭፈራው ለምግብ ጋብ ሲል በጀኔረተር ባትሪየን ለመሙላት ቻርጀር ስላስፈለገኝ ቦርሳው ትዝ አለኝ፡፡ ቦርሳዬን ብዬ ሳልጨርስ ልጁ ወደ እኔ ሲመጣ አየሁት፡፡ አጠገቤ ደርሶ ከትከሻው አውርዶ ሲያስረክበኝ "ሹክረን" አልኩና ተቀበልኩት፡፡ ከጥርጣሬዬ ግን አልተላቀቀኩም፤ ከውስጥ ያለኝ ገንዘብ፤ ውድ ዕቃዎቼ.... ለማስታወስ ሞከርኩ፤ ፈትሼ ለማረጋገጥ ግን እስከዛሬ የተገነዘብኩት የእነሱ ታማኝነትና ግልፅነት ይሉኝታ ስላስያዘኝ አልደፈርኩም፡፡ የጠፋም ነገር ካለ ለብቻዬ ስሆን አረጋግጣለሁ ብዬ ራሴን ገታሁት፡፡ በነሱ አባባል "አል ሀበሽ" ነኛ ምን ላድርግ፤ እንዲያም ሲል የአዲስ አበባ ፏዋሪ እንኳን የተረሳ አግኝቶ የያዙትን ነጥቆ የሚበር ቀማኛ ያለበት ከተማ የምኖር ገንጋኝ፡፡ ለማንኛውም ሥርዓቱ እስከሚያልቅበት ጊዜ እዚያው ቆይቼ ወደማድርበት ቤት እንዳደረሱኝ ተጣጥቤ ተኛሁ፡፡ ቦርሣውን ሲነጋ ነው ያየሁት የያዘው ነገር "እስከዓይን እስከጥርሱ" አንድም ሳይጎድል ሁሉም እንደነበረ አለ፡፡ በጣም ገረመኝ፤ ስለተጠራጠርኳቸውም ራሴን ወቀስኩት፡፡

ይህንን የሌብነት ስጋት አለመኖርና የብሔረሰቡን ያልተገባ ጥቅምን አለመፈለግ የሚረጋግጡ በርካታ ሁኔታዎች አጋጥመውኛል፡፡ ሽርቆሌ ወረዳ በነበርኩበት አንድ ምሽት እንዲሁ መረጃ አቀባዬ ከሆነችው ሲቲና ጋር ለመረጃ ስብሰባ በገጠር ቀበሌዎች ውለን ስንመለስ በመኪናው መንገድ ላይ በርካታ ፍየሎች ተኝተዋል፡፡ ምንድነው? ብዬ ጠየኩ "እዚሁ ነው የሚያድሩት" አለችኝ ሲቲና እንዴት ባለቤት የላቸውም? ጅብ አይበላቸውም? ሌባ አይነዳቸውም? ጥያቄዬን አከታተልኩ፡፡

> እዚህ አገር ጅብ የሚባል የለም ባለቤቶቹም ለእነሱ ማሳደሪያ ጋጣ አያዘጋጁም፤ የትም ውለው እዚሁ ያድራሉ፤ ሊያርዷቸው ወይም ሊሸጡዋቸው ሲፈልጉ ይወስዷቸዋል፡፡ ማንም የማንን ንብረት አይነካም፤ ሃራም ነው፡፡ ሰው በመተማመን ያምናል፡፡ ቢጠፋ እንኳን ለወሳጁ መልካም ስለማይሆንለት አይነካም፤ ሌባ የሚባል አይታወቅም ቅድም እንደነገርኩሽ ሰው ከተቸገረ ህብረተሰቡ ይረዳዋል፤ ያበለዋል፤ ያጠጣዋል፤ ሲሰርቅ ከተገኘ ግን ያገለዋል፤ ቢሞት እንኳን ዞር ብሎ

የሚያየው የለም። ስለዚህ ሌብነትን የሚሞክር የለም (ወ/ሮ ሲቲና፣ቃመ22/03/05)

በርታዎች ለፍየሎቻቸው ጋጣ፣ ለቤታቸው አጥር የሌላቸው፤ወርቅ ቆፍረው ይዘው በነፃነት የሚጓዙት፤ የወርቅ ግብይታቸው ገበያ ውስጥ በግላጭ የሆነው ከዚህ የተነሳ ነው። ሌባና ዘራፊ ከሌለ ስጋትና ጥንቃቄን ምን አመጣው? ቢራብ "አሰላማሊኩም" ብሎ ገብቶ የሚበላበት አል ከለዋ፣ ቢቸገር ካለስስት አንስቶ የሚሰጠው ሰው ሞልቶ በርታ ለምን ወደ ስርቆት ይገባል?

እነዚህ የበርታ ማህበረሰብ ባህላዊ እሴቶች የሆኑት ግልፅነትና ታማኝነት እንዲህ ሁሌም በዕለት ተዕለት ህይወታቸው የሚከወኑ፣ በተግባር የሚታዩ፣ ትውልዱ ጠብቆ እንዲያቆያቸውም ከላይ እንደተመለከተው በኑሮ ዘይቤያቸውም ሆነ በሥነቃሎቻቸው ተደጋግመው የሚመጡ ዕውነታዎች ናቸው። ስለ ተግባራዊ ቲዎሪ የሚያነሱት የመስኩ ምሁራን እንደሚያሳዩት (Bascom,1954; Okpewho,1992; ፈቃደ፣1991) የባህል የመትከል የማጠናከርና የመግታት ተግባር እንደዚህ በባህላዊ እሴቶች ሁሉ ተደጋግሞ በመምጣት የሚገለፅ መሆኑን ማየት ይቻላል።

በበርታ ብሔረሰብ ውስጥ የሰረጹት እነዚህ ባህላዊ ፈርጦች ልማትን ለማፋጠን አወንታዊ አሻራ ያላቸው ባህላዊ እሴቶች ናቸው። እነዚህ ምቹ ሁኔታዎች ቢዳብሩ፣ ቢለሙና ወደ ሌላውም ብሔረሰብ ቢስፋፉ ዛሬ ዋነኛ የልማት ፀር የሆኑት ሙስና፣ ብልሹ አሠራሮችና የአስተዳደር በደሎች ምንኛ ሊወገዱ እንደሚችሉ መገመት አያዳግትም። ክቡር ገና "የሙስና ባህላዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳቱ" በሚል ርዕስ ያቀረቡት መጣጥፍ ላይ እንደሚገልፁት የሙስናና ብልሹ አሠራርች ምክንያት የባህል መዝቀጥ እንደሆነ እንደሚከተለው ያስረዳሉ።

> … ከልክ በላይ ትርፍ ለመሰብሰብ መሻት፣ ሳይሠሩና ሳይደክሙ ሀብት ማካበት፣ ጎረቤት፣ ሠፈርተኛ ወይ ሀገር ሲጎዳ አይመለከተኝም ብሎ መቀመጥ ከሙስና የፈለቁ ሙስናን የሚያስፋፉ ባህሪዎች ናቸው።… ቀድሞ በሀገራችን የነበረው ከዘመድ፣ ከጎረቤትና ከአካባቢ ማህበረሰብ ጋር ተሳስቦና ተፋቅሮ የመኖር ልማድ በተለይ በከተሞች አካባቢ እየተዳከመ ነው። ከዚህ ቀደም ሀብታምና ደሃው ባንድ ሠፈር ውስጥ በእድር፣ በእቁብና በማህበር ተሰባስቦ ይኖር ነበር፤ ዛሬ ያ መልካም ባህል ደብዝዟል… በማህበረሰቡ ውስጥ ከዚህ ቀደም የነበሩት፣ ይሉኝታ፣ ሀቀኝነት፣ ሞራልና ግብረገብነት እየተዳከሙ የባህል መዝቀጥ ተምሳሌት በሆኑት ራስ ወዳድነት፣ አስመሳይነት፣ አመለካከቶችና እኩይ ባህሪያት እየተተኩ ናቸው። (ክቡር፣2004፣62)

እነዚህ ከላይ በክቡር ገና የተነሱት ሙስናንና ብልሹ አሠራርን የሚያሰፍኑ አሉታዊ ሁኔታዎች በበርታ ባህል የሚታዩ አይደሉም። ከልክ በላይ ትርፍ ማግበስበስ በበርታ ሀራም ነው፤ ቀድሞ በብዙ ማሳያ እንደቀረበው ጎረቤት፣ ሰፈርተኛ፣ ሀገር ሲጎዳ አይመለከተኝም ብሎ ማለፍ ፈፅሞ አይታሰብም። በበርታ ችግሩም ሆነ ደስታው፣ ጉዳቱም ሆነ ጠቀሜታው የጋራ ነው፤ የሁሉም የጋራ ችግርና የጋራ ጉዳይ ነው፤ ለብቻ መበልፀግና ለብቻ መቸገር የለም። በሰዎች መካከል ልዩነት ካለ የዕድሜ እንጂ የሀብትና የንብረት አይደለም። ሀብታሙም ደሃውም በጋራ አብረው ተሳስበውና ተረዳድተው ይኖራሉ። የባህል መዝቀጥ ተምሳሌት የተባሉት ራስ ወዳድነትንና፣ አስመሳይነትን የመሳሰሉ እኩይ ባህሪያት ማህበረሰቡ የሚፀየፋቸው ናቸው። ከዚህ ይልቅ የጋራ ትብብሮቹና መተሳሰቦቹ ጎልተው ይታያሉ። በተለያየ መልኩም ሰርጅተው ይገኛሉ። ስለሆነም እነዚህን የበርታን አዎንታዊ ባህላዊ እሴቶች በውል ተገንዝበው ቢያዳብሯቸው የማህበረሰቡን ሕይወት ለመለወጥ ዋነኛ ባህላዊ መሣሪያ ናቸው።

## 7.4. የዘመዳሞች ጎረቤታሞች የጋራ ትብብሮች

የበርታ ብሔረሰብ ባህላዊ እሴቶች ውስጥ የዘመዳሞች፣ የጓደኞችና የጎረቤታሞች የጋራ ትብብሮች የአካባቢውን ልማት ለማፋጠን በአወንታዊ መልካቸው መጠቀስ የሚችሉ ሌሎች ማሳያዎቸ ናቸው። እነዚህ ትብብሮች ሥራን በጋራ ለማከናወን፣ ገንዘብ አሰባስቦ ችግርን ለመሸፈን፣ የሠርግ ወጪን ሳይከብድ ተባብሮ ለመወጣት እንዲሁም ለተለያዩ ድንገተኛ ጉዳዮች አቅም ሲያንስ ለመደጋገፍ የሚከወኑ ሥርዓቶች ናቸው።

### 7.4.1."አመሃ" / የደቦ ሥራ

በርታዎች በጋራ ከሚከውኗቸው ሥራዎች አንዱ የግብርና ሥራዎችና የቤት ሥራዎች ናቸው። ለእርሻ ሥራ ማሳ ለማፅዳት፣ ለቁፋሮ[35]፣ለዘር፣ ለአረምና ለሰብል ስብሰባ እንዲሁም ሰብልን ለማከማቻ የሚጠቀሙባቸውን ጎተራዎችና ሰቀላዎችን ለመስራት የመንደሩ ኗሪ በጋራ በመውጣት ተባብሮ የመሥራት ባህል አለው። "ባለ አመሃው የሚሠራለትን የሥራ ዓይነትና የሚሠራበትን ቀን ቆርጦ ያሳውቃል። በቀኑ ሥራው ላይ ለተሰማሩት ሰዎች የሚሆን ምግብና መጠጥ ያዘጋጃል። የሚችል ከሆነ አርዶ ካልቻለም ገንፎና ሻይ ቡና አዘጋጅቶ ከሥራ መልስ ይጋብዛል። ሥራው በዙር ለሚፈልጉ ሁሉ የሚከናወን ይሆናል።

[35] በርታዎች የበሬ እርሻን ስለማያውቁ ማሳቸውን ለዘር የሚያዘጋጁት በ"ጳሌ" በመቆፈር ነው ።

## 7.4.2.“አታማተባ” /ዕቁብ

ይህ የዕቁብ መልክ ያለው ትብብር ሲሆን የሚተማመኑ ሰዎች በወረቀት ባልሰፈረ ደንብ በቃል ብቻ እየተመሩ በየሦስት ቀኑ፣ በየሳምንቱ ወይም በየወሩ የተወሰነ ገንዘብ በማዋጣት የሚረዳዱበት ነው። “አታማተባ” /ዕቁብ  አልፎ አልፎ የሚደረግ እንጂ በማህበረሰቡ ባህል የተለመደ ባለመሆኑ በስፋት አገልግሎት ላይ የዋለ አይደለም።

## 7.4.3.“ሙጅባ” / የሠርግ መዋጮ

“ሙጅባ” ልጃቸውን የሚድሩ ሰዎችን ለማገዝ የሚደረግ መዋጮ ነው። ሴቶች ለሙሽራዋ/ው እናት ወንዶች ለሙሽራዋ/ው አባት የሠርግ ድግሥ ወጫቸውን እንዲሸፍኑበት አዋጥተው የሚሰጡት ገንዘብ ነው። ይህ ትብብር ልጃቸውን የሚድሩ ሰዎች በሠርግ ወጪው እንዳይቸገሩና ካለሥጋት ልጆቻቸውን ደግሰው እንዲድሩ የሚያስችላቸው ነው። ከዚህ በተጨማሪም ሁሉም ሰው ያለውን ከየቤቱ ሠርቶ ይዞ በመምጣት የሠርግ ዕድምተኞችን የማስተናገድ ባህልም አላቸው።



ፎቶ14 በከሸፍ ቀበሌ በነበረ ሠርግ ላይ ዕድምተኞች ከየቤታቸው የሠሩትን በመያዝ ወደ ሠርግ ቤት ሲሄዱ

## 7.4.4.“ሀፍለታ ሻሂ”/ የሻይ እንጠጣ ፐሮግራም

“ሀፍለታ ሻሂ” አንድ ሰው ሚስት ለማግባት አስቦ ለጥሎሽ የሚከፍለው ገንዘብ ሲያጥረው፣ ለትምህርትም ሆነ በተለያየ ምክንያት ለአጭር ጊዜም ሆነ ለረጂም ግዜ ከአካባቢው ርቆ መሄድ አስፈልጎት ገንዘብ ካነሰው ወይም ከሌለው ለአባቱ፣ ለአጎቱ ወይም ለቅርብ ጓደኛው ጉዳዩን ያዋየዋል። ቤተሰቦቹ ወይም ጓደኛው ጉዳዩን ለሚመለከታቸው ሁሉ ከነገሩ በኋላ ሻይ እና ጥቂት የሚቀመሱ ነገሮች አዘጋጅተው አልከላዋ ውስጥ ጉዳዩን በማንሳት ሰው ሁሉ የቻለውን ሁሉ እንዲረዳው ያደርጋሉ። ወደ አካባቢው ጉዳዩን ሳይሰማ ድንገት የደረሰም ሰው ካለ ያለውን በመርዳት ተሳታፊ ይሆናል።

ይህ የመረዳጃ ፐሮግራም ለበርታ ብሔረሰብ አባላት ብቻ ሳይሆን ከሌላ ቦታ መጥተው እዚያ በቋሚነት ለሚኖሩና በእንግድነትም መጥተው ችግር ለደረሰባቸው ሁሉ የሚዘጋጅ ነው። ሀፍለታ ሻሂ አንዳንድ ጊዜ ተቸገርኩ ላለ ሰው ብቻ ሳይሆን በአጋጣሚ በተለያየ ምክንያት አካባቢውን ለሚለቅና ለማግባት ለተዘጋጀ ሰውም መሸኛና ድጎማ ለማድረግ በማሰብ ሰውየው ይዘጋጅልኝ ባይልም በጓደኞቹና ጎረቤቶቹ አነሳሽነት ሊዘጋጅ ይቻላል። በፐሮግራሙ ላይ አንዳንዴ ዘፈንና ጭፈራ ሊዘጋጅ ስለሚችል ወጣቶች ለመተያየና ለመተጫጫ እንደ ጥሩ አጋጣሚ ይወስዱታል።[36]

አሉላና ገብሬ ሀገራዊ ዕውቀትና የልማት ትስስርን ሲያስረዱ እንደሚሉት “የልማት ታዳሚ ህዝብ ባህላዊ ዕውቀት ስላለው ይህንን የዕውቀት ሃብት ልክ እንደተፈጥሮ ሃብትና ገንዘብ ለስኬት አስተዋፅዖ ያደርጋል... ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴም ሲገባ ..እንዳካባቢው ሁኔታ የሀገራዊ ዕውቀትን አስፈላጊነት ተገንዝቦና አስገንዝቦ በስፋት መጠቀም የሀገራዊ

---

[36] ቤጉክማባቱማቢ፣አዲስ ምዕራፍ፣13ኛ ዓመት፣ቁ 26፣ 2003ዓ.ም.

ዕውቀቶችን ጥራት... ሙያውንና ክህሎቱን አሻሽሎ ብክነትን መቀነስ ይቻላል፡፡" (አሉላና ገብሬ፣ 2004፣82)፡፡

እነዚህ የጋራ ትብብሮችም በወጉ ቢያዙ ብሔረሰቡ በተለይ የቁጠባን ባህል እንዲለምድና እንዲያዳብር የሚኖራቸው ሚና በቀላሉ የሚገመት አይደለም፡፡ ማህበረሰቡ በጋራ ሰፋፊ ማሳዎችን በማልማት ለቀለብ ብቻ ከማምረት ለገበያ ብሎ ወደ ማምረት፣ ሰፊ ጊዜውንም በ"አል ከለዋ" ውስጥ ሳይሆን በልማት ሥራዎች ላይ በመሠማራት እንዲያሳልፍ፤ የጋራ ትብብሮቹን መነሻ አድርጎ የቁጠባን ልማድ እንዲያዳብር ለማስተማርና ወደ ተግባርም ለማሸጋገር ጠቃሚ ባህላዊ መድረኮች ናቸው፡፡ እነዚህን ባህላዊ እሴቶቹንና ሀገር በቀል ዕውቀቶቹን መሠረት በማድረግ የተነሳን ልማታዊ ተግባር ማህበረሰቡ በቀላሉ የሚቀበለው፣ ለመተገበርም የማያንገራግርበት ይሆንለታል፡፡

በርካታ ወንዶች በአንድ ላይ ተሰብስበው የሚቀመጡበት "አል ከለዋ" ማህበረሰቡን ስለ አካባቢው ልማት ጉዳይ ለማወያየት፣ ለማስገንዘብና ለማነሳሳት ከስብሰባ አዳራሽ ይልቅ በጣም ምቹና ተመራጭ ሥፍራ ነው፡፡ በዚህ ቦታ "አዋቂዎቹን" ከፍ አድርጎ፣ ማህበረሰቡን ከስራቸው እያዩ የሚነግሩበት መድረክ የለም፡፡ ሁሉም መሬት ላይ እኩል ተቀምጠው ይወያያሉ፤ ሃሳብ ይለዋወጣሉ፤ ያልገባቸውን ይጠይቃሉ፤ ውሳኔያቸውን በጋራ ያሳልፋሉ፡፡ እዚያው የተገኘውን እየበሉ እየጠጡ ጊዜቸውን በሚያሳልፉበት በዚህ ስፍራ ተገኝቶ ስለ ነገ የአካባቢያቸው ልማት እዚያው አወያይቶ ወደ ተግባር ለማስገባትና ለውጥ ለማምጣት የቀለለ መንገድ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም በርታ በ"አል ከለዋው" ውስጥ በጋራ መምከር መወያየትና ውሳኔ ማሳለፍ የዕለት ተዕለት ልምዱና ባህላዊ መገለጫው ነው፡፡ የልማቱ አስፈፃሚዎች ይህንን ልማዳዊ ተግባር የልማት መሣሪያ ለማድረግ የምር ካሰበቡበትና ግምት ሰጥተውት በብልሃት ከያዙት እጅግ ቀላሉ መንገድ ይሆንላቸዋል፡፡

የተለያዩ ጉዳዮች ሲገጥማቸው የሚረዳዱባቸው የቤተዘመድ፣ የጓደኛሞችና የጎረቤታሞች የጋራ ትብብሮች የቁጠባ ልምድን ሊያዳብሩ የሚያስችሏቸው ጥሩ መሠረቶች ናቸው፡፡ የብድር ባህል በሌለበት የበርታ ማህበረሰብ የገጠር ብድርና ቁጠባ ተቋማትን ማስፋፋት

የሚል በሌሎች ማህበረሰቦች ዘንድ ሲሠራ የቻለ የልማት አቅጣጫ ለመተግበር ከመድከም ይልቅ እነዚህን የጋራ ትብብሮች እንዲጎለብቱ በማድረግ የገንዘብ አቅም የሚፈጥሩበትን መንገድ መፈለጉ የበለጠ ውጤታማ ይሆናል። እለዚያ ግን "ተበደርና የግብርና ግብዓቶችን ግዛ፣ትንሽ ትንሽ እየቆጠብክ ብድርህን ክፈል" ቢባል ተበድሮ ስለመክፈል ላለመደው የበርታ ብሔረሰብ ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሚሆን ቀደም ሲል ስለ አባ አቶም መኪና ያነሳነው ማሳያ ትልቅ ማረጋገጫ ነው።

## 7.5. የመንደር ማሰባሰቡ በጎ ጅምሮች

የክልሉ መንግሥት ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ ተበታትነውና ተራርቀው የሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎችን መሰረተ ልማቶችን ለሁሉም ለማዳረስና የአርሶ አደሩን አኗኗር ከመሠረቱ ቀይሮ የምግብ ዋስትናውን ለማረጋገጥ ውሃን ማዕከል ያደረገ በመንደር ማሰባሰብ ሥራ ጀምሮ በማከናወን ላይ ይገኛል። በዚህም በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዘመኑ 45,000 እማዎራዎችንና አባዎራዎችን ለማሰባሰብ ታቅዶ በ2005 ዓ.ም 39976 እማዎራዎችንና አባዎራዎችን በመንደር ማሰባሰብ እንደተቻለ የክልሉ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የአፈፃፀም ግምገማ ሪፖርት ያስረዳል (የቤጉክዕትዕአግሪ፣ 2005፣14)። ይሄ የመንደር ማሰባሰብ ፕሮግራም አዲስ የተጀመረና ከአራት ዓመት ዕድሜ በላይ ያላስቆጠረ በመሆኑ ጥናቱ ባተኮረባቸው ጥቂት አካባቢዎች ብቻ በቅርቡ በመተግበር ላይ ስለሆነ ያመጣውን ጥቅምና ጉዳት አፍን ሞልቶ ለመናገር የማይቻል መሆኑን ከግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል። ይሁንና በዚህ ጥናት በተካተቱት አቡራሙና ቆሽመንገል ቀበሌዎች ጅምር ስራዎች በመኖራቸው እዚህ ሊነሳ ቻለ እንጂ በጥልቀትና በስፋት የተዳሰሰ ጉዳይ አይደለም። በአቡራሙና በቆሽመንገል በመንደር የተሰባሰቡ በርታዎች የመንደር ማሰባሰቡን ጠቀሜታ ይናገራሉ።

> በሩቅ ያሉትንና ቶሎ ቶሎ የማናገኛቸውን ዘመዶቻችንን በቅርብ እንድናገኛቸው በማድረጉ በጣም ጥሩ ነው። ትምህርት ቤቶችና ጤና ጣቢያዎችም ቅርባችን ስላሉ ችግራችን ተቃሏል። ልጆቻችንም ሁሉ በአንድ ላይ ትምህርት ቤት ሄደው ይመለሳሉ። እኛም በጎልማሶች እንማራለን። ሴቶቹም ትምህርቱ ቅርብ ስለሆነ ስራ ሲጨርሱ ሁሉም ሄደው ይማራሉ። እንደሚሉትም መብራትና ውሃ በቅርብ ካገኘን ጥሩ ነው። ድሮ ግብር የምንከፍለው ማንጎ ሽጠን ነበር አሁን ማንጎውን ጥለነው ስለመጣን ትንሽ ተቸግረናል እንጂ ሌላው ጥሩ ነው ኢንሻላ ከዘመዶቻችን ሁሉ አብረን እንድንሆን አድርገውናል (ቡውይአቡ 09/03/05/፣ቡውይቆሽ18/04/05)።

በርታዎች በባህላቸው በጋራ መኖርን ስለሚወዱ በመንደር መሰባሰባቸውን አይጠሉትም። በቅሬታ የሚያነሱት አንዳንድ ያልተሟሉላቸው ነገሮች መኖራቸውን ቢሆንም በቦታ ርቀት የተነሳ ቶሎ ቶሎ የማያገኟቸውን ዘመዶቻቸውን በማቀራረቡ ተደስተውበታል። ይኸን ምቹ ሁኔታ መሠረት አድርጎ የአርሶ አደሩን ህይወት ከመሠረቱ ለመቀየር የታለመውን ዕቅድ ማሳካት የሚችልበትን ዘዴ በብልሃት መከወኑ ግን የክልሉ መንግስት የቤት ሥራ ይሆናል። አርሶ አደሮቹ በቅሬታ የሚያነሷቸውን ጉዳዮች ፈጥኖ በማስወገድ በጋራ የማምረትና የመጠቀም ዕድሉን ማስፋፋት ይቻላል። አካባቢውን ለማልማት ጥሩ መሠረትም ሊሆን እንደሚችል አጢኖ መሥራት ይኖርበታል።

## 7.6. ገንቢ የሆኑ የጤና ጉዳዮች

ስለልማት ጉዳዮች ሲነሳ በበሽታ ያልተጠቃና ጤናው የተጠበቀ ማህበረሰብ መኖር ዋነኛ አስፈላጊ ጉዳይ መሆኑ ግልፅ ነው። መንግሥታት ለዜጎቻቸው ጤና ትኩረት ሰጥተው እየሠሩ ያሉትም ከዚህ መነሻ ነው። በሀገራችንም መንግሥት የህዝቡን ጤና ለመጠበቅ ከነደፋቸው ፖሊሲዎች ውስጥ የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጆች እንደሆኑ ቀደም ሲል ተጠቅሷል። በጤና ኤክስቴንሽኑ ከተካተቱት ፓኬጆች ተፈፃሚነት አኳያ በበርታ ብሔረሰብ ባህል ያሉትን አዎንታዊ ሁኔታዎች ቀጥለን እንመለከታለን።

### 7.6.1. የግልና የአካባቢ ንፅህና አጠባበቅ

በበርታ ባህል የግልና የአካባቢ ንፅህና መጠበቅ እጅግ አስፈላጊ ጉዳይና ተዘወትሮ የሚተገበር ባህል ነው። በርታዎች የእስልምና ዕምነት ተከታዮች እንደመሆናቸው የዕምነታቸው አንዱ ምሶሶ የሆነውን በቀን አምስት ጊዜ መስገድ እያንዳንዱ ሰው ሳያዛንፍ ይተገብራል። ከስግደት በፊት ደግሞ ራስን “ጡሃራ”/ ንፁህ ማድረግ የግድ ነው። ስለዚህ ማንኛውም ሰው በመተጣጠብ የግሉን ንፅህና በሚገባ ይጠብቃል። ከዚህ የተነሳ ወደ ሠፈሮቻቸው ሲዘለቅ በየበሩ ላይ በቅድሚያ የሚገኘው በውሃ የተሞላ “አል ብሪክ”/ አነስተኛ የውሃ መያዢያ ዕቃ ነው። ማንም ሰው ያንን አንስቶ ካለችግር እንዲታጠብ ገና ከውጪ ተዘጋጅቶ ይቀመጣል።



ፎቶ 15 የበርታዎች የገላ መታጠቢያ ቤት

በበርታዎች የመኖሪያ ሠፈሮች ቆሻሻ ማየት የተለመደ አይደለም። ፍፁም ንፁህ የሆኑ አካባቢዎች ናቸው። ለመፀዳጃ የሚሆን ሽንት ቤትና ውሃ የያዘ ጀሪካን ያለበት የገላ መታጠቢያ ቤት በየሠፈሩ ይገኛል። ሁሉም ሰው ወንዱም ሆነ ሴቱ ወደ ሽንት ቤት ሲሄድ ውሃ በ"አል ብሪክ" ይዞ ነው። ተጠቅሞም ሲወጣ እጁን መታጠብ የተለመደ ተግባር ነው።

የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጆች አንዱ የሆነው የግል ንፅህና አጠባበቅ ፓኬጅ ዓላማ "በግል ንፅህና አጠባበቅ ጉድለት አማካይነት የሚተላለፉና የሚከሰቱ በሽታዎችን በመከላከል ጤናማና አምራች ህብረተሰብ ማፍራት" (የኢፌዴሪጤጥሚ፣1998፣2) የሚል ነው። የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎቹ እንደሚያስረዱት የግል ንፅህና አጠባበቅን አስመልክቶ

በብሔረሰቡ ቀድሞውንም የሚተገበር ባህል በመሆኑ ይህን ፓኬጅ ለመተግበር ምንም ችግር አልገጠማቸውም (ወ/ሮ አስረሳሽ፣ቃመ20/04/05፣ ወ/ሮ ማሪያ፣ቃመ20/08/06፣ አቶ አያሌው አሰፋ፣ ቃመ17/08/06) ከዚህ በመነሳት ለኤክስቴንሽን ፓኬጁ ያለችግር መተግበር ባህሉ ያደረገውን አስተዋፅዖ መረዳት አያዳግትም። "ሀገራዊ ዕውቀት በግብርና፣ በጤና አጠባበቅ፣ በምግብ ዝግጅት፣ በትምህርት፣ በተፈጥሮ ሀብት አያያዝና በሌሎች በርካታ ጉዳዮች ላይ ለመወሰን መሠረት ነው" (አሉላና ገብሬ፣2004፣78) የበርታ ብሔረሰብ ፓኬጁ በዓላማነት ይዞ የተነሳውን ከግል ንፅህና ጉድለት የሚመጡ በሽታዎችን መከላከል ለመተግበር ያልተቸገረው ንፅህናን ባህሉ አድርጎ ሲተገብረው የኖረ ሀገረሰባዊ ዕውቀት ስለሆነ ይህንን እሴት እንደ ጥሩ አጋጣሚ በመውሰድና በማበረታታት ሌሎቹንም ፓኬጆች እንዲተገብር የሚያስችል ምቹ ሁኔታ መፍጠር ያስችላል።

### 7.6.2. ለጤና ተስማሚ የሆነ መኖሪያ ቤት አሠራርና አያያዝ

ለሰዎች በመሠረታዊ ፍላጎትነት ከሚነሱ ጉዳዮች አንዱ መጠለያ ወይም መኖሪያ ቤት ነው። ቤት ለመኖሪያነት፣ ለመዋያና ለማደሪያ የሚጠቅምና ሰፊ ጊዜያችንን የምናሳልፍበት በመሆኑ ንፅህናው የተሟላና ምቹ መሆን ይጠበቅበታል። ይህ ከተጓደለ ግን ለቅዝቃዜ፣ ለሙቀት፣ ለተለያዩ አደጋዎችና ተላላፊ በሽታዎች እንድንጋለጥ ከማድረጉም በላይ ለአካላዊና ሥነልቡናዊ ቀውሶች ሊያጋልጠን ይችላል።



ፎቶ 16 የበርታ ቤቶቸ ውጫዊ ገፅታ

መኖሪያ ቤት "ለሰዎች አካላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ስነ አዕምሮአዊ ጤንነትና ደህንነት ለመጠበቅ አስተዋፅዖ ከሚያደርጉ መሠረታዊ ፍላጎቶች አንዱ ነው።" ብሎ የሚነሳው ለጤና ተስማሚ መኖሪያ ቤት አሠራርና አያያዝ ኤክስቴንሽን ፓኬጅ ዓላማው "ህብረተሰቡ ለጤና ተስማሚ የመኖሪያ ቤት እንዲኖረው በማድረግ እራሱንና ቤተሰቡን ከተላላፊ በሽታዎችና አደጋዎች እንዲከላከል ማድረግ" (የኢፌዴሪጤጥሚ፣1998፣3) የሚል ነው።



ፎቶ 17 የበርታ ቤቶች ውስጣዊ ገፅታ

ከላይ እንደተገለፀው በርታዎች የግል ንፅህናቸውን ብቻ ሳይሆን ቤታቸውንና አካባቢያቸውን በንፅህና የመያዝ ባህል አላቸው፡፡ ቤታቸው በአብዛኛው በተለይም በገጠሩ አካባቢ ከቀርከሃና ከሰንበሌጥ የሚሠራ ጎጆ ሲሆን ወደ ውስጥ ሲዘልቁ ንፅህናው እጅግ የሚያስገርም ነው፡፡ የትኛውም ቤት ከውስጥ ጣሪያና ግድግዳው አቅም በፈቀደ መጠን በማዳበሪያ የተሸፈነ ሲሆን ወለሉ ላይ ንፁህ የፕላስቲክ ምንጣፍ አያጣም፡፡ የቤት ዕቃዎች በንፅህና ተይዘው በወጉ ይቀመጣሉ፡፡ ከከተማ የቱንም ያህል የራቀ ቢሆን በበርታዎች ዘንድ ቤትንና ዕቃን በንፅህና መያዝ የተለመደ ባህል ነው፡፡

የበርታ ሴቶች ሌላው ቀርቶ ለእንግዳ ውሃ ለማቅረብ ሲዘጋጁ መጀመሪያ እጃቸውን እስከክንዳቸው ድረስ ታጥበውና ማቀራረቢያ ዕቃዎቻቸውን በሚገባ አጥበው ነው፡፡ ይህን የማታደርግ ሴት ገልቱ ናት፡፡

“አልበቲና ሃደኖ ነኘኦሌ ኒላሆ አጎን

አኰካቶነኘ መቲ አለን ኩንዲ”

“ብዙ ከምትወልድ ሴት ይልቅ ባለሙያ ሴት ስጠኝ”

“ሲኢጅማን ሁለንተን ከርቱ ቢን

ሁንበትሪን ሽሚያ አቡቡ ዱሩኑት”

“በማለዳ ቤቷን የማታፀዳና እሳት ፍለጋ የምትሄድ ዝንጉ ሴት አይጣልብህ”

ይላሉ በርታዎች፡፡ ከሴት ልጅ ባለሙያነትና ትጋት የሚጠበቁ ናቸው፡፡ የባለሙያነት መጀመሪያው ደግሞ ቤትን በንፅህና መያዝ ነው፡፡ ቤት ሳይፀዳና ሳይስተካከል ወደ ውጪ መውጣት ነውር ነው፡፡ ከዚህ በኋላ እሳት ተቀጣጥሎ ምግብ ይበሰላል፡፡ በምድጃዋ እሳት የሌላቷ ገልቱ ግን ቤቷን ሳታፀዳ ፍለጋ ትወጣለች፡፡ ይህ የሚያሳየን በርታዎች ለቤት ንፅህና ያላቸውን ቦታ ነው፡፡ ሴቶች ቤታቸውን ብቻ ሳይሆን ወንዶቻቸው የሚቀመጡበትን አል ከለዋም በንፅህና ይይዛሉ፡፡ የሚያድሩበትና የሚያበስሉበት ቤት የተለያየ ነው፡፡ አካባቢው በአብዛኛው ሙቀት በመሆኑ ከውጪም ሊያበስሉ ይችላሉ፡፡

ከቤታቸው ውጪ ያለው ሥፍራና አካባቢውም እንዲሁ በንፅህና የተያዘ ነው፡፡ ቡና የሚጠጡት ውጪ በመሆኑ ሁሌም በንፅህና ይያዛል፡፡ ይህ በመሆኑም የግልና የአካባቢን

ንፅህናን አስመልክተው የተነደፉትን የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጆች በቀላሉ ለመተግበር ችለዋል፡፡



ፎቶ 18 የበርታ ሴቶች የማብሰያና የመመገቢያ ዕቃዎች በዚህ መልኩ በንፅህና ተይዘው ይቀመጣሉ።

ይሄ ብሔረሰቡ እራሱንና ቤተሰቡን ከበሽታዎችና ከልዩ ልዩ አደጋዎች እንዲከላከል ያስቻለ ጠቃሚ ባህላዊ እሴትና ሀገረሰባዊ ዕውቀት ነው፡፡ የብሔረሰቡን ባህል በጥቅሉ ጎታችና ኋላ ቀር ነው ብሎ በመፈረጅና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ወሳኝነትና የበላይነት የሚያምኑት የዘመናዊነት ንድፈ ሃሳብ አራማጆች እንደሚሉት ባህልና ሀገረሰባዊ ዕውቀቶች የልማት እንቅፋቶች ናቸው ብሎ ሁሉን ለማዘመን ከመነሳት ይልቅ እነዚህንና ሌሎችን ባህላዊ እሴቶች እንደ ምቹ ሁኔታ በመቁጠርና በማጎልበት ጤንነቱ የተጠበቀ አምራች ዜጋ ለማፍራት ይቻላል፡፡

# ምዕራፍ ስምንት

## 8. የአካባቢውን ልማት የሚያስተጓጉሉ አሉታዊ ባህላዊ ጉዳዮች

በቀደመው ምዕራፍ መንግሥት የአገሪቱን ልማት ለማፋጠን በሀገር አቀፍ ደረጃ አቅዶ በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች እየተገበራቸው ካሉት የልማት ፖሊሲዎች ውስጥ የግብርና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምና የማህበረሰብ ጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጅ ለመተግበር እና የአካባቢውን ልማት ለማፋጠን በበርታ ብሔረሰብ ባህል ያሉትን ምቹ ሁኔታዎች ተመልክተናል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ደግሞ እነዚህ የልማት ፓኬጆችን ለመተግበር የሚፈታተኑ አሉታዊ ባህላዊ ጉዳዮችን ቀጥለን በተናጠል እንመለከታለን፡፡

### 8.1. የግብርና ልማት እና የበርታ ብሔረሰብ ባህል ተግዳሮቶች

> “አቡ ሁራይራ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- ‘ሀብት ማለት የገንዘብ ብዛት ሳይሆን የነፍስ (የውስጥ) መብቃቃትና መረጋጋት ነው’ (ቡኻሪናሙስሊም)” (ሪያዱ አስ-ሷሊሒን፣ 2004፣ 332)፡፡

ኢትዮጵያ በምትከተለው ግብርና መር ኢንዱስትሪያላይዜሽን ፖሊሲ መሠረት የግብርና ልማቱን ለማፋጠን የኤክስቴንሽን ፕሮግራም ተቀርፆ በሁሉም ክልሎች ተግባራዊ እንዲሆን እየተሠራ ይገኛል፡፡ አርሶ አደሩ ቀድሞ በልማድ ከሚያመርታቸው ሰብሎች ይልቅ  የኢኮኖሚ ጠቀሜታ ያላቸውን ሰብሎች አምርቶ ለገበያ በማቅረብ ተጠቃሚ እንዲሆን፣ ማዳበሪያና ምርጥ ዘርን ጨምሮ ልዩ ልዩ ግብዓቶችን እንዲጠቀምና ምርትና

ምርታማነቱን እንዲያሳድግ ባለሙያዎችን በማሰማራት በግብርና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ትምህርትና እገዛ ይሰጠዋል።

### 8.1.1. ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ

ከላይ የተጠቀሱት የግብርና ልማት ፕሮግራሞችን አፈፃፀም ስንመለከት ውጤታማነቱ እስከዚህም ሆኖ ይታያል። የበርታ አርሶ አደር ከዚህ በተለየ ሁኔታ የእርሻ ሥራን የሚያከናውነው ለዕለት ጉርሱ የምትበቃውን ብቻ ሲሆን ከዚያም የተረፈውን ሸጦ ባገኛት ገንዘብ ደግሞ ለአመት ልብሱና አነስተኛ ንግድ ለመነገድ የሚያስችለውን እሲኪያገኝ ብቻ ነው። በእርሻ ሥራ ሙሉ ጊዜውንና ጉልበቱን ማጥፋት አይፈልግም። ለቤት ቀለብ እምትሆነውን ካመረተ ብዙ ለማምረት እጅግም አይተጋም። አንዱ ቦታ መሬቱ አልሰጥ ካለ ሌላ ቦታ ሄድ ብሎ ይቆፍራል። የሚፈልጋትን ካገኘ በቃ። ካልሆነም እድሜ ለአገሩ መሬት ወደ ወርቅ ቁፋሮው ይዞራል። ስለዚህ የኢኮኖሚ ጠቀሜታ ያላቸውን ሰብሎች ለገበያ ማምረት፣ ግብአቶችን ተጠቅሞ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፣ መላልሶ አለስልሶ ማረስ የእሱን ትኩረት የሚስቡ ጉዳዮች አይደሉም። የበርታ አርሶ አደር "የእርሻውን ሥራ ለእኔ ተውት እስከዛሬ የሚበቃኝን ሳመርት ኖሬአለሁ ካልሆነም… " ባይ ነው። ይህንን አስመልክቶ የባምባሲ ወረዳ የግብርና ባለሙያ የሆኑ አባ አብዱራሂም የተባሉ መረጃ ሰጪ የሚሉትን እንመልከት።

> ልማትን በሚመለከት አካባቢው በእርሻ ነው እሚተዳደረው፤ ግን በጣም ወደ ንግድ ያዘነብላል፤ ንግድን ይወዳል። እርሻ አሁን ቅርብ ነው የለመደው ድሮ ከብት ያረባል፤ ከብት ሸጦ እህል ይገዛል። … እና አሁን እንግዲህ የመንግስት ፖሊሲዎች አሉ፤ ኤክስቴንሽን ፕሮግራሞች አሉ፤ የእንስሳት ፓኬጅ፣ የሰብል ልማት ፓኬጅ፣

> የኢኮኖሚ ጠቀሜታ ያላቸው ሰብሎች ፓኬጅ አለ፤ ያ ሁሉ ይሰጣል። አብዛኛው አካባቢው በዚህ በማዳበሪያ የመጠቀም ባህል ደካማ ነው። አካባቢው ያልተነካ ስለሆነ መሬትን ማዳበሪያ ከመጠቀም እዚህ እምቢ ሲለው ሌላ ቦታ ሄዶ ያርሳል። ከዚህ የተነሳ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የህዝብ ቁጥር እየጨመረ ነው። … ግን እንደሌላው አይደለም። እንደ አማራ እንደ ኦሮምያ ሌላ አማራጭ የላቸውም እነዛ፤ እርሻ ብቻ ነው። ይሄ እርሻ እምቢ ካለው ትቶ ወደ ንግድ ይገባል፤ እምቢ ካለ ወርቅ ቁፋሮ ይሠማራል፤ ካልሆነም ወደ ሱዳን ይገባል። ያያ ሁሉ ወደ ኋላ ያዘገዩን ነገሮች ናቸው። … በአካባቢው በረጅሙ ዘመን ግን እርሻን እንደመሠረታዊ ጉዳይ አይታይም (አባ አብዱራሂም፣ ቃመ22/03/05)።

ከላይ እንደተመለከትነው ግብርናና ገጠር ልማትን መሠረት በአደረገው የሀገሪቱ ዋነኛ ፖሊሲ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የተያዘው ዕቅድ በበርታ ማህበረሰብ ለዕለት ጉርስ ብቻ በማምረት ባህል ትልቅ ፈተና ገጥሞታል። ከ1987 ዓም ጀምሮ በተለይም ደግሞ በ1994 ዓ.ም ፖሊሲ ተቀርፆለት በመላ ሀገሪቱ እየተተገበረ፣ በሁለት አሃዝ የሚቆጠር የኢኮኖሚ ዕድገት እያስገኘ ነው የሚባለው የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ገና ጭል ጭል ማለት እንኳን በደንብ አልጀመረም። ማህበረሰቡ "የባህሌን እንጂ አዲስ ነገር አያስፈልገኝም" በማለት እየተቋቋመው ነው። ሀሳቡን ለማጠናከር አባ አብዱራሂም ቀጥሎ የሚናገሩትን እንመልከት።

> … ይሄ ቴክኖሎጂ ማስፋፋትና ማስረፅ ከተጀመረ ቆይቷል። ግን በህብረተሰቡ ላይ ያመጣው ለውጥ ይህን ያህል አይደለም። እኛ የራሳችንን አንለቅም የቆየ ባህላችን ነው። መሬት አሁን መሬት

> ዝግጅት ላይ እራሱ ሌላ ቦታ ላይ ሦስት አራት አምስት ጊዜ መሬት ለስልሶ ይዘራል፤ እኛ ጋ አይቀበሉም። እንደዚያ አድርጉ ብንላቸውም "አድካሚ ነው፤ የእኛ ይሻላል እኛ እናስተምራችኂለን ወይስ እናንተ ናችሁ እምታስተምሩን?!"ይላሉ "ለእኛ ስለ እርሻ ለምን ትነግሩናላችሁ እኛ ነን እምናውቀው ሥራችን ነው!" ይላሉ፤ ግን ረጅም ጊዜ 30 ዓመት 40 ዓመት አካባቢ እየሄደ ነው፤ እና ቅርብ ጊዜ ነው ይሄን ቴክኖሎጂ እየተቀበሉ ያሉት እንደውም ወደ ታች ደሞ ወደ እኛ በደንብ የገባ አይመስለንም። እንደውም ባምባሲ[37] ወረዳ በጣም ጥሩ ነው ይባላል እንጂ፤ ወደ ሸርቆሌ፣ ወደ መንጌ፣ ወደ ሌላ ቦታ እንደዛ አይመስለኝም ተቀባይነቱ የራሳቸውን ነው የሚከተሉት።
>
> ምንድነው አሁን? እነሱ ዛሬ ያርስና እህል ሲያገኝ ያንን ሸጦ ወደ ንግድ ነው እሚሄደው እርሻውን አያስተውሰውም። ሲደኸይ ወይም ሲከስር ነው እንደገና ተመልሶ ወደ እርሻ ይመጣል። እርሻ እሚሰራው ለመንደርደሪያ ነው በቃ፤ ትንሽ እስኪያገኝ፤ ይሄ ነው ባህሉ ማለት ነው። የቆየ ባህላችን ነው እንጂ የሚጠቅመን ምንድነው ማዳበሪያ አያምኑም፤ ያለማመን ነገር አለ ያንን ለቀው ዘመናዊውን ቢጠቀሙ እንደማይሻሻሉ እንደዛ ይላሉ በጣም ሃይለኛ እንትን ነው ያላቸው (አባ አብዱራሂም፣ ቃመ22/03/05)።

ከዚህ የምንገነዘበው የልማት ፖሊሲው የገጠመውን ባህላዊ ተግዳሮት ነው። መንግስት ሀገሪቱን ከድህነት ለማላቀቅና በኢኮኖሚ ዕድገት መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ

[37] ባምባሲ ለክልሉ ዋና ከተማ አሶሳ ቅርብ፣ ዋናው አስፓልት ዳር የምትገኝ፣ ከሰሜን የሀገሪቱ ክልል የመጡ ሠፋሪዎች ከነባሩ ብሔረሰብ ጋር መሳ ሆነው የሚኖሩባት ወረዳ ናት።

ለማሰለፍ እርሻና ገጠር ልማትን ቁልፍ መሣሪያ ነው እያለ ደፋ ቀና በሚልበት በአሁኑ ወቅት ሰፊ ለም መሬት ያለው የበርታ ብሔረሰብ ምርትና ምርታማነት ማሳደግ ብሎ ፈሊጥ ገና አልተዋጠለትም። በግብርና ሥራ ብዙ ደክሞ ምርትን ማሳደግ የእርሱን ጆሮና ልቡና የሚያነቃቁ ነገሮች አይደሉም። በ"ጻሌ"ው ቆፈር ቆፈር አድርጎ ማሽላውን ወይም በቆሎውን ከዘራ በቂው ነው። የአገር ኢኮኖሚ እድገት፣ ምርትና ምርታማነትን መጨመር፣ በምግብ ራስን ችሎ ለገበያ ማምረት የሚሉት ጉዳዮች ለእሱ ምኑም አይደሉም። ለራሱም ፍጆታ ቢሆን ምርቱ አጥጋቢ ካልሆነ ትቶት ወደ ወርቅ ቁፋሮው ይገባል።

ከወርቅ ቁፋሮው የቱንም ያህል ገንዘብ ቢያገኝ በቁጠባ ተጠቅሞ ራሱን ማበልፀግ፣ ሀብትና ንብረት ማሳደግ፣ በባንክ ይህን ያህል ሚሊዮን አለኝ ብሎ መሸለም፣ በእሱ ቦታ የላቸውም። ያገኘውን ይዞ ያቺ እስክታልቅ "ሃምዲሊላ" እያለ ከዘመዶቹ ጋር ተካፍሎ መብላት ነው አበቃ።

> አንዱ አሁን እዚህ መንጌ አካባቢ እዚያ ወርቅ ይቆፍርና ቆይቷል አሁን አይደለም ወርቅ እርካሽ በነበረበት ጊዜ 60 ሺህ ብር ያገኛል። በጊዜው በጣም ብዙ ነው እና ምን ይለዋል ጓደኛው "ስማ ይህንን ገንዘብህን አታጥፋ፤ ከተማ አካባቢ ቤት ሥራ፤ ታከራያለህ፤ ጥሩ ቤቶች አንድ አሥር ክፍል ሥራ፤ ካልሆነ ደግሞ ወፍጮ ትከል፤ ወፍጮ ከተከልክ ገንዘብህ አይጠፋም።" እሺ ይልና ለጊዜው ከዚያ ግን ወደዚያ አልሄደም ገንዘቡን ወዲያውኑ ጨረሰው። አራት ሚስት አግብቷል።
>
> መጨረሻ ላይ ተገናኙ "ምን ሆንክ እኔ ነግሬህ አልነበር ወይ? እኔ እንዳልኩህ ብታደርግ ኖሮ ዛሬ ዝም ብለህ አየር አትስብም" ይለዋል። ስማ አንተ አላህ ጋ ሄደህ መጣህ ወይ? ያኔ የሰጠኝ አላህ አሁን እንደማይሰጠኝ እርግጠኛ ነህ? ይለዋል። እይው በጣም ደካማ ሆነ

> እንትን ነው ይሄ ምንድነው "አሂራ ማለት የወዲያኛው ዓለም የእኛ ናት። ይህቺ የእኛ አይደለችም" ብለው ራሳቸውን እንትን ይላሉ። እዚህ ላይ ምንም ማለት አይደለም ትተን እንሄዳለን ብለው ተስፋ የመቁረጥ ይሁን የት ቦታ እንደማስቀምጠው አላውቅም፤ በቃ ሲያገኙ አገኙ፣ ሲሄድም ሄደ፣ ሲመጣም መጣ፣ በቃ ግድ የላቸውም። አላህ አመጣ አላህ ወሰደው፤ ግን እዚያ የአላህ ሚና የለም አስተሳሰብ ነው እንግዲህ ደካማ አስተሳሰብ ከመጥፎ እንትናች አንዱ የሚታየኝ ይሄ ነው እና ይሄ አብሮ መብላት አብሮ መጠጣት እንደመጥፎ ነገር አላየውም። በሃይማኖታችንም የሚያስተምረው ቁጠባን ነው። እነዚህ የሚበትኑ ሰዎች "የሰይጣን ወንድሞች" ነው እሚለው እና ቆጥቡ ነው ሃይማኖት አያዝም ባህሉ ነው ዝም ብሎ ደካማ ባህል እንደደካማ አድርጌ እሚቆጨኝ ይሄ ነው ለምን? አናድግበትም (አባ አብዱራሂም፣ ቃመ22/03/05)።

እንዲህ ነው በርታ ዛሬ ሰራ፤ አገኘ፤ ተካፍሎ በላ፤ ሲያልቅ አለቀ በቃ። ለነገ ጥሪት፣ ካፒታል፣ ቁጠባ፣ ስስት ብሎ ነገር የለም። ያመረተው ወይ ቆፍሮ ያገኘው እስኪያልቅ ቁጭ ብሎ ይበላል፤ ይዝናናል፤ ይደሰታል። ሙሉ ጊዜውን በእርሻ መሬቱ ወይም በሥራው ላይ ማሳለፍ የሚሉት ጉዳዮች ከእርሱ ዘንድ ቦታ የላቸውም። እንደውም እሚበላው ካጣ መሥራት የግድ አይጠበቅበትም። አላህንና ህሊናውን ካልፈራ ከአንዱ "አል ከለዋ" ወደ ሌላው እየዞረ መብላት ይችላል። ለምን መጣህ ብሎ የሚጠይቀው ወይም የሚታዘበው የለም።

### 8.1.2. ሰፊ ጊዜውን በእርሻ ሥራ ላይ አለማጥፋትና ለነገ አለመጨነቅ

የበርታ አርሶ አደር በእርሻ ማሳው ላይ ሰፊ ጊዜውን አለማጥፋት፣ ከራሱ ቀለብ አልፎ ለገበያ አለማምረት ጥሪት አለመቋጠርና ለነገ አለማሰብ ምንጩ የኖረ ባህሉ ነው ለማለት ያስደፍራል። ከላይ በተደጋጋሚ እንደታየው የበርታ ብሔረሰብ አኗኗር የጋራ ነው።

ኑሮውን አስመልክቶ በግሉ የሚያሳስበውም የሚያስጨንቀውም አይደለም፡፡ የፈጠረኝ አምላክ የሚገባኝን ስለሚያውቅ እሱ ይሰጠኛል፤ ባይ ነው፡፡ ለማሳያነት የሚከተለውን ተረት እንመልከት፡፡

> አንድ ሰው አንድ ጊዜ በዚህ ዓለም እኔ መድከም የለብኝም ከፈለገ ፈጣሪ ራሱ የሚያስፈልገኝን ባለሁበት ይስጠኝ ብሎ ይወስናል፡፡ አንድ ቀን ወደ መንገድ ሲሄድ አንድ ጋን ወርቅ ያገኛል፤ አሁንም ይሄንን ወርቅ እኔ ተሸክሜ አልሄድም ፈጣሪ ራሱ ቤቴ ድረስ ይውሰድልኝ ይልና ወደ ቤቱ ይመለሳል፡፡ ወደ ቤቱ ይመለስና ለጎረቤቱ መንገድ ላይ አንድ ጋን ወርቅ  አግኝቼ ነበር ከፈጣሪ ጋር ግን ስለተነጋገርኩ ከፈለገ ቤቴ ድረስ ያምጣት እንጂ እኔ አልሸከምም ብዬ ጥዬ መጣሁ ሲለው ጎረቤትየው በነገሩ በጣም ተደንቆና በሰውየው ትዕቢት ተገርሞ ወርቅ ተገኝቶ ተጥሎ ይመጣል ጥጋበኛ እኔ ተሸክሜ አምጥቼ የራሴ አደርገዋለሁ ብሎ ወደ ተባለው ቦታ ሲሄድ ጋኑን ያገኘዋል ሲከፍተው ግን ወርቅ ሳይሆን እባብ ሞልቶበት ያገኘዋል፡፡ በጣም ይናደድና ይሄ ሰውዬ እኔ በእባብ ተነድፌ እንድሞት አይደል ወርቅ ነው ያለኝ ቆይ እሰራለታለሁ በሎ ይዝትና በሌሊት ሄዶ ጋኑን ተሸክሞ ያመጣና በሰውየው ቤት ላይ ወርውሮ እባቦቹ እንዳይነድፉት ሮጦ ይሄዳል፤ ሰውየው ጠዋት ሲነሳ ግቢው ወርቅ በወርቅ ሆኖ ያገኘዋል፡፡ ስለዚህ ሰው በአላህ ካመነ አዱኒያ ቤት ድረስ ይመጣለታል፡ መጣር መጋር አያስፈልግም፡፡ የአንዱን ዕድልም ሌላው ሊበላው አይችልም ለተፈቀደለት ብቻ ነው (አባ አልሃሰን አህመድ፣ ቃመ23/02/03፣ ተረት 5)፡፡

ተረቱን ስንመለከተው የሰውየው ውሳኔ ከመነሻው ራሱንና ማህበረሰቡን ከፍ ሲልም እግዜሩን የሚፈትን ነው፡፡ ሰውየው ጥያቄውን ሲያነሳ ራሱ ያመነበትን ዕውነት ይዞ የፈጠረውን አምላክ በድፍረት ከፈጠርከኝ ልትመግበኝ፣ የሚያስፈልገኝን ልታቀርብልኝ ግድ ይልሃል እያለው ነው፡፡ የሚያስፈልገው ሲሰጠው ደግሞ ተንሰፍስፎ ተሸክሞ አልሄደም፣ እንደገና በድፍረት በራሱ ዕውነትና ዕምነት ላይ በመቆም እኔ ለሽክም አልተፈጠርኩም ማን ሊሸከምልህ ነው የሚያስፈልገኝን እቤቴ ድረስ አምጣት ብሎ ሄደ፡፡ ይሄ የፈጣሪውን ግዴታ የፍጡሩን መብት ያስረገጠበት ነው፡፡

ከፈጣሪ ጋር የተነጋገረውንና የተሰጠውን ሲሳይ ሊወስድብኝ ይችላል ብሎ ሳይፈራ ለጎረቤቱ መንገሩ ደግሞ አንድም የበርታን ግልፅነት በራሱ ማረጋገጡ፤ አንድም በርታ የሰው ሃቅ ስለማይነካ እንደማይነካበት እርግጠኛ ሆኖ ወይም እሱንም እንደ እግዜሩ ሊፈትነው ነው ለማለት ይቻላል፡፡ ጎረቤቱ ግን በፈተናው ወደቀ፤ የበርታን የሰው ሃቅ ያለመፈለግ ባህል ሰበረና አገኘሁ ያለውን ሲሳይ የራሱ ለማድረግ ሄደ፡፡ የገጠመው ዕውነት ግን የሚያሳየው ሰውየው ባህሉን ስላፈረሰ ፈጣሪው ቅጣት ጫነበትና ጋኑን እንዲሸከም አደረገው፤ በዚህም የአማኙን ጥያቄ በመመለስ የራሱን ታማኝነት አረጋጋጠ፡፡ ሰውየውን ደግሞ ፈጣሪን ከታመኑበት ሳይለፉ ሳይደክሙ የፈለጉትን ሲሳይ እቤት ድረስ አምጥቶ ይሰጣል ብሎ እንዲመሰክር አስቻለው፡፡

እንዲህ በሥነቃሎቹና በልዩ ልዩ ባህላዊ እሴቶቹ የተገነባው የበርታ ማህበረሰብ ለእለት ጉርስ የሚፈልገውን ካገኘ ስለ ነገና ስለ ትርፉ ትርፍ ሃብቶች የሚጨነቅ ባለመሆኑ ሰፊ ጊዜውን ማሳው ላይ በማጥፋት በግብርናው ዘርፍ የልማት ዕቅዱን መተግበር አልቻለም፡፡ ከላይ አባ ኢብራሂም ስለ “አሂራ” ያነሱትም ሀሳብ ይህንኑ የሚያጠናክር ነው፡፡ ይህ ደግሞ የመስኩ ምሁራን የባህልን ተግባሮች (functions) ከሚገልፁባቸው መንገዶች አንዱ የሆነው የባህልን የመትከልና የማጠናከር ተግባር የሚያሳይ ነው (Bascom፣1954፣ Okpewho፣1992፣ Finnegan፣1992፣ፈቃደ 1991)፡፡

ባህሉ ከላይ ባየነውና በኂላ በስፋት በሚነሱ ሥነቃሎች ራሱን እየተከለና እያጠናከረ በማህበረሰቡ ውስጥ ሰርጅቶ የኖረ በመሆኑ የበርታ ብሔረሰብ እንኳን በግሉ ትርፍ አምርቶ፣ ምርትና ምርታማነቱን በማሳደግ የራሱን ካፒታል ስለመጨመር፣ የአገር ኢኮኖሚ በሁለት አሃዝ ስለማሳደግ፤ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ምርቶች መርጦ ስለማምረትና ለገበያ ስለማቅረብ ሊጨነቅ ቀርቶ ነገው በአላህ እጅ ያለች ስለሆነች ምን እሆናለሁ ብሎ አይጨነቅም፡፡

ከዚህ የምንገነዘበው ደግሞ በሀገሪቱ ሌሎች አካባቢዎች ተተግብሮ ውጤት እያሳየ ነው የተባለው የልማት ፖሊሲ ከተጀመረ ከአሥር ዓመት በላይ ቢሆነውም በበርታዎች አካባቢ ውጤታማ ሳይሆን ለመቆየቱ የማህበረሰቡ ባህል ምን ያህል ተፅዕኖ እንዳሳደረበት ነው፡፡ በመሆኑም የማህበረሰቡን ባህላዊ ሁኔታዎች ሳያጠኑና ሳያውቁ ከዚያም በላይ አስቀድሞ ሳይሠሩና ሳይዘጋጁ አንዱ አካባቢ ተግባራዊ የሆነ የልማት ዕቅድ በሁሉም አካባቢ ሊተገበር ይችላል ብሎ መነሳት ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡

### 8.1.3. "የታታሪነት ችግር" ወይስ ባህሉን አለመገንዘብ

የበርታ ብሔረሰብ ባህላዊ ሁኔታዎች ከላይ ያየናቸው ሆነው ሳለ የክልሉ መንግስት በ2003 ዓም. በነደፈው የአምስት ዓመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ላይ የልማቱን ዕቅድ ላለማሳካት እንደ ዋነኛ ማነቆ በአፅንዖት ተገልፆ የሚገኘው የህዝቡ የታታሪነት ችግር ነው፡፡ ሃሳባችንን ለማጠናከር በክልሉን መንግሥት ዕቅድ ላይ የሠፈረውንና የብሔረሰቡን ባህላዊ ሁኔታ አያይዘን ቀጥለን እንመልከተው፡፡

> … የመጀመሪያው የሰው ሃይላችንን የሥራ ዝግጁነትና ታታሪነትን ማረጋገጥ ነው፡፡ ህዝባችን ሥር በሰደደ ድህነት ውስጥ ለዘመናት በመቆየቱና የተሻለ ኑሮን ለማጣጣም አጋጣሚውን አግኝቶ

ስለማያውቅ ከድህነት ተላቆ የተደላደለ ኑሮ ለመኖር ያለው ምኞትና ጉጉት በሚፈለገው ደረጃ ባለመሆኑ ይህንን የኑሮ መሻሻል ለማረጋገጥ የሚያስችል ፍላጎት፣ ዝግጁነትና የሥራ ታታሪነት ችግሮች በእጅጉ የሚታዩ ቁልፍ ማነቆዎች ናቸው።

የታታሪነት ችግሩ ዓመቱን ሙሉ በሥራ ላይ ባለመሠማራቱ፣ በቀን በአማካይ ከ2 ና 3 ሰዓታት ላልበለጠ ጊዜያት በመስራት፣ የግብርናን ስራ ወቅቱን ጠብቆ ባለመከናወንና እያንዳንዷን የግብርና ተግባር በወቅቱ ባለመፈፀም የሚገለፅ ነው። የሚያመርተው ምርትም ለቤተሰቡ የምግብ ፍጆታ አሟልቶ ለገበያም ጭምር በማምረት ከሚያገኘው ገቢ ኑሮው ለማደላደል የሚያስችለው አይደለም። …

ከባህልና ጎጂ ልማዶች ጋር የተያያዙ ችግሮችንም ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት የማስተካከል ሥራ ይሠራል። አርሶ አደሩን በማሳመንና ዴሞክራሲያዊ በሆነ ትግል ህይወቱን በታታሪነትና በፍጥነት ማሻሻል እንደሚችል ተከታታይነት ያለው ትምህርትና ቅስቀሳ በማድረግ ከተግባር ውጤትም እንዲማር በማድረግ አስተሳሰቡን መለወጥ ያስፈልጋል። በተጨባጭ ምርቱን እንዲያሳድግና የምግብ ፍጆታውን አሟልቶ ለገበያ የሚሆን ምርት እንዲያመርት ይደረጋል። በአብዛኛው በነባሩ ህብረተሰብ[38] ውስጥ ያለው የራስን የምርት ጊዜ እንደዋዛ እያባከኑ በዘመድ አዝማድ ጥገኛ የመሆን ባህልም ትኩረት ተሰጥቶት የሚቀረፍ ይሆናል (ቡጉክመየ5ዓዕትዕ፣2003፣ገፅ 14፣ አጽንዖቶቹ የኔ ናቸው)።

[38] ነባሩ ህብረተሰብ የተባሉት አምስቱ (በርታ፣ ጉሙዝ፣ ሺናሻ፣ ማኦና ኮሞ) የክልሉ ብሔረሰቦች ናቸው።

ከዚህ የምንገነዘበው የማህበረሰቡ ባህል የመንግሥትን የልማት ዕቅድ እንዴት ቀይዶ እንደያዘ ነው። እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ ደግሞ እንደመፍትሔ የተቀመጠውን ነገር ስናይ "ተከታታይነት ያለው ትምህርትና ቅስቀሳ በማድረግ ከተግባር ውጤትም እንዲማር በማድረግ አስተሳሰቡን መለወጥ" የሚል ነው። የተግዳሮቱ ምንጭ የማህበረሰቡ የኖረ ባህል መሆኑ እምብዛም ትኩረት አልተሰጠውም። መንግሥት የክልሉ ማህበረሰብ የተረሳ ስለነበርና ስር በሰደደ ድህነት ውስጥ የቆየ በመሆኑ የተሻለ ኑሮ አያውቅም፤ የመሻሻል ተስፋና ተነሳሽነት የለውም፤ ስለዚህ ለሥራ ታታሪ አይደለም ይላል።

ዕውነታው ግን ይሄ አይመስልም፤ ከላይ ከጠቀስናቸው መረጃዎች እንደሚታየው ማህበረሰቡ ያለበት የታታሪነት ችግር ነው ብሎ ለመደምደም አስቸጋሪ ነው። ምክንያቱም ያርሳል፤ ይነግዳል፤ በቀላሉ ለማግኘት አስቸጋሪ የሆነውን ወርቅ በባህላዊ መንገድ በመቆፈርና ከአፈር ውስጥ አጥቦ በማጣራት ብዙ ጊዜውንና ጉልበቱን ያፈሳል። ወርቅ ፍለጋውም ከመኖሪያ አካባቢው ሩቅ መንገድ መጓዝን በረሃ ላይ መዋል ማደርን ይጠይቃል። ያ ሁሉ ሆኖም ወርቁ ከነጭራሹ ላይገኝ ወይም የተገኘው ጥቂት ሊሆን ይችላል። ማህበረሰቡ ግን ፈጣሪ የፈቀደልኝን ነው ያገኘሁት ብሎ ሳያማርርና ሳይሰለች ለአድካሚው የወርቅ ቁፋሮ ይተጋል እንጂ ሰለቸኝ ብሎ አይተወውም። ይሄ ሁሉ ካልሆነ ደግሞ ሱዳን ድረስ እየተሻገረ ሥራ ፈልጎ ይሠራል።





ፎቶ 19 አድካሚው ባህላዊ የወርቅ ማምረት ሥራ

ብሔረሰቡ ለፍቶ ሠርቶ የመብላትን ጥቅምና የሥራ ትጋትን አስፈላጊነት በምሳሌያዊ ንግግሮቹም እንዲህ በማለት ያጠናክረዋል።

"ማበሽ ቅሊ አጉር"

"በስራ የሚተጋ ንጉስ ነው"

"ቡቡዳ ዋለቲላ ማንኩሾ ቀላኢ ኢንቲጎቲነ ዝሊ"

"አመድ አይበላም እህል ለማግኘት ሥራ"

"አሽቁል ጲሺ መንቆሽጋ አንጎቲኒ"

"ሳይሠራ ስለማይበላ ስንፍናን አስወግድ"

እነዚህ ምሳሌያዊ ንግግሮች ስንፍናን የሚጠየፉ፣ ሳይታክቱ መሥራትንና መትጋትን የሚያበረታቱ በመሆናቸው ብሔረሰቡ ለሥራ ትጋት የሚሠጠው ቦታ ከንግሥና የሚስተካከል እንደሆነ ያመለክታሉ። ተግቶ የመስራትን ጥቅም ተረድቶ ሳይታክት የሚማስነውን ይህን ብሔረሰብ የሥራ ታታሪነት ይጎድለዋል ማለት ታዲያ ዕውነትነት ያለው አይደለም። ችግሩ ባህሉ አብሮ ተካፍሎ መብላትን፤ ለነገ ብሎ አለማሰብን፣ ጥሪት አለመቋጠርን፣ ለነገ አላህ ያውቃልን፣ ስላስተማረው ያገኘውን ዘመድ አዝማዱን ሰብስቦ እስክታልቅ ያበላል፤ ስታልቅ ወደ ሥራ ይሠማራል። ይሄ ደግሞ ጥሪት እንዲቋጥር ስላላደረገው ያንን የመሰለ ለም መሬት ይዞ ሌላ ዓለም ሳይመኝ ኑሮዬ ይበቃኛል ብሎ እንዲኖር ባህሉ አስገድዶታል።

የበርታ ብሔረሰብ የታታሪነትን ጥቅምና የስንፍናን አስከፊነት እንደሚገነዘብ በተረቶቹ ደጋግሞ ሲያነሳው ማየት ይቻላል።

> በዱሮ ጊዜ በጣም ታታሪና ጎበዝ የሆነች ወንድን የምታስንቅ አንዲት ሴት ነበረች። በእርሻ ጊዜ በጠዋት ተነስታ ወደ ማሳዋ ትወርድና ስትቆፍር ውላ የሚያስፈልጋትን ዘርታ ትመለሳለች። በዚያው መንደር ከእርሷ እርሻ አጠገብ መሬት ያለው ሌላ ሰው ነበረ። እሱም በጠዋት ይነሳና በእርሻው አንድ ጫፍ ቁጭ ብሎ በጣቱና በአገጩ እያመለከተ ነገ ከዚህ ጀምሬ እስከዚያ ድረስ እቆፍርና ማሽላ ዘርቼ ይህን ያህል ኩንታል አመርታለሁ እያለ ሲወራ ይመሽለታል። አንድም ቀን ግን ተነስቶ ቁፋሮውን አይጀምርም። በመጨረሻ የምርት ወቅት ይደርስና ታታሪዋ ሴት በርካታ ምርት ትሰበስባለች። በዚህ ጊዜ የሁለቱንም ከእርሻቸው ላይ መዋል የሚያውቁና እሱ ባዶ እጁን ቀርቶ እሷ ብዙ በማምርቷ የተገረሙ ሰዎች ሲጠይቋት “እንደምታዉቁት እሱ በምላሱና በአገጩ ሲሰራ እኔ በእጆቼ ጠንክሬ ሰርቻለሁ፤ እንደኔ ከአፉ ይልቅ በእጆቹ ቢሠራ ኖሮ ከእኔ የበለጠ ምርት ያፍስ ነበር” አለቻቸው ይባላል (እማ ኢንሹ አብዱራሂም፣ ቡውይቆሽ18/04/05፣ ተረት 21)።

ከዚህ ተረት የምንረዳው በጠዋት ተነስቶ ተግቶ በማሳ ላይ የመሥራትን ጥቅም ነው። የክልሉ መንግሥት ግምገማ እንደሚያመለክተው ብሔረሰቡ ሰፊ ጊዜውን በእርሻ ማሳው ላይ ማሳለፉ የሚያመጣለትን ጥቅም ያልተረዳ አይደለም። ከላይ በተረቱ በንፅፅር የቀረቡት ወንድና ሴት ናቸው። ሴቷ “ወንድን የምታስንቅ ታታሪ” ተብላ መቀመጧም ወንዶች በተሻለ ታታሪ መሆን እንዳለባቸው በባህሉ እንደሚጠበቅ የሚያሳይ ነው። የሴቷ ስኬትና የወንዱ ከወሬና ከምኞት አለማትረፍ ደግሞ የስንፍናን አስከፊ ገፅታ የሚያመለክት ነው።

ይሄ የታታሪነትን ጥቅም በተረቶቻቸው ተደጋግሞ ሲመጣ እናየዋለን (ተረት 25፣26፣32)።

ከዚህ ደግሞ ብሔረሰቡ ሙሉ ጊዜውን በሥራ ላይ ማሳለፍን የሚጠላ እንዳልሆነ ያሳይል። ችግሩ ሠርቶ ያገኘውን ተካፍሎ መብላቱና ለነገ ብሎ ጥሪት ያለመቋጠሩ ነው። ስለዚህ ብሔረሰቡን በደፈናው "የስራ ታታሪነት ይጎድለዋል" ከማለት በእነዚህ በራሱ ተረቶች መነሻነት በማስተማር የተፈለገውን ለውጥ ማምጣት ይቻላል። ቀጥሎ የቀረበው ተረትየተግቶ መስራትን ጥቅምና ጥሪት አለመቋጠር የሚያስከትለውን ችግር የሚያሳይ የበርታዎች ተረት ነው።

> በድሮ ጊዜ ዝንጀሮዎች በጣም ጥበበኞችና ሃብታሞች ነበሩ ይባላል። አጉር ጋሱም የተባለ ንጉስም ነበራቸው። በአጉር ጋሱም መሪነትም ማሳቸውን ጠንክረው እያለሙ ሁሉንም ዓይነት እህል ያመርቱ ነበር። በዚህም እንደፈለጋቸው እየበሉ፣ እየጠጡና እየጨፈሩ ይኖሩ ነበር። ምርታቸውም ከፍተኛ ስለነበረ ሁሉንም አይጠቀሙበትም ነበርና ተርፎ የሚበላሸው ብዙ ነበር። ምግብም በየቦታው የተትረፈረፈ ስለነበረ የሚሸጥም ሆነ የሚገዛ አልነበረም። ስለዚህ ይሰበሰቡና የተትረፈረፈውን ምርት ምን እንደሚያደርጉት ተወያይተው ወንዝ ውስጥ ሊጨምሩት ይስማማሉ። ሃሳባቸውን ለአጉር ጋሱም ሲያማክሩት በነገሩ ይስማማና ታላቅ ድግስ ተደግሶ በየሀገሩ ያለው ዝንጀሮ ሁሉ ታድሞ ሲበላ ሲጠጣ ይከረምና በመጨረሻ የተረፈውን ምርት እየተሸከሙ "አንተ አስቀያሚ ምግብ ዞር በል ከፊታችን" በማለት በጋራ እየጮሁ ወንዝ ውስጥ ይጨምሩታል። ምንም ጥሪት ሳያስቀሩ ሁሉንም ነገር ዉሃ ስላስበሉት ከጥቂት ቀናት በኋላ የሚላስ የሚቀመስ ይጠፋል። አጉር ጋሱምን ጨምሮ ብዙ ዝንጀሮ በረሃብ

ያልቃል። ከዚያም አያስፈልገንም ብለው ወንዝ የጨመሩትን ምግብ ፍለጋ ይወጣሉ። ከዚያ ጊዜም ጀምሮ ምግባቸውን ፍለጋ ከዛፍ እዛፍ እንደዘለሉ፤ ተራራ እንደቧጠጡ፤ የሰው ነዶ እንደዘረፉ ሳይደላቸው ይኖራሉ (አቶ ሙርሳል ሰኢድ፣ ቡውይ22/02/05፣ ተረት 27)።

ይህን ተረት የነገሩኝ በተጠቀሰው ቀን በመቃዚን ቀበሌ ወንዶች ብቻ በተገኙበት የቡድን ውይይት ላይ ታታሪነትንና ጥሪት መቋጠርን አስመልክቶ ለተነሳው ውይይት በማስረጃነት ነው። ከቡድን ውይይቱ እንደተረዳሁት ህዝቡ ተግቶ በመሥራት ያምናል። ሆኖም ስለነገ ብዙም ስለማይጨነቅና አንዱ ቢያጣ ሌላው ስለሚሰጠው በርካታ ነገር በግሉ ማጠራቀምንና ማስቀመጥን ብዙ አይፈልግም። አይበለውና ድርቅና ሌሎች ተፈጥሮኣዊ አደጋዎች ቢመጡና ከላይ በተረቱ እንደተገለፁት ዝንጀሮዎች በሁሉም ሰው ዘንድ ምንም የሚቀመስ ቢጠፋስ ምን ታደርጋላችሁ? ብዬ ስጠይቅ በሰጡኝ መልስ "ሱዳንም ቢሆን ሄደን እንሠራለን፤ እዚያም ያሉ ዘመዶቻችን ስንቸገር ዝም አይሉንም" የሚሉ ጥቂት ሀሳቦች ተነስተው የነበረ ቢሆንም አብዛኞቹ ግን "ልምዱ ስለሌለን ነው እንጂ ጥሪት መቋጠሩስ ጥሩ ነበር" (መቃቡውይ22/02/05) ብለዋል።

በርታዎች የዕለት ጉርሳቸውንና የአመት ልብሳቸውን ለማግኘት ሱዳን ድረስ በመሄድ ሰሊጥ ያጭዳሉ፣ ከዚህ የረከሰ ወደዛ ከዛ የረከሰ ወደዚህ አምጥቶ በመነገድ በሚያገኙት ትርፍ ለራሳቸውና ለቤተሰቦቻቸው ልብስና ጫማ ይገዛሉ (አቶ አልሀሰን አብዱራሂም፣ ቃመ15/03/05)። ጥሪት ለመቋጠር ያልቻሉት በባህላቸው ተካፍሎ መብላትና ለመጪው አለመጨነቅ ስላለ እንጂ የሥራ ትጋት ስላጡ አይደለም። ይልቁንም ይህን የጋራ አስተሳሰብ ለልማት እንደ ጥሩ ዕድል ቆጥሮ በጋራ መብላትን ብቻ ሳይሆን በጋራ ሠርቶ በጋራ ለማደግም መሣሪያ ማድረጉ ጠቀሜታው የጎላ ይሆናል።

ከላይ የቀረቡትን ተረቶች ማስተማሪያ በማድረግም በየአል ከለዋው ተገኝቶ ህዝቡን እንዲወያይበት በማድረግ የተቀዛቀዘ የሥራ ስሜት አለ ብሎ ከታሰበ ለማነቃቃት፤ በባህሉ ያልተለመደውን ቁጠባና ጥሪት ማስቀመጥንም ጥቅም በማስረዳት የተፈለገውን ለውጥ ማምጣት ይቻላል። የባህሉም የአስተማሪነት ተግባር እዚህ ላይ ጠቃሚ ሚና ይኖረዋል ማለት ነው።

በባህልና ልማት ቁርኝት ላይ ትኩረቱን አድርጎ የተዘጋጀው የዩኔስኮ ሰነድ እንደሚያመለክተው "ሰዎች ከተፈጥሮኣዊ አካባቢያቸው ጋር ያላቸውን ዝምድና፣ እንዴት እንደሚጠብቁትና እንደሚያስተዳድሩት የሚኖራቸው አመለካከት የሚቀረፀው በባህላቸው በመሆኑ ባህል ለዘላቂ የአካባቢ ልማትና ጥበቃ አንቀሳቃሽ ሞተር ነው" (UNESCO,2010;) ይላል። ስለዚህ ይህን የልማት አንቀሳቃሽ ሞተር ተጠቅሞ የአካባቢውን ልማት ለማፋጠን ማህበረሰቡን በጥቅሉ "የሥራ ታታሪነት የለውም" ብሎ ከመደምደም ባህሉን እንዴት የልማት መሣሪያ እናድርገው? በሚለው መሠረታዊ ጉዳይ ላይ ትኩረት አድርጎ በባህሉ ዙሪያ ከጎሳ መሪዎች፣ ከሀይማኖት አባቶች፣ በማህበረሰቡ ዘንድ ተሰሚነት ካላቸው ሰዎች፣ ወዘተ ጋር አጥብቆ መመካከር፣ የሚሉትን ማዳመጥና ሃሳባቸውን ተቀብሎ ከልማታዊነቱ ጋር ለማዋሃድ በሥነቃሉና በሌሎች ባህላዊ ዘውጎቹ የሚገለፁትን የብሔረሰቡን ባህላዊ ዕውቀቶች መሠረት አድርጎ መነሳትና ከዚህ አኳያም ጠንክሮ መሥራት የክልሉ መንግስት ዋና የቤት ሥራ ሊሆን ይገባል።

በሽርቆሌ ወረዳ በተዘጋጀ የቡድን ውይይት ጊዜ ማህበረሰቡ ለምን ከራሱ ፍጆታ ያለፈ ምርት እንደማያመርት፣ ጥሪት ለምን እንዳማያስቀምጥ በሌሎች ክልሎች ልማታዊ አርሶ አደር እየተባሉ በመንግሥት የሚሸለሙ ሰዎችን አንስቼ ምሳሌ በመስጠት እንዲወያየበት ባደረግሁ ጊዜ ኢብራሂም በተባለ መረጃ ሰጪዬ የቀረበው ምሳሌ ይህንን ይመስላል።

> አንቺ እንዳልሽው ለልምድ ልውውጥ ተብሎ ከየወረዳው ሰዎች ተመልምለን ወደ አማራ ክልል ይዘውን ሄዱ፤ ይሄ አርሶ አደር ይሄን ያህል አምርቶ ሸጦ ይሄን ያህል ሺህ ገንዘብ አጠራቅሟል ምናምን እ ቆርቆሮ ቤት ቴሌቪዠን ምናምን አለው መኪና ገዝቷል ምናምን እያሉ ያሳዩናል ሰውየው ግን ጫማ እንኳን የሌለው ወላሂ ስሊፐር እንኳን የለውም፤ እኔ ለማን ነው የምታጠራቅመው ስለው ልጆቼን አስተምራለሁ ምናምን ይላል ወላሂ በደንብ የሚበላ እንኳን የጠገበ አይመስልም ሁሉም እንደሱ ናቸው በመጨረሻ ውይይት ተብሎ ስንቀመጥ የእኛ ሰው ካልበሉና ጫማ ከሌላቸው ሰዎች ልምድ ምንድነው የምንወስደው ብሎ በቃ እንደገረመን ተመለስን… ወላሂ… ሳልበላ ለማጠራቀም ከሆነ ምን ያረጋል ገንዘብ ሃላስ… ለነገ ምንድነው ነገ እኮ ባላህ እጅ ነው ወላሂ… (ቡውይሽር04/04/05)፡፡

በርታ ትርፍ ምርት አያስፈልገኝም፣ ያገኘኋትን ዛሬ በልቼ ተደስቼ ለነገ አላህ ያውቃል ባይ ነው፡፡ ታዲያ ይህንን ማህበረሰብ ለመለወጥ የሚያስፈልገው ባህሉን ራሱን በማልማትና መሣሪያ በማድረግ አመለካከቱን ማስቀየር እንጂ የክልሉ መንግሥት ዕቅድ እንደሚለው "ዴሞክራሲያዊ በሆነ ትግል ህይወቱን በታታሪነትና በፍጥነት ማሻሻል…" የሚቻል አይደለም፡፡ የቱንም ያህል ዴሞክራሲያዊ ትግል ቢደረግ ለውጥ ማምጣቱ ላይ አስቸጋሪነቱ አያጠራጥርም፡፡ ይልቁንም ባህላዊ መሠረቱን ለይቶ በማጥናት ከአካባቢው ሽማግሌዎች ጋር በጋራ መክሮ አዲሱን በነባሩ ላይ በመገንባት የሚታሰበውን ልማት ማምጣት ይቻላል፡፡ ከዚህ ውጪ የዘመናዊነት አስተሳሰብ አራማጆች እንደሚሉት "የማህበረሰቡ ባህል ለልማት ማነቆ ስለሆነ መወገድ ይገባዋል" ብሎ መነሳት ብዙ ርቀት የሚያስኬድ አይደለም፡፡

አሉላና ገብሬ እንደሚሉት "... ልማት እንዲመጣ ከተፈለገ ህዝቡን በውሳኔ አሰጣጥ ማሳተፍ፣ የህብረተሰቡን ፍላጎትና ባህል ግምት ውስጥ ማስገባት፣ እንዲሁም በአካባቢው የሚገኘውን ሀብትና ዕውቀት መጠቀም የግድ ነው" (አሉላና ገብሬ፣2004፣81):: ስለዚህ ከላይ ወደታች በሚወርድ የልማት ዕቅድና ዉሳኔ ብቻ ልማትን ማምጣት አስቸጋሪ በመሆኑና ከላይ በስፋት እንደታየውም የበርታ ብሔረሰብ የጋራ ጉዳዮችን በጋራ የመፍታት ባህሉ የጠነከረ ስለሆነ የታሰበውን የልማት ዕቅድ በጋራ መክሮበት፣ አስፈላጊነቱን አምኖበትና የራሱ ጉዳይ አድርጎት ለተግባራዊነቱ እንዲነሳ ለባህላዊ ሁኔታዎቹ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት የግድ ይሆናል::

ይሁንና የክልሉ መንግሥት ለባህል ጉዳዮች የሠጠው ትኩረት ከአሉታዊ ጎናቸው ላይ ብቻ ያተኮረ እንጂ ለልማት የሚኖራቸውን አዎንታዊ ሚና ያገናዘበ ባለመሆኑ ጎጂነታቸውን ጎታችነታቸውን የሚያጎላ ነው:: በፌዴራል ደረጃ ታዳጊ ክልሎችን ለማገዝ የተቋቋመው ቦርድም የግብርና፣ የጤና፣ የትምህርት፣ የውሃ፣ የመስኖ ወዘተ ባለሙያዎችን ከፌዴራል እየመደበ የክልሉን መንግሥት አመራር አካላትንና ህዝቡን እንዲያግዙ ሲያደርግ የባህልን ጉዳይ የሚመለከት ባለሙያ አለመመደቡ በልማቱ ሥራ ላይ ለባህል የተሰጠው ትኩረት አነስተኛ መሆኑን የሚያመለክት ነው::

ባህላዊ እሴቶችን መሠረት አድርጎ የሚነሳ የልማት ሥራ በርካታ ጥቅሞች አሉት:: በማህበረሰቡ ዘንድ ያለው ታላቅ ማህበራዊ ትሥሥር ለፈጣን ዕድገት ጠንካራ መሠረት ነው:: ሃገር በቀል ዕውቀትን፣ አካባቢያዊ ሀብትንና ጥበብን ከጥቅም ላይ በማዋልና ባህላዊ ኢንዱስትሪዎችን በማልማት ትልቅ የልማት ስኬት ማምጣት እንደሚቻል መረጃዎች ያመለክታሉ (UNESCO, 2012;4,)::



ፎቶ 20 የወርቅ ማምረቻ ቁሳቁሳቸውን ይዘው ወደ ሥራ ሊሠማሩ የተዘጋጁ ወጣት ሴቶች

የበርታ ባህል ከመነሻው ሲታይ አብዛኛው ሰው የገቢ ምንጩ የተመሠረተው በእርሻ ሥራ ላይ ብቻ አይደለም። ብሔረሰቡ ወርቅ አምርቶ የመሸጥ፣ የዕደ ጥበባት ውጤቶችንና በአነስተኛ የጎጆ እንደስትሪዎች ከሰሊጥና ከመሳሰሉት የቅባት እህሎች በባህላዊ መንገድ ዘይትና ቅባቶችን ማምረት፣ የመዋቢያ ነገሮችንና ሽቶዎችን ተፈጥሮኣዊ ከሆኑ ነገሮች ቀምሞ የመጠቀም፣ አነስተኛ ንግዶችን ሱዳን ድረስ እየዘለቀ የመነገድ ባህልና ልምድ ያለው ነው።

ይህን ሁሉ ሀገረሰባዊ ዕውቀት ያለውን የበርታ ብሔረሰብ "የሥራ ታታሪነት የለውም" ብሎ በደፈናው ከመደምደምና የኋላ ቀር አስተሳሰብ ባለቤት አድርጎ ከመፈረጅ እነዚህን ባህላዊ እሴቶቹን ከጋራ አኗኗር ልማዱ ጋር አስተሳስሮ በማልማት ወደ ትናንሽ ኢንዱስትሪዎች በማሳድግ አካባቢውን ማልማት ከማስቻሉም በላይ ተጨማሪ የሥራ ዕድልን ፈጥሮ ብሔረሰቡን ተጠቃሚ ማድረግ ይቻላል፡፡ ስለዚህ አካባቢውን ለማልማት ከተፈለገ በባህሉ መልካም መሠረቶች ላይ መነሳትና ህዝቡን አሳታፊና ተጠቃሚ በማድረግ ውጤታማ መሆን ይቻላል፡፡

## 8.2. የጤና ኤክስቴንሽን እና የበርታ ብሔረሰብ ባህል

መንግሥት ከነደፋቸው የልማት ፖሊሲዎች መካከል ከግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲ ቀጥሎ የጤና ፖሊሲ ተጠቃሽ ነው፡፡ ለዚህ የማህበረሰብ ጤና እንክብካቤ ፖሊሲ ማስፈፀሚያነት በገጠር የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጅ ትግበራ ከተጀመረ ብዙ ዓመታት ሆኖታል፡፡ የቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የነበረውን ቀዳሚ አተገባበር በመገምገም ባዘጋጀው የአምስት ዓመት የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ላይ ትኩረት ሰጥቼ እሰራዋለሁ ያለው አንዱ ጉዳይ ይሄው የማህበረሰብ ጤና እንክብካቤ ዕቅድ ነው፡፡ ዕቅዱ የገጠመው ተግዳሮት ቀጥሎ ይቀርባል፡፡

### 8.2.1. ባህላዊ ህክምና

የክልሉ መንግሥት ከላይ በተጠቀሰው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ውስጥ በክልሉ የሚኖሩት ነባር ብሔረሰቦች በጤና አጠባበቅ ጉዳዮች ዙሪያ ያላቸውን አመለካከት እና ወደፊት ምን መሠራት እንዳለበት እንዲህ በማለት ይገልፃል፡፡

እንደሌሎች የልማት አገልግሎቶች ሁሉ የጤና አገልግሎት ተጠቃሚነቱ የፍትሃዊነት ችግሮች ጎልተው የሚታዩበት ነው።… ሴቶችና ነባሩ ማህበረሰብ በአግባቡ ተጠቃሚ ካልሆኑ ደግሞ የተመረጡ የዘርፉ ግቦችን ማሳካት በፍፁም አይቻልም። ለፍትሃዊነቱ መጓደል ቁልፍ ምክንያቶች የአቅርቦት ችግርና አቅርቦቱ ሲሟላም በተለያዩ የግንዛቤና የአመለካከት ችግሮች ምክንያት ተጠቃሚ መሆን አለመቻላቸው ነው። ስለሆነም ሶስቱንም ማነቆዎች ማለትም የአቅርቦት የግንዛቤና የአመለካከት ችግሮች ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተን እንፈታለን።….

…. ሦስተኛው ማነቆ በየደረጃው የሚገኝ ከኋላ ቀር አስተሳሰብ ጋር የተያያዘ የአመለካከት ችግር ነው። በዚህ ረገድ በሽታን በዘመናዊ መንገድ በመከላከልና በዘመናዊ ህክምና መፈወስን ሳይሆን **በሁሉም ህብረተሰብ** በባህላዊ ህክምናና በጥንቆላ የማመን ከፍተኛ የሆነ ችግር አለ። ይህ ከፍተኛ የአመለካከት ትግል የሚያስፈልገው ነው። ስለሆነም የሃይማኖት መሪዎችን፣የአገር ሽማግሌዎችን፣ አመራሩን በማቀናጀት ተከታታይነት ያላቸው ኮንፈረንሶችና የህዝብ ውይይት በማድረግ ተጨባጭ ለውጥ እናስመዘግባለን። በተለይ ከሴቶች የስነ ተዋልዶ ጤና ጋር ተያይዞ የሚታይ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት በምናደርገው በዕቅድ የተመራ ከፍተኛ የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ፣ የአመለካከት ትግልና በምንፈጥራቸው ሞዴሎች አማካይነት ሙሉ ለሙሉ እናስወግዳለን (ቡጉክመየ5ዓዕትዕ፣ 2003፣ ገፅ 14፣ አጽንዖቶቹ የኔ ናቸው)።

ከላይ በክልሉ መንግሥት ዕቅድ እንደተገለፀው የበርታ ብሔረሰብ ጤናው ሲታወክ ወደ ባህል መድሃኒት አዋቂዎችና ኤሪዎች ዘንድ ሄዶ መታከምን አሁንም እየተገበረው ይገኛል። ሸርቆሌ ወረዳ አቤኤሬ ቀበሌ ላይ የሚኖሩ ቦሪድ አሻጉድ የተባሉ ኤሪ ቤት ተገኝቼ የሰበሰብኩት መረጃ ይህንን ለማረጋገጥ የሚያስችል ነው። ሰውየውን መጀመሪያ ያገኘሁዋቸው ሸርቆሌ ለገበያ መጥተው ሲሆን እንዲህ ዓይነት ሰው እንደምፈልግ ለሲቲና ቀድሜ ነግሬያት ስለነበር ገበያ ስታገኛቸው እቤት ይዛቸው መጣችና አስተዋወቀችን። እርሳቸውን ስለምፈልግበት ጉዳይ በሚገባ ካስረዳቻቸው በኋላ በማግስቱ ጠዋት ቤታቸው ከመጣሁ ሁሉን እንደሚነግሩኝና እንደሚያሳዩኝ ተስማማን።

በዚህ መሃል ሲቲና ሰሞኑን ከአንድ ሳምንት ለበለጠ ጊዜ ወገቤን ያመኛል እያለች በተለይም ስትተኛ በጣም እየተቸገረች ቆይታ ነበርና ይህንኑ በሽታዋን በቋንቋቸው ነገረቻቸው። ወዲያው ለምርመራና ለህክምና ልብሷን ከወገቧ በላይ እንድታወልቅ ነገሯት። ምንድነው ብዬ ስጠይቅ “ሊያክሙኝ ነው” አለችኝ። ከምርሽ ነው ስላት “ወላሂ” አለችኝ፤ ገረመኝና ቪዲዮ ካሜራየን አዘጋጀሁ። እንደታዘዘችው ቶቧን አውልቃ ከወገቧ በላይ ራቁቷን ሆና ከፊታቸው ቆመች። ውሃ ከጆግ ወስደው አፋቸውን ተጉመጠመጡ፤ ከዚያው ውሃ በጥቂቱ ወስደው ደግሞ ቢስሚላሂ ብለው ረጨት አደረጓትና የሚሰማትን አካባቢ በጣታቸው እየወጋጉ መፈተሽ ጀመሩ፤ ቀጥለውም በሽታው ይገኝበታል ያሉትን ቦታ በአፋቸው በመምጠጥ ቀጫጭን ሥራ ሥር የመሰሉ እንጨቶችን እየመዘዙ ያወጡ ጀመር። አልፎ አልፎ ደግሞ የሚምለገለግ ንፍጥ የመሰለ ነገር ባፋቸው መጠው በማውጣት ያሳዩንና ወደ ውጪ ይጥሉታል። ተገርሜ መከታተል ጀመርኩ። በዚህ ሁኔታ ወደ ሰባት የሆኑ ሥሮችን ከሆዷ፣ ከጀርባዋ፣ ከማጅራቷና ከትክሻዋ አካባቢዎች ባፋቸው እየመዘዙ ካወጡ በኋላ ክንዷን እጥፍ ዘርጋ እያደረጉ እንደማነቃቃት አደረጉና እንድትለብስ አዘዙዋት። ከሲቲና ሰውነት በኤሪው እየተመዘዙ የወጡት ሥራ ሥሮች አስገርመውኛል። የወጣበትን ቀዳዳ ለማየት ብሞክር ሰውነቷ ላይ ምንም አሻራ የለም።

ጥያቄየን መጀመሪያ የሰነዘርኩት ወደ ሲቲና ነበር፡፡ “ሲቲየ የምርሽን ንገሪኝ በዚህ ነገር ታምኚበታለሽ?” አልኳት፡፡ “እሱን ከተሻለኝ አብረን እናየዋለን” አለችኝ ባጭሩ፡፡ ከዚያም ሰዉየውን ምሳ አብልታ ነገ በጠዋት እንድንመጣ ነግረውን ተሰነባበትን፡፡ ጉዳዩን እንደገና አነሳሁት፡፡ ቢተሚና[39] የምትባል ሌላ መረጃ ሰጪዬ አብራን ስለነበረች ሁለቱ እየተቀባበሉ የሚሠራውን ተዓምር ያስረዱኝ ጀመር፡፡

> ወላሂ አሁን በቀድም በረሃ ወርቅ ተገኘ ተብሎ ስለተወራ ለመቆፈር ከመሥሪያ ቤት ሳላስፈቅድ አንድ ሳምንት ቆይቼ ተመለስኩ፡፡ ባለማስፈቀዴ በጣም ስለፈራሁ ለታላቅ እህቴ ጭንቀቴን ስነግራት አይዞሽ ብላ (ቁራጭ ሥር የመሰለ ነገር ካሰረችው ሻሽ አውጥታ እያሳችን) ይሄንን ሰጠችኝ፡፡ ሻሼ ውስጥ አድርጌው ቢሮ ገባሁ እንኳን አለቃዬ ሊቆጣኝ የት ነበርሽ? ያለኝ ሰው አልነበረም፤ ሰዓት ፊርማውን ባዶ ስላገኘሁት ግጥም አድርጌ ፈርሜበት ወጣሁ … ይሄ የሚያገለግለው ሰው እንዳይናገርሽ፣ የጠየቅሽውን ሁሉ እሺ እንዲሉሽ ምናምን ነው (ወ/ሮ ቢተሚና አልቃሲም፣ ቃመ28/02/05)፡፡

ሌሊቱን ሲቲና ምንም ሳታቃስት አደረች፡፡ ተሻለሽ ሲቲዬ ስላት ወላሂ ተሽሎኛል ንቅንቅ ሳልል ነው የነጋው በጣም ገርሞኛል ብላኝ በቀጠሮኣችን መሠረት ወደ ኤሪው ቤት ለመሄድ መዘጋጀት ጀመርን፡፡ ቢተሚና መንገድ መሪያችን ስለነበረች ሦስት ሆነን ወደ ኤሪው ቤት ባጃጅ ተኮናትረን በባጃጁ መግባት እስከሚቻልበት ድረስ በባጃጅ ከዚያም

---

[39] ቢተሚና በወረዳው አስተዳደር ጽ/ ቤት የፅዳት ሠራተኛ ስትሆን፣ በገበያ ቀን ገበያ ውስጥ ባህላዊ ምግቦችንና ሻይ በመሸጥና እንደማገኛውም የበርታ ሴት ወርቅ በመቆፈር የምትተዳደር መረጃ አቀባዬ ነች፡፤

ለአንድ ሰዓት ያህል በእግር ተጉዘን ስንደርስ ሠፈራቸው በሰው ተሞልቷል። ታካሚውና ታማሚ ቤተሰቡንና ዘመዱን ይዞ የመጣው ሰው ብዛት በግምት ወደ ሃምሳ ይጠጋል። ቀስ በቀስም  ቁጥሩ እየጨመረ ሄደ።

ሰውየው የእኛን መድረስ እየጠበቁ ኖሮ ሥራ አልጀመሩም። እንደደረስን ወጥተው እየሳቁ ተቀበሉን፤ የጠፍር አልጋና የላስቲክ ምንጣፍ ለመቀመጫ ውጪ ተሰናዳልንና በእንግዳ አቀባበል ባህላቸው መሠረት የሚጠጣ የሎሚ ጭማቂና ሻይ፤ የሚበላ ገንፎ በቄንቄፅ ቀርቦልን ተስተናገድን።

በኔ ግምት ሰውየው እቤት ለብቻቸው በተለየ ቦታ ላይ ተቀምጠው፣ (ካስፈለገም ተጋርዶላቸው) እጣን ተጫጭሶ፣ ደም ፈሶ፣ በልዩ የአምልኮ ሥርዓት ሥራቸውን የሚጀምሩ መስሎኝ ነበር። ያ ሁሉ ነገር ሳይኖር ትናንት ሲቲና ቤት እንዳደረጉት አፋቸውን “ቢስሚላ” ብለው በውሃ በመጉመጥመጥ ሥራቸውን በግልፅ ውጪ ሁሉም ሰው እያያቸው ጀመሩ። በርታዎች በባህላዊ ሥርዓታቸውም ድብቅ ነገር አለማወቃቸውና ለኔሪው እንኳን የተለየ የክብር መቀመጫና ልዩ የፈውስ ሥፍራ አለመኖሩ በሁሉም ክዋኔዎች ተደጋግሞ መታየቱ አስገረመኝ።

ሰውየው ቀጥሎ በሽተኞች እንዲቀርቡ አዘዙ። ታካሚዎች አስር አስር ብር ሰውየው የቆሙበት አጠገብ መሬት ላይ እያስቀመጡ ቀረቡ። መጀመሪያ ላይ የቀረቡት ሁለት ወንዶች አንድ የተራበ ህፃን የሚመስል ልጅ የታቀፈች እናትና አንዲት ሌላ ሴት ናቸው ሴትየዋና አንዱ ወንድ ከወገባቸው በላይ ያለ ልብሳቸውን አውልቀዋል። ህፃኑን እናትየዋ ታቅፋው ቀረበች። ሙሉ ለሙሉ እራቁቱን ነው። ሌላኛው ሰው የታመመው እግሩን ስለሆነ ልብሱን አላወለቀም።



ፎቶ 21 ኔሪ በሪድ አሻጉድ

ኔሪው ትናንት ሲቲናን እንዳደረጉት አራቱንም ህመምተኞች የሚያማቸውን ቦታ በእጃቸው እየፈለጉና ባፋቸው እየመጠጡ ሥራሥሮቹን መምዘዝ ቀጠሉ። የተለያየ ህመም ካላቸው በሽተኞች ተመሳሳይ ነገር እየተመዘዘ ሲወጣ አንድ ነገር ጭንቅላቴ ውስጥ ብልጭ አለ። በርታ ኑሮው በጋራ፣ ሀብቱም የጋራ እንደሆነ ሁሉ በሽታውም የጋራና ተመሳሳይ ነው እንዴ? ብዬ በጠርጣሪ እኔነቴ አሰብኩ። በርታዎች ግን ይሄን ለመጠርጠር ባህላቸው አይፈቅድላቸውም። "ቢስምላ" እያሉ የሚሆነውን በአድናቆት ይመለከታሉ። የህክምናው አንድ መሆንና ከበሽተኞቹ በኔሪው አፍ እየተመዘዘ የሚወጣው

ሥራ ሥር ተመሳሳይነት እጅግ የሚያስገርም ነው:: ለነገሩ ሁሉ ነገራቸው የጋራ ከሆነ በሽታና ፈውሳቸውስ ለምን አንድ ዓይነትና የጋራ አይሆን? የሚል የዋህ ግን ብዙ የሚያመራምር መላምት በጭንቅላቴ እያጉላላሁ የባህላዊ እሴቱ ክዋኔ መደጋገምና መመሳሰል የሚሰጠውን ሥዕል እያሰላሰልኩ ቀረፃዬ ላይ አተኮርኩ::



ፎቶ 22. ኔሪ ቦሪድ የአቶ አሊተኣድን የታመመ እግር በአፋቸው በመምጠጥ በሽታውን ሲያስወግዱ

ሌላው አስገራሚ ነገር ኔሪው የሁሉንም በሽተኞች የታመመ አካል፣ የውስጥ እግራቸውን ሳይቀር ሳይጠየፉ ባፋቸው እየመጠጡ በሽታውን ለማውጣት የሚያደርጉት ጥረት ነው:: ለተመልካች ዓይን ከባድ ቢሆንም እሳቸው ግን ምንም ቅር ሳይላቸው ያደርጉታል:: ሲጨርሱ የታከሙትን እንዲለብሱ አዘው ተረኞች እንዲመጡ ያደርጋሉ:: ህክምናው

በተመሳሳይ መልኩ እስከ እኩለ ቀን ድረስ ተካሂዶ ተጠናቀቀ። በጣም የሚያስደንቅው ነገር ኔሪው ከየበሽተኞቹ ሰውነት የሚመዝዋቸውን ሥራ ሥሮች በአፋቸው ይዘው ነው እንዳልል ሲጀምሩ አፋቸውን በውሃ ተጉመጥምጠው ነው፤ ህክምናውን ሲያደርጉም እያወሩ ስለሆነ ያን ያህል ሥራሥር በጉንጫቸው ይዘው ድምፃቸው ሳይወላከፍ ጥርት ብሎ ሊሰማ አይችልም። ይህ ሁሉ ጥርጣሬ የእኔ እንጂ በርታዎች አምነዋቸው ይታከማሉ፤ እንደተፈወሱም ይናገራሉ።

ከታካሚዎቹ መካከል አራቱን በመምረጥ ስለበሽታቸውና ስለህክምናው ጠይቄቸው ነበር። ከሽርቆሌ ለመታከም የመጡት አቶ አልታሊድ ሙሰኡድ ኔሪው ጋ የመጡት እግራቸውን ታመው ነው። "… የሚያመኝ ወገቤን፣ እግሬን፣ ጉልበቴን ነው፤ ቀደም ሲል አሶሳ ድረስ ሄጄ ብታከምም ጭራሽ እየባሰ እየሸመቀቀኝ ተቸገርኩ ቆይቶም አላንቀሳቅስ ብሎ አልጋ ላይ አስቀረኝ እንጂ መዳን አልቻልኩም። ሲጨንቀኝ እዚህ መጣሁ፤ እሱም ይኸው እንዳየሽው ከሰውነቴ ውስጥ በሽታውን እየመዘዘ ሲያወጣልኝ ተሻለኝ፤ እሱ ዘንድ መምጣት ከጀመርኩ ዛሬ ሦስተኛ ቀኔ ነው በጣም ተሽሎኛል" (አቶ አልታሊድ ሙሰኡድ ፣ቃመ29/0205)። በማለት የኔሪውን ፈዋሽነት አስረዱኝ።



ፎቶ 23 ኔሪው ከህመምተኛው እግር ውስጥ በአፋቸው መጠው ያወጡትን በሽታ/ ሥር መሰል እንጨት ኢያሳዩ

ወ/ሮ ኒመት ተማም ደግሞ የመጣችው ልጇን ልታሳክም ነው፤ ልጁ በጣም የታመመ መሆኑ በክሳቱ ያስታውቃል፡፡ ረሀብ የያዘው እንጂ በሽታ ብቻ እንዲህ ያደረገው አይመስልም፡፡ ዕድሜው ሁለት ዓመት ሊሞላው ነው፡፡ እናትየዋ ስለህመሙ ስትናገር፡-

> … ምግብ ይበላል ጡትም በሚገባ አጠባዋለሁ ግን እንደምታዩት ሰውነቱ መንምኗል፤ ትኩሳት አለው እንጂ ተቅማጥና ተውከት አያውቀውም፡፡ ጤና ጣቢያ አሳየሁት፤ መድሃኒት ሰጡት ግን አልተሻለውም፡፡ ይሄ ሁለተኛ ልጄ ነው፡፡ የመጀመሪያውንም እንደዚሁ እያመመብኝ እዚህ አምጥቼው ድኖልኛል፡፡ ግን ለኤሪው እሰጥሃለሁ ብዬ ቃል የገባሁትን ለመክፈል እጅ ስላጠረኝ እስከዛሬ ሳልከፍለው ቆየሁ፡፡ አሁን ይህኛውም እንደሱው ታመመብኝ፡፡ ጤና ኤክስቴንሽኖች አይተውት እንዳሳክመው ነግረውኝ ወሰድኩት አልዳነም፡፡ አሁን ለዛኛው ቃል የገባሁትንም ገንዘብ ይዤ ይህኛውንም እንዲያድንልኝ ነው የመጣሁት፤ ያኛው ስለዳነልኝ ይሽኛውም ይድንለኛል (ወ/ሮ ኒመት ተማም፣ ቃመ29/02/05)፡፡



ፎጾ 24 ወ/ሮ ኒመትና ታማሚ ልጇ/ ከጀርባ የህክምና ወረፋ የሚጠብቁ ሰዎች በጥቂቱ

እንደ ወ/ሮ ኒመት ዕምነት ልጇን ጤና ጣቢያ ወስዳው ፈውስ ስላላየች የሚድነው በኤሪው ህክምና እንጂ በዘመናዊ ህክምና አይደለም፡፡ የታመመባትም ቃሏን በማፍረሷ እንጂ በሌላ ምክንያት አይደለም፡፡ ስለዚህ ከዘመናዊው ህክምና ይልቅ በኤሪው ፈውስ ተማምና ነው ልጇን ይዛ የመጣቻው፡፡ ባለቤቷም ይህንኑ ያምናል የመጀመሪያው ልጁ ታሞ ከዳነ በኋላ ለኤሪው ቃል የገቡትን ሳይሰጡ ካካባቢው ርቆ ሄዶ ስለነበር የኤሪው መንፈስ ቃላቸውን ባለመጠበቃቸው ተቆጥቶ ይኸኛውን ልጅ በሽተኛ አደረገብን ባይ ነው፡፡ ዛሬ የመጡትም ይቅርታ ለመጠየቅና ለልጃቸው ፈውስ ፍለጋ ነው፡፡

አቶ አልመሃዲ ናስር ሌላው የኤሪውን ፈውስ ፈልገው የመጡ ናቸው፡፡ በሽታቸው ወገባቸውንና ጀርባቸውን ነው፡፡ መንቀሳቀስ እያቃታቸው አልጋ ላይ ለመዋል እስኪገደዱ ድረስ ታመው ነበር፡፡ ህክምናም ሞክረዋል፤ ገንዘብ ከመከስከስ ውጪ ምንም ስላልፈየደላቸው ወደ ኤሪው መጥተው ለመታከም ወስነው መጡ፡፡ ሁለት ቀናት እየተመላለሱ ህክምናውን እንደወሰዱ ጤናቸው ተሻሽሎ ራሳቸውን ችለው መራመድ እንደጀመሩ በፈገግታ ታጅበው ይገልፃሉ (ቃመ29/02/05)፡፡



ፎቶ 25. ኤሪው የህፃኑን ሰውነት በአፋቸው እየመጠጡ በሽታውን ሲያስወግዱና ወ/ሮ አሻም ለህክምናው ራሳቸውን አዘጋጅተው ቆመው እየጠበቁ

ወ/ሮ አሻ ረመዳን እንዲሁ እያመማቸው ብዙ ጊዜ የባህል መድሃኒቱንም ህክምናውንም ሲሞካክሩ ቆይተዋል። ግን ምንም የመሻል ምልክት አላዩም። እሳቸው እንደሚሉት የሚያማቸው የሡራ አካላታቸውን ነው፤ እንደ እሳት እያቃጠለ ያሰቃያቸዋል። ልባቸው ይደክማል። ዓይናቸውንም ይከልላቸዋል። ጤና ጣቢያ ሄደው የሰጧቸው መድሃኒት አላሻላቸውም። አሁን ኤሪው ጋ ያሸለኛል ብለው እንደመጡ ይናገራሉ (ቃመ29/02/05)።

አራቱም ሰዎች እንዲሚናገሩት ገንዘባቸውን፣ ጉልበታቸውንና ጊዜያቸውን ከመጨረስ ውጪ ዘመናዊ ህክምና ላለባቸው የጤና ችግር መፍትሔ አላመጣላቸውም። ስለሆነም በኤሪው ህክምና ላይ ተማምነው ፈውስ ፍለጋ መጥተዋል።

የክልሉ መንግሥት ይሄ አመለካከት በሁሉም ህብረተሰብ ዘንድ የተስፋፋ መሆኑን አይቶ በአፅንዖት የሚያነሳው ተግዳሮት ከላይ በተጠቀሰው ዕቅድ ውስጥ የሚገኘው "በሽታን በዘመናዊ መንገድ በመከላከልና በዘመናዊ ህክምና መፈወስን ሳይሆን <u>በሁሉም ህብረተሰብ በባህላዊ ህክምናና በጥንቆላ የማመን ከፍተኛ የሆነ ችግር አለ</u>።" (አፅንዖቱ የኔ ነው) የተባለው ነው። ማህበረሰቡ ደግሞ ከዘመናዊው ይልቅ ባህላዊው ፈውስ ውጤታማ ነው ይላል። ይሄ እንደ ችግር የቀረበ ጉዳይ በእርግጥ ችግር ነውን? ማህበረሰቡ በባህላዊ ህክምና ታክሞ አይድንምን? ለባህላዊ መድሃኒቱና ለአዋቂዎቹ የሚሰጠው ቦታ ምን ይሆን? የሚሉት ጥያቄዎች ሲነሱ የአስተሳሰብ ተቃርኖው በጉልህ የሚታይ ይሆናል።

ማህበረሰቡ እስከ ዛሬ ድረስ ኤሪው ቦሪድ አሻጉድና የባህል መድሃኒት አዋቂውን አባ ቤሎን[40] የመሰሉ ባህላዊ ሃኪሞች የሚሰጡትን መድሃኒቶች እየተጠቀመና እየተፈወሰ ኖሯል። አሁንም በእነሱው እየታከመ ነው። ከዘመናዊው ህክምና ይልቅም እነሱን እንደሚመርጥ የሚያሳየው በገጠር ጤና ተቋማት የማይታየው የሰው ብዛት በኤሪው ግቢ ጨረቃ መስሎ ወረፋ እየጠበቀ ሲታይ ነው።

[40] እኚህ ሰው ኤሪ ሳይሆኑ የባህል መድሃኒት ቀምመው የሚሡጡ አዋቂ ናቸው። ህክምናቸው ከኤሪው ፈፅሞ የተለየ ነው።

አባ ቤሎ የባህል መድሃኒት አዋቂ ናቸው፡፡ እሳቸው እንደሚሉት በባህላዊ መድሃኒታቸው ቲቢንና ወባን ጨምሮ አሉ የተባሉትን በሽታዎች ይፈውሳሉ፡፡ ፈውሳቸው ደግሞ በጤና ባለሙያዎች በተደረገ ምርመራ ሳይቀር እየተረጋገጠ ነው፡፡ እሳቸውና መሰሎቻቸው በሚሰጡት መድሃኒት አብዶ የሚዞር ሰው ድኖ ቤተሰብ መሥርቶ ሲኖር በዓይናቸው አይተዋል፡፡ ለማስረጃነት  የሚከተለውን መመልከት ጠቃሚ ነው፡፡

….ከዚያም ሰው ሲታመም በህልም ይታየኛል፤ ህልም አያለሁ በቃ ያንን ሄጄ እቆፍራለሁ፡፡ ያንን ቆፍሬ አምጥቼ እሰጣለሁ ሰዎች ይፈወሳሉ፡፡ አሁን ቲቢ ታመው የነበሩ አሥራ ሁለት ሰዎች አሉ መድሃኒቱን ወስደው ተመርምረው ነፃ የተባሉ፡፡ ጤነኛ መሆናቸውን ያረጋገጡ፤ ግን እኔ ህልም አይቼ ነው እምሠራው፡፡ ስለዚህ አሁን የእኔ አጎት አለ አሁን የአስተዳዳሪው አባት ማለት ነው፡፡ እሱ እንደዚህ ልፍስፍስ ብሎ ከእግሩ በታች ከሥራ ውጩ ከሆነ በኂላ መድሃኒት ሰጠሁ፤ ተመላልሼ አከምኩ፤ ያው እሚቀባ፣ እሚጠጣ እሰጣለሁ፤ እሚታጠን እሰጣለሁ፤ ተሽሎት ቆሞ እየሄደ ነው ብዙ ሰዎች በዚህ መልክ እየዳኑ ነው ያሉት፤ ያው በአላህ ሀይል ህልም ይታየኛል፤ ሄጄ አመጣለሁ የኔ ሰው ተፈውሶ አያለሁ፡፡

ያው እኔ እንደዚህ በመሥራቴ ያበደ ሰው አሁን መድሃኒት ተደርጎበት ነው፣ አብሾ ጠጥቶ ነው ይባላል፤ እንደዚህ ዓይነት ነገሮች እኔ መድሃኒት እሰጣለሁ፤ ያ ሰውዬ ይሻለዋል፤ አሁን እንደዚህ አሥራ ሦስት ልጅ የወለደ አለ፤ ድሮ አብዶ ልብሱን ጥሎ መልሰን በዚያ ሰበብ ያ ሰውዬ ድኖ ተዋልዶ ምን ብሎ ያቺ ትናንትና ያየሻት ልጅ ከእነሱ ነው የተሰጠኝ፡፡ ትልቅ ሰው ነው ይሄ ምንም ክፉ የለውም ምንም ችግር የለውም ብለው በስጦታ ነው የተሰጠችኝ ያቺ ሚስቴ

> ትንሽዋ ውሃ ያቀረበችልሽ አጎቷ ነበር እንደዚያ ሆኖ የነበረው ያው ተመላልሼ አከምኩኝ ያ ሰውዬ ዳነ ሥራ ላይ ነው (አባ ቤሎ፣ ቃመ02/03/05)።

ከአባ ቤሎ አባባል የምንረዳው ዘመናዊ ህክምና ያላዳነውን በሽታ ሁሉ እሳቸው እንደሚፈውሱ ነው። ማህበረሰቡም ያንን ስላመነና አይቶም ስላረጋገጠ ወደ ጤና ተቋማት ከመሄድ ይልቅ እሳቸው ዘንድ መታከምን ይመርጣል። የአዕምሮ ጤና ችግር ገጥሞት በእሳቸው ህክምና የተፈወሰው ሰው ለሚስትነት ሰጠኝ ያሏት ልጅ ከእሳቸው በዕድሜ እጅግ የምታንስና ልጃቸው የምትሆን ናት። ይህ የሚያሳየው ደግሞ በአባ ቤሎ ህክምና ላይ ያላቸውን ዕምነትና ለሥራቸው ዋጋ የሰጡትን ግምት ነው።

ከዚህ በተጨማሪ አባ ቤሎ ለሚያደርጉት ህክምና በቅድሚያ የሚያስከፍሉትን ገንዘብ በሽተኛው ሳይድን አይጠቀሙበትም። በሽተኛው ዳነም አልዳነም በቅድሚያ የተሰጣቸውን ገንዘብ ከቀሪው መድሃኒት ጋር ያስቀምጡና በሽተኛው መዳኑ ሲረጋገጥና መጥቶ "ድኛለሁ" ሲላቸው ይጠቀሙበታል። አለዚያስ? የሚሆነውን እንመልከት።

> …መጀመሪያ እኔ በሽተኛው ለመታከሚያ የሰጠውን ብር ከዚያ ሰውዬ እወስዳለሁ፤ ከዚያ መድሃኒቱን ለማምጣት ወደ ዱር እሄዳለሁ ልክ መድሃኒቱን ሳይ በቅጠል በምናምን ይታወቃል፤ እዚያ ሄጄ ቁጭ አረጋለሁ ያንን ብር፤ እቆፍራለሁ ቆፍሬ ከብሩ ጋር አምጥቼ ለመንሱር ነው እምሰጠው። እሱ ብቻ ነው የሚያውቀው ሌላ የሚያውቅ ሰው የለም።

> በሽተኛው ተመልሶ ይመጣል እዚያው ቀምሜ እሰጣለሁ ይዞ ይሄዳል፣ ይታከማል የሚጠጣ፣ ወይ የሚቀባ፣ እሚታጠን፣ እሰጠዋለሁ ወስዶ ሄዶ ታክሞ ሲሻለው የሚያሰበውን፣ የሚመኘውን፣ የሚፈልገውን፣ ነገር ጨምሮ ይሰጠኛል። በቃ  መድሃኒት ብዙ ጊዜ አሁን ሰውየው ላይሻለው ይችላል፤ አክሜዋለሁ አልተሻለውም፤ ግን ምንድነው አብዛኛው ሰው እንግዲህ ከራሱ ፍላጎት በቃ እኔ አልተሻለኝም ሌላ ቦታ ሄጄ አፈላልጋለሁ ግን የሰጠሁህን ብር ትቼልሃለሁ ብሎ ካለ ይቀራል፤ ስጠኝ ገንዘቤን እኔ አልተሻለኝም ካለ ይመለሳል። አይ እኔ አልተሻለኝም አንተ ግን የምትችለውን አድርገሃል ለፍተሃል ከእኔ ጋራ እኔ ይቅር ብያለሁ ካለኝ ነው እማስቀረው አለዚያ እመልሳለሁ። (አባ ቤሎ፣ቃመ20/03/05)

አባ ቤሎ ዘንድ የሚሄድ በሽተኛ ለህክምና የሚከፍለው ገንዘብ ካልተሻለው ይመለስለታል። በመንግስት ጤና ተቋማት ለህክምና የከፈለውን ገንዘብና መድሃኒት የገዛበትን ብር ባይሻለው የሚመልስለት ሰው የለም። ይህ በመሆኑም ከዘመናዊው ህክምና ይልቅ ባህላዊውን ህክምና ተማምኖ ወደዚያው መሄድን ይመርጣል። ከላይ እንደታየው በበርታ ባህል መዋሸት ሃራም በመሆኑም ብሩን ለማስመለስ ብሎ አልተሻለኝም የሚል ሰው አይኖርም። እንዳጋጣሚ ለማጭበርበር የሚፈልግ ሰው ካጋጠመ ግን ምን እንደሚሆን አባ ቤሎ እንዲህ በማለት ያስረዳሉ።

> ለምሳሌ ሰውየው ሄጄ ያንን መድሃኒት ቆፍሬ አምጥቼ ሰጠሁት ታከመ፤  ድኗል፤ ግን አልዳንኩም አለ፤ አልዳንኩም በቃ ብሬን መልስልኝ አለ። አሁን ያ መድሃኒት ከዚያ ቦታ ወይ ይበሰብሳል፤ወይ ደሞ ይጠፋል፤ ምክንያቱም ያ ሰውዬ አደራውን በልቷል። እኔም ቅር

> ብሎኛል ውስጤ ያውቃል  እሱንም አላህ አይቶታል ስለዚህ ያ መድሃኒት አይገኝም፡፡ ለሌላ ሰውም አይሆንም፡፡ አንደኛ መድሃኒቱ በውሸት አይሠራም፤ ዋሽቶ እንደዚህ አድርጌ፣ እንደዚህ አድርጌ ብዬ ብሰጥሽ ሳትጠቀሚበት ይጠፋል፡፡ ሁለተኛ ገበያ ላይ እንደዚህ እንደዚህ ተዘርግቶ አይሸጥም፡፡ በቃ ለሚፈልገው ሰው እዚህ ውስጥ ካለ ከዚህ እሰጠዋለሁ፤ ሄዶ ይጠቀማል፡፡ እቤቴም ቢሆን መድሃኒቱን በዚች ብቻ ነው እማስቀምጠው፡፡ ከዚያ ያለፈ ለዚያ ለበሽተኛው ነው እማደርሰው ተጠቅሞበት ከተሻለው ጥሩ አልተሻለኝም ካለ አልተሻለኝም ነው፡፡ ቢዋሽ… በቃ መድሃኒቱ ብቻ ነው እሚጠፋ እንጂ ሰውየው ምንም አይሆን፡፡ ይሄ መድሃኒት ግን አብሮ ይዞራል፤ በመድሃኒቱ ድኖ ጤነኛ ሆኖ ይኖራል አይደለም ዞሮ ሌላ ጊዜ ወይ ሌላ ዓመት ወይ ሌላ ጊዜ መልሶ ያ በሽታ ይመለሳል ድንገት ይታመማል ያኔ ዞሮ ይመጣል እራሱ አይቀርም፡፡ መታመሙ አይቀርም፡፡ ወይ ቲቢ ሊሆን ይችላል ወይ ነቀርሳ ሊሆን ይችላል ሌላ ነገር ሊሆን ይችላል ያ በሽታ መልሶ እንደሚያመውና መልሶ እንደሚጠይቅ አይቀርም፡፡… (አባ ቤሎ፣ቃመ20/03/05)

በሽተኛው ቀድሞ የከፈለውን ብር ለማስመለስ ብሎ ድኖ ሳለ አልተሻለኝም ቢል አባ ቤሎ የደከምኩበት ነው ብለው ብሩን አይወስዱም፡፡ ሳትቀየር እንዳለች ብሯን ይመልሱና በሰላም ያሰናብቱታል፡፡ እሱም ለጊዜው በጤንነት ይኖራል፡፡ ዞሮ ግን እጃቸው ላይ ይወድቃል፡፡ ለነገሩ ታካሚው በርታ ከሆነ ከመነሻውም አይዋሽም፡፡ ከዋሸም እራሱን እንጂ ማንንም አይጎዳም፡፡ በሽታው ተመልሶ በመምጣት አባ ቤሎ እጅ ላይ ይጥለዋል፡፡ በታካሚው ውሸት አባ ቤሎ ብቻ ሳይሆኑ ተፈጥሮም ስለምትቀየም መድሃኒቱ ይደርቃል፡፡ ተቆርጦ የተቀመጠውም ለሌላ በሽተኛ ቢሰጥ አይፈውስም፡፡ ይህ የሚያመለክተው ደግሞ ማህበረሰቡ በእያንዳንዷ ሁነት እርስ በርሱ ተማምኖ እንዲኖር

ያደረገውን የባህሉን ጥንካሬ ነው፡፡ ስለዚህ በቅንንት፣ በታማኝነትና በሃቅ የሚያገለግሉት አባ ቤሎ እያሉ ብዙ ወጪና እንግልት የሚያስከትለውን ህክምና የሚመርጥ ሰው የለም፡፡

ይህንን የብሔረሰቡን የጠነከረ ባህልና ዕምነት ታዲያ "ኋላ ቀር አመለካከትና ችግር" በማለት ብቻ ከዕምነቱ ለማላቀቅና ወደሚፈለገው ግብ ለመድረስ የሚቻል አይደለም፡፡ መፍትሔውም "በአመለካከት ትግልና በኮንፍረንስ" ብቻ የሚመጣም አይመስልም፡፡ ይልቁንም የብሔረሰቡ ማንነት ለተገነባበት ባህል፣ ሀገር በቀል ዕውቀትና ልማድ፣ ተገቢውን ትኩረት ሰጥቶ ማጥናትንና ራሱን መሠረት አድርጎ የአካባቢውን ልማት ለማምጣት ተግቶ መሥራትን ይጠይቃል፡፡

ልክ እንደ አባ ቤሎ ሁሉ የኔሪ ቦሪድን ፈውስ ፈልገው የሚሄዱት ሰዎች ለሚሰጣቸው አገልግሎት የሚከፍሉት ገንዘብ ጥቂት ነው፡፡ እዚያ በተገኘሁበት ወቅት ታካሚዎቹ በህክምናው ሥፍራ ያስቀመጡት ገንዘብ በአብዛኛው አሥር ብር ሲሆን ከሁለት እስከ አምስት ብር የሚደርስም ገንዘብ ጥቂት ሰዎች ሲያስቀምጡ አይቻለሁ፡፡ ኔሪው ግን አነሰ ጨምሩ ሲሉ አልሰማሁም እንደውም ገንዘቡ በእጃቸው የሚከፈል ሳይሆን እሚሰሩበት ቦታ ነፋስ እንዳይወስደው ጠጠር ተጭኖበት የሚጠራቀም ስለሆነ ኔሪው የማ የማ እንደሆነ እንኳን ልብ ብለው ስለማያዩት አያውቁትም፡፡ ስለዚህ ታካሚዎቹ ፈውሱን ለማግኘት የሚያወጡት ወጪ አነስተኛ በመሆኑ ከዘመናዊው ህክምና የሚመርጡበት አንዱ ምክንያት እንደሆነ መረጃ ሰጪዎቹ ይናገራሉ፡፡ “ጤና ጣቢያ ብንሄድ ወረፋው፣ መንገላታቱ፣ የሚያዙልንን መድሃኒት ለመግዛት ገንዘቡም ችግር ነው፤ የመድሃኒቱ ዋጋ ብዙ ስለሚሆን እዛ ሄዶ ከመንገላታት እዚህ በቀላሉ እንድናለን እሱም አብረን ስለምንኖር ብዙ አያስከፍለንም፤ ከሌለንም በነፃ ያክመናል” (ወ/ሮ ኒመትና ሌሎቹ፣ቃመ29/02/05)፡፡

የታካሚዎቹ ሀሳብ የዘመናዊ ህክምናው ውድነት እና የአገልግሎቱም ተደራሽ አለመሆን ወደ ጤና ጣቢያ ለመሄድ ፍላጎት እንደሌላቸው የሚያመለክት ነው፡፡ ማህበረሰቡ ጤና ጣቢያዎቹ በአቅራቢያው ቢኖሩም ተመርምሮ የሚታዘዝለትን መድሃኒት መግዣ ከሌለው ወደዚያ ከመሄድ ይልቅ ወደ ባህላዊ ልምምዱ ፊቱን ያዞራል፡፡ ይሄን ሳንረዳ ግን

በጥንቆላና በባህል ህክምና የማመን ችግር ነው ብለን ባለመድሃኒቶቹን ለማስጣል ብንሞክር ባደባባይ ማድረጉን ትቶ በድብቅ ይከውነዋል እንጂ ፈፅሞ ለውጥ ማምጣት አይቻልም:: የጤና አገልግሎት የሚሠጡትም ተቋማት ካለ ውጤት ተገንብተው ይህን ያህል ገንብተናል ለማለት ብቻ የሚያበቁ የሪፖርት ፍሬዎች ብቻ እንጂ የሚታሰበውን ጤናማ ማህበረሰብ ከመገንባት አኳያ የሚኖራቸው ፋይዳ ከቁጥር የሚገባ አይሆንም::

Cumming እንደሚሉት የ3ኛው ዓለም ድህነት ኢኮኖሚውን በማዘመን ብቻ ሊቀረፍ የሚችል የታሪካዊ ኋላ ቀርነት ውጤት ሳይሆን ይልቁንም "ምዕራቡ በደቡቡ" ላይ የፈጠረው ዘዴያማ የቅኝ ግዛት ውጤት ነው፤ ለልማት ስትራቴጂዎችና ፕሮጀክቶች አለመሳካት በዋና ምክንያትነት የሚነሱት ማህበረ ኢኮኖሚያዊ ወይም ፖለቲካዊ ጉዳዮች ሳይሆኑ በእያንዳንዱ ማህበረሰብ ውስጥ ያለው የባህል ልዩነትና ከዚህ አንፃር ማህበረሰቡ የሚኖረው ፍላጎት ነው (Cumming, 1990):: ይህን የ Cummingን ዓለማቀፋዊ እሳቤ ወደ ተነሳንበት ጉዳይ ብናመጣው የክልሉ መንግሥት የሚያነሳው "በሽታን በዘመናዊ መንገድ በመከላከልና በዘመናዊ ህክምና መፈወስን ሳይሆን <u>በሁሉም ህብረተሰብ</u> <u>በባህላዊ ህክምናና በጥንቆላ የማመን ከፍተኛ የሆነ ችግር አለ</u>::" (አፅንዖቱ የኔ ነው) ከሚለው ሃሳብ ጋር በቀጥታ የሚዛመድ ነው:: የማህበረሰቡ ጤና እንክብካቤ ሁሉን በአንዴው በማዘመን የሚፈታ ነገር አይደለም:: ይልቁን በአካባቢው ያሉትን ባህላዊ እሴቶችና በዚያም ላይ የሚመሠረተውን የማህበረሰቡን ፍላጎትና ዕምነት አጢኖና ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ ፈትሾ ማቀድ የተሻለ ይሆናል::

### 8.2.2. የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎትና ተግዳሮቶቹ

ባህል የማህበረሰቡ መሠረት የሆነው ቤተሰብ እንዲመሰረት፣ ትውልድ እንዲቀጥልና እንዲሰፋ ዋነኛ ጉዳይ የሆኑት ልጆች እንዲወለዱ የሚያደርገው እገዛ ብዙ ነው:: አንዳንዱ ባህል ልጆችን የሚያያቸው የቤተሰቡ በረከት አድርጎ በመሆኑ ልጆች ሲረገዙ የተለየ ደስታ ይሆናል:: ለእናታቸውም ሆነ ለህፃናቱ የተለየ እንክብካቤ ያደርጋል:: እናታቸው

በእርግዝናዋ እንዳትጎዳ ጤናዋ እንዳይታወክ ባህሉ የሚፈቅድላትን የመከላከያ ዘዴ ትጠቀማለች። በአራስነቷ ልዩ እንክብካቤ ይደረግላታል፤ እሷም ሆነች ልጇ ምናምን እንዳይተናኮላቸው ጥንቃቄ ይደረግላቸዋል። ለመታረስ የምትቆይበት ጊዜ፣ ከአራስ ቤት ወጥታ ለሥራ የምትሠማራበት ወቅት ሁሉ በበርታ ባህል ልዩ ልዩ እንክብካቤዎች እንደሚደረግላት ከላይ ባሉት ክፍሎች በስፋት ተገልጧል።

በተጨማሪም በበርታ ብሔረሰብ ልጆች ትውልድ እንዲቀጥል ዘር እንዲበዛ የሚያደርጉ በመሆናቸው በዝተው እንዲወለዱ ባህሉ ያበረታታል። ልጅ ሲወለድ ሥራ ያግዛል፤ ሲታመሙ ያስታምማል፤ ሲያረጁ ይጦራል፤ ሲሞቱ በክብር ይሸኛል። በመሆኑም ባህሉ ልጆችንና ወላጆችን በሚገባ ይንከባከባል። በተጨማሪም የሚስት ዋነኛ ተግባር ብዙ በመውለድ ቤቱን በልጆች መሙላት ነው ተብሎ በባህሉ ይታመናል።

የማህበረሰቡ ባህል እንዲህ ሆኖ ሳለ ወደ 16 ከሚደርሱት የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጆች ውስጥ አንዱ የሆነው የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ፓኬጅ የቤተሰብ ምጣኔን ያስተምራል። የፓኬጁ አጠቃላይ ዓላማ ማንኛውም ቤተሰብ ከገቢውና ከማስተዳደር አቅሙ በመነሳት ልጆችን መጥኖና አራርቆ እንዲወልድ የሚያደርግ ነው። ለተግባራዊነቱም መንግስት በገጠር የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎችን በማሰማራትና ኅብረተሰቡን በማስተማር ለቤተሰብ ምጣኔ የሚረዱ የወሊድ መከላከያ ዘዴዎችን በማደል መጥነው እና አራርቀው እንዲወልዱ የማድረግ ተግባር እያከናወነ ይገኛል። ይህ ተልዕኮ በአንዳንድ የሀገሪቱ ክልሎች መጠነኛ ተቀባይነት ቢያገኝም የቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ግን ተግዳሮት እንደገጠመው ከላይ ከተመለከትነው የአምስት ዓመት የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መረዳት ይቻላል።

በበርታ ባህል ወንድ የማስተዳድር አቅም ካለው ከአንድ በላይ ሚስት ማግባት ይችላል። እነዚህ ሚስቶች ከእያንዳንዳቸው የሚወለዱ ልጆች ደግሞ የቤተሰብ ቁጥሩን በእጅጉ ያንሩታል። እነሱ አድገው እንደዛው ሁለትና ሦስት አግብተው ሲወልዱ የህዝብ ብዛቱ እየጨመረ ይሄዳል። ከዚህ የተነሳ አንዳንድ አባቶች የልጆቻቸውን ቁጥር እንኳን በትክክል

መናገር ሲያዳግታቸው በመረጃ ስብሰባው ወቅት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ለምሳሌ ከላይ ያየናቸው ኄሪ ቦሪድ አሻጉድ ከአራት ሚስቶቻቸው 40 ልጆች እንደወለዱ፣ አሁን በህይወት 12 እንዳሉ እና አምስቱ ልጆቻቸው ደግሞ 30 እንደወለዱ ይናገራሉ፡፡ አባ አቶም ሙስጦፋ 19 ልጆች ወልደዋል፤ አሁን 13 አሏቸው 20ኛው ልጅ ደግሞ ተረግዟል፡፡ አብዛኛው የበርታ ቤተሰብ እንደዚህ ሰፊ ነው፡፡ ኑሮው በጋራ በመሆኑ ልጆችም ተወልደው በጋራ ያድጋሉ፣ ሲያድጉ ቤተሰብ ይረዳሉ፣ ሥም ያስጠራሉ፣ በሥራ ያግዛሉ፤ ሲታመሙ ያስታምማሉ... ስለዚህ ይወለዱ እንጂ ስላስተዳደጋቸው ብዙም የሚያስጨንቅ አይደለም፡፡

ከዚህ የተነሳ እናቶች የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ባሎች እንደሚከለክሉ መረጃ ሰጪዎች ያስረዳሉ፡፡ “የአንቺ ሚስትነት የሚረጋገጠው ስትወልጂ ብቻ ስለሆነ ሁሌ መውለድ አለብሽ ይሉናል፤ ካልወለድን ባል እንደሌለን እንቆጠራለን፤ ስለዚህ ደጋግመን እንወልዳለን፤ ደሞ ልጅ አላህ የሚሰጠውና የሚያሳድገውም የፈጠረው አምላኩ ስለሆነ እንደልባችን ብንወልድ ምንም ችግር የለውም፤ ልጅ ሀብት ነው” (ቡውይመቃሴብቻ፣18/02/05)፡፡

ከላይ ባየናቸው ትልልቅ ባህላዊ ጉዳዮች ምክንያት የቤተሰብ ምጣኔ፣ አራርቆ መውለድ የሚባሉ ጉዳዮች በብሔረሰቡ ዘንድ ሰሚ ያገኙ አይመስሉም፡፡ የክልሉ መንግስት "ከኋላ ቀር አስተሳሰብ ጋር የተያያዘ የአመለካከት ችግር ነው፡፡" ይበል እንጂ መሠረቱን ስናየው ባህላዊ ተግዳሮት በመሆኑ የሚፈታው ባህሉን ጠንቅቆ በማወቅና በዚያ ላይ ጠንክሮ በመሥራት እንደሆነ ከመስክ የተገኙት መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ "... ከፍተኛ የግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ፣ የአመለካከት ትግልና በምንፈጥራቸው ሞዴሎች አማካይነት ሙሉ ለሙሉ እናስወግዳለን፡፡" ተብሎ የቀረበው የመፍትሔ ሃሳብ ብዙም የሚያስኬድ አይመስልም፡፡

የበርታ ወንድ ከአንድ በላይ ሚስት እያገባ በርካታ ልጆችን ያፈራል፡፡ መንሱር ሁለት ሚስቶች አሉት፣ ከሁለቱ ሰባት ልጆችን አፍርቷል፡፡ አሁን ደሞ ሌላ ሚስት ሊያገባ ሽማግሌ ልኳል፡፡ "እኔም እንደ አባቴና እንደ አጎቶቼ ብዙ ልጆች እንዲኖሩኝ እፈልጋለሁ ልጅ አትውለዱ ማለት ሀራም ነው…ልጅ እኮ የሚሰጥ አላህ ነው የአላህን ስጦታ አልፈልግም ይባላል እንዴ.." (መንሱር ቤሎ፣ ቃመ02/03/05) መንሱር እንደሚለውና ከላይ በብዙ ማሳያ እንደተመለከተው የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጆቹን ለማስተግበር ከፍተኛ ችግር የገጠመው ቢሆንም በአብራሙ እና ቆሽመንገል ቀበሌ የሚገኙት የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ግን እነሱ በሚሠሩባቸው ቀበሌዎች ያሉት አርሶ አደሮች ፓኬጆቹን በሙሉ ተግባር ላይ እንዳዋሉ ይናገራሉ፡፡



ፎቶ26 የበርታ ህፃናት /ከሸፍ ቀበሌ/

"በእኛ ቀበሌ የጤና ፓኬጁን የመቀበልና የመተግበር ችግር የለም። አሥራ ስድስቱንም ፓኬጆች ተቀብለው በመተግበር ተመርቀዋል…" (ወ/ሮ አስረሳሽ ዳኜ፣ ቃመ20/04/05) ይላሉ። ይሁንና መሬት ላይ ያለው ዕውነት የሚያሳየው ግን በስብሰባና በስልጠና ላይ ፓኬጆቹን የተቀበሉ ቢመስልም ትግበራው ላይ ገና ብዙ የሚቀር ነገር መኖሩን ነው።

ወ/ሮ አስረሳሽ እና ወ/ሮ ማሪያ ሀሰን[41] እንደሚሉት የቤተሰብ ምጣኔ በአንዳንድ በመንደር ማሰባሰብ በታቀፉ በአቡራሙና ቆሸመንገል ቀበሌዎች ያሉ እናቶች ሙሉ ለሙሉ የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች ሆነዋል ቢባልም ሌላ ከግንዛቤ ያልገባ ባህላዊ ሁኔታ አለ። የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቱ ተግባር ላይ በመዋሉ አንድ ሴት ቀድሞ በአማካይ ከምትወልደው ከዘጠኝ እስከ አስር ከሚደርሱ ልጆች አሁን አገልግሎቱን በመውሰዷ በአማካይ አራት ልጆችን ብቻ ትወልዳለች። ይሄ ጥሩ ሆኖ ችግሩ የሚመጣው ከላይ እንደተጠቀሰው አንድ ወንድ እስከ አራት የሚደርሱ ሚስቶች ስለሚኖሩት ባሉት ሚስቶች ልክ የሚኖረው የቤተሰብ ብዛት ሲሰላ ነው።

አንድ የበርታ ወንድ ከአራት ሚስቶቹ አራት አራት ቢወልድ አሥራ ስድስት ልጅ ይኖረዋል፤ እሱና አራት ሚስቶቹ ሲደመሩ የቤተሰቡ ብዛት ወደ ሃያ አንድ ይደርሳል። ይህ አሃዝ በጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎቹ ሳይቀር ከግምት ውስጥ ያልገባ የቤተሰብ ምጣኔው ስኬት ፈተና ነው። ባለሙያዎቹ ትኩረት ያደረጉት ቀድሞ አንዲት ሴት በአማካይ የምትወልደውን የልጆች ቁጥር በመቀነስ ላይ ነው እንጂ አንድ አባወራ በሚኖረው የቤተሰብ ብዛት ላይ አይደለም። ከዚህ በተጨማሪም በሚስቶች መካከል በሚደረግ የልጅ ቁጥር መጨመር ፉክክርም ቤተሰቡ እየናረ ይሄዳል። "… ከአንድ በላይ ሚስት ያላቸው አባዎራዎች ሚስቶቻቸው የቤተሰብ ምጣኔ ተጠቃሚ ቢሆኑም አንዷ ሴት አዲስ ልጅ ስትወልድ ፉክክር ውስጥ ይገቡና እኔም አንድ አዲስ ልጅ መውለድ

[41] ሁለቱም በመንደር ማሰባሰብ በታቀፉ የተለያዩ ቀበሌዎች ተመድበው የሚሠሩ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ናቸው ፡፡

አለብኝ በማለት መከላከያውን ያቋርጣሉ። ሌላኛዋም እንዲሁ እያለች የልጆቻቸው ብዛት ይጨምራል…" (ወ/ሮ አስረሳሽ ዳኜ፣ ቃመቃመ20/04/05)

ዕውነታው ይሄ ሆኖ ሳለ ባለሙያዎቹ ሁሉም በመንደር የተሰባሰቡ ሴቶች የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆናቸውንና ዕቅዳቸውን ማሳካታቸውን በደስታ ይናገራሉ። ሪፖርታቸውም ይኸው "ስኬት" እንደሆነ መገመት አያዳግትም። የብሔረሰቡ ባህል ግን ልብ ሳይባል ዕቅዱንና ሪፖርቱን በተገለፀው መልኩ ሲያፋልሰው ይታያል።



ፎቶ 27 የበርታ ህፃናት አቡራሙ ቀበሌ

ስለዚህ የሚፈለገውን ግብ ለማሳካት የባህሉን ሚና ዘንግቶ በደፈናው የተዘጋጀ የስኬት ሪፖርት ማቅረብ ሳይሆን ለሴቶቹ ከሚሰጠው የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ጎን ለጎን ወንዶቹም መጥነው ሚስት የሚያገቡበትን መፍትሔ ከሃይማኖት አባቶችና ከብሔረሰቡ

አዛውንቶች ጋር ቁጭ ብሎ መመካከር አስፈላጊና በፅናት መተግበር ያለበትም ጉዳይ የክልሉ መንግሥት የቤት ሥራ መሆን አለበት።

### 8.2.3. የቅድመና የድህረ ወሊድ ክትትል አገልግሎትና ተግዳሮቶቹ

ሌላው የጤና ኤክስቴንሽኑ ፓኬጅ እና ሀገሪቱ በሚሊኒየም ግቡ እንድታሳካው ከሚጠበቅባት ዋነኛ ጉዳዮች አንዱ ሁሉም እናቶች የቅድመና ድህረ ወሊድ ክትትል በጤና ተቋማት እንዲደረግላቸውና ሲወልዱም በጤና ማዕከላት እንዲወልዱ ማድረግ ነው። ይህም የማንኛዋም እናት ሕይወት በወሊድ ምክንያት እንዳይቀጠፍና የህፃናትንም ሞት ለመቀነስ ያለመ ግብ ነው። ይሁንና የበርታ እናቶች ቅድመ ወሊድ ክትትል እንዳያደርጉም ሆነ በጤና ማዕከላት እንዳይወልዱ ባህላዊ ተፅዕኖ እንዳለባቸው ይናገራሉ።

> ከባሎቻችን ውጪ ሰውነታችንን ለሌላ ሰው መግለጥ፣ ማሳየት ሀራም ነው፤ ይህንን እናቶቻችንም አላደረጉትም፤ እኛም እንዳናደርገው ባሎቻችን ያስጠነቁቁናል። በእርግዝና ጊዜ ጤና ጣቢያ ሄደን ምርመራ እንድናደርግ ባህላችን አይፈቅድም፤ እኛም ይህንን ስለምናከብርና ሽማግሌዎችንና ባሎቻችንን ስለምንፈራ ወደዛ አንሄድም … ደሞ እኮ የሚመረምሩን ሴቶች ላይሆኑ ይችላሉ፤ ታዲያ እንዴት ለሌላ ወንድ ገላን ገልጦ ይሰጣል? በጣም ያሳፍራል፤ ባሎችም ቢያውቁ ይቆጣሉ… (ቡውይመቃሴብቻ18/02/05)

ይህ ከላይ የተጠቀሰው ማሳያ ሴቶች ብቻ በተሳተፉበት የቡድን ውይይት ወቅት እርጉዝ ሴቶች ቅድመ ወሊድና ድህረ ወሊድ ምርመራ ለምን ለማድረግ እንደማይፈቅዱ ሀሳባቸውን እንዲያቀርቡ በተደረገበት ወቅት የተነሳ ነው። ሴቶቹ በእርግዝና ጊዜ ሄዶ

ምርመራ ማድረግና በወሊድ ጊዜም እዛው መውለድ ከሚሰጣቸው ጥቅም በላይ ነውር ሆኖ ጎልቶ የሚታያቸው ገላቸውን ለሌላ ሰው ገልጠው የማሳየታቸው ጉዳይ ነው፡፡ የሴትን ገላ ከባሏ ውጪ ማሳየት በባህላቸው ሃራም ነው፡፡ ስለዚህ እናቶቻችን ያላደረጉትን ተግባር እኛም አንከውነውም ባይ ናቸው፡፡ እናቶቻቸው እነሱን ሲወልዱ ጤና ጣቢያ ባለመሄዳቸው የደረሰባቸው ጉዳት እንደሌለ ማስረጃዎቻቸው ናቸው፡፡ ባህላቸውም ስለማይፈቅድ እሱን አልፈው ጋት ለመራመድ አይችሉም፡፡ ጥሰው ካደረጉት ግን ሽማግሌዎችና ባሎቻቸው ይቆጣሉ፣ ይቀጣሉ፡፡ ስለዚህ የቀረው ይቀራል እንጂ ገላቸውን ገልጦ ለሌላ ለማሳየት ንክች አድርገው ወደ ጤና ጣቢያ አይሄዱም፡፡

ይህንኑ ሃሳብ ወንዶች ብቻ በተገኙበት የቡድን ውይይትም ተነስቶ ተመሳሳይ ምላሽ ከመገኘቱም በላይ ባህላዊ ፈርጦቹ በብሔረሰቡ አመለካከት ውስጥ እንዴት የሰረጹ እንደሆኑ ለማሳየት ከቡድን ውይይት ተሳታፊዎቹ አንዱ አባት በተረት አስደግፈው ያቀረቡትን ሃሳብ ማየቱ ጠቃሚ ነው፡፡

> በድሮ ጊዜ አንድ ሰው ሴት ልጁን ይድርና በባልና ሚስቱ መካከል አለመግባባት በመፈጠሩ ሚስት ባሏን ጥላ ወደ አባቷ ቤት ትመለሳለች፡፡ አባት ልጁ ትዳሯን ጥላ ለምን እንደመጣች ሲጠይቃት ባሏ እንዳልተስማማት እና እንደተጣሉ ሁለተኛም ወደ እሱ እንደማትመለስ ትነግረዋለች፡፡
>
> አባት ነገሩን በሚገባ ካዳመጠ በኋላ ልጂት ማምረሯንና ወደ ባሏም እንደማትመለስ በተረዳ ጊዜ ምንም አስተያየት ሳይሰጣት ተነስቶ ውሃ በአልብሪክ[42] ይዞ ወደ መፀዳጃ ቦታ ይወጣና ሆነ ብሎ አልብሪኩን ሰብሮ እያዘነ ይመለሳል፡፡ ልጅት አባቷ በጣም አዝኖና ተክዞ ስታገኘው ምን እንደሆነ ትጠይቀዋለች፡፡ አባትም አልብሪኬ ተሰበረ እጅግ በጣም

[42]አልብሪክ ከሸክላ የሚሠራ በርታዎች ወደ መፀዳጃ ሲሄዱ፣ ሊሰግዱ ሲሉ… ውሃ ይዘውበት የሚሄዱ ባህላዊ ዕቃ ሲሆን አሁን አሁን ከፕላስቲክ በተሠራ ተመሳሳይ ዕቃ እየተተካ ይገኛል፡፡

> ያሳዝናል ብሎ ይማረራል። በዚህ ጊዜ ልጅት ነገሩን በማቃለል አልብሪክ ቢሰበር ሌላ ይተካል ይህን ያህል ማዘን የለብህም ብላ ለማፅናናት ትሞክራለች፤ አባት መልሶ የተሰበረው አልብሪኬ ሰው አይቶት የማያውቀውን ጉያየን ሁሉ የሚያውቅ ነበረ፤ ሌላ አዲስ ሊገዛ ይችላል፤ እኔን ያሳዘነኝ ግን ጉያየን ለማያውቀው አዲስ አልብሪክ ማሳየቴ ነው ብሎ ይመልስላታል። በዚህ ጊዜ የአባቷ ምሳሌ የተገለጠላት ልጅ እኔም ገመናየን ሁሉ የሚያውቀውን ባሌን ዛሬ ብፈታ ነገ ሌላ ሰው ሊያይብኝ ነው ለካ ብላ ወደ ባሏ ተመለሰች ይባላል። ስለዚህ የሚስቱን ጉያ ከባሏ በስተቀር ለሌላ ማሳየት ነውር ነው። ምነው እናቶቻችን እኛን ሁሉ ሲወልዱ ካዋላጅ በቀር ማን ከጉያቸው ይገባ ነበር?… (ቡውይመቃወብቻ፣22/02/05)

ከላይ ከቀረበው ተረት የምንረዳው በበርታ ባህል ገላን ለሌላ ባዕድ ገልጦ ማሳየት ቀርቶ የመጀመሪያ ባልን ፈትቶ ሌላ በማግባት ላለመደው ሰው ማጋለጥ እንኳን የቱን ያህል የሚያሳዝን ጉዳይ እንደሆነ ነው። ከዚህ የተነሳ እናቶች ይህን ባህላዊ ህግ ተራምደው ቅድመና ድህረ ወሊድ አገልግሎት ለማግኘት ወደ ጤና ማዕከላት ለመሄድ አይፈቅዱም።

የክልሉ የጤና ጥበቃ ቢሮ ከ2004- 2005 ዓ.ም የነፍሰ ጡር እናቶች ጋር ያደረገውን የፓናል ውይይት እስመልክቶ ያቀረበው ሪፖርት ይህንኑ ሁኔታ በሚገባ የሚያጠናክር ነው።

> … የበርታ ሴቶች በወሊድ ጊዜም የሚወልዱት በጤና ተቋማት ሳይሆን በልምድ አዋላጆች እርዳታ ከቤት ውስጥ ነው። ምጥ ጠንቶ

> ለመውለድ አስቸጋሪ ሁኔታ ከገጠመና አዋላጇ የማህፀን ጥበት ነው ብላ ካሰበች ከተቻለ በአውራ ጣቷ ጥፍር እምቢ ካለም በተገኘው ስለት ነገር ብልቷን ቀድዳ ታዋልዳለች፡፡ የተቀደደው ብልት ቶሎ እንዲድን በማለትም ከእንጨት የሚገኝ ሙጫ ነገር ይደረግበታል፡፡ እንግዴ ልጅ ካስቸገረም ወላዷን በመዘቅዘቅና ሥራ ሥር ወቅጦ በማጠጣት እንዲወጣ ይደረጋል (ቡጉክመጤጥቢ፣2005፣22)፡፡

በበርታ ብሔረሰብ ወሊድ እስከ አሁን ድረስ የሚከናወነው ከላይ እንደቀረበው ፍፁም ባህላዊ በሆነ መንገድ ነው፡፡ "በጤና ተቋማት ሲወልዱ እናት ጤና ልጅም ደህና" የሚለውን መርህ ለመተግበር ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሆነ ከክልሉ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈፃፀም ትግበራ ሪፖርትም ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ "... የእናቶችና ህፃናትን ሞት ለመቀነስ ቢታቀድም በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ ግማሽ ዘመን... ከመቀነስ ይልቅ በከፍተኛ ደረጃ ጨምሮ ተገኝቷል" (የቤጉክዕትዕአግሪ፣2005፣32)

የበርታ ባህል ለዘመናዊው የጤና አገልግሎት እምብዛም ክፍት አለመሆኑን ከቀረቡት ማሳያዎች መረዳት ይቻላል፡፡ ባህላዊ ፈርጦቹ በሥነቃሎቹም ሳይቀር በተለያዩ መልኮች ተደጋግመው በመምጣት በብሔረሰቡ አመለካከትና ዕምነት ውስጥ እየሰረጹ በመሄድ ልማታዊ ጉዳዩን ይገዳደሩታል፡፡ ይህንን ባህላዊ ተግዳሮት ታዲያ ባህልን ጎጂና የማይጠቅም አድርጎ በመውሰድና በማጣጣል ዘመናዊ የሆነውን አገልግሎት ብቻ ተጠቀሙ በማለት መቅረፍ የሚቻል አይደለም፡፡ ከዚህ ይልቅ አገልግሎቱን የሚሰጡትን ሰዎች ቢቻል ከዛው ከብሔረሰቡ የፈለቁ ሴቶች እንዲሆኑ ማድረግና የዘመናዊውን ጤና አጠባበቅ ትምህርት በዋነኞቻቸው አማካይነት (በሃይማኖት መሪዎች፣ በዕድሜ ባለጠጎች) ለባሎችና ለትልልቅ እናቶች[43] ጭምር እንዲሰጥ በማድረግ የታለመውን ግብ ማሳካት ይቻላል፡፡ ባህላዊ ሁኔታዎች በማህበረሰቡ አኗኗር ዘዬ (ቅጥ) እና በግለሰባዊ ባህሪ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ በመሆናቸው ለባህላዊ ሁኔታዎችና አገላለፆች ተገቢውን ክብርና

[43] እነዚህ እናቶች ቀደም ሲል በጤና ተቋማት ያልወለዱ የአሁኖቹን ወላድ ሴቶች እናቶችን ማለት ነው፡፡

ትኩረት መስጠትና መደገፍ በማህበረሰቡ ዘንድ ያለን ተቀባይነት በማጎልበት መግባባት ላይ ለመድረስና የሚፈለገውን ልማት ለማምጣት ያስችላል (UNESCO,2004,6) የሚባለውም ለዚህ ነው፡፡

## 8.2.4. የሴት ልጅ ግርዛትና የሀርሻ ጭፈራ

ከጤና ዕቅዱ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ሌላው ጉዳይ የሴት ልጅ ግርዛትን ማስቀረት ነው፡፡ የበርታ ማህበረሰብ የግርዛት ሥነ ሥርዓት ከላይ በምዕራፍ ስድስት በቀረበው ሁኔታ በታላቅ ሥነ ሥርዓት የሚከናወን ትልቅ ባህላዊ በዓል ነው፡፡ በርካታ የበርታ ህፃናት በአንድ ላይ ሆነው ሠርግ የመሰለ ታላቅ ድግስ ተደግሶ እየተሞገሱ፤ ልዩ ልዩ ስጦታ እየተሰጣቸው የሚገረዙበት በመሆኑ እነሱም ሆኑ ቤተሰቦቻቸው እንደታላቅ ክብር የሚቆጥሩትና በጉጉት የሚጠብቁት ባህላዊ ክንዋኔ ነው፡፡

በሸርቆሌ ወረዳ የክልሉ ሴቶች ጉዳይ ቢሮ በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ዙሪያ ለመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሴት ተማሪዎች ባዘጋጀው የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና ላይ ተሳታፊ ሆኜ እንደሰማሁት ተማሪዎቹ ለምን እንደሚገረዙ ተጠይቀው ሲናገሩ በባህሉ ያልተገረዘች ሴት እቃ ትጨርሳለች፤ የምታቦካው የምትጋግረው አይበረክትም፤ ቤት ውስጥ አርፋ አትቀመጥም፤ ትባልጋለች፤ ዱርዬ ትሆናለች፤ ለባሏ ታስቸግራለች፤ ባጠቃላይ ነጃሳ[44] ናት፤ ሰላት አትሰግድም፤ እሷ የሰራችውና ያቀረበችው አይበላም የሚሉ አስተሳሰቦች አሉ፡፡

ከነዚህ ምክንያቶች በተጨማሪ አንዷት ሀሲና የተባለች ተማሪ ራሷን ምሳሌ አድርጋ ስታስረዳ እንዲህ ትላለች "ሴት ልጅ ካልተገረዘች ያልተቆረጠው አካል ትል ስለሆነ ውስጥ ውስጡን በልቶ ይገድላታል፤ ወይም ሽባ አድርጎ ያስቀራታል ስለሚባል ነው

[44] ነጃሳ እርኩስ እንደማለት ነው፡፡

የምንገረዘው፤ አሁን እኔ ከመገረዜ በፊት በጣም ያመኝ ነበር ከተገረዘኩ በኋላ ግን ጤናዬ ተመልሷል" (ተማሪ ሀሲና፣ቃመ05/03/05) ብላለች።

"…አሁን ይሄ ነገር እየጠፋ ነው እንደውም ሰው ሳይሰማ፤ አንዳንዶች ቦታ ላይ ጠፍቷል በተለይ የሴቶቹ ሌሎች ደግሞ የማያምኑበት ውስጥ ለውስጥ ያደርጋሉ፤ዛሬ ስብሰባ ውለው ማታ እሚያስገርዙም አሉ። ይቅር የሚባለውን ነገር ተቃውሞው በጣም ትልቅ ነው፤ ቁርአን አያዝም የሴቶቹን ግን በባህሉ ስለተለመደ ይደረጋል" (አባ ሃሚድ ተንጎሮ፣ ቃመ29/03/05)። ይህ የሚያመለክተው የሴት ልጆች ግርዛት በአደባባይ ይቅር እንጂ በቤት ውስጥ ዛሬም እየተከናወነ መሆኑን ነው።

ባህላዊ ዕምነቱ ይሄ ሆኖ ሳለ የጤና ፖሊሲው "ሴት ልጅን ማስገረዝ ተገቢ አይደለም" ሲል በርታዎች ካለምንም ማንገራገር አልተቀበሉትም። እንደ ጥንቱ በአደባባይና በታላቅ ድግሥና ሥነ ሥርዓት አይፈፅሙት እንጂ ጠዋት በስብሰባ ላይ "ሴቶችን እንዳታስገርዙ" ሲባሉ "እሺ" ብለው፣ ተስማምተው፣ በጭብጨባ አፅድቀው ይወጡና ማታ በድብቅ የሚያስገርዙ ብዙዎች ናቸው። ምክንያቱ በባህላቸው ያልተገረዘች ሴት ነጃሳ ከመሆኗም በላይ አለመገረዟ በሽተኛ አድርጎ "ሊገድላትም" ስለሚችል ነው። ማንም ሰው ደግሞ አያስፈልግም የተባለውን ነገር ያስወግዳል እንጂ በዚህ ሳቢያ መሞት አይፈልግም። ለሞት የሚያደርስ ምክንያት ባይኖርም በማህበረሰቡ ዘንድ እርኩስ መባልንም የሚፈልግ የለም። የረከሰችን ሴት ደግሞ ማንም ወንድ አያገባትም። ካለባል ቆማ መቅረት የምትፈልግ ሴት ስለማትኖር ደግሞ ግርዛቱ ጎጂ ልማድ ነው ቢባልም በይፋ ማድረጉን ትታ በድብቅ ትከውነዋለች። ምክንያቱም ያለመገረዝ ጥቅሙን ተጨባጭ በሆነ ማስረጃ የሚያሳምናት ማንም ሰው ሊኖር ስማይችል ነው።

ሀሲና ያልተገረዘች ሴት ብልቷ ትል ፈጥሮ እየበላ አመንምኖ እንደሚገድላት፣ ከአያቷና ከሠፈሯ ሌሎች ሴቶች ስትሰማ ነው ያደገችው። እሷም በብልቷ አካባቢ የማሳከክ ስሜት ሲፈጠር የጠረጠረችው ባለመገረዟ ምክንያት እንደሆነ ነው። በዚህ የተነሳ የተፈጠረባትን የእሞታለሁ ጭንቀት ለእናቷ ስትናገር እሳቸውም ጥርጣሬ እንደገባቸው ስለነገሯት

በድብቅ ገራዥ ጠርተው እንድትገረዝ ያደርጋሉ። ከዚያ በኋላ በሽታው ጠፋ እሷም በህይወት ቆየች። በርታዎች የመገረዝን ጥቅም የሚያሳዩበት ሀሲናን የመሰለ ምሳሌ አላቸው። በአንፃሩ ግን ጉዳቱን በደፈናው ከመዘርዘር ይልቅ በተጨባጭ ማስረጃ የሚያሳያቸው ሰው አላገኙም። ስለዚህ በአደባባይ ሴት ልጅን አትግረዙ ሲባሉ የመንግስት ትዕዛዝ ነውና እሺ ብለው በድብቅ እቤታቸው ይተገብሩታል። ለግርዛቱ የሚደረገውም ሥርዓት፣ ድግስና የሀርሻ ጭፈራው ስሙን ቀይሮ ይከናወናል።

ሀርሻ የበርታ ብሔረሰብ በሠርግና በልዩ ልዩ በዓላት ምክንያት የሚዘጋጅ የምሽት ጭፈራ ነው። በጭፈራው በጣም በዕድሜ የገፉ ሰዎች ካልሆኑ በሁሉም የዕድሜ ክልል የሚገኙ ሴቶችም ወንዶችም ተሳታፊ ይሆናሉ። ጭፈራውን ያስከተለው ጉዳይ ድግስ እየተበላና እየተጠጣ ይቆይና ምሽት ከ3 እና ከ4 ሰዓት በኋላ ጭፈራው ይጀመራል። ዘፈኑ በአብዛኛው በክራርና በከበሮ የሚታጀብ ነው። በተለይ ወጣቶቹ ሀርሻን ጓደኛ እንደማፍሪያና እንደመተጫጫ አጋጣሚ ስለሚቆጥሩት በናፍቆት የሚጠብቁትና በደስታ የሚከውኑት ነው። ወላጆችም ሃርሻ ጭፈራ ላይ ልጆቻቸው እንዳይታደሙ አይከለክሉም። ሀርሻ የሚጨፈረው ታዲያ በምሽት በመሆኑ ወጣቶችን ለልቅ የግብረስጋ ግንኙነት የሚጋብዝ ነው። በዚያ ሳቢያም ለኤች አይ ቪ ኤድስ፣ ላልተፈለገ እርግዝና የሚጋለጡ ወጣቶች ቁጥር እየጨመረ በመምጣቱ[45] የክልሉ የሴች ወጣቶችና ህፃናት ቢሮ ከላይ የተነሳውን የጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን የማስወገጃ ስልጠና በየወረዳዎቹ እየተዘዋወረ ለመስጠት አስገድዶታል።

---

[45] በተለይ በበርታ ብሔረሰብ ውስጥ ያለውን የኤች አይ ቪ ኤድስ ስርጭትንና ያልተፈለገ እርግዝና መጠኑን የሚገልፅ ከክልሉ ጤና ቢሮም ሆነ ከሴቶች ወጣቶችና ህፃናት ቢሮ ማስረጃ ማግኘት አልቻልኩም፡፡ ሲደረግ የነበረውም ዘመቻ ለሪፖርት እንጂ በጥናት ላይ የተመሠረተ ቁልጭ ያለ መረጃ የሌለው በመሆኑ ከባህላዊው ሁኔታ ጋር አያይዤ ማየት አላስቻለኝም፡፡ ማህበረሰቡን ስለኤች አይ ቪ ኤድስ አንስቼ ስጠይቅ ግን በባህላችን ከሚስት ውጪና በመሸታ ቤት የሚሠሩ ሌሎች ሀበሾች ጋ መሄድ ሃራም ስለሆነ በዚህ ተይዞ የሞተ ሰው የለም አናውቅም የሚል መልስ በተደጋጋሚ ሰጥተውኛል፡፡ ይህም ትኩረት ተሰጥቶት በሚመለከታቸው የክልሉ ቢሮዎች መጠናት ያለበት ጉዳይ ነው፡፡





ፎቶ 28 የሀርሻ ጭፈራ

ከላይ በማስረጃ እየተደገፈ ለማሳየት እንደተሞከረው የበርታ ብሄረሰብ ባህል በግብርናውም በጤናው ኤክስቴንሽን አተገባበር ላይ የሚያሳርፈው አሉታዊ ተፅዕኖ የጎላ መሆኑን ነው፡፡ ይህን ባህላዊ ተግዳሮት ደግሞ ኋላ ቀርና የልማት አደናቃፊ ነው በማለት ብቻ የታሰበውን ልማት በተፈለገው ፍጥነትና መጠን ማምጣት አይቻልም፡፡ የባህሉ አሉታዊ ተፅዕኖዎች ከላይ ወደታች በሚጫኑ "በእኛ እናውቅልሃለን" ገለፃዎች በቀላሉ የሚወገዱ አይደሉም፡፡ ሁሉን ዘመናዊ በማድረግም ፈፅመው ሊቃለሉ አይችሉም፡፡ ከዚያ ይልቅ የብሔረሰቡን ባህል ጠንቅቆ በማወቅና ማህበረሰቡንም በአካባቢው ልማት ላይ ተሳታፊና ተጠቃሚ በማድረግ ለውጥ ማምጣት ይቻላል፡፡

ስለ ሀገር ልማት ስንነጋገር ለልማታዊ ዕቅዱ ተግባራዊነትም ሆነ አለመሳካት የማህበረሰቡ ባህል የሚኖረው ሚና ከፍተኛና የማይታለፍ እንደሆነ በበርታ ባህል መነሻነት ከቀረበው ከዚህ ጥናት መረዳት ይቻላል፡፡ በጥናቱ የቀረቡት አብነቶችም መንግሥት በማህበረሰቡ ባህል ዙሪያ ጠንክሮ ቢሠራ ምናልባት አሁን ከሚታሰበው በበለጠ የተሻለ ውጤታማ ልማት ማምጣት እንደሚችል የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ የክልሉም መንግሥት በዕቅዱ ላይ ማነቆ ናቸው ብሎ ያስቀመጣቸው ባህላዊ ተግዳሮቶች የሚፈቱት በዴሞክራሲያዊ ትግል ብቻ ሳይሆን የብሔረሰቦቹን ባህል ጠቃሚ እሴቶች መነሻ አድርጎ ለሀገረሰባዊ ዕውቀቶች ቦታ በመስጠት አሳታፊ የሆነ የልማት አካሄድ በመከተል ነው፡፡

# ምዕራፍ ዘጠኝ

## 9. ማጠቃለያና ይሁንታ

በዚህ ምዕራፍ የሚቀርቡት ከጥናቱ ዓላማዎች አኳያ የተደረሰበት ውጤት የማጠቃለያ ሃሳቦችና በዚህ ጥናት የታየውን የበርታ ብሔረሰብ ባህል ከልማት ጋር ያለውን ቁርኝት በአብነት ወስዶ ባህል በልማት ላይ የሚያሳድረውን አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ተፅዕኖ ከግንዛቤ በማስገባት በአጠቃላይ ለክልሉ ልማት ተፈላጊውን ለውጥ ለማምጣት ወደፊት በሚመለከታቸውና በባለ ድርሻ አካላት ምን መደረግ ይኖርበታል የሚሉት የይሁንታ ሃሳቦች ይሰነዘራሉ፡፡

### 9.1. ማጠቃለያ

ባህል የአንድን ማህበረሰብ ማንነት፣ ዕምነት፣ አስተሳሰብ፣ ስለዓለም ያለውን አመለካከት፣ በሕይወት ውስጥ እርስ በእርስ በሚያደርገው መስተጋብር፣ ባህላዊ እንቅስቃሴዎችና ትዕምርቶች ለማወቅ የሚያስችል የማህበረሰቡ አውደ ጥበብ (Encyclopedia) ነው፡፡ በመሆኑም የዚህ ጥናት ዋነኛ ዓላማ አንዱ ፍሬ ጉዳይ የነበረው የበርታን ብሔረሰብ ባህል በጥልቀት ማጥናት ነበር፡፡ በዚህም የብሔረሰቡን ሁለንተና አመልካች የሆኑትን ባህላዊ እሴቶች ማለትም ማህበረ ባህላዊ መገለጫዎች የሆኑት አካላዊ መልክ፣ አለባበስና አጊያጊያጥ፣የምግብ አሠራርና አመጋገብ፣ እንግዳ አቀባበል በዝርዝር ተጠንተው ቀርበዋል፡፡

የአንድን ማህበረሰብ ባህል በግልፅ ለማወቅና የማህበረሰቡን ልዩ ባህላዊ መገለጫዎች ለመለየት ከሚያስችሉት ጉዳዮች መካከል የሕይወት ዑደት ሥርዓቶቹ ዋነኞቹ በመሆናቸው የበርታ ብሔረሰብ የጋብቻ፣ የልደትና ሞት ሥርዓቶችም ተጠንተዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የብሔረሰቡ ሀገረሰባዊ ልማዶች የሆኑት ክብረበዓላት፣ የአምልኮ ሥርዓቶችና ባህላዊ መድሃኒቶችም በጥናቱ ተካተዋል፡፡

ስለ አንድ ብሔረሰብ ባህል ለመናገር የሥነቃል ሀብቶቹ የሚኖራቸው ሚና ከፍተኛ መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ በመሆኑም የተገኙት ያህል የብሔረሰቡን ሥነቃሎች ተሰብስበው በዚህ ጥናት ውስጥ ከጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

በበርታ ባህል በተደጋጋሚ እየተሰናሰሉ ከሚመጡት በአጠቃላይ ስለ ብሔረሰቡ ተከባብሮ፣ ተረዳድቶና ተማምኖ በጋራ የመኖር ባህል፣ ዕውነተኝነት ወይም ሀቀኝነት፣ ፍትሃዊነት፣ እንግዳ ተቀባይነትና ቸርነት የሚያሳዩ፣ እርስ በእርስ ያለውን መስተጋብርና አብሮነት የሚያመለክቱ፣ ማህበራዊ ህይወቱን የሚያንፀባርቁና ከሌላው ማህበረሰብ የሚለዩት በርካታ ባህላዊ እሴቶች ያሉት ብሔረሰብ እንደሆነ ከጥናቱ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በዚህም ስለበርታ ብሔረሰብ አጠቃላይ ባህላዊ መልኮች ለማወቅ ይህ ጥናት የሚኖረው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው ማለት ይቻላል፡፡

የበርታ ብሔረሰብ ባህላዊ ፈርጦች መረባቸውን በሁሉም ባህላዊ መገለጫዎች በመዘርጋትና በመሰናሰል በአንዱ ባህላዊ መልክ የታየው አንድ ጉዳይ በሌላው ተደጋግሞ በመምጣት የብሔረሰቡን አስተሳሰብ እና ሰብዕና የገነቡና በውስጡም ሰርጅተው የኖሩ ናቸው፡፡ እነዚህ ባህላዊ እሴቶች በአንድ መልኩ ብሔረሰቡን እስከዛሬ አስተሳስረው ያኖሩ፣ ለአካባቢው ልማት በአዎንታዊ ጎናቸው የሚታዩና ሊዳብሩ የሚችሉ ሲሆኑ በሌላ መልኩ ደግሞ  ብሔረሰቡን ለተሻለ ህይወት እንዳይነሳሳና የአካባቢውን ልማት እንዳይፋጥን እያወላከፉ የሚገኙ መሆናቸውን ለማየት ተችሏል፡፡

ከባህላዊ እሴቶቹ ቢያሳድጓቸውና ቢያጎለብቷቸው ጠቃሚ የልማት መሣሪያ የሚሆኑ የጋራ ትብብሮችና የአኗኗር ልማዶች፣ መልካም አስተዳደርን፣ ከሙስናና ከአድሏዊ አሰራር የፀዳ ማህበረሰብን መገንባት የሚያስችሉ ሃቀኝነትና ዕውነተኛነት መሠረታቸው የሆነና ሌብነትና ቅጥፈትን የሚጠየፉ ባህላዊ ፈርጦች እንዳሉ በጥናቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

የማህበረሰብ ጤና እንክብካቤን አስመልክቶ ብሔረሰቡ ራስንና አካባቢን በንፅህና መጠበቅ በትጋት የሚተገበረው የዕለት ከዕለት ሁነት በመሆኑ የግልና የአካባቢን ንፅህናን ባለመጠበቅ ከሚመጡ በሽታዎች ራሱን የሚከላከልበት  በውስጡ የሠረጀ አወንታዊ ባህላዊ እሴት እንደሆነ ተረጋግጧል። ይህ ባህላዊ እሴት በሌሎች አካባቢዎች ቢስፋፋ ጠቃሚ ትምህርት ሊቀሰምበትና ፈጥኖ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል ቱርፋት እንደሆነም ታይቷል።

በሌላ መልኩ ደግሞ ለልማትና ለተሻለ ህይወት በሚደረገው ጉዞ ላይ ጥላቸውን የሚያጠሉ አሉታዊ ባህላዊ ጉዳዮች እንዳሉም በጥናቱ ለማረጋገጥም ተችሏል። እነዚህም የዚህ ጥናት ትኩረት በሆኑት ግብርና ኤክስቴንሽን እና የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጆችን ለመፈፀም በገጠሟቸው ተግዳሮቶች የሚገለፁ ናቸው።

ግብርና ኤክስቴንሽንን አስመልክቶ የልማት ዕቅዱ ዓላማ አርሶ አደሩ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀምና ሰፊ ጊዜውን በማሳው ላይ በማሳለፍ ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ ለገበያ ተፈላጊ ምርቶችን በማምረት የራሱንና የአካባቢውን ልማት በማፋጠን በሀገሪቱ የኢኮኖሚ ልማት ላይ የራሱን አስተዋፅዖ እንዲያደርግ ማስቻል ነው። የበርታ አርሶ አደር ግን ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚደረገውን ጉዞ የሚገዳደሩ ባህላዊ መሠረቶች አሉት።

ብሔረሰቡ በባህሉ በጋራ ተረዳድቶ በጋራ ያለውን ተካፍሎ የሚኖር በመሆኑ ለነገ የማይጨነቅና ኑሮዬ ይበቃኛል ብሎ መኖር የሚያስችል አመለካከት እንዲኖረው አድርጎታል። ስለዚህ ምርትና ምርታማነትን ማሳድግ፣ ጥሪት መቋጠር፣ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ምርቶች ማምረት፣ ምርጥ ዘር ማዳበሪያን የመሳሰሉትን የግብርና ግብዓቶችን በብድር ወስዶ መጠቀም በዶማ ከመቆፈር ይልቅ በዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች ማረስ የሚሉትን የመንግስት ተልዕኮዎች ለመፈፀም እምብዛም አይነሳሳም። በአካባቢው በስፋት የሚለሙትን ማንጎና ሰሊጥ እንኳን ከራሱ ፍጆታና በመጠኑ ሸጦ ለዕለት ፍላጎቱ ከመጠቀም ባለፈ በስፋት በማልማት ለትላልቅ ገበያ ሲያቀርብ አይታይም።

የጤና ኤክስቴንሽንን በተመለከተም አፈፃፀሙ የገጠመው ባህላዊ ተግዳሮት ብዙ እንደሆነ ማረጋገጥ ተችሏል። የአንድ አካባቢ ማህበረሰብን አምራች ዜጋ ለማድረግ በቅድሚያ ጤናው የተጠበቀ መሆን አለበት።

የጤና ኤክስቴንሽኑ ያካተታቸው ፓኬጆች ውስጥ በበርታ ብሔረሰብ ባህል ተፅዕኖ ምክንያት ተፈፃሚ ያልሆኑ አሉ። የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቱን ብናይ ቀድሞ አንድ ሴት በአማካይ ከስምንት እስከ አሥር የሚደርሱ ልጆችን ትወልድ የነበረውን በተለይ በመንደር ማሰባሰቡ በታቀፉ አርሶ አደሮች ዘንድ አገልግሎቱን በመጠቀም ወሊድ መጠኑ በአማካይ ወደ አራት እንደወረደ ባለሙያዎቹ ቢናገሩም በባህሉ አንድ ወንድ ከአራት በላይ ሚስት የሚያገባ በመሆኑና በሚስቶች መካከል በሚፈጠር የመውለድ ፉክክር ስኬታማ መሆን እንዳልተቻለ ተረጋግጧል።

የእናቶችና የህፃናት ሞትን ለመቀነስ ከሚደረገው ጥረት አኳያ ወላዶች በእርግዝና ጊዜ ክትትል እንዲያደርጉ ሲወልዱም በጤና ተቋማት እንዲወልዱ የሚደረገውም ጥረት በበርታ ባህል ሴቶች ከባላቸው ውጪ ሰውነታቸውን ለሌላ ሰው ማሳየት ነውር በመሆኑ ሳይሳካ መቅረቱ ተረጋግጧል። ይህ ዕውነታ በክልሉ መንግስት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ ሳይቀር በዋነኛ ማነቆነት የተቀመጠ በመሆኑም ችግሩ ተጨባጭ እንደሆነም ለማረጋገጥ ተችሏል።

በተለይ በገጠሩ አካባቢ የሚኖሩት የበርታ ብሔረሰብ አባላት በአካባቢያቸው የሚገኙ ኤሪዎች እና የባህል መድሃኒት አዋቂዎች በሚሰጡዋቸው አገልግሎት የሚተማመኑ በመሆናቸው በዘመናዊ የጤና አጠባበቅ ዘዴዎችና በጤና ተቋማት መገልገልን እንደማያስቀድሙ በጥናቱ ታይቷል።

የሴት ልጅ ግርዛትን አስመልክቶም በብሔረሰቡ ባህል ሴት ልጅ ካልተገረዘች ነጂስ/ ርኩስ ስለሆነች እሷ የሰራቻውና የአቀረበችው እንደማይበላ ከመታመኑ በላይ ያልተተለተለው ብልት ሴቷን “እየበላ አመንምኖ ይገድላታል” የሚል አስተሳሰብ ስላለ በአደባባይ ጎጂ

እንደሆነ የሚነገራቸውን ሰምተው በድብቅ እቤታቸው ሴት ልጆቻቸውን እንደሚያስገርዙ በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡

በአጠቃላይ ከእነዚህን በበርታ ብሔረሰብ ባህል ከታዩ ለልማት አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ባህላዊ እሴቶች በመነሳት ባህላዊ ጉዳዮችን ሁሉ በደምሳሳው ኋላ ቀርና የልማት አደናቃፊ ብቻ አድርጎ ከመውሰድ ይልቅ አዎንታዊ የሆኑትን የብሔረሰቡን ባህላዊ መልኮች አክብሮና አስፋፍቶ ለታሰበው ልማት ጥሩ መሠረትና መሣሪያ ለማድረግ መነሳት ጠቃሚነቱ የጎላ እንደሆነ ጥናቱ አረጋግጧል፡፡

በብሔረሰቡ ባህል የታዩት የልማት ተግዳሮቶች "ይሄንን አድርግ ይሄንን አታድርግ የተቀመጠልህ ተልዕኮ ስለሆነ ጥረህ ግረህ ፈፅም!!" በማለት ብቻ የሚፈቱ አይደሉም፡፡ በ"ዴሞክራሲያዊ ትግልና ቅስቀሳ" ብቻ የታሰበውን ለውጥ ማምጣትም አይቻልም፡፡ ይልቁንም በማህበረሰቡ አል ከልዋ ውስጥ በጋራ ቁጭ ብሎ ለመልካሞቹ ባህላዊ እሴቶች ዕውቅና በመስጠትና የሚጎለብቱበትን በጋራ በመወያየት እነሱን መነሻ አድርጎ ደግሞ "ጎጂ" የተባሉትንና አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድሩትን ቀስ በቀስ የሚቀረፉበትን ዘዴ በጋራ በመመካከርና በመማማር ለውጥ ለማምጣት መሥራት ተገቢ መንገድ ነው፡፡

ለዚህ ደግሞ አሁን በክልሉ ያለው ማህበረሰቡን በመንደር የማሰባሰብ መርሃ ግብር ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር ነው ለማለት ይቻላል፡፡ በጋራ ተሰባስቦ የመኖር ልምድ ያለውን የበርታን ብሔረሰብ ይበልጥ በአንድ አካባቢ በማሰባሰብ የልማቱ ቀዳሚ ተዋናኝ ለማድረግ በጣም ቀላል ነው፡፡ ለዚህ የሚጠይቀው ብልሃት ከላይ ወደታች ከሚወረወር የልማት ዕቅድ ይልቅ ወደ ህዝቡ ቀርቦ በአካባቢው ልማት ላይ በጋራ እንዲመክር፣ በጋራ የትብብር ዘዴዎቹ ተጠቅሞ ለዕለት ጉርስ ከመስራት ይልቅ ሰፋፊ እርሻዎችን በጋራ እንዲያለማ፣ አካባቢውን በጋራ እንዲንከባከብ በአጠቃላይ የልማት ዕቅዱን የእኔ ነው ብሎ እንዲገዛው ማድረግ ይቻላል፡፡

ተደራሽ አይደሉም የሚላቸውን የጤናና የትምህርት ተቋማትና መንገድ፣ ውሃና መብራትን የመሳሰሉ መሠረተ ልማቶች ተደራሽ በማድረግና በማሟላት በቅርብ እየተገኙ በማወያየትና በማስተማር የባህሉን ጠቃሚ እሴቶችና ሀገር በቀል ዕውቀቶችን ለይቶ በማጎልበት ባህሉን ራሱን አልምቶ አካባቢውን ለማልማት ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር እንደሚቻል በጥናቱ የተገኘው ውጤት ያመለክታል፡፡

በመጨረሻም ባህል የአንድ ማህበረሰብ ሁለንተናዊ መገለጫ በመሆኑ ባህላዊ እሴቶች በማህበረሰቡ ውስጥ ሰፊና የጠነከረ መሠረት ያላቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡ በተለይ በልማት ላይ የሚያሳድሩት አወንታዊም ሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚለካው በማህበረሰቡ ውስጥ ባለው የስረጃ መጠን ነው፡፡ በመሆኑም ባህል በልማት ላይ የሚያሳድረውን አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ ለማጥናት የሚነሳ ተመራማሪ እነዚህ ባህላዊ መልኮች በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን ቦታና በልማት ጉዳዮች ላይ ያላቸውን አቅም ለመመርመር በልዩ ልዩ ባህላዊ ዘዉጎች ተደጋግመው መምጣታቸውን፣ እርስ በርስ እየተሰናሰሉም ራሳቸውን መትከላቸውን መመርመር ዋነኛ ትኩረቱ መሆን ስለሚገባው ለዚህ እንዲረዳው በዚህ ጥናት የተገኘውንና ከጥቅም ላይ የዋለውን **የባህላዊ ፈርጦች ተደጋጋሚነትና ተመሳስሎ ዙር ገጠም ሥረጃ መረብ** የተሰኘውን ሞዴል ቢጠቀም ውጤታማ ሊሆን ይችላል ተብሎ ይታመናል፡፡

## 9.2. ይሁንታ / Recommendations

ከዚህ ጥናት ውጤት መገንዘብ እንደሚቻለው ባህልና ልማት ያላቸው ቁርኝት የጠበቀ መሆኑን ነው:: ስለዚህ ስለልማት ጉዳዮች ስናነሳ የባህልን ጉዳይ ወደ ጎን መተው የለብንም:: ይህ ሲባል ደግሞ የልማቱ አካባቢ ማህበረሰብን ባህል አዎንታዊና አሉታዊ መልኮች አጢነው ከተጠቀሙበት አጋዥ፣ በደፈናው ጎታች ነው ብለው ከደመደሙ ደሞ አደናቃፊ መልክ እንዳለው መገንዘብ ያስፈልጋል ማለት ነው:: በመሆኑም በልማት ጉዳዮች የሚመለከታቸው አካላት የባህልን ጉዳይ ትኩረት ሰጥተው እንዲሰሩ የሚከተሉት የይሁንታ ሀሳቦች ተሰንዝረዋል::

**የፌዴራል መንግሥት:-**

- በተለይም ልዩ ድጋፍ የሚሹ ክልሎችን ለማገዝ የተቋቋመው የፌደራል እገዛ ቦርድ ለክልሎቹ መንግሥታት ሙያዊ ድጋፍ የሚሰጡ የግብርና፣ የጤና፣ የመስኖ፣ የትምህርት፣ ወዘተ ባለሙያዎችን እንደሚልከው ሁሉ ባህል ለልማት የሚኖረውን አስተዋፅዖ ተገንዝቦ የአካባቢው ልማት እንዲጠና እገዛ እንዲያደርጉ የባህል ባለሙያዎችንም ልኮ ክልሉን ቢደግፍ::

- የባህል ጥናቶችና ምርምሮች ሀገሪቱ ለምትከተለው የልማት አቅጣጫ የሚኖራቸው ጉልህ አስተዋፅዖ ግምት ውስጥ በማስገባት የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦችን ባህሎች በዕውቀት እንዲጠኑና ልማቱን ለማፋጠን በግብዓትነት እንዲያገለግሉ አስፈላጊውን ድጋፍ ቢያደርግ::

**አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**

- በሚያካሂዳቸው የድህረ ምረቃ ፕሮግራሞች በተለይ ለፎክሎር ፕሮግራም በመስክ ለሚሠሩ ጥናትና ምርምሮች የሚመድበው ገንዘብ በጣም አነስተኛ በመሆኑ ጥናቶቹ ለሀገር ልማት የሚኖራቸው አተዋፅኦ ከግምት ውስጥ አስገብቶ ተገቢውን ገንዘብ ቢመድብ።

- በሀገሪቱ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ባህሎች ላይ የሚሰሩ ጥናቶች ለሚታሰበው ልማት የሚኖራቸውን ፋይዳ ከግምት ውስጥ አስገብቶ ከባለድርሻ አካላት ጋር ተባብሮ ከዩኒቨርሲቲ ኢንዱስትሪ ሊንኬጅ አቅጣጫው ጋር በማስተሳሰር ከጥቅም ላይ የሚውሉበትን መንገድ ቢያመቻች።

- በድህረ ምረቃ ፕሮግራም በባህል ዙሪያ ለሚደረጉ ምርምሮች የተሰበሰቡ የምስልና የድምፅ መረጃዎች ጠቃሚነታቸው ለሌሎች ጥናቶችም የሚተርፍ በመሆኑ ተደራጅተው የሚቀመጡበት ሥፍራ እንዲያገኙ አስፈላጊውን ትኩረት ቢሰጥ።

**ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር፡-**

- ባህል ለልማት የሚኖረውን ወሳኝ ሚና ተረድቶ የየብሔር ብሔረሰቦቹና ሕዝቦች ባህል የሚጠናበትን መንገድ ትኩረት ሰጥቶት ቢሠራ፣ የባህል ጥናቶቹም ትኩረት ባህላዊ እሴቶችን በመሰነድ ላይ ብቻ ከመሆን ባለፈ ለሀገሪቱ ልማት ከሚኖራቸው ሚና አኳያ እንዲሆኑ ቢደረግ።

- በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲና በሌሎች ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በሀገሪቱ የሚገኙ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ባህል ላይ የተደረጉ ጥናቶች

ለመፀሃፍት መደርደሪያ ሲሳይነት ተላቀው ለህዝብ በመድረስ ለባህላዊ እንዱስትሪው ልማት በግብዐትነት የሚያገለግሉበት ሁኔታ ቢፈጠር።

- የባህል ባለሙያዎችን ክህሎት ለማዳበር በአቅም ግንባታ ሥራዎች ላይ ትኩረት ሰጥቶ ቢሠራ።

- የማህበረሰቡ ባህላዊ ሀብቶች በወጉ ከተጠኑና ከተሰፋፉ የባህል ኢንደስትሪዎችን በማሳደግ ሰፊ የሥራ እድልን የሚፈጥሩና ለሀገር ኢኮኖሚም ከፍተኛ የገቢ ምንጭ የሚያስገኙ በመሆናቸው ከቱሪዝም ልማቱ ባላነሰ መልኩ ትኩረት ተሰጥቷቸው የሚለሙበትን መንገድ ቢፈልግ።

***ተመራማሪዎች***

- በባህልና ልማት ዙሪያ ጥናትና ምርምር የሚያደርጉ ተመራማሪዎች የባህልና ልማት ቁርኝት መታየት ያለበት ቁልፍ ጉዳይ መሆኑን ተገንዝበው ይህንን ጥናት መነሻ በማድረግ የማህበረሰቡ ባህል በልማት ላይ የሚያሳድረውን አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ በመመርመር የጥናቱን ግኝቶች በማስፋትና አዲስ ትምህርት በመጨመር ቢሠሩ።

**የክልሉ መንግሥት፡-**

- የክልሉን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ጨምሮ ለሚነድፋቸው የልማት ዕቅዶች ተፈፃሚነት በክልሉ ያሉ ብሔረሰቦች ባህል የሚኖረውን ጉልህ ድርሻ ከግንዛቤ በማስገባት በተለይ የነባሮቹ ብሔረሰቦች ባህሎች በዕውቀት እንዲጠኑ ቢያደርግ፡፡

- የየብሔረሰቡ ባህላዊ እሴቶች የባህልና ቱሪዝም ኢንዱስትሪውን ለማስፋፋትና ሰፊ የሥራ ዕድልን ለመፍጠርም ስለሚያግዙ ለክልሉ ልማት የሚኖራቸውን ጉልህ ሚና ከግምት ውስጥ በማስገባት በተለይ በበርታ ብሔረሰቦች ባህል ውስጥ የተለመዱት፣ በባህላዊ መንገድ የሚሠሩ የዕደ ጥበባት ውጤቶች፣ ሽቶዎችና መዋቢያዎች፣ ዘይቶችና ቅባቶች፣ የእጣኝኛ የጢሳጢስ ምርቶች ወዘተ ከአነስተኛ የጎጆ እንዱስትሪዎች ተነስተው የሚያድጉበትና የሚስፋፉበትን መንገድ ቢፈልግ፡፡

- በበርታ ብሔረሰቦች የተለመዱት የዘመዳሞችና ጎረቤቶች የጋራ ትብብሮች የህብረት ሥራዎችን፣ የቁጠባና ብድር ተቋሞችን ዓላማ በብሔረሰቡ ውስጥ ለማስለመድና ለማስረፅ ጥሩ መሠረቶች በመሆናቸው በጎ ጎናቸውን በማበረታታት የአካባቢውን ልማት ለማፋጠን ቢጠቀምባቸው፡፡

- በባህሎች መካከል ያሉ ውይይቶችና የልምድ ልውውጦች ለሚፈለገው ልማት ምቹ ሁኔታን የሚፈጥሩ ስለሆኑ በበርታ ብሔረሰብ ስለግልና የአካባቢ ንፅህና አጠባበቅ ያለው አዎንታዊ ባህላዊ ሁኔታ ጠቀሜታው ከፍተኛ ነውና በማስፋት ስትራቴጂው አማካይነት ይሄ ልምድ ወደሌላቸው ብሔረሰቦች የሚስፋፋበትን መንገድ ቢፈልግ በሌሎች ብሔረሰቦች ያሉ አዎንታዊ ባህላዊ ሁኔታዎች ለበርታ ብሔረሰብ እንዲተዋወቁ ቢያደርግ፡፡

- ከክልል ጀምሮ እስከ ወረዳ ድረስ ያሉ የባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች አስፈላጊው በጀትና ሙያተኛ ተመድቦላቸው ግብርና፣ ጤናና ትምህርትን ከመሠሉ ሴክተሮች ጋር በቅንጅት የልማቱን ሥራ የሚሠሩበትን ሁኔታ ቢያመቻች፤

- ከክልል ጀምሮ እስከ ወረዳ ድረስ ያሉ የባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች ውስጥ የሚመደቡ ባለሙያዎች በባህል ልማት ዙሪያ ተገቢው ክህሎት እንዲኖራቸው በአቅም ግንባታ ሥራዎች የሚታገዙበትን ሁኔታ ትኩረት ሰጥቶ ቢሰራ።

**ፖሊሲ አውጪዎች፡-**

- ባህል በልማት ላይ የሚያሳድረውን አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ ከጅምሩ በመረዳት የሚወጡ የልማት ፖሊሲዎች፣ ዕቅዶችና ስትራቴጂዎች ባህላዊ ሁኔታዎችን ያገናዘቡ እንዲሆኑ ቢያደርጉ።

- የባህል፣ ግብርና ልማት፣የጤና የትምህርት ወዘተ ዘርፎች በቅንጅትና በመደጋገፍ የሚሰሩበት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ዕቅዶች በወጥነት የሚተገበሩበት አቅጣጫ ቢነድፉ።

- የሚወጡ የልማት ፖሊሲዎች ከሚተገበሩባቸው አካባቢዎች ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የሚስማሙበትን መንገድ ቢፈለግ።

**የበርታ ብሔረሰብ/ ህዝብ**

- የብሔረሰቡ መገለጫ በመሆን እስከዛሬ ድረስ አስተሳስረው ያኖሩትን ተከባብሮ፣ ተረዳድቶና ተማምኖ በጋራ የመኖር፣ ዕውነተኝነት ወይም ሀቀኝነት፣ ፍትሃዊነት፣ እንግዳ ተቀባይነትና ቸርነት የሚያሳዩና ማህበራዊ ህይወቱን የሚያንፀባርቁ ባህላዊ እሴቶቹን አካባቢውን በጋራ አልምቶ በጋራ ተጠቃሚ ለመሆን የሚኖራቸውን አዎንታዊ ሚና ተገንዝቦ በልማቱ ውጤታማ ለመሆን እንዲውሉ ቢያደርጋቸው፡፡

- እርስ በርስ ተከባብሮና ተማምኖ በመኖር ግጭትን አስወግዶ በሰላም ለመኖር የሚተገብራቸው ባህላዊ ጉዳዮች ለአካባቢው ልማት አስፈላጊ የሆኑ መሠረታዊ ባህላዊ እሴቶች ናቸውና ጠብቆ ቢያቆያቸው፡፡

- ጥሪት አለመቋጠር፣ ለነገ አለማሰብና ምርትና ምርታማነትን አለማሳደግን የመሳሰሉት ባህላዊ ሁኔታዎች አብዝቶ ከመውሰድ ጋር ተያይዞ የተሻለ ህይወት እንዳይኖረው አሉታዊ ተፅዕኖ እንደሚያሳድሩበት በመገንዘብ ካለው የሥራ ትጋት ጋር በማያያዝ አካባቢውን ለመለወጥ የሚቻልበትን መንገድ በጋራ ተወያይቶ ቢፈልግ፡፡

- የጤና አጠባበቅን አስመልክቶ የግልና የአካባቢን ንፅህናን በመጠበቅ ረገድ ያሉት ባህላዊ እሴቶች ጠቀሜታቸው የጎላና በአዎንታዊ ሚናቸው የሚጠቀሱ በመሆናቸው ቢያጎለብታቸው፤ እንደሴት ልጅ ግርዛት፣ በጤና ተቋማት ለመገልገል አለመነሳሳትና የመሳሰሉትን ልማዶች በጋራ መክሮበት የሚሻሻሉበትን መንገድ ቢፈልግ፡፡

- በመንደር የመሰባሰቡ ፕሮግራም ብሔረሰቡ እንደሚናገረው በባህሉ ጠብቆ ያቆየውን የጋራ ህይወት የሚያጠናክር በመሆኑ ከመሠረተ ልማት አቅርቦቱ ጋር በማያያዝ ለጋራ ልማት የሚኖረውን ጠቀሜታ በጋራ መክሮ ይበልጥ ተጠቃሚ የሚሆንበትን መንገድ ቢያጎለብት፡፡

# ዋቢ ሠነዶች


ሐሰን ታጁ፣ (ተርጓሚ)። ኢማም አን-ነወዊ **ሪያዱ አስ- ሷሊሒን (ከሐዲስ ቁጥር 1-810)።** አዲስ አበባ፣ ነጃሺ ማተሚያ ቤት፣ 2004 ።

ሳሙኤል አክሊሉ "የጉሙዝ ብሔረሰብ ሀገረሰባዊ ልማድ በተለይ የጋብቻ ሥርዓትና ክዋኔ"፣ ጋብቻ"፣ (ቢኤ ዲግሪ)፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነፅሑፍ ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣2000 ።

ሺፈራው በቀለ፣ (አርታኢ)። **ባህልና ልማት በኢትዮጵያ።** አዲስ አበባ፣ ፎረም ፎር ሶሺያል ስተዲስ፣ 2004።

ባህሩ ዘርጋው ግዛው። **ዘርጋው የአማርኛ መዝገበ ቃላት።** አዲስ አበባ፣ንግድ ማተሚያ ቤት፣1994 ።

ተሰማ ሀብተ ሚካኤል ግጽው። **ከሣቴ ብርሃን ተሰማ የዐማርኛ መዝገበ ቃላት።** አሳታሚው ያልተገለፀ፣ 2002 ።

ተሾመ ሙሉጌታ። "በቤንሻንጉል ጉሙዝ በድባጢ ወረዳ የለቅሶ ሥነሥርዓት"፣ጋብቻ"፣ (ቢኤ ዲግሪ) የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነፅሑፍ ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1998 ።

ንጉስ ወዳጅነው። *"የበርታ ብሔረሰብ የባህል ምግቦችና መጠጦች አዘገጃጀትና አቀራረብ"።* (ኤም ኤ ዲግሪ)፣ በኢትዮጵያ ሥነጽሑፍና ፎክሎር፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃ ት/ቤት፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነፅሑፍ ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 2001 ።

አሉላ ፓንክረስትና ገብሬ ይንቲሶ። *“ሀገራዊ ዕውቀትና ተዛማጅ ቴክኖሎጂ በኢትዮጵያ”* **ባህልና ልማት በኢትዮጵያ።** 2004፣ 77-96

አሰፋ ወርቁ። “የሺናሻ ብሔረሰብ ባህላዊ ጋብቻ”፣ (ቢኤ ዲግሪ) የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነፅሑፍ ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣1995 ።

አቡበከር ሀሰን። “የሺናሻ ብሔረሰብ የሀዘንና የተስካር ሥርዓት”፣ ጋብቻ”፣ (ቢኤ ዲግሪ) የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነፅሑፍ ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣1998 ዓ.ም።.

አክሊሉ ባይሳ “የበርታ ብሔረሰብ ጋብቻ ሥነ ሥርዓትና የሠርግ ዘፈኖች”፣ጋብቻ”፣ (ቢኤ ዲግሪ)፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነፅሑፍ ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣2000 ።

እታገኘሁ አስረስ። “በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የማኦ ብሔረሰብ ባህላዊ የምግብ አዘገጃጀትና አመጋገብ”፣(ኤም ኤ ዲግሪ)፣ በኢትዮጵያ ሥነጽሑፍና ፎክሎር፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃ ት/ቤት፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነፅሑፍ ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፣ 2002 ።

ከበደ ሚካኤል። **ጃፓን እንደምን ሰለጠነች።** አዲስ አበባ፣ 1946።

ክቡር ገና። “የሙስና ባህላዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳቱ” ***ባህልና ልማት በኢትዮጵያ።*** አዲስ አበባ፣ ፎረም ፎር ሶሺያል ስተዲስ፣ 2004።

የማስታወቂያ ሚኒስቴር የፕሬስና ኦዲዮቪዥዋል መምሪያ። **የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች**። አዲስ አበባ፣ ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ፣1994 ።

የራስ ወርቅ አድማሴ። "*ባህልና ልማት ምንነታቸውና ትስስራቸው።*" **ባህልና ልማት በኢትዮጵያ**፣ 2004፣ 1-25

የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ማስታወቂያ፣ ባህል፣ ቱሪዝምና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ። **አዲስ ምዕራፍ** ። አንደኛ ዓመት ቁጥር1፣2፣እና3፣ 1996።

የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ማስታወቂያ፣ ባህል፣ ቱሪዝምና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ። **አዲስ ምዕራፍ** ። አስራ ሶስተኛ ዓመት ቁጥር 26፣ 2003።

የቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት *"የአምስት ዓመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ"።* መስከረም 2003 ዓ.ም (ያልታተመ)።

____________ ። *"የአምስት ዓመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የአፈፃፀም ግምገማ ሪፖርት" ።* ግንቦት 2005 ዓ.ም. (ያልታተመ)።

የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ጤና ጥበቃ ቢሮ። **የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ከ2004-2005 ዓ.ም. የተካሄደው የነፍሰ ጡር እናቶች ፓናል ውይይጥ ሪፖርት**። ሰኔ 2005 ዓ.ም.

የወጣቶችና ባህል ሚኒስቴር። **የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የባህል ፖሊሲ**። አዲስ አበባ፣ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1995።

የኢፌዲሪ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር። **የቤተሰብ ጤና አጠባበቅ ኤክስቴንሽን ፓኬጅ**። አዲስ አበባ፣ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣1995።

____________። **ለአርብቶ አደር ህብረተሰብ የግል ንፅህና አጠባበቅ ኤክስቴንሽን ፓኬጅ።** አዲስ አበባ፣ፊንፊኔ ማተሚያ ቤት፣1998።

____________ ። **ለአርብቶ አደር ህብረተሰብ ለጤና ተስማሚ መኖሪያ ቤት አሠራርና አያያዝ ኤክስቴንሽን ፓኬጅ።** አዲስ አበባ፣ኢትየ ጥቁር አባይ አታሚዎች፣ 1998።

የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር። የመስሪያ ቤቱን ራዕይ፣ ተልዕኮና አደረጃጀት ማስተዋዋቂያ መጽሄት። አዲስ አበባ፣ናሽናል ፕሪንቲግ ፕሬስ፣1995።

___________:: *የመስሪያ ቤቱን ራዕይ፣ ተልዕኮና አደረጃጀት ማስተዋዋቂያ መጽሄት*:: አዲስ አበባ፣ብራና ማተሚያ ቤት ፕሬስ፣1999::

___________ :: **ስትራቴጂያዊ ዕቅድ 2003-2007**:: ተልዕኮ፣ራዕይ፣ እሴት፣ግቦችና ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች፣አዲስ አበባ፣ናሽናል ፕሪንቲግ ፕሬስ፣2003::

ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ:: **መንግስትና የሕዝብ አስተዳደር**:: አዲስ አበባ፣ 1916::

ጌታመሳይ ግዛው:: "የሺናሻ ብሔረሰብ የቀብር ሥርዓት ክዋኔ ከፎክሎር ዘውጎች አንፃር"ጋብቻ":: (ቢኤ ዲግሪ) የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነፅሑፍ ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣2002::

ፈቃደ አዘዘ:: **የስነቃል መምሪያ**:: አዲስ አበባ፣ቦሌ ማተሚያ ድርጅት፣ 1991 ዓ.ም::

________________:: *ቱዘማ፦ፎክሎር (ባህል) እና ልማት በኢትዮጵያ*:: **ባህልና ልማት በኢትዮጵያ**፣ 2004፣ 97-136::

Adinew Abtew. "Poletical and Socio- Economic History of Asossa Warada, 1941-1991", MA Thesis in History, School of Graduate Studies, Addis Ababa University, 2011.

Barnard, Alan. **History and Theory in Anthropology**. Cambridge University Press, the Pitt Building, Trumpington Street, Cambridge, United Kingdom, 2004.

Bascom, William R. "Four Functions of Folklore". The Journal of American Folklore, American Folklore Society, Vol.67, No.266 (Oct.-Dec,1954), 333-349,.

Bayissa Iffa. "Adaptation Culture and Changing Environment; The Case of the Gumuz of the Diddassa valley (Kamasi Zone) West Ethiopia," MA Thesis in

Social Anthropology, School of Graduate Studies, Addis Ababa University, 2001.

Ben-Amos, Dan. **"Context in Context" Theorizing Folklore**: *Toward New Perspectives on the Politics of Culture.* Western Folklore Society. 1993.

**____________ "Folklore in African Society"** Research in African Literatures, Indiana University Press, (Vol. 6, No. 2, 1975, pp. 165-198).

Biniyam Nishan.. "Natural Resource Competition and Inter- Ethnic Relations: The Case of Indigenous Berta and the Settlers in Bambasi Woreda of Benshangul Gumuz Regional State, Western Ethiopia" MA Thesis in Regional & Local Development Studies, School of Graduate Studies, Addis Ababa University. 2010.

Bloor, Michael, Jane Frankland, Michelle Thomas &Kate Robson. **Focus Groups In Social Research Sage.** Publications Ltd,6 Bonhill Street, London EC2A 4PU,2001

Bronner, Simon J. 2007. **The Meaning of Folklore**: *The analytical essays of Alan Dandes.* Utah: Utah State University Press

Carlsson, Fredrik, Gunnar Köhlin, Alemu Mekonnen, & Mahmud Yesuf.. **Are Agricultural Extension Packages What Ethiopian Farmers Want? A Stated Preference Analysis.** Working Papers in Economics no.172, Department of Economics, Göteborg University. 2005.

Cavallaro, Dani. **Critical and Cultural Theory.** *Thematic Variations*, London and New Brunswick: The Athlone Press. 2001.

Cumming, Bob. (Translator). **No Life without Roots (Culture and Development)**, London and New Jersey, Zed Books Ltd, 1990.

Dawson, Catherine. **Practical Research Methods.** *A user-friendly guide to mastering research techniques and projects.* New Delhi, UBS Publishers Distributers PVt.Ltd, 2002.

Federal Democratic Republic of Ethiopia Populatlon Census Commission. **Summary and Statistical Report of the 2007 Population and Housing Census Results. Addis Ababa, 2008.**

Fekade Azeze. ***A FOLKLORE GUIDEBOOK FOR ETHIOPIA: an introduction to definitions and categories, field methods, and resources for revitalizing folklore*** **(unpublished),** 2010.

Finnegan, Ruth. **Oral Traditions and the Verbal Arts.** *A Guide to Research Practices*, London and New York: Routledge, 1992.

Gardener, Katy and David Lewis. **Anthropology, Development and Post-modern Challenge.** London, Pluto Press, 1996.

Gebre Yntiso. **Culture and Devlopment in Africa: Building on Positive Cultural Practices.** Addis Ababa: UNFPA and African Union, 2005.

Geertz, Clifford. **The Interpretation of Cultures.** New York: Basic Books, Inc, Publishers. 1973.

Goldstein, Kenneth S. A Guide for Field Workers in Folklore. Detroite: Gale Research Company, 1974.

Green, A. Thomas, (ed). **FOLKLORE.** *An Encyclopedia of Beliefs, Customs, Tales, Music, and Art* Santa Barbara, California: ABC-CLIO, Inc, 1997.

Kahn, Herman. **The Confucian Ethic and Economic growth**. In Mitchell A. Seligson and Johan T. Passe-Smith, eds, Development and Underdevelopment: The Poltical Economy of Inequality, Boulder: Lynne Rienne,(1993).

Landes, David. "Culture Makes Almost All the Difference". Culture Maters. Basic Books, Perseus Boos Group.2000.

Lewandowski, Joseph D. **Interpreting Culture.** *Rethinking method and truth in social theory*. Lincoln and London: University of Nebraska Press. 2001.

Mbakogu, A.Ifeyinwa. "*Is There Really a Relationship Between Culture and Development?* "UNESCO's culture and development, 2004, *37-43.*

Mulualem Bassie Desta. "Institutional and Administrative Capacity for Development: The Case of Benshangul Gumuz National Reginald State: Efforts, Problems and Prospects" MA Thesis in Social Anthropology, School of Graduate Studies, Addis Ababa University, 2001.

Ojameruaye, Emmanuel. Culture and Economic Development in Urhoboland. Unpublished paper, 6th Annual Convention & meeting of the Urhoboland Society at PTI, Warri.Nigerya, October 20-23, 2005.

Okpewho, Isidore. **African Oral Litrature.** Indiana University Press, 1992.

Pathfinder International Ethiopia. **The Ethiopian Health Extension Program**. Ethiopia's Health Extension Program: Pathfinder International's Support 2003-2007, 2008.

Peet, Richard and Elaine Hartwick. **Theories of Development *Contentions, Arguments, Alternatives*** Second Edition, New York London, the Guil Ford Press, 2009.

Radcliffe, Sarah, A; (ed). **Culture and Development in a Globalizing World, *Geographies, Actors, and Paradigms***, London & New York, Rutledge, Taylor & Francis, 2006.

Schoemaker, George H. **The Emergence of Folklore in Everyday Life.** *A Field Guide and Source Book.* Bloomington, Indiana: Trickster Press. 1990.

Sims, Martha C. and Martine Stephens. **Living Folklore**: An Introduction to the Study of People and Their Traditions, Utah: Utah State University Press. 2005.

Spielman, J. David, Dawit Kelemwork, and Dawit Alemu. **Seed, Fertilizer, and Agricultural Extension in Ethiopia,** International Food Policy Research Institute, Development Strategy and Governance Division,– Ethiopia Strategy Support Program II, Ethiopia. 2011.

Storey, John. **Cultural Theory and Popular Culture an Introduction.** Fifth edition University of Sunderland,2009.

Schech, Susanne and Jane Haggis. **Culture and Development**: *A Critical Introduction*, USA, Blackwell Publishing, 2000.

Tariku Feyissa.. "The Berta Economy: An Ethnographic Study of Social Organization of Production in the Western Ethiopia Borderlands, MA Thesis in Social Anthropology, School of Graduate Studies, Addis Ababa University, 2002.

Tesfaye G. Mariam, "A Study of Major Themes in Jablawi Folktales" MA Thesis, Foreign Language and Literature Department, Addis Ababa University, 1990.

Triulzi, Alessandro.**Salt, Gold and Legitimacy. Prelude to the history of a no-man's land. Bela Shangul, Wallaga, Ethiopia** *(ca. 1800-1898)*. Naples: Istituto Universitario Orientale,1981.

UNESCO. **CONVENTION on the Protection and Promotion of the Diversity of Cultural Expressions.** Paris, 2005.

____________ **The 2009 UNESCO Framework for Cultural Statistics (FCS),** UNESCO Institute for Statistics, 2009

____________. **The Power of Culture for Development,** 2010.

____________. **Culture: a driver and an enabler of sustainable development. 2012**

Weber, Max. **The Protestant Ethic and the Spirit of Capitalism.** Oxford University Press, New York, 1930.

.

# አባሪዎች

## አባሪ አንድ የመረጃ  አቀባዮች ዝርዝር

### ቃለመጠይቅ የተደረገላቸው መረጃ አቀባዮች

| ተቁ | የመረጃ ሰጪው ስም | ቦታ | ፆታ | ዕድሜ | ቃለ መጠይቅ የተደረገበት ቀን | ሥራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አባ ሙሳ ባበከር | መቃዚን | ወ | 35 | 20/02/05 | የዕደ ጥበብ ባለሙያ፣ባህላዊ ሙዚቃ መሣሪያ ተጨዋች |
| 2 | አባ ቦርዲ አሻጉድ | ሸርቆሌ/አቤኔሬ | ወ | 49 | 28/02/05 | አርሶ አደር፣ ኔሪ፣ የባህል መድሃኒት አዋቂ |
| 3 | አባ አልታኢድ ሙሰኡድ | አቤኔሬ | ወ | 60 | 29/02/05 | ሸቀጣሸቀጥ ነጋዴ (ኔሪው ዘንድ ለህክምና የመጡ) |
| 4 | ወ/ሮ ኒመት ተማም | አቤኔሬ | ሴ | 35 | 29/02/05 | የቤት እመቤት(ኔሪው ዘንድ ልጅ ለማሳከም የመጡ) |
| 5 | አቶ አልመሃዲ ናስር | አቤኔሬ | ወ | 40 | 29/02/05 | አርሶ አደር (ኔሪው ዘንድ ለህክምና የመጡ) |
| 6 | ወ/ሮ አሻ ረመዳን | አቤኔሬ | ሴ | 45 | 29/02/05 | የቤት እመቤት (ኔሪው ዘንድ ለህክምና የመጡ) |

| ተቁ | የመረጃ ሰጪው ስም | ቦታ | ፆታ | ዕድሜ | ቃለ መጠይቅ የተደረገበት ቀን | ሥራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 7 | አባ ቤሎ አዲቴ | ሸርቆሌ/ ቱመጡቤ | ወ | 57 | 02/03/05 | አርሶ አደር፣ የባህል መድሃኒት አዋቂ |
| 8 | አቶ መንሱር ቤሎ | ሸርቆሌ/ቱመጡቤ | ወ | 28 | 02/03/05 | አርሶ አደር፣ የባህል መድሃኒት አዋቂ |
| 9 | ወ/ሮ ማሪያ ሀሰን | አሶሳ /ቆሽመንገል | ሴ | 20 | 20/08/06 | የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያ |
| 10 | ወ/ሮ ቢተሚና አልቃሲም | ሸርቆሌ | ሴ | 50 | 28/02/05 | የባህል ምግብ ሻጭ፣ ፅዳት ሠራተኛ፣ |
| 11 | አቶ ፋይዝ አቡድልቃድር | ሸርቆሌ | ወ | 28 | 13/03/05 | የባህል ዘፈን በክራር ተጨዋች |
| 12 | ተማሪ ሀሲና አህመድ | ሸርቆሌ | ሴ | 17 | 05/03/05 | ተማሪ |
| 13 | ወ/ሮ ሲቲና አደም፣ | አሶሳ ከተማ | ሴ | 38 | 22/03/05፣25/04/05 | በግል ሥራ የተሠማሩ |
| 14 | አቶ አልሀሰን አብዱራሂም ሆጀሌ | አሶሳ ከተማ | ወ | 66 | 15/03/05 | አርሶ አደርና በግላቸው |
| 15 | አባ አቶም ሙስጠፋ | አሶሳ ከተማ | ወ | 67 | 25/04/05 | ቀድሞ የክልሉ ፕሬዘዳንት የነበሩ፣አሁን በጡረታ ላይ ያሉና የግል ሥራ የሚሠሩ |
| 16 | ወጣት አብዱልናስር አልሀሰን | አሶሳ ከተማ | ወ | 26 | 16/03/05 | በበርታ ቋንቋ ላይ ጥናት የሚያደርግ |
| 17 | አባ አልሀሰን አህመድ | አሶሳ ከተማ | ወ | 60 | 23/02/03 | የአገር ሽማግሌ |
| 18 | አባ ሀሰን አጃሱሊ | መንጌ/ ጊዜ ጠሪያ | ወ | 80 | 11/04/05 | አርሶ አደር |

| ተቁ | የመረጃ ሰጪው ስም | ቦታ | ፆታ | ዕድሜ | ቃለ መጠይቅ የተደረገበት ቀን | ሥራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 19 | አባ አልኑር መሃመድ | መንጌ/ ጊዜ ጠሪያ | ወ | 35 | 11/04/05 | አርሶ አደር |
| 20 | አባ ናይል አሚር | መንጌ /ከሽፍ | ወ | 95 | 14/04/05 | የከበሮና የእምቢልታ አስቀማጭ |
| 21 | ኢብራሂም አደም | መንጌ /ከሽፍ | ወ | 38 | 14/04/05 | አርሶ አደር የቀበሌ ሊቀመንበር |
| 22 | አባ አልኑር አብደላ | መንጌ /ከሽፍ | ወ | 65 | 14/04/05 | አርሶ አደር |
| 23 | ኢብራሂም አልፈኪ | መንጌ /ከሽፍ | ወ | 38 | 14/04/05 | አርሶ አደር ከበሮ መቺ |
| 24 | እስማኤል አልሻሪ | መንጌ | ወ | 48 | 16/04/05 | ወርቅ ነጋዴ |
| 25 | አባ ሀሚድ ናስር | ከሽፍ | ወ | 80 | 14/04/05 | አርሶ አደር/የእምቢልታ አስቀማጭ |
| 26 | እማ አልመል ሀሰን | አቡራሙ | ሴ | 55 | 20/04/05 | አርሶ አደርና የጫጉላ ቤት ታዛቢ |
| 27 | እማ ፋጢማ አሊ | መንጌ | ሴ | 55 | 16/04/05 | አርሶ አደር/ተራች |
| 28 | እማ ሀጂጀ አልጣሂር | መንጌ | ሴ | 45 | 16/04/05 | በወርቅ ቁፋሮ የተሰማሩ/ ተራች |
| 29 | አቶ አብዱረሂም ሀሰን አልበዴ፣ | ባምባሲ | ወ | 60 | 22/03/05 | የግብርና ባለሙያ፣ 30 ዓመት በግብርና ባለሙያነት የሠሩ |
| 30 | ወ/ሮ ነፊሳ መሀመድ | ባምባሲ | ሴ | 28 | 22/03/05 | የወረዳው የባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ኃላፊ፣ |
| 31 | አቶ ኢብራሂም ቃሲም፣ | ባምባሲ | ወ | 32 | 29/03/05 | የወረዳዋ አስተዳዳሪ፣ |

| ተቁ | የመረጃ ሰጪው ስም | ቦታ | ፆታ | ዕድሜ | ቃለ መጠይቅ የተደረገበት ቀን | ሥራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 32 | አባ ሀሚድ ቶንኮሮ | ባምባሲ | ወ | 59 | 29/03/05 | አርሶ አደር፣የባህል ሙዚቃ ተጨዋች |
| 33 | አቶ አያሌው አሰፋ | ባምባሲ | ወ | 38 | 17/08/06 | የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያ |
| 34 | ወ/ሮ አስረሳሽ ዳኜ | አቡራሙ | ሴ | 28 | 20/04/05 | የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያ |

# የተተኳሪ ቡድን ውይይት ማመሳከሪያ

| ተቁ | የቀበሌው ስም | ዓይነት | ሴት | ወንድ | ጠቅላላ ብዛት | ቀን |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | መቃዚን1 | ሴቶች ብቻ የባህላዊ ዘፈን መሪ፣ ባለውቃቢዎች፣ የባህል መድሃኒተኞች የተሳተፉበት | 7 | - | 7 | 18/02/05 |
| 2 | መቃዚን2 | ወንድ አባላት ብቻ ያሉት አዛውንት የጎሳ መሪዎች፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ የእጅ ሙያተኞች፣ የባህል መድሃኒት አዋቂዎች የተሳተፉበት | - | 7 | 7 | 22/02/05 |
| 3 | አቡራሙ | የአገር ሽማግሌዎች፣በጫጉላ ቤት የሚታዘቡ አዛውንት ሴት፣የደቦ ሥራ መሪዎችና ዘፋኞች | 4 | 5 | 9 | 09/03/05 |
| 4 | ሸርቆሌ | የታወቁ ወጣት የባህል ሙዚቃ ተጨዋቾች፣ ተረት ነጋሪዎች፣ ባህላዊ ሥርዓቶች ላይ ማህበረሰቡን በመምራትና በማስተባበር የሚታወቁ ሰዎች የተካተቱበት | 2 | 6 | 8 | 04/04/05 |
| 5 | ቆሽመንገል | የአገር ሽማግሌዎች፣ባህላዊ ወጌሻዎች፣ የእጅ ሙያተኞች፣ አዛውንትና ወጣቶች የተሳተፉበት | 4 | 7 | 11 | 18/04/05 |

# የተተኳሪ ቡድን ውይይት ተሳታፊዎች ዝርዝር

| ተቁ | ስም | ጾታ | ዕድሜ | ስራ/ መተዳደሪያ | ቀበሌ | ወረዳ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ አብዱራሂም መሀመድ ዚዳን | ወ | 40 | የቀበሌ ሥራ አስኪያጅ | መቃዚን | ሸርቆሌ |
| 2 | አባ አደም አልኑር | ወ | 75 | አርሶ አደርና ባህላዊ ወጌሻ | መቃዚን | ሸርቆሌ |
| 3 | አባ ባበከር አልሀጂ | ወ | 68 | አርሶ አደርና የሀገር ሽማግሌ | መቃዚን | ሸርቆሌ |
| 4 | አባ አልዛክር አብዱል ከሪም | ወ | 61 | አርሶ አደር፣የሀገር ሽማግሌና የጋብቻ አማካሪ | መቃዚን | ሸርቆሌ |
| 5 | አባ አልኑር ባበከር | ወ | 55 | አርሶ አደርና የባህል ሙዚቃ መሣሪያ ተጨዋች | መቃዚን | ሸርቆሌ |
| 6 | አቶ ሙርሳል ሰኢድ | ወ | 47 | አርሶ አደርና የእርሻ መሣሪያዎች ሠራተኛ | መቃዚን | ሸርቆሌ |
| 7 | አባ ሀሚድ አብደላ | ወ | 64 | አርሶ አደር፣ የባህል ሙዚቃ መሣሪያ አምራች፣ ጠጋኝና ተጨዋች | መቃዚን | ሸርቆሌ |
| 8 | ወ/ሮ ሲኪና አህመድ | ሴ | 45 | የቤት እመቤት፣ ባህላዊ ዘፈን ተጨዋች፣ ባለዛር (አጉዞ) | መቃዚን | ሸርቆሌ |
| 9 | ወ/ሮ ሁስና ሙሃዲን | ሴ | 42 | የባህል መድሃኒት አዋቂና አዋላጅ፣ባለዛር | መቃዚን | ሸርቆሌ |
| 10 | ወ/ሮ ሀጂጀ አፉላሎ | ሴ | 55 | አርሶ አደር፣ባህላዊ ዘፈን ተጨዋች ፣ባለዛር | መቃዚን | ሸርቆሌ |

| ተቁ | ስም | ጾታ | ዕድሜ | ስራ/ መተዳደሪያ | ቀበሌ | ወረዳ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 11 | ወ/ሮ ሀጂጅ ሀሚድ | ሴ | 40 | አርሶ አደር፣ባህላዊ ዘፈን ተጨዋች | መቃዚን | ሸርቆሌ |
| 12 | ወ/ሮ ቢቱል አደም | ሴ | 45 | የባህል መድሃኒት አዋቂና ባለዛር | መቃዚን | ሸርቆሌ |
| 13 | ወ/ሮ አርጁና ረመዳን | ሴ | 43 | የልምድ አዋላጅ | መቃዚን | ሸርቆሌ |
| 14 | ወ/ሮ ትላቲ ሱልጣን | ሴ | 47 | ባህላዊ ሙዚቃ መሣሪያ ተጨዋች | መቃዚን | ሸርቆሌ |
| 15 | ወ/ሮ አስያ ረጃ | ሴ | 47 | እርሻና ወርቅ ቁፋሮ | ሸርቆሌ | ሸርቆሌ |
| 16 | ወ/ሮ አኒማ አደም | ሴ | 38 | በአነስተኛ ንግድ የሚተዳደሩ | ሸርቆሌ | ሸርቆሌ |
| 17 | አቶ ኢብዱልመንጠል ከሊፋ | ወ | 38 | የወረዳው ምክትል አስተዳዳሪ | ሸርቆሌ | ሸርቆሌ |
| 18 | አባ ሙሳ አልኑር | ወ | 77 | የሀገር ሽማግሌና ተራች | ሸርቆሌ | ሸርቆሌ |
| 19 | አባ አቡዱል ጀሊል ከድር | ወ | 65 | ተራችና የአገር ሽማግሌ | ሸርቆሌ | ሸርቆሌ |
| 20 | አባ መሃመድ አልሀሰን | ወ | 70 | ተራች | ሸርቆሌ | ሸርቆሌ |
| 21 | አባ ሙሳ አህመድ | ወ | 78 | ተራችና የአገር ሽማግሌ | ሸርቆሌ | ሸርቆሌ |
| 22 | አባ ሀሚድ ሙሳ | ወ | 68 | ተራችና የባህል መድሃኒት አዋቂ/ የባህል ሙዚቃ መሣሪያ ጠጋኝ | ሸርቆሌ | ሸርቆሌ |
| 23 | አቶ አብዱልጀሊል ከድር | ወ | 35 | አርሶ አደር | አቡራሙ | አሶሳ |
| 24 | አባ አልበሽር አህመድ | ወ | 56 | አርሶ አደርና የሀገር ሽማግሌ | አቡራሙ | |

| ተቁ | ስም | ጾታ | ዕድሜ | ስራ/ መተዳደሪያ | ቀበሌ | ወረዳ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 25 | ወ/ሮ ሶፍያ መሃመድ | ሴ | 55 | አርሶ አደር | አቡራሙ | |
| 26 | አባ ሀሚድ ናስር | ወ | 82 | አርሶ አደርና የሀገር ሽማግሌ | አቡራሙ | |
| 27 | ወ/ሮ አስያ ረጃ | ሴ | 50 | አርሶ አደር | አቡራሙ | |
| 28 | አቶ አልኑር ሙሳ | ወ | 52 | አርሶ አደር | አቡራሙ | |
| 29 | እማ በትዑ አደም | ሴ | 40 | አርሶ አደር | አቡራሙ | |
| 30 | አቶ ባበከር ኡመር | ወ | 26 | አርሶ አደር፣ አፈጉባኤ | አቡራሙ | |
| 31 | እማ ሀጂጀ ባበከር | ሴ | 40 | አርሶ አደር | አቡራሙ | |
| 32 | አባ አል ኢማም መሃመድ | ወ | 48 | አርሶ አደር | ቆሽመንገል | |
| 33 | እማ ኢንሹ አብዱራሂም | ሴ | 56 | አርሶ አደር | ቆሽመንገል | |
| 34 | ወ/ሮ ሀይራ ሀሚድ | ሴ | 35 | አርሶ አደር | ቆሽመንገል | |
| 35 | አባ አልማሃዲ አልሁሴን | ወ | 82 | አርሶ አደር፣ የአገር ሽማግሌ | ቆሽመንገል | |
| 36 | አባ ባበከር አልኑር | ወ | 55 | አርሶ አደር፣ | ቆሽመንገል | |
| 37 | አባ አልኑር መሃመድ | ወ | 50 | አርሶ አደር፣ | ቆሽመንገል | |
| 38 | ወ/ሮ ሳሚያ ባበከር | ሴ | 42 | አርሶ አደር | ቆሽመንገል | |

| ተቁ | ስም | ጾታ | ዕድሜ | ስራ/ መተዳደሪያ | ቀበሌ | ወረዳ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 39 | ወ/ር ሃጂጀ ሙስጠፋ | ሴ | 44 | አርሶ አደር | ቆሽመንገል | |
| 40 | አባ አልፈኪ አደም | ወ | 50 | አርሶ አደር | ቆሽመንገል | |
| 41 | አቶ ሰቢጥ አሊ | ወ | 37 | አርሶ አደር | ቆሽመንገል | |
| 42 | አባ ሀሰን ሙሳ | ወ | 62 | አርሶ አደር | ቆሽመንገል | |

# አባሪ ሁለት የበርታ ተረቶች

## ተረት አንድ

በድሮ ጊዜ አንድ ሰው ሴት ልጁን ይድርና በባልና ሚስቱ መካከል አለመግባባት በመፈጠሩ ሚስት ባሏን ጥላ ወደ አባቷ ቤት ትመለሳለች፡፡ አባት ልጁ ትዳሯን ጥላ ለምን እንደመጣች ሲጠይቃት ባሏ እንዳልተስማማት እና እንደተጣሉ ሁለተኛም ወደ እሱ እንደማትመለስ ትነግረዋለች፡፡

አባት ነገሩን በሚገባ ካዳመጠ በኋላ ልጂት ማምረሯንና ወደ ባሏም እንደማትመለስ በተረዳ ጊዜ ምንም አስተያየት ሳይሰጣት ተነስቶ ውሃ በአልብሪክ[46] ይዞ ወደ መፀዳጃ ቦታ ይወጣና ሆን ብሎ አልብሪኩን ሰብሮ እያዘነ ይመለሳል፡፡ ልጅት አባቷ በጣም አዝኖና ተክዞ ስታገኘው ምን እንደሆነ ትጠይቀዋለች፡፡ አባትም አልብሪኬ ተሰበረ እጅግ በጣም ያሳዝናል ብሎ ይማረራል፡፡ በዚህ ጊዜ ልጅት ነገሩን በማቃለል አልብሪክ ቢሰበር ሌላ ይተካል ይህን ያህል ማዘን የለብህም ብላ ለማፅናናት ትሞክራለች፤ አባት መልሶ የተሰበረው አልብሪኬ ሰው አይቶት የማያውቀውን ጉያየን ሁሉ የሚያውቅ ነበረ፤ ሌላ አዲስ ሊገዛ ይችላል፤ እኔን ያሳዘነኝ ግን ጉያየን ለማያውቀው አዲስ አልብሪክ ማሳየቴ ነው ብሎ ይመልስላታል፡፡ በዚህ ጊዜ የአባቷ ምሳሌ የተገለጠላት ልጅ እኔም ገመናየን ሁሉ የሚውቀውን ባሌን ዛሬ ብፈታ ነገ ሌላ ሰው ሊያይብኝ ነው ለካ ብላ ወደ ባሏ ተመለሰች ይባላል፡፡

[46]አልብሪክ ከሸክላ የሚሠራ በርታዎች ወ ደመፀዳጃ ሲሄዱ፣ ሊሰግዱ ሲሉ... ውሃ ይዘውበት የሚሄዱ ባህላዊ ዕቃ ሲሆን አሁን አሁን ከፕላስቲክ በተሠራ ተመሳሳይ ዕቃ እየተተካ ይገኛል፡፡

## ተረት ሁለት

በአንድ አካባቢ ሰዎች በጋራ ቤት እየሰሩ ሲበሉ ሲጠጡ ሲፈነጥዙ ቀጥለውም እነሱንም ገድለው እንደሚበሏቸው የተረዳው ቀበሮ «ወይ ዓለማችን !ወይ እድላችን!ወይ ሰው!» እያለ ሲያዝን ሲያለቅስ አንድ አሳማ ያገኘውና ሁሌ ሰውና ዓለምን ስታማርር እሰማሃለሁ ምን ቢያጋጥምህ ነው ብሎ ይጠይቀዋል፡፡ እስካሁን ሰውን እና ዓለምን አታውቅም? ይለዋል አላውቅም እሺ አሳይሃለሁ ብሎ ቀጠሮ ይሰጠዋል፡፡

አንድ ቀን እንደልማዳቸው ሰዎች ተሰብስበው ሲሠሩ ጠላ ሲጠጡ ይቆዩና ቀበሮ ለመግደል ወደ ደን ሲገቡ የአሳማ መንጋዎች ያገኙና የተቻላቸውን ያህል ገድለው ይበላሉ፡፡ ቀበሮ ተደብቆ ስለነበር እንደ ዕድል ሆኖ ያመለጠውን አሳማ ያገኘውና የሆነውን ሲጠይቀው ሰዎች አሳሞችን በሙሉ መጨፍጨፋቸውንና እሱንም አምላክ እንዳወጣው ይነግረዋል፡፡ ይ□ውልህ ሰው ማለት ይሄ ነው እኔም ወይ ሰው ወይ ዓለም እያልኩ የማዝነው ለዚህ ነው፡፡ በሰው ምክንያት በዓለም ላይ ሰላም የለም፤ እኛን ይጨፈጭፋሉ፤ እርስ በርስ ይጨፋጨፋሉ አካባቢያቸውን ይጨፈጭፋሉ ሀዘኔ ለዚህ ነው ብሎ አስተማረው ይባላል፡፡

## ተረት ሶስት

አንድ ደሃና አንድ ሃብታም በጉርብትና ይኖራሉ፡፡ ሃብታሙ በሬ ደሃው ላም ስላላቸው ተስማምተው በጋራ በተራ ያግዳሉ፡፡ አንድ ቀን በሃብታሙ ተራ ጊዜ የደሃው ላም ትወልዳለች፤ ሃብታሙም በሬዬ ወለደ ብሎ ጥጃውን ይዞ ይገባል፡፡ ደሃው እንዴት በሬ ይወልዳል? ፍረዱኝ ይልና ለሰዎች ቢያቀርብ ሁሉም ለሃብታሙ አዳልተው ልክ ነው የወለደው በሬው ነው ብለው

ይፈርዳሉ። ቀበሮ ብልሃተኛ ስለሆነ ሰውየው እንዲፈርድለት ይጠይቀዋል፤ ሰዎችም ፍርዱን ለመስማት ይሰበሰባሉ። ቀበሮም ነገሩን ያዳምጥና አሁን ጊዜ የለኝም አባቴ ስለወለደ ለማረስ እየሄድኩ ነው ብሎ ይመልስላቸዋል። ሰዎችም ግራ ተጋብተው እንዴት አባትህ ይወልዳል? ብለው ሲጠይቁት በሬ ከወለደ ምን ችግር አለው እስቲ እናንተስ በሬ እንዴት ይወለወዳል? በማለት በጥበብ ትክክለኛ ፍርድ ሰጠ ይባላል።

## ተረት አራት

በአንድ ሀገር ውስጥ አውሬ እያደነ የሚበላ ምስኪን ደሃ ነበረ። ከዕለታት አንድ ቀን ወጥመዱን አጥምዶ ሲጠብቅ ወጥመዱ እባብና አይጥ ይዞ ያገኛል። አይ እነዚህስ የእኔው ብጤ ሚስኪን ናቸው እነሱን አልበላም ብሎ ይለቃቸዋል። በዚህ ጊዜ ቸርነት ያደረገላቸውን ደሃ እንዴት እንደሚረዱት ሲመካከሩ አይጥ አይ እኔስ አቅም የለኝም አንተ ከቻልክ እንጂ ስትለው እባቡ አስማተኛ ስለነበር ለደሃው በርካታ ወርቅ አምጥቶ በሳጥን ሞላለት። ሰውየውም በሳጥን የሞላውን ወርቅ ሲያይ በጣም ይደሰትና ሳጥኑን እንዲያሽግለት ለአንድ አንጥረኛ ይነግረዋል። አንጥረኛው ይሄ ደሃ ምን የሚታሽግ ኖሮት ነው በብረት አሽግልኝ የሚለኝ ይልና እስቲ ውሃ አምጣልኝ ብሎ ይልከውና ከፍቶ ሲያይ ወርቅ የተሞላ ሳጥን ነው ሳያንገራግር ሳጥኑን ያሽግና ሄዶ ለሃገሩ ንጉስ ይነግራል። ንጉሱም ደሃው እስከ ወርቁ ተይዞ እንዲመጣ ያዝና አስከፍቶ ሲያይ ወርቅ መሆኑን ያረጋግጣል። ደሃውምእ እንዲገደል ያዛል።

በዚህ ጊዜ እባቡበ ንጉሱ ቤት ገብቶ በምታምር ሴት ልጁ ዙሪያ ተጠምጥሞ ፊቱን በፊቷ አቅጣጫ እንዳደረገ ልጅቷ ትጮሃለች፤ ጩ□ቱን ሰምተው ሲገቡ የንጉሱ ልጅ እባብ ተጠምጥሞባት ያገኛሉ፤ ምን እንደሚያደርጉ ተጨንቀው ሳለ እባቡ ደሃው ከነወርቁ ካልተለቀቀና የአንጥረኛው ልብ ካልመጣልኝ አለቅም

ስላለ ንጉሱ ይስማማና አንጥረኛውን አስገድሎ ጉበቱን ያቀርባል ደሃውን ግን ወርቁን የሰጠው እባቡ እንደሆነ ስለገባውና ለወርቁ ስለጓጓ እንዳይለቀው ልጁን ይድርለታል፡፡

ከብዙ ጊዜ በኋላ ንጉሱ ሲሞት ደሃው በቦታው ይነግሳል፡፡ ሌላ ጊዜ ንጉሱን የሚቀናቀን ሌላ ንጉስ ሊወረው ሲመጣ እባብ አይጥን ይጠራና ጉዳዩን ያዋያታል፡፡ አይጥም ዘመዶቿን አስተባብራ የተቀናቃኙ  ንጉስ ወታደሮች አድፍጠው በተኙበት ይገቡና የመሳሪያዎቻቸውን ማንገቻ ይበጣጥሳሉ፤ እባቡና ዘመዶቹም ነድፈው ይገድሏቸዋል፤ በዚህ ጊዜ ጩ□ት የሰሙ ሰዎች ሲመጡ ሬሳ በሬሳ ላይ ተነባብሮ ያገኛሉ፤ በጠላቶቻቸውም ሞት ይደሰታሉ፣ ንጉሱም በሰላም ኖረ ይባላል፡፡

ከዚህ የምንረዳው ነገር ለሰው ልጅ ስትረዳው ብዙ ጥሩ ነገር ታገኛለህ፤ መጥፎ ስታስብ ደግሞ የባሰ መጥፎ ነገር ይገጥምሃል፤ ደሃውና አንጥረኛው አብረው የበሉ ጎረቤታሞች ነበሩ ግን ክፉ በማሰቡ የራሱን ህይወት አጣ ፡፡ ስለዚህ ክፉ ነገር ከመስራት ደግ ነገር ለመስራት መፍጠን ጥሩ ነው፡፡

## ተረት አምስት

አንድ ሰው አንድ ጊዜ በዚህ ዓለም እኔ መድከም የለብኝም ከፈለገ ፈጣሪ ራሱ የሚያስፈልገኝን ባለሁበት ይስጠኝ ብሎ ይዋስናል፡፡ አንድ ቀን ወደ መንገድ ሲሄድ አንድ ጋን ወርቅ ያገኛል፤ አሁንም ይሄንን ወርቅ እኔ ተሸክሜ አልሄድም ፈጣሪ ራሱ ቤቴ ድረስ ይውሰድልኝ ይልና ወደ ቤቱ ይመለሳል፡፡ ወደ ቤቱ ይመለስና ለጎረቤቱ መንገድ ላይ አንድ ጋን ወርቅ አግኝቼ ነበር ከፈጣሪ ጋር ግን ስለተነጋገርኩ ከፈለገ ቤቴ ድረስ ያምጣት እንጂ እኔ አልሸከምም ብዬ ጥዬ መጣሁ ሲለው ጎረቤትየው በነገሩ በጣም ተደንቆና

በሰውየው ትዕቢት ተገርሞ ወርቅ ተገኝቶ ተጥሎ ይመጣል ጥጋበጫ እኔ ተሸክሜ አምጥቼ የራሴ አደርገዋለሁ ብሎ ወደ ተባለው ቦታ ሲሄድ ጋኑን ያገኘዋል ሲከፍተው ግን ወርቅ ሳይሆን እባብ ሞልቶበት ያገኘዋል፡፡ በጣም ይናደድና ይሄ ሰውዬ እኔ በእባብ ተነድፌ እንድሞት አይደል ወርቅ ነው ያለኝ ቆይ እሰራለታለሁ በሎ ይዝትና በሌሊት ሄዶ ጋኑን ተሸክሞ ያመጣና በሰውየው ቤት ላይ ወርውሮ እባቦቹ እንዳይነድፉት ሮጦ ይሄዳል፤ ሰውየው ጠዋት ሲነሳ ግቢው ወርቅ በወርቅ ሆኖ ያገኘዋል፡፡ ስለዚህ ሰው በአላህ ካመነ አዱኒያ ቤት ድረስ ይመጣለታል፡ መጣር መጋር አያስፈልግመ፡፡ የአንዱን ዕድልም ሌላው ሊበላው አይችልም ለተፈቀደለት ብቻ ነው፡፡

## ተረት ስድስት

በድሮ ጊዜ የእኛ ማህበረሰብ የሚተዳደረው በአደን ነበር፡፡ አንድ ቀን አንድ ሰው ምግቡን ለማደን ሲሄድ ወንዝ ዳር ሲደርስ ጎርፍ ነበረ እዚያ አይጥ ያገኛል፤ በዚህ ጊዜ ልጅ ስሌለኝ ይህቺን አይጥ ወስጄ ልጄ አደርጋታለሁ ብሎ ያስብና ወደ ቤቱ ይወስዳታል፡፡ አብረው መኖር ሲጀምሩ አይጥዋ ወደ ሰውነት ተቀይራ ሴት ልጅ ትሆናለች፡፡ ሰውየው አድን ሄዶ የሚያመጣውንም እያበሰለች አብረው እየተመገቡ መኖር ይጀምራሉ፡፡ በኋላ የልጅቷ ዕድሜ ወደ ሃያ ዓመት ሲደርስ አባቴ ማግባት እፈልጋለሁ ትለዋለች፡፡ ሰውየውም ከዚህ አካባቢ የምትፈልጊውን ምረጪ በደስታ እድርሻለሁ ይላታል፡፡ እሷም እኔ የምፈልገውማ ጠንካራ ሰው ነው፤ ጠንካራ ምንድነው ነፋስ ነው? ንፋስማ ጠንካራ አይደለም ተራራ ላይ ሲደርስ ራሱ ተራራ ይመልሰዋል፤ እሺ ውሃ ነው ጠንካራ ሁሉን ነገር ይዞ የሚሄድ? ውሃም ጠንካራ አይደለም ንፋስ አቅጣጫውን ያስቀይረዋል፤ ታዲያ ምንድነው ጠንካራ? ድንጋይ ነው? አይ እሱም ጠንካራ አይደም፤ ታዲያ ምነድነው የምትፈልጊ? ተራራና ድንጋዩን

ራሱን የሚሰብር ነው የምፈልገው፤ ታዲያ እሱ ምንድነው? አይጥ ነው አለችው። ወደ ምንድነው የተመለሰችው ወደ ራሷ፤ ስለዚህ ሰው ዘመዱን ዘሩን ነው የሚፈልገው ማለት ነው።

## ተረት ሰባት

አንድ ሰውየ ለአደን በረሃ ይወርዳል፤ በመንገድ ላይ ሁለት እባቦች ያገኛል፤ አንድ ትንሽና አንድ ትልቅ እባብ ናቸው፤ ግንኙነት እያደረጉ ነበር። በዚህ ጊዜ እንዴት ይሄ ትልቅ እባብ ከትንሹ ጋር ግንኙነት ያደርጋል ብሎ ሰውየው ተናደደ እናም ትንሹን እባብ ለመግደል ፈለገና ድንጋይ አምጥቶ ሲወረውር ትንሹ አመለጠ፤ ትልቋ ሴት ነበረች ድንጋዩ ያገኛታል፤ ሰውየው የፈለገውን ባለመግደሉ እየተናደደ ወደ ቤቱ ተመለሰ፤ በእባቦች የተመሰሉት ሰይጣኖች ናቸው። እባቧ ሰውየው ቤት ትሄድና በድንጋይ ወገቤን ሰብሯልና ዛሬ ነድፌ እገድለዋለሁ ብላ ስትጠብቅ ሰውየው እቤቱ ሄዶ ለሚስቱ እናንተ ሴቶች እኩያችሁን አታውቁም በመንገዴ ላይ አንድ ትልቅ እባብ ከትንሽ እባብ ጋር ግንኙነት ሲያደርግ አግኝቼው ወገቡን በድንጋይ ቆረጥኩት ይሄኔ ሚስቱን ትቶ ከትንሷ እባብ ጋር እየማገጠ ይሆናል። ሲል ትሰማዋለች እባቧም የሰውየው ሃሳብ ስለገባት ሳትነድፈው ጥላው ሄደች ይባላል። ይሄ የሚያስተምረው ማንም ወንድ ከሚስቱ በስተቀር ሌላ ሴት ቤት መግባት እንደሌለበት ነው።

## ተረት ስምንት

በዱሮ ጊዜ ሶስት ወንድማማቾችና አንድ እህታቸው በበረሃ ይኖሩ ነበር አባታቸውና እናታቸው ሞተዋል። ለምግባችንም ሆነ ለኑሮ የሚያስፈልገንን ነገር ለማግኘት ወደ ሌላ አካባቢ ሄደን መሥራት ይኖርብናል ብለው

ተስማሙ:: ነገር ግን እታችንን ለማን ጥለናት እንሄዳለን? ተባባሉ እና አንድ ትልቅ ወርካ ስር ጉድጓድ ቆፍረው አመቻቹና ለሶስትና ለአራት ወራት እስከሚመለሱ ድረስ የሚበቃትን ምግብ አስገብተው ዘጉባትና የእኛ ግመሎች መጥተው ከጉድጓዱ ላይ ሲሸኑና በጆሮሽ ውሃው ከገባ ምልክት ይሁንሽ ያኔ ትወጫላሽ አለዚያ ግን እንዳትወጪ ብለው አስጠንቅቀው ተሰናብተዋት ይሄዳሉ::

አንድ ቀን የሌላ አካባቢ ንጉስ ለአደን ወደ አካባቢው መጥቶ ኖሮ እዚያ ዛፍ ስር ያርፋሉ፤ በዚህ ጊዜ የንጉሱ ግመሎች በጉድጓዱ አፍ ላይ ይሸናሉ፤ ልጂቷም ወንድሞቿ የመጡ መስሏት በር ከፍታ ስትወጣ ንጉሱ ሠይጣን መስሎት ይሮጥና ተረጋግተው ሲያዩ የምታምር ልጅ ናት ያቀርቡና ሲያነጋግሯት ታሪኩን ትናገራለች ንጉሱም ስለወደዳት ግንኙነት ያደርግና ትቷት ይሄዳሉ:: ልጅቷም በዚያ ምክንያት ታረግዝና እዚያው ጉድጓድ ውስጥ ትወልዳለች:: ወንድሞቿ ልጁ ከተወለደ በኋላ ሲመጡ ባዩት ነገር በጣም ተደናገጡና እኛ እህታችንን ብቻሽን ጥለንሽ ሄደን እንዴት ሁለት ሆነሽ ጠበቀሽን? ቢሏት የሆነውን ሁሉ ትነግራቸዋለች:: እነሱ ግን ሊያምኗት አልቻሉም:: እኛ ስንሄድላት እየወጣች ትማግጣለች ማለት ነው ስለዚህ መገደል አለባት ብለው ይወስናሉ:: ታናሸየው ወንድማቸው ግን ጉዳዩን ሳናጣራ እርምጃ ለመውሰድ አንቸኩል እኔ ሄጄ አጣርቼ እመጣለሁ ብሎ ይሄዳል::

መንገድ ላይ አንድ ሽማግሌ ያገኝና በዚህ አካባቢ ለአደን አዘወትሮ የሚወጣ ሰው ማን ነው ብሎ ሲጠይቀው የአገሩ ንጉስ እንደሆነ ይነግረዋል:: ልጁም የሆነውን ሁሉ ይነግረወና እንዴት አድርጎ ንጉሱ ቤት መግባት እንደሚችል ምክር ይጠይቀዋል:: ሽማግሌውም ብልሃተኛ ስለነበረ ንጉሱ ማንም ሰው የማያያት አንዲት ሴት ልጅ አለችው ከደንገጥሮቿ በስተቀር እሷ ጋ ቀርቦ የሚያውቅ ሰው የለም:: ለንጉሱ አንድ ውለታ ስለዋልኩለት አንተን በስልቻ

አድርጌ እደብቅና አይጥ ስላስቸገረኝ በአደራ አኑርልኝ እለዋለሁ እምቢ አይለኝም። እዚያ ከገባህ በኋላ የምታደርገውን አስብበት አለውና ሰውየውን በስልጫ አስሮ ከንጉሱ ቤት በአደራ ያስቀምጠዋል። አደራው የተቀመጠው ከንጉሱ ሴት ልጅ ቤት ስለሆነ ልጁ ቀስ ብሎ እየወጣ ከንጉሱ ልጅ ጋር ፍቅር ይጀምርና ያስረግዛታል። አባቷ በረሃ ላይ ያደረገውን ሁሉም ይነግራታል። ከዚህ በኋላ ሽማግሌው ወደ ንጉሱ ይቀርብና በአደራ ያስቀመጥኩትን ዕቃ ስለምፈልገው መልስልኝ ይለውና ይወስደዋል። በዚህ ጊዜ የንጉሱ ልጅ ደንገጡር ወደንጉሱ ቀርባ ንጉስ ሆይ ልጅቷ ምግብ በደንብ አትበላም፣ ሰውነቷም ተለዋውጧል፤ እኔ እንዳጥባትና እንዳለብሳትም አትፈቅድም ተቸግሬለሁ ብላ ስትነግረው መድሃኒት አዋቂዎች ያመጣና ሲያስመረምራት እርጉዝ መሆኗ ይታወቃል። በዚህ ጊዜ ንጉሱ ይደነግጥና ከአንዲት ደንገጡር በስተቀር እዚህ ቤት የሚገባ ወንድ የለም ከማን አረገዥሽው ብሎ ሲያፋጥጣት በአደራ ያስቀመጥከው የሽማግሌው ዕቃ ነው ትለዋለች። ሽማግሌው ተይዞ እንዲመጣ ያዛል። ሽማግሌው በሰራው ጥፋት መቀጣጫ እንዲሆን በህዝብ ፊት ሊገድለው ህዝቡ ሁሉ እንዲጠራ ያዛል።

ከዚያ በኋላ ሽማግሌው አንገቱ ወደሚቀላበት ስፍራ ይወሰድና ጥፋቱ ለህዝቡ ይነገራል። በዚህ ጊዜም የንጉሱ ልጅ ፍርዱ ከመፈፀሙ በፊት የምትናገረው እንዳላት ታስታወቅና እንድትናገር ሲፈቀድላት አባቷ ለአደን ወጥቶ የሠራውን ሁሉ ትዘከዝክና ጥፋተኛ ስለሆነ ከሽማግላ በፊጽ መገደል ያለበት እሱ እንደሆነ ታስረዳለች። በዚህ ጊዜ እሷን ያስረገዛት ልጅ እህቱን እስከ ልጇ ይዞ ይቀርባል ህፃኑም ሲታይ ቁርጥ ንጉሱን ስለሚመስል ህዝቡን ይቅርታ ጠይቆ ሽማግሌውንም በነፃ ያሰናብታል። እሱም የልጁን እናት ወንድሟም የንጉሱን ልጅ አግብተው ኖሩ ይባላል።

## ተረት ዘጠኝ

በድሮ ጊዜ አንደኛው ሃብታም ሌላኛው ደሃ የሆኑ ሁለት ወንድማማቾች ነበሩ። ሃብታሙ እጅግ ስስታም ደሃው ደግሞ ያለውን የሚያካፍል ቸር ነበሩ። ከእለታት አንድ ቀን ሦስት ሰዎች ደሃው ቤት መጥተው "እባካችሁ አሳድሩን መንገደኞች ነን" ብለው ይጠይቁታል። በጣም ይደነግጥና "እንደምታዩት ቤቴ ጠባብ ነው ለእናንተ አይበቃችሁም፤ ይልቅ የወንድሜ ቤት ሰፊ ስለሆነ እሱ ጋ ሄዳችሁ ብትጠይቁት ይሻላል" ብሎ ቤቱን ያሳያቸዋል። እንግዶቹም ወደዚያው አምርተው "አሳድረን: ይሉታል። ወንድሙ ግን "ማሳደሪያ የለኝም" ብሎ ያባርራቸዋል። እንግዶቹም ወደ ደሃው ቤት ይመለሱና "ግድየለም ከውጪ በርህ ላይም ቢሆን እናድራለን አንተ ብቻ ፍቀድልን" ሲሉት ወደ ሚስቱ ይገባና ጉዳዩን ያዋያታል። እሷም "አትጨነቅ እኛ መኝታ ላይ ያድራሉ ለሚበሉትም አትሳቀቅ የእኛን እራት ይበላሉ፤ለነገ አላህ ያውቅልናል።" ብላ ታፅናናውና ለሰዎቹ ያላቸውን አስተናግደው መኝታቸውን በመልቀቅ ያስተኟቸውና እነሱ ወጥተው ከውጪ ያድራሉ። ባልና ሚስቱ በጧት ተነስተው እንግዶቹን ለመሸኘት በሩን ሲከፍቱ እንግዶቹ ሄደው ቤታቸው ግን በወርቅ ተሞልቶ አገኙት ይባላል።

## ተረት አሥር

አዎር እሚባል ሰው አለ በተረቶች ኮሚክ ነው ኮሚክ የሆነ ሰው በእኛ በጥንቸል ይወከላል፤ ጥንቸል መልኳ አስቂኝ ስለሆነ።

አሳት አዎር ይባላል ፈስ በስልቻ ይጠራቅምና ሀብታም ቤት ይገባና ይሄን እቃ በአደራ አስቀምጡልኝ ይልና እዚያ ይስተናገዳል፤ አድሮ በማግስቱ ሊሄድ ሲል ያንን በአደራ ያስቀመጠውን ስልቻ ያስመጣና ጥሩ መስተንግዶ

ስላደረጋችሁልኝ በስልቻው ውስጥ ያለውን ስጦታ ሰጥቻችኋለሁ ግን የምትከፍቱት እኔ ከሄድኩ በኋላ ነው ብሏቸው ይሄዳል። እነሱም ካላቸው ሁሉ ነገር በስጦታ ሰጥተው ይሸኙታል፤ እንዳለው ከራቀ በኋላ ሲከፍቱት ሁሉም ፌስ በፌስ ሆኑ ይባላል።

የበቀደሙ አሆር ፌስ አጠራቅሞ ወጣ፤ እዛ ፍቱት ያላቸው፤ እሱ ጋ ብዙ ነገሮች ትዝ አሉኝ። እንደገና በቀደም የረሳኋቸው እና አሆር ንጉሱ ቤት ሲገባ አልሞ ነው የሄደው። ንጉሱ ቤት እንደገባ "አሜ አሆር!" ይሉታል አጎት አሆር ማለት ነው። አልጋ ቆንጆ ፍራሽ ተነጥፎለት ቁጭ በል ይሉታል። እዚህ ፍራሽ ላይ እኔ አልቀመጥም። የት ነው ታዲያ መቀመጥ እምትፈልገው ? አይ አጎቴ ዶሮች ናቸው፤ ዶሮች እሚቀመጡበት ቦታ ነው እምቀመጠው። ሄዶ ዶሮች ቦታ ይቀመጣል፤ አሁን ተመቸው እሚጠጣ ውሃ ሲሰጡት እኔ ሰው በሚጠጣበት አልጠጣም ዶሮች በሚጠጡበት ነው ይላል። በዚያው ይሰጡታል፤ ምግብም ዶሮች በሚበሉበት ይሰጠዋል፤ ሲመሽ መኝታውንም ዶሮች ቆጥ ላይ ይወጣል፤ ሌሊት አንዱን ዶሮ ይዞ ያስርና ቋቅ ሲል ምነው አጎት አሆር? ሲሉት አይ አክስቴ ዶሮ ጠጋ በይ ስላት እምቢ ስላለችኝ ነው። አሁንም አውራውን ሲያንቅ እና ሲጮህ ምነው? ሲሉት አጎቴ አውራ ዶሮ ጠጋ በል ስለው እምቢ ስላለኝ ነው ይላል። በኋላ ዶሮቹን ይሰበስብና ሌሊት ውልቅ ብሎ ይጠፋል።

እሱ ከሄደ በኋላ አስቀምጡልኝ ያለውን የአደራ ዕቃ ሲፈቱ በፌስ ይጨርሳቸዋል። ንጉሱ ተከተሉት ብሎ ወታደር ያዛል። ይከተሉታል፤ በዚህ ወጣ፣ በዚህ ወረደ፣ መዓት ጣጣ ነው በዚህ ውስጥ ያለው። እና ያባርሩታል፤ ሄዶ ዋሻ ውስጥ ይገባና ሊያመልጥ ሲል እግሩን ይይዙታል። ሲጎቱቱት እሱ እግሬ አይደለም ዝም ብላችሁ አትድከሙ ሲላቸው ይለቁትና ወጣ ያለውን የእንጨት ሥር ሲጎትቱ ኡ! ኡ! ብሎ ይጮሃል ውሸቱን፤ ሰዎቹ ዕውነት መስሏቸው ሲጎትት ሥሩ ይበጠስና ይሞታሉ።

ከንጉሱ ቤት የሠረቃቸውን ብዙ ነገሮች ይዞ ይሠወርና መኖር ይጀምራል። ከዚያም ቦለቄ ይዘራል፤ ቦለቄውን ሲጠብቅ ሲያሽት ቆቆች ይመጡና ለመብላት ሲሞክሩ ይይዛቸዋል፤ የበላችሁትን ቶሎ ብላችሁ መልሱ አለዚያ እገድላችኋለሁ ሲላቸው ዕንቁላላቸውን ይሰጡታል፤ ዕንቁላሉን ወስዶ ቀጭኔዎች እሚመላለሱበት መንገድ ላይ ያደርገዋል፤ ቀጭኔዎች ሲመጡ አንድ የማያይ ዓይነ ስውር ቀጭኔ ይመጣና ዕንቁላሉን ይረግጠዋል። ክፈለኝ ብሎ ሲይዘው ከአንገቱ ላይ አንድ ሁለት ጅማት አውጥቶ ይሠጠዋል። እሱን ወስዶ ሲሄድ አሞራ መጥቶ ይነጥቀዋል።

እንደዚህ እንደዚህ ሲል አሞራው መጥረቢያ አምጥታ ትከፍላለች። ያንን መጥረቢያ ይዞ ሲሄድ ሰዎች ሰው ሞቶባቸው ለመቅበር እንጨት መቁረጫ አጥተው ሲቸገሩ ይደርሳል። ይሄው እኔ እያለሁ ለምን ትቸገራላችሁ? ብሎ መጥረቢያውን ይሰጣቸዋል። እንጨት ሲቆርጡበት መጥረቢያው ይሠበርባቸዋል። ቶሎ ብላችሁ ክፈሉኝ አለዚያ ከዚህ ንቅንቅ የለም ይላቸዋል፤ እኛ ምንም የለንም ከፈለግህ ሬሳውን ይዘህ ሂድ ይሉታል። እሬሳውን ይዞ ይሄዳል፤ ወስዶ ወንዝ ዳር ያስቀምጠዋል። ወንዝ ዳር ሲያስቀምጥ ምን እንደተፈጠረ እዚያ ተረሳኝ ተያይዘው ይግቡ?... በቃ ሄደ በጣም ቆንጆ ነገር ነው ተረሳኝ ነብር ጋር የሚገናኙበት ቦታ አለ፤ ከእረኞች ጋር የሚገናኙበት ቦታ አለ የሰጡት ነገር አለ። ከዚያ ከሬሳው ለውጥ እና ወተት ይፈልጋል። ምግቡን በወተት ለመብላት የሆነ ነገር ይላቸዋል። ላም ይሰጡታል ለወተቱ ማለት ነው በዚያው ሲያስጨንቅ እንደገና ፍየል ይሰጡታል፤ የሆነ ቦታ ላይ ነብር መጥቶ ፍየሏን ይይዛል፤ አሁን ከነብር ጋር ነው ድርድሩ ነብር ይዞ እንትን ሲል ያታልላቸዋል። ብረት እሳት ውስጥ አስቀምጦ በጣም ሲቃጠል ያንን የፀሐይ ጥልቀት እይ እስቲ ይለውና ወደ ፀሐይዋ አፉን ከፍቶ ሲመለከት ያንን የጋለ ብረት አፉ ውስጥ ይከታል፤ ያሸንፋቸዋል።

## ተረት አሥራ አንድ

ሌላ አንድ ንጉስ ነበረ ንጉሱ እንዲወለድለት የሚፈልገው ወንድ ልጅ ብቻ ነበር። ሴት ልጅ አይፈልግም። አዋጅ አውጥቶ ነበር እና ከሚስቶቹ መካከል አንዷ አርግዛ ስትወልድ ሴት ናት። እና እንዳትገደልባት ደበቃ አሰደገቻት፤ ከሌላ ሚስቱ የሚወልደው ወንድ ልጅ ደግሞ አለው፤ ያቺ ለብቻዋ ተደብቃ ንጉሱ አባቷ ሳይሰማ ያደገችው ታድጋለች። ሰው ሳያያት በእናቷና በተወሰኑ ሰዎች ነው የምታድገው፤ በጣም ቆንጆ ልጅ ሆና ታድጋለች። በጣም እሷ ስትወጣ ፀሐይ ትጠፋለች ይባላል ከቁንጅናዋ የተነሳ።

አጋጣሚ አንድ ቀን ያ ወንድሟ ያያታል። ወዲያውኑ እንዳያት ይወዳታል። ካላገባኋት ብሎ ያብዳል፤ አባትየው የማጪያ ሥርዓት እንዲዘጋጅ ያዛል። ይህን ስታውቅ መስኮት ትሰብርና ትጠፋለች። ወንድሜ እንዴት ያገባኛል ብላ እሷ እናቷ ስለነገረቻት ወንድሟ መሆኑን ታውቃለች። ስለዚህ ጠፋች ፤ በዚህ መሃል የሽማግሌ ቆዳ መልበስ ትፈልጋለች እንዳትታወቅ፤ ስትሄድ፣ ስትሄድ፣ ሽትሄድ ሽማግሌ ታገኛለች። አባ፣ ሽማግሌ እንዴት ነው ቆዳው የሚወጣው? ትለዋለች። ቀላል ነው የግራር እሾህ አሽተሽ ጭንቅላቱ ላይ ብታደርጊ ወዲያው ነው ሙሽልቅ የሚለው ይላታል። ወዲያው እንዳላት ስታደርግ ሙትት ሲል ቆዳውን ላጥ አድርጋ አወጣችና ለራሷ ለበሰች። ከዚያ ሽማግሌ መስላ ትጓዛለች። ስትሄድ፣ ስትሄድ ባህር ያጋጥማታል አንቺ ባህር ሆይ እንዴት ነው አንቺን መሻገር የሚቻለው? በያዝከው በትር ብትመታኝ ለሁለት እከፈላለሁ። ባህሩን መታ ተሻገረችና ሌላ አገር ገባች። ሌላ ንጉስ ያለበት። ዛፍ ላይ ወጥታ ተደበቀች። ከዛፉ ሥር ውሃ አለ። የንጉሱ አሽከሮች ውሃው ጋ ሲመጡ ውሃው ውስጥ ዛፍ ላይ የተቀመጠ ሰው ያያሉ፤ ዛፉ ላይ ለመውጣት በጣም አስቸጋሪ ነበር እሷ ስትወጣ በመዝሙር ዛፌ ዛፌ የአያቴ ዛፍ ተነሺ ዝቅ ዝቅ በይልኝ ብላ ዝቅ ሲልላት ወጣችና ከፍ ከፍ በይ ስትል ከፍ ብሎላት ነው የወጣችው። አሽከሮቹ መጥተው ሲያዩ ውሃው ውስጥ ጥላ ያያሉ። ሰው

ያያሉ፤ ውረድ ይሉታል፤ አልወርድም፤ እንግዳው ዛፉን እንቆርጠዋለን፤ መቁረጥ ሲጀምሩ ዝቅ ዝቅ በይልኝ ብላ ስትዘምር ዝቅ አለ። ይዘዋት ሄዱ ወደ ቤተመንግስት እዚያ ሲሄድ ይሄን ሽማግሌ ከየት አመጣችሁ? ምንድነው እምትችለው ሥራ? ይላል ንጉሱ፤ አይ እኔ ዶሮ መጠበቅ እንጂ ሌላ አልችልም ትላለች።

ዶሮ እንድትጠብቅ ያደርጋሉ፤ ዶሮ እየጠበቀች ብቻዋን ስትሆን ሰው በሌለ ጊዜ ያንን የተሸፈነችበትን የሽማግሌ ቆዳ ታወጣና፣ ጌጠዋን ታደርግና፣ ማንም ሰው ሳያይ ራሷ ብቻዋን ትደሰታለች። የሆነ ምልክት ስታይ ወዲያውኑ ቆዳውን ለብሳ ሽማግሌ ሆና ቁጭ ትላለች። አንድ ጊዜ ዶሮቹን ውሃ ለማጠጣት ወንዝ ዳር ኩሬ የሆነ ነገር አለ እዚያ ይዛ ትሄድና አንድ ዱዳ ሰውዬ ደግሞ እዚያው ንጉሱ ቤት አለ እሱን ታምነዋለች መናገር ስለማይችል አልፈራችውም፡፤ እዚያ ውሃው ጋ ሲደርሱ ያንን የሽማግሌ ቆዳ አውጥታ ገላዋን ታጥባ ጌጦቿን አደረገች፤ ስትዝናና ያ ዱዳ ያይና ይገረማል። ማታ ሲገቡ እንኮይ በጣም የበሰለ እንኮይ በጣም ደስ የሚል እንኮይ ለቅሞ መጣ የተለያየ ዓይነት ያልበሰለ፣ ጮርቃ፣ መሀሉ ላይ በጣም የበሰለ ቢጫ ደስ የሚል አመጣና ለንጉሱ አቀረበ። ምንድነው? ሲባል ያልበሰለውን ጣለ እና የበሰለውን ሰጠው። ምንድነው እሚለኝ ይሄ ከአንተ ጋር የዋለው ዱዳ? አይ በብረት እሳት ውስጥ አርገህ ጭንቅላቴን አቃጥለኝ ነው እሚልህ፤ እሷ እንዳለች ብረት አግለው ሲተኩሱት ጮኸ ዱዳው በኋላ ይሸሻል። ይታመምና ይድናል። እንደገና ደግሞ እንደገና እንዲሁ ያኑኑ እንኮይ ያመጣል በኋላ ይህን ዱዳ ለምን እንሰቃየለዋን? ውሏቸውን በድብቅ ክትትል አድርጉ ብሎ አዘዘ ንጉሱ። ክትትል ተደረገ ልክ እንደለመደችው የሽማግሌ ቆዳውን አውጥታ ስትጨፍር የአባቷን ዝና እያወደሰች ብቻዋን ትጨፍራለች። ያንን ሁሉ አዩ ስለላ የሄዱት አሽከሮች አዩና ተመለሱ ምንም ሳይታዩ እቤት ሲገቡ ለንጉሱ ነገሩ፤ በነገታው ዛሬ ከእኔ ጋራ ነው እምትውለው አባባ ይላታል። ለምን? አይ

ገበጣ እንጫወታለን። እሺ አለ አሁን ገበጣ ጀመሩ በጣም ሃይለኛ ሆነ ሽማግሌው ገበጣ ጨዋታ ታሸንፈዋለች ውርርድ አለ እንግዲህ የተሸነፈ ቆዳው ይተረተራል የሚል ስላልቻላት ወዲያ ወዲህ ስትል እየሰረቀባት አሸነፋት ወዲያው ቆዳዋ ሲተረተር እሷ ወጣች፤ አግብቷት በሰላም ኖሩ ይባላል ።

## ተረት አሥራ ሁለት

አንድ ጥበበኛ ሰውዬ ነበር። ይሄ ጥበበኛ ሰውዬ አራዊትን ያስተዳድራል። ሚስቱ አንድ ቀን ሌሊት ተነስታ በአዕዋፍ ላባ የተከደነ ቤት ሥራልኝ ትለዋለች። ጉጉት ደግሞ ማታ ማታ አይታችሁ እንደሆን ቤት ላይ ይቀመጣል። የሚስትየዋን ጥያቄ ይሰማል። ባልየው ይሄ ምን ችግር አለው ነገ ከነገ ወዲያ ሊሠራ ይችላል ብሎ ቃል ገባላት ለእሷ።

ከዚያ በኋላ እንግዲህ አጠቃላይ አዕዋፍ ተጠሩ ማለት ነው። ከዚያ ጉጉት ሳይመጣ ቀረ በስብሰባው ላይ ሰውየው ጉጉት የታለ? ለምንድነው የማላየው? ብሎ ይጠይቃል። ለምን እንዳልተገኘ ልትነግሩኝ ይገባል። ብሎ ሲጠይቅ ጉጉት ይመጣል። አንተ የት ነበርክ? ብሎ ሲጠይቀው አይ እኔ እኮ ሁለት ነገሮችን አሰብ ነበርኩ። እዚያ ምንድነው ስታስብ የነበረው? ሲለው ከሞተ ሰውና አሁን በሕይወት ካለ ሰው የትኛው ይበልጣል? ከቀንና ከሌሊት ደግሞ የትኛው ይረዝማል? እነዚህን ሁለት ነገሮች ሳስብ ነበርኩ፤ ለዚያ ነው ወደ ኋላ የቀረሁት ሳልመጣ ይለዋል። እሺ ምን አገኘህ አሁን ከሞተ ሰው እና በሕይወት ካለው ሰው የትኛው ነው የሚበልጠው? ይለዋል። በሚስቶቻቸው ከሚመሩ ሰዎች የሞተ ሰው ይበልጣል። እሺ ከቀንና ከሌሊትስ የትኛው ነው የሚረዝመው? ሲለው የሌሊት ጨዋታ ከተጨመረበት ሌሊት ርዝማኔ ያንሳል አለው። እንግዲህ ጉጉት አዕዋፎችን ለማዳን ፈልጎ ነው። ከዚያ በኋላ ሰውየው ቁጭ አለና ታዲያ እኔ አሁን እነኚህ አዕዋፍን ላባቸውን ነቅዬ ቤት እንድሠራ

ያስተላለፈልኝ በሌሊት ሚስቴ ነች፤ እኔ ከሞቱ ሰዎች ውስጥ ነኝ ማለት ነኝ ብሎ አዕዋፍን ማረ ይባላል፡፡

## ተረት አሥራ ሦስት

አንድ ሰውዬ ብዙ ከብቶች አሉት፡፡ ከከብቶቹ መካከል አንድ አመፀኛ በሬ አለ፡፡ ሰውየው በከብቶቹ በሬ ምክንያት ሁልጊዜ ከጎረቤቶች ጋር ይጣላል፡፡ ተጨነቀ ምን ይሻለኛል? ማነው ይህን የሚሠራ? ብሎ ተጨነቀ፡፡ ከብቶቹን በረት ከዘጋ በኂላ ሁልጊዜ በረቱን ተሰብሮ የሰዎች እህል ተበልቶ ያድራል፡፡ ሁልጊዜ አሁን አንድ ነገር ማድረግ አለብኝ ብሎ አንድ በረት ነበር ሁለት አድርጎ ከብቶቹንም ለሁለት ከፍሎ አሳደራቸው፡፡ አሁን አንዱ በረት ሲሰበር አንደኛው በሰላም አደረ፤ ቀጥሎ የተሰበረውን በረት እንደገና ለሁለት ከፈለው፤ አሁንም አንዱ ሰላም አደረ ሌላው ተሰበረ፤ እያለ እያለ አመፀኛውን በሬ አገኘ፤ አመፀኛውን በሬ ባገኘ ጊዜ አንተ ነህ ከሰው ጋር የምታጣላኝ ስለዚህ መታረድ አለብህ ብሎ ወሰነ፡፡

በሬው ይታረድና ሰዎች ቅርጫ በሚደረግበት ጊዜ አምሳም፣ ሰላሳም፣ ብር የከፈለ አለ፤ እንደከፈለው ብር መጠን ይከፋፈላል፡፡ ሰውየው ግን ሲያርደው በነፃ ለማከፋፈል ነበርና ተከፋፍሎ ሲያልቅ በቃ በነፃ ውሰዱ ብሩን ትቸላችኂለሁ ይላል፡፡ ነፃ ከሆነማ ለምን እኔ ይህቺን ብቻ እወስዳለሁ? ብለው ሰዎች እርስ በርሳቸው ይደባደባሉ፡፡ ፖሊስ ይመጣል፤ ከዚያ የማነው በሬው ተብሎ ሰውየው ይታሰራል፤ ትንሽ ከታሰረ በኂላ ተፈታ፡፡

እሱ ስጋውንም አልወሰደም ቆዳውን ወስዶ የድሮ ከበርቴ ሰዎች ገንዘብ አያወጡም ቆዳውን ወስዶ እቤት እንዲደርቅ ያስቀምጠዋል፡፡ እዚያ ውስጥ አይጦች ይራባሉ፡፡ ሰውየው ቆዳውን ወስዶ ለመሸጥ ይፈልግና ወደ ገበያ ይዞ ይሄዳል፡፡ አይጦቹ አሉ እዚያ ውስጥ፤ ገበያው ሲደራና ሰው ሲበዛ አይጦቹ ፀሐይ ሲሞቃቸው እየወጡ ሲሮጡ ገበያው ተበታተነ፤ ረብሻ ይፈጠራል፡፡

እረብሻ ሲፈጠር የማነው ይሄ ቆዳ? የእሱ ነው። እንደገና ተደበደበ። ይዘህ ጥፋ ተባለ። አሁን ቆዳውን እንደገና ይዞ ይሄ ነገር በሕይወት እያለም ሲያስቸግረኝ ኖረ አሁንም አልተወኝም አለና ባህር ውስጥ መጣል አለብኝ ይልና ይዞ ይሄዳል። ከትከሻው ላይ አውርዶ ወደ ኋላ እጥላለሁ ሲል የደረቀው ጅራት አንገቱን ተልፎ ይዞት ወደ ባህሩ ውስጥ ገባ ይባላል።

## ተረት አሥራ አራት

አንድ ሰውዬ ነበር። ማሳ አለው። ማሳውን እያፀዳ እያለ የሆኑ ሶስት ሰዎች የሆነን ልጅ ሌባ ነው ብለው ያባርሩታል፤ ሲያባርሩት፣ ሲያባርሩት፣ ሲያባርሩት፣ ወደ ሰውየው ማሳ ይደርሳል። ሰውየው ደሞ ቆሻሻውን እያፀዳ ከምሯል ከዚያ እዚያ ሲደርስ እያባረሩኝ ነው ሊገሉኝ ነው አድነኝ ሲለው ሂድ እዚያ እተከመረው ሥር ግባና ተደበቅ ይለዋል። ሰዎቹ ሲደርሱ አንተ ሰውዬ የሆነ ልጅ በዚህ አላለፈም? ብለው ሲጠይቁት ያው እዚያ ቆሻሻ ውስጥ አለ ይላቸዋል። አይ ይሄስ እብድ ነው፤ ሰውየው አብዷል እንዴ? ምን ይሠራል ቆሻሻ ሥር? ብለው ጥለውት ይሄዳሉ። ሰዎቹ ከሄዱ በኋላ ልጄ ውጣ ሄደዋል ይለዋል። ይወጣና ትደብቀኛለህ ስል ታጋልጠኛለህ እንዴ? ሲለው ልጄ አለው ሃቅ ካላወጣህ ውሸት አያወጣህም፤ እኔ የለም ብል ኖሮ ይፈትሹና ያገኙህና ይገሉህ ነበር ሃቅ ስለተናገርኩ ነው አንተ የዳንከው አለው ይባላል።

## ተረት አሥራ አምስት

በአንድ አካባቢ ጦርነት ተነስቶ ኑዋሪው ሁሉ ወደ ሌላ ቦታ ሽሽት ሲያደርግ አንድ ሽባ እና አንድ ዐይነ ስውር ብቻ ይቀራሉ። ሁለቱም ለመሸሽ ስላልቻሉ ጨንቆዋቸው ሲወያዩ ሽባው ዐይነስውሩን አንተ እዘለኝና እኔ እየመራሁህ

መሸሽ እንችላለን ብሎት ተስማምተው ሽሽት ይጀምራሉ፡፡ ሲሄዱ ሲሄዱ ቆይተው ከአንድ ቦታ ሲደርሱ እነሱን ቀድመው የሸሹ ሰዎች ሚዳቁዋ አርደው በልተው የተረፋቸውን ሥጋ ጥለው ሄደው ያገኛሉ፡፡ ሽባው ለዐይነስውሩ ያገኙትን ሲሳይ ይነግረውና አውርዶት ጠብሰው እንዲበሉ ይነግረዋል፡፡ ከዚያም ሽባው የመጥበሻ እንጨት ሲሰበስብ እባብ ያገኝና ይገድለዋል፡፡ እሳቱን አቀጣጥሎ የሚዳቋዋን ሥጋ እየጠበሰም አንድ ተንኮል ያስባል፡፡ የሚዳቋውን ሥጋ ለእሱብቻ ለመብላትና የእባቡን ሥጋ ጠብሶ ለዐይነስውሩ ለመስጠት፤ ከዚያም በዕቅዱ መሠረት እባቡን ጠብሶ ለዐይነሥውሩ ሰጥቶ የሚዳቋዋን ሥጋ ለብቻው ይበላል፡፡ በዚህ ጊዜ ዐይነ ሥወሩ ያልበሰለ የእባብ ሥጋ አጋጥሞት በልቶት ኖሮ ዐይኑ ይበራል፡፡ በጣም ይደሰታል፡፡ ወደ በሉት ሥጋ ሲመለከትም ይለያይበታል፡፡ ምንድነው ብሎ ሲጠይቀው ለእሱ የሰጠው የእባብ ሥጋ መሆኑን ይገነዘባል፡፡ የሽባውም ተንኮል ስላናደደው አንተ ተንኮለኛ ሰው ነህ እዚሁ ትቀራታለህ ብሎ እዚያው ጥሎት ይሄዳል፡፡ ወደፊት ሲገሰግስም ቀድመዋቸው ከሸሹት ሰዎች ዘንድ ይደርሳል፡፡ ሰዎቹም በጣም ተገርመው እኛ አንተን ናሽባውን እዚያው ጥለናችሁ አልነበረም እንዴ የመጣነው? አንተ እንዴት ደረስክብን? ዐይንህንስ ምን አበራው? ሲሉት የእኔን ዐይን ያበራው ተንኮል ነው፡፡ ሁለታችን እኔ ልሸከመው እሱ መንገድ ሊመራኝ ተስማምተን ጉዞ እንደጀመርን ለእኔ ሳያዝን ይሄንን ክፉ ተግባር ዋለብኝ አምላክ ግን መድሃኒት አደረገልኝና ዐይኔን አበራልኝ እኔም በተንኮሉ መቀጣት አለበት ብዬ እዚያው ጥየው መጣሁ አላቸው ይባላል ስለዚህ ተንኮል መሥራት ጥሩ አይደለም፤ ተንኮል መሥራት የሚጎዳው ተንኮለኛውን ስለሆነ ተንኮል መሥራት እንዳታስቡ፡፡

## ተረት አሥራ ስድስት

በጥፋት ውሃ ጊዜ ኖህ ከፍጥረታት ሁሉ ተባዕትና እንስት እያደረገ ወደ መርከቡ ካስገባ በኋላ አንድ ትዕዛዝ ተናገረ ይኸውም አምላክ ምህረቱን እስኪልክልን ድረስ በመርከቡ ውስጥ  የግብረ ሥጋ ግንኙነት የተከለከለ በመሆኑ ማንም ይሄንን እንዳይፈፅም ብሎ ትዕዛዛ አስተላለፈ። ሌሊት ላይ ውሻ ተደብቆ ሚስቱን ሲገናኝ ድመት አይታ ኖሮ ሲነጋ ለኖህ ትናገራለች። ውሻ ተጠርቶ ሲጠየቅ አላደረኩም ብሎ ይክዳል። ኖህም ሁለተኛ እንዳይደረግ ድጋሚ ያስጠነቅቃል። ማታ ውሻ እንደለመደው ሲሰርቅ ተጣብቆ ይቀራል። ውሻ ከግብረስጋ ግንኙነት በኋላ ተጣብቆ የሚቀረው እምነቱን በማጉደሉና በመዋሸቱ ነው። ውሻና ድመትም የማይስማሙት ከዚህ የተነሳ ነው ።

## ተረት አሥራ ሰባት

በዱሮ ጊዜ ብዙ በሬዎችና ላሞች ያሉት ጀባ የሚባል አንድ ሰው ነበረ። ከብቶቹን ከመርባታቸው ብዛት የተነሳ መንጋ ሆነውለት ነበር። እሱም በጠዋት ተነስቶ ሳርና ውሃ ወደሚያገኙበት መስክ ያሰማራቸው ነበር። በጊዜው እሳት ስላልነበረ ምግቡ የላሞቹ ወተትና የዱር ማር ነበረ። ብርዱ ሃይለኛ በሆነበት ከዕለታት አንድ ቀን ማሩን በልቶና ወተቱን ጠጥቶ መስኩ ላይ ጋደም እንዳለ ሃይለኛ እንቅልፍ ድብን አድርጎ ይወስደዋል። ከእንቅልፉ ሲነቃ ከብቶቹ በብርሃን ተከበው ያገኛቸውና ወደ እነሱ ሲቀርብ ደስ የሚል ሙቀት ያለው የሚቀለቀል እሳት ያይና ይህን ሲሳይ ከብቶቹ ከየት እንዲያገኙት ሲጠይቃቸው አላህ እንዲሞቁት እንደሰጣቸው ይነግሩታል። እሱም በጣም በርዶት ስለነበረ እሳቱን እንዲያበድሩት ሞቆ እንደሚመልስላቸው ይጠይቃቸዋል። እነሱም ተስማምተው ይሰጡታል። ሰውየው ወስዶ የእሳቱን ጥቅም ካወቀ በኋላ ሊመልስላቸው አልፈለገም። ከብቶቹም ብርዱ ሲጠነክርባቸው ወደ ጀባ ይሄዱና

እሳታቸውን እንዲመልስላቸው ይጠይቁታል፡፡ እሱ ግን አልመልስም ብሎ ይከለክላቸዋል፡፡ ከዚያም ይመካከሩና ጀባን ይገድሉታል፡፡ በዚህም ሥራቸው አላህ ተቀጥቶ ወደ ጎሽነት ይቀይራቸዋል፡፡ እስከዛሬም በዱር እየኖሩ ሰደድ እሳት ሲያዩ እንደሸሹ ይኖራሉ፡፡

## ተረት አሥራ ስምንት

በድሮ ጊዜ ሰባት ወንዶች ልጆች ያሉት ሃብታምና አንድ ልጅ ያለው ደሃ በአንድ መንደር ይኖሩ ነበር፡፡ ሁሉም ልጆች ለንግድ የሚጠቀሙባቸው አንዳንድ አህዮች ነበሯቸው፡፡ ሰባቱ ወንድማማቾችና ብቸኛው ልጅ ለንግድ የሚሄዱበት መንገድ ተመሳሳይ በመሆኑ ሁሌም ይገናኙ ነበር፡፡ ከዕለታት ቀንድ ቀን ሰባቱ ወንድማማቾች ወደ ንግድ ሲሄዱ ይደክማቸውና ዛፍ ጥላ ሥር አርፈው ሳለ የደሃው ልጅ ብቻውን አህያውን እየነዳ ሲመጣ ያዩታል፡፡ ከሰባቱ ወንድማማቾች አንዱ ይነሳና "ተመልከት እኛ ሰባት ነን፤ አንዳችን ብንጠቃ ሌሎቻችን ተጋግዘን ጠላታችንን እናጠፋለን፤ አንተ ግን ነጠላ ነህ ማን ያግዝልሃል?" ብሎ ይጠይቀዋል ብቸኛው ልጅም "ለእኔ አላህ አለኝ፤ እሱ ያግዝልኛል" ይላቸዋል፡፡ በዚህ ጊዜ የጠየቀው ልጅ ይናደድና "እስቲ አሁን ሲያግዝልህ እንይ" ብሎ ጭንቅላቱን ሲለው ልጁ ይሞታል፡፡ እነሱም ሬሳውን ጥለውት ወደ ንግዳቸው ይሄዳሉ፡፡ ጥቂት ወራት ቆይተው ወደ ሠፈራቸው ሲመለሱ ብቸኛውን ልጅ ከገደሉት ሥፍራ ላይ አንድ እራስ የበሰበሰ በቆሎ ያገኛሉ፡፡ በቆሎ የመድረሻው ወቅት ባለመሆኑ ተገርመው እየተነጋገሩ ሳለ አንደኛው ልጅ የሚሆነው አይታወቅም እስቲ ልያዘው ይልና ከኮሮጆው ውስጥ ጨምሮት ወደቤታቸው ይሄዳሉ፡፡ ከንግድ እንደተመለሱ ያወቀው የሟች አባት የእሱን ልጅ አይተውት እንደሆን ይጠይቃቸዋል፡፡ እንዳላዩት ከመለሱለት በኋላ አንዱ ወንድማቸው "እሱንስ አላየነውም በመንገዳችን ላይ ግን የበሰበሰ በቆሎ

አግኝተን ተገርመናል ቆይ ላሳይህና ምን ታምር እንደሆነ ትነግረናለህ" ብሎ በኮረጀው የያዘውን በቆሎ ሊያሳየው ሲያወጣው የሰውየው ልጅ ጭንቅላት ይሆናል፡፡ ከዚያም "ልጄን ገደላችሁት" ብሎ ሲጮህ ሰዎች ይወጡና ይይዟቸዋል፤ ተገቢውንም ቅጣት ያገኛሉ፡፡

## ተረት አሥራ ዘጠኝ

አንድ ስስታም ሰው ከሚስቱ ጋር በአንድ ሰፈር ውስጥ ይኖር ነበር፡፡ ሁለቱም ስስታሞች ስለነበሩ እንግዶችን ተቀብለው አያስተናግዱም፤ ያላቸውንም አያካፍሉም፡፡ ሰውየው ታናሽ ወንድም ነበረው፡፡ ታናሽየውና ሚስቱ ግን ለጋሶች ናቸው፡፡ እንግዶችን ተቀብለው ማስተናገድና ተካፍሎ መብላት የዘወትር ተግባራቸው ነው፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን ሁለቱን ወንድማማቾች ራቅ ወዳለ ሥፍራ የሚያስኬድ ጉዳይ ይገጥማቸውና አብረው ለመሄድ ይስማማሉ፡፡ ስስታሙ ሰው ገና ካሁኑ ለወንድሙ ላለማካፈል ስለፈለገ "በል ሚስቶቻችንን ሄደን ስንቅ እንዲያዘጋጁልን እንንገር" ይለዋል፡፡ ለጋሱ ደግሞ "እኔ ስንቅ አያስፈልገኝም የሚስቴን እጅ እበላለሁ" ይለዋል፡፡ ስስታሙም እንደሱማ ከሆነ ደግ ይልና እቤቱ ገብቶ የሚስቱን እጆች ይቆርጥና ለስንቁ ይዞ ጉዞ ይጀምራሉ፡፤ አምሻሽ ላይ ከአንድ መንደር ሲደርሱ ወደ አንድ አልከለዋ "አሰላማሌያኩም" ብለው ይገባሉ፡፡ እዚያም ያሉ ሰዎች ተቀብለው በደንብ ያስተናግዷቸዋል፡፡ አረፍ እንዳሉም ቤቱን የሚያስቀይም ሽታ ይሞላዋል፤ ምንድነው ብለው ሲፈልጉ ስስታሙ ለስንቅ የቋጠረው ነገር መሆኑ ይታወቅና ፈተው ሲያዩት ሁለት የተቆረጠ እጅ ይሆናል፡፡ በዚህ ጊዜ ሽማግሌዎች ነገሩን ሲያጣሩ ስስታሙ ሰው ጥፋቱን በለጋሱ ወንድሙ ላይ "እሱ ነው እንዲህ እንዳደርግ የመከረኝ" በማለት ለመላከክ ይጀምራል፡፡ ለጋሱም ሰው "ለጉዟችን ስንቅ እንዲያዘጋጁልን ለሚስቶቻችን እንንገር ስለኝ የሚስቴን እጅ እበላለሁ

ያልኩህ ቆርጬ እበላዋለሁ ማለቴ አልነበረም። ሚስቴ በሚገባ ስታስተናግዳቸው የቆየችው ሰዎች በሄድኩበት ያስተናግዱኛል ማለቴ ነበር። የስስታምነትህ መጨረሻ ነው የሚስትህን እጅ ያስቆረጠህ" አለው ይባላል።

## ተረት ሃያ

በዱሮ ጊዜ አንድ ልጅ የነበረው ስስታም ሰው ነበረ። ያለውን ለማንም ሰው አያካፍልም። የሚያውቀው ሀብትን ለራሱ ብቻ ማከማቸት እና ከሌሎች መሰብሰብ፣ መቀበልና ማጠራቀም ብቻ ነበር። መስጠት የሚባል ነገር ፈፅሞ አያውቅም። አንድ ቀን ከልጁ ጋር ሆነው መንገድ ሲሄዱ ወንዝ ያጋትማቸውና ለመሻገር አባትየው ቀድሞ እንደገባ ደራሽ ውሃ ይመጣና ሊወስደው ያንገላታዋል፡፤ በዚህ ጊዜ ልጁ ከወንዙ ሊያድነው ፈልኮ አባዬ እጅህን ስጠኝ እጅህን ስጠኝ እያለ ሲጮህ መስጠት ያለመደው ስስታም እምቢ ብሎ ወንዙ ይወስደዋል። በኋላም ልጁ አባቱን እጅህን ስጠኝ እያልኩት እምቢ ብሎ ወንዝ ወሰደው ብሎ ሲነግራቸው አንድ ሽማግሌ አይ ልጄ የአንተ አባት ስጠኝን መች ይወድና ነው እሌን እንካ ብትለው ይተርፍ ነበር አሉት ይባላል።

## ተረት ሃያ አንድ

በዱሮ ጊዜ በጣም ታታሪና ጎበዝ የሆነች ወንድን የምታስንቅ አንዲት ሴት ነበረች። በእርሻ ጊዜ በጠዋት ተነስታ ወደ ማሳዋ ትወርድና ስትቆፍር ውላ የሚያስፈልጋትን ዘርታ ትመለሳለች። በዚያው መንደር ከእርሷ እርሻ አጠገብ መሬት ያለው ሌላ ሰው ነበረ። እሱም በጠዋት ይነሳና በእርሻው አንድ ጫፍ ቁጭ ብሎ በጣቱና በአገጩ እያመለከተ ነገ ከዚህ ጀምሬ እስከዚያ ድረስ እቆፍርና ማሽላ ዘርቼ ይህን ያህል ኩንታል አመርታለሁ እያለ ሲወራ ይመሽለታል። አንድም ቀን ግን ተነስቶ ቁፋሮውን አይጀምርም። በመጨረሻ

የምርት ወቅት ይደርስና ታታሪዋ ሴት በርካታ ምርት ትሰበስባለች። በዚህ ጊዜ የሁለቱንም ከእርሻቸው ላይ መዋል የሚያውቁና እሱ ባዶ እጁን ቀርቶ እሷ ብዙ በማምርቷ የተገረሙ ሰዎች ሲጠይቋት "እንደምታዉቁት እሱ በምላሱና በአገጩ ሲሰራ እኔ በእጆቼ ጠንክሬ ሰርቻለሁ፤ እንደኔ ከአፉ ይልቅ በእጆቹ ቢሠራ ኖሮ ከእኔ የበለጠ ምርት ያፍስ ነበር" አለቻቸው ይባላል።

## ተረት ሃያ ሁለት

በዱሮ ጊዜ አንድ ወጣት ሚስት ያገባና ሚስቱን አባቱ ዘንድ አስቀምጦ ለንግድ ከአካባቢው ርቆ ይሄዳል። ረጅም ጊዜም በመቆየቱ ሚስቱ ሌላ ወንድ በስርቆት ትለምዳለች። በዚህ መሃል  የባልየው አባት ይታመምና ሊሞት ያጣጥራል። ልጁም ሳይመለስ እንደሚሞት ስለተረዳ ሚስቱን ይጠራና ከአልጋዋ ሥር ጉድጓድ እንድትቆፍር ነግሯት ብዙ ከረጢት ወርቅ ይሰጣትና እንድትቀብረው ያደርጋል። ከዚያም ወርቁ የባሏ ድርሻ ስለሆነ ከንግድ ሲመለስ እንድትሰጠው ይነግራትና ይሞታል። ሴትየዋ በስርቆሽ ከለመደችው ሰው ጋር በፍቅር ከንፋ ኖሮ ወርቁን እሷና ፍቅረኛዋ እንዲጠቀሙበት በማሰብ የአባቱን ኑዛዜ ባሏ ሲመጣ ሳትነግረው ትቆያለች። አባቱ ምንም ሳይተውለት መሞቱ ያስገረመው ባል ውሎ ሲያድር ሚስቱ በምታሳየው አዲስ ባህሪ ጥርጣሬ ውስጥ ይገባና አንድ ዘመዱን አምጥቶ መናገርና መስማት እንደማትችል አስመስሎ ጉዳዩን እንድትሰልልለት በሠራተኝነት ያስቀምጣታል። ሚስት ባሏ ወጣ ሲል እንደለመደችው ውሽማዋን ትጠራና ባሏን እንደምትፈታውና ቤቱን ሸጦ እንዲያካፍላት እንደምታደርግ እሱ ደግሞ ቤቱን እንዲገዛውና ከዚያም የተቀበረውን ወርቅ አውጥተው ተጋብተው እንዲኖሩ እንዳሰበች ስትነግረው መስማት አትችልም የተባለችው ሠራተኛ ትሰማና ለባልየው ትነግረዋለች። ሚስጥሩን የተረዳው ሰውየ ሚስቱን ራቅ ወዳለ ሥፍራ ይልክና የተቀበረውን

ወርቅ ቆፍሮ አውጥቶ በምትኩ ከሰል በጆንያ ሞልቶ ይቀብርና እንደነበረ ይደፍነዋል። ሚስት እንደተመለሰች ጭቅጭቅ አንስታ እንዲፈታትና ቤቱንም ሸጦ እንዲያካፍላት ስትጠይቅ ባል ይስማማና ቤቱን ለውሽማዋ በአንድ ወቄት ወርቅ ሸጦ ፈትቷት ወደ ሌላ ቦታ ይሄዳል። በዚህ የተደሰቱት ሴትየዋና ውሽማዋ ቦታውን ሲቆፍሩ በወርቅ ፋንታ ከሰል ያጋጥማቸዋል። በዚህ ጊዜ ውሽምየው ቤቱን የገዛው ተበድሮ ስለነበር በጣም ይበሳጭና ለዚህ ሁሉ ያበቃሽኝ አንቺ ነሽ ብሎ ጭንቅላቷን ብሎ ገደላት ይባላል።

## ተረት ሃያ ሶስት

በዱሮ ጊዜ  ቀናተኛና ተጠራጣሪ ባል ያላት አንዲት ሴት ነበረች። ባሏ ቀነተኛነቱ የበዛ ስለነበር በወጣች በገባች ቁጥር እየነዘነዘ ሰላም ይነሳት ነበር። ሴትየዋ ግን ፍፁም ጨዋና ታማኝ ነበረች። የባሏ ንዝንዝ ሲበዛባት “እባክህ ተወኝ እኔ ምንም አላደረኩም እንዲህ ዓይነት ሴትም አይደለሁም ማድረግም አልፈልግም። አመል ካለብኝ ደግሞ አንተ ተቆጣጥረህ አታድነኝም ከፈለግሁ ተደብቄህ ሳይሆን እራስህ አዝለህ ለሌላ ወንድ እንድትሰጠኝ ማድረግ እችላለሁ” ትለዋለች። ባልየው ግን ምንም ንዝንዙን ሊያቆም አልቻለም። በዚህ ጊዜ ሚስትየዋ እልህ ውስጥ ትገባና ከሌላ ወንድ ጋር ፍቅር ትጀምራለች። አንድ ቀን ውሽማዋን ምሽት ላይ ከቤቷ ጓሮ መጥቶ እንዲጠብቃትና ሲመጣ ምልክት እንዲሰጣት ታደርጋለች። ማታ ባልና ሚስቱ እራት በልተው ቡና እየጠጡ ሳለ ውሽምየው ይመጣና እንደነገረችው ምልክት ይሰጣታል፤ በዚህ ጊዜ ሚስት ሆዷን እንዳመማት አስመስላ መንደፋደፍ ትጀምራለች፤ ባልም ይደነግጣል፤ እያቃሰተች አዝሎ ወደ ጓሮ እንዲወስዳት ትጠይቀውና አዝሎ ይወስዳታል፤ ጓሮ ሲደርሱ እልፍ ብሎ እንዲጠብቃትና ተፀዳድታ ስትጨርስ እንደምትጠራው ትነግረዋለች። እልፍ ብሎ እንደሄደ እሷ ከውሽማዋ ጋር ጉዳይዋን ፈፅማ ትሸኘውና ባሏን ጠርታ አዝሎ እንዲመልሳት አደረገች ይባላል።

## ተረት ሃያ አራት

በድሮ ጊዜ አንድ ሀገር ያስቸገረ ሌባ ነበር፡፡ የመንደሩን ፍየሎች በጎች፣ ዶሮዎች ሳይቀር እየሰረቀ አርዶ ይበላ ነበር፡፡ ከእለታት አንድ ቀን እንደልማዱ ፍየል ሠርቆ ተደብቆ ሲበላ የሰው ድምፅ ይሰማና ይደነግጣል፡፡ ድምፁ ወደ እሱ እየቀረበ ይመጣና አይዞህ አትፍራ እኔም እንዳንተው ሌባ ነኝ ይልቅ እኔ ስላልቀናኝ እርቦኛልና ትንሽ ሥጋ ስጠኝ ይለዋል፡፡ ሌባውም ይረጋጋና አብረው መብላት ሲጀምሩ ሃይለኛ ዝናብ መጣል ይጀምራል፡፡ በዚህ ጊዜ አስፈሪ ነጎድጓድ ይሰማና መብረቅ እየተምዘገዘገ መጥቶ ጓደኛውን ይገድለዋል፡፡ አብሮት የነበረው ሰው ሰይጣን እንደሆነና መብረቁም እሱን ለመግደል እንደመጣ የተረዳው ሌባ ነፍሴ አውጪኝ ብሎ ሲሮጥ አደናቅፎት ይወድቅና ግንባሩን የሾለ ድንጋይ መቶ ገደለው፡፡ መንደሩም ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ከሌባው ስጋት ተገላገለ ይባላል፡፡

## ተረት ሃያ አምስት

በአንድ ሀገር ውስጥ አንድ ልጅ የነበረው አንድ ሰነፍ ሽማግሌ ነበረ፡፡ ሁልጊዜ ልጁን አስከትሎ ጻሌውንና ትንሽ ዘር ይዞ ወደ ማሳው ይወርድና በዛፍ ጥላ ሥር ተቀምጦ ለልጁ በጣቱ እያመለከተ ከነገ ጀምሮ ለአይን እስከሚታየው ድረስ ያለውን መሬት ሁሉ ቆፍሮ እንደሚዘራው ይነግረዋል፡፡ ነገር ግን አንዱንም ቀን ሲቆፍር አይገኝም፡፡

እንዲሁ እያለው ከርሞ ብዙ ቀናት ካለፉ በኂላ አንድ ቀን ሽማግሌው የተለመደውን ወሬ ለልጁ ማውራት ሲጀምር ልጅየው “ይህን ሁሉ ቆፍረህና ዘርተህ ያመረትከውን ምን እናደርገዋለን?” ብሎ ይጠይቀዋል፡፡ “አንተ ሞኝ

ይህን ሁሉ ቆፍሬና ዘርቼ ያመረትኩትንማ በደህና ወጋ እሸጠውና አንድ አህያ እስከ ውርንጫዋ እገዛና አህያዋ ላይ ተቀምጬ ውርጭላዋን እያስከተልኩ እንደባላባቶቹ ወደ ገበያ እሄድባታለሁ" ይለዋል፡፡ ልጅየውም "እኔ በውርንጭላዋ ላይ ተቀምጬ ባጅብህስ?" ብሎ ሲጠይቀው አባት በጣም ይናደድና "አንተ የማትረባ የውርንጭላዋን ጀርባ ለመስበር ትፈልጋለህ?" ብሎ በያዘው ዱላ ግንባሩን ብሎ ገደለው ይባላል፡፡ የሰነፍ ሰው መጨረሻው እንዲሁ በምኞት ፈረስ እንደጋለበ መቅረት ነው፡፡

## ተረት ሃያ ስድስት

በዱሮ ጊዜ ሰባት ልጆች ያሉት አንድ ሰው ነበረ፡፡ ሰውየው ሰነፍ በመሆኑና መሥራት ስለማይወድ ልጆቹን እንኳን ለመመገብ አልቻለም ነበር፡፡ እሱና ልጆቹ የሚበሉት ሲቸገሩ ልጆቹን በእህል እየቀየረ መብላት ጀመረ፡፡ ስድስቱን ልጆች አንዱን በአንድ ከረጢት እህል ቀይሮ እየበላ ሰባተኛው ልጅ ሲቀር የወንደሞቹ እጣ ፋንታ እንዲህ የሆነው ባባትየው ስንፍና መሆኑን ተረድቶ ሌት ከቀን መሥራት ይጀምራል፡፡ በሰራው መጠንም ምርት ስላገኘ ስድስቱንም ወንድሞቹን የተሸጡበትን እህል እየመለሰ ነፃ ያወጣቸዋል፡፡ ተመልሰውም ከወንድማቸው ጋር ጠንክረው በመስራት ሀብታም ይሆናሉ፡፡ አባትየውንም እንዲህ ጠንክረህ መሥራት አቅቶህ ለእህል ስለሸጥከን አባታችን አይደለህም ብለው ካዱት ይባላል፡፡

## ተረት ሃያ ሰባት

በድሮ ጊዜ ዝንጀሮዎች በጣም ጥበበኞችና ሃብታሞች ነበሩ ይባላል፡፡ አጉር ጋሱም የተባለ ንጉስም ነበራቸው፡፡ በአጉር ጋሱም መሪነትም ማሳቸውን

ጠንክረው እያለሙ ሁሉንም ዓይነት እህል ያመርቱ ነበር። በዚህም እንደፈለጋቸው እየበሉ፣ እየጠጡና እየጨፈሩ ይኖሩ ነበር። ምርታቸውም ከፍተኛ ስለነበረ ሁሉንም አይጠቀሙበትም ነበርና ተርፎ የሚበላሸው ብዙ ነበር። ምግብም በየቦታው የተትረፈረፈ ስለነበረ የሚሸጥም ሆነ የሚገዛ አልነበረም። ስለዚህ ይሰበሰቡና የተትረፈረፈውን ምርት ምን እንደሚያደርጉት ተወያይተው ወንዝ ውስጥ ሊጨምሩት ስማማሉ። ሃሳባቸውን ለአጉር ጋሱም ሲያማክሩት በነገሩ ይስማማና ታላቅ ድግስ ተደግሶ በየሀገሩ ያለው ዝንጀሮ ሁሉ ታድሞ ሲበላ ሲጠጣ ይከረምና በመጨረሻ የተረፈውን ምርት እየተሸከሙ "አንተ አስቀያሚ ምግብ ዞር በል ከፊታችን" በማለት በጋራ እየጮሁ ወንዝ ውስጥ ይጨምሩታል። ምንም ጥሪት ሳያስቀሩ ሁሉንም ነገር ዉሃ ስላስበሉት ከጥቂት ቀናት በኋላ የሚላስ የሚቀመስ ይጠፋል። አጉር ጋሱምን ጨምሮ ብዙ ዝንጀሮ በረሃብ ያልቃል። ከዚያም አያስፈልገንም ብለው ወንዝ የጨመሩትን ምግብ ፍለጋ ይወጣሉ። ከዚያ ጊዜም ጀምሮ ምግባቸውን ፍለጋ ከዛፍ እዛፍ እንደዘለሉ፤ተራራ እንደቧጠጡ፤ የሰው ነዶ እንደዘረፉ ሳይደላቸው ይኖራሉ።

## ተረት ሃያ ስምንት

በድሮ ጊዜ በአንድ ሃገር ውስጥ በጣም ቆንጆ ልጅ ያለችው ሀብታም ሰው እና አንድ ደሃ ጎረቤቱ ይኖሩ ነበር። ደሃው ሰው የሀብታሙን ቆንጆ ልጅ ለማግባት ይፈልግና እንዲዲርለት አባትየው ጋ ሽማግሌ ይልካል። አባትየውም እንዴት ቢንቀኝ ብሎ አካኪ ዘራፍ ይላል። ደሃውም አላህ የሚያደርገውን አያለሁ ብሎ ዝም ይላል። ከጥቂት ቀናት በኋላም ሌላ ሀብታም ልጅቷን ለማግባት ይጠይቅና አባቷ ስለፈቀደለት ሠርግ መደገስ ይጀምራል። በባህሉ መሠረት የልጅቷ ባል አባቷ ቤት አጠገብ የጫጉላ ቤት ሲሰራ ደሃው ሰውየም ተመሳሳይ

ቤት አጠገቡ ይሰራል፡፡ የሠርጉ ቀን ሲበላ ሲጠጣ ሲጨፈር ይዋልና ሙሽራዋን ሚዜዎቹ ተሸክመው አዲስ ወደተሰራው ጎጆ ያስገቧታል፡፡ ጎጆዎቹ ተመሳሳይ በመሆናቸው ያስገቧት ደሃው ከሠራው ጎጆ ኖሮ ሙሽሪት ከደሃው ጋር ታድራለች፡፡ ነገሩ ሲታወቅ ሽማግሌዎች ተሰብስበው ልጅቷ የደሃው እንድትሆን አላህ ስለፈቀደ ነው ብለው ሚስትነቷን አፀደቁለት ይባላል፡፡

## ተረት ሃያ ዘጠኝ

ከዕለታት አንድ ቀን አንድ ቅን ሰው በመንገድ ሲሄድ አንድ ሰው እየተርበተበተ ከሚያሳድዱት ሰዎች እንዲደብቀው ይጠይቀዋል ሰውየውም የት አባቴ ልደብቅህ ያለሁት መንገድ ላይ ነው እኪሴ አልጨምርህ ወይስ ልብሴን አውልቄ ልሸፍንህ ብሎ ይጠይቀዋል አይ እሱማ በቀላሉ ያገኙኛል ብትውጠኝና ከሆድህ ውስጥ ብትደብቀኝ ይሻላል ይለዋል፡፡ እንዴት አድርጌ፣ ቢሆንስ ውስጤ ገብተህ ልትገድለኝ ትፈልጋለህ ይለዋል አይዞህ ምንም አትሆንም አፍህን ብቻ ክፈትልኝ ልግባ ይለዋል፡፡ ቅኑ ሰውም አፉን ሲከፍትለት ሰውየው ገብቶ ከሆዱ ውስጥ ይደበቃል፡፡ የሚያሳድዱትም ሰዎች ይደርሱና ሰውየውን አይቶ እንደሆን ሲጠይቁት አዎ ውጨዋለሁ ይላቸዋል፡፡ ሰዎቹም እብድ ነው እንዴ ብለው ጥለውት ፍለጋቸውን ወደፊት ይቀጥላሉ፡፡ መራቃቸውን ሲያረጋግጥ የዋጠውን ሰው ከሆዱ እንዲወጣለት ይጠይቀዋል፡፡ ሰውየውም ያልሰማሁህ እንዳይመስልህ ሰዎቹ ሆድህን ቀደው እንዲገድሉኝ ያለሁበትን የነገርካቸው ብወጣልህማ አሳልፈህ ልትሰጠኝ ነው እንደውም ሆድህ በጣም ተስማምቶኛል አልወጣም ብሎ አሻፈረኝ ይለል፡፡ ቢለምነው ቢለምነው እምቢ ይለዋል እንደውም ዝም ካላለ ሆዱን እንደሚተረትረው ያስፈራራዋል፡፡ ሰውየው እዛው ቆሞ ሲጨነቅ አንድ የሚያምር ወጣት ይመጣና ምን እንደሆነ ሲጠይቀው ችግሩን ዘርዝሮ ይነግረዋል፡፡ ወጣቱም በጣም ያዝንና ወደ ዱር

ገብቶ የሆነ መድሃኒትነት ያለው ቅጠል ይሠተውና አኝኮ እንዲውጠው ይነግረዋል። ሰውየውም እንደተነገረው ያደርጋ፤ በመጨረሻ የተዋጠው ሰውዬ ተበጣጥሶ ከሰውየው ሆድ ወጣለት ይባላል።

## ተረት ሰላሳ

በድሮ ጊዜ አንድ ወንድ ልጅ ብቻ የነበራት ብልህ ሴት ነበረች። ልጇ ብቻውን ስለሆነ ወንድም እንድትወልድለት ሁልጊዜ ይጨቀጭቃት ነበር። እሷ ሌላ እንደማትወልድ ስለተረዳች ከወንድም እኩል የሚሆን ጓደኛ እንደምትመርጥለት ትነግረውና ጓደኞቹን ተራ በተራ እያመጣ እንዲያስተዋውቃት ታደርጋለች። የመጀመሪያውን ጓደኛውን ሲያመጣ ሶስት እንቁላሎች ትቀቅልና ታቀርብላቸዋለች። ለልጇ አስቀድማ አንዳንድ እንቁላል ከበላችሁ በኂላ ቀድመህ ሁለተኛውን እንዳታነሳ ብላ አስጠንቅቃው ስለነበር የየድርሻቻን በልተው እንደጨረሱ ጓደኝየው ሁለተኛውን አንስቶ ለብቻው ይበላል። እናትየዋ ይሄን ስታውቅ ይሄ ጥሩ ጓደኛ አይደለም ራሱን ያስቀድማል እያለች የመጡትን ሁሉ ስትፈትን ትቆይና ሰባተኛ ላይ የመጣው ዕንቁላሉን እንደጨረሱ ሁለተኛውን አንስቶ ለልጇም እኩል ያካፍልና ይበላሉ በዚህ ጊዜ እናትየዋ ከወንድም እኩል የሆነ ጓደኛ ማለት ይሄ ነው፤ ሌሎቹ ራስ ወዳዶች ናቸው፤ ይሄ ግን ማካፈልን የሚያውቅ ስለሆነ ጥሩ ጓደኛህ ሊሆን ይችላል፤ አንተም ያለውን ለሌሎች የማያካፍል ብቻውን የሚበላ ስስታም ሰው እንዳትሆን ብላ አስተማረችው። እነዚያም ጓደኛሞች እስከ ዕለተ ሞታቸው ድረስ ሳይለያዩ እንደታናሽና ታላቅ ወንድም ተዋደው ኖሩ ይባላል።

## ተረት ሰላሳ አንድ

በድሮ ጊዜ አንደኛው በጣም ሀብታም ሌላው ደግሞ ደሃ የሆኑ ሁለት ወንድማማቾች በአንድ መንደር ውስጥ ይኖሩ ነበር። ሃብታሙ ሰው ታዲያ ለወንድሙ ቁብ የሌለው ስለነበረ አብሮ የሚበላና የሚጠጣው ከመሰሎቹ ሀብታሞች ጋር ነበር። ይህን የተረዳችው ሚስቱ ግን "ለምን እንዲህ ታደርጋለህ? ወንድምህን ልትረዳው ይገባል አንድ ክፉ ነገር ቢገጥምህ ቀድሞ የሚደርስልህ እሱ ነው። እነዚህ አብረውህ የሚያጫፍሩ ሀብታም ጓደኞችህ ግን ዞር ብለው አያዩህም።" እያለች ሁሌ ትወተውተው ነበር። ከዕለታት አንድ ቀን ሀብታሙ ሰው ጓደኞቹን መፈተን ፈለገና ትልቅ ሙክት አርዶ ከቤቱ መሃል የሰው አስከሬን አስመስሎ ጨርቅ ያለብስና ጓደኞቹን አስጠርቶ በድንገተኛ ግጭት የሰው ህይወት በእጁ እንዳለፈ ይነግራቸውና ምን ማድረግ እንዳለበት ምክር እንዲለግሱትና አስከሬኑን በመሰወር እንዲረዱት ይጠይቃቸዋል። ሁሉም በነገሩ ቢደነግጡም ማንኛቸውም ሊረዱት ፈቃደኛ ስላልሆኑ ቀስ በቀስ እስከችግሩ ጥለውት ይሄዳሉ። ከዚያም ሰዉየው ይነሳና ወደ ደሃው ወንድሙ ቤት ይሄድና "አሰላማሌይኩም" ይላል። "ማሌይኩም አሰላም" እያለ ወንድምየው ሲወጣ ሀብታም ወንድሙ ትክዝ ብሎ ከበሩ ቆሞ ያገኘዋል። ግራ የተገባው ወንድም ወደ ውስጥ እንዲዘልቅ ያደርግና ምን እንዳጋጠመው ሲጠይቀው ዘርዝሮ ይነግረዋል። በዚህ ጊዜ "አይዞህ አትጨነቅ ወንድሜ እንደሚሆን እናደርገዋለን; ሌላ ዘዴ ቢጠፋ እንኳን አንተ ወንድሜ ታስረህ ከምትንገላታ እኔ እንደገደልኩት ተናግሬ ቅጣቱን እቀበልልሃለሁ ተነስ እንሂድ" ብሎት ወደ ሃብታሙ ቤት ሲሄዱ ሃብታሙ ቤቱ መሃል ያለውን የታረደ ሙክት ይገልጥና ወንድሙን አቅፎ ስሞ "ይቅርታ አድርግልኝ ይህንን ያደረኩት ለመፈተን ነው። እኔ ከሀብታም ጓደኞቼ ጋር ስበላ ስጠጣ አንተን ዞር ብዬ አላየሁህም ነበር፤ እነሱ ችግሬን ስነግራቸው ጥለውኝ ሸሹ አንተ

ወንድሜ ግን በደሌን ሳትቆጥር ነፍስህን ልትሰጠኝ ቆረጥህ አላህ በዚህ አስተማረኝ" ብሎ ለወንድሙ ካለው ሁሉ አካፍሎት በደስታ ኖሩ ይባላል፡፡

## ተረት ሰላሳ ሁለት

በድሮ ጊዜ ሁለት ሽማግሌዎች በጉርብትና ይኖሩ ነበር፡፡ አንደኛው አንድ በሬ ሲኖረው አንደኛው ደግሞ የእርሻ ማሳ ነበረው፡፡ በለማሳው እርሻውን በወቅቱ አርሶ የዘራውን ሰብል ሲያይ ባለበሬው ይመቀኝና በማሳው ውስጥ በሬውን ለቆ ያስበላበታል፡፡ በዚህ የተናደደው ሰውዬ ወደ ባለበሬው ይሄድና ባስበላበት ሰብል ፋንታ አንድ ከረጢት ማሽላና አንድ ዶሮ እንዲሰጠው ይጠይቀዋል፡፡ ሽማግሌው ግን አመፀኛ ስለሆነ አልሰጥም ይልቅ "ከሰው ፊት ከፍ ከፍ ብለህ ለመታየት አትሞክር ማጉዚ ተማፍሌ በቃ ተርመናሉ አሻን ቱሜር ማነፁሩኚ ነትፍቂ (ከቡድኑ መካከል ረዘም ያለ ሰው ጎራዴ ያገኘዋል)" ብሎ ይሰድበዋል፡፡ በተደጋጋሚም በሬውን ወደ ማሳው እየለቀቀ ያስበላበታል፡፡ በዚህ ጊዜ ሰውየው ወደ ዳኛ ይሄድና ይከሰዋል፡፡ ተጠርቶም ሲጠየቅ የሆነውን ሁሉ ሳይክድ ዘርዝሮ ይናገራል፡፡ ዳኛው ጥፋተኛ መሆኑን አረጋግጠው በሬው ተሸጦ እህሉ ለተበላበት ሰው እንዲሰጥ ይፈርዱበታል፡፡ ሰውየውም "ከሰው ፊት ከፍ ከፍ ብለህ ለመታየት አትሞክር ብለኸኝ ነበር፤ ከፍ ከፍ ያልኩት ግን እኔ ሳልሆን አንተ ነበርክ፤ ይሄ ደሞ የምትመካበትንን በሬ ሳይቀር እንዳሳጣህ ተመልከት፤ ይልቅ እንደኔ ዝቅ ዝቅ ብለህ ሥራ" አለው ይባላል፡፡

## ተረት ሰላሳ ሶስት

በድሮ ጊዜ ቀበሮና ውሻ አደን ወጥተው ሳሉ ሃይለኛ ዝናብ ይይዛቸዋል። ዙሪያቸውን ሲመለከቱ አንድ ዋሻ ያዩና ወደዚያው ሄደው ይጠለላሉ። እነሱ እንደገቡ ዋሻው የአንበሳ ኖሮ እሱም ዝናቡ አባሮት መጥቶ ወደ ዋሻው ይገባል። በዚህ ጊዜ አያ ውሻ ደንግጦ ማላዘንና መጮህ ይጀምራል። ብልጧ ቀበሮ እንዴት ከአንበሳው እንደሚያመልጡ አሰላሰለችና "አያ ውሻ እባክህ አትጩህ ይልቅ ቅድም አድነን የጣልነውን ትልቅ አጋዘን ሌላ አውሬ ሳይወስደው ለአያ አንበሶ አምጣና ስጠው" ስትል ብልጠቷ የገባው ውሻ እሺ ብሎ ተፈትልኮ አዋሻው ይወጣል። ትንሽ ቆይታም ለአያ አንበሶ "አይ ይሄ ውሻ አጋዘኑን ችሎ ማምጣት የሚችል አይመስለኝም በጣም ትልቅ ነው። ሄጄ ልርዳውና ተጋግዘን እናምጣው እንጂ" ስትለው በአጋዘኑ ስጋ የጎመዠው አንበሳ ምንም ሳይጠራጠር እሷንም እንድትሄድ ይፈቅድላታል። እሷም በብልጠቷ የሁለቱንም ህይወት እንዴት እንዳዳነችና በአያ አንበሶ ሞኝነት እየሳቀች ሮጣ አመለጠች ይባላል።

## ተረት ሰላሳ አራት

በዱሮ ጊዜ ሶስት ወንዶች ልጆች ያሉት አንድ አባት ነበረ። ልጆቹም ለንግድ ራቅ ወዳለ ስፍራ እየሄዱ ነግደው ይመለሱ ነበር። ከዕለታት አንድ ቀን ልጆቹ ለንግድ ሄደው ሳለ አባትየው በጠና ይታመማል። ልጆቹ ሳይመለሱ እንደሚሞት ሲያውቅም አንድ ሽማግሌ ይጠራና ሀብቱን ይናዘዝላቸውና ይሞታል። ልጆቹ ሲመለሱም የአባታቸውን መሞት ሲሰሙ በጣም ያዝናሉ። ቆይቶም ኑዛዜውን የተቀበለው ሽማግሌ ይመጣና ኑዛዜውን አስረክቦ ይሄዳል። አባትየው የተናዘዘው ለትልቁ ልጅ ወርቅ፣ ለመካከለኛው አፈር፣ ለመጨረሻው ደግሞ ላም ነበር። ሁሉም ውርሳቸውን ሲያዩ ግራ ይጋባሉ። በኋላም አንድ

ትልቅ ሴትዮ ዘንድ ይሄዱና የአባታቸው ውርስ ግራ እንዳጋባቸው በዝርዝር ያስረዷታል። ሴትዮዋም ቀላል ነው "ወርቅ የተናዘዘልህ ትለቀኛው ልጅ ኑሮህ በንግድ ይሆናል፤ አፈር የተሰጠህ ደግሞ ብዙ የምታመርት አራሽ ትሆናለህ፤ ላም የተናዘዘልህ ደግሞ የበረታህ ከብት አርቢ ትሆናለህ" ማለት ነው ብላ ታስረዳቸዋለች ልጆቹም በአባታቸው ምርቃትና ስጦታ እየተገረሙ ወደ ቤታቸው ተመልሰው እንደተነገራቸው በንግድ በእርሻና በከብት እርባታ የተሳካላቸው ሰዎች ሆነው በደስታ ኖሩ ይባላል።

## ተረት ሰላሳ አምስት

በዱሮ ጊዜ ሰባት የተለያየ ቀለም ያላቸው በሬዎች በአንድ መንደር ውስጥ ይኖሩ ነበር። ቀለማቸውም ጥቁር፣ ነጭ፣ ቀይ፣ ቡላ፣ ቡናማ፣ ቡራቡሬ፣ አሻልማ ነበር። በመንደሩ የሚኖር አንድ አንበሳም ነበረ። አንበሳው በበሬዎቹ ህብረት እየተናደደ እንዴት በተናጠል እንደሚበላቸው ሲያሠላስል አንድ ዘዴ ይመጣለታል። ወደ በሮቹም ቀርቦ ሲያይ ጥቁሩ በሬ ነጠል ብሎ ሣር ሲግጥ ያየውና ለስድስቱ ጠጋ ብሎ "ይሄ ጥቁር በሬ ቀለሙ እኮ ከሩቅ ስለሚታይ ጠላት ይጣራል እሱን ካላሰወገዳችሁ ሁላችሁም በእሱ ምክንያት ማለቃችሁ ነው" ይላቸዋል። በሮቹም በጉዳዩ ይደነግጡና ጥቁሩን በሬ እንዲያስወግድላቸው ይፈቅዱለታል። በሌላ ቀን ደግሞ ነጩ ተመሳሳይ ችግር እንደሚያመጣባቸው ይነግራቸውና እሱንም አሳልፈው ይሠጡታል። እንዲህ እንዲህ እያለ ስድስቱን ከጨረሰ በኋላ አንዱ ብቻውን ሲቀርና ማንም ተከላካይ እንደሌለው ሲያረጋግጥ "አያ በሬ መቼ ብበላህ ይሻለሃል?" ብሎ ያጠይቀዋል ብቻውን በመቅረቱ ከመበላት ውጪ አማራጭ እንደሌለው የተረዳውም በሬ ምንም ሳይመልስ በአንበሳው እግር ሥር ራሱን ለመበላት ተወ ይባላል።

## ተረት ሰላሳ ስድስት

በድሮ ጊዜ አውራ ዶሮ፣ አይጥ፣ እባብና ወፍ በጓደኝነት ይኖሩ ነበር። ከዕለታት አንድ ቀን በጋራ ጎሽ አድነው ይጥሉና ወደ አንድ ጎጆ ወስደው እኩል ለመካፈል ሲዘጋጁ አውራ ዶሮ ተንኮል ያስብና ወፏን ለብቻዋ ጠርቶ እባቡን ቢገድሉት የሚካፈሉት ሥጋ ብዙ ሊሆን እንደሚችል ይነግራታል። እሷም "እንደሱ ከሆነማ ቀላል ነው እኔ እራሴ እገድለዋለሁ" ብላ በመንቆሯ እራሱን ቸክችካ አይኑን አጥፍታ ትገድለዋለች። በዚህ ያላበቃው አውራ ዶሮ ወደ አይጥ ደሞ ይሄድና "ይህቺ ወፍ ብዙ ሥጋ ስለምትበላ እሷን ብንገድላት እኮ ለሁለት ሥጋውን መካፈል እንችላለን" ይላታል። አይጢትም "ይህማ ቀላል ነው" ብላ ወፊትን ጭራዋን አንጠልጥላ ድንጋይ ላይ ፈጥፍጣ ትገድላትና ሥጋውን ሁለት ቦታ ይካፈሉታል። አውራ ዶሮ አሁንም ሥጋውን ለብቻው መውሰድ ስለፈለገ አይጢትን "በይ አሁን ሥጋውን ወደየቤታችን ከመውሰዳችን በፊት የሚያየን ሰው እንደሌለ ወጥተሽ አረጋግጪ እኔ እዚሁ ሥጋውን እጠብቃለሁ በደንብ ዙሪያገባው እንዲታይሽ ደግሞ ትንሽ ሥጋ ቁረጭና አናትሽ ላይ አድርጊ" ይላታል። እሷም እንደነገራት አድርጋ ወጥታ ስትቃኝ ጆፌ አሞራ አንጠልጥሎ ይወስዳታል። በዚህ ጊዜ አውራ ዶሮ ሥጋውን ሰብስቦ እያሰረ ሳለ ውሻ ሽቶት ወደ ጎጆዋ ሲገባ አውራ ዶሮን ያገኘዋል አያ ውሾም አውራ ዶሮውን አንዴ "ሃኝ" ሲልበት እየጮኸ ጥሎ ይሸሻል። አያ ውሾም በአጋጣመው ሲሳይ እየተደሰተ ሆዱ እሲኪጠግብ በልቶ የተረፈውን ይዞ ሄደ ይባላል።

## ተረት ሰላሳ ሰባት

በዱሮ ጊዜ ፈፅሞ ሀሰት ተናግሮና ዋሽቶ የማያውቅ አንድ ሽማግሌ ሰው ነበረ። ሰውየው የምታምር ልጃገረድ ልጅ አለችው። እሷም አባቷን በጣም ትወደው

ስለነበር ማግባት የሚትፈልገው እንደሱ ዕውነተኛ ሰው እንደሆነ ትነግረዋለች። እሱም ልጁን የሚድረው ፈፅሞ ዋሽቶ ለማይውቅ ሰው እንደሆነ ይናገር ስለነበር ከዕለታት አንድ ቀን አንድ ሰው ወደ ስውየው መጥቶ መዋሸት ስለማያውቅ ልጁን እንዲድርለት ይጠይቀዋል። ሰውየውም ሊፈትነው ስለፈለገ በቅድሚያ "አብረሽኝ ወደ መንገድ ትሄዳለህ ስለዚህ ለስንቃችን የሚሆን ዳቦ ግዛ" ብሎ ገንዘብ ይሰጠውና ጉዞ ይጀምራሉ። ሲሄዱ ሲሄዱ ይውሉና ስለደከማቸው በጥላ ስር አረፍ ብለው እህል ለመቅመስ ይወስናሉ። ሰውየውም አንድ ዳቦ ያወጣና ለሽማግሌው ይሰጠዋል፤ ሽማግሌው የበላት ዳቦ ስላላጠገበችው እንዲጨምርለት ሲጠይቀው ሌላ አለመኖሩን ይነግረዋል። ከዚያም ተነስተው ጉዞኣቸውን ይቀጥላሉ። በመንገዳቸው ላይም አንድ ወርቅ የተሞላ ማሰሮ ያገኙና ለመካፈል ይቀመጣሉ። በዚህ ጊዜ ሽማግሌው ወርቁን ከሶስት ቦታ ዕኩል ይፍለዋል። ሰውየው ግራ ተጋብቶ "እኛ ሁለት ነን ሦስተኛው ድርሻ የማነው?" ብሎ ሲጠይቀው "እሱማ የስንቃችንን ዳቦ ለበላብን ሰው ነው" ይለዋል። "እንዴ ዳቦአችንን ማን የበላብን መሰለህ? እኔ እኮ ነኝ ሶስተኛው ድርሻ የኔ መሆኑነዋ" ሲለው "አንተ የለየልህ ስግብግብና ዋሾ እንደሆንክ በዚህ አረጋገጥኩ ወርቁንም ሆነ ልጄን መውሰድ አትችልም" ብሎ ጥሎት ሄደ ይባላል።

# አባሪ ሶስት ተጨማሪ ፎቶዎች

## የኔሪ ቦሪድ ህክምናዎች









## ቃለ መጠይቅ ከታካሚዎች ጋር





## የአጹም ጹም ጭፈራዎች











M2U00173


M2U00157





## የሀርሻ ጭፈራዎች






# አልጡሩምቢያ









# የወርቅ ግብይት





# የቡድን ውይይት











ቃለምልልስ ከአባ አቶም ሙስጦፋ ጋር



ቃለምልልስ ከአባ አልሀሰን አብዱራሂም ሆጀሌ ጋር





# አባሪ አራት የየቀን ውሎ ማስታወሻ

ይህ የውሎ ማስታወሻ ለመረጃ ስብሰባ በምስራባቸው ወረዳዎች በሦስት ጊዜያት ማለትም ከሐምሌ 11/ - ነሐሴ 9/ 2003፣ ከጥቅምት 4- ታህሳስ 30/ 2005 እና ከሚያዚያ 14- 2006 በቆየሁባቸው ቀናት በእየዕለቱ የገጠሙኝን ነገሮችና ያከናወንኳቸውን ተግባራት ያቀረብኩበት ነው፡፡

ለመጀመሪያው ጉዞ ከመነሳቴ በፊት ቀድሞ የማውቀው የበርታ ብሔረሰብ ተወላጅ የሆነ የአሶሳ ሰው  አዲስ አበባ ለአንድ ሳምንት ለገፅ ለገፅ ትምህርትና ለአለበት ፈተና መጥቶ ስለነበር ደውዬ ፈለግሁትና  ስለጉዞዬ አንዳንድ መረጃ እንዲሰጠኝ በቀጠሮ ተገኛኝተን ነበር፡፡ ሀሰን አልመሃዲ ይባላል፡፡ የምሄድበትን ዓላማ ከነገርኩት በኋላ በመረጥኩት ወረዳ ውስጥ የሚኖሩት አብዛኞቹ የበርታ ብሔረሰብ አባላት መሆናቸውንና መረጃ በማግኘት ረገድ ያለኝ ዕድል ግማሽ ግማሽ እንደሆነ እንዲህ በማለት አስረዳኝ፡፡ "በርታዎች መጀመሪያ ባገኙሽ ጊዜ ዓላማሽን በደንብ የሚያስረዳልሽ ሰው አግኝተሽ ከተቀበሉሽ እንደራሳቸው ስለሚቆጥሩሽ መረጃ የማግኘትም ሆነ በአካባቢው የመቆየት ምንም ችግር አይገጥምሽም፤ ነገር ግን በሆነ ምክንያት ከጠረጠሩሽና ካልፈቀዱሽ እንደዛው ምንም ነገር ሳታገኚ ልመለሺ ትመለሻለሽ፡፡ ስለዚህ ደህና ሰው መፈለግ ይኖርብሻል፡፡ በተረፈ ከዚህ ድረስ ሄደሽ ካለምንም ጥቅም ትመለሻለሽ ብዬ አላስብም አይዞሽ!" በማለት ዕውነቱን በግልፅ በመናገር አበረታታኝ፡፡

ስለመንገዱ ጠየቅሁት መንገዱ በአውቶቢስ ትንሽ አስቸጋሪና የሚያንገላታ መሆኑንና ከቻልኩ በአውሮፕላን ብሄድ የተሻለ እንደሚሆን፣ ማደሪያ ቦታን አስመልክቶም ሆቴሎች እንዳሉና ቀድሞ በመደወል ሊያሲዝልኝ እንደሚችል ነገረኝ ፡፡ ወደ ቤቴ ተመልሼ በአውሮፕላን ብሄድ ምን ያህል እንደሚያስወጣኝና ባለኝ ገንዘብ እንዴት ቆይቼ እንደምመለስ ከተወያየሁ በኋላ ከራሴ ገንዘብ ጨምሬም ቢሆን በአውሮፕላን መሄዱ የተሻለ መሆኑን ከባለቤቴ ጋር ስለተስማማሁ የደርሶ መልስ ትኬት ቆረጥኩ፡፡

**ሰኞ ሐምሌ 11 ቀን 2003 ዓ.ም.**

ለጉዞና ለቆይታዬ የሚያስፈልጉኝን ዕቃዎች አዘጋጅቼ ከአዲስ አበባ ቦሌ አየር ማረፊያ 6:30 ሰዓት ተነስቼ በጂማ - አሶሳ 8:45 ላይ ደረስኩ። ቀድሞ ወደ ተያዘልኝ ሆቴል ሄጄ ዕቃየን ካሳረፍኩና ከተጣጠብኩ በኋላ ለምሳ ወደ ሆቴሉ በረንዳ አመራሁ ። የምበላውን አዝዤ እንደተቀመጥኩ በመኝታ ክፍሎቹ የውጪ ግድግዳ ላይ የአልበርት አነስታይንና የዊሊያም ሼክስፒር ፎቶግራፎች በትልልቁ ተስለው አየሁ። ሆቴሉ ቀደም ሲል ትምህርት ቤት የነበረ ይመስላል። አልጋ አከራዩን ይህንኑ ጥርጣሬየን ሳነሳለት "ኧረ አይደለም ያውልሽ የእኛ አገሩም ሰው ፎቶ" ብሎ የኦሮሞ ሰው ምስል አሳየኝ። አይኖቼን በሁሉም አቅጣጫዎች ሳዟዙር አንድም የክልሉን ሰው የሚያሳይ ምስል አጣሁ። በጣም አስገረመኝም፤ ጥያቄም አጫረብኝ፤ በጥያቄዬ እንዳልገፋ አልጋ አከራዩ ጥሎኝ ሄዷል፤ እኔም ገና ከመምጣቴ… ብዬ ተውኩት።

10:30 ላይ ወደ ክልሉ ፕሬዘዳንት ጽ/ቤት አመራሁ። የመጣሁበትን ተናግሬና አስፈቅጄ ወደ ቢሮአቸው ገባሁ። ፕሬዘዳንቱ አቶ አህመድ ሀሰን ይባላሉ። የበርታ ብሔረሰብ አባል ናቸው። ቀደም ሲል የግብርና ሚኒስቴር ሚንስትር ዴኤታ ነበሩ። የመጣሁበትን ዓላማና ስለወደፊት የጥናቴ ዕቅድ በዝርዝር አስረዳኋቸው። ፍፁም ተባባሪ በሆነ መንፈስ ሀሳቡን ተቀብለው በሁሉም መንገድ የክልላቸው ባህል እንዲጠና ፍላጎት እንዳላቸውና በአምስት ዓመቱ የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅዳቸውም ውስጥ ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ በመሆኑ በክልሉ ባህል ዙሪያ የሚሰራን ማንኛውም ሰው በደስታ እንደሚቀበሉና ለእኔም የተቻለውን ሁሉ እገዛ እንደሚያደርጉልኝ ጠቅሰው ከክልሉ የባህልና ቱሪዝም ቢሮ ጋር በቅርብ እየተገናኘሁ እንድሠራና ወደ መረጥኩት ወረዳ ሄዶ ለመሥራት የሚያስችለኝ ደብዳቤ እንደሚጽፉልኝ፣ እንዲሁም አብራኝ በመሆን ቋንቋውን በማስተርጎምና አካባቢውን በማስተዋወቅ የምትረዳኝ ሴት እንደሚያዘጋጁልኝ ነግረውኝ በማግስቱ ለመገናኘት ቀጠሮ በመያዝ ተለያየን።

ለቆይታዬ ተስፋ ሰጪ ነገሮችን የሰነቅሁበት ቀን ነበር። ከዚያ በኋላ ያለውን ጊዜ ለማረፍ ስለፈለግሁ ወደ ሆቴሌ ሄጄ በጊዜ ተኛሁ። በሆቴሉ በከፍተኛ ድምጽ የሚጮህ ሙዚቃ ስለነበር የውጪው ድምጽ እንዳይረብሸኝ ቴሌቪዥን ከፍቼ አልጋ ውስጥ ገባሁ። ትንሽ ተገላብጬ እንቅልፍ ወሰደኝ ከምሽቱ 6፡02 ሰዓት ላይ የበረታ ድምጽ ቀሰቀሰኝና ነቃሁ። ከእኔ ክፍል ቀጥሎ ለአልጋ አከራዩ ቢሮ፣መኝታና ለጥገና ቁሳቁሶች ማኅሪያነት የምታገለግል ክፍል እንዳለች ቀን ሂሳብ ስከፍልና ስመዘገብ አይቻለሁ። የቀሰቀሰኝ ድምጽ ከዚያች ክፍል የሚመጣ ነው። የሆቴሉን መዘጋት በሙዚቃው ጩኸት መቋረጥ አረጋግጫለሁ። አከራዩና ሌላ ሰው ግን ጮክ እያሉ በኦሮምኛ ወሬያቸውን ያስነኩታል፤ ይስቃሉ፤ እኔ እደመጥ እኔ እደመጥ ይሻማሉ። ከሚያወሩት እንደተረዳሁት ሰውየው የአልጋ አከራዩ እንግዳ ነው ጮክ እያሉ የአገራቸውን ወሬ ይጠርቃሉ። ያሉበት አካባቢ የመኝታ ቦታ፣ ድምፃቸውም ደምበኞችን እንደሚረብሽ፣ ከጉዳይም አልጣፉት። እንደመናደድ ከጀለኝና እናቴ «የኦሮሞ እንግዳ!» የምትለውን ሳስታውስ ለብቻዬ አስፈገገኝ። የባህሉን ተፅዕኖ ግን ሳላጤነው አልቀረሁም። ምንም ማድረግ ስለማልችል ደክሟቸው ወይ እንቅልፍ ጥሏቸው ቶሎ እንዲያበቁ እየተመኘሁ መገላበጤን ተያያዝኩት።

**ማክሰኞ ሐምሌ 12 ቀን 2003 ዓ.ም.**

ዛሬ የክልሉ መንግስት ወደ ባህል ቢሮ የሚፅፍልኝን ደብዳቤ ወስጄ የዕለቱን ሥራ ለመጀመር ወደ ፕሬዘዳንቱ ቢሮ ሄጄ ሳለ የአንድ ወንድ ለቅሶ ሰማሁና ደነገጥኩ፤ "የፕሬዘዳንቱ ሾፌር መኪናዬን እጠብልኝ ብሎ በእንግዳ ፊት አዋረደኝ" ነው መነሻው። የጠገበ ኮበሌ ነው አማራ ይመስላል፤ ኦሮምኛም ይናገራል። ለቅሶውንና አለቃቀሱን ሳይ "የወንድ አልቃሻ!?" ብዬ ተገረምኩና የወንድ ልጅ ለቅሶው በሆዱ ነው የሚለውን የአማራ አባባል አስታወሰኝ። እዚህ ይሄ አይታወቅ ይሆን? እንዲህ በሆነ ባልሆነው ሲነፋረቁ ይሆን የሚውሉት በየአደባባዩ!? እግዜር ይወቅ።

ባህል ቢሮ 4:30 ላይ ደርሼ ከክልሉ የተፃፈልኝን ደብዳቤ ሰጠሁ። የቢሮ ኃላፊው የሉም፤ ተወካዩ አንድ ሌላ ኤክስፐርት ጨምረው አነጋገሩኝ። ዓላማዬን ካስረዳሁ በኋላ በቢሮው እስከ ዛሬ የተሰሩ ጉዳዮችን ማየት እንደምችልና ለመረጥኩት ወረዳም ደብዳቤ እንደሚጽፉልኝ ነገሩኝ። ከዚያ ሰዓትም ጀምሬ በየብሔሩ ባህል ላይ የተሰሩ ሥራዎችን ለብቻዬ የማንበቢያ ክፍል ተዘጋጅቶልኝ ቀኑን ሙሉ ሳነብ ዋልኩ። ከንባቤ እንደተረዳሁት የተወሰኑ ጅምር ሥራዎች አሏቸው አብዛኞቹ በመለስተኛና በሁለተኛ ደረጃ መምህራን የተደረጉ ሙከራዎች ናቸው። "የአምስቱ ብሔረሰቦች ሥነቃል ስብስብ (የመጀመሪያ ሥራ)" በሚል ርዕስ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ትምህ/ባህል ቢሮ በ1996ዓ.ም የተሠራ ባለ 24 ገጽ ሥራና የሽናሻ ብሔረሰብ ባህል አጭር ቅኝት በሚል ርዕስ በቤ/ጉ/ የወጣቶች ስፖርትና ባህል ቢሮ በ1996 ዓ.ም. የተሠራ ባለ 32 ገጽ ሥራ በዚህ ቀን አንብቤ ዋልኩ።

ለነገም የቀሩኝን ለማንበብና በአስተርጓሚነት የተመደበችልኝን ሴት ከሄደችበት ወረዳ እስክትመጣ ለመጠበቅ ወስኛለሁ።

የክልሉ መንግስት የእንግዳ ማረፊያ እንዲሰጠኝ ስለፈቀደልኝ ዛሬ ከሆቴል ወደዚያው ተዛውሬአለሁ ። ፀጥ ያለ ቦታ ስለሆነ በሰላም ለመቀዘም፣ ለማንበብና ለማረፍ ምቹ ቦታ በመሆኑ ቆይታየን ያቀልልኛል ብዬ እገምታለሁ።

**ረቡዕ ሐምሌ 13 ቀን 2003 ዓ.ም.**

ዛሬ የጀመርኩትን ንባብ በባህል ቢሮ ለመቀጠል 2:45 ላይ ተገኘሁ። 4:30 ላይ አቶ አክሊሉ (የባህል ኤክስፐርት) ቡና ያስፈልገኝ እንደሁ ወጥተን መጠጣት እንደምንችል ነገረኝ። በአቅራቢያው ወደሚገኝ "የጀበና ቡና" የሚሸጥበት ቤት ወሰደኝ። ቤቱ ከአካባቢው በተገኘ ቀርከሃ የተሰራ ዛኒጋባ ሆኖ በአስፓልት ዳር የሚገኝ ነው። መቀመጫውን ጨምሮ ጠረጴዛዎቹና ሌሎች ቁሳቁሶች ከቀርከሃ ባህላዊ በሆነ መንገድ የተሠሩ ናቸው። በርካታ ሲኒዎች የተደረደሩበት ሰፊ ረከቦት ተሸፍኖ ከፍ ያለ መደብ መሰል ቦታ ላይ ተኮፍሷል። ከፊት ለፊቱ አንድ የአካባቢው፣ አንድ የመሃል አገሩን የሚመስሉ እጣን ማጨሻዎች

ተቀምጠዋል፡፡ የተጎዘጎዘው ነገር አረንጓዴ የዛፍ ዝንጣፊ ሲሆን ስሙን ጠይቄ የሚነግረኝ ሰው አላገኘሁም፡፡ የኒም ዛፍ ዝንጣፊ ይመስላል፡፡ የቡና ቤቷ ልጅ የጎዘጎዘችው ግን ቄጤማን እንዲተካላትና ካለ ዋጋ በቅርቧ ካለ ዛፍ ቆርጣ ያመጣችው መሆኑን ነግራኛላች፡፡ በአንዱ የቤቱ ጥግ አንዲት ልጅ እግር ሴት ግማሽ ኪሎ የሚሆን ቡና በመጥበሻ ላይ አድርጋ ትቆላለች ሳይሆን ታምሳለች፡፡ ይሄ ሁሉ ቡና እንዴት በአንድ ላይ ተስተካክሎ እንደሚበስል አምላክ ይወቅ፡፡

ለእኛ የመጣልን ቡና ቀድሞ ፈልቶ የተዘጋጀ ነው፤ አንድ አንድ ስኒ ጠጥተን ስድስት ብር ከፍለን ወጣን፡፡ ስንወጣ ስገባ ልብ ያላልኩት የዛኒጋባው ግድግዳ ከውጪ በረጃጅም ሰንበሌጥ የተሸፈነ መሆኑን አየሁ፡፡ በበጋ ወራት ሙቀቱን ለመከላከል እንደሆነ ኤክስፐርቱ ነገረኝ፡፡

ከሰዓት በኋላ ግማሹን ጊዜ የተረፈኝን ንባብ በመቀጠል፣ "የማኦና ኮሞ ብሔረሰቦች ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎችና አጨፋፈር" በሚል ርዕስ በታደሰ ፊጤ በ1997 ዓ.ም. በወጣቶችና ባህል ቢሮ የተሠራ ባለ 16 ገፅ ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎችን የሚያሳይ ሥራ፣ "የሥርዓተ ፆታ ጉዳዮችና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በኮሞ ብሔረሰብ" በሚል ርዕስ በገዛኸኝ ግርማና አብዮት ሽፈራው በ2000 ዓ.ም የተሠራ 68 ገጽ ያለው መለስተኛ ጥናት በማንበብ አሳላፍኩ፡፡ ለእኔ ስለክልሉ ብሔረሰቦች ባህል እንዳውቅ በዓይን መክፈቻነት ያገለገሉኝ ስራዎች ናቸው፡፡

ግማሹን ደግሞ በቢሮው የኤግዚቢሽን ክፍል የሚታዩትን የአምስቱን ነባር ብሔረሰቦች (የበርታ፣የጉሙዝ፣የሺናሻ፣ የማኦና የኮሞ) ባህላዊ የሥራና የሙዚቃ መሣሪያዎች ፎቶግራፎችና ሥዕሎች ስጎበኝ ቆይቼ በቀሪው ጊዜ የሼህ ኦጄሌን ቤት ለማየት ሄድኩኝ፡፡

ቤቱ ብቻውን ያለአጥር የቆመና ዙሪያውን እንዳይወድቅ በባላዎች የተደገፈ የሳር ቤት ነው፡፡ በዙሪያው ኑዋሪዎች በቅርብ ስላሉ የጓሮ አትክልቶችን አልምተዋል፡፡ ቤቱ ምንም ጥበቃ የማይደረግለት ባዶ ቤት እንደሆነ ተነግሮኛል፡፡ ፎቶግራፍ ከውጪ አንስቼው ተመለስኩ፡፡

ዛሬም የምጠብቃት ሴት አልገባችም ግን በስልክ ተገኝታ ዛሬውኑ እንደምትመጣ ተናግራለች። እግዜር ይርዳኝና ትግባልኝ። እሷ ከገባችና ሁኔታዎች ከተመቻቹ ነገ ወደ ባምባሲ ወረዳ የምሄድ ይመስለኛል።

**ሐሙስ ሐምሌ 14 ቀን 2003 ዓ.ም.**

ዛሬ ሲቲና ስለመጣች ተገናኘን ። ሲቲና ጥቁር ረጅም ፍልቅልቅ በርታ ነች። አማርኛ ኦሮምኛ ትግሪኛ፣ በርትኛና አረብኛ አቀላጥፋ መናገር ትችላለች። ለመግባባት ጊዜ አልወሰደብንም የመጣሁበትን ስነግራት በሁሉም መልክ ልትረዳኝ ዝግጁና ፈቃደኛ መሆኗን ስለገለፀችልኝ ደስ አለኝ፤ ነገር ግን ነገ ሸርቆሌ ወደሚባል ወረዳ ስለምትሄድና የምትመለሰው ከሶስት ቀን በኋላ በመሆኑ ከሰኞ በኋላ መገናኘት እንደምንችል ስትነግረኝ አብሬያት ሸርቆሌ መሄድ እችል እንደሁ ጠየቅኋት፤ ደስ እንደሚላትና እንደውም ወረዳው የበርታዎች መኖሪያ በመሆኑ ብዙ የበርታ ሽማግሌዎችን ልታገናኘኝ እንደምትችል ስትነግረኝ አብሬያት ለመሄድ ተነሳሳሁ።

ከሲቲና ጋር አብረን ምሳ ከበላን በኋላ ቡና ለመጠጣት ሌላ የታወቀ የጀበና ቡና ቤት ይዛኝ ሄደች። ቤቱ በስፋቱም ሆነ በአደረጃጀቱ ከትናንቱ በጣም ትልቅ ነው። በርካታ የበርታ ጀበናዎች የዳቦ መጋገሪያ ገበር ምጣድ ውስጥ የከሰል ፍም ተደርጎበት ተደርድረው ሲታዩ ቡናው የሚጠታው በጀበና እንጂ በስኒ አይመስልም። በጣም አስደነቀኝ፤ ሌሎች በመጠናቸው ትላልቅ የሆኑ አራት ጀበናዎች ደግሞ ተቀጣጥሎ በተሠራ አራት የከሰል ማንደጃ ላይ ተጥደዋል። እንደዚህ ያለ የተለያየ ምድጃ ያለው ከሰል ማንደጃ አይቼ አላውቅም። በአጠቃላይ ቤቱ ጀበና ብቻ በመሆኑ የጀበና ማምረቻ እንጂ የቡና መጠጫ ቤት አይመስልም።

የጀበናዎቹ መብዛት በጣም ስላስገረመኝ ሲቲናን ጠየቅኋት፤ ጀበናዎቹ የበዙት በበርታ ባህል ቡና አንዴ በአንድ ላይ በገባው ሰው ልክ ብቻ ስለሚፈላና ከአንድ ጀበና ለመጣ ለሄደው ስለማይቀዳ እንደሆነና ዝርዝሩን በኋላ ልትነግረኝ ተስማማን። ለእኛ ከተደረደሩት ጀበናዎች አንዱ ተነስቶ ለሁለታችን ብቻ ሁለት ስኒ ተቀድቶልን ተመለሰ። አጠገባችን

ከእኛ ተከታትለው የገቡ ሰዎች ነበሩ ለእነሱ ለእኛ ከመጣው ጀበና አልተቀዳላቸውም ሌላ ጀበና መጥቶ ሁለት ስኒ ብቻ ተቀዳላቸው።

ጀበናዎቹ በመሃል አገር "የትግሬ ጀበና" በመባል የሚታወቀው ጡት የሌለው ጀበና በመሆኑ የሚቀዳው በአፉ ነው። ቡናውን አንስቼ ቀመስኩት ግሩም ጣዕም ያለው ቡና ነበር። ይህንን የቡና ጣዕም ከ25 ዓመት በፊት ግምቢ/ወለጋ ሥራ ስጀምር ሄጄ የቀመስኩት ዓይነት መሆኑ አስገረመኝና የዬት አገር ቡና እንደሆነ ባለቤቷን ስጠይቃት የግምቢ ቡና መሆኑን አረጋገጠችልኝ።

በሥራ ላይ ያሉትንና ለታይታ የተደረደሩትን ጀበናዎችና ስኒዎች አስፈቅጄ ፎቶግራፍ አንስቼ ለሁለት ስኒው ቡና የተለመደውን ስድስት ብር ከፍለን ወጣን።

ከሰዓት በኂላ ሲቲና ሥራ ስላላት ተለያየን። እኔም እንድትረዳኝ ስላዘጋጁልኝ ሴት የክልሉን ፕሬዘዳንት ለማመስገን ወደ ቢሮቸው ሄጄ ሸርቆሌ የመሄድ ሀሳቤን ስነግራቸው በጣም ተደስተው እንደውም እዚያ ወረዳ ከባምባሲ ይልቅ ያልተነካካውን ባህል ላገኝ እንደምችል በመጥቀስ ለጉዞ የሚሆን መኪና እንደሚያዘጋጁልኝ ሲነግሩኝ በጣም ተደሰትኩ። አመስግኜአቸው ቀሪውን ጊዜ በባህል ቢሮ በንባብ አሳለፍኩ።

ወደ 11፡00 ሰዓት ላይ ከሲቲና ጋር ተገናኘንና ስለ አካባቢው ስጠይቃት ህዝቡ እንግዳ ተቀባይና ሙስሊም ህብረተሰብ እንደሆነ ስትነግረኝ ፕሬዘዳንቱ "ያልተነካካውን" ባህል ካሉኝ ጋር እና ከአዲስ አበባ ስነሳ ሀሰን "አንዴ ከተቀበሉሽ" ያለኝን አገናዝቤ አለባበሴን ማመሳሰል እንዳለብኝ ወስኜ ሲቲናን የበርታ ሴቶች የሚለብሱትን ባህላዊ ልብስ እንድታጋዛኝ ጠየኳት ። ወደ ሱቅ ሄደን "ቶብ" የሚባለውን የባህል ልብስ እስከ አላባሹ በብር 370 ገዛን። ቶብ አራት ሜትር ተኩል የሆነ ብትን ጨርቅ ሲሆን የተለያየ ደረጃ አለው እንደጥራቱ ከ200 ብር እስከ አንድ ሺህ ብር የሚሸጥ ቶብ አለ። ሲለበስ ከውስጥ ፒጃማ ወይም ውስጥ ልብስ መሰል ቀሚስ ይለበስና ቶቡ በአንድ በኩል በሰውነት ልክ ትከሻ ላይ ታስሮ የሚተርፈው ሰውነት ላይ በመጠምጠም እስከ እራስ ጭምር በመሸፈን ይጣፋል። ከአዲስ አበባ ስነሳ የአለባበሴን ጉዳይ አስቤበት ስለነበር በተለያዩ ጊዜ በስጦታም

በግዢም ያጠራቀምኳቸውንና ጭራሽ ለብሼያቸው የማላውቃቸውን የሙስሊም ድሪያዎች ይዤ ነበር ። ሆኖም የበርታው ቶብ ከዚያ ስለሚለይ ገዛሁና እነሱን ለመቀየሪያ አዘጋጀኋቸው።

**አርብ ሐምሌ 15 ቀን 2003 ዓ.ም.**

የምንሄድበት ወረዳ ሸርቆሌ ከአሶሳ 90 ከ/ሜ ትርቃለች፤ ሲቲና እኔና ሾፌሩ ሆነን ቁርስ በላንና ለጉዞ የሚያስፈልጉንን አንዳንድ ነገሮች ገዛዝተን ልክ 3:00 ሰዓት ላይ ጉዞ ጀመርን። ድሪያዬን ለብሼና ተከናንቤ እውነተኛ ሙስሊም መስያለሁ። የምንሄድበት የጠጠር መንገድ ሆኖ አንዳንድ ቦታ የተጎዳ በመሆኑ እንደልብ ስላላስኬደን አንድ ሰዓት ከሰላሳ ደቂቃ በኋላ ሸርቆሌ ደረስን። ወረዳው የሲቲና የትውልድ አካባቢ በመሆኗ ሁሉም ሰው ያውቃታል፤ ከተማዋ እጅግ አነስተኛ የገጠር ቀበሌ ነች፣ በአብዛኛው የበርታ ብሔረሰብ አባላት የሚኖሩባት ስትሆን ጥቂት ኦሮሞዎች አንዳንድ አማሮችና ትግሬዎች ይኖሩባታል። ቤቶቹን ቆጥሮ ለማዳረስ ብዙ ጊዜ አይፈጅም ጥቂት ሱቆች አራት አምስት ሆቴል መሰል ነገሮች አራት አምስት ጫት መሸጫዎች አምስት ሱቆች ጥቂት መኖሪያ ቤቶች በቃ ። አንድ አነስተኛ ጤና ጣቢያ፣ አንድ አንደኛ ደረጃና አንድ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አንድ ፖሊስ ጣቢያና ጥቂት የአስተዳደር ቢሮዎች ደግሞ ያሉት መንግስታዊ ተቋማት ናቸው አበቃ።

ሲቲና አንዳንድ ጉዳዮቿን ከተኳኮሰች በኋላ መረጃ ሰጪዎችን ሊያገናኙን የሚችሉ ሰዎችን አፈላልጋ አገኘች፤ ቀኑ አርብ በመሆኑ ግን ሽማግሌዎቹ ከሰላት ሲመለሱ እንደሚያገናኙን ስለነገሩን ወደ «ሲቲና ፓላስ» አመራን።

**«ሲቲና ፓላስ»**

ሲቲና ለሸርቆሌ ወረዳ የስኳርና ዘይት ጅምላ አከፋፋይ ነጋዴ ነች። ከአሶሳ ባላት የጅምላ ንግድ ፈቃድ ስኳርና ዘይት እያመጣች ለሸርቆሌ ቸርቻሪ ነጋዴዎች ታከፋፍላለች። ዋነኛ መኖሪያዋ አሶሳ ቢሆንም ሸርቆሌ ለሥራ ስትመጣ የምታርፍባት ቤት አለቻት። ሸርቆሌ

አልጋ አይገኝም፤ ያለውም አንድ ሆቴል ውስጥ ሁለት አልጋዎች ብቻ ናቸው ያሉት፡፡ ስለዚህ እንግድነት ሄዶ የሚታደረው በየዘመዱ ቤት ነው፡፡ እንደኔ ለሥራ የሄደ ሰው ያሉትን አልጋዎች ማግኘት ካልቻለ እየተዳበለም ቢሆን ማደር ግዴታው ነው፡፡ ደግነቱ በበርታ እንግዳ ክብርና ብርቅ ስለሆነ ወደ አንዱ አልከልዋ ጠጋ ብሎ አሰላማሊኩም ማለት ብቻ ነው፤ ተንከባክበው ያሳድሩታል፡፡

የሲቲና ፓላስ የተሰራችው በአካባቢው በቀላሉ ከሚገኘው ቀርከሃ እና ሰንበሌጥ ነው፤ ግድግዳው በቀርከሃ ተገድግዶ ጭቃ ተመርጓል፤ ጣሪያው ከውስጥ ላስቲክ ተወጥሮበት በሰንበሌጥ ተከድኗል፤ መዝጊያዋ መሽጎሪያና ቁልፍ ማስገቢያ የተሰራለት አንድ አሮጌ ቆርቆሮ ነው፡፡ አጥር ቅራቅንቦ የሚባል ነገር የለም፤ ለብቻዋ ጉብ ብላለች «ሲቲና ፓላስ»፡፡ የማብሰያና መታጠቢያ ቤት ብቻ ከጓሮ ሌላ አለ፡፡ ከፍተን እንደገባን ሙሉ ዕቃ ያለባት ባለ  ሳሎንና አንድ መኝታ ክፍል ቅልብጭ ያለች  ቤት መሆኗን ስመለከት ተገረምኩ፡፡ ሲቲና አንቺ አሶሳ ስትሄጂ ማን ይጠብቅልሻል የሚያድርልሽ ሰው አለ? ብዬ ጠየቅሁ፡፡ ማንም የለም ስሄድ ቆልፌ እሄዳለሁ፤ ስመለስ ከፍቼ እገባለሁ አለችኝ አቃልላ፡፡ እንዴት ሌባ ምናምን የለም? አልኳት፡፡ አይ ሌባ የሚባል ነገር በበርታ አይታወቅም ማንም የማንንም ሀቅ አይነካም፤ ሀራም ነው፡፡ ሰው ከተቸገረ ማህበረሰቡ ይረዳዋል፤ ያበላዋል፤ ያጠጣዋል እንጂ ስርቆት አይታወቅም እና ቆልፌ እሄዳለሁ፤ በመጣሁ ጊዜ ከፍቼ እገባለሁ አለችኝ፡፡ በሁኔታው እየተገረምኩ ምሳችንን እዚያው ሰርተን ቡናችንን ጠጥተን ወጣን፡፡

ለመረጃ ሰጪነት የተፈለጉት ሽማግሌ ከሰላት መልስ ሲፈለጉ ዛሬ አለመኖራቸውንና አሶሳ መሄዳቸውን እንደተነገራቸውና ሲመለሱ እንደሚያገናኙን የተላኩት ሰዎች መጥተው ነገሩን፡፡ በዚህ መሀል ሲቲና አንድ ሀሳብ አመጣች፡፡ ከሽርቆሌ በ8 እና በ10 ኪሎ ሜትር ላይ አንድ የባህል መድሃኒት አዋቂ እንደሚገኙና እሳቸውን ሄደን ብናነጋግራቸውስ አለችኝ፡፡ እኔም በፍጥነቷ ተገርሜ በጣም ደስ እንደሚለኝ ነግሬያት ከሽርቆሌ አንድ ሴት በርታ (ዘመዷ) ናት ጨምረን በመኪና ወደዛው አመራን፡፡ ከመኪና ወርደን ሰላሳ ደቂቃ ያህል እንደተጓዝን አንድ በበርካታ ጎጆዎች የተከበበች ንፁህ መንደር

ደረስን:: አለባበሴ እንደእነሱ ስለነበር የሚቀበሉኝ በፈገግታና በቤተኛ ስሜት ነበር:: ያገኘናቸውን ሰዎች ሰላም እያልን ወደ ሽማግሌው ቤት አመራን:: ቋንቋቸው በርትኛ ቢሆንም ሰላምታቸውን ጨምሮ በአብዛኛው ንግግራቸው የአረብኛ ቃላትን ይጠቀማሉ:: ሲገናኙ "አሰላማሊኩም ማሊኩም፤ አሰላም" ተባብለው እጃቸውን አንስተው መዳፋቸውን በየደረታቸው ላይ በማድረግ አለዚያም በመተቃቀፍና ትከሻ ለትከሻ በመግጠም ለረጂም ጊዜ ስለጤንነታቸው እየተጠያየቁ ይቆያሉ:: ይሄ ለመጤውም ሆነ ለራሳቸው ብሔር አባል አንድ ዓይነት ነው እኔንም እንዲሁ ነው ሰላም የሚሉኝ ቢደናገረኝም እነሱ የሚያደርጉትን እያየሁ ቀጠልኩ::

ሽማግሌው ቤት ስንደርስ እቤት አለመኖራቸው ተነገረን:: እኛን ወደ አንደኛዋ ሚስታቸው ቤት እንድንገባ ነግረውን ሽማግሌውን የሚጠራ ሰው ላኩልን::

ቤቱ እንደማንኛውም የገጠር ቤት ከውጪ ሲያዩት የሳር ክዳን ቤት ነው፤ በሩ አጭር በመሆኑ በጣም ዝቅ ካላሉ ለመግባት ያስቸግራል፤ ወደ ውስጥ ስንዘልቅ የቤታቸው አያያዝ ያስደነግጣል፤ ቤቱ እጅግ ንፁህና በሥርዓቱ የተያዘ ነው፤ ዙሪያውን ደማቅና ንፁህ አልጋ ልብሶች የተነጠፈባቸው አራት አልጋዎች ተደርድረዋል በአንድ ጥግ ቆጥ ነገር ተሰርቶለት አራት ኩንታል ማሽላ ተደርድሮ ይታያል:: በሌላው ጥግ በመለስተኛ ጠረጴዛ ላይ የተወሰኑ የቤት ቁሳቁሶች ተደርድረዋል:: ማብሰያ ክፍላቸው ለብቻ በመሆኑ ከዚህ በላይ ዕቃ በቤቱ ውስጥ አይታይም:: ከአንዱ ግድግዳ ጥግ ወደ ሌላው ረጅም ገመድ ተዘርግቶ ቶብ የሚሰኘው የሴቶቹ የባህል ልብስ በሥርዓቱ እየታጠፈ ተሰቅሎ ሲታይ ለሽያጭ ወይም ለምርጫ የተዘጋጀ ይመስላል:: ልዩ ልዩ ህብረ ቀለማት ስላሉትም ለጎጆዋ ልዩ ድምቀትን ሰጥቷታል::

ገብተን በአንዱ ጥግ ባለ መለስተኛ ድንክ ላይ እንደተቀመጥን በጀግ ውሃ ከላዩ ላይ ብርጭቆ ለመጨለፊያ ተቀምጦበት ከፊታችን ቀረበ:: ማንኛውም እንግዳ ከሩቅ የሚመጣ በመሆኑ የእግር መንገዱና ሙቀቱ አድክሞት እቤት ሲገባ ሌላ ነገር ከመቅመሱ በፊት ውሃ በትንሹ መጎንጨት ይኖርበታል:: ወይም ተጉመጥሙጦ በመትፋት ልቡን

ማቀዝቀዝ አለበት፡፡ ምን ቢጠማው እቤት እንደገባ ውሃውን ግጥም አድርጎ መጠጣት "ልብን ይሰብራል" ተብሎ ስለሚታሰብ በመጠኑ መጎንጨት ወይ መጉመጥመጥ ነው ያለበት፡፡ ከውሃው ላይ ካለ የእንጀራ ፍቅፋቂ የሚመስል ድርቆሽ ነገር "አላብሬ" ይሉታል በተን ተደርጎበትም ሊቀርብ ይችላል፤ ከሌለ ግን ውሃው ብቻውን ይቀርባል፡፡ እኛም እንደባህሉ ከውሃው ተጎነጨን፡፡

የገባንበት ቤት የሽማግሌው ሁለተኛ ሚስት ቤት ነው፡፡ ሚስትየዋ ጉድ ጉድ ማለት ስትጀምር ሲቲናን እባክሽ እንዳይቸገሩ ምንም ነገር እንዳታደርግ ንገሪያት አልኳት፤ በእኛ እንዲህ አይባልም የምታደርገው ማድረግ የምትችለውን ብቻ ስለሆነ ዝም ብሎ የሚቀርበውን መስተናገድ ብቻ ነው፤ በበርታ ለይሉኝታ ተብሎ የሚደረግ ነገር የለም አትስጊ አለችኝ፡፡

እንግዳ መምጣቱን የሰሙ በአካባቢው የሚገኙ ሰዎች አንድ አንድ እያሉ ወዳለንበት ቤት መሰብሰብ ጀመሩ፤ሁሉም ሰላምታቸው ረጅምና ለሁላችንም እኩል ነው እንግዳ ስለመጣ ደስ የተሰኙ ይመስላሉ ሁሉም ፊታቸው በደስታ ያበራል፡፡

ሽማግሌውን ሊጠራ የሄደው ሰው ይዟቸው መጣ፤ አጭር ጥቁር ጠና ያሉ በርታ ናቸው፡፡ አባ ቤሎ አቦቴ ይባላሉ፡፡ በአንድ ትከሻቸው ቦርሳ የምትመስል አነስተኛ የሰሌን ኮሮጆ አንግተዋል፡፡ በአንድ እጃቸው አንካሴ ይዘዋል መድሃኒት ሊቆርጡ የሄዱ ይመስላል አንካሴውን ከውጪ በር ላይ ሰክተው ወደ ውስጥ ዘለቁ ከጥቁር ፊታቸው ውስጥ ጥርሳቸው እንደ ፀሐይ ያበራል፡፡ ተነስተን ተቀበልናቸው ሁላችንንም እያቀፉ ሰላምታ ሰጡን ለእኔና ለእነ ሲቲና የተለየ ሰላምታ የላቸውም እኔንም ልክ የሚያውቁኝና ናፍቀውኝ የቆዩ ይመስል ደግመው ደግመው እያቀፉ በቋንቋቸው ጤንነቴን እየጠየቁ ሰላም አሉኝ፡፡ ሁሉም በርታዎች እንደዚያ ናቸው፤ እኔም እንዲህ ሲሆን እንግድነት ስላልተሰማኝ በጣም ደስ አለኝ፡፡

አነስ ያለች መደገፊያ ያላት መቀመጫ ቀርባላቸው ከፊት ለፊታችን ተቀመጡ፤ ከሲቲና ጋር ከተገናኙ ብዙ ጊዜ ስለሆናቸው ደጋግመው ጤንነታቸውን ይጠያየቃሉ፡፡

የመጣንበትን ዘርዝራ ነገረቻቸው በፈገግታ እየተመለከቱኝ ያዳምጠጧታል። በዚህ መሃል ጉድ ጉድ ስትል የነበረችው ትንሽዋ ሚስታቸው ሶስት ብርጭቆዎችና በአነስተኛ ጆግ የሎሚ ጭማቂ ይዛ ገባች። ከሽርቆሌ የሄድነው ሦስት በመሆናችን የቀረበው የሎሚ ጭማቂ ለሶስታችን ተቀድቶ አለቀ። አባ ቤሎን ጨምሮ ሌሎቹ አልተሰጣቸውም። እኔ ግራ ገባኝ ቢያንስ ሽማግሌው ከዱር መጥተው ለዚያውም የቤቱ አባወራ ሳይሰጣቸው ለእኛ ብቻ ተቀድቶ በማለቁ ለእሳቸውስ ብዬ ለመግደርደር ቃጣኝ። ሲቲናን እሳቸውስ ስላት ዝም ብለሽ የቀረበልሽን ጠጪ በኋላ እነግርሻለሁ አለችኝ።

በበርታ ባህል ለእንግዳ የሚዘጋጅ ነገር የእንግዳው ብቻ ነው ቀድሞም በእንግዳው ቁጥር ልክ ተመጥኖ ስለሚዘጋጅ የሚተርፍ ነገር የለም። እንግዳ ስለመጣ አባወራው ቅድሚያ አይሰጠውም ካስፈለገ ለእርሱ ሌላ ይዘጋጃል፤ ሌላው ቀርቶ ሁለት እንግዶች በተለያየ ጊዜ ተከታትለው ቢገቡ ለመጀመሪያው እንግዳ ከተዘጋጀው ለሁለተኛው ወይም ዘግይቶ ከመጣው ጋር አብሮ ምግብ አይቀርብም። እንዳገባባቸው ለየብቻ ተዘጋጅቶ ይቀርብላቸዋል። ቤተሰቡ ቡና እየጠጣ ወይም እየተመገበ እንግዳ ቢመጣ ለቤተሰቡ ከተዘጋጀው ቡና አንዱ አባል ቀርቶበት አይሰጠውም። ለቤተሰቡ የተዘጋጀው ለቤተሰቡ ይሰጥና ለእንግዳው ሌላ ይዘጋጃል እንጂ ቅድሚያ ብሎ ነገር የለም ሁሉም የዕድሉን ሁሉም ለጉሮሮው የታዘዘለትን ያገኛል እንጂ የአንዱን ለአንዱ መስጠት በበርታ ባህል አይታሰብም ።

ትልቋ ሚስታቸው መምጣታችንን ሰምተው ከቤታቸው መጡ። ሰላምታውን እንደተለመደው ለሁላችንም እኩል ከሰጡ በኋላ ከአባ ቤሎ ጎን ተቀመጡ። የበርታ ሰላምታ አንድ ጊዜ ተደርጎ የሚያበቃ አይደለም ካስፈለገ፣ ከናፈቁ፣ወይ ከተቀበሉ በየጨዋታው መሃል እየተነሱ እንደ አዲስ እያቀፉ ሰላም ሊሉ ይችላሉ። ትልቋ ሚስትም "አይ ሲቲና!!!" እያሉ በየመሃሉ እየተነሱ ከሶስት ጊዜ በላይ ሰላም ብለዋታል፤ ታዲያ አያዳሉም እኔም የሚሉኝ ባይገባኝም እቅፍ እያደረጉ እንደሷው ሰላም ብለውኛል።

ለአባ ቤሎ ሲቲና የመጣሁበትን ስትነግራቸው ደስ ብሏቸው የምፈልገውን መረጃ ሁሉ ሊሰጡኝ እንደሚችሉ ቃል ገቡልኝ። ከዚህ በኋላም እንደቤተሰባቸው አባል እንደሚቆጥሩኝና እዚያ ድረስ ሄጄ ስለጠየኳቸው ደስ እንዳላቸው ነገሩኝ። በማግስቱ ቅዳሜ ስለሆነ ሽርቆሌ ገበያ በመሆኑ እዚያ እንደሚመጡና ቃለምልልሱን እዚያው ማድረግ እንደምንችል ተስማማን።

በዚህ መሃል የልጃቸው አንደኛዋ ሚስት ሻይ አፍልታ ከትንሽ ፔርሙስና ከሶስት ብርጭቆዎች ጋር ይዛ በመምጣት አሁንም ለሶስታችን ብቻ ቀድታ ሰጠችን። በመጀመሪያ በዚያ ገጠር ውስጥ ብርጭቆና ፔርሙስ መኖሩ በራሱ በጣም አስደነቀኝ። ሁለተኛ በሻዩ መልክ በጣም ተገርሜና ጎምጅቼም አንስቼ ስቀምሰው  በህይወቴ እንደዚያ ግሩም ጣዕም ያለው የሚጣፍጥ ሻይ ቀምሼ እንደማላውቅ ተሰማኝ። ያለሁት ገጠር በበርታ አርሶ አደሮች ቤት መሆኑ እጅግ አስደነቀኝ። ምን ዋጋ አለው ድገሙኝ እንዳልል የተፈላና የቀረበው ሶስት ብርጭቆ ብቻ። ያለኝ ዕድል ቃናውን ምላሴ ላይ አስቀርቼ እየተገረምኩ መሄድ ብቻ ነው። ንጽህናቸውና ምጣኔያቸው በጣም ያስገርማል። ውጪ ወጣንና ፎቶግራፍ እንዳነሳቸው ፈቃዳቸውን ጠይቄ ካነሳኋቸው በኋላ ለነገ ቀጠሮ ይዘን ተለያየን።

የትራንስፖርት ብር ለአባ ቤሎ ስሰጣቸው እጄን ይዘው በአጭሩ "ሽኩረን" አሉኝ። ብዙ መደነቅ ስላላየሁባቸው አንሷቸው ይሆን እንዴ? ብዬ ሲቲናን ስጠይቃት "አያንሳቸውም አሁን አንቺን እንደ ቤተሰባቸው ስላዩሽና ስለወደዱሽ በምታደርጊው ነገር ሁሉ ከዚህ የበለጠ አያመሰግኑሽም። ምክንያቱም ልጃቸው ሆንሽ በቃ። ብታደርጊም ቤተሰብ ስለሆንሽ ነው፤ ባታደርጊም ስለሌለሽ ነው። በእነሱና በአንቺ መካከል ከዛሬ ወዲያ ይሉኝታ የለም በቃ። ከፈለጉ አንቺ ባትሰጫቸውም የሚያስፈልጋቸውን ሊጠይቁሽ ይችላሉ። ካለሽ ታደርጊያለሽ፤ የለኝም ካልሽ ደግሞ ሰስተሽ ሳይሆን ስለሌለሽ ነው ብለው ያምናሉ። በበርታ ያለሽን ማካፈል እንደሰላምታ ነው፤ የሚያስደንቅ፣ አንዱን ረጂ ሌላውን ተረጂ የሚያደርግ አይደለም። ስለዚህ ብዙም ያላመሰገኑሽ ስለወደዱሽና እንደልጃቸው ስላዩሽ እንጂ የሌላ አይደለም።" አለችኝ ሲቲና። አቤት ባህል! ይሉኝታ የሌለበት ንጹህ ወዳጅነት እንዴት ደስ ይላል።

ዕውነት ለመናገር እኔ ራሴ ዘመዶቼ ቤት ሄጄ የተመለስኩ እንጂ ቋንቋና ባህላቸውን የማላውቅው ሰዎች ጋር ያለሁ አልመሰለኝም። የእኔው አገር አማራ ቢሆን እኔን ለማወቅ ስንት ቀን ይፈጅበት ነበር? ስንት ነገሮች በይሉኝታ እየተሸፋፈኑ ይጎፈዩ ነበር? በዕውነት በርታዎች እንዴት ነፍስ ናቸው?

ከአባ ቤሎ መንደር ስንመለስ መሽቶ ስለነበር ቀጥታ ወደ ሲቲና ፓላስ አመራን። ሽርቆሌ መብራት የለም ሲያሻው ሲያሻው በጀነሬተር እስከ ምሽቱ አራት ሰዓት የሚሰራ መብራት አለ። ሆኖም ሲቲና አልቀጠለችም፤ ስለዚህ ቻርጅ ተደርጎ በሚሰራ ማሾ እራታችንን አበሳስለን በላንና ዞር ዞር ለማለት ወጣን።

በመኪናውን መንገድ ላይ በርካታ ፍየሎች ሞልተውበታል። ምንድነው? ብዬ ጠየኩ "እዚሁ ነው የሚያድሩት" አለችኝ ሲቲና እንዴት ባለቤት የላቸውም? ጅብ አይበላቸውም? ሌባ አይነዳቸውም? ጥያቄዬን አከታተልኩ። "እዚህ አገር ጅብ የሚባል የለም ባለቤቶቹም ለእነሱ ማሳደሪያ ጋጣ አያዘጋጁም፤ የትም ውለው እዚሁ ያድራሉ፤ ሊያርዷቸው ወይም ሊሸጡዋቸው ሲፈልጉ ይወስዷቸዋል። ማንም የማንን ንብረት አይነካም፤ ሃራም ነው። ሰው በመተማመን ያምናል። ቢጠፋ እንኳን ለወሳጁ መልካም ስለማይሆንለት አይነካም፤ ሌባ የሚባል አይታወቁም ቅድም እንደነገርኩሽ ሰው ከተቸገረ ህብረተሰቡ ይረዳዋል፤ ያበለዋል፤ ያጠጣዋል፤ ሲሰርቅ ከተገኘ ግን ያገለዋል፤ ቢሞት እንኳን ዞር ብሎ የሚያየው የለም። ስለዚህ ሌብነትን የሚሞክር የለም" አለችኝ። እኔም በሁኔታው እየተገረምኩና የማህበረሰቡን ዕምነት እያደነቅሁ በፍየሎቹ ላይ እየተረማመድን ወደ አንዷ ቡና ቤት ገባን። በነገራችን ላይ ሽርቆሌ ሌባ ብቻ ሳይሆን ለማኝም አይታይም፤ በቆየሁባቸው ቀናት አንድም ለማኝ አላጋጠመኝም።

በቡና ቤቷ ውስጥ እነ ሲቲናን የሚያውቅ አንድ ሰው መጥቶ ተቀላቀለን። ሰውየው ሞተር ብስክሌት አከራይ ነው፤ ሽርቆሌ ጊዘን ከምትባል የሱዳን ጠረፍ በ23 ኪ/ሜ ርቀት ላይ ነው እምትገኘው። ጊዘን ሲደረስ ቱመት የሚባል ወንዝ ኢትዮጵያና ሱዳንን ይለያል። የሽርቆሌም ሰው ሆነ የሱዳን ሰዎች ወደ ሁለቱም ሀገራት በቀላሉ እየገቡ ይገበያያሉ፤

ይዝናናሉ፤ ያሻቸውን ይፈፅማሉ። ቪዛ፣ ይለፍ፣ ምናምን የሚባል ነገር የለም። ታዲያ የሸርቆሌ ህዝብ ወደ ሱዳኗ ጊዘን ለመግባት ሲፈልግ 23ቱን ኪሎ ሜትር ብር 50 ከፍሎ በሞተር ሳይክል ተፈናጦ መሻገር ይችላል። ሰውየው ይህን አገልግሎት በመስጠት ኑሮውን የሚገፋ ነው። በዚህ ሥራ የሚተዳደሩ ብዙ ሰዎች እንዳሉ አጫወቱኝ ሸርቆሌ። እንዲህ ቅርብ ከሆነና ለመግባት ችግር ከሌለው እኛስ ብንሄድ ብዬ ሃሳብ አቀረብኩ። እንደውም እሁድ በሱዳኑ ጊዘን ገበያ ስለሆነ ከፈለግሽ እኛዋ ጊዘን ድረስ በመኪና ሄደን ከዚያ በኋላ መኪና ስለማይፈቀድ በእግራችን ወንዙን ተሻግረን መግባት እንደምንችል ፈቃደኛ ከሆንኩም ወንዙን እሱ በሞተር እንደሚሻግረኝ ነገረኝና ተስማምተን ስለመሸ ወደ ቤታችን በፍየሎች ላይ እየተረማመድን ተመለስን።

**ቅዳሜ ሐምሌ 16 ቀን 2003 ዓ.ም.**

ዛሬ እኔና ሲቲና ሁለት ትልልቅ ጉዳዮች አሉን። እኔ አባ ቤሎን ሲመጡ ጠብቄ ቃለ ምልልሱን ማድረግ ሲቲና ደግሞ ስኳርና ዘይቷን ለነጋዴዎች ማከፋፈል፡፤ ስለዚህ ማታ በተስማማነው መሠረት ጧት ተነሳን፤ ሲቲና ቤት እንግዳ መምጣቱን የሰሙ የሸርቆሌ በርታዎች ሥጋ ገዝተው ይዘው በጠዋት መጡ። የሲቲና ዘመዶች ናቸው። አንዱ የወረዳዋ ምክትል አስተዳዳሪ ሲሆን ኢብራሂም ይባላል። ሌላኛው አፈጉባኤው ነው፤ አህመድ ነው ስሙ። ወደ መታጠቢያ ቤቷ ደርሼ ተጣጥቤ ስመለስ እውጪ በተንተረከከ የከሰል ፍም ላይ ወንዶቹ ሥጋ እየዘለዘሉ ይጠብሳሉ፤ ሲቲና ማባያውን ታዘጋጃለች።

ሰላም ብያቸው ወደ ውስጥ ገባሁና ዕቃዎቼን አስቀምጬ ወደ እነሱ ወጣሁ፤ ሥጋውን አሰብኩት እነሱ እስላም ናቸው ሸርቆሌ የክርስትያን ሥጋ ቤት የለም ስለዚህ የሚያሸሞነሙኑት ሥጋ ያለጥርጥር የእስላም ነው። እንዴት ልሆን ነው ልበላ? ወይስ ላልበላ? እነሱ አንዴ እንደብሔራቸው አባል ተቀብለውኛል፤ እንዴት ባደርግ ይሻላል? አስተዳዳሪውና አፈ ጉባኤው ትንሽ ዘመናዊ ስለሆኑ ጥያቄ ሰነዘርኩ። ኢብራሂም አልኩት ከሚጠብሰው ሥጋ ላይ ዐይኑን ሳያነሳ "አቤት!" አለኝ አሁን ይሄ ሁሉ ዝግጅት የእስላም ሥጋ አብልተህ ልታሰልመኝ ነው? አልኩት በቀልድ መልክ "አይ ስንቅነሽ እኔ በዘመኔ

እስላምና ክርስትያን ፍየል አይቼም ሆነ ለይቼ አላውቅም አንቺ የምታውቂ ከሆነ ግን ክርስትያኗን መርጠሽ አምጪና አርድልሻለሁ!" ሲለኝ ያልጠበቅሁት መልስ ስለነበር በጣም አሳቀኝ። ከዚያ በኋላ "ይልቅ አንቺ ይሄንን በሸንኩርትና በቆጭቆጫው እያደረግሽ ብይ ወባ እሚባል በዞርሽበትም አይዞር፤ ከፈለግሽ አዲስ አበባ ስትደርሺ ክርስትና ተነሺ፤ አሁን በርታ ነሽ በቃ!" ሲለኝ እየሳቅሁ ተቀብየው ያለምንም መሸማቀቅ በላሁ በጣም የሚጣፍጥ ጥብስ ነበር። እውነት ክርስትያን ፍየል ይኖር ይሆን እንዴ?! ለማንኛውም ተበላ!!ከተሰለመም ተሰለመ ማለት ነው!

ከቁርስ በኋላ የሲቲናን ስኳርና ዘይት ለማከፋፈልና አባ ቤሎን ለመቀበል ወጣን፤ ነጋዴዎቹ ሲጠብቋት ስለነበር ወዲያው መጥተው ተከፋፈሉት ስንጨርስ አባ ቤሎ ስለመጡ ወደ ቤት ይዘናቸው ሄደን ቃለ ምልልሱን አደረግን። (ስክርብ ከገጽ 1-12ን ይመልከቱ)

ከቃለ ምልልሱ በኋላ አባ ቤሎን አስተናግደን ወደ ቤታቸው ሸኘናቸው። ከሰዓት በኋላ ካለንበት በ14 ኪ/ሜ ርቀት ላይ ወደሚገኘው ወደ ሲቲና እናት ቤት ሄድን። ቦታው ገጠር ቢሆንም መኪና ስለሚያስገባ መንደሯ ድረስ በመኪና ገባን። እኔ ሲቲና ሹፌሩና ከሽርቆሌ የያዘው ጓደኛው ነበርን። እንደደረስን ሰላምታ እየሰጠን ወደ ውስጥ ዘለቅን በስተቀኛችን በኩል አንድ ረዥም ቆርቆሮ የተመታ ዳስ ነገር አለ በውስጡ በርካታ ወንዶች ተሰብስበዋል። መምጣታችንን ሲያውቁ እየወጡ ሰላም አሉን ከዚያ ወደ እናቷ ቤት ገባን እንደአባ ቤሎ ቤት ሁሉ ግቢውም ቤቱም  ንፁህ  ነው የቤቱ አያያዝም ተመሳሳይ።

እናትየዋ የሚያምሩ የበርታ ባልቴት ናቸው። በልጅነታቸው በፊታቸውና በእጃቸው ላይ ለጌጥ ብለው የተተለተሉት አሻራው ደብዝዞ ይታያል። በደስታና ደጋግመው ሰላም በማለት ተቀበሉን፤ እቤት እንደገባን የተለመደው ውሃ እና የእንጀራ ፍቅፋቂው/ አላብሬ የተደረገበት ውሃ ቀረበልን ሲቲና እሱን እኔ ውሃውን ተጎነጨን። ከእናቷ ጋር ስለእኔም ስለእሷም ከተጠያየቁ በኋላ ወደ እህቷ ቤት እንድንመጣ ተጠራንና እዚያ ሄድን።

የእህትየዋ ቤት ባህላዊው ጎጆ ቢሆንም ውስጡ ዘመናዊ ቤት ይመስላል በዚያ ገጠር ውስጥ ኮንትሮ ቢፌ ያየሁበት ቤት፡፡ እዚያ ቤት ያየሁት ባህላዊ ነገር የሚሰግዱበት ሰሌን ነው "አልሙስሊያ" ይባላል፤ የምትሠራው እህትያዋ ሆና ልዩ ልዩ ቀለማት በተነከረ ሰሌን የሚሰራ ነው፡፡ ቀለማቱ እዚያው ካሉ ባህላዊ ነገሮች ቅጠላ ቅጠልና ከጥቀርሻ የሚሰሩ ናቸው፡፡ ሰሌኑ አራት ማዕዘን ሆኖ ጫፉ ላይ ጠበብ ብሎ የሰጋጁ ግንባር የሚያርፍበት ቦታ አለው፡፡ ተሠርቶ ያለቀውንና አገልግሎት የሚሰጠው ተሠቅሏል ሌላ በመሠራት ላይ አለ፡፡ እሷም ቤት ሻይ ተፈላልን ወንዶቹ እኛን ተከትለው ወደ ቤት አልገቡም፡፡ ሾፌሩን ጓደኛው ወንዶቹ ወዳሉበት ዳስ ስለሄዱ እዚያው ተላከላቸው፡፡ የወሰደላቸው ወንድ ልጅ ነው ወደ ዳሱ ሴቶች አይሄዱም፡፡

እነ ሲቲና እናት ሠፈር ትንሽ ከቆየን በኋላ ወደ ሽርቆሌ ተመለስን ፡፡ ቤት ገብተን እራታችንን አብስለን ከበላን በኋላ የሲቲናን ፓላስ የቆርቆሮ መዝጊያ መለስ አድርገን ተኛን፡፡ እኔ ትንሽ ስጋት ቢጤ ተሰምተኛል፡፡ ምክንያቱም እሷ ስኳር ሸጣ ወደ ሶስት መቶ ሺህ የሚጠጋ ብር ይዛለች፡፡ ስኳር ስትሸጥ ደግሞ ብዙ ሰው አይቶናል፡፡ እኔም ቢሆን እንዳቅሜ ጥቂት ብሮችና ንብረቶች አሉኝ፡፡ አሁን የእሷን ብር ቀን ያየ ሰው ቢመጣስ? ምን የሚያግደው ነገር አለ? ሲቲና ግን ስሜትም አልሰጣት፡፡ ብሩን ስትቆጥር አምሽታ በስስ ፌስታል አሰረችና እራስጌዋ ያለ ጠረጴዛ ላይ እንደአልባሌ ዕቃ ጣል አድርጋው ተኛች፡፡ እሷ በርታ ነቻ! ምን ሃሳብ አለባት! እኔ ግን አማራ! ጠርጣሪ! ሰጊ! ፈሪ… እግዜር ይጠብቀን! እንቅልፍ ቶሎ በወሰደኝ!

**እሁድ ሐምሌ 17 ቀን 2003 ዓ.ም.**

እኛም ብሩም ሰላም አደርን ሽርቆሌ ነዋ! ጠዋት ተነስተን ለጊዘን/ ሱዳን ጉዞ ቁርስ በልተን ቡና ጠጥተን ተዘጋጀን፡፡ አርብ ዕለት አብራን አባ ቤሎ ቤት የሄደችው ቢተሚና መጥታለች፡፡ ዛሬም አብረን ልንሄድ፡፡ ከቁርስ በኋላ ቶቤን አለበሱኝና "ሑምራ" ቀቡኝ፡፡ ባህላዊ ሽቶቸው ነው አቤት መዐዛው ተያይዘን ወጣን ፡፡

ኢትዮጵያው ጊዘን ስንደርስ አራት ሰዓት አካባቢ ይሆናል። ከሽርቆሌ የምታንስ ከተማ ናት ግን ሞቅ ሞቅ ያለች የጠረፍ ከተማ። ሙቀቷ ልብስ ያስጥላል፡ መገላለጥ አይቻልም እንዴት ይኮናል? መኪናችንን እዚያው አቁመን ወደ ሱዳኑ ጊዘን ለመግባት ተሰናዳን። ወንዙን ከተሻገርን በኋላ አንድ ኪሎ ሜትር ያህል በእግር መጓዝ አለብን ሱዳኗ ጊዘን ለመድረስ። ስለዚህ ሁለት አማራጭ አለን በሞተር ሳይክል ወይም በእግር ወንዙን አቋርጦ መግባት። እኔ በእግር መሄዱን መረጥኩ ሞተሩን አላመንኩትም ግን ወንዙን ካለድልድይ ገብቶ ማቋረጡ ደግሞ ሌላ ፈተና ነው። ሆኖም አንዴ መጥቻለሁ አልመለስ በእግር እንሂድ ስል ሁሉም ተስማሙ እነሱ ለምደውታል ሞተሩ የተመረጠው ለእኔ ነበር።

ከመውጣታችን በፊት እኛ ድንበር ላይ ያሉ ፖሊሶች መታወቂያ እንድናሳይ ጠየቁን፤ አሳየን። እንደነገሩ እየዘቀዘቁም ጭምር አዩትና መልሰውልን ምን እንደምንገዛ ደግሞ ጠየቁን፤ ግራ ገባኝ ዘይት፣ ሳሙና፣ ከሰል፣ስንኩርት ይዞ መግባት አይቻልም። ለምን? እኛ አገር አለ፤ እነዚህን እንዳንገዛ ተነገረን። ተስማምተን ወደ ወንዙ በእግር ዘለቅን። ውሃው ከጉልበት በላይ ስለሚሆን ቶቤን ሰብስቤ የምፈራውን ውሃ በህይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ ገባሁበት። ውስጡ አሸዋማ ነው። እንደምንም ተሻገርኩት።

በዚያ በኩል ያሉት የሱዳን ፖሊሶች ዝም ብሎ ከማየት በስተቀር ወዴት ነው? ከየት ነው? መታወቂያ፣ ቅብርጥስ፣ አይሉም ወይም እዚህኛው ማዶ ስናሳይ ስላዩ ይሆን? ወይስ አንጀባ የሚበዛው እኛ አገር ብቻ አላውቅም። ዝም ብለን አልፈናቸው በማንጎ ደን ውስጥ በእግር መገስገስ ጀመርን። ከ40 ደቂቃ ጉዞ በኋላ ሱዳን ጊዘን ከተማ ደረስን። ትናንት ሽርቆሌ ከሲቲና ስኳር ሲገዙ ያየኋቸው ነጋዴዎችና ብዙ ሰዎች እዚያ አሉ። ገበያው ሞቅ ያለ ነው። ለመገበያያ የሱዳንም የእኛም ብር እኩል ያገለግላል። እንደውም በወቅቱ ደቡብ ሱዳን የመገበያያ ገንዘብ ለውጥ ስላደረገች ሱዳናውያን የእኛን ብር አጥብቀው ይፈልጋሉ። ብዙ ሰዎችም እንድንቀይራቸው ሲጠይቁን ነበር።

ገበያውን ተዘዋውረን ብዙ ነገሮችን ገዛን በተለይ ኦሞና ሳሙና በጣም ርካሽ ነው። ሌላው የማይረሳ ነገር የገበያው ውስጥ ሻይ ነው። ከተማዋ ከእኛ አገር ይልቅ በጣም ስለምታቃጥል ውሃ ጥሙ አይጣል ነው። መድሃኒቱ ግን የገበያው ሻይ ነው። ድንጋይ ላይ ቁጭ ተብሎ ግሩም ሻይ መጠጣት ይቻላል። እዚህ ተገዝቶ ስለሆነ ከጣመ መደጋገምም ይቻላል። አቤት ሻይ! አባ ቤሎ ቤት የጠጣሁት የዚህ ተፅዕኖ ይሆን? ሻይን በርታና ሱዳን ያፍሉት።

ሱዳን ጊዘን ገበያ ውስጥ እስከ 7፡00 ሰዓት ቆይተን የመልስ ጉዞ አደረግን በእግር። የገዛናቸውን ዕቃዎች ከባዶቹን በጋሪ ጭነን የተቀሩትን ሲቲና በሻንጣ ውስጥ አድርጋ የቶቧን ጫፍ እንደማቶት እራሷ ላይ አስተካክላ ቂብ አደረገችው። ምንም ዓይነት የእጅ ድጋፍ ሳያስፈልገው አንከብክባ ወንዙ ጋ ስንደርስ ጢም ብሎ ሞልቷል። ደራሽ ውሃ ከላይ መጥቶ ነው። አንዲት ፒክ አፕ መኪና ወንዙ ውስጥ በአሸዋ ተይዛ ወደ ስምንት የሚደርሱ የሱዳን ወታደሮች ለማውጣት ይታገላሉ። ሰው እስከ ወገቡ በሚደርሰው ውሃ ያቋርጣል። የእኔ ሀሞት ፍስስ አለ፤ ቅድም እሰከ ጉልበቴ የሚደርሰውን ውሀ በስንት ፍርሃት ተሻግሬ እዚህ ውስጥ ደፍሬ መግባት የማይታሰብ ነው። ሲቲናን እኔ አልገባም አልኳት፤ "ምን ትሆኛለሽ ታዲያ ከዚህ በኋላ እየጨመረ እንጂ እየቀነሰ አይሄድም" አለችኝ። ጨነቀኝ፤ በኋላ ከአንድ በርታ ጋር በቋንቋዋ ተነጋገረችና "ሂጂ ከእርሱ ጋር እሱ ያሻግርሻል" አለችኝ። የያዝኩትን ዕቃ ቦርሳዬን ጨምሮ እነሱ ይዘውልኝ በአንድ እጄ ልብሴን ሰብስቤ በአንድ እጄ የበርታውን ክንድ ይዤ ገባሁ እስከ ጡቴ ይደርሳል ውሀው። እየጮሁኩ፣ እሱም በቋንቋው እያበረታታኝ በጭንቅ ተሻገርን። በጣም አስፈሪ ነበር። ሁለተኛ ውሃ ውስጥ እንደማልገባ ማልኩኝ።

እኛ ጊዘን ስንደርስ ዕቃችንን አስፈትሸን አልፈን አንዲት ሆቴል ውስጥ ገባን፤ በንኬል ሳህን ውሃ አቀረቡልኝና እግሬን ታጥቤ ተንፈስ እንዳልኩ ምሳ በልተን ጉዞ ወደ ሸርቆሌ ቀጠልን። ስንደርስ በጣም ደክሞኝ ነበር ሲቲና ፓላስ ገብተን እንዳረፍን ቡና ማቀራረብ ጀመረች። ቆላችና ለእኔ ካሸተተችኝ በኋላ ይዛው ወደ በሩ በመሄድ ውጪውን ሁሉ

አሻተተችና ተመለሰች ለምን ስላት "ቆሌዋ እንዲሸታት ነው" አለችኝ እየሳቀች። ቡናችንን ጠጥተን እንደጨረስን እራት አብስለን በልተን ተኛን።

**ሰኞ ሐምሌ 18 ቀን 2003 ዓ.ም.**

ዛሬ ወደ አሶሳ የሄዱት መረጃ ሰጪ ሽማግሌ በመመለሳቸው እሳቸውን ለማግኘት ሄድን እራቅ ወዳለ ቦታ የዘመድ አርባ ስለሆነ እዚያ እንደሄዱና ማምሻውን አለዚያም በማግስቱ እንደሚመለሱ ስለተነገረን ወደ ቤት ተመለስን። ወደ ቤት ስንሄድ የሲቲና የእህት ልጅ ዕድሜው 10 ዓመት ይሆናል ዘመናዊ በሚባል ኖኪያ ሞባይል የሱዳንኛ ዘፈን ከፍቶ ያስማናል። በሞባይሉ ተገርሜ እንዲያሳየኝ ጠየኩት፤ ሰጠኝ አገላብጬ አይቼ የማነው? ስለው "የእኔ" አለኝ። ከየት አመጣኸው? ስል "ወርቅ ቆፍሬ ገዛሁት" አለኝ፤ ሲም ካርድ የለውም ምክንያቱም ሸርቆሌ ኔት ወርክ እምብዛም አይሠራም ቢሠራም እሱ እሚደዋወለው ሰው የለውም፤ ለምንህ ገዛኸው? ስለው "ዘፈን ለመስሚያና ጌም ለመጫወቻ" አለኝ ተመልከቱ የበርታ ህፃን ወርቅ መቆፈርና ማግኘት ከቻለ የንብረት ባለቤት መሆን ይችላል ማለት ነው። ዘመናዊ ሞባይል ገዝቶ ጌም ይጫወታል፤ ሙዚቃ እየሰማ ይዝናናል፤ የቦሌ ልጆች ይሄን ቢሰሙ ምን ይሉ!? ገረመኝ፤ ስምህ ማን ነው? አልኩት "አህመድ" አለኝ፤ "ሸቀብ" ሲሉት ሰምቼ ስለነበር ሸቀብስ? ስለው "እሱም ስሜ ነው" አለኝ  ምን ማለት ነው ብዬ ስጠይቅ ሲቲና "ሽብር" ማለት ነው አለችኝ፤ "የተወለደው ተገንጣዮቹ እዚች ከተማ ገብተው የበጠበጡና 24 ሰው ገድለው ብዙ ቤቶች አቃጥለው የሄዱ ዕለት ስለሆነ ሸቀብ ተባለ። በእኛ ባህል ከክስተቶች ጋር የተያያዘ ስም ማውጣት የተለመደ ነው እሱ ግን ትምህርት ቤት ሲገባ የስሙ መልዕክት ጥሩ ስላልሆነ አህመድ ተባለ በቤት አካባቢ በብዛት የሚጠራው ግን ሸቀብ በሚለው ነው አለችኝ፤" አቤት ባህል! መሃል አገር አብዮት፣ መንግስቱ፣ መስከረም የሚባሉ ልጆች ታወሱኝ።

ሽማግሌው ስላልተመለሱ ቃለ ምልልሱን ሳናደርግ ቀረን በሸርቆሌ ሙቀት እየተጠበስን ቀኑ ተገባደደ፡፤ ደግነቱ የበርታዎች ፍቅር ሁሉን ያስረሳል። ሲቲና ጋ እንግዳ እንደመጣ ያወቀ በርታ ሁሉ ያለውን ይዞ ይመጣል፤ ሲያጫውተን ይውላል። ጨዋታቸው

በአብዛኛው በበርትኛ ስለሆነ እኔ ባልሰማም ሲቲና አልፎ አልፎ ታስተረጉምልኛለች፣ እነሱም በአማርኛ ትንሽ ቀጥለው ወደራሳቸው በርትኛ ይዞራሉ። ከዚያ የኑግ ልጥልጥ ከሚመስል መልካቸው ውስጥ ከሚገኘው ሃጫ በረዶ ከመሰለ ጥርሳቸው የሚፈልቀው ፈገግታቸው ቋንቋቸውም ባይገባ ፈገግ እንዲሉ ስለሚጋብዝ ቀለል እንዲልና ባይተዋርነት እንዳይሰማ ያደርጋል።

አዳር በሲቲና ፓላስ ሆነ። እንደው ይህቺን ሲቲናን ባላገኝ የት ነበር እምከርመው ብዬ ሳስብ ዕድለኛ እንደሆንኩ ይሰማኛል። ከዚህ በኋላ እንኳን እሷም ባትኖር አንዱ በርታ ቤት አሰላማሊኩም ብዬ መግባት ነው አንዴ ልጃቸው ሆኛለኋ!

**ማክሰኞ ሐምሌ 19 ቀን 2003 ዓ.ም.**

ሲቲና በጠዋት ተነስታ የብረት ድስት ዳቦ ጋገረች ማታ ስታቦካ አይቻታለሁ። በብረት ምጣድ ልትጋግረው ነው ብዬ አስቤ ነበር፤ ነገር ግን አንድ ወፍራምና ከባድ ብረት ድስት ጥዳ ዘይት በመቀባት ምን የመሰለ ዳቦ ጋገረች። በጠዋት ቡናው ቀርቧል፤ ቤቱ ተጫጭሷል፤ ደስ ይላል። ለቁርስ ከልኳንዳ ጉበት፣ ጨጓራና ሥጋ አስገዝታለች። እኔ ዱለት ልትሰራ መስሎኝ ነበር ግን አይደለም ጨጓራው ተጣጥቦ ተዘለዘለ፤ ጉበቱም በትልልቁ ተከተፈና አብሮ ተጠበሰ፤ ነጭ ሽንኩርት ገብቶበታል። ለማባያ ቀይ ሽንኩርት ጥሬውን ሰንጠቅ ሰንጠቅ ተደርጎ፣ ቆጭቆጫ የሚባለው ከአረንጓዴ እርጥብ ሚጥሚጣ ቅመማ ቅመም ተጨምሮበት የተለነቀጠ አዋዜና ሎሚ ተዘጋጅቷል።

ሲቲና ንቁ ስለሆነች ለእኔ "ይሄን ምግብ ካልወደደችው" ብላ ይመስለኛል ዕንቁላል ስልስ በተጨማሪ ሠርታለች። ሾፌሩም ካደረበት ስለመጣ ሁላችንም ለቁርሱ ታደምን፤ ጉበቱን ቀመስኩና ወደ ለመድኩት እንቁላል አደላሁ። ሾፌሩም ከመነሻው የጀመረው ዕንቁላሉን ነው። እነ ሲቲና ግን የጉበት ጥብሳቸውን በፍቅር ተመግበውት ገበታው ከፍ አለ።

የሲቲና ቡና እየተንተከተከ ስለቆዬ ወረደ። የብረት ድስቱ ዳቦ ለቡና ቁርስ ቀርቧል፤ "ዛሬ ገብርዔል ስለሆነ የገብርዔል ፃዲቅ ነው" ብላ ቆረሰችው መጀመሪያ የምታሾፍ መስሎኝ

"እስላሚ ገብሬልን ዘካሪ!" አልኳት "የምሬን ነው ስንቅዬ እያሾፍኩ እንዳይመስልሽ በእያመቱ እኮ ቁልቢ እሄዳለሁ!" ስትለኝ የምሯ እንደሆነ ገባኝ። አንዴ ተቸግራ ተስላ ስለደረሰላት ገብርዔልን እንደምትዘክር ነገረችኝ፤ በርታ ነቻ ጣጣ አላት? የቀረበውን ፀዲቅ የቡና ቁርስ አድርገን ቡናችንን አክትመን ወጣን፤ መረጃ ሰጪው ሽማግሌ ፍለጋ። በነገራችን ላይ ከቡናው እኩል ሻይም ነበረ በበርታ ሁለቱም እኩል ነው የሚቀርቡት ስኳሩ በዛ ተደርጎ፤ ስኳርና በርታ ነፍስና ሥጋ ናቸው ባለፈው ስኳር የተወደደ ሰሞን አንድ ኪሎ በሰባና በሰማኒያ ብር እንደገዙ ነግራኛለች ሲቲና። ሁሉ ምግባቸው ውስጥ ስኳር ይገባል ጭሳቸው ውስጥ ሳይቀር እና የስኳር ፍጆታቸው ብዙ ነው። ባይሆን የማይደፍሩት የሚያቃጥል ነገር ነው። እንደሲቲና ያሉት የተለዩት ካልሆኑ በስተቀር።

መረጃ ሰጪውን ሰው አግኝተናቸው ዓላማውን ሲቲና ካስረዳቻቸው በኋላ በጉዳዩ ተስማምተው  ሌሎች ሽማግሌዎችን ጨምረው በማግስቱ እንደሚጠብቁን ነግረውን አመስግነን ተለያየን። ቢተሚና እምትባለው አባ ቤሎ ጋ አብራን የሄደችው በርታ እቤቷ ልትወስደኝ እንደምትፈልግ ስለነገረችን ስኳርና ሻይ ቅጠል ገዛሁና ወደዚያው አመራን። የቢተሚና ቤት የሌሎቹ በርታዎች አምሳያ ናት ንፁህ ቅልብጭ ያለች ጎጆ። አጎንብሰን ወደቤት ዘለቅን፤ ቢተሚና ከበረሃ ስላልመጣን በቅድሚያ የምንጎነጨው ውሃ ባታቀርብልንም መጀመሪያ የሚጣፍጥ የሎሚ ጭማቂ አቀረበችልን፤ የሎሚው መጣፈጥ ሚስጥር አልገባኝም እቤቴም ጨምቄ እጠጣ ነበር ግን እንደዚህ ጣፍጦኝ አይደለም የእነሱ ይለያል።

ቢተሚና ቡና ልታፈላ ሽር ጉድ ትላለች፤ ቡናው ቀራርቦ በማጨሻ ላይ እሳት ተደረገና ጭስ አደረገችበት ማዕዛው ሌላ ነው። ጭሱ ከምን እንደሚሰራ ጠየቅሁ በባህላዊ መንገድ እዚያው እንደሚሰራ ነገረችኝ  እንጨቱ "ቀቃዊስ" ከሚባል ዛፍ ነገር ሥር ተቆፍሮ የሚገኝ ሲሆን ልዩ ልዩ መዓዛ ያላቸው ቅጠሎች፣ ሰንደል የሚሉት እንጨትና ሁምራ እሚባለው ሌላ እንደሽቶ የተቀመመ ነገር አብረው ተቀምመው ስኳር በእሳት በማቅለጥ እንዲያያዝ  ይለወሳል፤ ከዚያ ማጨስ ነው ሲያዩት ቡና ዓይነት መልክ አለው፤ ለእኔም አዘጋጅተው እንደሚሰጡኝ ቃል ገቡልኝ።

**ረቡዕ ሐምሌ 20 ቀን 2003 ዓ.ም.**

ጠዋት ከሽማግሌው ጋር በነበረን ቀጠሮ መሰረት ቃለ ምልልሱን ለማድረግ ወደዚያው አመራን፤ እጨምራቸዋለሁ ያሉት ጓደኛቸው የሉም፡፡ ከእሳቸው ጋር ቃለ ምልልሱን አደረግን ሲቲና፣ ነፊሳ ( የወረዳው ባህልና ቱሪዚም ፅ/ቤት ሀላፊ) እና እኔ ሆነን ቃለ ምልልሱን አደረግን፡፡ ሲቲናና ነፊሳ ማህበረሰቡ አባላት በመሆናቸው እነሱም የሚያውቁትን ሽማግሌው ያላነሱትን ወይም የዘነጉትን በመጨመር እየተሳተፉ እስከ ምሳ ቆየን፡፡ የሰላትና የምሳ ሰዓት በመድረሱ አመስግኛቸው መለያየት ነበረብን፡፡

ስለአቀባበላቸውና ስለሰጡኝ መረጃ ምስጋናዬን ሳዝጎደጉድ፣ የእነሱን ባህል ለማጥናት ከአዲስ አበባ ድረስ መምጣቴ እንዳስደሰታቸውና ከእንግዲህ በማንኛውም ሰዓት ብመጣ እሳቸው እንኳን ባይኖሩ ቤታቸው ቤቴ እንደሆነ፣ እንደ ቤተሰባቸው እንደሚቆጥሩኝ በደስታ ነገሩኝ፡፡ ቃለ ምልልሱን ያደረግነው በአቅራቢያው በሚገኝ የግራር ዛፍ ጥላ ሥር ስለነበር እኛ ለምሳ ወደ ቤታችን፣ እሳቸው ለሰላት ወደ አልከለዋቸው አመሩ፡፡ አባ አብዱራሂም አማርኛ ስለሚችሉ ለመግባባት አልተቸገርኩም ነበር፡፡ ስለማህበረሰቡ ባህል አንስተን ያልተጫወትነው ነገር የለም በጣም ደስ ብሎኛል፡፡ (ስክርብ ከገፅ 13-28 ይመልከቱ)

**ሐሙስ ሐምሌ 21 ቀን 2003 ዓ.ም.**

ዛሬ ቀኑን እንደተለመደው አሳለፍኩ፤ የሰበሰብኩትን መረጃ በማዳመጥና በመቆዘም፡፡ ሲቲና ስኳር ልታመጣ አሶሳ ሄዳለች፡፡ ጭና የምትመለሰው ነገ ነው፤ እንድታስተዳድረኝ ለቢተሚና ነግራታለች፡፡ ቀኑን ብቻዬን ስለነበርኩ ለቁዘማ ተመችቶኛል፡፡ እስካሁን የሰበሰብኩትን መረጃ መምህሩ ካዘዘውና ቤን አሞስ ስለ አፍሪካ ፎክሎር ጥናት ካለው ጋር ለማዛመድ ሞከርኩ ቤን አሞስ የሚያወራውም ሆነ መምህሬ የሚፈልገው ስነ ቃል ስብሰባ ላይ ያተኮረ ስለመሰለኝ የሰበሰብኩት ሁሉ ከንቱ የሆነ ያህል ተሰምቶኛል፡፡ ስለዚህ ጥሩ ስሜት አልነበረኝም፡፡

የስነ ቃል ክዋኔ የራሱ ሰዓት አለው:: ክዋኔውም እንዲሁ ለየት ይላል:: የሥራ፣ የሠርግ፣ የጨዋታ(የመዝናናት) ቃል ግጥሞች፣ እንቆቅልሾች፣ ተረቶችና የመሳሰሉት የራሳቸውን ጊዜና ቦታ ይሻሉ:: እኔ ወደ ሸርቆሌ የመጣሁበት ወቅት ደግሞ ክረምት በመሆኑ እነዚህ ህይወታዊ እንቅስቃሴዎች ዝግ የሚሉበት እንደውም ጭራሽ የማይከሰቱበት ጊዜ ነው:: እንዴት አድርጌ ይሆን የማገኛቸው??? ጌታ ይወቅ!! ቀድሞ ባደረግሁት ሙከራ መረጃ ሰጪዎችን በእግረ መንገድ አንስቼ ተረት፣ እንቆቅልሽ፣ ቃል ግጥሞች… እንዲነግሩኝ ስጠይቃቸው አንድ ሁለት ወርውረው ማስታወስ እንደማይችሉ ይነግሩኛል:: እና እንዴት ሊኮን ይሆን?

**አርብ ሐምሌ 22 ቀን 2003 ዓ.ም.**

የተለዬ ቀን አልነበረም፤ ዛሬም ውስጤ ባዶ እንደሆነ ነው:: የዋልኩት እቤት በመሆኑ አንዳንድ ሰዎች እየመጡ ሲቲናን እየጠየቁ ተመልሰዋል:: አብዛኞቹ ስኳር ፈላጊዎች ናቸው:: ሴቶቹ "ቶብ" የሚባለውን የባህል ልብስ ለብሰው ነው የሚመጡት፤ በዚህ መካከል አንድ ነገር ልብ ብያለሁ ጫማቸው ኮንጎ ጫማ ሆኖ ከቶቡ ከለር ጋር የሚስማማ፣ በከተማ አነጋገር "ማች የሚያደርግ" ነው:: የቢተሚና ኮንጎዎች መቀያየር ነው ያነቃኝ:: ከዚያ በኋላ የማያቸውን ሴቶች ጫማ መከታተል ጀመርኩ፤ ስምም ሆኖ አገኝሁት::

የበርታ ሴቶች የከለር ምርጫ በአብዛኛው ጥቁርና ደማቅ ከለሮችን ነው:: ቶባቸው አንዳንዱ ከስሩ በጥበብ መሳይ ጥልፍ የተከፈፈ ነው:: የኮንጎ ጫማቸውም ሆነ የስሊፐራቸው ከለር ከቶባቸው ከለር ከአንዱ ጋር የሚመሳሰል ነው:: የአሮጊቶቹ እንኳን ሳይቀር፤ በጣም ገረመኝ:: ሲቲና አምሻሽ ላይ መጣች:: ስኳሯን ጭና፤ እንዴት እንደቆየኒት ተጨንቃ ጠየቀችኝ:: ወይ ጉድ የበርታዎች ደግነት እንዴት ደስ ይላል?! ጭራሽ ለራሴ ጉዳይ የሄድኩ መሆኔን እስክረሳ ድረስ  እዚያ መገኘቴን ለእነሱ ጥቅም እንደሆነ ያደርጉታል:: ምንም ሳልቸገር ቢተሚና ስትንከባከበኝ እንደቆየች ብነግራትም ጥላኝ መሄድ እንዳልነበረባት ደጋግማ ትናገራለች ስትገርም! ይልቅ እሱን ተይውና

የአገርሽ ሴቶች ጫማ ከቶባቸው ከለር ጋር ማች የሆነበትን ምክንያት ንገሪኝ እስቲ? አልኳት።

"በዕውነት እንዲያ እንደሆነ አላውቅም ስንቅዬ ልብ ብየውም አላውቅ፤ አንቺ እኮ ጉደኛ ነሽ፤ እንደዚያ ሆኖ አገኘሽው? እግር እግራቸውን ስታዪ ነዋ የሰነበትሽው!" ብላ ወደ ቀልድ ቀየረችው። ዕውነቴን ነው ሲቲና የቢተሚናን ጨምሮ የእህትሽ፣ የአክስትሽ፣ በቀደም እናትሽ ቤት ስንሄድም የእናትሽ ጫማ ከልብሳቸው ጋር የሚመሳሰል ነበር ስላት ደነቃት ቆይ ቢተሚናን እንጠይቃታለን። እኔ ልብ ብየውም፣ አስቤበትም፣ አላውቅ ብላ ልብሷን መቀያየር ጀመረች።

እስቲ ዛሬ ከመንገድ ስለገባሽ እኔ "የአማራ ቡና" ላፍላልሽ ስላት "ታዲያ ቆሌዋ ከየት መጣች እንዳትልሽ በበርትኛ መለማመን ይኖርብሻል" ብላ አሾፈችብኝ፤ ግድ የለም እሷ ምንም ስለማይሳናት አማርኛ ትሰማለች ብያት ቡናውን አቀራርቤ ማፍላት ጀመርኩ። እንደሙያዬ ቆልቼ ካፈላሁ በኋላ መቅዳቱ ላይ ስደርስ ነገር መጣ። እኔ በአፉ በሚቀዳ ጀበና ቡና አፍልቼ አላውቅም፤ እነሱ በቀላሉ ስለሚቀዱት የሚያስቸግር አልመሰለኝም ነበር። ልቅዳህ ስለው ግን ምጣኔውን ባለማወቁ እየተድበከበከ አስቸገረኝ። ሲቲና መሳቂያ አገኘችና መንከትከት ጀመረች "አላልኩሽም ቆሌዋ በበርትኛ ስላልተለማመንሻት ተቆጥታ ነው ቡናውን ያደፈረሰችብሽ" በማለት ሳቀችብኝ አይ ሲቲና ለመሳቅ የተፈጠረች በርታ!! "ከበሮ በሰው እጅ ያምር ሲይዙት ያደናግር" ብዬ እራሷ እንድትቀዳ ቦታውን ለቀቅሁላት "አይ ስንቅዬ!" እያለች መጀመሪያ ጭሱን ሞቅ አደረገችውና ቀድታ ሰጠችኝ እየተሳሳቅን ጠጥተን ጨረስን።

**ቅዳሜ ሐምሌ 23 ቀን 2003 ዓ.ም.**

ዛሬ ቅዳሜ በመሆኑ የሲቲናን ስኳር ለማከፋፈል ወደ አራገፈችበት ቦታ በጠዋት ወጣን። ሲቲና ትገርማለች የሚወስዱት ነጋዴዎች ሁሉም ያለአድሎ እንዲወስዱ እኩል ታከፋፍላለች። የንግድ ፈቃዳቸውን እያየች፤ ከገጠር ቀበሌዎች ለመጡት ሳይቀር የቀበሌ ማረጋገጫ ወረቀት እየጠየቀች ነው የምትሸጠው። አለዚያ አይቻልም ብላ ትመልሳለች።

በእርሷ እምነት ስኳር የምግባቸው መሠረት የሆነውን በርታዎች በውድ እንዲገዙ የሚያስገድዷቸው እነዚህ ህገወጥ ነጋዴዎች ናቸው። ስለዚህ የምታየው የእሷን ቶሎ ሽጦ መገላገል ሳይሆን የወገኖቿን ጥቅም ነው በርታ ነቻ! ስትገርም።

አከፋፍለን ስንጨርስ ወደ ገበያ ገባን። ቢተሚና ገበያ ውስጥ የሻይ መሸጫ መደብ አላት። ከፊት ለፊቷ ትልቅ ከሰል የሞላበት ማንደጃ አድርጋ፣ የተለያዩ ሻይ ማፍያዎችና የቡና ጀበናዎች ደርድራለች። ስኒና ብርጨቆም አለ። የሽርቆሌ "ካፍቴሪያ" መሆኗ ነው። አገልግሎቱን የሚፈልግ ሰው ዙሪያውን በተጋደመ እንጨትና በተደረደረ ድንጋይ ላይ ሆኖ የፈለገውን አዞ ይጠጣል። እኛ ስንደርስ ሁሉንም ሰላም ብለን ባገኘነው ባዶ ቦታ ላይ ተቀመጥን። ቢተሚና ሻይ ወይ ቡና የምንፈልገውን ጠየቀችን፤ ሁለታችንም ሻይ መረጥን። እዚያው ገበያ ውስጥ ቁጭ ብለን ግሩም ሻይ ጠጣን። አቤት ሻይና በርታ! ሱስ ያሲዛል ሻያቸው። ታዲያ የስኳሩን መጠን ችሎ ነው "ያለ ስኳር" የሚባል ነገር እንግዳ ነው ለእነሱ።

ወደ ቤት ተመልሰን ምሳ አዘጋጅተን ተመገብን፤ ሲቲና ቡና ልታፈላ ስትሰነሰዳ ሰሞኑን የሥራ ቀን በመሆኑ ያልጠየቁን የመንግሥት ሠራተኞች አንዳንድ እያሉ መጡና ቤቷ መሙላት ጀመረች። ሁሉም የሚችለውን ነገር እየያዘ ነው የሚመጣው፤ አንዳንዶቹ በርታዎች መጠጥም ስለሚቀማምሱ ቢራ ሁሉ አለ። ጨዋታው ደራ፤ አብዛኞቹ የመጣሁበትን ጉዳይ ያውቃሉ። እኔም ብዙዎቹን በቆይታዬ በአይን አውቃቸዋለሁ። ጥቂት አዲስ ሰዎች አሉ።

በመሃል ሲቲና ወደ አንድ ሰው እያመለከተችኝ "ኢብራሂም ቃሲም ይባላል፤ የወረዳዋ አስተዳዳሪ ነው፤ እስካሁን ያላየሽ ወባ አሞት ስለከረመ ነው" ብላ አስተዋወቀችኝ። የበርታ ባለስልጣናት ከተራው ህዝብ በምንም አይለዩም። ቢሮአቸው ወንበር ላይ ሲቀመጡ ካልሆነ በስተቀር ባለስልጣን መሆናቸውን ለማወቅ ያስቸግራል። የትም ከማንኛውም ሰው ጋር እንደልብ ይገናኛሉ። ፕሮቶኮል፣ ኩራት፣ ቅብጥርጥርስ እዚያ አይታወቅም። የወንዶቹ አለባበስ የሁሉም ማለት ይቻላል ረጃጅም ነጭ ጀለብያ ነው።

አንዳንዶቹ እራሳቸው ላይ ነጭ ጨርቅ ይጠመጥማሉ፤ ከጀለብያቸው በላይ ሰደርያ የደረቡም አሉ። ጫማቸው አካባቢው ስለሚሞቅ ይመስለኛል የሁሉም ነጠላ ጫማ ነው የአንዳንቹ የፕላስቲክ፣ ያንዳንዶቹ የቆዳ። ታዲያ ወደ ቤት ሲገባ በር ላይ እየተተወ ነው። ሱሪና ኮት ወይ ጃኬት የሚለብሱ በጣም ጥቂት ስለሆኑ ባለስልጣኑን ከሌላው በአለባበሳቸው መለየት አይቻልም። እንደውስ በበርታ የሰው ልዩነት በዕድሜና በፆታ ካልሆነ በቀር የት አለና?!

ጨዋታቸው በአማርኛም በበርትኛም ነው። እኔም ስለቆይታዬ እያስብኩ፣ ስለማህበረሰቡ እንግዳ ተቀባይነት እየተገረምኩ አዳምጣቸዋለሁ። በመሃል ከጨዋታቸው ጋር በምን እንደተያያዘ ባላውቅም "ይህን የመሰለ ነገር ልንገራችሁ" በማለት አስተዳዳሪው ንግግር ጀመረ ጆሮየን አቆምኩ መናገር የጀመረው ተረት ነው። ፈጥኜ ይቅርታ ጠየቅሁትና እንደዚህ ያለ ነገር ለእኔ ጥናት ስለሚጠቅመኝ እንድቀዳው ጠየቅሁት። "የሚጠቅምሽ ከሆነ ተዘጋጅቼ ሌላ ጊዜ እነግርሻለሁ ለዛሬው መቀዳቱ ይቅርብኝ" አለኝ ሳስገድደው አልፈለኩም፤ የለብኝኝም፤ ከማሃል አንዱ "ተረት የሚናገር አያት ነው እሱ አያት ሆኗል ብዙ ተረት ሊነግርሽ ይችላል" በማለት ቀለደበት። ሁሉም ሳቁ። ሌሎች የሚችሉም ካሉ እንዲነግሩኝ ማግባባት ጀመርኩ። በእርሱ እየቀለዱ ሌላ ጊዜ ስመለስ ሰብስበው እንደሚቆዩኝ ነገሩኝ። በዚህ ሁኔታ እየተጫወቱ አምሽተው ስለመሸ እየተሰናበቱን ወጡ። አይ በርታዎች ምነው እንደእነሱ ሁሉ ሰው ግልጽና የዋህ ቢሆን?!

**እሁድ ሐምሌ 24 ቀን 2003 ዓ.ም.**

ዛሬ ሌሊት የረመዳን ፆም የሚያዝበት በመሆኑ ሲቲና እናቷን ፆም ለማስያዝ መሄድ አለባት። አብሬያት መሄድ እችል እንደሆን ጠየኳት። ከፈለግሽ እኔም ብቻሽን ጥየሽ ከምሄድ በጣም ደስ ይለኛል አለችኝ። ቁርሳችንን በልተን ቡናችንን ከጠጣን በኋላ ትናንት ለበዓሉ የገዛዛችውን ዕቃዎች ሸክፈን ወደ እናቷ መንደር አመራን። እንደደረስን በድጋሚና ፆም አብሪያቸው ለመያዝ በመምጣቴ ሁሉም ሰው ደስታው ወሰን አልነበረውም። ሁሉም

እየደጋገሙ፣ እያረፉ፣ እየተነሱ እያቀፉ ሳሙኝ። እኛ ወደ ሴቶቹ እልፍኝ ገባን ሹፌሩን ይዘው ወንዶቹ ወደ አል ከለዋቸው አመሩ።

ሾፌሩ ግራ ገብቶታል፤ ሲያገኘኝ ክርስትያን ነበርኩ አሁን የለየልኝ እስላም ሆኛለሁ፤ እና የማድር ስላልመሰለው በጥያቄ ዐይን ያየኛል። ስለገባኝ ዝም አልኩት። ከተስተናገድንና ትንሽ ከቆየን በኋላ ግን ከሲቲና ጋር ተመካክሬ አስጠራሁትና እኔ እዚሁ እንደማድርና መሄድ ከፈለገ ወደሾርቆሌ ተመልሶ ነገ እንዲመጣልን ካልፈለገ ግን ማደር እንደሚችል ስነግረው በድንጋጤ "እዚሁ ልታድሪ?!" ብሎ ጠየቀኝ መልሴ አዎ ሲሆንበት እያቅማማ "ነገ በስንት ሰዓት ልምጣልሽ?" ሲለኝ እንደተመቸህ ከቻልክ እረፈድ ሲል አልኩት "ደህና እደሪ" ብሎ ወደ መኪናው አመራ። አንድ ክርስቲያን እህቱን እስላሞች ስለማረኩበት ያዘነ መሰለኝ። አማራ ነዋ ምን ያርገው?! በርታ ቢሆን…

የሲቲና እናት መንደር ሴቶች በበዓል ዝግጅት ተወጥረዋል። እኛም አንዳንድ ነገር ተራዳን ምሳ በላን ቡና ተፈላ ሁሉም በበርታ ሥርዓት ተከናወነ። ሲቲና ለእናቷ ጦም መያዣ ፍየል ገዝታለች ታርዳ እየተዘጋጀች ነው። አካባቢው በጣም ከመሞቁ የተነሳ ውሃ ጥሙ አይጣል ነው የበርታዎች የሎሚ ጭማቂ ባይኖር ምን ይውጠኝ ነበር።

እየመሸ ሲሄድ የሌሊቱን የፆም መያዢያ ሥርዓት ለማየት ብጓጓም ልቤ ግን ለሁለት ተከፍሏል። በእስካሁን ቆይታዬ የሰበሰብኩት መረጃ ለተሠጠኝ የቤት ሥራ መጥቀሙ እያጠራጠረኝ መጥቷል። እንደው በከንቱ ሰለምኩ ይሆን? እናቴ ጉድሽን አላየሽ ዛሬ በበርታዎች መንደር የእስላም ፆም ልይዝ መሆኑን ብትሰሚ ምን ትይ ይሆን!?

ሴቶቹ ጉድ ጉድ ሲሉ ቀኑ እየመሸ ሄደ። እኔን ሰላም ለማለት ብዙ ሰዎች መጥተው ሄደዋል። በእንግድነቴም ምክንያት ልዩ ልዩ ነገር ከየቤቱ እንደተላከልኝ ሲቲና ነግራኛለች። ሲመሽ በጣም ስለደከመኝ ተጣጠብኩና አረፍ አልኩ። እነሲቲና በበርትኛቸው እያወሩ እየተሳሳቁ ምግብ ያዘጋጃሉ። ያልተሰራ ነገር የለም ገንፎ፣ ማባያው ቁንቁፅ፣ጥብሱ፣ወጡ፣የሎሚ ጭማቂው ሾርባው ዳቦው ምኑ ቅጡ ሁሉም ተዘጋጅቶ እንዳለቀ ትንሽ ለማረፍ ጋደም ጋደም አልን።

ወደ ዘጠኝ ሰዓት ገደማ ሴቶቹ ተነስተው ጉድ ጉድ ሲሉ ወንዶቹ ወደ መስኪድ ሄዱ ትንሽ ቆይተው ሴቶቹም ወደዚያው አመሩ ሼኪው አዛን ሲል ይሰማኛል እየተገላበጥኩ ሰግደው እስኪመለሱ ጠበቅሁ።

ሲመለሱ ሸር ጉዱ ተሟሙቆ ቀጠለ። ከተሠራው ምግብ ለወንዶቹ ወደ አልከላዋው ተላከ። እኛ ካደርንበት ቤት ቅርብ ስለሆነ ድምፃቸው ይሰማኛል የወንዶቹ ቡናም ተፈልቶ ተላከ። ከዚያ በኋላ ጊዜው የሴቶቹ ነው እነሲቲና ቤት እኔ በእንግድነት ስላለሁ ብዙ ሴቶች ያሰናዱትን እየያዙ ወደኛ ተሰበሰቡ። የሲቲና እናት ታላቅ በመሆናቸው እንደፀሎትም እንደምርቃትም የመሰለ ነገር በበርትኛ አደረጉና መብሉ ተጀመረ።

ለእኔ በዚያን ሰዓት መብላት አስቸጋሪ ነበር። የፋሲካ ሌሊት ቤታችን ሁሉ ሰው ተነስቶ ሲበላ ላለመብላት የምነሳ እኔ ብቻ ነበርኩ። ስንት ቀን ተለምኜ ያልሆነልኝን አሁን እንዴት እንደምሞክረው ግራ ገባኝ። እኔን ብለው መጥተው አልበላም አይባል ነገር። እንደነገሩ ስለካክፍ ቆዩሁ ሲቲና ስለነቃች እንዳይስገድዱኝ ትከላከላለች። ምግቡ እያበቃ ስለሆነ እንደገና መመራረቅ ተጀመረ፤ ሁሉም አሜን ይላል። ምርቃቱ ሲያበቃ ሴቶቹ አንድ አንድ እያሉ ወደቤታቸው ተመለሱ። እኔም በተዘጋጀልኝ መኝታ ላይ ጋደም አልኩ።

**ሰኞ ሐምሌ 25 ቀን 2003 ዓ.ም.**

ዛሬ ፆም በመሆኑ ሾፌሩ እንደመጣልን ወደ ሸርቆሌ በጠዋት ተመለስን። ሸርቆሌ ፀጥ ብላለች። "የፆም የመጀመሪያ ቀን ይከብዳል" ይላሉ። ሁሉም ሰው ንቁ አይመስልም፤ ሙቀቱም ገና በጠዋቱ አይሏል። እቤት ስንደርስ እኔ ፆመኛ ባለመሆኔ ቁርሴን አዘጋጅቼ በላሁ። ብቻ መመገብ ሲያስጠላኝ ሾፌሩን አስጠራሁት፤ "አትፆሚም እንዴ?" አለኝ። እያሽሟጠጠኝ እንደሆነ ገብቶኛል ዝም ብዬ አሳለፍኩት።

ከሰዓት በኋላ ሲቲና አባ መሃመድ ወደሚባሉ ሰውዬ ቤት ይዛኝ ሄደች። ከእናቷ ዘንድ መልዕክት ይዛላቸው የመጣች ይመስለኛል። ወደ ግቢያቸው እንደዘለቅን አገኘናቸው ረዥም ጥቁር የበርታ አዛውንት ናቸው። "ምነው በፆም እንግዳ ይዘሽ መጣሽ?" አሏት

ጉዳዩን ነገረቻቸው የእኔንም ሸርቀሌ መገኘት ጭምር ቀስ ብዬ እሳቸውንስ ባነጋግር ስላት "እንደውም ተረት ያውቃሉ ቆይ ልንገራቸው" ብላኝ ወዲያው ነገረቻቸው እሳቸውም ያለምንም ማቅማማት ተስማሙና ነገ በዚህ ሰዓት እንድንመጣ ነግረውን መልዕክቱን አድርሰን ተመለስን፡፡

**ማክሰኞ ሐምሌ 26 ቀን 2003 ዓ.ም.**

ዛሬ በቀጠሮአችን መሠረት አባ መሃመድ ቤት ሄደን፡፡ እቤት አገኘናቸው፡፡ ቤት ስለሚሞቅ በግቢያቸው ጥላ ቦታ ፈልገን ተቀመጥንና ቃለ ምልልሱን ቀጠልን፡፡ አባ መሃመድ ሰሞኑን ዘመድ ሞቶዋቸው ራቅ ወዳለ ቦታ ቆይተው እንደነበረ ሲቲና ስለነገረችኝ ያንን በማስታወስ ከለቅሶ ሥነ ስርዓት ጀምሮ በበርታ ባህል ያለውን ነገር እንዲነግሩኝ ጠየኳቸው፡፡ በደንብ አብራሩልኝ በተጨማሪም አንድ ሦስት ተረቶች ነግረውኛል፡፡ ለሚጠበቅብኝ ሥራ ይጠቅሙኝ ይሆናል፡፡ እስከ አስር ሰዓት ተኩል አብረናቸው ከቆየን በኋላ አመስግነን ተመለስን፡፡ (ስክርብ ከገፅ 29- 37 ይመልከቱ)

**ረቡዕ ሐምሌ 27 ቀን 2003 ዓ.ም.**

ዛሬ የፆሙ ሦስተኛ ቀን ነው፡፡ ሸርቀሌ በፆሙ ምክንያት ረጭ ብላለች፡፡ ብዙ የሰው ዝውውርና እንቅስቃሴ አይታይም፡፡ እምትነቃቃው የፈጥር ሰዓት ሲደርስ ነው፡፡ ሙቀቱ እያየለ የመጣ ይመስላል፤ ፊፅሞ አያንቀሳቅስም፡፡ ለቀለብ ከአሶሳ ይዘነው የመጣነው ነገር እየተገባደደ ስለሆነና ሲቲናም ስኳር ጭና መምጣት ስላለባት ነገ ወደ አሶሳ ሳንሄድ አንቀርም፡፡ እሰከ ዛሬ የሠራሁትን ስመዝነው ብዙም ሚዛን ሊደፋልኝ አልቻለም፡፡ በሌላ በኩል ሳየው ግን ስለበርታ ባህል የሚያስረዱ ብዙ መረጃዎች እንዳገኘሁ በማሰብ እፅናናለሁ፡፡

ወደ ከሰዓት ላይ ከቤት ወጣ እንዳልን አባ አብዱራሂምን አገኘናቸው፡፡ አንዳንድ ነገሮች ልጠይቃቸው መፈለጌን ስነግራቸው አሁን ወደ አባ መሃመድ ቤት እየሄዱ ስለሆነ ከዚያ ሲመለሱ ፈጥር ካልደረሰ ልንገናኝ እንደምንችል ሲነግሩኝ ለምን አብረን እዚያው

እንሄድም አለቻቸው ሲቲና ተስማማንና ጉዞ ቀጠልን ገር ገሩን እያወራን በመንገድ ነፊሳን ስናገኛት ይዘናት ሄድን፡፡ አባ መሃመድ ቤት ስንደረስ ከቤት አገኘናቸው፡፡ አባ አብዱራሂም የመጡበትን ጉዳይ በበርትኛ ቋንቋ ነገሯቸውና የእኛን አብረን መምጣት ምክንያት ሲገልፁላቸው በተለመደው ጥላ ሥር እንድናርፍ ተደረገና ወደ ቃለ ምልልሱ ገባን በቀደም ስንነጋገር ያለገለፁልኝ፣ የተዘለሉ፣ ወይም ተጨማሪ መረጃ ከሌሎች ሰዎች ጠይቀው ያመጧቸውን ጉዳዮች አንድ በአንድ እያነሱ አራቱም እየተፈራረቁ ካጫወቱኝ በኋላ የፈጥር ሰዓት በመድረሱ አመስግኛቸው ተለያየን፡፡ (ስክርብ ከገፅ 38-49 ይመልከቱ)

**ሐሙስ ሐምሌ 28 ቀን 2003 ዓ.ም.**

ዛሬ በጠዋት ተነስተን ጉዞ ወደ አሶሳ አደረግን፡፡ ከአሶሳ በወጣሁ በአስራ ሦስተኛ ቀኔ መመለሴ ነው:: እንደደረስን ወደ ማረፊያዬ አመራሁ ገብቼ ትንሽ እንደቆየሁ ኃይለኛ ነጎድጓድ ያለው ዝናብ መውረድ ጀመረ፡፡ ተጣጥቤ አልጋ ላይ አረፍ እንዳልኩ እንቅልፍ ይዞኝ ሄዶ ኖሮ ስነቃ ጨላልሟል፡፡ ሲቲና ለፈጥር እንድመጣ ልጆቿን ላከችብኝ፡፡ እቤቷ ስደርስ እሷ እየሰገደች ነው፡፡ ቤቱ ግን ተሟሙቋል፡፡ የሽርቆሌ ቤታችን ታወሰችን እዚህ ለማፍጠሪያ ሁሉም ነገር አለ፡፡

በትልቅ ትሪ ላይ ከፍራሾቹ አጠገብ ጥቂት ተምር፣ ሙዝ፣ ሾርባ፣ የሎሚ ጭማቂ፣አላብሬ ተደርድረዋል፡፡ በሌላ ትሪ ደግሞ መረቅና ወጣ ወጦች፡፡ ከሾርባው ቀድተው ሰጡኝ፤ መጀመሪያ ግን የሎሚ ጭማቂ እንዲሰጡኝ ጠየቅሁ ልጅቷ ቀድታ ሰጠችኝ፡፡

ሲቲና ሰላቷን ጨርሳ መጣች፡፡ ከሁለቱ ልጆቿ ትንሹ እድሜው አሥራ ሁለት ይሆናል ለካ ፆመኛ ኖሮ ሰዓት ስለደረሰ መጀመሪያ ሁለት ፍሬ ተምር ብቻ እንዲበላና እንዲያፈጥር ነገረችው፡፡ ትልቋ ሳትፆም ትንሹ መፆሙ አስገረመኝና ጠየቅሁ እሷ እንደ አባቷ ክርስትያን ነች አትፆምም አለችኝ፡፡ አይ ሲቲና ታሪከ ብዙዋ በርታ! ለካ ባለቤትዋ ኦሮሞ ናቸው ክርስትያን፡፡

እንዴ ሲቲዬ በርታ ሆነሽ እንዴት ኦሮሞ ለዚያውም ክርስቲያን እንድታገቢ ተፈቀደልሽ? ስላት "ታሪኩ ብዙ ነው እናቴ አሁን ሳፍጥርበት ከፈለግሽ በአጭሩ በኋላ እነግርሻለሁ" አለችኝ:: ዕውነቷን ነው ቀኑን ሙሉ ስትፆም ውላ ገና ሳታፈጥር በጥያቄ ማጣደፍ ልክ አይደለም:: ዝም አልኳት ግን በጣም እየከነከነኝ ነበር::

እሷም መጀመሪያ ትንሽ ተምር፣ ቀጥላ ሙዝ፤ በላችና ብዙ የሎሚ ጭማቂ ጠጣች:: እማይቻለው ውሃ ጥሙ ነው ባይ ናት:: ከዚያ በኋላ ምግብ ቀረበ:: ለእኔ የለመድኩትን እንጀራ በወጥ እሷም የባህሏን ገንፎ በቁንቁፅ ተያያዝነው:: ሽርቆሌ እያለን እነዚህ ሁሉ አማራጮች ስላልነበሯት በተገኘው ነገር ነበር የምታፈጥረው:: የዛሬው ግን ድግስ ይመስላል ሁሉም ነገር ሙሉ ነው:: ለእኔ ብላ ምን ያህል እንደተቸገረች ገባኝ፤ በርታ ባትሆን የውለታዋን ሸክም ባልቻልኩት ነበር::

አቦሉ ቡና እንደተጠጣ እኔ ሳላነሳ እራሷ የቅድሙን ጥያቄ መመለስ ጀመረች:: "ከቤተሰቦቼ ወደ ትምህርት ቤት የተላኩት እኔ ብቻ ነበርኩ:: እና እየተማርኩ እያለ አለማየሁ አስተማሪ ነበር ሲያየኝ ወደደኝ መሰለኝ አላስገባ አላስወጣ አለኝ:: ዘመዶቼ ለጋብቻ እንደማይፈቅዱለት ስነግረው ግዴለሽም ወደ አሶሳ ይዤሽ እጠፋለሁ አለኝ::" ያኔ የት ነበራችሁ? ጠየኳት:: "ጊዜን ነና የተወለድኩበትን ቦታ አሳይቼሽ የለ? ከዛ እኔም ልጅ ነኝ የጊዜውን ፍቅሬን እንጂ የሚያስከትለውን መዘዝ አልገመትኩም እሺ አልኩት ከዛ ቅያሬ እንደምንም ጠይቆ ይዞኝ አሶሳ ገባ:: ዘመዶቼ አጎቶቼ በሙሉ አበዱ፤ እንገድላለን አሉ፤ ለጊዜው ስለደበቀኝ ያለሁበትን በቶሎ ማወቅ አልቻሉም በመሃል የመጀመሪያ ልጄን አረግዣለሁ::

ይህንን ሲሰሙ አበሻ ክርስትያን አግብታ አዋረደችን በማለት ሁሉም አደሙብኝ:: እናቴ ልጄ አይደለችም ብላ ካደችኝ:: በኋላ ተሰብስበው ይመክሩና እሺ ምን እናድርግ አሁን ነጥቀን ብናመጣት ማን ያገባታል? አንዴ ከሃበሻ አርግዛለች ምን ይደረግ? ሲባል አንዱ የአጎቴ ልጅ "እዚያ ሆና ከምታሰድበን እኔ አገባታለሁ" ሲል እንዴት እንደሚሰርቁኝ

ይማከሩና አሶሳ መጥተው ያለሁበትን ማሰለል ይጀምራሉ። ዓለማየሁ አምጥቶ ያስቀመጠኝ ከትግሬዎቹ ሰፈር[47] በመሆኑ በቀላሉ ሊያገኙኝ አልቻሉም።"

ትግሪኛውን የለመድሽው ያኔ ነው እንዴ? "አዎ ያኔ ነው። እናልሽ ሳያገኙኝ እንደዛቱ ልጄን እወልዳለሁ። ልጅቷ ለክረምት ትምህርት አዋሳ ሄዳ ነው እንጂ አሳይሽ ነበር 24 ዓመቷ ነው። ልጅቷ ስድስት ወር ሲሞላት ያለሁበትን ይደርሱበታል። ስድስት ሆነው መጥተው እኔን እስከ ልጄ ንብረትም የቻሉትን ያህል ይዘው ወደ ሸርቆሌ ይወስዱኝና ዘጠኝ ወር ያስቀምጡኛል። እሱ ይጨነቃል ደፍሮ መምጣት አልቻለም ይገድሉታል፤ በኋላ እኔ ሳደባ፣ ሳደባ፣ ቆይቼ ሲዘናጉልኝ ልጄን ብቻ ይዤ እመጣና እንደገና አብረን መኖር እንጀምራለን። አሁንም እነሱም አድብተው ሲሰርቁኝ ተመልሼ ስመጣ ሦስቴ ነው አራቴ ሞክረው ሲያቅታቸው ተውኝ ጊዜውም እየተለወጠ መጣ አሁን ታርቀን እንዳየሽን እንኖራለን።" ብላ በአጭሩ ተረከችልኝ። ምናልባት ሲቲና ከባህሏ ያፈነገጠች የመጀመሪያዋ በርታ ሳትሆን ትቀራለች? በጣም ገረመኝ። ስንጫወት አምሽተን ወደ ማረፊያዬ አደርሰውኝ ተመለሱ። ውሎየን መዘጋገብኩና ተኛሁ።

**አርብ ሐምሌ 29 ቀን 2003 ዓ.ም.**

ዛሬ ወደ ሸርቆሌ ስለምንመለስ ሲቲና ስኳርና ዘይቷን እስከምትጭን እኔ ለቆይታ የሚያስፈልጉንን ነገሮች ስገዛዛ አርፍጄ ምሳ በላሁና ጉዞአችንን ቀጠልን። አምሻሽ ላይ ስንደርስ እዚያም ዝናብ ይጥላል። ስኳሩን አራግፈን ማፍጠሪያ ሰዓት በመድረሱ ወደቤት ገባን ቤቱን አፀዳድተን ጉድ ጉድ ካልን በኋላ ሲቲና አፈጠረችና ቡናችንን ጠጣትተን ተኛን። ነገ ከኢብራሂም ጋር ተረት ሊነግረኝ ተቀጣጥረናል ምን ያህል ይዞልኝ ይመጣ ይሆን?

**ቅዳሜ ሐምሌ 30 ቀን 2003 ዓ.ም.**

---

[47] አሶሳ ትግሬ መንደር፣ አረብ መንደር የሚባሉ ሠፈሮች አሉ በበዛት የተጠቀሱት ሰዎች እንጂ ተወላጁ የማይኖርባቸው ነበሩ ድሮ አሁን ግን ከስያሜአቸው በስተቀር ህዝቡ ተቀላቅሎ ነው የሚኖረው።

እንደተለመደው በጠዋት ተነሳን ሲቲና ዛሬ አትፆምም ምክንያቱም የወር አበባ ላይ ያለች ሴት ስለማትፆም። ሌላ ቀን ታካክሳለች፤ የእሷን ማፍጠሪያ ደግሞ ለሌላ የሚያፈጥርበት ለሌሌው ትሰጣለች። ስለዚህ ቡናችንን ጠጥተን ቁርሳችንን በልተን ወጣን። ስኳሩን እንደተለመደው አከፋፍለን ለምሳ ወደቤት ተመለስን። ከፈጥር በኋላ ቤታችን አንድ አንድ እያለች ሞላች። የወረዳው አስተዳዳሪ ሳምንት በይቆይ ያከረመውን ተረት ይነግረኛል ብዬ እየጠበቅሁት ነው። ትንሽ ቆይቶ መጣ። ጨዋታው እንደተለመደው ሲደራ እኔ ሥራዬን ቀስ ብዬ አስታወስኩ። ሁሉም ንገራት ንገራት አሉት "እሺ እነግራታለሁ መቅዳት ከፈለግሽም ትችያለሽ" አለኝ። እሺ ብዬ መቅረፀ ድምፄን አስተካከልኩ። አከታትሎ ሦስት ተረቶችን ነገረኝ። (ስክርብ ከገፅ 50-52 ይመልከቱ)። አመስግኜ ቴፑን አጠፋሁና። ተረቶች ለማህበረሰቡ ያላቸውን ፋይዳ ለሁሉም እንደቀልድ ሠነዘርኩ። ያው ጀግንነትን፣ታማኝነትን፣ሰው ወዳድነትን፣ ታታሪነትን ወዘተ ለማስተማር፤ ክፉ ድርጊትንና ጠባይን ለመውቀስና ለማረቅ እንደሆነ ነገሩኝ። አያቶች ለልጆቻቸው ተረቶችን በመንገር ልጆች ታማኞች፣ ጥሩ ሰዎች፣ እንግዳ ተቀባዬች ሃቀኞች እንዲሆኑ፤ውሸት፣ቅጥፈት፣ስርቆት፣ ጥላቻ እንዳይማሩ እርስ በርስ እንዲዋደዱና እንዲከባበሩ ያስተምራሉ። ልጆቹም በታሪኩ ደስ እየተሰኙ እኔም እንደ ጥሩው ሰው መሆን አለብኝ ይላሉ እያሉ በመቀባበል አስረዱኝ ሰዓቱ እየመሸ በመሆኑ ሁሉም ወደ ቤታቸው ሲሄዱ እኔና ሲቲናም ወደ መኝታችን አመራን።

**ዕሁድ ነሐሴ 01 ቀን 2003 ዓ.ም.**

ዛሬ ከሸርቆሌ ወራዳ የሰበሰብኩትን መረጃ ቁጭ ብዬ ሳዳምጥና የውሎ ማስታወሻዬን ሳነብ ዋልኩ። የተሰበሰበው መረጃ ብዙ ነው። ከትዕዛዙ አንፃር በቂ ይሁን አይሁን ግን አላውቅም። እንደውም እሱን ሳስብ ትዕዛዙ ሁሉ ያልገባኝ ይመስለኛል። በየዘውጉ የሚከለሰፍ፣በቂ ነገር ያለኝ አልመሰለኝም እና ከራሴ ጋር ሙግት ገጥሜ አረፈድኩ። ሲቲና መመሰጤን አይታ አልረበሸችኝም የራሷን የቤት ሥራ እየሠራራች ነው። ዛሬ ወደ ቤታችን ማንም ሰው አልመጣም ። የእኔም እንግድነት እየተረሳ ቤተኛ መሆኔ እየታወቀ መጥቷል። እንደውም "ቀይዋ በርታ" እንደሚሉኝ ሲቲና ነግራኛለች።

ዕውነታቸውን ነው አንድም ቀን ከባህል ልብሳቸው ውጪ አይተውኝ አያውቁም፤ የሚበሉትን እበላለሁ፤ የሚጠጡትን እጠጣለሁ፤ ሰላት ብቻ ስገጂ እንዳይሉኝና ጉዴ እንዳይፈላ እንጂ ከመልኬ ፍካት በስተቀር ሁለንተናዬ በርታ ሆኗል።

ዛሬ ማታ ሲቲና ስለስራዬ ጠየቀችኝ "እንዴት ነው ስንቅዬ የምትፈልጊውን መረጃ አገኘሽ?" አለችኝ እኔ እንጃ በርካታ ሥነ ቃሎችን እፈልጋለሁ፤ ለምሳሌ በቃል የሚባሉ ግጥሞች፣ ሙሾዎች፣ የሠርግ ዘፈኖች፣ ኪንታሊያዎች ፀፀሪናዎች አልኳት። "እነሱ እኮ ታዲያ አሁን አይገኙም አሁን ክረምት ነው፤ የእኛ ሰው የሚደኸይበት ጊዜ። እነሱን ለማግኘት በጥር በየካቲት ነው መምጣት ያለብሽ ያኔ ምርቱም አለ፤ ወርቁም እንደልብ ይገኛል፤ ተሂዝሮ እስከ ሱዳን መነገድ ይቻላል፤ ብር እንደልብ ሲሆን ሠርጉም፣ድግሱም ፈንጠዝያውም ያኔ ይደራል። ያኔ የምትፈልጊውን ታገኛለሽ። አሁን ክረምት በዚህ ላይ ረመዳን እነዚህን ነገሮች አሁን ማግኘት የምትችይ አይመስለኝም። ምን ይሻላል?" ብላ መልሳ ጠየቀችኝ። ለጥቂት ጊዜ ዝም ብያት ብቻዬን በውስጤ እያወራሁ ቆየሁ። ያለችው ነገር ዕውነት ነው ከዚህ በኋላ ሸርቆሌ በመቀመጥ እሷን በያመኛ ጎኗ ከማንገላታት ውጪ የማገኘው ነገር አልታይሽ አለኝ። አሶሳ ተመልሼ መረጃዎቼን በደንብ ማብላላት ጠቃሚ መስሎ ስለታየኝ አንቺን አሁን ሸርቆሌ የሚያቆይሽ ጉዳይ አለ እንዴ? ብዬ ጠየኳት "አይ እኔ ለአንቺ ሥራ ነው እንጂ የኔማ ቅዳሜ ለት አልቋል" አለችኝ። እንግዳው አሶሳ እንመለሳ ስላት "የሚሻል ይመስለኛል፤ የምትፈሊጊው ነገር የሚገኝ ከሆነ እያጠያየቅን እኔ በየሳምንቱ ስኳር ላመጣ ስመጣ አብረን መምጣት እንችላለን፤ ከዘህ በኋላ የሠርቆሌ ቆይታሽ ብዙ ጠቃሚ አይመስለኝም።" ስትለኝ ነገ ወደ አሶሳ ለመመለስ ተስማማንና ተኛን።

**ሰኞ ነሐሴ 02 ቀን 2003 ዓ.ም.**

ዛሬ አምሻሽ ላይ ከሸርቆሌ ወደ አሶሳ ተመለስን፡፡ አዕምሮዬ ውስጥ ብዙ ሀሳቦች ይተራመሳሉ፤የምን ይገፔ ልመለስ ጥያቄ ሰቅዞ እንደያዘኝ አምሽቼ ወደ ማረፊያዬ ሄጄ የቀዳሁትን ሳዳምጥ ቆየሁ፡፡ ሲቲናን መጠየቅ ያለብኝና ስትሠራቸው ማየት ያለብኝ ባህላዊ መዋቢያዎች፣ጭሳጭሶችና ምግቦች እንዳሉ ሲታሰበኝ ማስታወሻዬ ላይ አስፍሬ ተኛሁ፡፡

**ማክሰኞ ነሐሴ 03 ቀን 2003 ዓ.ም.**

ሲቲና ዛሬ ፆመኛ ናት፡፡ ጠዋት ቁርሴን በልቼ ወደ እሷ ቤት ስሄድ ልብስ ታጥባለች፡፡ ውጪ ወንበር አምጥተውልኝ ተቀመጥኩና ማታ በማስታወሻ ስለያዝኳቸው ነገሮች አነሳሁባት፡፡ አሠራራቸውንም እንድታሳየኝ ጭምር፡፡ "እሺ ስራዬን ልጨርስና ገበያ ሄደን አንዳንድ ነገሮችን ገዝተን እንመጣና አሳይሻለሁ፡፡ ጪሱን መታጠን ከፈለግሽ ደግሞ አደርግልሻለሁ" አለችኝ፡፡ ደስታውን አልችለውም አልኳት፡፡

ከሰዓት በኋላ ለጭሶቹ የሚያስፈልጉትን ነገሮች ለመግዛት ወጣን በርካታ ነገሮችን ገዛች አንዱንም አላውቅም፡፡ ከሎሚ በቀር ስማቸውን እየጠራች ከያሉበት ተዟዙረን ገዛን፡፡ እስካሁን ከእኔ ጋር ስትደክም ለሲቲና ምንም ነገር አድርጌላት ስለማላውቅ አንድ ነገር መግዛትና በስጦታ መልክ መስጠት እንዳለብኝ ስለተሰማኝ መቀመሚያ ሽቶ ለመግዛት የሚሸጥበት ሱቅ እንደገባን አንድ ቶብ (የበርታ ሴቶች የባህል ልብስ) አይታ አስወረደችና ዋጋውን ጠየቀች፤ በጣም ያምራል፡፡ ስምንት መቶ ብር አላት፡፡ ተከራከረችው፤ትንሽ ቀነሰ አምስት መቶ ሽጥ አለችው ይሄ ሁሉ በበርትኛ ነው ሲቲና እከስራለሁ አላት፡፡

ትታው ልትሄድ ስትል ተከራከሪና እኔ ነኝ እምገዛልሽ በጣም ያምራል አንቺም ወደሽዋል ስላት በርታ ጋ ድብብቆሽ የለም ይህንኑ ቃል በቃል ነገረችው "ወላሂ እከስራለሁ ሲቲና እሷ ልትገዛልሽ ከሆነ ግን ወላሂ እሷ አስባ ልትከፍልልሽ ካለች እኔ ልክሰር ክፈሉ ወላሂ" አለ፡፡ ዕውነቱን እንደሆነ ያስታውቃል፤ ቢያንስ ሰባት መቶ ብር ሊሸጠው ይችላል፡፡ ግን እንግዳ እከፍላለሁ ብሎ፤ ወገኑ ለሆነችው ለእሷ ሌላ አስቦ እሱ አልቀንስም ማለት

አልፈለግም እንደሚከስር ዕውነቱን ተናግሮ እንዳያስቀይመኝ አምስት መቶ ተስማማ። በዚህ ቅንነቱ አላህ ሌላ ሲሳይ ይሰጠዋላ!! እንደዚህ ናቸው በርታዎች!

ከገበያ ተመልሰን ሲቲና ቤት ስንደርስ አካባቢው ተሸብሯል። የለቅሶና የጨኸት ድምጽ ስንሰማ ደነገጥን በተለይ ሲቲና ተርበተበተች ከቤታቸው ፊት ለፊት ታሞ የነበረ የመስተዳድር ሾፌር ሞቶ ነው። ሲቲና ከተሳፈርንበት ባጃጅ ዘላ ወርዳ ጥላኝ እየጮኸች ወደ ለቅሶው ቤት ገሰገሰች። እኔም ደንግጫለሁ የገዛነውን ዕቃ ሰብስቤ ወደ ግቢ ገባሁ። ግን የሞተው በርታ ይሆን? እያልኩ አስብ ነበር። የበርታ የለቅሶ ሙሾ ለመሰብሰብ አይ የሰው ነገር!!

እቤት ስገባ ተደናግጠው አጥሩ በር ላይ ያሉትን ልጆቿን አገኘኋቸው ሴቷ ታለቅሳለች፤ እስትረጋጋ ቆየሁና ስለሟቹ ጠየቅሁ አማራ ነው ለዚያውም ጴንጤ አይ ኪሳራ!

ሲቲና ለቅሶው ስለረበሻት ነገሮቹን መሥራት አይታሰብም። ምናልባት ነገ ከቀብር በኋላ ካልደከማት ታሳየኝ ይሆናል።

**ረቡዕ ነሐሴ 04 ቀን 2003 ዓ.ም.**

ዛሬ እቤት ቁጭ ብዬ መረጃዎቼን በድጋሚ ሳዳምጥ ዋልኩ። ትንሽ ዋጋ ያለው ነገር እንደሰበሰብኩ እየተሰማኝ ነው። ሲቲና ቀብር ስለዋለችና ከፆሙ ጋር ለቅሶው ስላደከማት እንድታርፍ ተውኳት። ዝናቡም የሚያንቀሳቅስ አይደለም። ምግብ እንደነገሩ ቀማምሼ ከቤቴ ሳልወጣ በመረጃዬ ስቆዝም አምሽቼ ተኛሁ።

**ሐሙስ ነሐሴ 05 ቀን 2003 ዓ.ም.**

ጧት 3፡00 ሰዓት አካባቢ ሲቲና መጣች። ስኳር ለማስፈቀድ ወደ ንግድ መምሪያ እየሄደች ነው። ነገ እንደተለመደው ጭና ሸርቆሌ ትሄዳለች። ስለዚህ ከነገ ጀምሮ እስከ እሁድ ድረስ እሷን ማግኘት የማይሞከር ነው። አሶሳን ሳልለቅ ተጨማሪ መረጃዎች ካስፈለጉኝ ለመጨመር የሰበሰብኩትን ዳታ ማንበብና የተቀዳውን ማዳመጥ ስለሚኖርብኝ እሷ እስክትመለስ ይሄን ስሠራ መቆየት እንዳለብኝ አቅጃለሁ።

ቀኑን በዚህ ሁኔታ አሳልፌ ወደ አስር ሰዓት ላይ ወደ ክልሉ ፕሬዘዳንት ቢሮ ከሲቲና ጋር ሄደን አክራሞታችንን በአጭሩ ሪፖርት አደርግን። የቸገረኝ ነገር ካለ ጠየቁኝ ምንም እንዳልተቸገርኩ ግን ተገቢውን መረጃ ለመሰብሰብ ጥሩ ጊዜ እንዳልመረጥኩ ክረምቱና ረመዳን እንደልብ መረጃ እንዳላገኝ እንደተገዳደሩኝ ነገርኳቸው። ታዲያ ምን አሰብሽ ሲሉኝ የያዝኩትን ይዤ ሰኞ ለመመለስ እንዳሰብኩ ነገርኳቸው ስላደረጉልኝም መልካም ነገር አመስግኛቸው ወጣሁ። አሁን የት እንደምሄድ ሲጠይቁኝ ሲቲና ቤት ለፈጥር እንደምሄድ ገልፀንላቸው ተለያየን።

ሲቲና ቤት ደርሰን ትንሽ እንደቆየን የፕሬዘዳንቱ አጃቢ መኪና ይዞ መጣና ሲቲናን አስጠራ። ወጥታ ስትመለስ ዘምቢል ሙሉ ዕቃ ይዛለች። "ምን እንደሆን ታውቂያለሽ ስንቅዬ?" አለችኝ ምንድነው ስላት "የፕሬዘዳንቱ ሚስት ለአንቺ የላከችው ማፍጠሪያ ነው" አለችኝ። በዘንቢሉ ውስጥ ዶሮ ወጥ፣ ገንፎ፣ ሾርባ፣ ዳቦ፣ ተምር ሳይቀር አለበት የበቆሎ እሸት ቅቅልን ጨምሮ። አቤት በርታዎች ይሄ ሁሉ እኔ እንግዳ ስለሆንኩ ነው ስልክ ደውዬ አመሰገንኩ "ባህላችን ነው ሸርቆሌ ሄደሽ ተደበቅሽና ቤቱን ሳናሳይሽ ረመዳን ገባ፤ ሌላ ጊዜ እንክሳለን" አሉኝ ሚስትየዋ አቤት ገርነት!!

**አርብ ነሐሴ 06 ቀን 2003 ዓ.ም.**

ቀኑም ምሽቱም በንባብ፤ በማዳመጥና በቁዘማ አለቀ። አሁንም ግን የጠራ ነገር አልታይሽ እያለኝ ነው።

**ቅዳሜ ነሐሴ 07 ቀን 2003 ዓ.ም.**

ዛሬ ሲቲና ስኳሯን በጊዜ ሻሽጣ 9:00 ሰዓት አካባቢ አሶሳ መመለሷን ደወለችልኝ። ተነስቼ ወጣሁና እሷው ቤት አመሸሁ። ነገ ጠዋት ጀምረን ቁንቁጹንም፣ ዲልካውንም፣ ጭሱንም ለመስራት ተቀጣጥረን እቤት አድርሳኝ ተመለሰች።

**ዕሁድ ነሐሴ 08 ቀን 2003 ዓ.ም.**

በጠዋት ተነስቼ ሲቲና ቤት ደረስኩ ቁርስ እዚያው ተዘጋጅቶልኝ በላሁ። እስከዚያ ሲቲና ዕቃዋን ማቀራረብ ጀመረች። የሽቶዎቹንና የጨሶቹን አቀማመም እያሳየችኝ መሥራት ጀመረች ቪዲዮ ካሜራ ስለሌለኝ ሂደቱን በቃሏ እንድትነግረኝ አድርጌ ቀዳኋት። (ስክርቭ ከገፅ 53- 56 ይመልከቱ።)

**ሰኞ ነሐሴ 09 ቀን 2003 ዓ.ም.**

ዛሬ ወደ አዲስ አበባ ተመላሽ በመሆኔ ጠዋት ሻንጣዬን ሳዘጋጅና እንዳንድ የቀሩኝ ነገሮች ካሉ ብዬ መረጃዎችን ስፈትሽ አውሮፕላን ማረፊያ የመገኛዬ ሰዓት ደረሰ። ምሳዬን በልቼ ከሲቲና ጋር ከቦታው ደረስን ዕቃዬን አስፈትሼ እንደጨረስኩ ሲቲናን ወደ ቤት እንድትመለስ ተሰናበትኳት። ስመጣ ግራ እንዳልተጋባሁ ስመለስ በጣም ጨነቀኝ፤ ሲቲና ማልቀስ ጀመረች በርታዎች ይሄው ናቸው በፍፁም ማልቀስ እንደሌለባት ስነግራት ፊቷን አዙራ ጥላኝ ሄደች። አልታወቀኝም እንጂ እኔም እያለቀስኩ ኖሯል ለካ ሲገርም!

አውሮፕላኑ 8፡30 ላይ መጥቶ ተሳፈርን 9፡30 አካባቢ አዲስ አበባ ደረስን። የአንድ ወር የቤንሻንጉል ቆይታዬ በዚሁ ተጠቃለለ። አላሃምዲሊላሂ!

# አባሪ አምስት

## በመስክ ስራ በቃለ ምልልስ የተሰበሰበ መረጃ ማሳያ

***ቃለ ምልልስ አንድ***

***የመረጃ ሰጪዎች ስም፡-***

1. አባ ቤሎ አዲቴ፣ ***ዕድሜ***፡- 52[48] ***ሥራ፡-*** ግብርና **ልዩ *ሙያ*** ፡- የሀገር ባህል መድሃኒት አዋቂ፣ **ብሔር፡-** በርታ
2. መንሱር ቤሎ፣ ***ዕድሜ***፡- 28፣ ***ሥራ፡-*** ግብርናና ወርቅ ቁፋሮ፣**ልዩ *ሙያ*** ፡- የሀገር ባህል መድሃኒት አዋቂ ( ሥራውን ከአባቱ ለመውረስ የተዘጋጀ)፣ **ብሔር፡-** በርታ

***መረጃዉ የተሰበሰበበት ቀን፡-*** ሐምሌ 16 ቀን 2003 ዓ.ም ከ6፡00-8፡00 ሰዓት

***ቦታ***፡- በቤንሻንጉል ጉሙዝ ብ/ክ/ መንግሥት ሸርቆሌ ወረዳ በሲቲና ቤት ውስጥ

***ቃለ ምልልሱ የተደረገው፡-*** በበርትኛ/ ሩጣና ቋንቋ

**የአማርኛ አስተርጓሚ፡-** ሲቲና አደም

***መረጃ ሰብሳቢ፡-*** ስንቅነሽ አጣለ

***ሥራውን እንዴት ጀመሩት?***

*መጀመሪያ ይህን ሥራ የጀመርኩት ያው ታምሜ ነበረ፤ ዕድሜዬ ለአቅመ አዳም እንደደረሰ ያው ታመምኩኝ አንድ ዓመት ሙሉ ተኛሁ፤ ሀኪም ቤት ብወሰድ፣ በቁስ*

[48] እሳቸው ዕድሜያቸውን 52 ዓመት ነው ቢሉም ወደ 70 ዓመት እንደሚሆናቸው መገመት ይቻላል፡፡

ብታይ በሼኪ ብታይ፣ እንደዚህ ባህል መድሀኒት የሚሠሩ ቦታዎች ሁሉ ተወስጂ ዓመት ሙሉ ከመሬት አልነሳም ምን አልልም ህልም አየሁ፤ ህልም አይቼ የሆነ የአክስቴ ልጅ አለች አንሻ ነው ስሟ የሆነ ቦታ ሄደህ እዚያ የምትድንበት መድሃኒት አለ የሚል ህልም ታየኝና እስቲ አንሻን ጥሩልኝ ብዬ እሷ ተጠራችና በአልጋ ወስዳችሁ እዚያ ቦታ አድርሱኝ ብዬ እዚያ አደረሱኝ ያቺ የአክስቴን ልጅ እስቲ ይሄንን ቆፍሪ አልኳት እንደተቆፈረ እስቲ ነይና ሰውነቴን ነካኪኝ አልኳት ከዚያ ወደ ቤት መለሱኝ በአልጋ፤ ልክ ከሰዓት አካባቢ እንደዚህ ግድግዳ ይዤ ቆሜ መሄድ ጀመርኩ። ከዚያ በኋላ ቀጥ ብዬ መሄድ ጀመርኩ። ከዚያም ሰው ሲታመም በህልም ይታየኛል ህልም አያለሁ በቃ ያንን ሄጄ እቆፍራለሁ። ያንን ቆፍሬ አምጥቼ እሰጣለሁ ሰዎች ይፈወሳሉ። አሁን ቲቢ ታመው የነበሩ አሥራ ሁለት ሰዎች አሉ መድሃኒቱን ወስደው ተመርምረው ነፃ የተባሉ። ጤነኛ መሆናቸውን ያረጋገጡ፤ ግን እኔ ህልም አይቼ ነው እምሠራው። ስለዚህ አሁን የእኔ አጎት አለ አሁን የአስተዳዳሪው አባት ማለት ነው እሱ እንደዚህ ልፍስፍስ ብሎ ከእግሩ በታች ከሥራ ውጬ ከሆነ በኋላ መድሃኒት ሰጠሁ፤ ተመላልሼ አከምኩ፤ ያው እሚቀባ እሚጠጣ እሰጣለሁ፤ እሚታጠን እሰጣለሁ፤ ተሽሎት ቆሞ እየሄደ ነው ብዙ ሰዎች በዚህ መልክ እየዳኑ ነው ያሉት፤ ያው በእግዚአብሔር ሀይል ህልም ይታየኛል፤ ሄጄ አመጣለሁ የኔ ሰው ተፈውሶ አያለሁ።

እኔ ብዙ ጊዜ አተኩሬ የምሠራው ሰው ሲታመም ብቻ ነው፤ ሰው ሲታመም ድኖ ይሄዳል። ሰው እሚገድል፣ ሰው እሚጎዳ፣ መንግስትን እሚጎዳ፣ ሰው እንዲበተን ሰው እንዲጣላ፣ ሰው የወንጀል ሥራ ውስጥ እንዲገባ እንደውም አላውቀውም። ያ ሰው ይነግረኛል፤ ይሄን ይሄን ያመኛል ይላል፤ ሄጄ እተኛለሁ ይታየኛል፤ ያንን የሚፈልገውን መድሃኒት ሄጄ እቆፍራለሁ። አምጥቼ መስጠት ነው ይፈወሳል፤ በዚህ መልክ ነው ሥራዬን እምሠራው ። እዚህ ውስጥ ያለ አሁን ራሱን የታመመ፣ ወገቡን የታመመ እሰጥና ሂድና ይሄንን ሞክር እለዋለሁ ሄዶ ይሞክራል ሄጄ እኮ ተሻለኝ ይላል።

ያው እኔ እንደዚህ በመሥራቴ ያበደ ሰው አሁን እንትን ሊመው ይችላል መድሃኒት ተደርጎበት ነው፣ አብሾ ጠጥቶ ነው ይባላል፤ እንደዚህ ዓይነት ነገሮች እኔ መድሃኒት

እሰጣለሁ፤ ያ ሰውዬ ይሻለዋል፤ አሁን እንደዚህ አሥራ ሦስት ልጅ የወለደ አለ፤ ድሮ አብዶ ልብሱን ጥሎ መልሰን በዚያ ሰበብ ያ ሰውዬ ድኖ ተዋልዶ ምን ብሎ ያቺ ትናንትና ያየሻት ልጅ ከእነሱ ነው የተሰጠኝ። ትልቅ ሰው ነው ይሄ ምንም ክፉ የለውም ምንም ችግር የለውም ብለው በስጦታ ነው የተሰጠችኝ ያቺ ሚስታቸው[49] ትንሽዋ ውሃ ያቀረበችልን አጎቷ ነበር እንደዚያ ሆኖ የነበረው ያው ተመላልሼ አክምኩኝ ያ ሰውዬ ዳነ ሥራ ላይ ነው።

***ምን ያደርጋሉ አሁን ሲቆርጡ ሲሄዱ? ቆርጠው ሲመለሱ እንዴት ነው የሚቀምሙት፣ እሱን ሁሉ ጠይቂአቸው።***

መጀመሪያ እኔ መቶ ብር ከዚያ ሰውዬ እወስዳለሁ፤ድፍን መቶ ብር፤ እሄዳለሁ ልክ መድሃኒቱን ሳይ በቅጠል በምናምን ይታወቃል፤ እዚያ ሄጄ ቁጭ አረጋለሁ ያንን መቶ ብር፤ እቆፍራለሁ ቆፍሬ ከመቶ ብር ጋር አምጥቼ ለእሱ ነው እምሰጠው። እሱ ብቻ ነው የሚያውቀው ሌላ የሚያውቅ ሰው የለም።

***ለልጃቸው?***

አዎ እሱ ያስቀምጣል ያ ሰውዬ ይመጣል፤ እዚያው ቀምሜ እሰጣለሁ ይዞ ይሄዳል፤ ይታከማል፤ የሚጠጣ፣ ወይ የሚቀባ፣ እሚታጠን፣ እሰጠዋለሁ ወስዶ ሄዶ ታክሞ ሲሻለው የሚያሰበውን፣ የሚመኘውን፣ የሚፈልገውን፣ ነገር ነው እሚሰጠኝ ከዚያ ያቺ መቶ ብር አብራ ነው ከቀሪው መድሃኒት ጋር የምትቀመጥ ሌላ እስከሚተካ ማለት ነው፤ አይለየውም ገንዘቡ ለእሱ ተብሎ እንደዚያ የሚቀመጥ ነው።

***ሰውየው መልሶ ይወስደዋል ብሩን?***

አይወስደውም።

---

[49] ትንሽዋ ሚስታቸው ዕድሜዋ ወደ 25 የሚገመት ሲሆን ቀድመን እሷ ቤት በመግባታችን ለቃለ ምልልሱ ቀጠሮ የወሰድነው እዚያ ነበር።

*ከመድሃኒቱ ጋር የት ነው እሚቀመጠው?*

እሳቸው ጋር እዚህ ውስጥ (*መድሃኒት ማስቀመጫዋን ከሰሌን የተሠራች ቦርሳ መሰል ኮሮጆ እያሳየች።*) ይቀመጥና ሲድን ሰውየው ከዚያ ይጠቀሙበታል።

*ካልዳነስ?*

አሰላም ማሊኩም። ማሊኩም አሰላም[50] በቃ መድሃኒት ብዙ ጊዜ አሁን ሰውየው ላይሻለው ይችላል፤ አክሜዋለሁ አልተሻለውም፤ ግን ምንድነው አብዛኛው ሰው እንግዲህ ከራሱ ፍላጎት በቃ እኔ አልተሻለኝም ሌላ ቦታ ሄጄ አፈላልጋለሁ ግን የሰጠሁህን ብር ትቼልሃለሁ ብሎ ካለ ይቀራል፤ ስጠኝ ገንዘቤን እኔ አልተሻለኝም ካለ ይመለሳል። አይ እኔ አልተሻኝም አንተ ግን የምትችለውን አድርገሃል ለፍተሃል ከእኔ ጋራ እኔ ይቅር ብያለሁ ካለኝ ነው እማስቀረው አለዚያ እመልሳለሁ።

***መድሃኒቱን ሊቆርጡ ሲሄዱም ሆነ ለበሽተኛው ሲሰጡ እንደው እሚያደርጉት ፀሎት አለ ወይ? ወይም ቅደመ ሁኔታ አለ ወይ? ከቤት ሲወጡ ጀምሮ የሚይዙት ቁሳቁስ መቆፈሪያ ምንድነው? ከቤት መጀመሪያ ሲወጡ እንዴት አርገው ነው እሚወጡት? እዚያ ደርሰው መድሃኒቱን ያዩበት ቦታ ደርሰው ሲቆፍሩ የሚያደርጉት ሥነ ሥርዓት አለ ወይ? ይዘውስ ሲመጡስ? እሰቲ የሚያደርጓትን ጥቃቅኗን ሁሉ እንዲነግሩኝ ጠይቂያቸው።***

አንደኛ እኔ ስሄድ አንካሴ ነገር ይገኔ ነው የምሄደው መቆፈሪያ ለብቻ ነው ይገኔ የምሄደው ልክ እንደሄድኩ ብዙ ጊዜ ይጫወታል፤ ወይ ደሞ አይተሽ ይጠፋል፤ እንደዚህ እያየሽው ይሠወራል መድሃኒቱ፤ እባብ ሁሉ ሊታይሽ ይችላል፤ እዚያ ቦታ ላይ እባብ ሁሉ ይመጣብሻል፤ ስለዚህ ያንን አንካሴ እንደዚህ ሰካ! ሳደርግ እባብም ከሆነ ጥቅልል ብሎ እዚያው ቁጭ ይላል፤ መድሃኒቱም እዚያው ይቆየኛል ከዚያ በኋላ ያንን አንካሴ

---

[50] በበርታዎች በጨዋታ መካከል እንደአዲስ ሰላምታ መለዋወጥ፣ ተነስቶ መሳሳም የተለመደ ነው ወደ ኋላ አብራራዋለሁ።

እንደሰካሁ እቆርጣለሁ፤ ከሰካሁ በኂላ ነው እምቆፍረው ብሩንም እዚያው ቂጭ አድርጋለሁ። እባቡ አሁን ያን ብር ሲያይ ይሄዳል፤ ቀጥ ብሎ ይሄዳል አልመታውም አይገደልም፤ ከዚያ ቆፍሬ ወዲያው ከብሩ ጋር አገናኛለሁ እቃዬ ውስጥ እከታለሁ ብድግ ብዬ ያንን አንካሴ ንቅል አድርጌ እሄዳለሁ። መድሃኒቱ እንደወጣ ብሩ ላይ ነው እማስቀምጠው። እንዳይሸሽ እንዳይሰወር ማለት ነው። ከዚያ ቀጥ ብዬ መጥቼ አንካሴውን በር ላይ እሰካለሁ ወደ ሌላ ጎራ አልልም፣ ሰው ሰላም አልልም ቀጥ ብዬ ወደ ቤቴ ከዚያ ገብቼ አስቀምጣለሁ።

*ምን ሰዓት ነው እሚቆርጡት? ከቀኖቹስ የትኞቹን ቀኖች ይመርጣሉ?*

ምንም ቀጠሮ አልሰጠውም አሁን ሰው ታሞ ይመጣል ቤት ደሞ የተዘጋጀ የለም፤ ያ እሚፈለገው ነገር ቀጥ ብዬ በተፈለገው ሰዓት ሄጄ አምጥቼ እሰጠዋለሁ ቀን ሰኞ ነው ረቡዕ ነው ሀሙስ ነው አልልም። ቤት ካለ ግን ያው እቤት ያለውን እሰጣለሁ።

አሁን ስትሄጂ የአንዱ በሽታ ዓይነት አንዴ ብቻ ነው እምታመጪው ሁለተኛ ድጋሚ ስትሄጂ አታገኚውም ስለዚህ ስትቆፍሪ በዛ አርገሽ ነው መቆፈር ያለብሽ፤ ለሌላ ጊዜም እንዲጠቅም አድርገሽ እንጂ በድጋሚ ሄደሽ ወዲያውኑ አገኛለሁ የሚባል ነገር የለም። ተፈልጎ ሌላ ጊዜ በአጋጣሚ ልታገኚው ትችያለሽ እንጂ አንዴ እዚያ ቆፈርኩና እዚያው አገኘዋለሁ ማለት አይቻልም፤ ሊሰወርሽ ይችላል።

***ስለዚህ አሁን መድሀኒቶቹን የሚያገኙባቸው የተወሰኑ ቦታዎች የላቸውም እነሱንም በድጋሚ አያገኟቸውም ማለት ነው ምክንያቱም ቅድም ሀልም ማየት አለብኝ ብለውኛል።***

በቃ አንዴ አገኘሽ አይደለም ድጋሚ የለም ሌላ ቦታ ነው የሚያሳይሽ እዚያ ሄደሽ እንደገና ፈልገሽ ማምጣት እንጂ በድጋሚ ማግኘት የለም። አንዴ ብቻ እንደተገኘ በብዛት ማውጣት ነው።

ለምሳሌ ሰውየው ሄጄ ያንን መድሃኒት ቆፍሬ አምጥቼ ሰጠሁት ታከመ፤ ለምሳሌ ድኗል፤ ግን አልዳንኩም አለ፤ አልዳንኩም በቃ ብሬን መልስልኝ አለ። አሁን ያ መድሃኒት ከዚያ

ቦታ ወይ ይበሰብሳል፤ወይ ደሞ ይጠፋል፤ ምክንያቱም ያ ሰውዬ አደራውን በልቷል። እኔም ቅር ብሎኛል ውስጤ ያውቃል እሱንም እግዚአብሔር አይቶታል ስለዚህ ያ መድሃኒት አይገኝም። ለሌላ ሰውም አይሆንም። አንደኛ መድሃኒቱ በውሸት አይሠራም፤ዋሽቶ እንደዚህ አድርጌ፣እንደዚህ አድርጌ ብዬ ብሰጥሽ ሳትጠቀሚበት ይጠፋል። ሁለተኛ ገበያ ላይ እንደዚህ እንደዚህ ተዘርግቶ አይሸጥም። በቃ ለሚፈልገው ሰው እዚህ ውስጥ ካለ ከዚህ እሰጠዋለሁ፤ ሄዶ ይጠቀማል። እቤቴም ቢሆን መድሃኒቱን በዚች ብቻ ነው እማስቀምጠው። ከዚያ ያለፈ ለዚያ ለበሽተኛው ነው እማደርሰው ተጠቅሞበት ከተሻለው ጥሩ አልተሻለኝም ካለ አልተሻለኝም ነው፤ ያው ዕቃዋ ይህቺ ናት ማስቀመጫ ቦታ ማቀያየርም አይቻልም።

***አሁን ቢዋሽ ሰውየው ብሩን ላለመክፈል አልዳንኩም ብሎ ቢዋሽ መድሃኒቱ ይጠፋል ግን በሰውየው ላይ የሚደርስበት ነገር አለ?***

በቃ መድሃኒቱ ብቻ ነው እሚጠፋ እንጂ ሰውየው ምንም አይሆን። ይሄ መድሃኒት ግን አብሮ ይዞራል፤ በመድሃኒቱ ድኖ ጤነኛ ሆኖ ይኖራል አይደለም ዞሮ ሌላ ጊዜ ወይ ሌላ ዓመት ወይ ሌላ ጊዜ መልሶ ያ በሽታ ይመለሳል ድንገት ይታመማል ያኔ ዞሮ ይመጣል እራሱ አይቀርም። መታመሙ አይቀርም። ወይ ቲቢ ሊሆን ይችላል ወይ ነቀርሳ ሊሆን ይችላል ሌላ ነገር ሊሆን ይችላል ያ በሽታ መልሶ እንደሚያመውና መልሶ እንደሚጠይቅ አይቀርም።

***ያኔ ምን ያደርጋሉ? እንዲህስ ዓይነት ሰው አጋጥሟቸዋል?***

አንዴ ከልጄ ጋር ያጎት ልጆች ናቸው የእኔ የወንድም ልጅ ናት አሁን የዛሬ ሁለት ዓመት ታመመችና እንደዚህ ስብርብር አደረገኝ መቀመጥም መቆምም አቃተኝ ብላ ልጄ መንሱር[51] አሻት እንግዲህ ወደ ልጁ እያስተላለፍኩ ነው ነገ ሞት አለ ምን አለ ልጄ

---

[51] መንሱር የአባ ቤሎን የባህል መድሃኒት ዕውቀት ለመውረስ የተዘጋጀ ልጃቸው ሲሆን መድሃኒት ቆርጠው ሲያመጡ የሚቀበልና ሥራ ያሉትን የሚሠራ ነው። በቃለምልልሱ ወቅት አብሯቸው የነበረ በመሆኑ በምላሹም ይተባበር ነበር።

ነው እግረ መንገዱን አወቂው እኔ ነገ ሚች ነኝ ትልቅ ሰው ነኝ እኔ እሱ የኔን ዕውቀት ይዞ እንዲሄድ እያሳየሁት ነው። አሁን የዛሬ ሁለት ዓመት ያቺ እህቱ ታመመችና ሄዶ መድሃኒት ቆፍሮ አሻት ዳነች። ሁለት ብር ሰጠችው። ቆይታ መቼ ተሻለኝ ዝም ብለህ ነው እንጂ እኮ መቼ ተሻለኝ ስትለው ሁለት ብሩን አንስቶ እንቺ ብሎ ሰጣት፤ ከዚያ ብዙ ቆይቶ አራት ቀን ሙሉ እንደዚህ ኩርምትምት ስትል ለአባቷ ሄደችና እኔ እኮ መንሱር እንደዚህ እንደዚህ ብሎ አሽቶኝ ነበረ፤ የዛሬ ሁለት አመት አልተሻለኝም ብዬ ግን ብሩን አስመልሼዋለሁ ሂድና አንተ ለምንልኝ መጥቶ ይሽኝ ብላ አባቷን ላከች አባቷን ስትልክ እኔ ደግሞ ትናንት ማታ ዝም ብዬ ሄጄ እሽትሽት ሳደርጋት ዛሬ ተነስታ ወጥታ ሽንቷንም ሸናች፤ ይሄውና ይቺን አሥር ብር አባትየው መጥቶ እግሬ ላይ ወድቆ ለምኖ ሰጠኝ ዛሬ።

አሁን ለምሳሌ አብዛኛው ሰው ወባ ይታመማል እኛ የተወሰነ መድሃኒት ነው የምንሰጠው ያንን ይጠጣል ወዲያው በትውከት ይወጣለታል በቃ። ለወባ ይህቺ ተቀጥቅጣ ትጠጣለች። (ትንሽ ሥር ከሰሌኗ ኮሮጆ ፈልገው በማውጣት እያሳዩኝ) ከዚያ በኋላ ሰውየው ያስታውከዋል በቃ። ትኩሳቱና ማንቀጥቀጡ ያቆማል።

ሌላ አሁን ሰው ቡዳ ይበላዋል አይደለም ለእሱ ሁሉ እንሰጣለን። አሁን ቡዳ የሆነ ሰው እዚህ እኛ መሃል ይሆናል ቅድም ሥጋ እንደጠበስነው ማለት ነው መጥቶ ወይ ሲቲና ላይ ወይ አንቺ ላይ ዓይኑ ያርፋል እንበል መድሃኒቱን ስሰጥሽ እከሌ ነው የበላኝ ብለሽ ትጮሂያለሽ። ገና መድሃኒቱ ሲሰጥ፤ በቃ ዝም ብሎ ቡዳ የሆነ ወይ እነዚህ ጅብ የሚሆኑ ሰዎች አሉ ይባላል አይደለም እሱ ቢመጣ ቅድም ስጋ እንደምንጠብስ መድሃኒቱን ትንሽ እሳት ላይ ብናደርግ በቃ ፊስ ብቻ ይለቅበታል፤ ፊስ ብቻ ይለቅበትና ወይ ወጥቶ እልም ብሎ ይጠፋል ከመሃላችን።

***ስንት ልጆች አሉዎት?***

ስድስት ልጆች አሉኝ አምስት ወንድ አንዲት ሴት፤ ብዙ ሙተውብኛል ትልቋ ሚስቴ ያቺ አብራን ቁጭ ብላ የነበረችው አሥራ አንድ ነው የወለደች ሙተውባት ነው እንጂ ትንሿ አንድ ብቻ ነው የወለደችው ፡፡

*እንዴት ነው ሚስቶችዎ አይጣሉም ወይ እንዴት ተስማምተው ይኖራሉ?*

እንዲጣሉም እንዲዋደዱም የማደርገው እኔ ነኝ፤ ካላዳላሁ ሁለቱንም እኩል አድርጌ ከያዝኩኝ ሁለቱንም የሚበሉትን እሚጠጡትን እኩል ካመሟላሁኝ እኔ እኩል ሰላም ካልኳቸው ከጠየቅኋቸው ካቀራረብኳቸው ጥልም እማመጣው እኔው እራሴ ነኝ ፍቅርም እማመጣው እኔው እራሴ ነኝ፡፡

*ትናንት የገባንበት የማ ቤት ነው?*

የትንሿ ቤት ነው፤ ትልቋ ቤት አልገባችሁም፡፡ እሷ ግን ልታያችሁ መጥታለች፡፡ የመንሱር እናት ናት፡፡

*መንሱር የመጀመሪያ ልጅዎ ነው እንዴ?*

አይደለም ሌሎች ትልልቆች አሉ እነሱ ግን የኔን ዕውቀት ለመቅሰም ፍላጎት የላቸውም እንደገናም ደግሞ ራሳቸውን ዘመናዊ አድርገው ስለሚያስቡ ሊከተሉኝ አልፈለጉም፡፤ እሱ ግን እንግዳ ሲመጣ ይቀበላል ጫካ ስሄድ መጥቶ ይጠራኛል ስለዚህ የእኔን ፈለግ የሚከተል እሱ ብቻ ነው እንጂ ሌሎቹ ታሪኩንም አያውቁት፡፡

*መንሱር ስንት ሚስት አለህ?* ሁለት፡፡ ***ድሮ እርሶ ሲያገቡ የነበረውና አሁን በነመንሱር ጊዜ ያለው የሰርግ ሁኔታ ምን ይመስላል****?*

ድሮ እህል ነው የወሰድኩት ገንዘብ አልሰጠሁም አሁን አምስት ሺህ፣ አስር ሺህ፣ ሰባት ሺህ፣ ጥሎሽ ይጠየቃል ልዩነቱ እሱ ነው፤ ሁለተኛ ፍየል ድሮ ሁለት አሁን አምስት ስድስት ነው እሚጠየቁት ብዙ ነው አሁን፤ድሮ ልዩነቱ ጠላ ተጠምቆ ስንት ኩንታል እህል በቃ በጠላ ብቻ ሰው ድብልቅልቅ እስከሚል እስከሚሰክር ነበር አሁን ግን ጠላ

የለውም ጭፈራ ብቻ ነው፤ ሰው ወደ ቤቱ ቶሎ ይመለሳል ድሮ ሳምንት ተብሎ ነበር ድግስ አሁን የለም።

*እስቲ የሠርግ ግጥም ይንገሩኝ የሚዘፈነውን በወንዱ ቤት በሴቱ ቤት?*

ለወንዱ "አብሽሪያ አሪት" ይባላል፤ለሴት "አሩዛ" ይዘፈናል።

*ሰው ችግር ሲገጥመው እንዴት ነው የምትረዳዱት?*

እንከፋፈልም አንለያይም አሁን ለምሳሌ ሰው ታሞ ሊተኛ ይችላል፤ ታሞ ከተኛ ምግብ አብስለን እናመጣለታለን፤ ፍራንክ እናግዘዋለን እንዲታከም፤ ልጆቹ ሚስቶቹ እቤት ውስጥ የሚቸገሩ ከሆኑ እህል አካፍለን አምጥተን አስፈጭተን እንሰጣለን የሚቸገረውን ሰው ለመርዳት አብረን እንሠራለን። እኛ ልዩነት ቀይ ነው፣ ጥቁር ነው ፣ይሄ ከዚህ መጥቷል፣ ይሄ ከሩቅ አገር ነው፣ አናውቀውም፤ ይሄ ቤተሰብ የለውም ፣አንረዳውም፣ አናግዘውም፣ የሚባል በእኛ ባህል የለም። ሌላ ብሔረሰብ ከየትም ይምጣ ታሞ ከሆነ፣ ተቸግሮ ከሆነ፣ እናግዘዋለን፣ እንረዳዋለን እስከሚሻለው ድረስ ሰው መሆኑን ብቻ በማየት እንረዳዋለን ልዩነት የለም። አንድ ጎጃሜ መጥቶ ወደ አርባ ዓመት ከእኛ ጋር ኖሯል አሁን በርታ ሆኗል በቃ። አደም አብደላ ይባላል።

*እሺ መንሱር አንተም ሁለት ሚስት አለኝ ብለኸኛል ስንት ልጆች አሉህ?*

አምስት፤ አንድ ወንድ ከአንዷ አራት ከሌለዋ አንድ።

*ሁለት ሚስት ማስተዳደር ትችላለህ? እንዴት ሁለት አገባህ ?*

አዎ እችላለሁ፤እርሻ አርሳለሁ፤ ወርቅ እቆፍራለሁ፤ ልጆች ሲታመሙ በባህል መድሃኒት አክማቸዋለሁ ካልሆነም እዚያ ጤና ኬላ አለ እዚያ እወስዳቸዋለሁ። ወርቅ ቆፍሬ፣ እርሻ አርሼ፣ ልጆቼን እያሳደግሁ ነው።

*አንተ ዘንድ ለህክምና የሚመጡ ሌሎች ሰዎች አሉ እንዴ?*

እኔ ሂድና እንደዚህ ዓይነት አምጣ ብሎ ካዘዘኝ አባቴ ከጫካ ሄጄ አመጣለሁ፤ትንሽ እየደከመ ስለሆነ፤ አባቴ ስላለ ብዙ ለመስራት አልፈልግም ፡፡

***ዕድሜህ ስንት ነው?***

28 ላይ ነኝ፡፡ ***በስንት ዓመትህ አገባህ?***

7 ዓመት ይሆነኛል ካገባሁ፡፡ አዲሷን አምና ነው ያገባኋት፡፡ ***ሌላ ማግባት ታስባለህ ወይ?***

በቃኝ፤ አላገባም፡፡

***እስቲ ለቅሶ ሲሆን እንዴት ነው በእናንተ ባህል?***

በኛ ባህል ያው ሰው ሲሞት ይገነዝና አስፈለጊው ተከናውኖ መቃፍር ይቆፈርና ተወስዶ ይቀበራል፤ ያን ዘመድ የሞተበትን ለማስተዛዘን ሁሉም ሰው ተሰብስቦ በአንድ ቤት ይመጣሉ፤ በቃ ማዘን የለብህም ቀኑ ደርሶ ነው የሞተው ሁላችንም እኛ እንሄዳለን እንጂ እሱ አይመጣም፡፡ አይዞህ ብለን አንድ ሦስት ቀን አራት ቀን ቁጭ ብለን እዚያ ቤት እናፅናናለን፤ ከዚያ በኋላ ሁሉም ወደየቤቱ ይሄዳል፤ ከዚያ ደብዳቤ ይፃፋል፤ እገሌ ሞቷል ተብሎ ለየብሔረሰቡ ይላካል፤ ሰው ከተቀበረ በኋላ ሳይቀበርም ቢሆን ድረሱ ይባላል፤ ቅርብ የሆነው ከአራት ቀን በኋላ እንበተናለን እሩቅ የሆኑት እንደሰሙ እየመጡ ይደርሳሉ፡፡ ከዚያ እነሱም እየረሱ ይሄዳሉ፡፡

***ሴቶቹና ወንዶቹ በለቅሶ በሰርግ ያላቸው ግንኙነትና መረዳዳት እንዴት ነው?***

በኛ ባህል ሠርግ ከሆነ ያው ሚስት ይታጫል፤ ጥሎሽ ይከፈላል፤ የሠርጉ ድግስ ሲደርስ ቤተዘመድ ይሰበሰብና እስቲ ምን አዘጋጅተሃል? ምን ይቀርሃል? ምን ጎዶሎ አለህ? ምንድነው እምንሞላው? እኛ ምን አቅም አለን? ይባላል፡፡ ይሄን ይሄን አድርጌአለሁ ይሄ ይሄ ደግሞ ገና ይቀረኛል ይላል ከዚያ ሁላችንም ቤተሰብ የሆንን ሰዎች አቅማችን የሚፈቅደውን እናዋጣና ይህንን ይህንን እናደርጋለን ብለን ሥራውን ተከፋፍለን ሠርተን

ያ ልጅ እቤቱ እስከሚገባ ድረስ፤ ሥርግ ተደርጎ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የሚፈለገውን እገዛ እናግዛለን፡፡

ለቅሶ ከሆነ ሴቶች ውሃ በመቅዳት እንጨት በማምጣት ምግብ በማብሰል ሴቶች ናቸው የሚወጡት፤ ወንዶች ደግሞ ብር፣ ስኳር፣ ቅጠል ሻይ ያመጣሉ፤ ወንዶች ለቅሶ ሲደርሱ አንድ ስኳርና ሻይ ቅጠል ያመጣሉ፤ ወይም ቡና፣ ወይ አምስት ብር፣ አሥር ብር፣ ሃያ ብር የየአቅሙን ይሰጣል፤ ለለቅሶው ቦታ ከዚያ በኋላ ተሰብስበው ያስተዛዝናሉ፤ በሰባት ቀን ቁረአን ይቀራል፤ በዚያን ጊዜ ሻዩ፣ ምግቡ በደንብ ተዘጋጅቶ አካባቢው ሁሉ ይሰበሰባል ይስተናገደል፤ ይበላል፤ ይጠጣል፤ ከዚያ ይሰነባበታል፤ ለቅሶው አበቃ ማለት ነው፡፡ አርባ ቀን ሲሞላው አርባ ቀን ደርሷል ተብሎ ይጠራል፤ ሰደቃ ይደረጋል፤በቃ፡፡

ለምሳሌ ልጅ ከሆነ የሞተው ገና የተወለደ ልጅ ከሆነ ለቅሶ አይቀመጡም፤ ለዓለሙ አዲስ ነው፤ ሰው አያውቀውም፤ ከማህበረሰቡ ጋራ ያደረገው ግንኙነት የለም፤ እናት ብቻ በመውለዷ ወይ አባት ብቻ በመውለዱ ያዝናል፤ እነሱን ብቻ ማጽናናት ነው እንጂ ለቅሶ አይቀመጡም፡፡ ሃጢአት የለበትም ማለት ነው ልጁ፡፡

በወሊድ የሞተች ሴት ብዙ ሊለቀስላት አይገባም፤ ምክንያቱም ሰውነቷ ቁስል ነው ተብሎ ይታሰባል፤ ለቅሶ በበዛ ቁጥር ሰውነቷ ስለሚቆስል አታልቅሱ ይባላል፡፡

በመብረቅ ሰው ከሞተ ሰው በሚቀበርበት ቦታ አይቀበርም፤ ለብቻው ነው የሚቀበረው፤ በአዲስ ከፈንም አይጠቀለልም፤ በራሱ በለበሰው ልብስ ነው የሚከፈነው፤ ውሃ የበላውም ሰው እንዲሁ ነው፤ ምክንያቱም ድጋሚ ደስታ ተሰምቶት ሞቱ በድጋሚ ሰው በመብረቅ እንዳይሞት፣ ውሃ እንዳይበላው ነው እንጂ የሚቹ ችግር አይደለም፡፡

*ራሱን ያጠፋ ሰውስ?*

አሁን ለምሳሌ የታነቀ ሰው እግዚአብሔርን የከዳ፣ ሃይማኖተ ቢስ ተብሎ ይገመታል፡፡ አይለቀስለትም፤ አይታዘንለትም፤ራሱን ያጠፋ የሱን ነፍስ ያስቀመጠው እግዚአብሔር ነው እሱ ነው መውሰድ ያለበት፤ራሱ ግን እግዚአብሔር ሳይፈልገው ራሱ አደረገው

ተብሎ ስለሚገመት አይለቀስለትም፤ አይታዘንለትም፤በቃ ይቀበርና ቤተሰብ ብቻ ሊሰማው ይችላል ግን ማስተዛዘን የለም፤ "ራሱን ላጠፋ አትዘንለት" የሚል ተረት አለ።

***ማታ ማታ ከሥራ በኋላ ወይም ሥራ በማይበዛ ጊዜ ተረት የማውራት ባህል አላችሁ ወይ?***

ተረት ተረት የላም በረት እንደሚባለው

ኪንታሊያ - እንቆቅልሽ

የንዱኖ - ንገረኝ / ተናገር

አመደጅማ - የሆነ ነገር አውቃለሁ

እንዚኔ - ምን ታውቃለህ

"ሊዌ ሊዌ በቅ" - የሆነ ነገር ተጥመልምሎ ወደቀ ምንድነው?

እንጀራ ይላል፤ ካላወቀ እንደእናንተ ሀገር ስጠኝ እንደምትሉት ፈረስ ስጠኝ ይባላል።

***ይሄ በእኛ እንቆቅልሽ ነው የሚባለው በእናንተ ምን ይባላል?***

ኪንታሊያ

ፈረስ ስጠኝ ይባልና ሰጠሁህ ሲባል አንተ ስትጎተት እኔ በፈረስ ጋልቤ ጋልቤ……

እሽ አሁንስ ምን ታውቃለህ

እኔ ምንም አላውቅም

እሺ እንጀራ ማለት ነው።

ኪንታሊያ - እንቆቅልሽ

የንዱኖ - ንገረኝ/ ተናገር

አመደጅማ - የሆነ ነገር አውቃለሁ

እንዚኔ - ምን ታውቃለህ

- አገላብጠህ ደከመህ

ወዎንድ - ወፍራም የእንጩት ግንዲላ

ኪንታሊያ - እንቆቅልሽ

የንዱኖ - ንገረኝ/ ተናገር

አመደጅማ - የሆነ ነገር አውቃለሁ

እንዚኔ - ምን ታውቃለህ

አዚንተጉሙ ወደላቫሮ- እርሻ ውስጥ ጀራፍ ይዞ የሚያርስ

ኮንቱ - አተዛም

ሺጀኝ - አተዛም

ሚያ - አተዛም

ተም- አተዛም

ጌሪ - አተዛም

ሜሬሬ - አተዛም

ናና ሾላ

ናና ሞላ

እሳቸው የተጠየቁትን ፍየል፣ በግ፣ በሬ፣ላም ብዙ ነገር ጠሩ አላወቁም ከዚያ በኋላ ምላጭ ብሎ ነገራቸው፡፡

ኪንታሊያ - እንቆቅልሽ

የንዱኖ - ንገረኝ/ ተናገር

አመደጅማ - የሆነ ነገር አውቃለሁ

እንዚኔ - ምን ታውቃለህ

ተደረን ሸሚኖሞቫ- ሰፌድ ተንቀረቀበ

እሳቸው አላወቁም ቤት አሉ፣ውሻ አሉ፣ ዶሮ አሉ፣ አለዩም

ፈረስ ስጡኝ አላቸው ሰጡት ፈረስ ላይ ተቀምጬ እንደዚህ ተዝናንቼ አንተን ገደል ሰድጄ አምፈልገው ቦታ ደርሼ ስመለስ መልሱ

ቄንቄጽ - የሚበላ እንደተልባ የሚምለገለግ ገንፎ የሚበሉበት

ሲቲና፡- አባ ቤሎ ደከማቸው ይበቃናል እያሉ ነው፡፡

*እሺ በጣም አመሰግናለሁ በይልኝ፡፡*

አንቺ ልጃችን ነሽ ምስጋና አያስፈልግሽም፡፡ እቤቴ የመጣሽ ጊዜ ፍየል ሳላርድልሽ ቀረሁ ሌላ ጊዜ ስትመጪ አስቀድመሽ ንገሪኝ አደራ እያሉሽ ነው፡፡

*እሺ በይልኝ፡፡*

ኮይስ! ኮይስ! ተነስተው ለሰላት ለመተጣጠብ ወጡ፡፡

## ቃለ ምልልስ ሁለት

- **የመረጃ አቀባዮች ስም፡-**

1. አብዱረሂም ሀሰን አልበዴ፣ ***ዕድሜ***፡- ለመናገር አልፈቀዱም፣ በግምት 60 አካባቢ ይሆናሉ። ***ፆታ***፡- ወንድ ***ሥራ***፡- የግብርና ባለሙያ፣ 30 ዓመት በግብርና ባለሙያነት የሠሩ **የትምህርት ደረጃ** ፡- በግብርና ዲፕሎማ፣ **ብሔር**፡- በርታ

2. ሲቲና አደም፣ ***ዕድሜ***፡- 38፣ ***ፆታ***፡- ሴት፣ ***ሥራ***፡- ነጋዴ፣ **የት/ ደረጃ**፡- ዲፕሎማ በግብርና ኤክስቴንሽን፣ **ብሔር**፡- በርታ

3 ነፊሳ መሀመድ ***ዕድሜ***፡- 28፣ ***ፆታ***፡- ሴት፣ **የት/ ደረጃ**፡- የመጀመሪያ ድግሪ በቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ፣ ***ሥራ***፡- የወረዳው የባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ኃላፊ፣ **ብሔር**፡- በርታ

***መረጃዉ የተሰበሰበበት ቀን***፡- ሐምሌ 20 ቀን 2003 ዓ.ም ከ4፡00-6፡00፣ ***ቦታ***፡- በቤንሻንጉል ጉሙዝ ብ/ክ/ መንግሥት ሸርቆሌ ወረዳ ፀጥ ያለ ቦታ መርጠን ግራር ዛፍ ሥር።

***ቃለ ምልልሱ የተደረገው***፡- በአማርኛ ቋንቋ

***መረጃ ሰብሳቢ***፡- ስንቅነሽ አጣለ

***በቅድሚያ ስለበርታ ብሔረሰብ ባህል መረጃ ለመስጠት ስለተባበሩኝ በጣም አመሰግናለሁ። ስሞትን ዕድሜዎትን ሥራዎትን ጨምረው ስለበርታ ማህበረሰብ የሚያውቁትን ቢነግሩኝ።***

ስሜ አብዱራሂም ሀሰን አልበዬ እባላለሁ የግብርና ባለሙያ ነኝ አንድ 30 ዓመት በግብርና ሙያ ሠርቻለሁ። ትምህርት ደረጃዬ አሥራ ሁለት ሲደመር ሁለት ተመርቄአለሁ።

በርታ ብሔረሰብ ማህበራዊ ኑሮ አብሮ መኖርን በሚመለከት በጣም ሰው ወዳድ ነው፤ባህሪው እንዴት ነው ሰው ቀይ ይሁን ጥቁር፣ አጭር ይሁን ወፍራም፣ የእግዚአብሔር ሥራ ነው ስለዚህ እግዚአብሔር የፈጠረውን መጥላት፣ መግደል አስፈላጊ አይደለም። ዳኝነትን በሚመለከት ለምሳሌ ግጭት ቢፈጠር ወደ ዳኛ ፍርድ ቤትም አያዞቱሩም። ፍርድ ቤት ብዙ ጊዜአቸውን አያጠፉም እዚያው ነው የሚያለቀው በብሔረሰቡ በራሳቸው፤ ይቀመጣሉ  ሽማግሌዎች ይወሰኑና እርቅ ይወርዳል። እኔ በቅርብ የማውቀው በዚህ በደርግ ዘመን አንድ ጊዜ ኦሮሚያ የገባ የኛ ወረዳ አለቤጊ ወረዳ የሚባል፤ እዚያ ያሉና እዚህ የሚኖሩ የበርታ ሰዎች አሉ እና ዓመታዊ የዳኝነት ግምገማ ይደረግ ነበረ እና ስንት ፋይሎች አያችሁ? ስንት ተወሰነ? ስንት ወደዚህ ዓመት ተላለፈ? የሚል ነገር  ግምገማ ይካሄድ ነበርና ምንም ባዶ ነው እዚህ በኩል የመጣው በተለይ ወደ ሾርቆሌ፣አሶሳ፣ ባምባሲ ያለው ምንም ዜሮ ነው ምንም  ፋይል የለም፤ "ምንድናችሁ እናንተ? ውሸታችሁን ነው እንዴ? እናንተ አትሠሩም እንዴ? አትጣሉም?" ብለው ሰዎች ገረማቸው ከቤጊ 3ሺህ 4ሺህ ፋይል ሲቀርብ አንድ ወረዳ ላይ እዚህ ጋ ምንም ባዶ፤ አይ እኛ ችግር የለም ሳይሆን ችግራችንን እዚያው ነው እምንፈታው ይሄ በአገር ሽማግሌ ማለት አንድ እዚህ ሴንተር ላይ ካለ እዚያ ነው በአንድ ሰው ነው የሚዳኙት ይቅር ካለ ቀረ! እሚቀጣም ካለ እዚያው እንዲቀጣ፤ አረቦች ከገቡ በኋላ ደግሞ በሸሪያ ነው፤ መቶ ፐርሰንት በእስልምና በሚያዘው መሠረት ነው የሚፈፀመው።

የቆዩ የበርታ ብሔሮች ጋብቻ ከቤተሰብ ነው እሚጋቡ አብዛኛውን ጊዜ ከሩቅ አይጋቡም ከቤተሰብ ነው የአጎት ልጅ እንደዚህ ይጋባሉ፤ ሸሪያው በሚያዘው መሠረት ማለት ነው ያ ማለት ከሌላ ተከለከለ ማለት አይደለም፤ ግን ሰዎች ደስ የሚላቸው አባትና እናት እሚወስኑት ደስ የሚላቸው እንደዚያ ሲሆን ነው የእህቴን ልጅ ለልጄ የወንድሜን ልጅ እየተባበሉ ነው ጋብቻ የሚፈጸመው እና ሽማግሌ ይጠይቃል። አሁን አሁን ነው እንጂ

ልጅቷን ጠይቆ እንትን እሚባል ነገር የለም፤ አባትና እናት ወሳኝነት አላቸው አባቴ ካለ እናቴ ካለች ከእነሱ ቃል አልወጣም ወንዱም ሴቷም ማለት ነው እነሱ ይጠየቃሉ፤

***ሽማግሌ ስሄድ እንዴት እንደሆነ ምን ይዞ እንደሚሄድ እንዴት እንደሚጠይቅ ሥርዓቱን እስቲ በደንብ ይንገሩኝ?***

ሽማግሌዎች ሲሄዱ ምንም ይዘው ሄደው የሚባል ነገር ሌላ ቦታ ላይ ያለው ሳር ምናምን የሚባል የለም፤ይሄዳሉ አሰላማሊኩም ማሊኩም አሰላም እሚተዋወቁ ሰዎች ናቸው፤ ከሩቅም አይመጡም። ስለዚህ ነው የመጣነው ይቺን ልጅ ለወንድሜ ልጅ እሱም እራሱም እኮ ይሰጣል እኮ የእኔ ልጅ ለአንተ ብሎ ግን የሩቅ በሚሆንበት ሰዓት ሰዎች ይሄዳሉ። ቡና ይቀርባል ቡና የግድ ነው በቡና ላይ እኛ የመጣነው ለዚህ ለዚህ ነው ብለው ይገልፃሉ። ለአባቷ አባቷ እኔ እምወስነው ነገር የለኝም እሰበስባለሁ፤ሌሎች ሰዎች እጠራለሁ፤ይህቺ ልጅ የኔ ብቻ አይደለችም የብዙ ሰው ስለሆነች እነሱን ሰባስቤ የሚሉትን ነገር በቀጠሮ፣ቀጠሮ ይያዝና ይመለሳሉ፤ቀጠሮ ተይዞ በቀጠሮ ቀን እነዚያ በሙሉ ይሰበሰባሉ ይነጋገሩበታል፤ እሚሆን ከሆነ በተደረሰበት ውሳኔ ይሰጣል አንዳንድ ጊዜ ምንድነው እሚያረጉት ልጁ የሚያጨው ልጅ በነበረበት ባደገበት ጊዜ ውስጥ ተወልዶ እስከ አሥራ ምናምን አመት አሥራ ስምንት ሃያ ዓመት ድረስ እዚያው የኖረ ነው ያውቁታል። አንድ ተሳስቶ ወይ ተጋፍቶ ወይ ዝም ብሎ አንድ ቀን ያጠፋው ካለ ያስታውሳሉ፤ "አንድ ቀን ስሄድ በመንገድ ላይ ገፍቶኝ አለፈ፤እና ይቀጣለልኝ" ይላል ለዚህ ነው እሚሰበሰቡ፣ ይቀጣልኝ፤ አንዳንዶቹ ደግሞ "አንድ ቀን ገበያ ልኬው ወይ የሆነ ነገር እንደዚህ አልተላከልኝም"፤ እና ይነሳል ማንኛውም የማይረቡም ቢሆኑ ይነሳሉ፤ እሚረቡም ይነሳሉ መጨረሻ ላይ ይሰጣል። የተባለውም እንትን ይቀጣል፤ ከፈለገ መቶ ብር፣ ሃያ ብር፣ አሥር ብር እንደዚህም ይቀጣና ይወሰንለታል ማለት ነው።

እና ደረጃ አለው መጀመሪያ ሲሰጥ "አከል በረካ" ይባላል፤ እንግዲህ ክፍያ ይጀመራል ሴረሞኒ የሚደረገው ነገር አከል በረካ እሚባል ነገር አለ እቤት መከፍቻ ሲመጡ አንድ በግ ሊሆን ይችላል፣እንዳቅሙ ሚስት ፈላጊው አከል በረካ ይጠየቃል ቡና ይጠጣል

ይመረቅለታል፤ የመጀመሪያ በር መክፈቻ ነች እሷ ከዚያ በኋላ ያ አካል በረካ ከሆነ በኋላ የሚቀጥለው እንግዲህ ዋናው ጥሎሽ ይጣላል።

በፊት የነበረው ምንድነው ማር ይቀርባል፤ጨው ይመጣል፤ ማለት ለምግብና ለምን የሚሆን ነው ይሄ የተወሰነ ማሩም ይበጠበጥና በሳህን ተደርጎ ይጠጣል፤ብዙ ጊዜ በስኒ በስኒ በማንኪያ በማንኪያ ተደርጎ ይበሉታል፤ማር ይበላል በቃ ደስ ይላቸዋል ትልቅ ነገር ሆኖ ማለት ነው።

*ማር መጀመሪያ የሚቀርብበት ተምሳሌት ይኖረው ይሆን?*

እዚያ ላይ እኔ እንጃ ሥርዓቱ ነው በቃ የጋብቻ መክፈቻ በሚሆንበት ሰዓት ማር ማቅረብ ትክክል ስለሆነ ነው፤ ሌላ ነገር አይጠይቁም፤ ጠላ አይገባም ሌላ ነገር የሚመጣ ነገር የለም። ግን በዋናው ሠርግ ላይ ጠላ እሚጠቀሙም አሉ እና እንደዚያ ነው። እህል ይቀርባል፣ ፍየል፣በግም ይቀርባል።

**ሲቲና፡-**[52] ማለት ሸንኩርት፣ ዘይት፣ ሚጥሚጣ፣ስኳር፣ቡና፣ፍየል ይወሰንና ያንን ለዚያ ፍየል ሊያስበላ የሚችል የእህል ዓይነት ማስፈጫ ቁንቁጽ ሁሉ ይቀርባል፤ማባያ እነዚያ ሁሉ ይቀርቡና ቤተዘመድ አጎት፣አክስት፣ቤተሰብ፣ የእሱ፣የእሷ ቤተሰቦች ያው የአጎት የአክስት ልጆች ስለሆኑ ማለት ነው ሁሉም ይሰበሰቡና አንድ ቀን ብሉ ይባሉና ይበላሉ፤ከሠርግ በፊት ያው ተመርቆ ተሰጠው ማለት ነው። መክፈቻው ናት እቺ ከዚያን በኋላ የዛን ቀን ይቀመጡና ይቆርጣሉ፤ይህንን ልብስ ያመጣል ለእናት የሚመጣ ልብስ አለ፤ጣቃ ፣ለልጅቷ የሚቀርብ አለ፣ ለተሸከማት ለሞግዚት፣አንድ ቶብ ይዞ እንደሚመጣ ቃል ይገባል ያንን ሁሉ የዛን ቀን ይቆረጣል፤የድግስ ብር ይቆረጣል፤ ለድግስ ይሄን ያህል ገንዘብ ታመጣለህ ለድግስ ተብሎ ይሄን ያህል ፍየል ይሄን ያህል ዘይት፣ ይሄን ያህል ሽንኩርት፣ ይሄን ያህል በርበሬ፣ይሄን ያህል ጨው፣ይሄን ያህል ቡና፣ይሄን

[52] በዚህ ቃለ ምልልስ አባ አብዱራሂም ሲናገሩ የረሱትን ወይም የዘለሉትን ነገር ሲቲናና ነፊሳ ጣልቃ እየገቡ ያስረዱኝ ነበር ስለዚህ እነሱ ሲገቡ ስማቸውን በመጥቀስ አስቀምጨዋለሁ።

ያህል ሱኳር ይሄ ሰው ለሥርገኛው መጥቶ በልቶ ጠጥቶ የሚሄደው ማለት ነው ያቺን ይጨርሳል፤ ከጨረሰ በኋላ ደግሞ "አልፋ ተሃ" እሚባል አለ ያ አልፋ ተሃ ልጃችንን ሠጥተናል በቃ በፈለገው ጊዜ መውሰድ ይችላል በለው የሚወስኑ ናቸው፡፡

እሷ ደግሞ በቃ ኖርሽም አልኖርሽም ቤተዘመድ አሥር ሳንቲም ብትሆን ትደርስሻለች፤እሱ ልጁ ነው የሚያመጣው እንደገና ለሁለተኛ ጊዜ "አልፋ ተሃ" ማለት ነው ከመክፈቻው ቀጥሎ ሰጥተናል ብለው ከወሰኑ በኋላ የሚፀድቅበት ነው ሃምሳ ብርም ሊሆን ይችላል መቶ ብርም መቶ ሃምሳ ብርም ሊሆን ይችላል አቅሙ የፈቀደውን "አልፋ ተሃ" ብሎ ይሰጣል፤ ከዚያ በኋላ ያችን "አልፋ ተሃ" ሁሉም አክስቶችና ታላላቅ እህቶቿ ናቸው እሚካፋሉት እነዚህ ደግሞ ይህቺን የእገሌ ልጅ ያገባችው የመጣላት "አል ፈተሃ" ነው ተብሎ ቡና ካለ እዚያው ትጠጫለሽ፤ የመጣውን ነገር ከቀመስሽ ቀምሰሻል ካልቀመስሽ ግን በብር ተቀይሮ ባለሽበት አገር ይላክልሻል ለምን አዲስ አበባ አትሆኚም፣ይህቺ የእከሌ ልጅ ያገባችው አል ፋትሃ ነው ተብሎ አሥር ሳንቲምም ብትሆን ትደርስሻለች፡፡ ይቺ በባህሏ እሷ ናት ያለችው ከዚያ በኋላ ልጅቷ የዚያን ቀን ልብስ አምጥተው ያለብሷታል አንድ ልብስ ይልካል የእሱ ናት ለመባል ከዚያ ሁለት ሴቶች ይመጣሉ በቃ የእሱ ነው ተብሎ እሷ በዚያን ቀን የእሱ ልብስ የሱ እንግዲህ ቶብ አትለብስም በዚያን ጊዜ ይቺ ሻርብ፣ ድርያ፣ ጉርድ እንደዚህ ለልጃገረድ የሚሆን ነገር ይልካል፡፡ እሷን አጥበዋት ምን ብለው ትለብሳለች፤ በክብር መጀመሪያ እዚያው እቤቷ እያለች ያለብሷታል የዚያን ቀን ይበታተናሉ፤ በቃ እሱ ነው እሚከታተላት ማለት ነው ሥርጉ እስከሚደርስ ድረስ፡፡

*ቶብ ያገባች ሴት ብቻ ናት የምትለብሰው?*

አዎ በፊት እንደዚያ ነበር አሁን ግን ተቀይሯል፡፡ ራስ መሸፈን አሁን ኒካ አስራ ከጨረሰች በኋላ ነው ቶብ እንዳይወርድ የማይፈቀድላት፣ አሁን ልትገለጥ ትችላለች ክልክል አይደለም ግን አሁን ቤቷ ከገባች በኋላ ነው ግዴታ ቶብ መልበስ ቶብ ከሰውነቷ መውለቅ የሌለበት ሠርግ ተደርጎ ከሳምንት በኋላ ውጪ ካየች በኋላ ራቁት መሄድ አትችልም

በሻርብ በምናምን መሄድ አትችልም ያው ቶብ ነው መልበስ ያለባት ግን ምንድነው ያለው የእሱን ልብስ ስለመልበሷ ገና እዚያው ቤታቸው እያለች ያ ይደረጋል በቃ የእከሌ እጮኛ ናት ሰርጉ ደርሷል እየተባለ ቀን ይቆረጣል መቼ ድግስ እንደሚደገስ፣ለነዚያም ቤተሰብ ይነገራል እዚያም እዚህም ይደግሳሉ ወንድ ነው ወደ ሴቷ ቤት የሚመጣ፤ እዚያ ቤት አጠገብ ቤት ይሠራል እሷ ቤተሰቦች አጠገብ ጎጆ ይሠራልና ልክ የሠርጉ ቀን እሱ የሰራው ቤት ነው የምትሰጠው ልጅቷ ከዛ ለአንድ ሳምንት ያክል እሱ ጋራ እዚያ ትቆያለች፤ቀን ቀን ወደ ቤተሰቦቿ እየሄደች ማታ ማታ ነው የሚያመጧት  ከአራት ሰዓት በኋላ ለአንድ ሳምንት ያክል ከዚያ የሳምንቱ መጨረሻ ቀን በቃ ውጪ ወጣች ተብሎ ከራማ ተደርጎ ምን ተደርጎ እሱ ይሄድና ይዟት እናታቸው ቤት ይገባሉ፤እሷ እናት ቤት ይገባሉ ቤተኛ ሆነ ማለት ነው ይሄ ልጅ እንግዲህ የዚያን ቀን አንድ በግ ነገር ታርዶ እንደገና ይደገሳል፤በቃ ሰርጉ አለቀ ማለት ነው እሷም ባለትዳር ሆነች ቤት አደረገች ይባላል፡፡ ከዚያ ይኖራሉ ድሮ እንደዚህ ነው፡፡ ሳትወልድ አትሄድም ነበር ባሏ ቤት ልጅ ይዛ ነው እምትሄደው፤ አሁን እንደዚያ የለም አገባች በሳምንቷም ይዟት ሊሄድ ይችላል በፊት ግን ወልዳ አርግዛ ሊያቅበጠብጣት ይችላል፤ ባህሪ ሊቀየር ይችላል፤ እዚያ ወልዳ በአመቷ ልጅ ይዛ ነበር ወደዚያ ምትሄደው አሁን ግን ዛሬ አግብታ ነገም ይዟት ሊሄድ ይችላል፡፡ ዛሬውም ማታ ሊወስዳት ይችላል፡፡

ህግ እሚጠፋ ቀን በእኛ ባህል ማለት ነው እንግዲህ ዛሬ ሠርግ ተደርጓል ቤተሰብ ሁሉ አለ፤ ሁለት አሮጊት ሴቶች ይሰጣሉ፤ልጅቷ ቤት እነሱ እሷ ከመሄዷ በፊት አንድ ሜትር አቡጀዴ ይገዛና ይሸረጥላታል  በእናንተ ሙዳይ ነው የሚባለው በእኛ ሃራ ነው እሚባለው የደም ጨርቅ ማስቀመጫ እሱን ይዘው ይሄዱና ሁለቱ አሮጊቶች ቁጭ ይላሉ እቤት ውስጥ ልጅቷ ከመሄዷ በፊት…

*ተደብቀው ነው?*

ይታወቃል በቃ በባህል ይታወቃል፡፡ እነሱ ብቻ ናቸው ያንን ሁኔታ የሚከታተሉ ሌላው ይሄዳል፤ከዛ ልጁ እዚያው ቤት አለ ከዚያ ልጁን ልትመታው ትችላለች ልትተናኮለው

ትችላለች ተብሎ ይታሰባል ጉልበት ምናምን ሊኖር ይችላል ቤተሰብም ይጨነቃል ምን ሆና ይሆን እንዴት ስማችን ጠፋ ወይ ምንድነው ክብራችን በቃ የዚያን ቀን ማታ የሴቷ ቤተሰብ ጭንቀት ላይ ነው እሚሆነው፤ ከዚያ በኋላ ያ ሲፈፀም እነሱ እልል ይላሉ፤ ያችን ይዘው ይመጣሉ።

*ማለት እሚገናኙት እነሱ ባሉበት ነው?*

ባሉበት ነው! ክፍል እንደዚህ ጓዳ ነገር ይኖራል እዚህ በር ላይ ነው እሚቀመጡት ማየት አለባቸው።

**አባ ኢብራሂም፡-** ትርጉም አለው ማለት አንዳንድ እንትኖች እሚያጠፉ አሉ ያ ደም ላይታይ ይችላል በዚያ ላይ እኔ ድንግል ነኝ እሱ የራሱ ችግር ነው መአት ነገሮች አሉ እዚያ ጣጣ ውስጥ አንዳንዴ የሰው ባህሪም አይታወቅም ብዙ ብዙ ነገሮች ስለሚከሰቱ ለዚያ ምስክር ናቸው ሴቶቹ፤ ያ ሚስጢር ነው ሌላ ሰው አይሰማውም፤ ሴቶቹ ብቻ ናቸው ሀላፊነት ይወስዳሉ፤ ደስ ካላቸው ወዲያውኑ እልል ይላሉ ጭፈራው ይቀልጣል፤ እናት ትፎክራለች፤ እህቶች ይፎክራሉ ሁሉም ቤተሰብ ይፎክራል ልጃችን ጨዋ ናት ይባላል።

*ስለዚህ ድንግልና በማህበረሰቡ ክብር ነው ማለት ነው?*

በጣም ክብር ነው! በጣም! በጣም! በጣም! በጣም!

**ሲቲና፡-** *ያጣች ለት ግን ምናልባት ላይኖራት ይችላል ያጣች ለት የለም በቃ ወይ እሱም ወጥቶ ይሄዳል ወይም ይበሳጫል እነዚያ እናቶች ያረጋጋሉ፤ይህንንም ሃላፊነት አለባቸው ለምሳሌ ተበሳጭቶ አንድ ነገር እንዳያረጋት የሆነ ጥፋት እንዳይሠራ ፤ ብዙ ጊዜ የማይኖራት አትገኝም በባህሉ ከሌላት በቃ ጠፍታ አጎቷ ቤት የሆነ ነገር ማድረግ አለባት ከማግባቷ በፊት እንደዚያ እንዳለች እንዲታወቅ ይደረጋል እንደሌላት ታውቆ አንዱ ኒካ እንዲያስርላት ያ ሥርጉ ድግሱ እንዲቀር ተደርጎ ማለት ነው በውስጥ አዋቂነት በቃ ቤተሰቡ ብቻ አውቀውት ለከሌ ሰጥተናል ግን በሰው ፊት እንግዲህ እሷ እርኩስ ናት*

በቃ። የእኛን ባህል የእኛን ወግ ያጎደፈች ተብሎ በቃ ምንም ዓይነት ስህተት እንዲገኝ አይፈለግም በሴት ልጅ ላይ ማለት ነው። ይሄ አለ ካልሆነም ደግሞ እነደዚያ ደብቃ ወደዚያ ከሄደች ሥጋዋን ቁርጥ አድርገው ነው ያንን ደም አሳይተው ሚስጢሩን ሌላ ጊዜ የሚያወጡ አሮጊቶቹ ያ ነበረ በባህሉ በፊት አሁን አላት የላትም የሚል አሁን እየቀረ ነው ያው ስልጣኔው መጥቶ ተፈቃቅደሽ ተነጋገረሽ ተዋደሽ ትመጪያለሽ ያው ውስጣችሁን ራሳችሁ ታውቃላችሁ ማለት ነው ለሰዎቹ የሆነ እሚያረጉትን አርገው ያሳያሉ አለቀ ነገሩ ብዙ እንትን የለም ግን በዚያን ጊዜ የነበረው ባህል ይሄ ነው በቃ ምንም ዓይነት ስህተት ምንም ዓይነት ችግር እንዲገኝባት አይፈቀድም ያንም ከሆነ ደግሞ በቤተሰቦቿ ዘንድ እርኩስ ናት በቃ።

***ጥሩ፣ አሁን እንግዲህ አገባች ሄደች ወደ ባሏ ጋ ማለት ነው ትዳር መሠረቱ ከዚህ በኋላ እንግዲህ እርግዝና ይመጣል ፤ከዚህ በኋላ ወሊድ አለ፤ ከወሊድ በኋላ ደግ ሞ ያለ ነገር አለ እሱ ደግሞ እስቲ እንዴት ነው ንገሩኝ እስቲ?***

**አባ ኢብራሂም፡-** እኔ እማወቀውን ልናገርና ሲቲና የበለጠ ታብራራዋለች። ታረግዛለች ወይ እናቷ ቤት ሄዳ ትወልዳለች እዚህም ብትሆን ያለችው ወይ አክስቷ ወይ የአጎቷ ሚስት ስለሆነች ችግር የለውም የፈለገችበት ትወልዳለች ስትወልድ የግድ አርባ ቀን ትቆያለች ቤት ውስጥ ሳትወጣ በአርባ ቀን ሌላ ዝግጅት አለ ልጁ ራሱ ወደ ውጪ ይወጣል…

***ወንዱም ሴቱም እኩል ነው በአርባ ቀን?***

እኩል አይደለም እንዴ ሲቲና?

**ሲቲና፡-** እኩል ነው እዚህ ላይ ግን በሳምንቱ ስም ይሰጣል አሁን አቡዱራሂም ለመባል ልክ በተወለደ ሳምንት አባትየው ይደግሳል ለሴትም ለወንድም እኩል ነው እሚደገሰው መጀመሪያ ስትወልድ የመጀመሪያ ልጅ ከሆነ እናቷ ጋ እንድትወልድ ይመረጣል ይህቺም አክስቷ ናት እኮ ግን ምን ይሆናል ሴት የወለደችበት ወንዶች አይገቡም ፍራሽ ፣ አልጋ

አንዳንዱ ወንድ አርባ ቀን እስከሚሞላት አይገባም አንዳንዱ ደግሞ እዚያው ልጅ እያጠበም ምን እያለም ይቆያል በተፈጥሮአቸው አሁን ለምሳሌ ከወለደችበት ቤት ውሃ ቀድተው ቢሰጡት የሚያስታውከው አለ፤ አዕምሮው የማይቀበልለት አለ እዚያ የተሠራ ገንፎ ሻይ ቡና የማይጠጣ አለ ሦስት ወር እስከሚሞላቸውም የሚፀየፉ አሉ ሚስቶቻቸውን ማለት ነው አንዳንዱ ደግሞ እዚያው እየበላ እየጠጣ እያረሳት ደግሞ እሚኖር ደግሞ አለ ግን ምንድነው ያለው እዚያ ሴትየዋ በምትወልድ ጊዜ እናቷ ይኖራሉ ታርሳታለች፤ ልጅ ታጥብላታለች፤ ምን ትላለች፤ ያቺም አክስቷ ናት እኮ የባሏ እናትም አክስቷ ናት እምትሆነው ሩቅም አይደለችም ያው በጋራ ሆነውም የሚያርሱበት ጊዜ አለ አርባ ቀን ድረስ ትቆያለች እቤት ውስጥ አትወጣም።

አሁን ለምሳሌ ልጁ ብቻውን ተትቶ አይወጣም ሰይጣን እንትን ይለዋል ይባላል በእኛ ባህል። ሴትየዋ እስከ አሥራ አምስት ሃያ ቀን ውሃ እየተሞቀ ነው እምትታጠበው፣ በቀዝቃዛ ውሃ አትታጠብብም፤ ትታሻለች፤ እንደገና ደግሞ ከአራሷ ቤት አመድ አይወጣም፤ እሳት አይጫርም፤ ምክንያቱን ልጁ እትብቱ እስከሚቀረጥ እሳት እራሱ አይጠፋም፤ እሳት ሁል ጊዜ ይነዳል፤ ሌሊት ሁሉ ይነዳል፤ አመዱ ደግሞ እስከ አርባ ቀን አይወጣም፤ አርባ ቀን ሞልቷት ስትወጣ የልጁ ቅዘን እዚያ ሲነድ የነበረ አመድ ሲጠቀሙበት የነበረ ዕቃ የእሳት መጫሪያ የነበረ ልጁ እትብቱ እንዲደርቅ ተደርጎ በገል በምጣድ ስባሪ የሚያደርጉት አለ ይሄ የአጉሎ ፍሬ እሷ እሳት ላይ እንዲህ ታደርጊና እስከሚፈነዳ ድረስ እሷ ታሽታ ነው እትብቱ ላይ የምትቀባው እነሱ እነሱ ኮተቶች እቃዎች በሙሉ ልክ በአርባ ቀን ይሄድና ምን እንጨት ነው የሚመረጠው እንጨቱን አላውቀውም የግራር እንጨት ዓይነት እሱ ሥር ይጣላል፤ እሩቅ ነው እንግዲህ ሴቶች ተሸክመው ተሸክመው ቀጥ ብለው ይሄዱና ተሰልፈው እዚያ ይደፋሉ፤ እልል ይባላል፤ እሱን ጥለው ይመጡና እሷን ያጥቧታል፤ ንፁህ ልብስ ትለብስና ኩል ትኳልና በቃ ትሞሸራለች፤ እንግዲህ ልክ ሰላሳ ቀን ሲሞላት ጨሏ ትጀምራለች፤ ያ ጨሏ አንድ አስራ አምስት ቀን ለሃያ ቀን ልክ ሙሽራ ሆና ትወጣለች፤ ድግስ ይደገሳል፤ ይበላል፤

ይጠጣል፤ የዚያን ቀንም እሷ ወደ ውጪ ስትወጣ በቃ መጨረሻው ይሄ ይሆናል፤ አሁን ሞግዚት ይመጣላታል፡፡

*የልጁ ሰገራ እና አመዱ እስከ አርባ ቀን ውጪ የማይጣው ለምንድነው?*

ሲቲና፡- የልጁ ሠገራ ውጪ ከተጣለና ሰው ቢረግጠው ሆዱን ይቆርጠዋል ተብሎ ስለሚታሰብ ነው፤ ሠገራው እስከ አርባ ቀን እቤት ነው እሚሰበሰበው፤ እስከ አርባ ቀን አይወጣም፤ የልጁ እጣቢም አልጋ ሥር ነው እሚደፋው፤ መረገጥ የለበትም ሆዱን እንዳይቆርጠው ሴትየዋም ብቻዋን አትወጣም፤ ሽንት ቤት መሄድ ከፈለገች ሰው አጅቧት የጥላ መድሃኒት እጇ ላይ ታስሮ ነው ሥራ ሥር እጇ ላይ ይዛ ነው እምትወጣ እሱም በፀሐይ አትወጣም ወይ፤ጥዋት ወይ ማታ እንጂ ቀን አራስ አትወጣም በቃ እነዚህ እነዚህ የነበሩ ባህሎች ናቸው፡፡

ያቺ በሳምንቱ እምትደገስላት የስም መስጫ ቀን ለሴትም ለወንድም እኩል ነው ሰባት ቀን ነው ስም ሲሰጥም አባት ነው ስም የሚሰጠው አባት በሌለበት ወኪል ያስቀምጣል ለምሳሌ በአካል የለም ሌላ ቦታ ሄዷል ለሥራ ወይም የለም፤ ወይ የእሱን ታላቅ ወንድም ወይ የእሱን ታናሽ ወንድም እንጂ ማንም ሊሰይምለት አይችልም ራሱ ነው ስም የሚያወጣው ወይ አባቱ፤

*ሴቶች አያወጡም?*

አያወጡም ሴቶች በባህል አያወጡም፡፡

*ስም ሲያወጣ ከምን መነሻ ነው የሚያወጣው?*

በቃ ስም በእኛ ያጎት ያባቱ ስም በአባቴ እሰይማለሁ ካለ ለምሳሌ አባ አብዱራሂም ልጅ አለው ሀሰን አብዱራሂም ሀሰን ይባላል በአባቱ ስም መልሶ የሰየመው ማለት ነው፡፡ ወይ ወንድሙ ከመጽሐፍ ጋር የተያያዙ ስሞች ናቸው የሚሰጡት ሴቶችም እንደዚህ ናቸው፤ ስም ከጉብዝና ጋርም ይያያዛል፤ ሀሰን የሚባል ሰው ጎበዝ ከሆነ ልጁ ጎበዝ እንዲሆንለት

ሀሰን ሊለው ይችላል፤ ሴትም ከሆነች እንዲሁ። እና የእኛ ስም ድግግሞሽ ነው ብዙ ጊዜ፤

**አባ አብዱራሂም፡-** በስም አወጣጡ የልጅቷ ቤተሰቦችም ድርሻ አላቸው ሴት ልጅ ከሆነች በእናቴ ስም ይሰየምልኝ፤ በእናቴ ስም ነው እማስጠራት ብላ ከባሏ ጋራ ትስማማለች፤ ሦስት አራት ልጅ ከወለዱና ቤተሰብ በበዛ ቁጥር ከመጀመሪያው ውጪ ከቤተሰቡ ስም ሌላ የቁርዐን ስሞች ተፈልገው ይሰጣል፤ በሬድዮ ወይም ሲጠራ የሰሙትንም ሊሰይሙ ይችላሉ ጥሩ ከሆነ በቃ።

**ሲቲና፡-** አሁን ተቀይሯል ይሄ የለም አሁን ዓለማቀፉ ስሞች ገቡ እኮ እነ ሜሪ፣እነ ቢላደን እነ ኦባማ አሁን አለ እኛ ጋ በዕውነት!

*እሺ ድግሰዋ እንዴት ነች የስም ማውጫዋ?*

እንዳቅሙ ነው አሁን ለምሳሌ ሰውየው ፍየል ገዝቼ የልጄን ስም አወጣለሁ ቤቴ "ስሚያ" አለ ካለ ወንዶቹን ጠርቶ ይመጣል፤ ከዚያ በፊት ሴትየዋ በወለደች በሦስተኛው ቀን ወንዶች ብቻ ተጠርተው ውጪ እሚባላ አለ፤ ሴቶች አይጠሩም ያን ቀን። በአርባ ቀን ወንዶቹም ሴቶቹም ይጠራሉ። ድግሱ የሚሠራው ሁሉም ጎረቤት ተከፋፍሎት ነው ለድግሱም የሚሆነው ነገር ከየቤቱ ይመጣል ለስራው ሰዎች ይመደባሉ፤ ለምሳሌ ነፊሳና ሲቲና ይሄን ይስሩ ስንቅነሽና እንደዚህ ደግሞ ይሄኛውን ተብሎ ይመረጣል፤ ከዚያ በኋላ እነዚያ ሰዎች ሃላፊነት ወስደው ከቤታቸው የሚያስፈልገውን ይዘው ይመጣሉ፤ አንድ ክፍል ይሰጣቸዋል፤ እዚያ ይሠራሉ፤ አራሷ ቤት ምንም የሚገባ ነገር የለም ወይ እናቷ ወይ እህቶቿ ወይ ሌላ ሄደሽ ጠይቀሽ ትወጫለሽ በቃ ስራው ግን የሚሠራው ሌላ ቦታ ነው፤ እሷም የበሰለ ነው እሚመጣላት።

**አባ አብዱራሂም፡-** አሁን ለምሳሌ ምንድነው ወጪ በግል የለም በባህሉ ለምሳሌ ለሠርግ እህል ይመጣል፤ ጥሬው ነው እሚመጣው ቀጥታ ለአካባቢው ይበተናል፤ ፈጭተው እንጀራውን ጋግረው፣ ገንፎውን ሠርተው፣ ይዘው ይመጣሉ፤ ይሄ ነው የቆየ ባህሉ

ወፍጮ በሌለ ጊዜ ለአንድ ሰው ስለሚከብድ ተከፋፍለው በመውሰድ ይፈጩታል፤ እህል በሚከፋፈልበት ጊዜ ጭፈራ አለ እህሉ ከተከፋፈለ ጀምሮ የሠርጉ ጭፈራም ይጀመራል ማለት ነው፤ በሻማ ነው እሚወስዱት በሰከንድ ሁለት ኩንታል ሦስት ኩንታል ይበተናል።

*እስቲ ስለግዝረት ንገሩኝ በበርታ እንዴት ነው እሚከናወነው?*

**አባ አብዱራሂም፡-** ሁላችንም በዚህ ነገር ውስጥ አልፈናል፤እኔ አሁን አያቴ እዚህ ገገር ነበሩ እና እኔ በምገረዝበት ሰዓት ትልቅ ዳስ ነው፤ የአሁኑ የማንም ሀብታም ሠርግ እንደዚህ አይደለም በጣም ትላልቅ ዳሶች አሉ፤ በሬ ይታረዳል፤ ነጋሪት ይጎሰማል፤ በቃ ጭፈራው ሦስት ቀን አራት ቀን እስከ ሳምንት ይጨፈራል፤ ***የስንት ዓመት ልጅ ሆነው ነው?*** ስድስት ዓመቴ ልጆች ነን። ማልቀስ ጥሩ አይደለም ካለቀሰ ፈሪ ነው የሚባለው ስለዚህ እኔ ሁሉን ነገር ችዬ ጥርሴን ነክሼ ካሳለፍኩኝ ሽልማቴ በጣም ብዙ ነው በጣም እሸለማለሁ በቃ ሁሉም እየመጣ አምበሳ እኔን የሚተካኝ እሱ ነው ከብት እሚሰጠኝ አለ፤ብር እሚሰጠኝ አለ ብዙ ነገር አገኛለሁ እንክብካቤ ይደረግለኛል፤ ግዝረቱ በቡድን ነው የአካባቢ ልጆች ይሰበሰባሉ፤ ያአጎቴ ልጆች ካሉ በአንድ ቦታ ላይ ብዙ ሆነን ልንገረዝ እንችላለን ይሄ ድግስ አለው ድሮ እንግዲህ ፤ ሴቶቹም እንደዚሁ ናቸው በጣም ትልቅ አምስት ስድስት የአንድ ቤተሰብ አንድ ላይ ሆነው ይገረዛሉ ትልቅ ሠርግ ነው እሚመስለው እንጂ ግርዛት አይደለም እኔ እማስታውሰው ማለት ነው፤አሁን ይሄ ነገር እየጠፋ ነው እንደውም ሰው ሳይሰማ፤ አንዳንዶች ቦታ ላይ ጠፍቷል በተለይ የሴቶቹ ሌሎች ደግሞ የማያምኑበት ውስጥ ለውስጥ ያደርጋሉ፤ዛሬ ስብሰባ ውለው ማታ እሚያስገርዙም አሉ። ይቅር የሚባለውን ነገር ተቃውሞው በጣም ትልቅ ነው፤ቁርአን አያዝም የሴቶቹን ግን በባህሉ ስለተለመደ ይደረጋል፤

*እስቲ ሲቲና ስለ ግዝረትሽ ጊዜ ንገሪኝ አስታውሺና?*

**ሲቲና፡-** የእኔ ጊዜ አርባ ሁለት ሴቶች ሁነን ነው የተገረዝነው፤እኔ የመጨረሻዋ ትንሽ ነኝ አርባ ሁለት ሴት ማለት እንግዲህ በጣም ብዙ ነው እንግዲህ ዳስ ተጥሎ አልጋሽ

ይመጣል እናትሽ ትመጣለች በቃ ተሰብስበሽ ልብስ ይገዛልሻል፤እንደሙሽራ ሂና ይደረግልሻል፤ በቃ ጎበዝ እንደዚህ ግዝረት ሊደረግ ነው እዚያ ሰፈር ተብሎ ህዝብ ይሰበሰባል፤ ዙምባራው፣ጭፈራው፣ በቃ ሶስት ቀንና አራት ቀን ጠላው እዚያው ጠላ ይሰጣቸዋል፤ የሚጨፍሩ ሰዎች እንግዲህ እኛ ግቢ እማይሰራ ቢሆንም እዚያ ጠጥተው ሰክረው እንዲጨፍሩ ይፈለጋል፤ የእከሌ ቤተሰቦች ግርዛት ነገ ሊፈፀም ነው ተብሎ ገራዣዋ በበቅሎ ነው እምትመጣው በቅሎ ተሞሽራ ተሽልማ በቃ ጠቅላላ ነጭ በነጭ ለብሳ ሰው በብዛት ሆኖ ሄዶ ያመጣታል እሷ እንግዲህ ይሄ እሚገረዝበት በሙዳይ ተደርጎ ነው እሚመጣው፤ እኔ ካደግሁ በኋላም የእኔ ዘመድ ነበረች ገራዥ እና ብዙ ቦታ ይዛኝ ትሄዳለች፤ ብዙ ቦታ ተጠርታ ስትሄድ ያለው ክብር ሌላ ነው፤ ዶሮ ብቻ ነው እምትበላው፤ ሳምንት ሙሉ ልጆቹ እስከሚሻላቸው ማለት ነው፤ እዚያው ሆና ይሄን ቀቡ፤ ይሄን አድርጉ የባህሉ ይሄ የሚፈጨው ጥላሽቱ ምኑ አይቀርም እና ጥሩ ነበረ በዚያን ጊዜ ይሄን ያህል ይከብድ ነበር መኣት ወጪ ነው የሚወጣው፤ ግን ሀይማኖታዊ አይደለም፤ በቃ ሱና ነው በኪዳን አይፈቀድም ግዝረት ግን ሰዎች ያልተገረዘች እቃ ጥጨርሳለች፤ እምታቦካው እምትጋግረው አይበረክትም፤ ቤት ውስጥ አርፋ አትቀመጥም፤ ትባልጋለች፤፤ ዱርዬ ትሆናለች ለእሱ አትሰማም ፤ ለሶላት አይመቿም አባባሎች ናቸው እንግዲህ ያልተገረዘች ነጃሳ ናት ዓይነት ተብሎ ይታሰባል፤ ስለዚህ ተገረዘች መባል በራሱ ክብር ነበረው በዚያን ጊዜ፤ በቃ በራሱ የእከሌ ልጆች ተገረዙ ወንዶችም ሴቶችም የአንድ ቤተሰብ ሰዎች አንድ ላይ ተሰብስበው ነው እሚገረዙት፤ ለወንዶቹ አንድ ዳስ ለሴቶቹ ሌላ ዳስ ይሰራና ሰውየውም እንደዚሁ በዚሁ ዓይነት ሁኔታ ነው የሚመጣው ለእያንዳንዱ የሚከፈል ገንዘብ አለ ዶሮ ልትሰጪ ትችያለሽ፤ በዚህ ዓይነት በቡድን ነበር የሚደረገው አሁን ግን ያው ትምህርቱም ያው አንዳንድ የተወሰኑ ሰዎች የተቀበሉ አሉ፤ እዚያው ስብሰባ ውለው መጥተው ልጅቷ ገና ሳታድግ ነው አሁን ገና ልክ ሳምንት ሳይሆናት ወይም አሥር ቀን፣ ወይም አንድ ወር ሳይሞላት ወዲያው ነው እሚያስገርዝዋት፡፡

በፊት ትልልቅ እስኪሆኑ የሚቆዩት አንድ ወጪውን በአንዴ ለማውጣት፣ ሁለት ቤተሰቡ በሙሉ እንግዲህ ሀብታሙም ያለውም የሌለውም ቤተሰቡ በሙሉ ተሰብስቦ አንድ ላይ በአንድ ለማድረግ ነው፤ ያንን አማራጭ ለመጠቀም ነው። ሦስተኛ ምን አለ ሁሉም ሰው ተሳትፎ እንዲያደርግ ነው፤ በዓመት እህል ተከምሮ፣ ተሰብስቦ ከገባ በኋላ ዝናብ በማይኖርበት ትምህርት ቤት በመሃል በሚዘጋበት ጥር ላይ ያችን ጠብቀው ነው ያንን ድግስ እሚደግሱት ለምን ነፃ ናቸው ልጆቹ እዚያው ይገኛሉ፤ እርሻ የለም በቃ ቢሆኑም ወርቅ ቦታ ነው የሚሆኑት እሱም ለአንድ ሳምንት ቢቀር ምንም ችግር የለውም፤ አራተኛ ሰው ወደ ሱዳን አይጠፋም በበጋ፤ በክረምት አካባቢ ነው ሰው ለሥራ ወደ ሱዳን የሚሄደው ለድግስ የሚሆን እህል አለ፤ በጋ ስለሆነ ገንዘብ አይቸግርም፤ ሮጥ ብለሽ ሄደሽ የሆነ ቦታ ብትቆፍሪ ወርቅ አታጪም፤ እህልም ቤት አታጪም፤ ፍየሎችም በክረምት ይወልዱና ለዚያን ጊዜ ይደርሳሉ።

ስለዚህ ለመብላት ለመጠጣት ዝግጁ በሆነ ጊዜ ነው እንጂ ክረምት ላይ ግዝረት አይፈቀድም። ለምን ላይድን ይችላል ቁስል ተብሎ ይታሰባል፤ የሚያስታምማቸው ሰው አይገኝም ሶስተኛ የሚደረገው ውጪ ነው ቤት አይገባም እንደውም ወደ ቤትሽ ልትመጪ ስትይ እኮ ዶሮ ታርዶ ግንባርሽን ደም አስነክተውሽ ነው እንደገና ቤት እምታይው፤ ተገርዘሽ መጥተሽ እኮ ዝም ብለሽ ቤት አትገቢም፤ ከዳሱ ወደ ቤትም ለመምጣት ይደገሳል። አሁን ዳስ ውስጥ ቆየሽ አንድ ሳምንት በሚቀጥለው ሳምንት ቤት እሚገባበት ቀን ነው ይባልና አንዳንዶቹ እትን ያደርጋሉ፤ ቤታቸውን ያዘጋጃሉ፤፤ ዶሮ እሚያርድ ሰው ይኖራል ሥጋ እሚገዛ ሰው ሊኖር ይችላል፤ እዚያም እራሱ ሥጋ ታርዶ ቅርጫ ይካፈላሉ፤ በቃ ወደቤቱ ይዞ ይሄዳል። ከዚያ ልጅቷ ወደ ቤቷ ትሄዳለች፤ ወንድምሽም ተገርዞ ከሆነ ተለያይተሽ ነው የከረምሽው አሁን አንድ ላይ ትገባላችሁ በአንድ ላይ ይበላል።

ሌላ ምንድነው በእኛ ያልገለፅነው ባልና ሚስት አብረው አይበሉም ቀርበው አይበሉም። ወንዱ አልከለዋ አልመረፋ የሚባለው በቀደም እነወንድዬ የተቀመጡበት እኛ ሠፈር እዚያ ነው እሚበሉት ወንዶቹ። የአካባቢው ወንድ በሙሉ ተሰብስቦ ትንሽ ልጅም ቢሆን

ቤት ውስጥ አይበላም፤ሁሌም። ምግብ እንግዲህ ሥጋም ሊሆን ይችላል፤ ዶሮም ሊሆን ይችላል፤ ገንፎም ሊሆን ይችላል፤ እንጀራም ሊሆን ይችላል፤ ተሠርቶ አሁን ለምሳሌ ጧት ተነሳች ቡና ታፈላለች፤ ቁርስ ትሠራለች፤ ያንን ቁርስ ለወንዱ ተቆርሶ ይሄድለታል ወደዚያ። ቡናው ጋር ማለት ነው ለራሷ አንድ ስኒ ትቀዳና ወይም ሄዶ ሲመለስ ምናልባት ላይበቃ ይችላል ትልና ትልካለች ይሄዳል እነ አቡድልናስርን የሚያክሉ ልጆች ወንዶች ይወስዳሉ፤ ያንን ቡና ይቀዳል ልጁ ጨርሶ ያመጣል፤ ሁለተኛና ሦስተኛ ይፈላል፤ አሁንም ያደርሳል ልጁ ምሳ ሰዓት ይደርሳል፤ እሷ ምሳዋን ሠርታ ሁሉን ነገር ታደርግና ለምሳሌ ወይ የእሱ እናት ወይ የእሷ እናት ወይ እህቶቿ ወይ የእሱ እህቶች እንግዲህ ጎረቤታሞች ናቸው አብዛኛው ጊዜ ምሳ ተሰርቶ ለሴቶቹ እዚህ ለብቻ ይቀመጣል፤ ለወንዶቹም ለብቻ ይቀመጣል፤ ወጣቸውም እንደዚሁ ለየብቻ ለወንዶቹ እዚያ ይልካሉ፡፤ ከዚያ የሴቶቹ እዚህ ጋ ይጠራሩና ትንንሽ ሴቶች እነዚያ ያየሻቸው እነ ሚሚ እነ እዱና እነሱ ደሞ እናታቸው ጋ እዚህ ተሰብስበው ይበላሉ። ወንዶቹ እዚያ ይበላሉ፤ ከዛ ይለያያሉ ማለት ነው። ሌላ ቤትም እንደዚሁ ይሠራል እንደዚሁ ተሰብስበው ይበላሉ ወንዶቹ ግን በጋራ ማለት ነው አንድ ቦታ ነው የሚበሉት አንድ አልከለዋ ነው ያላቸው አንድ አልመረፋ ስር ተሰብስበው ነው እሚበሉት የጠፋ ሰው የታመመ ካልሆነ ወይ ሌላ ቦታ ሂዶ ካልሆነ በስተቀር አይለያዩም።

ሰዓት ሲደርስ እዚያ ይሄዳል ኖረውም አልኖረውም ነው፤ ግን አሁን ለምሳሌ ሀብታም ይኖራል ደሀ ይኖራል እሱ ቤት ሥጋ ነው እኔ ቤት ሽሮ ነው አይደለም የእሱን ቤት ሥጋ በልቼ የኔም ሽሮ ይበላል። እዚያ ቀርቦ አብረው ነው እሚበሉት ያቺም ሴቶች እንደዛ አይለያዩም ቡናም ሲፈላ እንደዛ፣ ሻይም ሲፈላ እንደዛ እኔ ሻይ የለኝም ቤቴ አሁን ስኳር አልገዛሁም ስለዚህ ስኳር ስላልገዛሁ ዛሬ እዚያ ያለው ከእኔ ጋራ እሚበሉ ሰዎች ጋር አልሄድም ማለት የለም። በቃ ዝም ብዬ ሄጄ ቁጭ እላለሁ፤ እንግዳም ከመጣ አሁን ለምሳሌ እንግዳ መጥቶ አርፏል አይደለም የሆነ ቦታ ላይ ተሰብስቦ እዚያ እንግዳ ወዳለበት ይኬዳል።

*በቀደም እኛ ጋ እንደመጡት?*

አዎ! በቃ አይተሻል አይደለም ተሰብስበው ወደ እኛ መጡ ሴቶቹ፤ ውሃቸውን ያላቸውን ይዘው ይመጣሉ፤ኖረም  አልኖረም ያላቸውን ቤት ያፈራውን ይዘው ይመጣሉ እንጂ እከሌ ቤት በግ ታርዷል ስለዚህ እኔ ሄጄ አልበላም አይባልም። ለየት ያለው ባህል እሱ ነው።

***ስለዚህ ቤቱ ስለሌለው ምሳውን ሳይበላ ወይ እራቱን ሳይበላ የሚውል ሰው የለም ማለት ነው?*** የለም ስለሌለው ቤት ውስጥ? የለም እኔ ቤት ካለ መጥቶ ይበላል ወይ ከሌለኝ እኔ አሁን አስባለሁ እንደማይኖራት እንግዲህ ወይ ቤቱ ጭስ አይታይም፣ ወይ ዝም ብሎ እንግዲህ እንገናኛለን፤ ወይ በወንዝ፣ ወይ በእንጨት እንገናኛለን አይደለም? ቤቷ ምንም ነገር እንደሌለ ነግራኛለች፤ እቤት ያለውን እኔ ቆርሼ እልክላታለሁ[53] ለልጆች ስጪ እንደዚህ ብዬ ወይ ዱቄት ካለኝ ማዳበሪያ ውስጥ ነይ ዱቄት አለ ውሰጂ ስታስፈጪ እወስዳለሁ ብዬ እልክላታለሁ።

**አባ አብዱራሂም፡-** እንደውም ይሄ ባህል ለእኛ ወደ ኋላ መቅረት ምክንያት ነው የሚባልበት ሁኔታ አለ። ምክንያቱም አሁን አንቺ ዝም ብለሽ ዓመቱን ሙሉ ምንም ሳትሰሪ መኖር ትችያለሽ፤ ከአልከለዋ አልከልዋ አሰላማሊኩም ብለሽ ከሄድሽ 30 ሰው ይመጣል እዚያ እንደሰውየዉ ሁኔታ እንደታዋቂነቱና አንጋፋነቱ አልከለዋ ካለ ሰዎች እዚያ ይሰበሰባሉ፤ እኔ አሁን ያንን እያየሁ ከመጣሁ የመጣውን ሁሉ መመገብ እችላለሁ እና አንድ በጣም አልምጥ የሆነ ሰው ዓመቱን ሙሉ ሊበላ ይችላል እየዞረ ቤንሻንጉል ውስጥ፤ከዚህ ጀምሮ በቃ ምንም ሳይሠራ ይኖራል።

እንግዳ ደግሞ ይሻማሉ አንድ ቀን መንጌ ሄድኩኝ መንጌ ስሄድ ረመዳን ነበረ አጎቴ ና አለኝ ሄድኩኝ አልከልዋ 30 አርባ ሰው አለ ሄድኩኝ ሜዳ ላይ ነው፤ እኔ ስሄድ ነገር

---

[53] የሲቲና አክስት እኔን ድንች እንድገዛላቸው ጠይቀውኝ ሲወስዱ እንደራሳቸው ቤተሰብ ስላዩኝ አላመሰገኑኝም እንኳ!

ይነሳል እንግዳዬ መጣ ብሎ አጎቴ ሲነግራቸው ለምንድነው ያልነገርከን? አንተ ወንድም ከእኛ በላይ የምትበልጠን ለምንድነው? አንተ እንግዳ ይዘህ ትመጣለህ አትነግረንም? እና ከመጥላት ሳይሆን እንግዳ ከመውደድ ያኔ እኔ ተሳስቷል እሱ እኔ በራሴ ነው የመጣሁት አልኳቸው ለማስታረቅ እኔ በራሴ መጣሁ እንጂ እሱ አልጠራኝም፡፡

***ሲቲና፡-*** *ቀድመን ብትነግረን እንዘጋጅ ነበር ልክ አባ ቤሎ አንቺን ይገኘ ስሄድ እንዳሉት ዝም ብለሽ ይዘሻት መጣሽ መዘጋጀት ነበረብኝ እንዳሉት፡፡*

**አባ አብዱራሂም፡-** እና ይሄ የተለመደ ነው  ከሱዳን ሳይቀር ሰው ቢመጣ የት ነው የአባ አብዱራሂም ቤት ብሎ ቀጥታ ይመጣል፡፡ ምንም ችግር የለም ሲመጣ እኔ ባልኖርም አል ከለዋው አለ ዕቃውን አውርዶ፣ አልጋ አለ፣ ፍራሽ አለ፣ ገብቶ እዚያ እየተስተናገደ ይጠብቀኛል፡፡ ቤተሰቦቼም ወዲያውኑ እንግዳው እንደመጣ ወዲያው ቡና ውሃ ይሰጣሉ፡፡ አይጠብቁኝም፡፡ እንደዚህ ካላስተናገደች ሴትየዋ ብቁ አይደለችም፤ ትፈታለች፤ እንግዳ ካላስተናገደች፤ አለሁኝ የለሁም እኔን ስሜን ጠርቶ የሚመጣ ካዲሳባ ይምጣ፣ ከየት ከመጣ በፈለገበት ሰዓት መስተናገድ አለበት፡፡

እና የእኛ ባህል እንዲህ ነው ጦም የሚያድር ብቻውን የሚበላ የለም ነውር ነው፡፡ ወንዶች አሁን እሷ ቅድም እንዳለችው ወንዶች ለብቻ ካባቶቻቸው ጋር ሴቶች ለብቻ ከእናቶቻቸው ጋር እንደ ጠንካራ ጎን ነው እሚያዩት፡፡ ምንድነው ወንድ ልጅ ሰባት ዓመት ከሞላው ወይም ጥርሱን ከሸረፈ በኋላ አባቱን ሊተካ የሚችል ነው ተብሎ ነው እሚታሰበው፤ እና ሁሉን ነገር መለማመድ አለበት፡፡ ተመልሶ ከእናቱ ስር እማማ እራበኝ እያለ ሳህን የሚጠርግ ከሆነ አይረባም ልጁ ነው የሚባለው፡፡ ያድጋል ግን አይረባም ነገ አይረባም ይባላል፡፡ እናትም ይሄን ስለምታውቅ ልጇ እንዲሰደብ አትፈልግም ሂድ ወደ ወንዶች ትላለች ፡፡

***አሁን ወንዱ ለትዳርና ለሃላፊነት በቃ እሚባለው የዕድሜ ጊዜ አለ አሁን በአንዳንድ ባህል የሚካሄዱ አንዳንድ ሥርዓቶች አሉ እንደግዝረቱ እንደእናንተ ማለት ነው***

*ከአንደኛው ዕድሜ እርከን ወደሌላው ለመሸጋገር የራሱ ሥርዓት አለው በበርታስ የሚከናወን ነገር ወይም እሚጠበቅበት ግዴታ አለ ወይ?*

**አባ አብዱራሂም፡-** ይሄን በኋላ በጥናትሽ ውስጥ የምትደርሽባቸው ብዙ ነገሮች ይኖራሉ፤ አሁን ፍንጭ ነው እምሰጥሽ። አሁን እዚህ ጋ ምንድነው ልክ ማደግ ሲጀምር ልጁ ጥርሱን እንደሰበረ የግድ ቁርዓን መማር አለበት። ከቻለ ማለት ነው ቁርዓን ለመጨረስ ሁለት ዓመት፣ ሦስት ዓመት፣ አሥር ዓመት ሊፈጅበት ይችላል በቅርብ እሚያስተምር ከሌለም እሩቅ ሀገር ሊሄድ ይችላል ለመማር ከዚህ እንደ ነጆ፣ ወለጋ፣ ለቀምት ከዚህ እንደ ሱዳን፣ ሩቅ ቦታ ሊሄድ ይችላል እዚያ እንጨት እየተሸከመ፣ ውሃ እየቀዳ፣ ማገዶ እየሰበሰበ፣ ማታ ማታ ማገዶ እያነደዱ ነው ሻማ ምናምን የለም፤ እና እንደዛ እየሆነ ይለማመዳል። ይሄ አንዱ ልጁን መፈተሻ ነው። ያንን ተቋቁሞ፣ ችግሩን ተሸክሞ ያንን ከቻለ አንደኛ ረሃብን ጥሎ ከመጣ አልቻለም ማለት ነው። ቆሎ ቆርጥሞ ሁሉን ነገር ችሎ ያንን ካሸነፈ አንድ ቁርዓኑን ከጨረሰ ማለት ነው አንድ ምልክት ነው ችሏል።

ሌላው ደግሞ ገንዘብ ይሰጠዋል፤ ንግድ ያለማምደዋል፤ ነጋዴ የሆነ ከሆነ የሆነ ዶሮ ግዛ ሽጥ ይለዋል። ይሄ ልጅ የራሱን ገንዘብ ሰርቶ ወይ ለራሱ ወይ ለአባቱ ንግድ ሲያገኝና የራሱን ንብረት ማፍራት ከጀመረ ራሱን ችሏል ይባላል። በዚህ ጊዜ እንግዲህ ብዙ ልጆች ኖረው ለሀላፊነት የሚበቃ ትልቁ ሊሆን ይችላል፤ የመጨረሻው ልጅ ሊሆን ይችላል፤ እንደ ጥንካሬአቸው ነው። ትልቁ ሞኛ ሞኝ ከሆነና ትንሹ ያንን ነገር ካሟላ አባት ይሄ የትም ቦታ ብሄድ እሱ ካለ ግቢዬ አይደፈርም ብሎ ተስፋ ይጥልበታል። ከዚያ ሁሉን ነገር ሚስጥራዊ ነገሮች በሙሉ ካሉ፣ ሰነዶች ካሉ፣ መሣሪያም ካለ እነዚህ በሙሉ ይሄ ነው ብሎ ያስቀምጣል። በልጁ ችግርን መቻልና ነገሮችን ደግሞ በቃ ብቃት ብቃቱን የማሳየት በሚያደርጋቸው ነገሮች አባቱን ተክቶ አካባቢው ራሱ ዕውቅናና ምስክርነት ይሰጣል። ከልጆችህ ሁሉ ይሄኛው ነው ይላል። አጎቱ ራሱ ከአንተ ልጆች ይሄኛው ነው ለእኛ የሚሆን ይላል። ልጁም በዚያ እየተገነባ ይሄዳል ከዘያ በሀዋላ አንድ አደጋ ወይም ችግር ቢመጣ እሱ ነው እሚወከለው አረፍኩኝ ይላል አባት ከዚያ በኋላ እንዲህ ዓይነት ልጅ እስከሚገኝ ድረስ እሱ ራሱ ነው ሀላፊነቱን የሚመራው ዕድሜውም

ሄዶ ማለት ነው። ያ ልጅ ከተገኘ አላሃምዲሊላ አላህ ሰጥቶኛል ለማንኛውም ነገር እሱን ጠይቁት ለንግዱም ለእርሻውም ይላል። እና ልጁ ከሰባት ዓመት ጀምሮ ነው ፈተና ውስጥ የሚገባ አቅም እንዲፈጥር።

***ቅድም በመጠኑ አንስተናል ይሄ ባህላዊ የሽምግልና ሥርዓትን በተመለከተ ቅድም እንደነገሩኝ ብዙ ክስ ወደ ፍርድ ቤት የሚሄድ በማህበረሰቡ አይታወቅም፤ በሽማግሌዎች ይፈታል ግጭቶች ደግሞ የተለያዩ ናቸው ለምሳሌ በግጭት የሰው ነፍስ ቢጠፋ እንዴት ይሸመገላል?***

**አባ አብዱራሂም፡-** እኔ አሁን በራሴ ልምድ ማለት ነው እዚህ የተገዳደሉ አስታርቄ አውቃለሁ። እና ያያራ እሚባል ቦታ አለ እዚያ ወጣቶች ናቸው፤ ተጣሉ፣፤ አንደኛው ሞተ ዘመዳሞች ናቸው። አንደኛው ወደዢያ ማዶ ነው፤ አንደኛው ወደዚህ ማዶ ነው፤ ክስ ይሄዳሉ ክስ ተጀመረ፤ ፖሊስ ምን ምን ሄደ ምን ሄደ አልተቻለም።

ስለዚህ አንድ ሽማግሌ መጣና አብዱራሂም ለምን እነዚህን ሰዎች ለምን አንሞክርም? ለምንድነው እማናስታርቃቸው? ፍርድቤቶቹ ነገር አይቆርጡም፤ ደግሞም ወደ ሰላም አይመጡም፤ አንዱ ቢቀጣ፤ አንዱ ቢሰቀል፣ አሁንም ቂም ነው እሚያተርፉት። ስለዚህ ለምንድነው እማንሞክረው? እችላለን አልኩኝ እኔ ደሞ በድፍረት እና ሄድኩኝ ከሽማግሌዎች ህጋችን ምን ይላል? በመጽሐፉ ራሱ ያዛል። አንድ የተበደለ የሴቶች ጉዳይ ሲታይ ከሴቶች ወገን የተወሰኑ ሰዎች እንዲኖሩ ይላል። በዚህ በዱላም ይላል ከዚህ ወገን የተወሰኑ ተራ ሰዎች አይደሉም ቢረግሙ የሚፈሩ እነዛን ነው። ከዚያ አንድ ሰባትና አሥር፣ ከዚህ አንድ አሥር ባጠቃላይ አንድ ሃያ እኛ ደግሞ እዚህ መሃል አንድ አምስትና ስድስት ሆነን ተያያዝነው ጉዳዩን «የሞተ ሞቷል አሁን ደግሞ ሌላ ለመግደል ስትፈልጉ ሁለት ይሞታል አንዱን አጣችሁ አያሳዝናችሁም ወይ? ለሞተ ሰው አታዝኑም? አንድ በዚህ በኩል እዩት፤ ሁለተኛ ደግሞ መፅሐፋችን ምንድነው እሚለው? ማነው የሰው ደም እሚፈልግ? አላህ ነው ወይስ ሰው ነው? አላህ ተበቀሉ ብሎ አዟል? እናንተ ቁርዓን ታውቃላችሁ አምጣ አሳየኝ ቁርዓን ውስጥ ክፉ ነገር ሲያጋጥማችሁ

*ለእግዚአብሔር መልሱ አይልም ወይ?» ይላል። «ይላል ብለህ አፍህን ሞልተህ ተናገር፤ ታዲያ አንተ ለማድረግ እምትፈልገው የትኛውን ነው?»*

እርስ በራሳቸው ወዲያው አንተ ከአላህ ጋር ልታጣላን ነው? ይላሉ እርስ በራሳቸው ወዲያው በጣም ደሙ የፈላ ሰው ሲነሳ ይይዙታል፤ መጨረሻ ላይ ጧት የጀመርን በሁለት ሰዓት አሥር ሰዓት አካባቢ ጨረስን። ተፈታ ነገሩ፡ ሁሉም ቦታ የደረሰ ስለሆነ ክሱን ማንሻ ተፃፈ፤ አስገባን። ሰዎቹ መጨረሻ ላይ ሰዎቹ በሬ አመጡ፤ ታረደ፤ «ደም ተቀባቡ አትበሉን እንደዚሁ ይታረዳል ይሄው ተቃቅፈናል» ተቃቀፉ፤ እርስ በራሳቸው ተላቀሱ፤ ቀረ። ይሄ ነገር ከሆነ አንድ ሃያ ዓመት ይሆናል ምንም ነገር የለም። እና እስከዚህ ድረስ ይፈታል። ከሞት በላይ የለም የገንዘብ ጉዳይ ማሪሽ በማሪሽ ነው እሚያልቀው ።

*ካሳ ምናምን የለም?*

ምንም ካሳ የለም ማን ይበላዋል? አይቀበሉም ። ካሳ ቁርአን ያዛል፤ ከተቀበለው ሰውየው ግዴታ አይደለም ቤተሰብ ደሞ የልጄን ደም እበላለሁ ወይ? ይላል አይቀበልም፤ ማህበረሰቡም የልጁን ደም ሸጦ በላ ስለሚል ካሳ አይቀበሉም። እንደዚህ ነው የምናስታርቀው በእኛ በሉ አሁን ሰላት ሰዓት እየደረሰ ስለሆነና ከሰዓትም ሥራ ሥላለኝ ይበቃናል፤ ሌላ የምትፈልጊው ነገር ካለ ሌሎች ሽማግሌዎች ጋር አገናኝሻለሁ፤ በደህና ዋሉ።

***እሺ በጣም አመሰግናለሁ። ከእርሶ የምፈልገው ነገር ካለ ግን ደግመን መገናኘት እንችል ይሆን?***

ይቻላል! ይቻላል! ስትፈልጊኝ ላኪብኝ።

***እሺ በጣም አመሰግናለሁ ደህና ይዋሉ።***

## ቃለ ምልልስ ሦስት

- **የመረጃ አቀባዮች ስም፡-**

1. መሃመድ አልናስር **ዕድሜ**፡- በግምት 70 **ሥራ፡-** ግብርናና ንግድ፣ **የትምህርት ደረጃ ፡-** መሠረተ ትምህርት፣ **ብሔር**፡- በርታ መረጃዉ የተሰበሰበበት ቀን ሐምሌ 26 ቀን 2003 ዓ.ም እና ከ8፡00-10፡30 ሰዓት ቦታ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ብ/ክ/ መንግሥት ሸርቆሌ ወረዳ በሸማግሌው ግቢ ውስጥ

2. ሲቲና አደም፣ **ዕድሜ፡-** 38፣ **ፆታ፡-** ሴት፣ **ሥራ፡-** ነጋዴ፣ **የት/ ደረጃ፡-** ዲፕሎማ በግብርና ኤክስቴንሽን፣ **ብሔር**፡- በርታ

3. ነፊሳ መሀመድ **ዕድሜ፡-** 28፣ **ፆታ**፡- ሴት፣ **የት/ ደረጃ፡-** የመጀመሪያ ድግሪ በቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ፣ **ሥራ፡-** የወረዳው የባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ኃላፊ፣ **ብሔር**፡- በርታ

- **ቃለ ምልልሱ የተደረገው፡-** በአማርኛ ቋንቋ
- **መረጃ ሰብሳቢ**፡- ስንቅነሽ አጣለ

***እሺ አባ መሃመድ በመጀመሪያ ስለበርታ ብሔረሰብ ባህል ለማነሳቸው ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ፈቃደኛ ስለሆኑ በጣም አመሰግናለሁ፤ ሰሞኑን ራቅ ወዳለ ቦታ ዘመድ ስለሞተ እዚያ ከርመው መምጣትዎን ሰምቻለሁ እስቲ ሰው ሲሞትስ የሚደረገው ሥርዓት ምንድነው በበርታ? ህፃን ሲሞት፣አዋቂ ሲሞት፣የአገር ሽማግሌ ወይም የጎሳ መሪ ሲሞት የመሳሰለው የሚከናወነው ሥርዓት እንዴት ነው? ስለሱ ቢነግሩኝ፡፡***

እሺ ይጠቅመኛል ያልሽውንና የማውቀውን ሁሉ እነግርሻለሁ፡፡ በሞት ጊዜ በዕድሜና በታዋቂነት ልዩነት አላየሁበትም፤ ያው ሰው ይሞታል፤ ሲሞት የሬሳ አስተጣጠብ ሥነ ሥርዓቶች አሉ፤ መጀመሪያ ሊሞት ሲቃረብ ዘመድ ካለው ሻዲያ ወስዶ ሻዲያ ማለት አላህ አንድ መሆኑን መሀመድ ደግሞ ነብይ መሆኑን ይመሠክራል፡፡ ይህ ቃል ካሉ

እንደወጣ መሞት አለበት። ይሄ ነው አንዱ ትልቁ እምንጠነቀቀው እዚያ ላይ ነው ዘመድ ካለው ማለት ነው፤ ግን ሰው በዚያን ሰዓት ጭንቅ ውስጥ ነው ከቻለ የተረጋጋ ሰው ከሆነ እነዚያን ሁሉ አስወግዶ ሻዳ እንዲያደርግ መቻል አለበት። ሻዲያ ትልቁ ነገር ነው ፤ ከዚያ በፊት ህይወቱን እያወቀ በጣም በሽታው እማይተርፍ ከሆነ ይገምታሉ ሰዎች ስለ ንብረቱ የሆነ ነገር እንዲል ይጠየቃል። ስለ ልጆቹ፣ ብዙ ወንድሞች አለህ ማነው ለአንተ ልጆች እምትወክለው? ትልቅ ሀላፊነት ነው ለልጆች ማን ትወክላለህ? ሞት አትፍራ፤ ሞት ይመጣል፤ እሚቀር ነገር አይደለም፤ ላትሞትም ትችላለህ፤ ግን ድንገት ብትሞት ለልጆችህ ማንን ትወክላለህ? እከሌን ወክያለሁ ይላል።

### *ውርስ ጋብቻ አለ እንዴ በማህበረሰቡ ውስጥ?*

አዎ አለ ግን ውርስ አንለውም፤ ምክንያም በግዴታ የሚፈጠር ነገር አይደለም። በግዴታ መውረስ አለብኝ ብሎ ሌላ ቦታ እንደምንሰማው ሳይሆን ልጆች ካሉዋት በተለይ ልጆቿ ሌላ ሰው ጋ ሄደው ከሚያድጉ አጎታቸው ጋ ሄደው ቢያድጉ ይሻላል ከሚል ነው እንጂ ከሴትየዋ ቁንጂና ከሴትየዋ ከወጣባት ገንዘብ ተያይዞ አይደለም። ንብረቱን ሳይሆን ልጆቹን ማን ያሳድጋቸዋል እንጀራ አባቱ ሌላ ከሆነ ልጆቹ በትክክል አያድጉም፤ ሴትየዋ ራሷ ደግሞ ባሌ ስለሞተ የሌላ ሰው ፊት ልጆቼ ማየት የለባቸውም ብላ ይህንኑ ትመርጣለች፤ ነገሩ ግን አለ በዚህም ሆነ በዚያ ።

### *እሺ ወደጀመሩት ወደ ኑዛዜው እንመለስ*

እና ኑዛዜው ለሀብቱ፣ ለመሬቱ፣ ለልጆቹ ለሁሉም ነገር ይወክላል፤ከዚያ በኋላ ሰዎች አሉ ከሞተ እሱ የተናገራቸው ነገሮች ተግባራዊ ይሆናሉ እሱ ባለው መሠረት፤ ሻዳ ወስዶ ሲሞት እንግዲህ ይታተባል። የሬሳ አስተጣጠብና አገናነዝ ሥርዓቶች አሉ፤የሙስሊም ህግ በሚያዘው መሠረት ለሴቶች ሱሪ ነው እሚሰራላቸው፤ በሱሪ መልክ ነው ከፈኑ ለወንዶች ደግሞ ሽርጥ ነው ተለዋውጠው ማለት ነው። የሙስሊም ህጉ ነው

እንደዚህ የሚያደርጋቸው ሴቶች ሱሪ መልበስ አለባቸው ወንዶች ደግሞ ሸርጥ ይሠራላቸዋል። ይሄ እስከሚሠራ ሰዎች መቃብር ቦታ ሄደው እየተቆፈረ ነው ፀሎት ይደረጋል። ከዚያ በኋላ መቅበር ነው፤ ሴቶች ቀብር ቦታ አይሄዱም ለምንድነው ስለሚጮሁ ስለማይችሉ ስለሚያለቅሱ አንዳንዶቹ በጣም እሚችሉ ቢሄዱ ምንም አይደለም እኔ የሄደች ሴት አይቻለሁ። አላለቅስም ብላ አስፈቅዳ ማለት ነው። እንዳያለቅሱ ነው የተከለከሉት ሌላው ቀርቶ እዚያ ቤት ውስጥ ማልቀስም የተከለከለ ነው። ቤት ውስጥም ቢሆን ማልቀስ ማለት ቁጪት ነው ንዴት ነው ለምን ሞተብኝ ማለት ነው። እና ከማን ጋር ነው እሚጣላው ከፈጣሪው ጋር? ሁለተኛ በፈሰሰው እምባ ልክ ሟቹ ይቃጠላል ይባላል። ለምንድነው ሰው እምታሰቃዩ ሴቶች አልቅሳችሁ? ግን ወንዶች ራሳቸውም እሚያለቅሱ አሉ አልችል እያሉ አያበዙትም እንደሴቶች እንጂ።

**ነፊሳ፡-** እኔ ያየሁት የቀረ ደግሞ ሬሳው በሚታጠብበት ጊዜ ያ ውሃ ሬሳው የታጠበበት ውሃ እንዳይበተን ማለት ነው ወደ አንድ ቦታ ነው የሚገደበው…

**ሲቲና፡-** እዚያው ነው እንጂ የሚቀመጠው እዚያው ይቀመጥና የእሱ ልብስ፣ ይጠቀምበት የነበረው ማንኛውም ቁሳቁስ ተሰብስቦ መጋረጃ ይጋረድበትና ለአንድ ሳምንት እዚያ ይቆያል፤አስክሬኑ የሄደበት ሰሌኑ አልጋው ያለበሱት ልብስ ተመልሶ ይመጣና ለአንድ ሳምንት ቆይቶ ይታጠባል። በሳምንቱ ታጥቦ ይመጣና ለሚወደው፣ ለቤተዘመድ፣ እንግዲህ ቅርብ ለሆነ መውሰድ ለሚፈልግ ይሰጣል። ካለበለዚያ ወስደው ወይ መስኪድ አካባቢ ወይ እንደዚህ ልብስ ለሌላቸው ሰዎች ይሰጣል ይሄ አስተዛዘን አካባቢ ላይ ትንሽ ላግዛቸውና…

**ነፊሳ፡-** ቆይ የአስክሬን እጣቢው ጋ የቀረ ነገር አለ። እኛ አካባቢ ያ ውሃው የተደፋበት አፈር በአስራ አምስተኛው ቀን ከዚያ ተወስዶ ወደ ሌላ ቦታ ነው ትልቅ ዛፍ ተፈልጎ እንደገና ይቀበራል። ያ አፈር ምሽት ላይ ሁሉም ዘመድ ይሄዳል እና ይሄም አለ…

***ለምን ይሆን እንዲህ የሚደረገው?***

ለምን የሚለውን እንግዲህ በኂላ በጥናቱ ላይ ስትዘልቂ ጠይቁ እነግርሻለሁ።

**ሲቲና፡-** እሱ ነው አስተዛዘኑ ላይ ለምሳሌ ሴቶች እዚያ መጋረጃ ሥር ወይ ባል ሞቶ ከሆነ ሚስቶቹ፣ እህቶቹ እናቱ ካለች እዚያ መጋረጃ ውስጥ ነው እሚቀመጡት። ለአንድ ሳምንት ያክል በእጃቸው አይበሉም። ልክ ሰውየው ተቀብሮ ወዲያው እንደመጣ ውሃ ይደፋባቸውና ቁጭ ይላሉ። አዘንተኞች ይባላሉ። ከዚያ በሀዋላ እነሱ ያው ሥጋ አይበሉም። ለአንድ ሳምንት ያህል ሀዘኑ እስከሚያልፍ ድረስ እዚያው መጋረጃ አጠገብ የሰውየው ልብስና ቁሳቁስ በተቀመጠበት አጠገብ ይቀመጣሉ። አስተዛዛኞች እዚያ አካባቢ እንግዲህ እሚላላኩ ሥራ እሚሠሩ ቤተዘመድ ሁሉ ይሰበሰባል። ለቅሶ ደራሽም ይመጣል። ለቅሶ ሲደረስ ያው ባለፈው እንደነገርኩሽ ዱቄት፣ ሊጥ ይዘው ይመጡና እሱ ነው እንግዲህ እየተገነፋም እየተጋገረም ለሀዘንተኛ እሚሰጠው፤ ወንዶች ደግሞ ስኳር፣ ቅጠል ሻይ፣ ቡና፣ ገንዘብ፣ ይዘው ይመጣሉ። እዚህ ስመጣ እኔ እንግዲህ ሊጥ ይዤ መጣሁ አይደለም ወሃ ከሌለ ውሃ ሄጄ እቀዳለሁ። የእኔ ሠፈር ነው ምናምን የሚባል ነገር የለም፤ እንጨት ከሌለ እንጨት ሄጄ አመጣለሁ፤ ሁለት ቀንም ሦስት ቀንም ከሌላ ቦታ መጥቼ እዚህ ላስተዛዝን እችላለሁ። ምግብ ማብሰሉ ምን ማለቱ የሠፈር ሰው ወይም ከሌላ ቦታ የመጣው ሀዘን ስለሆነ በጋራ ነው እሚሰራው።

***እድር እሚባል ነገር አለ?***

እድር እሚባል ነገር የለም፤አይታወቅም። እና ሁሉም ሰው ለቅሶ አለ ከተባለ ሥራ እንደሚኖር የሚሠራላቸው ሰው እንደማይኖር ስለሚታሰብ ልጅ ያለውም ህፃን ልጇን ይዛ መጥታ እዚያው ነው እምታስተዛዝነው እና እንደዚህ ዓይነት ነው። ወንድ ይሁን፣ ሴት ይሁን፣ ትንሽ ይሁን፣ ትልቅ ይሁን፣ ሀብታም ይሁን፣ ደሃ ይሁን ሞት ላይ እኩል ነው። ምናልባት ሰፋ ብሎ ትልልቅ ሰዎች እሚያውቁት ሰዎች ከሌላ ቦታ እስከ አርባ ቀን ድረስ የሚመጡበት ሁኔታ ሊሆን ይችላል። እዚያ አካባቢ ላይ ያሉት ቤተዘመዶች እዚያው ይቆያሉ። ልክ ሲመጣ እንግዲህ ለወንዶች እሚቀርብ ሻይ ቡና ትልልቅ ጎረምሶች ይለዩና ያ ልጅ በቀደም ለትዳር መሥፈርት ያልሽው አንዱ ትልቅ

ሰው ሲሞት ይችላል አካባቢው ላይ ሀላፊነት ይሰጠዋል። ይህንን ውሰድና ሻይና ቡና እዚያ እምታስተናግዱት እናንተ ናችሁ ይባላል። ያ ልጅ የዚያን ጊዜ ሀላፊነት ወስዶ ያንን ሃላፊነት በሥርዓት ከተወጣ በቃ ደርሷል፤ ቤቱን መያዝ ይችላል፤ የሚል የሚያሳድሩበት ዕምነት አለ። የሴቶችም ሴት እዚያ በአበላል ላይ እንደሚለያዩ ለቅሶ ላይም ከወንዶች ጋር በአንድ ላይ አይቀመጡም ። የለቅሶው የመጨረሻ ቀን ወንዝ ወርዶ ልብስ አጥቦ ወንዶቹ እዚያው ቁርዓን ይቀራሉ። ሴቶቹም ቤት ውስጥ ያለውን አዘጋጅተው ሴትዮዋን በቃ እንግዲህ ሀዘን ይበቃል ብለው የፅናናሉ። ልብሱን አጥበው ወደቤት ያመጣሉ፤ ቤቱን ይጠራርጋሉ፤ አጽድተው ነው እሚበተኑት። ወንዶችም እንደዛው ወንድየውን እዛ አጽናንተውት ይሄዳሉ። ወንድ ልጅ ሀዘን አያጠብቅም፤ ውጪ ነው የሚቀመጠውም፤ አይጋረድለትም፤ ወንዶች ይመጣሉ፤ የሚቀበሏቸውም የሚያስተናግዷቸውም ወንዶች ናቸው ይሄ ነው ልዩነቱ።

ነፊሳ፡- እኔ አንድ ያየሁት ነገር አለ፤ ማለት ትልልቅ ሰዎች ሲሞቱና ህፃናት ሲሞቱ በሚለው ላይ አሁን እኔ ያየሁት የእናቴ አክስት ስትሞት ትልቅ ሆና ነው የሞተችው፤ መቶ ዓመት ምናምን ይሆናታል። እሳቸው ሲሞቱ በጭፈራ ነው የተሸኙት፤ አልተለቀሰላቸውም። እንደውም በእልልታ እየተጨፈረ ለምንድነው ሲባል ዕድሜአቸው በጣም ሄዷል በጣም በልተዋል ኖረዋል ምንም እሚለቀስላቸው የለም ተብሎ ነው ያኔ በእልልታ ነው የተሸኙት፤ ዘመዶቻቸው እየፎከሩ ነው የሸኘዋቸው ማለት ነው።

አባ መሃመድ፡- ለዛ ለሞተ ሰው የሚደረግ ጭፈራ እራሱ ባህላዊ ነው። መሬት አመታቱ አካሂዱ ትርኢቱ የተለየ ነው። ቃላቱ እራሱ እና እየተረሳ ነው ባሁኑ ሰዓት። አንዳንድ ጊዜ እንደዚሁ ያጋጥማል። በጣም ቆንጆ የለቅሶ ሙሾ ልበለው በእናንተ ቋንቋ በጣም ላረጁና በጣም ታሪክ ለሠሩ መሪዎች ሰዎች ነው እሱ ነገር  መሪዎች ሲሞቱ ማልቀስ አይፈቀድም ይጨፍራሉ።

***ይሄን ሙሾውን ግጥሙን የሚደረድር የታወቀ ሰው አለ ወይስ ሁሉም ሰው ነው የሚገጥመው?***

ይታወቃል፤ ህብረተሰቡ ውስጥ ያ ሰው ካልሞተ በስተቀር አያወርድም። የሚያውቁ ሰዎች አሉ እነሱ ናቸው የሚመሩ።

*አሁን እነዚህ ሰዎች ይገኛሉ?*

ይኖራሉ፤በርቀት ላይ ይሆናሉ እንጂ ከተፈለጉ ይገኛሉ።

**ሲቲና፡-** ሌላ ምን አለ ለምሳሌ የእኔ አያት ከሆነች የሞተችው የእናቴ እናት ወይም የአባቴ እናት ትልቅ ከሆነች ለእኔ በሉ አያቴ የሞተችበትን ብዬ አጎቶቼ አክስቶቼ እንዲቀጡልኝ አደርጋለሁ ተሰብስበን ብዙ ሆነን …

*ለምን?*

አያታችን ስለሞተች እምንቀልድባት፣ እምንጫወትባት፣ እምታዝናናን፣ ተረት እምትነግረን፣ ምሳሌ እምትነግረን፣ ሄደን እምናርፍባት፣ እምትንከባከበን፣ አጣን ማለት ነው። እሷን በማጣታችን ካሳ ስጡን ብለን እንጠይቃለን። ልጆቿን እናቶቻችንና አባቶቻችንን መልሰን ማለት ነው። ከዚያ በኋላ እነሱ አንድ ፍየል ተሰጥቷችኋል ይባላል። የልጆች መብያ ቀን አለ ደሞ ሌላ ፕሮግራም እንግዲህ እሷ ከሞተች በኋላ በሳምንቷ በሚበተኑበት ቀን ነው። ይሄ የሚጠየቀው ልክ በዛ ሳምንት ልብስ ታጥቦ ይመጣል አይደለም፤ ካሳው ካልተሰጠን ልብስ እቤት አይገባም ብለን ተሰልፈን ቤት እንዘጋለን። ከዛ በቃ ይሄን ሰጥተናል፤ ይሄን ሰጥተናል፤ እባካችሁ ፀሐይ ነው፤ ልብስ ይግባ፤ እንግዲህ ጫወታ ነው ይሄ ለቅሶ የለም እኛ አናለቅስም። እነሱ ሊያለቅሱ ይችላሉ እናታቸው ስለሞተች። እኛ አናለቅስም በቃ ያንን አምጡ ብለን ያንን እንቀበልና ከዚህ ውስጥ ከአክስትም ውስጥ ማለት ነው በቃ የምትፈልጉትን እኔ እከፍላለሁ ብሎ ሌሎቹ ሳይደርሱ አንዱ ሃላፊነት የሚወስድ ሰው ከተፈጠረ በቃ አንለቀውም። ቃል ይገባልናል፤ እሷም ከሞቷ በፊት ለልጆቿ ትታው የምትሄደው አለ እኔ ከሞትኩ ለልጆቼ ይሰጥልኝ ትላለች።

*ሴት አያት ብቻ ነች?*

ወንድ አያትም ቢሆን ሁሉም አያት እንዲሁ ነው ትቶልን የሚሄድ ነገር ይኖራል፡፡ ከዚያ በኂላ በሚበላበት ቀን ሁሉም አያት የሆነ በሙሉ ይገኛል፡፡ አያት የሆነ በላሽም አልበላሽም ትገኛለሽ፡፡ ካልተገኘሽ  አንቺን ይቀጡሻል፡፡ አጋጣሚ ካልነበሩና ለቅሶም ሳይደርሱ ከቀሩ የዚያን ቀን ሊደርሱ ይችላሉ፡፡ ይዘው ግጥም አድርገው ያስሩና የት ነበርሽ? ለምድነው ያልሰማሽው? እንዴት አልሰማሽም? ለምንድነው መጥተሽ እዚህ የአያትነትሽን ያልተካፈልሽው? ትቀጫለሽ! ትባያለሽ፤ ትቀበያለሽ፡፡ አንቺ ልክ እነዚያ ታስረው እንደተፈቱ አንቺንም አሥረው ቀጥተው ይለቁሻል፡፡ የተሰጡት ፍየል ታርዶ ይበላል፤ ህፃናት በሙሉ የልጅ ልጅ አይቀሩም ተሰብስበው ይጨፈራል፤ ይደነሳል፤ ፀሐይ ላይ በቃ ሲጨፍሩ ነው እሚውሉ የዚያን ቀን ለእነሱ ብቻ ነው፡፡ ለሌላ ትልቅ ሰው አይደርስም፡፡ ሌላ ሰው ጣልቃ አይገባም፡፡ ከዚያ በኂላ ይበላል፤ ይጠጣል፤ እህል ይሰጣቸዋል፤ ብርም ይከፈላል፤ በቃ በልተው፣ ጠጥተው ወደ ቤታቸው ይሄዳሉ፤ ይሄ አያት ሲሆን ነው፡፡

ከዚያ ሌላ ደግሞ ሰው ሞቶ አርባ ቀንም አልፎ ጭራሽ ያልሰማ ሰው ሊኖር ይችላል ዘመድ ነው ይመጣል፤ ለቅሶ ክልክል ነው ይመጣል ወንዱ የሚያለቅሱ ወንዶች ይኖራሉ፤ የማያለቅሱም ይኖራሉ፤ ሴቶች ግን ዛሬ ለምን ዓመት እቆይም ያ ለቅሶ ያለቅሳሉ፡፡ ሳያዩሽም ዓመት ከቆዩ ያለቅሳሉ፡፡ በእኛ ባህል ሳያዩሽ አሁን ዓመት ቆይተሽ ትመጫለሽ አይደለም የት ቆይተሽ እንደመጣሽ፣ታመሽም ጥሩ ሁነሽም ሊሆን ይችላል፤ ግን በመጥፋትሽ ብቻ ምን ሁና ነው የጠፋች ተብሎ ልክ ሊያዩሽ ሲመጡ ያለቅሳሉ፤ ለቅሶም ከሆነ ዓመትም ቢቆይ ይደረሳል፡፡

***ቅድም አያት ስትሞት ልጆች ተረት የምትነግረን፣ የምታስቀን፣ የምትንከባከበን፣ ይላሉ ብላችሁኛል ተረት ለልጆች የሚነግሩ ታሪክ የሚነግሩ አያቶች ናቸው ማለት ነው?***

***አባ መሃመድ፡-*** ይህን ሀላፊነት የሚወስደው አያት ነው። የወንዱም የሴቱም ለዚህ በቃ ተረት ንገረን፤ ማታ ማታ ወይ እራት እስከሚደርስና ወደ መኝታ እስከምንሄድ ሥራችን ያ ነው አያት ሥር ሽጉጥ ብሎ ተረት ንገረኝ እንላለን።

***እነዚህን ተረቶች እኔ እፈልጋቸዋለሁ ማን ሊነግረኝ ይችላል?***

አይጠፋም ንገሩኝ ስትይ አስታውሶ መንገሩ ይቸግር እንደሁ ነው እንጂ…

***አሁን እርሶ የልጅ ልጅ አይተዋል ተረት የመንገርም ግዴታ አለብዎት ለልጅ ልጆችዎ ተረት ይነግሯቸዋል?***

አዎ የቻልኩትን ያህል

***እስቲ ይስታውሱና ለእኔ ተረቶችን ይንገሩኝ?***

ተረት "ፀፀሪና" ይባላል አያቶች ናቸው የሚናገሩት። ልጆች ተሰብስበው እባክሽ ፀፀሪና ንገሪን ይላሉ። እሷ አታስቸግሩኝ ከየት አመጣለሁ ትላለች። ትለመን ትለመንና መናገር ትጀምራለች። ተረት ቀን አይነገርም ማታ ነው የሚነገረው፤ ቀን ልጆቹ አስቸግረው መናገር ግዴታ ከሆነ ፀጉር ከቅንድብ ላይ ይነጭና ይነገራል። አለዚያ ማታ ብቻ ነው። ረጃጅም ተረቶች ሲሆኑ ልጆች እየሰሙ እንቅልፍ ይወስዳቸዋል። ይህ ከሆነ በማግስቱ ይቀጥላል፤ እማ አልጨረስነውም እኮ ብለው እንድትቀጥልላቸው ያደርጋሉ። እስቲ ትዝ ካለኝ አንዱን ልንገርሽ።

ተረት 1

አዎር እሚባል ሰው አለ በተረቶች ኮሚክ ነው ኮሚክ የሆነ ሰው በእኛ በጥንቸል ይወከላል፤ ጥንቸል መልኳ አስቂኝ ስለሆነ።

አንት አዎር ይባላል ፈስ በስልቻ ይጠራቅምና ሀብታም ቤት ይገባና ይሄን እቃ በአደራ አስቀምጡልኝ ይልና እዚያ ይስተናገዳል፤ አድሮ በማግስቱ ሊሄድ ሲል ያንን በአደራ ያስቀመጠውን ስልቻ ያስመጣና ጥሩ መስተንግዶ ስላደረጋችሁልኝ በስልቻው ውስጥ

ያለውን ስጦታ ሰጥቻችኋለሁ ግን የምትከፍቱት እኔ ከሄድኩ በኋላ ነው ብሏቸው ይሄዳል። እነሱም ካላቸው ሁሉ ነገር በስጦታ ሰጥተው ይሸኙታል፤ እንዳለው ከራቀ በኋላ ሲከፍቱት ሁሉም ፊስ በፊስ ሆኑ ይባላል።

ተረት 2.

ሌላ አንድ ንጉስ ነበረ ንጉሱ እንዲወለድለት የሚፈልገው ወንድ ልጅ ብቻ ነበር። ሴት ልጅ አይፈልግም። አዋጅ አውጥቶ ነበር እና ከሚስቶቹ መካከል አንዷ አርግዛ ስትወልድ ሴት ናት። እና እንዳትገደልባት ደበቃ አሰደገቻት፤ ከሌላ ሚስቱ የሚወልደው ወንድ ልጅ ደግሞ አለው፤ ያቺ ለብቻዋ ተደብቃ ንጉሱ አባቷ ሳይሰማ ያደገችው ታድጋለች። ሰው ሳያያት በእናቷና በተወሰኑ ሰዎች ነው የምታድገው፤ በጣም ቆንጆ ልጅ ሆና ታድጋለች። በጣም እሷ ስትወጣ ፀሐይ ትጠፋለች ይባላል ከቁንጅናዋ የተነሳ።

አጋጣሚ አንድ ቀን ያ ወንድሟ ያያታል። ወዲያውኑ እንዳያት ይወዳታል። ካላገባኋት ብሎ ያብዳል፤ አባትየው የማጪያ ሥርዓት እንዲዘጋጅ ያዛል። ይህን ስታውቅ መስኮት ትሰብርና ትጠፋለች። ወንድሜ እንዴት ያገባኛል ብላ እሷ እናቷ ስለነገረቻት ወንድሟ መሆኑን ታውቃለች። ስለዚህ ጠፋች ፤ በዚህ መሃል የሽማግሌ ቆዳ መልበስ ትፈልጋለች እንዳትታወቅ፤ ስትሄድ፣ ስትሄድ፣ ሽትሄድ ሽማግሌ ታገኛለች። አባ፣ ሽማግሌ እንዴት ነው ቆዳው የሚወጣው? ትለዋለች። ቀላል ነው የግራር እሾህ አሽተሽ ጭንቅላቱ ላይ ብታደርጊ ወዲያው ነው ሙሽልቅ የሚለው ይላታል። ወዲያው እንዳላት ስታደርግ ሙትት ሲል ቆዳውን ላጥ አድርጋ አወጣችና ለራሷ ለበሰች። ከዚያ ሽማግሌ መስላ ትጓዛለች። ስትሄድ፣ ስትሄድ ባህር ያጋጥማታል አንቺ ባህር ሆይ እንዴት ነው አንቺን መሻገር የሚቻለው? በያዝከው በትር ብትመታኝ ለሁለት እከፈላለሁ። ባህሩን መታ ተሻገረችና ሌላ አገር ገባች። ሌላ ንጉስ ያለበት። ዛፍ ላይ ወጥታ ተደበቀች። ከዛፉ ሥር ውሃ አለ። የንጉሱ አሽከሮች ውሃው ጋ ሲመጡ ውሃው ውስጥ ዛፍ ላይ የተቀመጠ ሰው ያያሉ፤ ዛፉ ላይ ለመውጣት በጣም አስቸጋሪ ነበር እሷ ስትወጣ በመዝሙር ዛፌ ዛፌ የአያቴ ዛፍ ተነሺ ዝቅ ዝቅ በይልኝ ብላ ዝቅ ሲልላት ወጣችና ከፍ ከፍ በይ ስትል

ከፍ ብሎላት ነው የወጣችው። አሽከሮቹ መጥተው ሲያዩ ውሃው ውስጥ ጥላ ያያሉ። ሰው ያያሉ፤ ውረድ ይሉታል፤ አልወርድም፤ እንግዳው ዛፉን እንቆርጠዋለን፤ መቁረጥ ሲጀምሩ ዝቅ ዝቅ በይልኝ ብላ ስትዘምር ዝቅ አለ። ይዘዋት ሄዱ ወደ ቤተመንግስት እዚያ ሲሄድ ይሄን ሽማግሌ ከየት አመጣችሁ? ምንድነው እምትችለው ሥራ? ይላል ንጉሱ፤ አይ እኔ ዶሮ መጠበቅ እንጂ ሌላ አልችልም ትላለች።

ዶሮ እንድትጠብቅ ያደርጋሉ፤ ዶሮ እየጠበቀች ብቻዋን ስትሆን ሰው በሌለ ጊዜ ያንን የተሸፈነችበትን የሽማግሌ ቆዳ ታወጣና፣ ጌጠዋን ታደርግና፣ ማንም ሰው ሳያይ ራሷ ብቻዋን ትደሰታለች። የሆነ ምልክት ስታይ ወዲያውኑ ቆዳውን ለብሳ ሽማግሌ ሆና ቁጭ ትላለች። አንድ ጊዜ ዶሮቹን ውሃ ለማጠጣት ወንዝ ዳር ኩሬ የሆነ ነገር አለ እዚያ ይዛ ትሄድና አንድ ዱዳ ሰውዬ ደግሞ እዚያው ንጉሱ ቤት አለ እሱን ታምነዋለች መናገር ስለማይችል አልፈራችውም፡፤ እዚያ ውሃው ጋ ሲደርሱ ያንን የሽማግሌ ቆዳ አውጥታ ገላዋን ታጥባ ጌጧን አደረገች፤ ስትዝናና ያ ዱዳ ያይና ይገረማል። ማታ ሲገቡ እንኮይ በጣም የበሰለ እንኮይ በጣም ደስ የሚል እንኮይ ለቅሞ መጣ የተለያየ ዓይነት ያልበሰለ፣ ጮርቃ፣ መሀሉ ላይ በጣም የበሰለ ቢጫ ደስ የሚል አመጣና ለንጉሱ አቀረበ። ምንድነው? ሲባል ያልበሰለውን ጣለ እና የበሰለውን ሰጠው። ምንድነው እሚለኝ ይሄ ከአንተ ጋር የዋለው ዱዳ? አይ በብረት እሳት ውስጥ አርገህ ጭንቅላቴን አቃጥለኝ ነው እሚልህ፤ እሷ እንዳለች ብረት አግለው ሲተኩሱት ጮኸ ዱዳው በኋላ ይሸሻል። ይታመምና ይድናል። እንደገና ደግሞ እንደገና እንዲሁ ያኑኑ እንኮይ ያመጣል በኋላ ይህን ዱዳ ለምን እንሰቃየለዋን? ውሏቸውን በድብቅ ክትትል አድርጉ ብሎ አዘዘ ንጉሱ። ክትትል ተደረገ ልክ እንደለመደችው የሽማግሌ ቆዳውን አውጥታ ስትጨፍር የአባቷን ዝና እያወደሰች ብቻዋን ትጨፍራለች። ያንን ሁሉ አዩ ስለላ የሄዱት አሽከሮች አዩና ተመለሱ ምንም ሳይታዩ እቤት ሲገቡ ለንጉሱ ነገሩ፤ በነገታው ዛሬ ከእኔ ጋራ ነው እምትውለው አባባ ይላታል። ለምን? አይ ገበጣ እንጫወታለን። እሺ አለ አሁን ገበጣ ጀመሩ በጣም ሃይለኛ ሆነ ሽማግሌው ገበጣ ጨዋታ ታሸንፈዋለች ውርርድ አለ እንግዲህ የተሸነፈ ቆዳው ይተረተራል የሚል ስላልቻላት ወዲያ ወዲህ ስትል እየሰረቀባት አሸነፋት ወዲያው

ቆዳዋ ሲተረተር እሷ ወጣች፤ አግብቷት በሰላም ኖሩ ይባላል ። አሁን እንግዲህ እስከማስታውሰው ነው፤ ብዙ እርስቻለሁ ከውስጡ። የሰላት ሰዓትም ስለደረሰ ይበቃናል።

*እሺ አባ መሃመድ አመሰግናለሁ፤ በሌላ ቀን መገናኘት እንችላለን?*

ኢንሻ አላህ ከተቻለ ግን ትንሽ ሥራ አለችኝ ሰው እልክባችኋለሁ።

*እሺ አመሰግናለሁ፤ ደህና አምሹ።*

## ቃለ ምልልስ አራት

ሐምሌ 27 ቀን 2003 ዓ.ም. ከሰዓት በኋላ ከ8፡30-11፡00 በድጋሚ ከአባ መሃመድ፣ አባ አብዱራሂም፣ ከነፊሳና ሲቲና ጋር። ቦታ በአባ መሃመድ ግቢ ውስጥ።

***እሺ በቀደም ስናወራ አስከሬን የታጠበበት አፈር ቆይቶ ለምን ተወስዶ እንደሚቀበር ጠይቄ መጥቻለሁ ብለሸኛል ለምን እንደሆነ ንገሪኝ***

**ነፊሳ፡-** አፈሩ እራሱ ሲወጣ የራሱ የሆነ ሥነ ሥርዓት አለው። ወንድ ከሆነ በስምንተኛው ቀን ልብስ በሚታጠብበት ቀን ማለት ነው አንድ ቀን ሲቀረው ያ አፈር እጣን ይጨሳል፤ ከዚያ በኋላ ልብሱ የተቀመጠበት አልጋ አለ ብለናል ትናንት እዚያ ላይ እጣኑን ስምንት ጊዜ ያዞራሉ። የሴቷም ከሆነ በስድስተኛው ቀን ሰባት ጊዜ ያዞራሉ። አፈሩ ወደ ውጪ የሚሄደው አፈሩ እቤት ውስጥ ከቀረ ነፍሱም እዚያው ውስጥ ቀረ። እዚያ ላይ ሠርግ ምናምን ሊኖር ይችላል፤ እዚያ ነፍስ ላይ ይጨፈራል፤ ጥሩ አይሆንም። ስለዚህ ነው ወደ ውጪ ተወስዶ አፈሩ እንደገና የሚቀበረው፡፤ ነፍሷ እስከ ስምንትና ሰባት ቀን አፈሩ ውስጥ አለች ተብሎ ይታመናል ።

**ሲቲና፡-** ሌላ የረሳነው ሰባተኛው ቀን ላይ እንግዲህ ሰዎቹ ሰባት ቀን ሙሉ ቤት ውስጥ ቁጭ ብለዋል፤ ሌላ ቦታ አልሄዱም፤ ሰው ጋር አልተቀላቀሉም፤ አዘንተኞች ናቸው።

የሆነ የእንጨት ዘር አለ በጣም እሚበራ "አቀንፃ" ነው እሚባለው እና እሱ እንደዚህ ሰባቱ ይታሰርና፣ እሳት ውስጥ ይሆንና፣ ልብሱ አጠገብ የነበሩት አዘንተኞች እሳት እንዲያዩ ይደረጋል። ሰባት ጊዜ ወደ እነሱ እያቀረቡ ዐይናቸው ላይ እንዲበራ ይደረጋል። ወደ ፊታቸው ቀርቦ ማለት ነው። ሁሉም እነዛ አዘንተኛ የነበሩ  በአርባ ቀን አርባ ቀን ሲደርስ በሚከበርበት ቀን አሁን ሽቶ አይጠቀሙም፤ የገላ ሳሙና አይጠቀሙም፤ ሌላ ቅባት አይቀቡም፤ ፀጉራቸውን አይሠሩም፤ አዘንተኛ የሆኑ ሰዎች ማለት ነው በቃ ልብሱ ይታጠባል፤ ወዲያውኑ እንደታጠበ ነው እሚለብሱት። የዚያን ጊዜ የሽቶ ዓይነት፣ የገላ ሳሙና ዓይነት፣ እንደዚህ እንደዚህ እየነኩ ሰባት ጊዜ ገላቸውን እንዲያስነኩ ይደረጋል። እሱም በአርባ ቀኑ እንግዲህ ቅባት ተቀቡ፤ ፀጉራችሁንም ተሰሩ፤ ተብሎ አንዳንዶቹ እሰከ ዓመት አንዳንዶቹ እስከ ስድስት ወር የማይሠሩ አሉ። ልክ እናንተ የሀዘን ልብስ እንዲያወልቁ ቅቤ እንደሚቀባ ማለት ነው። የኛ የሽቶ ዓይነት እንትን የምናደርገው "ዲልካ"፣ ሽቶ የተቀላቀለ ይቀርብና ሰውነታቸውን እንዲያስነኩ ይደረጋል። ገላቸውን ካስነኩ በኋላ ሌላ ጊዜ ሽቶ መጠቀም በአጠቃላይ እሚሸት ነገር መጠቀም ይችላሉ ማለት ነው።

ሌላው ቅድም አባ መሃመድ ያነሱት ሬሳ ሲገነዝ ማለት ነው የሰንደል እንጨት ይፈጫል፤ ሽቶ ይዘጋጃል፤ እልብሱ ላይ ይርከፈከፋል። መገነዣው ላይ ማለት ነው፤ ሰውነቱን በሙሉ ይቀባል፤ የተዘጋጀው አይተርፍም፤ ሁሉም ነው እሚጨመረው፤ ከዚያ በኋላ ነው እሚቀበረው የቀሩት እነዚህ ናቸው።

ሰው ሲሞት የሬሳ ሽቶ፣ ሰንደል፣ ማህለብ እነዚህ ሦስቱ ፣ መርፌ፣ክር መገነዣ ገዝቶ ነው እሚያስቀምጠው አብዛኛው ሰው ልክ እሱ ሲሞት ከዚያ ወስደው ነው እሚገንዙት፤ ለምሳሌ በሰፈር ያልተዘጋጀ ሰው ቢሞት ከእሱ ተውሰው ወስደው ይገነዝና ሌላ አዲስ ተገዝቶ ይተካል። እናቴ የዛሬ አሥራ ስድስት ዓመት ጀምሮ ነው ከፈን ገዝታ ያቀመጠች፤የሰንደል እንጨቱ ከሱዳን ነው የሚመጣው አሁን በጣም ውድ ነው።

በጋብቻ አካባቢ በቀደም ዲልካ ያልንሽ በሠርግ ጊዜ የበርታ ልጅ ልታገባ ልክ 15 ቀን ሲቀረው የድግሱ እህል በቀደም እንደ ነገርንሽ ለሚሠሩ ሰዎች ከተከፋፈለ በኋላ ልጅቷ ከዚያን ቀን ጀምሮ ከሰው ጋር አትገናኝም። ተጠበቀች፣ ወደ ቤት ተመለሰች ማለት ነው። እሷን አሁን ፀጉሯን ፈቶ መሥራት፣ ጥፍሯን፣ ለሂና እንዲዘጋጅ ተረከዟን መፈግፈግ፣ ጭስ ላይ ማስቀመጥ፣ ይዛ እምትሄደውን ጭሳ ጭስ፣ ሽቶ፣ ዲልካ፣ እሚባል አለ የእህል ዘር ነው እሱ ተፈጭቶ ዱቄቱ ይቀርባል። ከዛ በኋላ እሱ በጭስ ነው እሚበስለው ዘጠኝ ቀን ስምንት ቀን ይፈልጋል እሱን ለማድረስ ያ የሰንደል እንጨት ይጨመራል...

### *ቆይ የዲልካውን አሠራር ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ንገሪኝ*

አሠራሩ አንድ ክንድ ያህል በሎቅያ ወይም የጭስ ጉድጓድ ይቆፈራል። ከዚያ በኋላ "አልጠለህ" የሚባል የእንጨት ዘር አለ፤ የዚህ ሁኖ ቀዩ ቀዩ የግራር እንጨት በጣም የቆየ ያረጀ እንጨት ነው እሚፈለገው ለሱ። ከዚያ ደግሞ የወተት ቅል የምናጥንበት አለ፤ ወይራ አይደለም፤ ሌላ አለ "ሀሹህር" ይባላል በበርትኛ እቤት አሳይሻለሁ አለ። እሱ ይከተከትና ይቀመጣል። ያ እህሉ ይፈጫል፤ ለዲልካ የሚሆነው ፍሬውን አሳይሻለሁ፤ አሶሳ አለ፤ ማሽላ ይመስላል፤ ግን አይደለም። "አዱሁል" ይባላል። እሱ ተፈጭቶ ይቦካል፤ እሚቦካው በምንድነው በሎሚ ውሃ፣ ሰንደል፣ "አልማህለብ"፣ ቅርንፉድ ይደረግና ይዘፈዘፋል። አልማህለብ የሎሚ ፍሬ ነው እምትመስለው አለ እቤት አሳይሻለሁ እነሱ ይዘፈዘፉና አራት ቀን አምስት ቀን ይቆያል። አብሮ ከዚያ በእሱ ውሃ ነው እሚቦካው፤ ይቦካና ትልቅ ጎርንዳ ሳህን ትፈልጊና ሊጡን ግርግዳው ላይ ትጠፈጥፊያለሽ፤ ከዚያ ጪሱ ላይ እንዲህ ትደፊዋለሽ።

ሙሉ ቀን ይጨስበታል፤ እያነሳሽ እሳቱን ትቆሰቁሻለሽ። ሊጡን እንደገና እያነሳሽ በዚያው በሎሚ ውሃ ታቦኪና ትጠፈጥፊዋለሽ። እንደዚያ እያለ ለሰባት ቀን ይቆያል፤ እየታጠነ፤ ከዚያ በኋላ ልክ ቡኒ ቀለም ይፈጥራል፤ በስሎ በሥርዓት በዘይትና ደሞ በውሃ ሽቶ በደምብ ቤት አለ አሳይሻለሁ የበርታን ባህል በደምብ ማወቅ ስላለብሽ እንደተፈጠርሽ

ቁጭ ብለሽ ገና ትጣጠኛለሽ። ከዚያ በደምብ ይዘጋጃል የሽቶ ውሃ በደምብ ተደርጎ ይቀርባል፤ በቅርንፉድ በሰንደል የተነጠረ ዘይት ደግሞ አለ። ለሙሽራ የሚነጠረው በሰም ነው ሰም በጣም ቆንጆው ሰም ይለይና ወፈር እንዲል ዘይቱ በደንብ ይደረግበታል ሰም በተጨማሪ በድሮ ታሪክ ምን ተብሎ ይታመናል የቆዳችንን ቀዳዳዎች ይከፍታል ተብሎ ስለሚታመን እሱ አብሮ ይሠራና ይቀርባል።

በእናንተ ለሙሽራ ሚዜ ተብሎ ይሠጣል አይደል? ሚዜ ተብሎ የሚሰጣት ሰው የሚያሽ ማለት ነው። ያቺ ሚዜ ለሰባት ቀን ማታ ማታ እሷንም እሱንም ታሻለች ማለት ነው። በተቀመመው ዲልካ፣ ለወንዱም ለሴቷም ሴት ናት እምታሽ፤ ከዚያ በሰባተኛው ቀን ለእሷ ለሚዜዋ ልብስ ይገዛላታል፤ ትሸለማለች። ከሰባተኛው ቀን በኂላ ከሠርጉ በኂላ ማለት ነው ሚስት ናት እምትቀጥለው ባሏን ማሸት፤ ያ በቀደም እህቴ ቤት ያየሽው ከሰሌን የተሠራው ምንጣፍ አልሙስሊያ ላይ ይቀመጥና የዲልካ የራሱ የሆነ ልብስ አለው እቤት አሳይሻለሁ ለዲልካ ተብሎ የሚመጣ የተለየ ልብስ አለ ጥቁር ነው በጣም የሚውረገረግ ለስላሳ ሃር ነገር ነው እሱ ወንዱ ይዞ ይመጣል። ለምንድነው ዲልካውና ዘይቱ ቢነካው መልኩ አይቀይርም ሽታውንም የማያዝ አቅም አለው። ለስላሳ ነው በጣም ታሽቶ ሲነሳ ያንን አሽርጦ ነው እሚነሳው። እሷም ትታሻለች፤ ባሏ ሳይሆን እሚሻት ሴቶቹ እቤት እሚውሉ ማህበር አላቸው። ያቺ በሙሽርነት ጊዜዋ የምታሻት በዕድሜ እኩያዋ የሆነች አብሮ አደጓ ናት ይህን ሥርዓት ስታከናውን በስሟ አትጠራም "ሃቤ" ትባላለች። የእነ እገሌ እናት ትባላለች። ክብር ናት እሷ ናት የምታሻት። ሚሽጢሯንም የምታውቅ ማለት ነው።

ከሠርጋቸው በኂላ ማታ ማታ ባልየው ይታሻል። ለብዙ ቀን ማለት ምነው። ሙሽራ መሰልክ ይላሉ ሰውየውን ሰው ሲያገኘው ሰውነቱን ሲያዩ አብረቅርቆ አምሮበት ሲያዩ እከሌ ሽታው ጠረኑ ሙሽራ መሰለ ይባላል። የዲልካው ጠረን ላንቺ አይሸትሽም አጠገብሽ ለተቀመጠ ሰው ግን ሌላ ነው ይታወቃል ። ወንዱ ሙሽራ በሙሽርነት ጊዜው ገበያ ሲወጣ አክሮባጅ ይዞ ይወጣል። በዚያ ይታወቃል ሂናም ይደረግለታል። እጁ ላይ ከመዳፉ ውጪ የጣቱን አጋማሽ ጀምሮ ሴቷም ጥፍሯ ይደረግላትና መዳፍና ክንዷ በዲዛይን ሂና

ይደረጋል። የእሱም እግሩ ላይ ውስጥ እግሩን ብቻ ይደረጋል ለሦስት ለአራት ወር እንደዚህ ሙሽራው ከባድ ሥራ አይሠራም። እየዞረ ብቻ ያንን ያሳያል መንገድ ላይ ሲሄዱ "አረስ" ይሉታል ሙሽራ ማለት ነው።

*ዲልካ ለሙሽራ ብቻ ነው እሚደረገው?*

ማንኛውም የበርታ ሴት ሆነ ወንድ ይህንን ባህል ያውቀዋል። ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮላት ሴቷ ማዘጋጀት የምትችልበት ሁኔታ ካለ ታዘጋጃለች። ባሏ አሁን ያመው ይሆናል፤ ይደክመው ይሆናል፤ እንዲዝናና ማድረጊያ ነው። ሰውነቱ የደከመውን ለማነቃቃት ምን ለማድረግ ነው እሚፈለገው እሱ። ስለዚህ ሁል ጊዜ ሴትየዋ በሷን አክብራ ወዳ እምትኖር ከሆነ እሱ አይጠፋም ከቤቷ። በማንኛውም ጊዜ ይደረጋል፤ ችግር የለውም። ሴቷም በማንኛውም ጊዜ ማድረግ ትችላለች ግን ይሄ ዲልካ ሁምራ ምናምን እምንለው ነገር ባል የሌላት ሴት አታደርግም።

*ለምን?*

ባል የሌላት ሴት የማታደርግበት ምክንያት አንድ የፍላጎት ማነቃቂያ ነው ተብሎ ይታሰባል። ስለዚህ እሷ ካደረገች ሌላ ወንድ ሊመኛት ነው እ.. ዲልካ ምድረን ደግሞ ሌላ ነገር እያደረገች መሆኑን አመልካች ነው ስለዚህ ትዳር የሌላቸው ሰዎች ራሳቸውን ከዚህ ነፃ ማድረግ ይፈልጋሉ። የፈቱ፣ ባላቸው በአካባቢው የሌለ፣ የሞተ ከሆነ እንዲጠቀሙ አይመከርም። ጭስ ላይ አይቀመጡም፤ ዲልካና ሁምራ አይጠቀሙምም፤ ለምን ወንዱ ውስጡ ሊያስብ ስለሚችል ፍራቻም ይሉኝታም ነው።

***ቆይ ሲቲዬ አንድ ጥያቄ ላንሳ አሁን በሙሽርነት ጊዜ የምታሻቸው ሴት እሱንም እሷንም ታሻለች በዚያ መካከል እንደው ማለት በእስልምና ሴቶች ከወንዶች ያላቸው ግንኙነት ውስን ስለሆነ ያቺ እምታሸው ሴት እንዴት ታምና ነው ሴትስ ለምን ሆነች ወንድ ለምን አያሸውም ሙሽሮቹ የሚታሹት ለየብቻ በየቤታቸው ነው ብላችሁኛል።***

እሱ በእርግጥ ምንድነው መሰለሽ ከዚህ ከእጅ ወደዚህ ከዚያ ከእግሩ እዚህ ጋ ምናምን ታሸዋለች። አሁን የሆነ ሰውየው ምንድነው አማች ነው አማች ደግሞ በጣም ይፈራል። በቃላት ንግግር እንኳን ገደብ አለው። በእኛ መዳፈር የለም ስለዚህ ይሄን ሰውዬ ለክብር ተብሎ ነው የተሰጠችው ያቺ ልጅ ለእሱ ክብር ተብሎ ነው። ስለዚህ በጣም ይወዳታል፤ ማክበርም ግዴታ አለበት እሱ።

እሷ ደሞ ስትሄድ የጓደኛዋን ክብር ለማስጠበቅ፣ የቤተሰቦቿን ክብር ለማስጠበቅ፣ እዚያ አካባቢ ያለውን የቤተሰባዊ ባህሉ ክብሩ የእከሌ ዘር፣ የእከሌ ቤተሰብ፣ የሚባል አለ ያን ያን እንድታስጠብቅ ስለሆነ አንደኛ በዚያ ውስጥ ነው ራሷን አድርጋ እምትሄደው። ሁለተኛ እሱም ራሱ ሲያስቀምጥ አማች እንደሆነና የክብር ሰው እንደሆነ ነው። ስለዚህ ሲታሽም ሙሉ ልብሱን አያወልቅም። ሚስቱ ስትሆን ነፃ ነው። በዚህ ጊዜ ግን እንዳይደክመው፣ ቅር እንዳይለው፣ አንደኛ መዝናኛ የለም ገጠር ነው፤ የማዝናኛም ዓይነት ጭምር ስለሆነ ወንዶቹ መዓት አለ። እዚያ የእሱ ጓደኞች፣ ሚዜዎች፣ እነሱ ባሉበት፣ እነሱ ሁሉ እኮ ተቀባብተው እንደዚህ እናድርገው፣ እንደዚህ ይሁን፣ እንደዛ ይሁን፣ ይላሉ። እኔም ይደረግልኝ ይላሉ። እናንተ ገና ናችሁ ሰውነታቸው ዲልካ አይቀምስም፤ ካላገቡ ወንዶቹም መጀመሪያ ቀን ማየት የሚችሉት የሙሽርነታቸው ቀን ነው። ሂና ራሱ አያደርጉም። በእኛ ነውር ነው። ስለዚህ ሰርግ ለማድረግ ያሰበ ሁሉ በምኞት ያንን ሥርዓት ለማየት ይፈልጋል። ስለዚህ ሰውየው በእነዚህ ሁሉ የተከበበ ስለሆነ እንደዚህ ለሌላ ነገር ይዳረጋሉ፤ ሌላ ነገር ያስባል፤ የሚለው ነገር አይታሰብም።

*ሁምራ እሚባለው ከዲልካው የሚለየው በምንድን ነው?*

ሁምራ ፈሳሽ ነው፤ ሽቶ ነው፤ የሽቶ ውሃ ምናምን ተቀላቅሎ ነው። እኛ በቀደም ሱዳን ስንሄድ ያደረግነው ነው ሁምራ። ዲልካ አላደረግንም ገና ነው። አሁን ይሄ ሁምራ እኛ ውጪ አድርገን እየሄድን ነው በእኛ ባህል ግን አይፈቀድም። ቤት ውስጥ ብቻ ነው እሚፈቀደው፤ ለምን ይሄ ሁምራ እኔ እንደዚህ ካደረኩኝ ይሄን ሽታ የሚያውቅ ሌላ ወንድ ሊኖር ይችላል፤ በርታ ሊኖር ይችላል፤ እና ይሄ ሁምራ ሲሸትው ወይኔ ማናት?

ምን ዓይነት ሴት ናት? ይህን ሁምራ ያደረገች ብሎ ያስባል። በማሰቡ ብቻ ኃጢዓት ትገቢያለሽ፤ በመመኘቱ ብቻ። ስለዚህ ወደ ውጪ እንዲደረግ አይፈቀድም። ባልና ሚስቶች ቤታቸው ሆነው ፍቅር ሊሠሩ፣ ጥሩ ነገር ሊያደርጉ ብቻ ነው እሚፈቀድ።

አሁን ሁምራ ካደረግሽ ሁሉም የበርታ ወንድ ልቡ ይቆማል። ምን እንደሆነ አታውቂውም፤ ግን ስለሸተተው ነው። እኛ ዝም ብለን ተቀብተን እንሄዳለን፤ ግን የሆነ ወንድ ብታገኚ ይጨንቀዋል። ምን ሆኖ ነው እሚጨነቀው? ብለሽ ስትዪ ዲልካው ነው። ለምንድነው ይህን ሽቶ አድርገሽ የመጣሽው?[54] ብሎ እሚቆጣሽ ሁሉ አለ ሊመታሽ ሁሉ እሚነሳ ሰው አለ በቃ ቤተሰብ የሆነ በቃ ሊመታሽ ይነሳል…

**ነፊሳ፡-** ገጥሞኛል እኔ የሆነ ሥልጠና ገብተን ሲቲ እንደምትለው የሆኑ ሴቶች ተቀብተው ሲሄዱ ለምንድነው ተቀብተሽ የመጣሽው? እኔ አልቻልኩም! እስከሚል ድረስ ሰውየው ማለት ነው ያውቁታል ወንዶቹ።

**ሲቲና፡-** ያውቁታል በጣም ስለሚያውቁት ሌሎች ብሄረሰብ ወንዶች አያውቁትም። የእኛ ብቻ ናቸው ስለሚያውቁት፤ በቃ አይፈልጉትም ዝም ብሎ በዘፈቀደ እንዲሆን አይፈልጉትም። ሁለተኛ ሁሉም ሰው እንዲያውቀውም ስለማይፈልጉም ጭምር ነው። ሌላ ወንድም እንዲያውቀው አይፈልጉም። ቅናት አለባቸው ያ ቅናት አሁን ይመጣበታል፤ እሱ ልክ ሲመጣበት ለምንድነው እንደዚህ ያደረግሽው?! ብሎ ሊደባደቡ ሁሉ እሚነሱ ሰዎች አሉ። እና የራሱ የሆነ እሚፈጥረው እንትን አለና ብቻዋን እምትኖር ሴት ትዳር የሌላት ያላገባች አታደርግም። አሁን ያላገባች ሴት ሁምራ አይፈቀድላትም፤ ገና ነቻ! ማንኛውም ሽቶ ማድረግ ትችላለች፤ ልታገባ ስትል ሠፈሩ በሙሉ በሽቶ ነው እሚናወጠው። በቃ ሠርግ አለ እዚህ ሠፈር ይባላል። ትልልቅ ሴቶች ተሰብስበው ነው እሚሰሩት አክስቶች፣ አያቶች ናቸው ይህንን ዲልካ እሚሠሩ ቁጭ ብለው አጠገቡ። ሁምራው ራሱ በባህላዊ መንገድ ነው እሚቀመመው አሳይሻለሁ ዓይነቶቹ አሉ ዱፍራ

[54] አሶሳ ተመልሰን እራት እምበላበት ሆቴል ሲቲና ተቀብታ መጥታ የማያውቃት ሰው ሱዳን የኖረ ትግሬ አቤት ዲልካሽ! ብሎ በመጎምጀት ሲያናግራት አጋጥሞኛል

እሚባል አለ አልሁምራ እሚባል አለ ሸክሾካ እሚባል አለ ዝም ብሎ ከነፍሪያቸው እሚገቡ ተፈጭተው እሚጨመሩ አሉ ስትሰሪ ሠፈሩ በሙሉ ንውጥ ይላል በሽታ ።

*ስትሰሪው ለማየት እችላለሁ?*

አዎ ዲልካው ብዙ ጊዜ ስለሚፈልግ እኔም እራሴ ጊዜ የለኝም እሱን ለመቀመም የሰርግ ወቅት ቢሆን የትም ሲሰራ ታገኛለሽ ግን ተሠርቶ የተቀመጠውን አሳይሻለሁ። ሁምራውን ግን ጊዜ አይፈጅም የአንድ ሰዓት ሥራ ነው አብረን መሥራት እንችላለን።

***እሺ አባ አብዱራሂም ምን ቀረ በቀደም ተረት አስታውሼ እነግርሻለሁ ብለውኝ ነበር?***

**አባ መሃመድ ፡-** ተረት አዲስ ነገር ማምጣት አልቻልኩም ያ የበቀደሙን ግን እጨርሳለሁ። የበቀደሙ አሆር ፈስ አጠራቅሞ ወጣ፤ እዛ ፍቱት ያላቸው፤ እሱ ጋ ብዙ ነገሮች ትዝ አሉኝ። እንደገና በቀደም የረሳኋቸው እና አሆር ንጉሱ ቤት ሲገባ አልሞ ነው የሄደው። ንጉሱ ቤት እንደገባ "አሜ አሆር!" ይሉታል አጎት አሆር ማለት ነው። አልጋ ቆንጆ ፍራሽ ተነጥፎለት ቁጭ በል ይሉታል። እዚህ ፍራሽ ላይ እኔ አልቀመጥም። የት ነው ታዲያ መቀመጥ እምትፈልገው ? አይ አጎቴ ዶሮች ናቸው፤ ዶሮች እሚቀመጡበት ቦታ ነው እምቀመጠው። ሄዶ ዶሮች ቦታ ይቀመጣል፤ አሁን ተመቸው እሚጠጣ ውሃ ሲሰጡት እኔ ሰው በሚጠጣበት አልጠጣም ዶሮች በሚጠጡበት ነው ይላል። በዚያው ይሰጡታል፤ ምግብም ዶሮች በሚበሉበት ይሰጠዋል፤ ሲመሽ መኝታውንም ዶሮች ቆጥ ላይ ይወጣል፤ ሌሊት አንዱን ዶሮ ይዞ ያስርና ቋቅ ሲል ምነው አጎት አሆር? ሲሉት አይ አክስቴ ዶሮ ጠጋ በይ ስላት እምቢ ስላለችኝ ነው። አሁንም አውራውን ሲያንቅ እና ሲጮህ ምነው? ሲሉት አጎቴ አውራ ዶሮ ጠጋ በል ስለው እምቢ ስላለኝ ነው ይላል። በኋላ ዶሮቹን ይሰበስብና ሌሊት ውልቅ ብሎ ይጠፋል።

እሱ ከሄደ በኋላ አስቀምጡልኝ ያለውን የአደራ ዕቃ ሲፈቱ በፈስ ይጨርሳቸዋል። ንጉሱ ተከተሉት ብሎ ወታደር ያዛል። ይከተሉታል፤ በዚህ ወጣ፣ በዚህ ወረደ፣ መዓት ጣጣ ነው በዚህ ውስጥ ያለው። እና ያባርሩታል፤ ሄዶ ዋሻ ውስጥ ይገባና ሊያመልጥ ሲል

እግሩን ይይዙታል። ሲጎቱቱት እሱ እግሬ አይደለም ዝም ብላችሁ አትድከሙ ሲላቸው ይለቁትና ወጣ ያለውን የእንጨት ሥር ሲጎትቱ ኡ! ኡ! ብሎ ይጮሃል ውሸቱን፤ ሰዎቹ ዕውነት መስሏቸው ሲጎት ሥሩ ይበጠስና ይሞታሉ።

ከንጉሱ ቤት የሠረቃቸውን ብዙ ነገሮች ይዞ ይሠወርና መኖር ይጀምራል። ከዚያም ቦለቄ ይዘራል፤ ቦለቄውን ሲጠብቅ ሲያሸት ቆቆች ይመጡና ለመብላት ሲሞክሩ ይይዛቸዋል፤ የበላችሁትን ቶሎ ብላችሁ መልሱ አለዚያ እገድላችኋለሁ ሲላቸው ዕንቁላላቸውን ይሰጡታል፤ ዕንቁላሉን ወስዶ ቀጭኔዎች እሚመላለሱበት መንገድ ላይ ያደርገዋል፤ ቀጭኔዎች ሲመጡ አንድ የማያይ ዓይነ ስውር ቀጭኔ ይመጣና ዕንቁላሉን ይረግጠዋል። ክፈለኝ ብሎ ሲይዘው ከአንገቱ ላይ አንድ ሁለት ጅማት አውጥቶ ይሠጠዋል። እሱን ወስዶ ሲሄድ አሞራ መጥቶ ይነጥቀዋል።

እንደዚህ እንደዚህ ሲል አሞራው መጥረቢያ አምጥታ ትከፍላለች። ያንን መጥረቢያ ይዞ ሲሄድ ሰዎች ሰው ሞቶባቸው ለመቅበር እንጨት መቁረጫ አጥተው ሲቸገሩ ይደርሳል። ይሄው እኔ እያለሁ ለምን ትቸገራላችሁ? ብሎ መጥረቢያውን ይሰጣቸዋል። እንጨት ሲቆርጡበት መጥረቢያው ይሠበርባቸዋል። ቶሎ ብላችሁ ክፈሉኝ አለዚያ ከዚህ ንቅንቅ የለም ይላቸዋል፤ እኛ ምንም የለንም ከፈለግህ ሬሳውን ይዘህ ሂድ ይሉታል። እሬሳውን ይዞ ይሄዳል፤ ወስዶ ወንዝ ዳር ያስቀምጠዋል። ወንዝ ዳር ሲያስቀምጥ ምን እንደተፈጠረ እዚያ ተረሳኝ ተያይዘው ይግቡ?... በቃ ሄደ በጣም ቆንጆ ነገር ነው ተረሳኝ ነብር ጋር የሚገናኙበት ቦታ አለ፤ ከእረኞች ጋር የሚገናኙበት ቦታ አለ የሰጡት ነገር አለ። ከዚያ ከሬሳው ለውጥ እና ወተት ይፈልጋል። ምግቡን በወተት ለመብላት የሆነ ነገር ይላቸዋል። ላም ይሰጡታል ለወተቱ ማለት ነው በዚያው ሲያስጨንቅ እንደገና ፍየል ይሰጡታል፤ የሆነ ቦታ ላይ ነብር መጥቶ ፍየሏን ይይዛል፤ አሁን ከነብር ጋር ነው ድርድሩ ነብር ይዞ እንትን ሲል ያታልላቸዋል። ብረት እሳት ውስጥ አስቀምጦ በጣም ሲቃጠል ያንን የፀሐይ ጥልቀት እይ እስቲ ይለውና ወደ ፀሐይዋ አፉን ከፍቶ ሲመለከት ያንን የጋለ ብረት አፉ ውስጥ ይከታል፤ ያሸንፋቸዋል። ይሄ ብቻ አይደለም ጣጣው በጣም ብዙ ነው አስተካክዬ እየነገርኩሽ አይደለም ጫፉን ለዚህ ያክል የተያያዙ ሌሎች ነገሮችም አለ።

***እሺ አመሰግናለሁ ሌላስ እንደው ምሳሊያዊ አነጋገሮች እንቆቅልሾች የምታስታውሱት ይኖራል?***

**ሲቲና፡-** አለ በእኛም ለምሳሌ፡-

- ሁባ ቶሬና አዶሚፀው - የሚዞር እግር የዶሮ ኩስ ይዞ ይመጣል።
- አላዓማና ሰቶ ገለማ ቆርኖ - ቁራ ነጭ ነበረች የጠቆረችው አደራ በልታ ነው ታማኝ ያልሆነ ሰው ሲያጋጥም እንዲህ ይባላል።

***ሌላስ የምታውቋቸውን ሁሉ ንገሩኝ እስቲ?***

ሞልተዋል አሁን ማስታወስ አቃተን እንጂ ሞልተዋል

- ጎብሎን ጎሮ ነዛል ጎብሎን ጎሮ ሃራ ዘላሁ ጎቦራን ዘሁ - እግር ላክ እግር ብትልክ እንቅፋት ቢመታውም ይድናል ምላስ ከላክ ግን የሚመልሰው ነገር የለም ነው። አንዴ ተናግረሃል በምላስ የምታቆስለው አይድንም ነው።

ሌላ ጊዜ ስትመጪ መአት ነገር ጽፈን እናቆያለን አሁን ማስታወስ አቃተን እንጂ መዓት ነው። ለዛሬ ይሄው ነው!

***እሺ በጣም አመሰግናለሁ ሁላችሁንም። ከመጨረሻችን በፊት ግን ለአባ አቡዱራሂም ጥቂት ጥያቄዎች አሉኝ የመንግስትን የልማት ፖሊሲዎችና ባህሉን አስመልክቶ እንደው በዚህ ወረዳም ሆነ በክልሉ በመንግስት ከወረዱ የልማት የፖሊሲ አቅጣጫዎች በባህሉ ተፅዕኖ ሰይተገበሩ የቀሩ ወይም እስካሁን ባህላዊ ተግዳሮት ያለባቸው ይኖሩ ይሆን የሚያውቁት ካለ ቢነግሩኝ?***

**አባ አብዱራሂም ፡-** ልማትን በሚመለከት አካባቢው በእርሻ ነው እሚተዳደረው፤ ግን በጣም ወደ ንግድ ያዘነብላል፤ ንግድን ይወዳል፤ እርሻ አሁን ቅርብ ነው የለመደው ድሮ ከብት ያረባል፤ ከብት ሽጦ እህል ይገዛል። በተለይ በ1950ዎቹ በ1957/56 አካባቢ የከብት እልቂት ተፈጠረና ከብቶች አለቁ። ስለዚህ የግድ የሚገዛ ነገር

ሳይኖረው እራሱ ወደ እርሻ ገባ ከመግዛት ማለት ነው:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እርሻ ተለማመደ:: እና አሁን እንግዲህ የመንግስት ፖሊሲዎች አሉ ኤክስቴንሽን ፕሮግራሞች አሉ የእንስሳት ፓኬጅ፣ የሰብል ልማት ፓኬጅ፣ የኢኮኖሚ ጠቀሜታ ያላቸው ሰብሎች ፓኬጅ አለ ያ ሁሉ ይሰጣል:: አብዛኛው አካባቢው በዚህ በማዳበሪያ የመጠቀም ባህል ደካማ ነው:: አካባቢው ያልተነካ ስለሆነ መሬትን ማዳበሪያ ከመጠቀም እዚህ እምቢ ሲለው ሌላ ቦታ ሄዶ ያርሳል:: ከዚህ የተነሳ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የህዝብ ቁጥር እየጨመረ ነው:: እንደዱሮው መሬት ተፈልጎ እንደልብ ማግኘት ይቸገራል:: ከዚህ አምስት አመት ወዲህ ትምህርቱ በስፋት በመሰጠቱ አሁን ማዳበሪያ መጠቀም ልምዱ እየመጣ ነው:: አሁን ቆንጆ ተሸላሚዎች አሉ በእርባታውም በኢኮኖሚ ጠቀሜታ ባላቸውም ቢሆን ህዝቡ ይሳተፋል:: ግን እንደሌላው አይደለም:: እንደ አማራ እንደ ኦሮምያ ሌላ አማራጭ የላቸውም እነዛ እርሻ ብቻ ነው:: ይሄ እርሻ እምቢ ካለው ትቶ ወደ ንግድ ይገባል እምቢ ካለ ወርቅ ቁፋሮ ይሠማራል፤ ካልሆነም ወደ ሱዳን ይገባል:: ያያ ሁሉ ወደ ኋላ ያዘገዩን ነገሮች ናቸው:: አሁን ቅርብ ግን ወደ እርሻ ወደ ልማት የገባንበት ሁኔታ አለ እረጅሙ ዘመን ግን እርሻን እንደመሠረታዊ ጉዳይ አይታይም በአካባቢው ::

***ዘመናዊ ከሆነው እኛ ከምንሰጠው ቴክኖሎጂ ይልቅ እሱ በባህላዊ መንገድ የሚጠቀመውን በመመረጥ የእኛን ያለመቀበል ነገር የለም ወይ? ለምሳሌ ማህበረሰቡ በባህሉ የራሱ የሆነ ዕውቀት አለው ያንን እንተውና የኛን ብቻ ተቀበል ስንለው አንዳንዴ ያኛው የተሻለ ሆኖ ይገኛል::***

አሃ እንደምትይው ይሄ ቴክኖሎጂ ማስፋፋትና ማስረፅ ከተጀመረ ቆይቷል፤ ግን በህብረተሰቡ ላይ ያመጣው ለውጥ ይህን ያህል አይደለም:: እኛ የራሳችንን አንለቅም የቆየ ባህላችን ነው:: መሬት አሁን መሬት ዝግጅት ላይ እራሱ ሌላ ቦታ ላይ ሦስት አራት አምስት ጊዜ መሬት ለስልሶ ይዘራል:: እኛ ጋ አይቀበሉም፤ እንደዚያ አድርጉ ብንላቸውም "አድካሚ ነው፤ የእኛ ይሻላል እኛ እናስተምራችኂለን ወይስ እናንተ ናችሁ እምታስተምሩን?!" ይላሉ "ለእኛ ስለእርሻ ለምን ትነግሩናላችሁ እኛ ነን

እምናውቀው ሥራችን ነው!" ይላሉ፤ ግን ረጅም ጊዜ 30 ዓመት 40 ዓመት አካባቢ እየሄደ ነው እና ቅርብ ጊዜ ነው ይሄን ቴክኖሎጂ እየተቀበሉ ያሉት እንደውም ወደ ታች ደሞ ወደ እኛ[55] በደንብ የገባ አይመስለንም እንደውም ባምባሲ[56] ወረዳ በጣም ጥሩ ነው ይባላል እንጂ ወደ ሽርቆሌ፣ ወደ መንጌ፣ ወደ ሌላ ቦታ እንደዛ አይመስለኝም ተቀባይነቱ የራሳቸው ነው።

ምንድነው አሁን እነሱ ዛሬ ያርስና እህል ሲያገኝ ያንን ሽጦ ወደ ንግድ ነው እሚሄደው እርሻውን አያስተውሰውም ሲደኽይ ወይም ሲከስር ነው እንደገና ተመልሶ ወደ እርሻ ይመጣል። እርሻ እሚሰራው ለመንደርደርደሪያ ነው በቃ፤ ትንሽ እስኪያገኝ ይሄ ነው ባህሉ ማለት ነው። እንዳልሽው የቆየ ባህላችን ነው እንጂ የሚጠቅመን ምንድነው ማዳበሪያ አያምኑም፤ ያለማመን ነገር አለ ያንን ለቀው ዘመናዊውን ቢጠቀሙ እንደማይሻሻሉ እንደዛ ይላሉ በጣም ሃይለኛ እንትትን ነው ያላቸው።

አሁን አንተ ለምንድነው ወርቅ እምትቆፍረው? ወርቅ ምን ያደርግልሃል? እንላለን ወርቅ ቆፍረው እነማን በለፀጉ? ከወርቅ ቆፋሪው ወርቅ ነጋዴው ነው ሀብታም የሆነው ቆፋሪው ይለፋል ዛሬ የሚያወጣውን ሽጦ ዛሬ ቀኑን ነው እሚውልበት።

***አዎ ወርቅ ቆፍረው ብዙ ብር ያገኛሉ አንዳንዴ ሲቀናቸው ብዙ ሺህ ብርም ሊሸጡ ይችላሉ ያንን ብር የማጠራቀም የመቆጠብ ባህላቸው እንዴት ነው ለምንድነው ወርቅ ቆፍረው እማይከብሩት?***

---

[55] እኛ የሚሉት የሽርቆሌ ወረዳን ነው።

[56] ባምባሲ ለክልሉ ዋና ከተማ አሶሳ ቅርብ፣ ዋናው አስፓልት ዳር የምትገኝ፣ ከሰሜን የሀገሪቱ ክልል የመጡ ሠፋሪዎች ከነባሩ ብሔረሰብ ጋር መሳ ሆነው የሚኖሩባት ወረዳ ናት።

በጣም ደካማ ነው እኔ በግሌ በጣም ነው እሚያናድደኝ። ቆፍረው ያገኛሉ አያያዙ ዜሮ አይጠቀሙበትም። ለምሳሌ እስከ ስልሳ ሺህ መቶ ሺህ ብር የሚያገኝ አለ በአንድ ቀን፣ በአንድ ጊዜ፣ በአንድ ቁፋሮ ማለት ነው። ያንን ገንዘብ ሲያገኝ ባህሉ በቀደም ያነሳነው  የጋራ ነው። እኔ ዛሬ ይሄንን ብር ካገኘሁ  በርቀት ያለ ወንድሜ ትዝ ይለኛል፤ አባቴ ትዝ ይለኛል፤ የረሳኋት አክስቴ ትዝ ትለኛለች፤ እና እነሱን እጠራና ዛሬ አርጄ አስደስታቸዋለሁ። ሚስት እስከ አራት ማግባት እችላለሁ። አንድ ሚስት ከነበረችው ሁለተኛ ሚስት ያስባል፤ ሦስተኛ ሚስት  እንደዚህ። ስለዚህ ወርቅ መቆፍሩንም ያቆማል። ያ ገንዘብ እስከሚያልቅ ድረስ እንደገና ዞር ብሎ አያይም። እና ባብዛኛው ባዶ እጅ የሚያስቀራቸው ይሄ ነው።

በዚያ ላይ ምን ቢሠራ ይሻላል? ብዬ አስባለሁ። በግሌ የማውቃቸው ሰዎች አሉ። አንዱ አሁን እዚህ መንጌ አካባቢ እዚያ ወርቅ ይቆፍርና ቆይቷል አሁን አይደለም ወርቅ እርካሽ በነበረበት ጊዜ 60 ሺህ ብር ያገኛል። በጊዜው በጣም ብዙ ነው እና ምን ይለዋል ጓደኛው "ስማ ይህንን ገንዘብህን አታጥፋ፤  ከተማ አካባቢ ቤት ሥራ፤ ታከራያለህ፤ ጥሩ ቤቶች አንድ አሥር ክፍል ሥራ፤ ካልሆነ ደግሞ ወፍጮ ትከል፤ ወፍጮ ከተከልክ ገንዘብህ አይጠፋም።" እሺ ይልና ለጊዜው ከዚያ ግን ወደዚያ አልሄደም ገንዘቡን ወዲያውኑ ጨረሰው። አራት ሚስት አግብቷል።

መጨረሻ ላይ ተገናኙ "ምን ሆንክ እኔ ነግሬህ አልነበር ወይ? እኔ እንዳልኩህ ብታደርግ ኖሮ ዛሬ ዝም ብለህ አየር አትስብም" ይለዋል። ስማ አንተ አላህ ጋ ሄደህ መጣህ ወይ? ያኔ የሰጠኝ አላህ አሁን እንደማይሰጠኝ እርግጠኛ ነህ? ይለዋል። እይው በጣም ደካማ ሆነ እንትትን ነው ይሄ ምንድነው "አኺራ ማለት የወዲያኛው ዓለም የእኛ ናት። ይህቺ የእኛ አይደለችም" ብለው ራሳቸውን እንትትን ይላሉ። እዚህ ላይ ምንም ማለት አይደለም ትተን እንሄዳለን ብለው ተስፋ የመቁረጥ ይሁን የት ቦታ እንደማስቀምጠው አላውቅም፤ በቃ ሲያገኙ አገኙ፣ ሲሄድም ሄደ፣ ሲመጣም መጣ፣ በቃ ግድ የላቸውም።

ብሩ ካለ ቁፋሮውንም አይሠሩም። ዛሬን ነው የሚኖሩት። ገንዘቡ እስከሚያልቅ ይለብሳል፤ ቆንጆ ከተማ ይገባል፤ የትም ቦታ ይሄዳል፤ ዜሮ እስከሚገባ እንደዚህ ነው። ባለው ላይ መጨመር ወይ የያዘውን ራሱ ቁም ነገር ላይ ማዋል የለም። ቢኖርም ከስንት አንድ ነው። እሱም በስንት ምክር፣ በስንት ቁጣ፣ ካለሆነ አሃምዲሊላ በከራማ ነው። በቃ እንብላ ይቺኛዋ ትመጣለች፤ አሁንም ሌላ ሚስት እዚችኛዋ ጋ ዛሬ ታረደ ያቺኛዋ ማኩረፍ ትጀምራለች፤ "እዚያች ጋ ወፍራም በግ ነው ያረድከው እኔጋ ምን ስለሆንኩ የማን ልጅ ስለሆንኩ ነው ቤቴ የማይታረደው?" አሁን ሦስተኛዋም ትጮሃለች።

እንደዚህ ሲል ሌላ ዘመድ ደግሞ ለእኔ አላክልኝም ይላል። ያኛውን አብልተህ እኔን የረሳኸኝኝ ምን አጠፋሁ? እሩቅ እኮ ነው። አይ የሄው ልኬልሻለሁ፤ አንድ ሃምሳ ብር መቶ ብር ወይ ነይና ውሰጂ፤ እንደዚህ ሲባል በቃ ያልቃል። እንደገና ተመልሶ ወደ ቁፋሮ ይሄዳል እንጂ ያ ባለፈው የሆነውን ችግሩንም አያስታውሰውም። አላህ አመጣ አላህ ወሰደው፤ ግን እዚያ የአላህ ሚና የለም አስተሳሰብ ነው እንግዲህ ደካማ አስተሳሰብ ከመጥፎ እንትኖች አንዱ የሚታየኝ ይሄ ነው እና ይሄ አብሮ መብላት አብሮ መጠጣት እንደመጥፎ ነገር አላየውም። በሃይማኖታችንም የሚያስተምረው ቁጠባን ነው። እነዚህ የሚበትኑ ሰዎች "የሰይጣን ወንድሞች" ነው እሚለው እና ቆጥቡ ነው ሃይማኖት አያዝም ባህሉ ነው ዝም ብሎ ደካማ ባህል እንደደካማ አድርጌ እሚቆጨኝ ይሄ ነው ለምን አናድግበትም።

***እሺ ሁላችሁንም ስለሰጣችሁኝ መረጃ በጣም ነው እማመሰግነው ብዙ ነገር ነው የሰጣችሁኝ እግዜር ይስጥልኝ።***

## ቃለ ምልልስ አምስት

ስም፡- ሲቲና አደም፣ ዕድሜ፡- 38፣ *ሥራ፡-* የጅምላ ንግድ፣ የትምህርት ደረጃ፡- በግብርና ኤክስቴንሽን ዲፕሎማ፣ ብሔር፡- በርታ መረጃዉ የተሰበሰበበት ቀን ነሐሴ 08 ቀን 2003 ዓ.ም ምሽት ከ3፡30- 6፡30 ሰዓት፣ ቦታ፡- በቤንሻንጉል ጉሙዝ ብ/ክ/ መንግሥት አሶሳ በመረጃ ሰጪዋ ቤት

ቃለ ምልልሱ የተደረገው፡- በአማርኛ ቋንቋ

መረጃ ሰብሳቢ፡- ስንቅነሽ አጣለ

***እሺ ሲቲና እሳካሁን ስለደረግስልኝ የማስተርጎም፣ መረጃ ሰጪ የማገናኘት፣ እኔን የመንከባከብ ሥራ ከልቤ እያመሰገንኩ እስቲ ከሌሎቹ መረጃ ሰጪዎች ጋር ባለፈው ባደረግናቸው ቃለ ምልልሶች አንዳንድ ባህላዊ ምግቦችንና መዋቢያዎችን ምንነትና አሠራር አሶሳ ስንመለስ አሳይሻለሁ ብለሽኝ ነበርና እስቲ ከበርታ ገንፎና ማባያው ቄንቄጽ አሠራር እንጀምር፡፡***

እሺ የገንፎው መብያ አንቺ እንዳልሺው ቄንቄፅ ነው እሚባለው፡፡ በበርታ ባህል ውስጥ በጣም ተመራጭ ባህላዊ ምግብ ነው፡፡ የእህል ዘር ስለሆነ ይዘራል፤ በሦስት ወር በሁለት ወር የሚደርስ አለ፡፡ እሱን አበባው ካበበ በኋላ የአበባው ቡጥ ተቆርጦ፣ ተከትፎ፣ ውሃ ተጥዶ፣ የፈላ ውሃ ላይ ይጨመራል፡፡ ከዚያ ይንተከተክና አመድ የሆነ የሚመረጥ ዛፍ አለ የእሱ አመድ ይዘፈዘፍና ውሃውን አጥልሎ ጠብ ይደረግበታል፡፡ ቶሎ እንዲሞትና ፍሬው ጓጓላ እንዳይፈጥር፡፡ ሁለተኛ ያው በፊት ዘይት አልነበረም ሽንኩርት ያደርጉና እሱን ያው በእሱ መብያ ነው በቃ፡፡ በተለያዩ ነገሮች ተጨምሮ ክክ ላይ፣ ምስር ላይ አተር ላይ ይጨመራል፤ ለምን ቶሎ እንዲያሟሚው ስለሚፈለግ ማለት ነው፡፡ ከዚያ እሱ ይደረግና ጨው፣ ሽንኩርት ካለ አቁላልቶ ይጨመራል፡፡ ከዚያ አብሮ ተዋህዶ በገንፎ ይበላል ማለት ነው፡፡ ይሄ ተመራጭ ምግብ ነው አንደኛ ምንም ጉልበት ሳይጠይቅ የመዋጥ እትን አለው፡፡ ሁለተኛ ልብ ያቀዘቅዛል፡፡ አሁን ጨጓራ ያለባቸው የተፈጨውን ዱቄት ይጠጡታል፤ ደረቁን ማለት ነው፡፡

ከዚያ ያ ቄንቄጽ ለምን ይጠቅማል? ለምሳሌ ሳይቆረጥ ጊዜው ከዘገየና ትንሽ ከጠነከረ እሱን ቆርጦ ከትፎ ፀሐይ ላይ አስጥቶ ደሞ ተመልሶ ወቅጦ ዱቄቱን መጠቀም ይቻላል። በሁለት መንገድ ነው ማለት ነው። በጥሬው እሸቱ ይበላል፤ እንደገና ደግሞ ደርቆ ተፈጭቶ ዱቄቱ ያገለግላል።

*እንደ ቅቤ ቄንቄጽን ለገንፎ መብሊያ ነው እምትጠቀሙት?*

አዎ አይታወቅም፤ አሁን እኛ ጋ ገንፎ በቂቤ ቢባል አይታወቅም አንደኛ የእኛ ገንፎ የቦካ ገንፎ ነው እንደናንተ ዱቄቱን ውኃ ላይ ተጨምሮ አይደለም። የእኛ ገንፎ መጀመሪያ ያው ዱቄቱ ወይ ማሽላ ወይ በቆሎ ሊሆን ይችላል ይቦካል። ማታ ተቦክቶ ጠዋት ነው እሚሠራው፤ እርሾ ገብቶ ልክ እንጀራ እንደምናቦካው እሱም እንደዛ ይቦካል በእርሾ። ከዚያ ያድርና ያ ወጥቶ ተበጥብጦ ወደ ምጣድ ይጨመራል። ከዚያ እያማሠልሽ፣ እያማሠልሽ፣ እያማሠልሽ፣ እየወፈረ፣ እየወፈረ፣ እየወፈረ፣ ይሄድና ከዚያ እያዋሃድሽ ትሄጂና ቀጭን ከሆነ ወይም እንዳይኮመጥጥ ከተፈለገ ትንሽ ዱቄት ይነሰነስነታል ከላይ። ካልሆነ ዱቄቱ ተገንፍቶ እሚበላው "አልአሲዳ" ነው እሚባለው እሱ ደሞ ወይ እርሻ ቦታ እሚሠሩ፣ ወይ እንደዚህ ደቦ ነገር ሲኖር፣ ወይ ድንገት ልጆች እንዳይርባቸው ነው በዱቄት ተሠርቶ እሚሰጥ እንጂ በበርታ ባህል ተቦክቶ ያላደረ ገንፎ አይበላም።

ለምንድነው እሱ ያፈረጥማል፣ያወፍራል ተብሎ ይሰጋል። አሁን ለወጣቶች ያልቦካ ሲበሉ ይወፍራሉ ስለሚባል እሱ እንዳይሆን ማታ ተቦክቶ ጠዋት፣ ወይ ጠዋት ተቦክቶ ማታ ነው እሚገነፋው። አብዛኛውን ጊዜ የሚጠቀሙት አዳሁኔ፣ ሰርኜ፣ አዳብሬ፣ አልፌቴሪታ የሚባሉ የማሽላ ዘሮች አሉ እነሱ ናቸው ለገንፎ እሚሆኑት።

ገንፎው በትኩሱ ሳይቀዘቅዝ ነው እሚበላው እየተርገበገበ ነው እንጂ ከቀዘቀዘ በኋላ ሰው አይበላውም። ወዲያውኑ ሰው በተሰበሰበበት ትኩሱ ተገንፍቶ መቅረብ አለበት፤ እንጂ የዋለ ያደረ አይቀርብም።

*መሃሉ ጎድጉዶ ነው ቄንቄጹ እሚገባው እንደቅቤ?*

መሃሉ ጎድጉዶ አይደለም! አይደለም! ድፍኑን ሳህን ላይ ይገለበጣል። እንደውም የማገንፊያው ምጣድ ቅርፊት አለ መጨረሻ እሚቀር እንዳይቀዘቅዝ በእሱ ይሸፈናል። ቁንቁጹ ዙሪያውን ነው እሚደረገው እንጂ መሃሉ ጎድጉዶ እንደ ቅቤ አይጨመርም። ድፍን ነው። ሥጋ ካለም እዚያው ላይ ይጨመርና የሥጋውን ፍሬ ወይ በእጅ ያከፋፍላሉ። ገንፎን እንግዲህ እንደነገርንሽ አልከልዋ ውስጥ ብዙ ሰው ነው አንድ ላይ የሚበላው አሥር፣ አሥራ አምስት ሰው ሊኖር ይችላል። ስለዚህ ሥጋውን አብቃቅተው ይከፋፈላሉ ማለት ነው።

***እስቲ አሁን በሙሽርነት ጊዜ ለመዋቢያና ሰውነት ለማነቃቂያ ስለምትጠቀሙበት ዲልካና ሁምራ ባለፈው በደንብ ነግረሽኛል፤ ለጭሳጭስ የምትጠቀሙባቸውም ነገሮች አይቻለሁ እስቲ ስለ እነሱ አቀማመም ደግሞ ንገሪኝ።***

ስለእነሱ አሰራር አንደኛ ይሄ እንጨት የእራሱ አለው። ያው ሴቶች በሚሞሽሩ ጊዜ፣ በሚወልዱ ጊዜ፤ እንዲሁም በማንኛውም ሰዓት ወጣት ልትሆን ትልቅ ሴት ልትሆን ትችላለች ጤንነቷን ለመጠበቅ የተለያዩ የእንጨት ዓይነቶች አሉ። አንደኛው እንጨት የሚቆራሰም ቆራሱማ እንጨት አለ። እሱ ይከተከትና መዓት የሽቶ ዱቄት አለ፤ እነ ሰንደል፣ እነ አልማህለብ፣ እነ ቢተሱዳድ እሚባሉ ደረቅ የሽቶ ዓይነቶች አሉ። እነሱ ይወቀጣሉ፤ ለብቻ ከዚያ ደግሞ ሰንደል የውሃ ሽቶ አለ፤ አልማህለብ የውሃ ሽቶ አለ፤ አልሱረቲያ አለ፤ እነዚህ እነዚህ ይቀመሙና አንድ ላይ ያ እንጨት ለብቻ ተከትክቶ ሎሚና ስኳር አብሮ ይዘጋጅና ሎሚ መጀመሪያ ትጨምሪያለሽ፤ ቀጥሎ ስኳር ትጨምሪያለሽ፤ ስኳሩ ይቃጠላል፤ ልክ የሻይ ከለር በሚፈጥር ጊዜ እንጨቱን ወስደሽ ትጨምሪያለሽ። ከዚያ በኋላ እሱን ታገላብጪ፣ ታገላብጪና ሰውነቱን በሙሉ ከተዋሃደ በኋላ ዱቄቱን የሽቶ ዓይነት ትነሰንሺበታለሽ። አሁንም ታዋህጂና የውሃውን ሽቶ በመጨመር አዋህደሽ ክዳን ባለው ዕቃ ውስጥ ታስቀምጫለሽ።

ከዚያ በፈለግሽ ሰዓት ሁለት ፍሬ ወጣ እያደረግሽ ማጨስ ነው። ለምሳሌ ውሃ ሽቶ ባይኖርሽ እሱን ልብሽን አጥነሽ ለመልበስ ትችያለሽ። ሁለተኛ ለገላ ሽታ ለመቀየር፤

ሦስተኛ የቤትን ሽታ ለመቀየር ይጠቅማል፡፡ አራተኛ ለምሳሌ ለመሃፀን ፈሳሽ ሊኖር ይችላል፤ ምን ሊኖር ይችላል፤ እሱን አድርገው ይታጠኑታል፡፡ እርጥቡ ቢኖር ጥሩ ካልሆነም ውሃ አርከፍክፈው ጉድጓድ ውስጥ በማድረግ ይታጠኑታል፡፡ በበርታ የምትታጠንበት ጉድጓድ የሌላት ሴት የለችም፡፡ ወይ ኩሽና አጠገብ ወይ ዕቃ ቤት በር ሥር አካባቢ ትንሽ ጉድጓድ ትቆፈርና ለዚሁ ጉዳይ ትዘጋጃለች፡፡

በሚታጠኑ ጊዜ ብርድ ልብስ ያስፈልጋል፤ መቀመጫ ያስፈልጋል፤ ቅቤ ለመቀባት አይወደድም በእኛ ባህል፡፡ የማር ሰፈፍ "በስምስም ዘይት" ይቀልጣል፡፡ ስምስም ዘይት የሰሊጥ ዘይት ነው፡፡ ዘይቱ ቅርንፉድ፣ የሎሚ ወይም የብርቱካን ቅርፊት ይጨመርበትና እነሱ በደንብ አብረው ይበስላሉ፡፡ ሰሙን ትከቺበታለሽ፤ ሰሙ ዘይቱን ወፈር ያደርገዋል፡፡ ከዚያ እሱን ተቀብተሽ ነው የምትታጠኚው፡፡ ይሄ ገላሽ እንዳይሰነጣጠቅ ነው፡፡ ሌላ የማሩ ሰፈፍ የቆዳ ቀዳዳዎችን ይከፍታል ተብሎ ስለሚታመን ጭሱ ወደ ሰውነትሽ እንዲገባ ለማድረግ እሱን ተቀብተው ነው እሚገቡት፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ጠዋት ወይ ማታ ነው እሚደረገው፡፡ ትኩስ የወለደች አራስ ሴት ደሙ ካቆመላት ጊዜ ጀምሮ እስከ አርባ ቀን በተከታታይ ትታጠናለች፡፡ ለምሳሌ ቁርጥማት ሊኖራት ይችላል፤ ድካም ሊኖራት ይችላል፤ እነዛን እምታስወግድበት ጥሩ ዘዴ ነው ይሄ ጭስ ማለት ነው ያው ያገቡ ሴቶችና እናቶች ናቸው ይህንን ጭስ የሚጠቀሙት፡፡ የተዘጋጀው ማጠንት ይሄውልሽ ይሄን ይመስላል፡፡

***እሺ ሲቲዬ ስለአደረግሽልኝ ቀና ትብብር ሁሉ በጣም አመሰግናለሁ፡፡***